# ከጋምቤላ እስከ ሁመራ!

## ለሱዳን መሬት ከተሰጠ ይመጣል መከራ!

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው!
All rights reserved

መጀመሪያ ታተመ መጋቢት 2001 ዓም
ሲያትል ዋሽንግተን
አሜሪካ

Copyright 2009 Amare Afelae Bishaw.
First edition March 2009
Printed in U.S.A

Published by Gugsa Magazine
P.O.BOX 492
Seattle WA 98111
U.S.A

የደራሲው መልዕክተ ሣጥን ቁጥር
P.O.BOX 492
Seattle WA 98111
U.S.A

ከአማረ አፈለ ብሻው!
Amare Afelae Bishaw.

## ክፍል አንድ

### ማውጫ


ምዕራፍ 1 ምስናጋ እና መታሰቢያ ገጽ 2-4
ምዕራፍ 2 ፈር አስጨባጭ ገጽ 5-6
ምዕራፍ 3 በታሪካችን እንኩራ እንጅ አንፈር ገጽ 7-9
ምዕራፍ 4 ለአንባቢያን ከፀሐፊይ ገጽ 10-17


## ክፍል ሁለት


ምዕራፍ 1 የኢትዮጵያ ታሪክ ከፍጥረት እስከ ልደት ገጽ 18-21
ምዕራፍ 2 የኢትዮጵያ ታሪክ ከክርስቶስ ልደት እስከ እስልምና ሃይማኖት ምስረታ ገጽ 22-25
ምዕራፍ 3 ከእስልምና ምስረታ እስከ ንግሥት ዮዲት ገጽ 26-30
ምዕራፍ 4 ከንግሥት ዮዲት እስከ ዘመነ መሳፍንት ገጽ 37-40
ምዕራፍ 5 ከዘመነ መሳፍንት እስከ አጤ ምኒልክ ገጽ 40-47
ምዕራፍ 6 አጤ ምኒልክና የኢትዮጵያ ደንበር መደናበር ጅመራ ገጽ 47-57


## ክፍል ሶስት


ምዕራፍ 1 የኢትዮጵያ ዳር ደንብር በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ገጽ 58-65
ምዕራፍ 2 ባለሥልጣኖች በጎንደር መሬት ሊሰጡ ማቀድ ገጽ 66-85
ምዕራፍ 3 ደርግና ዳር ደንበር ገጽ 101-106
ምዕራፍ 4 ዳር ደንበር በርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ዘመን ገጽ 107-108
ምዕራፍ 5 ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን ሊሰጥ ነው ገጽ 109-116
ምዕራፍ 6 በድንበር ብቻ ከተጻፉት ለማስረጃ ገጽ 119-122
ምዕራፍ 7 የኢትዮጵያ ድንበር ኮሚቴ የድምጽ ሠነድ ገጽ 127-142


## ክፍል አራት


ምዕራፍ 1 የታሪክ ቅኝት ስለ ወልቃይት ገጽ 146-150
ምዕራፍ 2 ወልቃይት ወደ ትግራ ሲከለል ጎንደሬዎች ዝም አሉ ገጽ 151-163
ምዕራፍ 3 "ትግርኛ በመናገሩ ብቻ በጥላቻ እንዲታይ ሆኖአል ገጽ 168-170
ምዕራፍ 4 ለወልቃይት የጎንደር ልጆች ገጽ 173-177
ምዕራፍ 5 ትግሬ ነን ላላችሁ የወልቃይት ልጆች ገጽ 177-186


## ክፍል አምስት


ምዕራፍ 1 ለወያኔ ደጋፊዎች የትግራይ ልጆች ገጽ 187-195
ምዕራፍ 2 ወያኔና የትግራይ ሕዝብ አንድ አይደለም ገጽ 195-202
ምዕራፍ 3 የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ! ገጽ 202-207
ምዕራፍ 4 ይድረስ ለድርጅቶች ገጽ 208-213
ምዕራፍ 5 የኢትዮጵያ ምሁራን ገጽ 214-222
ምዕራፍ 6 እንደ ቀይ ባህር ዓባይንና አጋዴን እንዳናጣ ገጽ 223-230
ምዕራፍ 7 የአጤ ቴዎድሮስ አጽም የት ደረሰ? ገጽ 231-233
ምዕራፍ 8 ጠቅላላ ሠነድ ገጽ 234-238




## ምዕራፍ 1

### ምስጋና


በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን! ከሁሉ አስቀድሜ ለዚህ ዓለም ጌታ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይድረሰው! የጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች ም/ 2 ቁ/10 "በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል" ይላል። በዚህ በስደቱ ዓለም የተለያዩ ችግሮች ሲደርስብን ልዑል እግዚአብሔር ሰዎችን እየላከ ችግራችን ይቀርፍልናል። እንዴ ይሆናል ብዬ ባላሰብኩት በሕልሜ እንኳን በማላልመው መንገድ የሞራል ውድቀት ደርሶብኝ እግዚአብሔር በጥበቡ ጥሪትን ልኮ አስወገደልኝ። እናት ስም ስታወጣ "ጥሪት"አለች የእኔ ዓይነት ማዕቀብ ሰዎች ሲደርስባቸው ጥሪት ጭንቀታችን እንደፈታህ ለአንተም ልዑል እግዚአብሔር አይለይህ። ይህን መጽሐፍ በምጽፍበት ወቅት በማናችውም ጉዳይ በማማከር የተባበሩኝ ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛውና አቶ ፈንታሁን ጥሩነህ፥ ወይዘሮ የካባ ሲሳይ እምባው፤ ሳደረጋችሁልኝ ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ።

የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ የተባለውን መጽሐፍ ያስመረቁልኝ ወይዘሪት ድንበር ነሽ ደበብና አቶ ደሴ ታደሰን፤ አመሰግናለሁ። ይህን መጽሐፍ ለአንባቢ ያደረሱልኝ አቶ ደሴ ታደሰ፤ አቶ ክንፈ ተሰፋዮና አቶ ሹመት ጉዳይን ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉት ወዳጆን ከልብ አመሰግናለሁ።

አቶ አያናዝጊ <u>አ|ወልቃይት</u> የተባለውን ሊያሳትሙት የጻፉትን መጽሐፍ እንድጠቀምበት ስለፈቀዱልኝ አመሰግናለሁ። መጽሐፍ ለሚጽፍ ሰው አንድ ገጽ ሠነድ ይጠቅማል። ስለዚህ መጽሐፍ፥መጽሔትና ጋዜጣ፤ በመስጠት ብቻ ሳይሆን መጽሐፍት ያዋሱኝን ጭምር አመሰግናለሁ። በተለይ አቶ ብርሃኑ ጣሰው፤ አቶ መልኩ በላይነህ፤አቶ አባይነህ መሸሻ፤ አቶ ሞገስ መርሲ ዔአዘን፤ ወይዘሮ በላይነሽ ተክለ ሃይማኖት፤ አቶ አበበ ድባቡ፤ ሊቅ ዶ/ር ጌቱ ገላየ፤አቶ ሰሎሞን አንተነህን ከልብ አመሰግናለሁ። እናንተ ውድ ወገኖቼ ጠቃሚ ሰነድ ባትልኩልኝ ኑሮ ይህን መጽሐፍ ጽፌ ለአንባቢ ማቅረብ አልችልም ነበር። በድጋሚ ከልብ አመሰግናለሁ።

ሌላው በአሜሪካ አገር ካሉት ኢትዮጵያውያን መደበሮች ዩስተን ቴክሳስ ግሩ ግሮሰሪን ከልብ አመሰግናለሁ። ምክንያቱም ሒሳቡን በተሉ ስለሚልኩልኝ ነው ሌሎች መደበሮች ግን በየሳምንቱ ስልክ እየደወልኩ መጠየቁ ስላሰለቸኝ" ይጥቅማችሁ" በማለት የተውኳቸው ብዙ ናቸው። እንኳን አስበው ሂሳብ ሊልኩ ቀርቶ በተደጋጋሚ ተጠይቀው ሂሳብ የማይከፍሉ ናቸው።

## መታሰቢያ

ይችን ከጋምቤላ እስከ ሁመራ የምትለውን መጽሐፌን ከዚህ ለሚከተሉት ኢትዮጵያውያን! መታሰቢያ ትሁናቸው:: በኢትዮጵያ የሚኖሩ ወገኖቻችን ከጋንቤላ እስከ ሁመራ የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት መሬት ለሱዳን ሊሰጥ በማሰቡ መሬታችን አንሰጥም ብለው ከሱዳን ወታደርና ከወያኔ ወታደር ጋር ተታኩሰው ለሞቱትና ታስረው ለሚሰቃዩት ንብረታቸውን ለተዘረፉት ቤታቸውን እንዲለቁ ተደርጎ በችግር ለሚሰቃዩት!

ከአገር ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን 1999 ዓም ጀምረው የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚሽን በሚል ተደራጅተው ዜናውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ በማድረግና ሠላማዊ ሰልፍ በማዘጋጀት ለኢትዮጵያ ዳር ደንበር ለማስከበር ለተዘጋጁት ኢትዮጵያውያን!

የኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ ለባዕድ መሰጠቱን በዓለም ዙሪያ ላሉ ኢትዮጵያውያን በመግለጽና የሀገሪቱን ታሪክ ያውቃሉ የተባሉትን ምሁራንና በደንበር ከተማና ገጠር ንዋሪ የሆኑትን ብቻ ሳይሆን ሱዳን ውስጥ ከታሰሩበት ቦታ በስልክ አነጋግረው ችግራቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቅላቸው በማድረግ የታገሉ የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮንና የጀርመን ድምጽ የራዲዮ ጣቢያ የአማርኛ ዜና ዘጋቢዮችና ሠራተኞች! የግል የዜና አውታሮችና (ጋል ቶክ) አዘጋጆች! ስለደንበሩ ለደከሙ ኢትዮጵያውያን!

ለጀኔራል ነጋ ተገኝና ለኮሎኔል አስናቀ እንግዳ፤እንዲሁም ለአቶ አሰፋ ጫቦ! ለጋንቤላው ተወላጅ ለአቶ አባንግ! እንዲሁም ደግሞ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ (ኦርቶዶክስ) ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና መሠረቱን ዶግማና ቀኖናውን ለያይተው ለሚያስተምሩ ለአባ ወልደተንሣይ አያልነህና በስደት ዓለም ላሉ የቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎች! የወንጌል ዝበሬዎች! በመጨረሻ ለጸኛ ወይዘሪት ብርቱካን ዴመቅሳ እና ለሥልጣኑ ሕዝብ ለዲሞክራሲ ሲታገሉ ደማቸው ለፈሰሰው ኢትዮጵያውያን መታሰቢያ ትሁናቸው::

በሃይማኖት ሆነ በሕግ መጽሐፍት
እንደጻዋሽ ነበር ትእዛዛት ቀደምት
እውነት ተደብቃ ውሸት ተከብራለች
ካልዋሸሽ ተብላ ብርቱካን ታስራለች
ይታወቅ እውነቱ ንገሪያቸው አትስጪቸው ጤና
ሁልግዜም ደህና ሰው አላሉሽምና
አለኝ ብሩኅ ተሥፋ በኢትዮጵያ አገሬ
ጭማቂ እጠጣለሁ ከብርቱካን ፍሬ::



## ምዕራፍ 2
## ፈር አስጨባጭ

ይህን ከጋንቤላ እስከ ሁመራ የተባለውን መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሳሁበትን ምክንያት ቅድሚያ ላብራራ ይፈቀድልኝ:: 2000 ዓም ላይ የዳ/ዊ አጤ ቴዎድሮስ የ140 ዓመታቸው መታሰቢያ አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ የተባለ መጽሐፍ ለመጻፍ ጀምሬ በማጠቃለል ላይ ሳለሁ የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ሁኔታ መነሳት ጀመረ:: ይህን የድንበር ጉዳይ ከመጽሐፉ ውስጥ በአንድ ክፍል ለማጠቃለል አስቤ ስጀምር መጽሐፉ ትልቅ ሆነብኝ:: በዚህ ወቅት አቶ ፈንታሁን ጥሩነህን ስለ ሁኔታው አማከርኳቸው እርሳቸውም "ድንበሩን በተመለከተ ራሱን ችሎ በአንድ መጽሐፍ ቢወጣ ይሻላል:: የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ለብቻው ይውጣ" አሉኝ:: እኔም ከዚያ በኋላ መልቀምና መልክ እንዲይዝ ማስተካከል ስጀምር ብዙ ወራት ወሰደ::

የኢትዮጵያ ችግር ከአደር አደር እየባሰ እንጂ እየተሻሻለ ባለመምጣቱ የነበራትን ገናና ታሪክ ሳነብ አለቅሳለሁ:: በተለይ ነባሩን ታሪኳን ስመለከት ሰላም ይነሳኛል:: አገር የሚመራው ድርጅት ስልጣኑን ለማሰንበት ሲል ብቻ የኢትዮጵያን ከጋንቤላ እስከ ሁመራ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ለሱዳን አሳልፎ ሊሰጥ መሆኑን የተለያዩ የዜና አውታሮች የንፋስ ድምጽ ራዲዮ ዘግበዋል::

ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንድነት ተነስቶ ዳር ደንበሩን ማስከበር ይኖርበታል:: እንዲሁም በሃይማኖት ምክንያት የሚደረገው ጠብና ግድያ ማቆም ይኖርበታል የሚል እምነት አንጸባርቄአለ:: ይህ መጽሐፍ ግለሰቦች በተናገሩትና በጻፉት ላይም ነጥቦችን በማንሳት በሰነድ አስደግፎ መልስ ይሰጣል::ጠቅለል ባለ መልኩ ድርጅቶችን ሆነ ምሁራንን መንቀፉን ዘግቧል:: በመጨረሻ ግን የአጤ ቴዎድሮስ አጽም የት ይውደቅ ብሎ ጥያቄ አቅርቦ ያልፋል::

አንባቢያን ለማስገንዘብ የምፈልገው ነገር ቢኖር እኔ የምጽፈው አንዱን ቡድን ለማስደሰት ሌላውን ቡድን ለማስከፋት አይደለም:: መጽሐፉን ብትገዙት ባትገዙት እኔ ግድ የለኝም:: እኔን ደስ የሚለኝ ነገር መጽሐፉ ከማተሚያ ቤት ወጥቶ ከተወሰኑ አንባቢያን እጅ ከገባ በኋላ ትልቅ ደስታ ይሰማኛል:: የእኔ ትርፍ የተሰማኝን መግለጽ የሀገሬን ጉዳይ መግለጽ ነው:: ሌላው ሳሳስብ የምወደው ነገር ቢኖር ይህ መጽሐፍ በቋንቋ ጥራት በቃላት አመራረጥ ረገድ ከታየ እኔ ለዚህ ዓይነት ብዙም አልሰጎድበትም:: ለእኔ ጥራትና ብቃት ብዬ የምወስደው በያንዳንዱ ምዕራፍ በዋቢ ሠነድ መዝግቦ ማቅረብን ነው:: ሌሎች ጊዜውም የሰው ኃይልም ኑሮአቸው ለአንባቢ ማራኪ አድርገው ያቀርባሉ:: ለዚህ እኔ አልሆንኩም::

መጽሐፉ ይሸጥልኛል በሚል ወይም እኔ እገሌን አስደስታለሁ በሚል ለመጻፍ ስላልተነሳሁ የብዙ ሰዎች ስም ሊነቀፉ ይችል ይሆናል። ይህ ነቀፌታ ለተረዳው ቂመኛ ነቀፌታ ሳይሆን ጤነኛ ነቀፌታ ነው። ለወደፊቱ መንቃቀፍ ትምህርት እንዲሆነን በር ይከፍታል የሚል እምነት አለኝ። ባይገርማችሁ ከሚያኮርፉት መካከል ተነቃፊው ብቻ ሳይሆን የተነቃፊው ባልንጀራና ቤተሰብ ነኝ ባዩ ነው። በውጭ አገር በአሜሪካ ስንኖር የኢትዮጵያ ታሪክና ሁለመናውን ጠብ ርግፍ አድርገን ከተውነው ውለን አድረናል። ነገር ግን መተቻቸትና መነቃቀፍን በስዓት ስብሰባ ሆነ ግብግ አለመገኘትን በተመለከተ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ሁሌም ተሎ አይመጣም አልያም ደግሞ እርሱ ማነው እኔንና እኛን የነቀፈ እንላለን ለምን?።

ይህ ከጋንቤላ እስከ ሁመራ የተባለው መጽሐፍ በ5 ክፍልና በ30 ምዕራፍ የተከፈለ ሲሆን በእርግጥ አንዳንድ ምዕራፍ ረዘም ይላል። እኔ ከሌሎች ደራሲያን ጥቅስ ስወስድ መጽሐፉ በታተመበት ማዕረግና ስም እመዘግባለሁ። ከዚያም አንድን መጽሐፍ ከመጽሐፌ በፊት የደራሲውን ስም ከጻፍኩ በኋላ በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ "---"ሲሉ ጽፈዋል እያልኩ እጽፋለሁ። ሁለተኛ ያነን መጽሐፍ ከሌላ ምዕራፍ ላይ ጥቅስ ስወስድ መጽሐፉን እንጂ የደራሲውን ስም አልጠቅስም። 65 ገጽ ከሆነው መጽሐፍ ይባላል። መጣጥፍ ደግሞ ከ5 ገጽ እስከ 64 ገጽ ያለው ይሆናል። ከ1 ገጽ እስከ 4 ገጽ በራሪ ወረቀት ይባላል። ጥቅስ እስካልተወሰደ ድረስ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው።

አላንባቢያን ማሳሰቢያ ከጎንደር ወደ ትግሬ የተከለሉትን ወረዳዎችን በተመለከተ ጠቅለል ባለ መልኩ "ወልቃይት" እያልኩ እጽፋለሁ። ወልቃይት የጎንደሬው ብቻ ሳይሆን የአማራው አባት ዋና ባድማ ስለሆነ ወልቃይት እያልኩ እጽፋለሁ። ወልቃይት ሰፊና ትልቅ አገር የነበረ በመሆኑ ሌሎችን ወረዳዎች ቀርቶ የአማራውን ሕዝብ አጠቃሎ ሊይዝ የሚችል አገር በመሆኑ ወልቃይት እያልኩ እጽፋለሁ። እንዲያውም ወልቃይት ያለ ሕግ ከጎንደር ወደ ትግሬ የተከለለ በመሆኑ በጎንደር ያሉትን ወረዳዎች ብቻ ሳይሆን ከወሎ ወደ ትግሬ የተከለሉትን ወረዳዎች ሳይቀር ያጠቃልላል። ምክንያቱም ከወሎ ወደ ትግሬ የተወሰዱት ወረዳዎች ያለ ሕግ መሆኑን ታሪክ ይነግረናል። ሌላው መጽሐፍ በጎንደር ላይ ጠበቅ አድርጎ የያዘ ይመስላል። እኔ ጠብቤ ለመሄድ ፈልጌ ሳይሆን 1ኛ ሁኔታው የተከሰተበት በመሆኑ 2ኛ ደግሞ ሰነዶች የበዙበት በመሆኑ እንጂ በሌላ አለመሆኑን ለአንባቢያን አሳስባለው።

መልካም ንባብ አማረ አፈለ ብሻው!



## ምዕራፍ 3
## በታሪካችን እንኩራ እንጅ አንፈር!

አባ ቀውስጦስ የስሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ ይግባኝ ለክርስቶስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 58 "ምን አልባት ሳይሰሙን ምን አደከመን እንል ይሆናል። ነገር ግን እነሱ ሰሙም አልሰሙም እኛ መናገር አለብን። ፀሐይ የሚሞቀኝ የለም ብላ ከመውጣት፤ወንዝም የሚጠጣኝ የለም ብሎ ከመፍሰስ እንደማያቋርጥ ሁሉ መምሕራንም የሚሰማን የለም ብለን ዝም ማለት የለብንም" ሲሉ ጽፈዋል። "መምሕራንም የሚሰማኝ የለም ብለን ዝም ማለት የለብንም" የሚለውን ጥቅስ ስወስድ እራሴን መምሕራን አድርጌ ቆጥሬ እንዳልሆን እንድትገነዘቡልኝ አደራ እላለሁ። የጥቅሱ መዝጊያ ስለሆነ ለመጨረስ ፈልጌ ነው። የብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ አባባል ደግመን ደጋግመን ማለት ላልሰሙት ማሰማት ይኖርብናል። ጉዳዩ የማንነት መሰረት በመሆኑ ነው።

ይድነቃቸው ተሰማ፥ ሰምና ወርቅ ተሰማ እሸቴ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 41
"ባለስልጣኖቹ እስኪያስቡበት
መናገራችሁን እንዳትተውት"
ሲሉ ጽፈዋል። ዓላማችን ከግቡ እስኪደርስ ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን ጠንክረን መግፋት እንዳለብን ያመለክተናል። እኔም ተስፋ ሳልቆርጥ የኢትዮጵያን ባህልና ታሪክ ቋንቋ ትውልዱ እንዲያውቅ ያቅሜን በምጽፈው መጽሐፍ መግቢያ ሁሌም አንርሳ ማለቴን አልተውም። አንድ አይነት ኮትና ሱሪ ለብሳችሁ ሼሚዝና ከራባት ከሌለው መልካም ቆዳ ጫማ ለብሳችሁ የእግር ሹራብ ከሌለው ያምራል? የፈለግነውን ያህል ብንሰለጥን ያለ የራስ ታሪክና ባሕል ቋንቋ ሊኮራ አይቻልም። ለአንባቢያን የማሳስበው ሁሌም አንድ ነገር አለ! ያም ቋንቋችን፥ባህላችን የማንነት መለያችንን ማክበር የአገራችን የኢትዮጵያን ስም አረቦች "ሀበሻ" አውሮፓውያን "አብሲኒያ" የሚሉነን ፈጽመን መቀበል የለብንም። አገራችን ስሟ ኢትዮጵያ እንጂ የውጭ ሰዎች በሰጡን ስም አንጠቀም! እያልኩ የታሪክ ማስረጃ እየጠቀስኩ ሳሳስብ ቆይቻለሁ። ዛሬም አሳስባለሁ።

ዶ/ር ሒሩት ወልደ ማርያም ሐመር መጽሔት 15ኛ ዓመት ቁጥር 16 የካቲት/መጋቢት 2 ሺህ ዓም ገጽ 21 "እኛ ሁሉን ነገር ከውጭ ሲመጣ ነው የሚያምረን ልክ የሚመስለን ይኼን ዝቅተኛ አመለካከት ማስወገድ አለብን። ለራሳችን ለሀገራችን ለሕዝባችን ለዕውቀታችን ለሃይማኖታችን ለባህላችን ቀና በጎ የሆነ አመለካከት እንዲኖረን ያስፈልጋል። ራሳችን በራሳችን ካላከበርን ሀብታችንን ታሪካችንን በጥንቃቄ ካልያዝን ማንም አያከብረንም። ሌላውም የሚከብረን የራሳችን ስናከብር ነው" ብለዋል። በእርግጥ በተለይ ለዘመናዊ

የአመጽ አማኞች ባህልን፣ሃይማኖትን ማክበር እንደ ባዕድ አምልኮ ስለሚቆጥሩት እኛም ይህን እየሰማን ማስተጋባት የለብንም::

መምሕር ብሩክ ገብረ ሊባኖስ ማደስ ወይስ ማፍረስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 103" ኢትዮጵያውያን ፕሮቴስንታስት ስለታሪክና ቅርጽ ጥላቻ ያደረበት አንድ ኢትዮጵያዊ ፓስተር በአንድ ፕሮግራም ላይ ሲጸልይ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ የታሪክና የቅርጽ የባህልና የሥርዓት ፍቅር ከዚህ ሕዝብ አእምሮ ታስወጣ ዘንድ በኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ ብሎ ጸለዬ" ሲሉ ጽፈዋል:: የኢትዮጵያን ታሪክና ቋንቋ ባህል እኛ አክብረን ሌሎች እንዲያከብሩ ማስተማር ይኖርብናል:: በእርግጥ በዛሬው ዘመን በተለይ በውጪ ዓለም ያለን ኢትዮጵያውያን ዘመናዊ ምሁራን ብቻ ሳይሆኑ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ምሁራን ሳይቀር በግዕዝ ቋንቋ ከመጻፍ በፈረንጅ ቋንቋ የሚጽፉ ብዙ ናቸው:: በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ የቤተ ክህነት ተማሪዎች ማክበርና ማስከበር ያለባቸው ግዕዝ ቋንቋን መሆኑን ረስተው ወይም ዘንግተው ሲጽፉ የሚታዩ በፈረንጅ ቋንቋ ነው:: ካህናትና የቤተ ክርስቲያን መምሕራን ጉራማይሌ ቋንቋ መጠቀም ከጀመሩ ውለው አድረዋል:: ይህ ሊታሰብበት የሚገባ በውጭ አገር ያላችሁ ሆናችሁ በአገር ቤት ያላችሁ የቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተማር ስትነሱ ጥሪት ባለ በአማርኛ ካስተማራችሁ ምዕመናኑ እናንተንም ሊያከብራችሁ ይችላል:: ሕዝበ ክርስቲያኑም ባህሉን ቋንቋውን እንዲያከብር ይሆናል:: ነገር ግን ሕጻናትን ለማስተማር ከሆነ በሚገባቸው ቋንቋ አስተምሯቸው::

ለምሳሌ "እርቶዶክስ" ሃይማኖት ተከታዮች ነን ማለት ምን ማለት እንደሆነ በጥሞና ልናጤነው ይገባል:: ሌሎች አርቶዶክስ አማኞች ታቦት የላቸውም:: ለምሳሌ የግብጽ አርቶዶክስ ሃይማኖት ካህናት ሆኑ ጳጳሱ አይገረዙም:: ከእኛ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጾሞች አሉ በሌሎች አርቶዶክሶች የእኛን ያክል ጾም የላቸውም::የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶዎች ደግሞ አሪትን ከወንጌል አጣምረን የምናመልክ ነን:: በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ሃይማኖት ብለን ልንጠራ ይገባናል ይላሉ:: ከዚህ መጽሐፍ ጥቅስ እስካልተወሰደ ድረስ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እያልኩ እጽፋለሁ የኢትዮጵያ ቀመር የራሳችን ሲሆን ከኖህ ጀምሮ የመጣ አቆጣጠር ነው:: የሰው ወርቅ አያደምቅ! እንደሚባለው ነው እንጂ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የኢትዮጵያን 2000 ዓም በዓል (ምሊንየም) መከበር ይኖርበታል ብለው እያከበሩት ባሉበት ወቅት እኛው ኢትዮጵያውያን የራሳችን የቀን መቁጠሪያ ማክበሩን ትተነዋል:: ለምሳሌ አንድ ወዳጄ መጽሐፍ ሜጋ ማከፋፍያ ገዝተው ልከውልኛል:: በመርሳት ደረሰኙ ከመጽሐፉ ውስጥ አብሮ መጥቶ ስመለከተው በኢትዮጵያ ቀን ሳይሆን የተጻፈው በጎርጎሬዎስ ቀን መቁጠሪያ ነው ለምን?

ሜጋ ማከፋፈያ ኃ/ተ/የግ/ማኅበር ደረሰኝ ቀን 22/3/08 ይላል:: በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ አገር በቀል የሆነ ድርጅት የሚያዘጋጀውን ደረሰኝ በአገሩ የቀን መቁጠሪያ ማዘጋጀት ሲገባው እንዴት ቅኝ ገዥ በሆነው የጎርጎሬዎስ



የቀን መቁጠሪያ (ካላንደር)ደረሰኝ አዘጋጅቶ እየጻፉ ሕዝቡ ማንነቱን እንዲረሳ ያደርጋል? ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ሳሳስብ እወዳለሁ:: አባቶቻችን የሚሉት አባባል አለ ያም "መንገድ በምን ይቀራል" ይላሉ:: ለምሳሌ መንገድ ከሚሄዱ ሰዎች መካከል አንዱ ልጠዳዳ ብሎ ሲቀር ባልንጀሮቹ ብዙ ጎዳና ሕደዋል:: ይህ ሊጸዳዳ ወደ ኋላ የቀረው ሰው ከእነዚህ ሰዎች ለመድረስ ልቡ እስኪጠፋ መሮጥ አለበት:: አለበለዚያ ብቻውን ይሆንና ለብዙ አደጋ ይጋለጣል:: አንድ ነገር በጊዜው ሊታረም ካልቻለ ከዋለ ካደረ ስተቶች በዝተው ኋላ ለመመለስ ችግር ይሆናል:: የቀን መቁጠሪያችን ሆነ ግዕዝ ፊደላችን እህንግዜ አጥብቀን መያዝ ይኖርብናል:: ጊዜ ከተሰጠው ከዋለ ካደረ "እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ" እንደተባለው እንዳንሆን እናስብበት::

አስቻለው ከበደ ክርክቤዴል ሳዶፍ ኢትዮጵያና የሰማይ ኃያላት በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 52 "በግዕዝ ሰብዕ ማለት ሰው ማለት ሲሆን በኦሮመኛ ሰባ ጉዳ ማለት ሕዝብ የሚል ትርጓሜ ይሰጣል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚተነትኑት በግዕዝ ሰብዕ የሚለው የሰው መጠሪያ ቃል ሰብዐ (ሰባት) ከሚለው ቁጥር የተወሰደ ሲሆን ይህም የሰው ተፈጥሮ ከአራት የመሬት ባህሪ (መሬት÷ውኃ+ንፋስና እሳት)እና ከሶስት የመለኮት ባሕሪ (ነቢባት ሃያዊትና ልባዊት) በአጠቃላይ ከሰባት ባህሪ የተፈጠረ መሆኑን ለማመልከት ነው:: እያንዳንዱ የግዕዝ ፊደላት ለምሳሌ ከሀ ግዕዝ እስከ ሆሳብዕ ያለው የፊደል ቆጠራ በሰባቱ ቀናትና በሰባቱ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ተመሳጥሮ የተቀናበረ መሆኑን ነው" ሲሉ ጽፈዋል:: የራስን ታሪክ ማወቅ ይጠቅማል:: ጥቅሙም ለራስ ብቻ ሳይሆን እልፍ ለጎረቤት ልጅ ይሆናል:: ቀስ እያለ ከጎረቤት ወደ መንደር ከመንደር ወደ ደብር ከደብር ወደ ምክትል ከምክትል ወደ ወረዳ ከወረዳ ወደ አውራጃ ከአውራጃ ወደ ክፍለ ሀገር ከክፍለ ሀገር ወደ ሐገር ይዛመታል:: ስለዚህ የራስን ቋንቋ ታሪክና ባህል ሃይማኖት መጠበቅ ስልጥንና እንጂ ኋላቀርነት አይደለም::

አለቃ ታየ ወልደማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 6 "ታሪክ መማርና ማወቅ ለብዙ ነገር ይጠቅማል:: መጀመሪያ የድንቁርና ዕውርነት ዓይን ይከፍታል:: ሁለተኛ ሰው የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት የፍጥረቱንም ብዛትና የልዩ ልዩ ወገንንም ዓይነት የዓለምንም ታላቅነትና ሰፋት ያይበታል:: ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ እስከ ዘመን የሆነውን ሁሉ ነገር ሲማር ጥንት እንደ ተፈጠሩ አስቀድሞ እንደ ነበረ ሁኖ ያውቃል:: በዓለም ያሉን ልዩ ልዩ ሕዝብ አገራቸውና ጠባያቸውን ያምላኮቻቸውን የመንግሥታቸውን ሥርዓትና አኗኗራቸውን በታሪክ ሲመለከት ሲመረምር ሲያስተውልም በቤቱ ተቀምጦ ዓለም ሁሉ ዙሮ መርምሮ እንዳየ ሰው ይሆናል" ሲሉ ጽፈዋል::

## ምዕራፍ 4
## ለአንባቢያን ከፀሐፊው!

ከዚህ በፊት በጻፍኳቸው መጽሐፍት በተለይ አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች በተባለውና የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፎቼ ላይ አንባቢያን አንዳንዶች አልተደሰታችሁም። በእርግጥ አንድ ግለሰብ ሁሉንም ሊያስደስት አይችልም። አስተያየታችሁን ለጻፋችሁልኝ እጅግ በጣም ከልብ አመሰግናለሁ። ነገር ግን ጓደኞቻችሁ አንብበው የነገሯችሁን ይዛችሁ እናንተ ሳታነቡት ለጻፋችሁልኝ አንባቢያን አክብሮት የለኝም። ተውሳችሁ ሆነ ገዝታችሁ ገጽ በገጽ ጠንካራ ጎኑንና ደካማ ጎኑን ገምግማችሁ ለጻፋችሁልኝ አንባቢያን በድጋሚ ከልብ አመሰግናለሁ። አንባቢዮቼ የተቀየማችሁበት በሁለት ምክንያት ነው።

"1ኛው የኤርትራን ካርታ ከኢትዮጵያ ካርታ አውጥተሃል
2ኛው ወያኔንና የትግሬን ሕዝብ በአንዳይን አትቶ ትላለህ" የሚሉ ናቸው።

1ኛውን አስተያየት በተመለከተ ምዕራፍ ከፍቼ መልስ ልሰጥበት አልፈልግም ነበር ነገር ግን በብዛት የመጣው አስተያየት በመሆኑ መልስ አስፈለገው። 2ኛውን አስተያየት በተመለከተ ክፍል 5 ምዕራፍ 2 እንድታነቡ እላለሁ። ወደ 1ኛው አስተያየት ልመለስና የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድ ናቸው። ደጋው የኤርትራ ሕዝብ ከጎንደር ደንቢያ ቋራ፤ በተለይ ብሌኑ ከጎጃም አገው ምድርና ከወሎ ሰቆጣ የሄደ ሲሆን ሌላው የሀማሴኑ ሕዝብ ደግሞ ከትግራይ አጋሜ የሔደ ነው። ራሳቸው ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ አፍወርቅ ትግሬ ናቸው። ነገር ግን በታሪክ አጋጣሚ ቅኝ ገዥዎች ከቀደም ጀምሮ በምጽዋ ብቅ እያሉ ስለቆዩ ሕዝቡን ባንዳ አድርገውታል። ይህ አባቶቼ ባንዳ የሆነ ትውልድ በ4ኛው አጤ ዮሐንስ ዘመን እንራስ ወልደ ሚካኤል የግብጽን ጦር መርተው የመጡ ናቸው። ከዚያም ግብጽ በ4ኛው አጤ ዮሃንስ ጀግንነት ተደብድቦ ሲባረር ባንዶች አፈሩ። ኋላም ጣልያን ቀስ በቀስ መግባት ሲጀምር ሁኔታው ልውጥውጥ እያለ ይሄድ ጀመር። ጣሊያን መላ ባሕረ ነጋሽን ተቆጣጥሮ ስሟን ኤርትራ ብሎ ጠራት። ከዚያም በአድዋ ጦርነት ድል ሲሆን ጣልያን ባለበት ቆመ። በዚህ ወቅት የባህረ ነጋሽ ሕዝብ ባንዳ ያልሆነው ከቈስ እስከ ንጋዴ ወደ ኢትዮጵያ እየመጣ ይኖር ጀመር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ እንደ ዜጎቹ ቆጥሮ እያስተማረ አንሮአቸዋል። በኤርትራ የነበሩ ከ4ኛ ክፍል በላይ አይማሩም ነበር። ከዚያም ወታደርነት እንጂ ሌላ ከፍት ስራ አልሰጣቸውም። በ1928 ዓም ጣልያን የአድዋን ደም ለመመለስ ወደ ኢትዮጵያ ሲዘምት ኤርትራውያን ታጥወቅ ኢትዮጵያን ወግቷል። ከሚገርማችሁ ነገር ቢኖር እነዚህ ኤርትራውያን ከጦርነቱ ሲመቱ ጣልያኖች አይቀብሯቸውም ነበር።



ጳውሎስ ኞኞ <u>የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 129 "በጦር ሜዳ የወደቁትን የኢጣሊያኖችን ራሳ ብቻ ጥቁር ተወላጆች እያነሱ እንዲቀብሩና የጥቁሩን ራሳ እንደወደቀ እንዲተውት ከኢጣሊያ አለቆቻቸው ጥቁር ወታደሮች ታዘዙ። ሹምባሽ አንዶም ተስፋጽዮን ወደ ኢጣሊያዊው አለቃቸው ቀርበው ጥቁሮች ከነጮች ጋር አብረው ጎን ለጎን እየተዋጉ ሁሉ በቀብር ጊዜ ለምን ልዩነት ይደረጋል? ብለው ጠየቁ። ይህ ጥያቄ በኢጣሊያኖች ዘንድ እንደ ድፍረት ስለተቆጠረ ሹምባሽ አንዶም ተቀጡ። ሹምባሽም ሌሊቱን አምልጠው ከኢትዮጵያውያን ጋር ተደባለቁ። ከዚህ በኋላ ብዙ ኤርትራ ተወላጆች ከኢጣሊያ እየከዱ ወጡ" ሲሉ ጽፈዋል። ኤርትራውያን ከጣሊያን እየከዱ ወደ ኢትዮጵያውያን የተቀላቀሉት ቀንበር ጠቦባቸው እንጂ ለኢትዮጵያ ነፃነት ብለው አልነበረም። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ኤርትራውያንን እንወዳቸው ነበር። ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ በ1929 ዓም የጣሊያ ጦር እጃቸውን እንዲሰጡ ሲጠየቁ ምህረት የጠየቁ ከላይ የተጠቀሰው ከጣልያን ከድተው ከርሳቸው ጋር ለነበሩ ኤርትራውያን ነበር።

ሀዲስ አለማየሁ <u>ትዝታ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 187 "1ኛ ከኢጣሊያ ጦር ሠራዊት አምልጠው በዚያ ጊዜ ከራስ እምሩ ጦር ጋር የነበሩትን ኤርትራውያን ከሌሎች የራስ ሠራዊት አባሎች የተለዩ ቅጣት እንዳያገኛቸው ሙሉ ምህረት እንዲደረግላቸው" የሚል ጥያቄ ነበር ያቀረቡት ሲሉ ጽፈዋል። ኤርትራውያንን በተመለከተ ምን ራስ እምሩ ብቻ ራስ ካሳ በማይጨው የጦር ግንባር ላይ ቅድሚያ የሚመጡት ኤርትራውያን ወታደሮች በመሆናቸው በእነሱ ላይ ጥይት መተኮስ ልባቸውን ያቆስለው እንደነበር በ1929 ዓም በስደቱ ወቅት ለአንድ የፈረንሳይ ተወላጅ ለአጤ ኃይለ ሥላሴ ጥያቄና መልስ ሲያደርግላቸው ራስ ካሳም እንዲሁ የሰጡት መልስ አለ። ያን በፈረንሳይኛ ተጽፎ የነበረ መጽሐፍ በቅርቡ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ለንባብ ቀርቧል።

ጸሐፊ ማርሴል ግሪዮል ተርጓሚ ሳቀች አክሊሉ <u>የንጉሠ ነገሥቱ ትውስታ በ1929 ዓም</u> በተባለው መጽሐፍ ራስ ካሳ በገጽ 59 "የመጀመሪያውን አጥቂ ኃይል መትተው የሚጋርዱ የኤርትራ ወታደሮች ከዚያ ቀጥሉ መሣሪያ ታግዘው የሚዋጉ የመንግሥት ወታደሮች ቀጥሉ ደግሞ ከፊተኞቹ እጅግ የከፋ የሚመስሉና ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ ብቅ የሚሉ ፋሺስቶች ናቸው። ፋሽስቶች ከሌሎቹ ቋሚ ወታደሮች በበለጠ ሁኔታ ጦርነቱን በጋለ መንፈስ ተሚልተው ያካሂዱታል። ተራ ወታደሮቻቸውን መስራት የማይፈልጉትን ሥራ ሁሉ እንዲሰሩ የሚያስገድዱዋቸው ይመስላል። እነኚህ ቋሚ ወታደሮች ምንም እንደ ፋሽስቶቹ ብዙ ፍላጎት ባይኖራቸውም ከኤርትራውያኑ የበለጠ ፍላጎት ነበራቸው። እጅግ የበረቱት ከኋላ በመሆናቸው የፊተኞቹን ወደፊት ይገፏዋቸው ነበር። ይህም አመጻደብ በነጮቹና በኛ መሀል የደም ወንድሞቻችንን አስመርተው ጣልቃ በማስገባታቸው እነዚህን ማጥቃት ልባችንን ያውከው ነበር። እንዲህ ያለውን ድርጊት ማወዳደር የሚቻለው በጣሊያኖቹ ፊት ሕፃናትና ሴቶችን እንደማሰለፍ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የታሪክ መጽሐፍት በጥሞና ላስተዋለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኤርትራውያንን እንወዳቸው ነበር። ይህ ሁኖ ጣልያን በኢትዮጵያ አርበኞች

ተደብድቦ ሲደክም የሁለተኛው ዓለም ጦርነት አውሮፓ ተጀምሮ ስለነበር ትንሽ ርዳታ እንግሊዞች አድርገው ጠላት መባረሩ አይካድም። እንግሊዞች አስመራ ላይ በነበሩበት ወቅት የኤርትራ ሕዝብ ወደ ኢትዮጵያ መቀላቀል ይፈልግ እንደነበር ታሪክ ዘግቦታል።

ሹመት ሲሻኝ የኤርትራ ሕዝቦች የአንድነት ትግል በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 8" ከኢትዮጵያ ጋር እንቀላቀል የሚለው ጥያቄ በአገሩ በሰፊው የተሰራጨ መሆኑን በመጥቀስ ጉራራ ውስጥ ይሰራ የነበር አንድ አሜሪካዊ ተመልካች ለፕሬዝዳንት ሩዝቬልት በመጋቢት 1935 ዓም በጻፈው ማመልከቻ ላይ በኤርትራ የሰሜን ጠረፍ ላይ የሚገኙት ጎሳዎች እንኳ ሳይቀሩ ኢትዮጵያውያን ነን ብለው ቆመዋል። በአስመራ፣በምጽዋ፣በከረንና በሌሎችም ከተማዎች ውስጥ ያሉ ሱቆች የኃይለ ሥላሴን ፎቶግራፍ በግድግዳው ያልሰቀለ የለም። ራሱ የእንግሊዝ አስተዳደርም ቢሆን ይፋ በሚያወጣቸው መግለጫዎች አይጥቀሰው እንጂ በውስጥ ሪፖርቶቹ የአብዛኛው ሕዝብ ምኞት ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድ መሆኑን ያረጋግጣሉ በ1936 ዓም አጋማሽ ላይ ብርጋዴር ሎንግሪግ ወደ ሎንደን ባስተላለፈው ዘገባ ላይ የተማረው ወጣት እንዳለ የአንድነት ታጋይ ነው። ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች እንዲሁም በተዋህዶ አገር ሰፊ ገቢያ እናገኛለን ብለው ተስፋ የሚያደርጉ ነጋዴዎችም ለአንድነት ቆመዋል ይላል" ሲሉ ሊቀ ጠበብት ሹመት ሲሻኝ ጽፈዋል። ኤርትራውያን ይህን ብለው በመነሳታቸው በታሳቀ የድርድር ዲፕሎማት ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ጥረት 700 ሰዓት ገለፃ በማድረግ 300 ሰዓት በአውሮፕላን ተጉዘው የተባበሩት መንግሥታት ወኪል እንዲልክ ሁኖ ሕዝቡ መዋሐድን መርጦ ሳለ (ፌዴሬሽን) የሚለውን ቢያስቀምጥባቸውም በራሳቸው የተጣለባቸውን በጥሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲቀላቀሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍቅር አያቸው እንጂ አሳገለላቸውም። የአጤው መንግሥት ከፍተኛ የሆነ ተቋም መስርተው እነሱን ለማስደሰት ጥረት አድርገዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን ልማት እያደረገ ኤርትራውያን ከአረብ አገሮች ጋር ተለጣፊ ሁነው ጀበሃን መሰረቱ።

አበራ ለማ ኢትኦጵ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 13 ሰኔ 1992 ዓም ገጽ 16 "ከ300 በላይ የሚሆኑ የመንግሥት ወታደሮችን በተለያዩ ውጊያዎች ላይ ማርኮ አሊጊደር በሚባል ሥፍራ በአሰቃቂ ሁኔታ አስሮ ለረዥም ጊዜ አቆይቷቸው ነበር። እኛ ወደ ተሰነይ እያጠቃን መጠጋታችንን ሲያውቁ እነዚያን ምርኮኞች ወታደሮች በሙሉ ከእስር ቤት አውጥቶ እጅና እግራቸውን እያሰረ በመትረየስ አጨዳቸው። ቀጥሎም ቤንዚን እያርከፈከፈ አቃጠላቸው፡ ጀብሃ ይህን ዘግናኝ እልቂት ከፈፀመ በኋላ የጋሽን ድልድይ በፈንጅ አፈራርሶ ሸሽቶ ጠበቀን ያንን እልቂት በዓይኔ አየሁ። እመራው በነበረው የጋዜጠኞች ቡድን አማካኝነት ድርጊቱን በካሜራ ቀረፅን ቆስለው የተረፉ 2 ወታደሮችን ቃል መጠየቅ አደረግንላቸው። ሙሉ ዘገባውን ሠርቼ ለሬዲዮ ስርጨት አቀረብኩ። ቢሮክራሲው የሻጥር እጁን ጫነበትና ከስርጭት አገደው። እኔና የቅርብ አለቃዬ አቶ የወንድወሰን ዓለሙ ሃዘናችንን ውጠን ቀረን" ሲሉ ጽፈዋል። ይህን የመሰለ ሌላም ታሪክ መጥቀስ ይቻላል።



ግደይ ባህር ሹም አሞራ በተባለው መጽሐፋቸው ሻዕቢያ ምርኮኛን ከጎድጓዳ መሬት ላይ አጠራቅመው በርሃብና በጥማት ሲደክሙ አሞራው እየበላቸው የሞቱ መሆናቸውን ጽፈዋል።

ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ ሞት የተፈረደባቸው 17 ሺህ የኢትዮጵያ ሠራዊት አይ ምጽዋ የተባለውን መጽሐፍ እንብቤ አንጀቴ አሯል ከኤርትራውያን ጋር በቅቶኛል። ስለዚህ ከእነሱ ጋር መራቁን እንጂ መደጋገፉን በእኔ እምነት አልፈልግም። የተማረኩት የኢትዮጵያ ወታደሮች የኤርትራን መንገድ እንደሚቆፍሩ

ሻለቃ ስለሽ ፍስሃ አንድነት ለአንድነት በተባለው መጽሐፋቸው ጽፈዋል። ወያኔና ሻዕቢያ ጦርነት ውስጥ ከገቡ ጀምሮ በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያንን ለመውሰድ ሻዕቢያ ያላደረገው ጥረት የለም። ዶ/ር ቅጣው እጅጉ እንደነገሩኝ "የኤርትራ መንግሥት ወያኔን ለመጣል የምትፈልጉ ከሆነ የተማረኩትን ወታደሮች አሰልጥነን እስከ ትጥቃቸው እኔም ያሰለጠናችኋቸው ወታደሮች የት አሉ ብዬ ስጠይቅ መንገድ ከሚሰሩበት ወስደው አሳዩኝ። ከገላቸው ላይ ልብስ የሚታየው ከተፈጥሮ አካላቸው ላይ ብቻ ሲሆን ጫማና ከናቲራ የላቸውም። ለምን ልብስ እንደማያለብሷቸው ስጠይቅ የደርግ ወታደሮች በመሆናቸው ነው" አሉኝ ሲሉ ነግረውኝ ነበር።

በተለይ የማቀርባቸው ወገኖቼ ወደ አስመራ የሚያደርጉትን ጉዞ አጥብቄ ተቃውሜ ነበር። ያን አንጋፋን በዓለም አንቱ የተባለውን ምሁር ሳይንቲስት እንጅነር ቅጣው እጅጉ አላግባብን ብሎ የነበረው ከሻዕቢያ ጋር ተቀራርቦ የጦር መሳሪያ ተቀብሎ ምርኮኞችን ይዞ ኢትዮጵያን ከወያኔ ነፃ ማውጣት ይቻላል በሚለው አመለካከታቸው አለመደገፌ ነበር። ዛሬ ጋሽም አኩርፈው እያናግሩኝም። ያቀያየመን የግል ግጭት ኑሮን ሳይሆን ሻዕቢያ ለኢትዮጵያ ወዳጅ ሊሆን አይችልም በማለቴ ነው። ከሊቅ ዶ/ር ቅጣው ጋር በያዘው እምነቱ ባንግባባም በሌላው ግንኙነታችን ጨርሰን አልቆረጥነውም ነበርና በ1994 ዓም ዋሽንግተን ዲሲ በነበረው የኳስ ጨዋታ ወቅት ከመሄዳችን በፊት ከሰዎች ጋር እንዳገናኛቸው ጠየቁኝ። አኳዮ ከሚኖሩ ከአቶ መልኩ በላይነህ ጋር ኢትዮጵያን አስመልክቶ ሰንወያይ እርሳቸው" በቅርቡ የመሰረትነው ድርጅት አለ ብለው እነ ዶ/ር ስለሽ አያሌው ሲሉ ሰምቻለሁ" ሲሉኝ እኔም "የትጥቅ ትግል አያስፈልግም እላለሁ ደግሞ ከሻዕቢያ ጋር ተገናኝተው ነው እንጂ ዶ/ር ቅጣው፤ የመሰረቱት ድርጅት አለ። ከሰዎች ጋር አገናኘኝ እያሉ ጠይቀውኛል " ስላቸው አቶ መልኩ "ከነዚህ ሰዎች ጋር ከተገናኙ ምናልባት ለወደፊቱ ሁለገብ የሚለውን ዓላማ ወደ ሰላማዊ ትግል ሊቀይሩ ይችሉ ይሆናል እናገናኛቸው አሉኝ። እኔም አሳቡን ሲቀ ዶ/ር ቅጣው ስነግራቸው በጣም ደስ አላቸው።

ዋሽንግተን ዲሲ ስንደርስ ቀኑ ቀጠሮና ሰዓት ተወሰነ። ዶ/ር ቅጣው እጅጉ ካረፉበት ሆቴል ሆነ ስብሰባው። ከዚያም 1ኛ ዶ/ር ስለሽ አያሌው 2ኛ አቶ መልኩ በላይነህ 3ኛ አቶ ክንፈ ተሰፋዬ ሁነው መጡ። አቶ ክንፈ ዶ/ር ስለሽ

ድርጅት ደጋፊ ይሆን አይሁኑ አላውቅም አንድም ቃል አልተነፈሱም። ዋሽንግተን ዲሲ የሚኖሩ የዶ/ር ስለሽ ድርጅት ባልደረባ አቶ ዘነበ፤ ቆየት ብለው መጡ። እኚሁ አቶ ዘነበ አስመራ ደርሰው የመጡ ናቸው። አቶ መልኩና እኔ አገናኝ ስለሆን እኔ "ዶክተር እንጅኔር ሳይንቲስት ቅጣው እጅጉ ይባላሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር ሊቀ መንበር ናቸው" ብዬ አስተዋወኩ። አቶ መልኩ ደግሞ "ዶር ስለሽ አያሌው ይባላል" ብለው የድርጅት ስም አልጠሩም። አቶ ዘነበ ቆይተው መጡ ተሉ ሄዱ። ዶ/ር ቅጣው ወዲያው የድርጅታቸውን መርሃ ግብር ከቦርሳቸው አውጥተው ሰጡ። በነ ዶ/ር ስለሽ አያሌው፤ በኩል የድርጅት ስም ሆነ መርሃ ግብር የለም። ድርጅታቸው ማን እንደሚባል ቅድሚያ ማስተዋወቅ ነበረባቸው ግን አላደረጉም። ዶ/ር ቅጣው ድርጅታችሁ ማን ይባላል አላሉም።

ውይይት ከመጀመሩ በፊት "እኔ ይቅርታ ዶ/ር ስለሽ እንዳዬት ዶ/ር ቅጣው ከእናንተ ጋር የፈለጉት ለመወያየት ነው። የድርጅታቸውን ስም ሆነ መርሃ ግብር ሰጡአችሁ። ነገር ግን እናንተ ድርጅታችሁ ማን ይባላል። መርሃ ግብሩ መተዳደሪያ ደንቡን ለእርሳቸውም ስጡ? ብዬ ተናግሬ ሳልጨርስ ዶ/ር ስለሽ "የድርጅቱ ፕሮግራም ይሰጣል" ብለው ዘጉት። መነጋገር ያለባቸው ሁለቱ በመሆናቸው እኛ አድማጮች ሆን። ታዲያ ዶ/ር ቅጣው "እናንተምኮ ሀሳብ ስጡን" ብለው ወደኛ ውይይቱን አመጡት "እኔ በበኩሌ ቅድም የጠየኩት የድርጅት መርሃ ግብር በነዶ/ር ስለሽ በኩል አልተሰጠም! የድርጅታቸው ስም ማን እንደሚባል አልነገሩንም ሌላው እኔ ሊቀ ቅጣው እንደምታውቀው በግሌ የትጥቅ ትግል ለኢትዮጵያ አያስፈልግም እላለሁ በተለይ ከሻዕቢያ ጋር የሚደረገው ግንኙነት ለኢትዮጵያ አጥፊ ነው" ብዬ ተናግሬ ሳልጨርስ ዶ/ር ስለሽ፡ "ሻዕቢያም ለኢትዮጵያ ቅዱስ ነው! ወያኔን ያለ ትጥቅ ትግል መጣል አይቻልም" አሉ። ከዚያም 6 ሰዓት ሙሉ ውይይት ተደርጎ ካንድ ወር በኋላ ሊገናኙ ተስማምተው ተለያየን። ዶ/ር ስለሽ ከግብር አበሮቻቸው ጋር ተሰብስበው ዋሽንግተን ዲሲ ጠበቁአቸው። በዚህ ቀን ዶ/ር ቅጣውን ብር የሰጡአቸው መሆናቸውን ለእኔና ለአቶ መልኩ ነግረውናል። ይህ የነዶ/ር ስለሺ አያሌው ድርጅት ስሙ ሳይታወቅ ከስሟል። ይህን ታሪክ ላነሳበት የፈለኩበት ምክንያት ምስጢር ለማውጣት ፈልጌ ሳይሆን እኔ ኢትዮጵያ ከሻዕቢያ የምታገኘው ጥቅም የለም ያለ ድህነት በቀር? የሚል አመለካከቴ ዛሬም አልተቀየረም።

ሻዕቢያን ካልደገፍክ የምትሉኝ ወዳጆቼ በእሳት የተቃጠሉትን አሞራ የበላቸው ራቁታቸውን ቀን ፀሐይ ማታ ብርድ የሚፈራረቅባቸውን ወገኖቼን የሞቱት የተሰቃዩት አልበቃ ብሎ ሌላ ለኢትዮጵያ ስቃይ እናምጣ እንዴ? የኢትዮጵያ ሕዝብ በኤርትራ ምድር ደሙ ፈሷል ይህን ያደረገው ወገኖቻችን ናችሁ ብሎ እንጂ በሌላ አይደለም። ሌላው ቀርቶ ከመቶ 98 እጅ የሚሆነው የትግራይ ሕዝብ በ1984 ዓም ንብረቱን ብቻ ሳይሆን ጥርሳቸው ወልቆ የተባረሩት ወገኖቻችን ማስታወስ እፈልጋለሁ በእኔ ዓይን ኤርትራን የማያት እንደ ጎረቤት አገር አድርጌ ነው። የኤርትራን ካርታ ቆርጠው ያወጣሁት ወድጄ አይደለም። እነሱ እኛ ሰላም እንዳናገኝ በጎሳ እንድንከፋፈል አድርገዋል። በእነሱ አገር 9



ጎሳዎች ሲኖሩ ለአንዱ እንኳን እንዲደራጅ አልፈቀዱለትም። ነገር ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር እንዲደራጅ ሲገፉ ኑረዋል። ቀደም አይደለም ዛሬም ይህን ዓላማቸውን እያስፋፉት ናቸው ስለዚህ በእኔ እምነት ከዚህ በፊት አንድ ነን ብለን ገድለውናል ወገኖቻችሁ አይደለነም ካሉን ጨርሰን ልንርቃቸው ይገባል።

<u>የመጽሐፉ አንባቢ</u> ሲጽፉልኝ እንዲህ ብለዋል "እንኳን ዛሬ ቀደም ሲል ተመስርቶ የነበረው ጀብሃ የኤርትራን ክርስቲያኖች ሲገድላቸው ነበር። ዛሬ እስላሞች እየተስፋፉ ናቸው። የእስላም አክራሪዮች በትንሿ ኤርትራ አይደለም በትልቋ ኢትዮጵያም አክራሪነትን ለማስፋፋት የሚያደርጉትን ተንኮል ይጠፋሃል አልልም። ታዲያ የኤርትራ ክርስቲያኖች ሲደበደቡ እኛ ኢትዮጵያውያን ዝም ብለን ልንመለከት ነው?" ሲሉ ጽፈዋል። አባቴ ልበል ወንድሜ አልያም ወገኔ ልበልና መልስ ልስጣቸው "ወደሽ ተተደፋሽ ቢገፉሽ አይከፋሽ" ነው። ልክ ነው እርሶ እንዳሉት ጀብሃ ሲመሰረት ጀምሮ ክርስቲያኖችን መፍጀቱ ይታወቃል ራስ አስራተ ካሳም ክርስቲያኖች ማለቃቸው አሳዝኖአቸው ነበር አቶ ኢሳያስንና ሌሎችን ወደ ጀብሃ ጎራ የላኳቸው። ነገር ግን አቶ ኢሳያስና ባልንጀሮቻቸው በዚያው ሰምጠው ቀሩና ሻዕቢያን መስርተው እንሆ ለኢትዮጵያ ጠላት ሁነዋል። ወገኖቻችን ናችሁ ብለን ስንሞት ኑረናል ለወደፊቱ ኤርትራውያንን እስላሞች ቢያጠቋቸው ከሮማ ወታደር መጥቶ ይርዳቸው እንጂ በእኔ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘምቶ መሞት ቀርቶ በኤርትራ ምክንያት ውሃ እንኳን እንዲጠማው አልፈልግም። ወገናችን ናቸው ባሉን ወቅትማ የኢትዮጵያ ንብረት በኤርትራ ምድር ፈሷል። ስለዚህ በእኔ እምነት አሰብንና አፋርን የኤርትራን ሕዝብ ለይቼ ነው የማያቸው።

ኤርትራንና አሰብ አስተዳደርን በተመለከተ ልዩነት አላቸው። ኤርትራውያን እኛ ወገኖቻችን ናችሁ ስንላቸው እነሱ አይደለነም ብለው ወግተውናል። የአሰብ አስተዳደር ወገኖቻችን አፋሮች ግን እንኳን ሰው ግመሉ የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ያፈቅራል የሚሉ ወገኖቻችን የአፋርን ሕዝብ ለመርዳት መጣሩን አምንበታለሁ። የአፋር ሕዝብ ወገኔ ያለውን መርዳት ትተን እንዴት ኤርትራውያንን ወገኖቻችን አይደላችሁም ያሉትን ለማገዝ እንስሰፋለን? እኔ በበኩሌ የማውቃቸው ኤርትራውያን ባልንጀሮቼን የማያቸው እንደማንኛውም የሰው ልጅ እንጂ እነሱ ዛሬ ከወያኔ ጋር ተጣልተው ወያኔን በመጥላቴ የሆዴን አውጥቼ አልነግራቸውም። የማወጋቸው ሌላ ለላውን ነው። ስለዚህ ከዚህ መጽሐፍ፡ ላይም ቢሆን እምነቴ ኤርትራ ወደድነም ጠላነም አገር ሁናለች። የተባበሩት መንግሥታት 184ኛ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት 53ኛ አገር መሆንዋን ባምንም ቅሉ ወገኔ የሚለኝን የአሰብ አስተዳደር የአፋርን ሕዝብ ግን ከኤርትራ ሕዝብ ለይቼ ማየት እንዳለብኝ አምናለሁ። ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ አፈወርቅ ከጀብሃ ተለይተው የራሳቸውን ድርጅት ከመሰረቱ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ተናግረው አያውቁም። እንዲያውም በ1983 ዓም ኤርትራን ከመቆጣጠራቸው በፊት አውሮፓ ውስጥ የተናገሩት "ለኢትዮጵያ የ100 ዓመት የቤት ስራ ሰጥጫታለሁ" ብለው ነበር። የኢትዮጵያን ሕዝብ

አንድ ሁኖ እንዲኖር አይፈልጉም:: ከወያኔ ጋር በ1990 ዓም ከተጣሉ ወዲህ ደግሞ አፍቃሪ አማራ ሁነው መጥተዋል:: ዛሬ የኢትዮጵያ ጥቅም ሲቀርባቸው ደግሞ በአውሮፓና በአሜሪካ የሚኖሩትን ግለሰቦች በጎሳ ስም እየሰበሰቡ ማደራጀታቸው እየታወቀ "አንዲት ኢትዮጵያ" የሚል መጽሔት አውጥተዋል:: ከኤርትራ ጋዜጠኞች ጋር ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ ያደረጉትን ቃለ መጠየቅ በሶስት ቋንቋ ተጽፎ በቅንጅት ወቅት የሞቱትን ኢትዮጵያውያን ሥዕል ይዞ የወጣው መጽሔት ያነበበ በትክክል እውነት መስሎት የእርሳቸው አሽከር እንደሚሆን ግልጽ ነው::

ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ ሓንቲ አንዲት (ዋን ኢትዮጵያ) በተባለው መጽሔት 2000 ዓም ገጽ 3 " ክፍፍሉን ምክንያት ለማድረግ ሕገ-መንግሥት ነው:: ሕዝብን በብሔር ብሔረሰብ ከፋፍሎ በክልል መወሰን ከዚያ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም:: እውነት ነው:: በብሔር ብሔረሰቦች የነበሩና አሁንም ያሉ ናቸው:: ብሔረሰቦችን በክልል ደረጃ ለይቶ በማደራጀት ሕዝብን መከፋፈል የታየው ግን በወያኔ ስርዓት ነው" ሲሉ ተናግረዋል:: ይህ ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ አፍወርቅ የተናገሩት ትክክለኛ ነው:: ነገር ግን ይህን መመሪያ ነድፈው የሰጡ እርሳቸው ናቸው:: በእርግጥ ሌላም እውነተኛ ታሪክ ተናግረዋል ገጽ 2 "ወያኔ መጀመሪያውኑ ትግራይን ነፃ አወጣለሁ የሚል ፕሮግራም ይዞ የተነሳ ነው:: ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ፕሮግራም ነበረው ወይም መላዋን ኢትዮጵያ የሚመለከት አጀንዳ ይዞ የተነሳ ነው ሊባል አይችልም:: ይህንን ታሪክም የሚረሳው አይደለም" ሲሉ ተናግረዋል:: ትክክል ነው:: ወያኔን በመጀመሪያ መክረውና አደራጅተው ከአረብ አገር የመጣላቸውን ስጦታ ችረው አደራጅተዋል:: ነገር ግን ወያኔ ለሪፓፕሊክ መንግሥት ምስረታ ሳይሆን ለብሔር ነፃነት እንዲታገል ዓላማውን እንዲቀይር ማድረጋቸው አይካድም ይህን ወያኔዎችም አልካዱም ያምናሉ::

<u>የህወሓት ኮሚኒስት ሃይል የ10 ዓመት ጉዞ ግምገማ</u> ሐምሌ 1977 ዓም ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 22 "የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር ይባል የነበረው ድርጅት የትግራይ ጥያቄ የብሔር ጥያቄ ሳይሆን የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው:: መንገሻ ስዩም የትግራይን ሕዝብ ትግል ሊመራ ይችላል የሚል አቋም ይዞ በቀረበበት ወቅትም መንገሻ የትግራይ ሕዝብ ጠላት እንጂ መሪ ሊሆን አይችልም ጥያቄውም የብሔር ጥያቄ እንጂ የቅኝ ግዛት ጥያቄ አይደለም ብሎ ተቃውሟል:: የተጠቀሱት ስህተቶች በ1969 ዓም መጀመሪያ አካባቢ ተሻሽሎ በወጣው የህወሓት ፕሮግራም በመሰረቱ ታርሟል" ሲል ጽፏል:: ሕዝቡን በብሔር ማደራጀት የሚባለውን ግን የመከሩ አቶ ኢሳያስ ናቸው:: የተነደፈውን ሕገ መንግሥት በመጀመሪያ ጥሩ ነው ብለው ተናግረው ነበር:: ይህ ሕገ መንግሥት የፀደቀው ሚያዝያ 25 ቀን 1986 ዓም ሲሆን ጥር በ1987 ዓም አሜሪካ መጥተው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችን የሚወክል ሕገ መንግሥት ተመስርቷል ብለው ደግፈው ተናግረው ነበር:: ነገር ግን በግንቦት 1990 ዓም ደግሞ ሳረብ አገሮች የሰጡት ቃለ ምልልስ ተመልከቼ በወቅቱ የማያፍሩ ከተስካር እንዝፈን አሉ በሚል ጹሑፍ በሳተናው ጋዜጣ ታትሟል::



ጌታቸው ረዳ <u>ዜጋ መጽሔት</u> ሶስተኛ ዓመት ቁጥር 8 ሰኔ 1994 ዓም ገጽ 6 " የኢትዮጵያን መበተን እያወሩ በታኞችን አያስጎምጁ:: ለአንድነት ኃይሉችም ስለመበተንዋ መርዶ እየነገሩ የሚጫወቱትን የማስፈራራት ጨዋታ አሸብር ዳርጌን ተው አቁም በሉት እንዳሉት አያቴ እኔም አቁም! ልበልምት? ይህች ትበተናለች ትፈርሳለች የምትባል ቃል ለብዙ ዓመት ከአፍዎ አልጠፋ አለችምሳ? የጤና ይሆን? በእኛ በኩል ኤርትራ ትምጣ ትሂድ ጭንቀታችንን ዱሮ ጥለነዋል:: ሕዝባችን ናችሁ ስንላቸው ባዕዳን እና ጎረቤታሞች ነን ይሉናል! የወደብ የይገባናል ጥያቄ ስናቀርብ ደግሞ መሬቷን እንጂ እኛን ሕዝቦቿን አይፈልጉነም እያሉ ይከሱናል:: መጨበጫ መያዣ ስላጣንባቸው የኤርትራ መምጣትና መሂድ ከእንግዲህ ወዲህ ባጭር አማርኛ ጭንቀታችን አይደለም:: ቢፈልጉ ደግሞ ÷አይዋኒንና÷ በዓድዋ ትግርኛ ቁርጠን ይወቁ ማለት ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህን ምዕራፍ ከመዝጋቴ በፊት አንድ ነገር ጣል ሳደርግ እፈልጋለሁ:: በምጽፈው መጽሐፍ ሁሌም ቢሆን የትጥቅ ትግል መጥሳቴና በተለይም ከሻዕቢያ ጋር የሚደረገውን መረዳዳት አልደግፍም:: ብታምኑም ባታምኑ ሻዕቢያ ለወያኔ ያልሆነ ለሌሎች በተለይም "አድኀ" አህያ ሲለው ለነበረው ለአማራው ሕዝብ ሊሆን አይችልም:: አስታውሱ በ1965 ዓም የኢሕአፓ የመጀመሪያው ከአረብ አገር ሰልጥኖ የገባው በሻዕቢያ ሜዳ ነበር:: ሻዕቢያ ኢሕአፓን የጠየቀው "ኤርትራ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው በል" ብሎ ነበር:: ኢሕአፓም አለለት ይህን በመቀበሉ ምክንያት ግማሾች ተበሳጭተው አዲስ አበባ የገቡ መሆናቸውን አቶ ተስፋዬ መኮንን ይድረስ ለባለ ታሪኩ በተባለው መጽሐፍ ጽፈውታል:: ውለው አድረው ሻዕቢያ ደግሞ ወያኔን መስርቷል:: ከዚያም በወያኔ ኢሕአፓን አስመትቶ ወያኔን የእርሱ የጥይት ማብረጃ አድርጓል:: ኢሕአፓ ከሁለት ሲከፈል ኢዴህን መስርተው እነ አቶ ጌታቸውና አቶ ታምራት ሳይኔ የወያኔ የጥይት ማብረጃ ሁነዋል:: እንደዚያ ተደርጎ ደርግ ወድቆ ወያኔ በገባው ቃል ኪዳን መሰረት ኤርትራን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የሰጣቸውን ጠልቶ ሌሎችን በተለይም በኢትዮጵያ አንድነት ላይ እምነት ያላቸውን ድርጅቶች ይደግፋል ማለት ዘበት ነው:: ለሻዕቢያ ከወያኔ የሚሻለው ፈጽሞ ሊኖር አይችልም:: ስለዚህ ከሻዕቢያ ጋር ተጠግቶ ሕዝብን ማስጨረስ ትክክል አይደለም ብያለሁ:: እኔ ይህን በማለቴ አንዳንዶች ጠላት ነህ ተብዬ ልፈረጅ አይገባም::

# ክፍል ሁለት

## ምዕራፍ 1

## የኢትዮጵያ ታሪክ ከፍጥረት እስከ ልደት

ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ለመጻፍ ስጀምር የኢትዮጵያን ረጅም ታሪክ ነካክቼ ነው ወደ የመጽሐፉ መነሻ የምደርሰው። ሁሌም ተመሳሳይ መልዕክት አስተላልፋለሁ። ኢትዮጵያ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምራ ያለች አገር መሆንዋን ማሳሰብ ደስ ይለኛል። ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ሚሊዮን ዓመታት እድሜ ያስቆጠረች አገር ናት። የሀገራችን ታሪክ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጀምሮ አሁን ካለንበት ለመድረስ የበቃችው በአባቶቻችን ቆራጥነት ነው።

(ቀደሰ) ዓለማየሁ ሞገስ ደርሶ ሁሉም ሁሉን ይወቅ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 13" የሰው ዘር የተፈጠረው መጀመሪያ በኢትዮጵያ እንጂ የዚያን ጊዜም ሰው እንደሚያምነው በኢየሩሳሌም እስያ አይደለምና በዓባይ ሸለቆና በእየቆላው ይፈለግ ብል የቂል መሣቂያ ሁኜ ለብዙ ቀን ቆየሁ። ይህ በተነገረ ከ30 ዓመት በኋላ ሉሲ ተገኘች። ዐባይን ሸለቆ ግን ከመሪዎች ብዙዎቹ ስለማይወዱት እስካሁን አጥኚ ቡድን ባለመላኩ ቀኑን እንደኔ ትብኒቱን ይቆጥራል። የግብጽን መንግሥት የመሠረቱት ጠቢባንም ያስተማሩ ኢትዮጵያዊያን ናቸው በሚል ርዕስ ተነሥቼ ለመተግበር ከዛሬ 22 ዓመት በፊት የውጭ ርዳታ ጠይቄ ከዩንቨርስቲህ ድጋፍ ካገኘህ እንረዳሃለን የሚል መልስ በማግኘቴ የኛን ዩንቨርስቲ ብጠይቅ መሪዎች በቅናትና በጥመት ተጠምደው የድጋፍ ደብዳቤ ባለመጻፋቸው ሳላረጋግጠው አረጀሁ" ሲሉ በ1987 ዓም ጽፈዋል።

ኢትዮጵያ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምራ ያለች አገር ናት። ኢትዮጵያ ዓለም ከተፈጠረ ጀምራ ያለች አገር አይደለችም የምትሉ ካላችሁ እኛ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያውያን የተጻፈን ማመን ከተቸገርን ፈረንጆች ወደው ሳይሆን የታሪክ ሐቅ አስገድዷቸው ሊበድቁት ያልቻሉት ድንቅነሽ ሉሲ በዓለም ከተጠራቀመው የሰው ልጅ አጽም ግንባር ቀደም መሆንዋን መስክረዋል። አሁን በቅርቡም በኢትዮጵያዊው ከርሰ ምድር ተመራማሪ ሰላም ከእርሷ የሚልቅ አጽም ተገኝቷል። ይህን ማመን ካቃታችሁ ውሃ ፈሳሽ ነው ቢባሉ ውሃ አይፈስም የሚሉ ነጩን ጥቁር ጥቁሩን ነጭ የሚሉ ሰዎችን ማሳመን አይቻልምና ልባችሁን አምላክ መልሶ በታሪካችሁ የምትኮሩ ያድርጋችሁ እላለሁ።

የሰው ዘር ከኢትዮጵያ ወደ ኤስያ እስራኤል በከብት እርባታና በሌላ ሁኔታ ተስፋፍቷል። ሰሙቲክ ቋንቋ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ የመጣ አስመስለው



አንዳንድ የታሪክ ሰዎች ሲጽፉ ኑረዋል። ነገር ግን በቅርቡ በብልጽግና በሳይንስ ጥናት የተደገፈ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ጀምሮ በጥቂት ኢትዮጵያውያን የተጻፈው ትክክለኛ ታሪክ በመሆኑ መጻፍ ይቻላል። ሊቀ ጠበብት ማርቆን በርገር ብላክ አቴና በተባለው መጽሐፋቸው ሰሙቲክ ቋንቋ ከአፍሪካ ከኢትዮጵያ ጣና ላይ ተነስቶ በዓለም መሰራጨቱን ጽፈዋል። የጥቂት ኢትዮጵያውያን የታሪክ መጽሐፍ ውድቅ አልሆነም። በአረብ አገር ከግድብ ላይ የተገኘው ጹሑፍ ፊደል ቅርጽ ኢትዮጵያውያን የጻፉት እንጂ ሌሎች የጻፉት አይደለም። ዛሬ ሰልጥነናል የሚሉት ሕዝቦች ገና ቅጠል ለብሰው በሚሔዱበት ወቅት ኢትዮጵያ ስለ ሥልጣን ሕዝብ ዲሞክራሲ ታውቅ ነበር።

ለምሳሌ በአክሱም ዘመነ መንግሥት ለ100 መቶ ዓመታት በተከታታይ 10 ዓመት ብቻ መንገሳቸው ለምን እንደሆነ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪዎች ሳይተነትኑበት መቅረታቸው ይገርማል። የአክሱሙን ታሪክ እንለፈው ከተባለ ከ912 ዓም እስከ 1261 ዓም የነበረው የዛጉዌ ነገሥታት የላሊበላውን ታሪክ በምንመረምርበት ወቅት 40 ዓመት ሲሞላው አጤ ሥልጣኑን አስረክቦ ይሔዳል የሚለውን ለምን የኢትዮጵያ የታሪክ ተመራማሪዎች ሳያጤኑት ቀሩ? የኢትዮጵያ ታሪክ ከክርስቶስ ልደት በፊት ብዙ ጥበብ የነበረበት የሃይማኖት ግንዱ የተመሰረተበት ነበር። ለምሳሌ ከሙሴ በፊት እምነት በኢትዮጵያ ነበር ይህ ማለት በሕገ አበው "እኛን የፈጠረ አንድ አምላክ አለ" ብለው ያመልኩ ነበር። በዚህ ወቅት ካህን ራጉኤል ወይም ዮቶር የሚለውን ያጤኗል።

ኦሪት ዘጸአት ም/3ቁ 1"እንሆ ሙሴ የምድያም ካህን የሆነውን የዐማቹን የዮቶርን በጎች ይጠብቅ ነበር" ይልና ም/ ዘጸአት ም/ 18/ቁ 1 "የምድያም ካህን የሆነው የሙሴ ዓማት የቶር እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር መርቶ ባወጣቸው ጊዜ ለሙሴና ለእስራኤል ሕዝብ ያደረገላቸውን ነገር ሁሉ ሰማ ስለዚህም በእርሱ ዘንድ ትቶአት ሂዶ የነበረችውን የሙሴን ሚስት ሴፓራን እንዲሁም ከሙሴ የተወለዱትን ጌርሾምና ኤሊዓዘር የተባሉትን ሁለቱን ልጆችውን ይዞለት መጣ" ይልና ሙሴ በፍርድ ሥራ አልችል ብሎ ስለተመለከተው እንዴት ዳኞችን መምረጥ እንዳለበት መክሮት ከስራ ላይ ያዋለው መሆኑን ከገለፀ በኋላ ደግሞ ኦሪት ዘኁልቁ ም/12 ቁ /1"ሙሴ ከኩሽ ነገድ የሆነች ኢትዮጵያዊት ሴት በማግባቱ ምክንያት ሚርያምና አሮን በሐሜት" የነቀፉት መሆናቸውን ጽፏል። ከላይ ዘጸአት ም/3ቁ1 ላይ የምድያም ካሕን የሚለው ምድያም የምትባለው በጎጃም ክፍለ ሀገር አገው ምድር አውራጃ ናት።

ዶ/ር ኃይሌ ወልደሚካኤል አብረኖት በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 3 "የአባይ ሸለቆ የዓባይ ወንዝ ውጤት ነው። የዓባይ ሸለቆም የመጀመሪያው ጉልህ ማኅበራዊ ህይወት የተደራጀበት፣ የተፈጥሮ ክስተቶች ግንዛቤ ያገኙበትን የሰው ልጅ ጉልህ የሃይማኖት፣የፖለቲካ ፣የኢኮኖሚ፣የሥነ ምግባርና የሳይንስ ሥርዓትና ሚስጥር የለየበትና በየፈርጁ ያደራጀበት ነው። መደበኛ ግብርና ማለትም ከብት ማርባት፣ አዝርዕት መዝራት፣ የመገልገያና የማመምረቻ መሣሪያዎች ማምረት አልባሳት መሥራት ከብቶችን በወተት፣ በሥጋ፣ በትራንስፓርትና በእርሻ ምንጭነት መጠቀም በመስኖ እርሻ መገልገል በውሃ

መጓጓዝ በአንድ አምላክ ማምለክ የጽሑፍ ባህል ማመንጨት የሃይማኖት ካህናት ማፍራት አስከሬን ማቆየት የጂኦሜትሪን ሳይንስ ማዳበር ወዘተ የተመሰረተበት ሁሉ ብልጫታዎች መጀመሪያ የታዩት በዓባይ ሸለቆ ውስጥ ነው:: በሌላ አነጋገር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ በተናጠል ሳይሆን በተደራጀ መልክ ከተፈጥሮ ጋር በውል የታገለበትና በኋላም የሰው ልጅ ከራሱ ጋር መታገል የጀመረበት በዓባይ ሸለቆ አካባቢ መሆኑ ተረጋግጧል" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህ ሊሆን የቻለው ኖኅ ከመርከብ የወጣውም በኢትዮጵያ ነው::

መምሕር ፍስሓ ጽዮን ከማ፣ መርኆ አዳም ወግዕዝ አዳምና ግዕዝ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 59 "ኖኅ ከነልጆቹ ከመርከብ ከወጣ በኋላ የተቀመጠው በምድረ ኢትዮጵያ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: አንባቢያን አንዳንዴ አዲስ ታሪክ አንድ ሰው ደጋግሞ ሲጽፍ ልብ ወለድ መስሎ አንዳንድ ሰዎች ሊቀበሉት አይችሉ ይሆናል:: ታሪክ በታሪክነቱ ካየነው ግን ይዘገያል እንጅ እውነቱ መውጣቱ አይቀርም:: ስለዚህ ኖኅ ከመርከብ የወጣው በኢትዮጵያ መሆኑ ብዛት ያላቸው የታሪክ መጽሐፍት ዘግበውታል::

ያሬድ ግርማ ኃይሌ የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 124 "ኖህ ለዘመናት እንደቆዬ ሚስቱ እሜቴ አይከል ስትሞትበት በጭልጋ ምድር እንደቀበራት ትውፊታዊና ሌሎች መረጃዎች ኖህም ከሚስቱ ተለይቶ ከኖረ በኋላ በጎንደር ከተማ ሲሞት በመቃብሩ ላይ ምንጭ ፈልቆ በርካታ ሰዎችን ይፈውስ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: እኒህ ደራሲ አራራት የሚባለው ተራራ ያለው ዘጌ አውራጃ ውስጥ መሆኑንና ተራራውን የጎበኙ መሆናቸውን ጽፈዋል:: ቁርከ ያለው ተራራ በዓለም ካሉት 26ኛ መሆኑንና ኖህ ከመርከብ የወጣው በኢትዮጵያ መሆኑን አስረግጠው ጽፈዋል:: ባይገርማችሁ ሌላም ታሪክ ልጥቀስ ያም የኖህ መርከብና የጎንደር ፋሲል ግንብ አሰራር አንድ አይነት መሆኑን ሳይቀር ጽፈዋል:: አንዳንድ አባቶችና አፈ ታሪኩ ደግሞ በጎጃም አገው ምድር አውራጃና በዘጌ አውራጃ ጎንደርን አልፎ ዋልድባ ድረስ የሃይማኖት መመስረቻ አድርገው ይቆጥሩታል:: ለምሳሌ የሃይማኖት መምህራን ይህን ታሪክ ጠንከር አድርገው እያስተማሩ ናቸው::

ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀድሽ በ1997 ዓም ታህሳስ 29 ቀን ጎንደር አደባባ ኢየሱስ/ ባለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሲያስተምሩ "የጎንደር ጃንተከል ዋርካውና የፋሲል ግንብ ግምጃ ቤት ማርያም ቤት አደባባይ ኢየሱስ አሰራሩ ጌታችን በተወለደበት በናዝሬት ይመስላል" ሲሉ አስተምረዋል:: በሃይማኖት መምህራን በኩል እንዲህ እያስተማሩ ነው:: ወደ ነበርኩበት ልመለስና ይህ ከሆነ ጀምሮ የሰው ዘር ከላይ እንደተጠቀሰው በታሪክ የአባይ ዙሪያ መነሻቸው መሆኑ ታውቋል:: ከተማቸው ሜርዊ ይባል ነበር:: ይህም ዛሬ ገሉ ያልተገኘበት ሲሆን ይህ ከተማ ከ74 ነገሥታት መካከል በተለይም ከ50ኛው ነገሥታት ጀምሮ በከፍተኛ እውቀት የሞላበት ነበር::

ዛሬ ሜርዌ አልያም ሚርዊ ሌላም ሌላ እየተባለ የሚጠራው ረጅም ዘመን የነበረው ከተማ እንደነበር ተረስቶ ከ880 ዓመተ ዓለም ጀምሮ በተመሰረተው



በአክሱም ከተማ ብቻ ተወስነን የቀድሞውን ታሪክ ለማወቅ ጥረት አልተደረገም:: ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል ሲነግሱ ከዘውዳቸው ላይ የዘንዶ ምልክት ያደርጉ ነበር:: የሩቁን ትተን የቅርቡን ታሪክ ስንመረምር ከንግሥት ሳባ በፊት በኢትዮጵያ የነገሡት 73 ሲሆኑ እርሳቸው 74 መሆናቸውን ሠነዱ ሲያስረዳ እርሳቸው ሲነግሡ ዘውዳቸው የዘንዶ ምልክት ያለው ነበር::

ታዲያ ኢትዮጵያውያን እምነት ስለነበራቸው የዓለም መድኃኒት ጌታ የሚወለደው በእስራኤል መሆኑን ይነገራቸው ስለነበር እርሳቸው በ1013 ዓመተ ዓለም ነግሠው ሳል በሀገሪቱ አንቱ የተባሉ ነጋድራስ ታምሪን በቻይናና በሕንድ ንግዱን ሲነግዱ ኑረው ሲመለሱ በእስራኤል በኩል በመመለሳቸው የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ ተመልክቶ በመምጣቱ ብልህ ንጉሥ ተወልዷል ብሎ ሲነግራቸው ሲያድጉ የሰሙት የዓለም ጌታ መስሎአቸው ብዛት ያላቸው ንጉሦችና ንግሥቶች አስከትለው በ1010 ዓመተ ዓለም እስራኤል ሄዱ:: ከዚያም የዓለም መድኃኒት መሆኑን በእንቆቅልሽ ጥያቄ አዋክበውት አለመሆኑን አሳምነዋል:: ታዲያ ሴት መሆን አይቀርም እርሳቸውም ንግሥት ሳሆኖም ሁለቱም አርግዘው ተመለሱ::

ንግሥተ ሳባ እብነለሐኪም የኋላውን ምኒልክ ሲወልዱ ንግሥት ሳሆያ ዛጉዌን ወልደዋል:: ሁለቱም ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ወደ ኢየሩሳሌም አባታቸውን ሊጠይቁ ሕደው እብነ ለሐኪም የቤተ መንግሥቱን ሲማሩ ዛጉዌ ደግሞ የቤተ መቅደሱን ትምህርት ተምረው 12 ሺህ እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን ጽላተ ሙሴን በመያዝ ወደ ኢትዮጵያ መጡ:: እብነ ለሐኪም ቀዳማዊ አጼ ምኒልክ ተብሎ 75 ንጉሠ ነገሥት ሁነው በኢትዮጵያ ሲነግሡ "እንደ አባቴ እንጂ እንደናቴ አልነግሥም" ብለው ከዘውዳቸው ላይ የአንበሳ ምስል ማድረጅ የተጀመረው በ982 ዓምተ ዓለም ወዲህ ነው:: በሃይማኖት በኩል ይህን ሲመስል አገር በማስተዳደር በኩል ደግሞ ጠንካራና አይበገሬ ጀግኖች ነበሩ:: በትምህርት እድገት ያሳዩ ቢሆኑ ኑሮ ከ70 መርከብ በላይ የነበራቸው ነጋድራስ ታምሬ በዓለም ላይ እየዞሩ የሚነግዱ ሀብታም አይሆኑም ነበር:: ስለዚህ ኢትዮጵያ ጠንካራና ሀብታም አገር ነበረች::

## ምዕራፍ 2

## የኢትዮጵያ ታሪክ ከክርስቶስ ልደት እስከ እስልምና ምስረታ

ታህሳስ 29 ቀን 1 ዓም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ናዝሬት ሲወለድ በኢትዮጵያ ነግሰው የነበሩት እጨ ባዜን ናቸው። በዚህ ወቅት ኢትዮጵያውያን "የአይሁድ ንጉስ የተወለደው ወዴት ነው" እያሉ የእጅ መንሻ ይዘው ወደ እስራኤል አምርተዋል። እነዚህ የጌታችን መወለድ አውቀው ኮከቡን እየተከተሉ የሄዱት ኢትዮጵያውያን ከ4 ቦታ የተነሱ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ዛሬ ባለው የጎሳ አባቶች መሆናቸውን የታሪክ ሠነዱ ዋቢ ነው። ቀደም ሲል በግዕዝ የተጻፉ ብዛት ያላቸው የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍት ነበሩ። እነዚህ መጽሐፍት ምናልባት በድርቡሽ ጦርነት ወቅት ወደ ሱዳን የተወሰዱ ይመስላል። እነዚህን መጽሐፍት ሱዳን አግኝተው ወደ አማርኛ እየተረጎሙ እያሳተሟቸው ነው። ሱዳን ውስጥ የተገኙትን መጽሐፍት ዛሬ ባለቤታቸው መሪ ራስ ኤ ኤም አማን በላይ ናቸው። እኚህ አባት ቀደም ሲል በኢትዮጵያውያን የተጻፉትን መጽሐፍት "እንዲ እንደጻፈው" እያሉ እያሳተሙአቸው ነው።

መሪራስ አማን በላይ ጉማ መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁጥር 1 ሐምሌ 1993 ዓም ገጽ 29 "እጨ ባዜን በኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ በነገሡ በ8ኛው ዘመን መስራቅ በኩል ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ ኮከብ ወጣ። መስቀለኛም የሆነ በሩቅ እግርና እጁን ዘርግቶ የቆመ ሰው የመሰለ ነበረ። ብርሃኑ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ሰሜን መስዕ ያመለክት ነበር። ይህ ኮከብ ለኢትዮጵያውያን የጌታን መወለድ ያበሰረ። 1ኛ በዚህን ጊዜ በደሸት ከተማ ጎንጅ ጎጃም የሚቀመጠው በተስፋ ሲጠባበቅ የነበረው አጎሻ ጃቦን ዮጵ የሚባለውን የግዮን ብጫ ወርቅ እንቁዮጳዝዮን እንቁዮጳ ግዮን የሚባለውን ሉል ድንጋይ የወርቅ ሐመልማል ማለት ወርቁን እንደሰፌድ ሆኖ የተሰራውን ይዞ በሰሩ ሶስት ንጉሶችን አስከትሎ ከጣና ደሴት ተነስቶ ኮከቡ ወደሚያመለክትበት ምድር ጉዞአቸውን ቀጠሉ። አጊሻ ሻቦ አማናቱ ሲማር አማራ ጎማ፤ 2ኛ ከአናርያ ዙባ ከተማ የሚቀመጠው የመደባይ ጎማ የደንጊና የሰገል የማጂና የአርመን ንጉሥ መጋል ከኤውላጥ ንጉሥ መካድሺ ከአቢል ንጉሥ አውር ከአፋር አፍሪካ ንጉሥ ሙርኖ ጋር ሆኖ ከወርቅ ሐመልማል የተሰራ መጎናፀፊያ እጀጠባብ የሰንደል እንጨትና እጣን ከርቤም የከበረውን ሉል ወርቅ ይዞ ኮከቡ ወደሚያመለክተው ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም በጥንቱ ናግራ ኤደን በዛሬው የመን አድርጎ ጉዞውን ቀጠለ። የገዳዲ ልጅ ሰፋ የአሮሞ ጎማ።"

"3ኛ ከዋይዝ ከተማ በተርሴስ ደሴት በዛሬው አፋር የሚቀመጠው የእዜባውያን አዛል-አዳል የአፍርሴካውያን ንጉሥ አጋቦን በኢንኤ ጌዜር ከአውባው ንጉሥ ሳዱንያ ሀጂሶን ባል ሜሌክ ኢቡል ሰላም ከሳባ ከተማ



የሚቀመጠው አርስጣ ጋር ሆነው ወርቅና እጣን ከርቤም ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም ቀይ ባሕርን ተሻግረው በምስራቅ በኩል ወጥቶ ብርሃኑ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገውን ኮከብ አይተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። አፈርስካ አፈርስካውያን የሆኑ እነዚህ ንጉሦች ሁሉም የንጉሥ ዘውድ የደፉ ናቸው። ለእነዚህ ለአስራ ሁለቱ ንጉሦች የበላያቸው በኢትዮጵያ ዋና ከተማ አክሱም የሚቀመጠው ንጉሠ ነገሥት እጨ ባዜን ነው። እነዚህ ንጉሦች በግመሎቻቸውና በፈረሶቻቸው ከምድራቸው የእህልና የወርቅ የከርቤና የእጣን አይነቶችና ልዩ ልዩ ልብሶች ገፀ በረከቶች ይዘው የንጋቱ ኮከብ ብርሃኑን ለሚያመለክታቸው የሠላም ንጉሥ ጋዳ ገፀ በረከት ለማቅረብ ጉዞ ቀጠሉ" ሲሉ ጽፈዋል። ከዚህ በላይ በታሪክነታቸው ከተጻፉት ጥቅስ ተወስዷል። ይህን የሚደግፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይኖር ይሆን?

<u>መዝሙረ ዳዊት</u> ምዕራፍ 72÷9 "በፊቱም ኢትዮጵያውያን ይሰግዳሉ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ፤የተርሴሴና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን አበርክተው ይሰግዱለታል" ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ ስጦታ የሚያበረክቱ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ልብ አምላክ ዳዊት ተናግሯል። ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ ኢትዮጵያውያን ቀደም ጀምረው በህገ አበው አንድ አምላክ አለ ብለው ያመልኩ ስለነበር ነው። ለዚህም ነው <u>ትንቢተ አሞጽ</u> 9÷7 "የእሥራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም" ብሎ ሊናገር የቻለው እንደዛሬው ትውልድ ሳይሆን የዱሮ አባቶቻችን አምላክን ያከብሩ በመሆናቸው ነው። በማቴዎስ ወንጌል 2÷2 "የከዋክብት ተመራማሪዮች ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ" ይላል። ምንም ይሁን ምን ለኢየሩሳሌም ምስራቅ ኢትዮጵያ እንጂ ማንም አገር ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ሰብዓ ሰገል ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን በሚመለከት ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስና ከዚህ በታች ስማቸውን የምጠቅሰው የታሪክ መጽሐፍት ዋቢ ናቸው።

1ኛ መሰረተ ስብሀት ለአብ ትውፊታዊ ሐሳብ ዘመንና ታሪክ ገጽ 36
2ኛ ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም ክርስትና በኢትዮጵያ ገጽ 52
3ኛ ቃለ አዋዲ መጽሔት ቁጥር 2 ሚያዝያ 1990 ዓም ገጽ 5

<u>የማቴ</u> 2÷ 13 "የከዋክብት ተመራማሪዮች ከሄዱ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ ሄድሮስ ሕጻኑን ለመግደል ስለሚፈልገው ተነስና ሕጻኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ወደ ግብጽ አገር ሽሽ እስከምነግርህም ድረስ በዚህ ቆይ አለው" የተባለው ይደርስ ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈ ነበር። እመቤታችን ድንግል ማርያምና ዮሴፍ መቅደሳዊት ማርያም ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል። የነበሩበትም በዛሬው ጣና ውስጥ ነበር። ቀደም ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጣ በትንቢት ተጽፎ ነበር። ለምሳሌ <u>መዝሙረ ዳዊት</u> 68÷ 31 "የሰላም መልእክተኞች ከግብጽ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያም ፈጥና እጅዎችዋን ወደ እግዚሮብሔር ትዘረጋለች" የተባለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያ መምጣቱን ሲያብራራ ነው።

አዋልድ መጽሐፍት የምንላቸውም ይህን ጠቅሰውታል:: አቤቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ከድንግል ማርያም ተወልደህ ሄሮድስ ሊገልህ በፈለገህ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ተሰደህ በጣና ደሴት ለዓራት ዓመት ስትኖር ኢትዮጵያን ባርከህ በጎንህ የፈሰሰውን ደምና ውሃ በሊቀ መልአኩ በቅዱስ ዑራኤል አማካኝነት በሀገሪተቷ ላይ ረጭተህ ተራሮቿን ባርከህ ወንዞቿዋን ቀድሰህ የእህል በረከት ይውረድላት ወተትና ማር የሚፈስባት አገር ትሁን ብለህ ኢትዮጵያን ለእናትህ ለማርያም ዓሥራት አድርጌ ሰጠሁሽ ስትል ቃል ኪዳን የገባህላትን አስበህ በደላችንን ይቅር ብለህ ከረሃብ ከበሽታ ከጦርነት አድነህ ሰላምና ፍቅርን አንድነትን እንድትሰጠን እንለምንሃለን:: ዮሴፍ ማርያም እና ሰሎሜ ኢየሱስ ክርስቶስን ይዞ ከሄርዶስ በሸሹ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው መኖራቸው ከላይ ተገልጿል ኢትዮጵያ የሰው ልጆችን ሳይሆን የዓለም መዳህኒት ጌታችን ያስተናገደች አገር ናት:: ከዚህ ከፍ ተብሎ የተብራራው ጌታችን መዳህኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢትዮጵያ መጥቶ መኖሩን በተመለከተ በታሪክ መጽሐፍት ተገልጿል::

1ኛ ዋልድባ በሀገረ እግዚአብሔር አቢሲንያ የአርበንታት ገዳም ታሪክ ገጽ 17
2ኛ አለቃ አያሌው ታምሩ ወላዲት አምላክ በኢትዮጵያ ገጽ 48
3ኛ መራሪስ አማን በላይ መጽሐፈ ሱባኤ ዘበአማን ካልዕ እየሱስ ክርስቶስ በኢትዮጵያ ገጽ 406-411-413
4ኛ መምህር አለማየሁ ኃይለ ሥላሴ ታሪክ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሃ ገጽ 18
5ኛ ዘመድኩን በቀለ ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ ገጽ 22

ክርስትና ሃይማኖት ማለትም ጥምቀት በኢትዮጵያ ያስተማረ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት አስተምረዋል:: በኢትዮጵያ የመጡት ሐዋርያትም 6 መሆናቸውን የታሪክ መጽሐፍት ዋቢ ናቸው:: ይህን የምዘረዝረው አንባቢያን እንዳይጠራጠሩ በታሪካቸው እንዲኮሩ ነው:: ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የምጠቅሳቸው የታሪክ መጽሐፍት ሐዋርያት በኢትዮጵያ መጥተው ማስተማራቸውን የሚገጸውን ይሆናል::

1ኛ አምበር መስቀልየ በዲበ መስቀል፤መስቀሌን በመስቀለኛ ላይ አኑር ገጽ 64
2ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት ከመጀመሪያው እትም ገጽ 86 ከሁለተኛው እትም ገጽ 108
3ኛ አባ ጎርጎርዮስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ 21
4ኛ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ትምህርተ ክርስትና ገጽ 149
5ኛ የኔሰው አስረሴ ትቤ አክሱም ሙኑ አንተ ገጽ 67
6ኛ አባ ተሥፋ ስላሴ ሞገስ ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የይሁዳ አንበሳ ነው ገጽ 100
7ኛ መምሕር ቸሬ አበበ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽናት 1 መጽሐፍ ገጽ 96

ለምሳሌ እንዳንድ የበስማም ቁሶችና የአውሮፓ ሰዎች ክርስትና ሃይማኖት የተሰበከው በውጭ ሰዎች አስመስለው ይጽፋሉ:: ነገር ግን ትክክል አይደለም:: ክርስትና ሃይማኖት የተሰበከው ቅድሚያ ጌታችን የኢየሱስ በኢትዮጵያ



በኢትዮጵያ መጥቶ በማስተማሩ ነው:: ለምሳሌ ሌሎችን የክርስቲያን ሊቅ ነን ባዮችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከ12 ዓመቱ 18 ዓመቱ የት እንደነበረ ብትጠይቋቸው መልስ የላቸውም:: ኢትዮጵያውያን ግን መልሳቸው በኢትዮጵያ እየተዘዋወር እያስተማረ ነበር ይላሉ:: ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሰ በኋላ በጆርንድ ጃንደረባው ባኮስ ግንቦት 8 ቀን 34 ዓም በዓለም ከተሰበሰቡት ሕዝቦች መካከል በጴጥሮስ የተሰበከውን ትምህርት ተቀብሉ በሠረገላ ሲሄድ ባለ መንፈስ ቅዱስ በፍሊጶስ አድሮ ጃንደረባውን እንዲያነጋግረው ከላከው በኋላ ተጠምቆ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ ጀምሮ ክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ማስተማር ጀመረ::

1ኛ መጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 26-33
2ኛ ዘመድኩን በቀለ ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ ገጽ 4

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መጽሐፍት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ብዛት ያላቸው መጽሐፍት መጥቀስ ይቻላል:: ከዚያም በኋላ ጃንደረባው ባስተማረው ትምህርት ሕዝቡ ገብቶት በ330 ዓም ወዲህ የመንግሥት ሃይማኖት ሁኖ ታወጀ:: በሃይማኖት በኩል እንዲህ ሲል በአስተዳደር በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰችበት ወቅት ነበር:: የዛሬው ትውልድ በዓይን የሚታይ ቅርስ ሰላማና ነበር የሚባለው ታሪክ ልብ ወለድ መስሎ ስለሚታየው እንጂ ኢትዮጵያ በ335 ዓም የሮማው ገዥ አቻ መንግሥት ኢትዮጵያ መሆንዋን አምኖና አክብሮ በአስተዳደር ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት እንኳ አብረን እንተባበር ብሎ ለአጤ አብርሃ ወአጽብሃ የላከው ደብዳቤ ታሪክ መዝግቦት ይገኛል:: ክርስቲያኖች ባንድ ባሀሪና በሁለት ባሀር ትርጉም ጭቅጭቅ በገጠሙበት ወቅት የአይሁድ እምነት ንጉሥ ፈንሃስ በየመን ይኖሩ የነበሩትን ክርስቲያኖች በማጥፋቱ አጤ ካሌብ መርከባቸውን ጭነው ወደ የመን ዘምተዋል::

ንጉሠ ነገሥት አጤ ካሌብ በየመን የሚኖሩ ክርስቲያኖችን ከታደጉ በኋላ የፈረሱ ቤተ ክርስቲያኖችን አድሰዋል:: ከዚያም ደጃዝማች አብርሃ ንጉሠ የመን ብለው ሹመው አጤ ካሌብ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መንግሥታቸውን ለልጃቸው ሰጥተው ገዳም ገብተዋል:: የመን የነበሩት ንጉሥ አብርሃ በ570 ዓም ወደ መካ ዘመቻ ማድረግ ጀመሩ:: በዚህ ዘመን ነቢዩ ሙሐመድ የተወለዱ ተብሉም ተጽፏል:: ንጉሥ አብርሃ መካ ደርሰው በጣዖት የሚያመልከውን ሕዝብ ክርስትና ሳያስተምሩ ሙተው ቀርተዋል:: ወታደራቸው ከሞት የተረፈው ሳውዲ ዓረቢያ ገብቶ መኖር ጀመረ:: ለምሳሌ የእስልምና ሃይማኖት መስራቹን ጡት አጥብተው ያሳደጉት እሙሃይመን አል አበሽ ወይም ደግሞ በረከቱል አል ሐበሺንና ሌሎችን መጥቀስ ይቻላል:: እስልምና ሃይማኖት ሲመሰረት የመጀመሪያውን አላህ አክብር ያሉት በላይ ገብረ እግዚአብሔር ቢላል ሌሎችም የአረብ ስደተኞችን እየመሩ ወደ ኢትዮጵያ የመጡትን ዛሬ ድረስ በአረብ አገር ቅይጥ ሁነው የቀሩትን ጥቁር ኢትዮጵያውያን በዚያን ወቅት ከሞት የተረፉት ናቸው::

# ምዕራፍ 3

## ከእስልምና ምስረታ እስከ ንግሥት ዩዲት!

ቅዱስ ቁርአን መቅድሙ ገጽ 7 "ኢትዮጵያ ልጆቿን በመከከላቸው ልዩነት ሳታደርግ አፍቅራና አስተባብራ ከመኖሯ በላይ እንግዶችንም ቢኾን በአክብሮት ተቀብላ የምታስተናግድ አገር መኾኗ የታወቀ ነው። ነቢዩ ሙሐመድ በ610 ዓ.ል በተነሱ ጊዜ ነገዶቻቸው ተከታዮቹን ስለአሠቃዩዋቸው ሐበሻ (ኢትዮጵያ)የእውነት አገር ናት በውስጧም ሰውን የማይበድል እርሱም ዘንድ አንድም የማይበድል ንጉሥ አለና ወደዚያ ብትኼዱ መልካም ነው። "በማለታቸው በመጀመሪያ በ615 ዓ.ል.የነቢዩ ሴት ልጅና ኸሊፋው ዑስማን የአጎታቸው ልጅ ጃዕፈር የሚገኙበት 16 ስደተኞች ዳግመኛም ከመቶ በላይ የሚኾኑ የሃይማኖት ጥገኞች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው 15 ዓመት በመልካም ጥገኝነት ተቀምጠዋል።

ጠላቶቻቸውም ስደተኞች ተይዘው እጃቸው እንዲመለስላቸው ቢጠይቁ ንጉሡ ገንዘብ ያላጠፉ፣ነብስ ያልገደሉ መኾናቸውን አጣርቶ አሳልፎ አልሰጥም በማለቱ ጥገኝን አሳልፎ ያለመስጠት ሕግ ከኢትዮጵያ ንጉሥ ተጀመረ፤ እንደሚባል ነቢዩ ሙሐመድም ለተከታዮቻቸው ሐበሾችን ኢትዮጵያውያኖችን ካልወጉዋችሁ አትውጓቸው ማለታቸው ይነገራል። ንጉሡም ድርብ ምንዳ ያለው ጻድቅ ንጉሥ መኾኑ በቁርአን በ3ም 199 አንቀጽ 28 .52-54 አንቀጽ ተገልጿል" ይላል።

ሐጂ ሙሐመድ ሣኒ ሐቢብ <u>እስልምና እና የታላቁ ነቢይ የሙሐመድ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 47 "ቁረይሾች ያመኑትን ሰዎች መጨቆንና ማስቃየታቸው እየቀጠለ ስለ ሄደ በተለይ ጠንካራ ወገን በሌላቸው ሰዎች ከፍ ያለ ችግር ደረሰባቸው። በዚህ ጊዜ ነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያ የእውነት ሀገር ናት ንጉሥዋም መልካም ሰው ነው፤ በሱ ዘንድ ማንም ሰው አይበደልምና የአላህ ፈቃድ ሆኖ መከላከያ ኃይል እስከናገኝ ድረስ ወደ እዚህ ሄዳችሁ ጊዜ ብታሳልፉ መልካም ነው። ስላሏቸው ከነቢይነት ዘመን 5ኛው ዓመት በሽሽግ ወደ ሐበሻ መሰደድ ጀመሩ" ሲሉ ጽፈዋል።

የእስላም ስደተኞች በኢትዮጵያ መጥተው በሰላም መቀመጣቸው በመካ ላሉ ቁረሽዎች ዜናው ደረሳቸው። በዚህ ወቅት ቁረሽዎች ለንጉሥ እርማህ ብዙ ገጸ በረከት እስይዘው ወደ ኢትዮጵያ ላኩ። የአጋሜ አውራጃ ንጉሥ ስደተኞችን በባልደረባነት የሚያስተናግዱ ናቸው። ከመካ ወርቃቸውን ይዘው የመጡት ቁረሽዎች በገንዘብ ገዝተው ለመውሰድ ነበር አሳባቸው ንጉሥ እርማህ ግን ምክንያቱ ምን እንደሆነ ከሳሽና ተከሳሾችን ከአከራከሩ በኋላ "ስደተኞችን አሳልፌ አልሰጥም" በማለት አሳፍረው መለሱአቸው።



ሒራ አሳታሚና አከፋፋይ የግል ማህበር <u>የሐበሻው ሂጅራና ሙሃጂሮች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 36 "ሙሃጂሮቹን ለመውሰድ የመጣው ልዑክ (ቡድን)የቅሌት ማቁን ተከናንቦና ይዞት የመጣውን ገፀ በረከት ተሸክሞ በመጣበት እግሩ ተመልሶ ሔደ። ከአንድ የተከበረ ወገን ወደ ሌላ የተከበረ ወገን የተላከ ገፀ በረከት መመለስና ተቀባይነት ማጣት በጣም አሳፋሪና ቅስም የሚሰብር ሊሆን ይችላል። የሐበሻው ሂጅራ ኢስላምንና አዲሱን አመለካከት የተከታዮቹ አገር ከሆነ አካባቢ ውጭ ለማስፋፋትና ለማስተዋወቅ ይልቁንም ለገዥዎችና ለሹማምንቱ ለማስረዳትና ለማሳመን ችሉአል" ሲሉ ጽፈዋል።

ዶ/ር ላጵሶ ጌ ድሌቦ <u>የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሠረቶችና መዛሪያዎች</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 199 "ቁረይሾች ግምባር የዘመቱ የሀበሻ ወታደሮችን ቁጥር በሚመለከት በኡሁዱ ጦርነት 3000 በኸንደቁ ጦርነት ደግሞ 10000 ነበር" ይሉና "ሀበሾችና የመካ ወታደራዊ ድርጅት በሂጅራ ዘመን በሚል ርዕስ በ1916 ባዘጋጀው ጹሑፍ የመካ አዋማዊ ቁረይሸሾችን ወደ ሽንፈትና ውድቀት ያደረሱት አሀበሾች የተባሉ ኢትዮጵያዊ ወታደሮች ናቸው በማለት ጽፎአል" ሲሉ ጽፈዋል።

የኢትዮጵያ ልጆች የዕስላም ሃይማኖት መስራቾች ሲደበደቡ ትክክል አይደለም በማለት በመንግሥት ታዘው ሳይሆን በፈቃዳቸው ዘምተዋል። የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ለእስልምና ሃይማኖት እድገት ያደረጉት ጥረት ተክዶ እንሆ ዛሬ ወንድሞቻችን እኛን ክርስቲያኖችን እየገደሉን ነው። እስልምና ሃይማኖት ትክክል ትርጉሙ የተረዳው ምዕመን ከሆነ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ላይ ጦርነት ማንሳት ፈጽሞ አይችልም። ምክንያቱም የነቢያቸው ትዕዛዝ "ኢትዮጵያውያንን ካልወጓችሁ አትውጓቸው" በማለት አስተምረዋል። ለምሳሌ ይህ ወንድሙን ማጥፋት ተግባር መቅረት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ራሳቸው ሙስሊም ወንድሞቻችን ማስተማር ይገባቸዋል።

አህመድ ሙነወር ሰይድ ኢብራሂም <u>የእስልምና ድንጋጌ የአመጣጥ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 102 "አላህ ሙስሊሞቹን ፀሎታዊ ስግደቶችን እንዲያከናውኑ፤ ዘካትን (አስራትን) እንዲያበረክቱ፤ ሐጂን እንዲያደርጉ፤ ውሉችን እንዲያከብሩና እንዲፈጽሟቸው ሰውን ያለአግባብ እንዳይገድሉ ጥቃትን እንዲከላከሉ እነኚህንና የመሳሰሉትን ደንግጓል" ሲሉ ጽፈዋል።

አንባቢያን ብተለይም እስላም ወንድሞቼ "ሰውን ያለአግባብ እንዳይገድሉ ጥቃትን እንዲከላከሉ" የሚለው ሕግ ምንን ያመለክታል? ቅዱስ ቁርዓንን ደግሜ ደጋግሜ አነበብኩት ነገር ግን "ሰው ግደል ትጸድቃለህ" የሚል ተጽሉ አላነበብኩም። በሀገራችን በአንዳንድ አካባቢ ወንዶች አንበሳ ካልገደሉ ወንዶች የማይባሉ ይመስላቸዋል። ገዳማቱ ቤተ ክርስቲያኑ እየተቃጠለ ነው። ባንድ ሳምንት 4 ታላላቅ ገዳማት ተቃጥለዋል። ይህ ሁሉ ድፍረት ግን መልካም አይደለም።

ዲ/ን ናትናኤል ታምራት <u>እግዚአብሔር ለምን ዝም አለ?</u> በተባለው መጣጥፋቸው ከገጽ 12-19 የጻፉትን አቤቱታ ሳነብ ከልብ አዘንኩ:: ይህን የእርሳቸውን ጹሑፍ ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይመልከቱ:: ሌላው በጎርጎርዮስ አቆጣጠር ጥር 12 ቀን 2008 የተቀረፀ ዲቪዲ ተመለከትኩ:: የሰው ልጅ እንደ በግ በአንገቱ መታረድ ይገባዋል ወይ? እነዚህ ክርስቲያን ወገኖቻችሁ መሆናቸውን እንዴት ረሳችሁ? ኧረ መልካም ጅምር አይደለም? በኢትዮጵያ ታሪክ ክርስቲያንና እስላም አብሮ በሰላም የኖረበት መሆኑን ነው ተጽፎ ያነበብነው? አክራሪዎች ለክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን ለእስላም አማኞችም የሚተኙ አይደሉም:: የፓኪስታን ሆነ የሌሎችን የእስላም አገሮች እልቂት በአክራሪውና ሰላም ፈላጊው ሕዝብ መካከል እያለቀ ያለውን ማስተዋል ይጠይቃል::

ዘማሪት ፀዳለ ጎበዜ <u>አቤቱ የሆነብንን አስብ</u> በተባለው የመዝሙር ዲቪዲ ያቀረቡት ክር ላይ የሚያሳዩት ሥእሉ ክርስቲያኖች በእስላሞች የተገደሉ መሆናቸውን ሲሆን የክርስቲያኖች ቤታቸው ሆነ ቤተ ክርስቲያኑ የተቃጠለውን እያሳዩ ለእግዚአብሔር ይዘምራሉ:: ክርስቲያኑ የእምነታችን አንዱ መፈተኛ በመሆኑ ወደ እግዚአብሔር አንጋጦ በማልቀስ ላይ በመሆኑ ደስ ሊላችሁ አይገባም:: ይህ በጣም ድፍረት መልካም አይደለም:: የሚገርመኝ አንድ ነገር አለ:: ያም ሰው ካልገደላችሁ አትጠድቁም" የሚል ሃይማኖት መኖሩን አላውቅም:: ከቅዱስ ቁርዓን ላይ አልተጻፈም::

ታዲያ የት አመጣችሁት? ሰው መግደልን ደስ የሚለው ሠይጣን እንጂ እግዚአብሔርን አምናለሁ የሚል ሰው አለ ብዬ አላምንም:: የኢትዮጵያ ቀጥተኛ (አርቶዶክስ) ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በአክራሪ እስላሞች እየተደበደቡ ነው:: በእርግጥ የኢትዮጵያ እስላሞች ሁሉም ይህን እኩይ ድርጊት ይደግፋሉ ማለት አይደለም:: ከዚህ የሚከተለውን ሰነድ ስጽፍ አለፍ አለፍ እያልኩ የጥቅስ ምልክቱን እያስገባሁ ባንድ ሰብስብ አድርጌ አገለብጠዋለሁ::

<u>ኢትእጽ መጽሔት</u> ቅጽ 5 ቁጥር 057 ሚያዝያ 1996 ዓም ገጽ 36 "አበሻ የእውነት ምድር ነች" ነቢዩ መሐመድ" ይላል አርስቱ ደግሞ ኒውስ አርስቱ "ኢትዮጵያዊያን እስላሞች እንጂ በኢትዮጵያ የምንገኝ እስላሞች አይደለነም" ይላል:: ልክ ናቸው ወያኔዎችና አንዳንድና አክራሪዎች ጠብ ለማፍለቅ ስለፈለጉ "በኢትዮጵያ የሚኖሩ እስላሞች" እያሉ ያወሩ ስለነበር እነዚህ መርዘኞች ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ ኢትዮጵያውያን እስላሞች" በሚለው አስተካክለው ጽፈዋል:: "በአክሱም ጽዮን አካባቢ መስጊድ ካልሰራችሁ ብሉ ያካባቢውን እስልምና ተከታይ ዜጎችን ወጥሮ ቢይዛቸውም ካልጠፋ መሬትና ቦታ ምነው እዚህ ላይ ስሩ እንባላለን ለጥላቻና ለቅራኔ እንጋበዛለን በማለት እንቢታውን ገልጿል" ይሉና::

"በሀገር ቤት በዲሞክራሲና በነፃ መንቀሳቀስን አሳቦ የጊዜው አገራዊ አንገብጋቢ የፖለቲካ ጥያቄ የአዳዲስ ሃይማኖቶችና እምነቶች ማነስ ይመስል



በሃይማኖት ስም ለሚንቀሳቀሱና ፍቃድ ለጠየቁ የውጭ ድርጅቶች አላንዳች ገደብ በሩን በርግዶ ከፍቷል:: እነዚህም ድርጅቶች አላንዳች ጠያቂ እንደልብ በመላው የሀገሪቷ ግዛቶች ይንቀሳቀሳሉ:: ያሻቸውን ራዕይና እምነት ይሰብካሉ፤ ያስፋፋሉ:: ከሁሉ በላይ የሚያሳዝነው ሕዝቡ ለመጤዎቹ ያለውን ንቀት ባሳየና እንቢታውን ገልጦ ጆሮ አልሰጥ ባለ ቁጥር በመንግሥት ባለሥልጣናት የሚደርስበት መዋከብ ቀላል አይደለም:: ይባስ ብለውም ሰባኪዎቹ የመንግሥትን ባለስልጣናት በሙስና በማጥመድ በሚጠሩት ስብሰባ በግድ እንዲገኙ ያስገድዱታል" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ጥቅስ የተወሰደበትን የጻፉት ሰብሰብ ብለው መሆናቸው የስማቸው ብዛት ይገልጻል::

<u>ሙዳይ</u> መጽሔት ሰኔ 1985 ዓም ከጅቡቱ ሁነው የኢትዮጵያ እስላሞች ለኢትዮጵያ የክርስቲያን አባቶች መለያየትን በተመለከተ የጻፉትን ጹሑፍ በጥሞና ሳስተዋለው የዛሬዎችን ከይሲዮች ዘመር ብለን እንዳናይ ያደርገናል:: ይህን በሰኔ 1985 ዓም የጻፉትን ጹሁስ ቀንጭቤ ከማቀርበው ይልቅ ሙሉውን ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይመልከቱ:: ይህን አንብበው የዛሬዎን ደግሞ አጢኑ::

በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ እስላሞች ከኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ጋር ችግር እንዲፈጠር ያደረገ የወያኔ መንግሥት መሆኑን ከላይ የተነበበው ጥቅስ ያስረዳል:: ለዚህም ነው ነባሩ የኢትዮጵያ እስላሞች ይህን እኩይ ድርጊት አይደግፉም ያልኩት:: ከዚህ በፊት በምጽፋቸው መጽሐፍት እስልምና ሃይማኖት ከመስራቹ እስከ አማኙ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ደግፎት ከዚህ የደረሰ መሆኑን በታሪክ ሠነድ አስደግፌ ስጽፍ እባካችሁ በክርስቲያኖች ላይ ክፋት አታስቡ የሚለውን አልተውኩም:: ዛሬም ቢሆን እባካችሁ ማለቴን አልተውም:: ነገም ከነገ ወዲያም ጌታችን መዳኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቂምን መያዝ እንደሌለብን አስተምሮናል ይህን እርሱ ያስተማረውን ትምህርት በመያዝ ስንደበደብ አልቅሰን ዝብ ብለናል::

<u>ትንቢተ ሚክያስ</u> 7+2 "ደግ ሰው ከምድር ጠፍቶአል:: በሰውም መካከል ቅን የለም፤ሁሉ ደምን ለማፍሰስ ያደባሉ፤ሰውም ሁሉ ወንድሙን በመረብ ለመያዝ ይከታተላል እጆቻቸውን ለክፋት ያነሳሉ" ሲል ጽፏል:: በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ መንግሥትና የክርስቲያኖች ጠባቂ ነን ባዮች የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ዝም ማለቱ ነው::

"ክርስቲያን መሳይ አባቱን ገዳይ ይድረስ ለጳጳሳት"ትገርማላችሁ የምትጠብቁት ምዕመን ሲደበደብ ለፀሎት ምዕመናኑን ጠርታችሁ እግዚአብሔር ይማራችሁ ሳትሉ መቅረታችሁ በእናንተም ላይ አንድ ቀን ፍርድ መምጣቱ አይቀርም! በእርግጥ እኛ በዓይናችን ልናይ አንችል ይሆናል ነገር ግን እናንተ ከፉ ረኞች በታሪክና በእግዚአብሔር ፍርድ ማግኘታችሁ አይቀርም:: ለሩቅ ምስራቅ ሕዝብ እልቂት የኢትዮጵያን ምዕመናንን ለፀሎት የጠራችሁ ስትሆኑ እንጠብቀዋለን የምትሉትን መንጋ ሲታረድ ግን ድምጻችሁ ጠፍቷል::

ዲያቆን በጋሻው ደሳለኝ የመስቀሉ ስር ቁማርተኞች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 61" ከዓመት በፊት ጃፓኖች ሱናሚ በሚሉት የጎርፍ መጥለቅለቅ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዓላማችን 260.000 ዜጎቿን ስታጣ በእርስዎ ትዕዛዝ ለሞቱት ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ጸሎት እንደተደረገላቸው የምናስታውሰው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው:: ዛሬ ግን ለገዛ ወገንዎ የጸሎትን ቸርነት መከልከልዎ መላውን ኢትዮጵያዊ ከልብ መጉዳቱ ብቻ ሳይሆን የሚሰሩት ስራ ሁሉ ለጽድቅና ለበረከት ሳይሆን ለታይታ መሆኑን ያመለክተ ነጸብራቅ ነው:: ግድያውን ባይቃወሙ እንኳን ስቆቃና ሀዘን የከበደውን ኢትዮጵያዊ እህት ወንድም እናት አባት የሞተበትን መከረኛ ሕዝብ ለማፅናናት መቼ ብቅ አሉ? መስቀልን እኮ ማክበር የሚቻለው እንደ ክርስቶስ ለሕዝብ እየሞቱ እንጅ በሽቶ የሰከረ ነጫጭ ቀሚስ እያጠለቁ አይደለም" ሲሉ ጽፈዋል::

በ2001 ዓም ላይ እስላም ወንድማችን አዲስ አበባ ላይ አራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ሲሰግድ ተይዟል:: እንዲሁም የካ ሚካኤል ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብቶ አላህ አክብር ብሎ ሲሰግድ ተይዟል:: ጎንደርም እንዲሁ ጥምቀተ ባህሩ ላይ ችግር መነሳቱና በሀረርም እንዲሁ ብጥብጥ ተነስቶ ነበር:: ይህ በውነቱ መጥፉ ጅምር አይደለም:: እስላም ወንድሞቻችን ከዚህ በፊት በአንድነት ተፋቅረን አብረን መኖራችን ታሪክ የዘገበው ሲሆን ዛሬ ግን በአንዳንድ አክራሪ ምክንያት ሰላም እየጠፋ ነው:: ስለዚህ አስቡበት የወያኔ መንግሥት ለራሱ ሥልጣን መሰንበቻ ሲል የማይፈነቅለው ድንጊያ የለም:: ይህ የእርሱ ሴራ ከሆነ ራሳችሁን ነፃ አድርጉ እንጂ አትወቀሱ:: ወያኔ ከዚህ በፊት ይዞት የተነሳው ካርድ ሁሉ ተቃጥሎበታል የቀረችው ይች በሃይማኖት ጉዳይ ሕዝቡን ማጋጨት መሆኑ ግልጽ ሲሆን ይህን ተጠቅመው አንዳንድ አክራሪዎች ሕዝብ መፍጀታቸውን እንዲያቆሙ ጥረት ማድረጉ የግራ ቀኙ የሃይማኖት መሪዎች ጉዳይ ይሆናል::

ይህ ከሆነ በኋላ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ወጣቶች ሰብስበው ግራና ቀኙን የሃይማኖት አጥባቂዮች ነቅፈዋል:: በክርስቲያኑ በኩል የተናገሩት ቃል አግባብ አይደለም "አንዳንድ ደብተሮች የክርስትና ደሴት ናት የሚሉት" ሲሉ ታሪክም አትናገሩ ማለታቸው ነው:: ኢትዮጵያ የእምነት ደሴት ናት ያሉት አንዳንድ ደብተሮች ከማንም ፀሎት ቤት ገብተው ሰው አልገደሉም:: ሰው እንደበግ አላረዱም:: ይህ እግዚአብሔር ለምን ዝም አለን? የተባለው መጣጥፍ ሆነ ድቪዲዩ የሚያሳየው ክርስቲያኖች በጎጀራ መታረዳቸውን ነው:: ይህ ደግሞ ወንጀል ነው:: ከዚህ ዝቅ ብሎ የሚነበበው ታሪክ የሚያሳየው ሥዕላቸው የታረዱ ሰዎች ሲሆን ከዚህ መጽሐፍ ላይ ሲወጣ በደንብ ሁኖ አይታይም:: ይህን ካልኩ በኋላ ደግሞ ከዚሁ ቀጥሎ ያለው እስላም ወንድሞቻችን በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ላይ እርስ በርስስ የደረሰውን ችግር በመቃወም ጅቡቱ ሁነው የጻፉትን ያሳያል:: ስዚህም ነው ሁሉን እስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መቀየም የለብንም የምለው::

## . ወሎ

- ወሎ መካነ ሰላም በሚባው ወረዳ እጅግ ብዛት ያላቸው መስጊዶች በአንድ ባለሀብት ልግስና ተሰርተዋል::
- በከሚሴና ባቲ በ1998 ዓ.ም በጥምቀት በዓል ላይ ግጭት ፈጥረዋል።
- ብዙ መድረሰዎች (የቁርአን) ት/ቤቶች ተሠርተዋል።
- ከሚሴ ሀገረ ስብከቱ ፊት ለፊት መስጊድ ለመገንባት ክርክር ላይ ናቸው:: እስካሁንም ይህ ነገር አዘል ጥያቄዎቻቸው መፍትሄ አላገኘም::
- በ1998 ዓ.ም ደሴ ቁራናችን ሸንትቤት ተገኝበን በሚል ሰበብ በደሴ ሲኒማ አዳራሽ ውስጥ ህዝብን ሰብስበው መንግስት መፍትሔ ካልሰጠን ሀገርን ከሚረብሹ አሸባሪዎች ጎን እንሰለፋለን እያሉ ንፁሁን የእስልምና ማህበረሰብ ሲያነሳሱ ነበር::

## . ጎንደር

የአበራ ጊዮርጊስንና የበዓታ ለማርያም የጸበል ቦታዎችን የይገባኛል ...ያቄ በማቅረብ ከቆዩ በኋላ አንድ አልሞት ባይ ተጋዳይ ግለሰብ በፈጸመው ...ኔታ ተነሣሥተው በ4/10/98/

1. የቂርቆስ ክፍለ ከተማ የእስላም ወረዳ ይባል፣
2. በክርስቲያን መካነ ታችን ይብቃ፣
3. ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ለምን ትባላለች?
4. ግራኝ መሐመድ ያረፈበት ቦታ ላይ ሐውልታችን ሲሰበር መንግስት ድጋፍ አላደረገልንም
5. ለምን በክርስቲያን ስም እንጠራለን የሚሉ ነጥቦችን ለዞኑ መስተዳድር አቅርበዋል።

... ... ... አቡን እንድርያስ በተገኙበት እና የዞን መስተዳድር ላይ



- ከምስት ያላነሱ «የወታደር» ማሠልጠኛዎች ተገኝተዋል።
- በ18/10/98 የጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ለማቃጠል ሲንቀሳቀሱ ፖሊስ ቀሃ ወንዝ ላይ መልሰዋቸዋል።
- በ20/10/98 ዓ.ም ኑር ዓሊ በሚባል ሹፌር በከባድ መኪና ከነተሳቢው የተመረዘ ሰይፍ ሲገባ ተጠቆሞ ሳይያዝ ቢቀርም በ23 ሽፈሩ ቁጥጥር ሥር ውሎአል:: ከሥርጭት የተረፈው 63 ሰይፍ መስጊድ ውስጥ ሲገኝ ከ 24-26 በተደረገ ፍተሻ 111 ሰይፍ ተገኝቷል::
- በ27/10/98 ሙክታር ሳሀል ጅብሪል የተባለ እስላም የሚያጠቃበትን ካርታ አነስተኛ ካሜራና የእጅ ሰዓት ይዞ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገዳማ በሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ላይ ጥቃት ለመፈጸም ሲል ከመንበረ መንግስት መድኃኒዓለም ግቢ በፖሊስ ተይዟል።
- የጥንቶቹ ሽማግሌ እስላሞች በሁኔታው ተደናግጠው ከዚህ ውጭ ነን በማለት ጥቃት አካሒደው የጦር ማሠልጠኛቻቸውን ጠቁመዋል።

### በማሠልጠኛው ከተገኙት ነገሮች መካከል

- ፋክስ፣ኢንተርኔት፣
- የአራቱ ጉባኤያት መምህራንና የደቀ መዛሙርቶቹ ስም ዝርዝር ለተለያዩ እስላማዊ መንግሥታት ፋክስ የተደረገበት ቀና ቀናዎቹ ናቸው።
- የጭልጋው አጥማቂ መነኩሴና የአባ ጊዮርጊስ ዲያቆን ተደብድበዋል።

ፅጉሜ ላይ የታሰሩት ይፈቱ በሚል ስላማዊ ሰልፍ ሲያካሄዱ ሲሞክሩ ከመንግስት ጋር ተጋጭተዋል :: ስአዲስ አበባው የመስጊድ ግንባታ ጥያቄ በአንድ ቀን ስግደት 29,000 ብር ድጋፍ ተዋጥቷል፡ በሞባይልም ማበረታቻም ይሰጥ ነበር::

## 7. ኢሊባቡር ጅማ

*በ1998 ዓ.ም*

- ክርስቲያን ሴቶች ውሃ መቅዳት አይችሉም ይደፈራሉ::
- ጉልላታቸው ተነሥቶ ጨረቃና ኮከብ የተሰቀለባቸውና ወደ መስጊድነት የተለወጡ አብያተ ክርስቲያናት አሉ:: ቅኔ ማህሌት ውስጥ ጫት ተቅሟል።
- ዲያቆናት ተገደው ስለመው ቁራን ይማራሉ::

ጌታን ሽሽ መመታመም አይችሉም::



### *1998 ዓ.ም*

ነሐሴ 10 ጀምሮ አስገድዶ የማስለም መርሀ ግብር አውጥተው ነበር::
ከመስከረም 16 1997 ዓ.ም ጀምረው ተገደው ከ 488 በላይ ክርስቲያኖች ሰልመዋል።
ከ 2000 በላይ ተፈናቅለዋል።
ከ350 ቤቶች በላይ ተቃጥለዋል ንብረታቸው ተዘርፈዋል።
ሶስት አብያተ ክርስትያናት ተቃጥለዋል ተዘርፈዋል። ለዚህም ማስረጃ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ያወጣው መግለጫ ለመጥቀስ ቢያስፈልግም ሙቱ፣ ጎሬ፣ ያንፋ ማርያምን መጥቀስ ይቻላል።

## . አዋሳ

ሆነ ተብሎ በተቀነባበረ ዘዴ በአንድ የቁራን ብጣሽ ስም ብጥብጥ በማንሳት ምህርት እንዲስተጓጎልና ምንም የማያውቁ ሰዎች እንዲገነሱቱ አድርገዋል።

## . ወለጋ

ምዕራብ ወለጋ ቆንጎ የምትባል ቦታ ቢያንስ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል:: ክርስቲያኖችም በከፍተኛ ፍጥነት በመሰደድ ላይ ናቸው:: ይህም የጥፋት ልዑክ የሆኑ የሙስሊም አባላት በሁሉም ቦታ በፍጥነት እየተስፋፉ መሆኑን ያመለክታል።

## . ጅማ /አጋሮ/

ጥቅምት 5 ቀን 1999 ዓ.ም የጻድቁን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ክበረ ዓል ላይ ሴሲት ቤተ ክርስትያኑን በመውረር 8 ሰዎች በእሳቃቂ ሁኔታ/ ገጀራና በእሳት ተቃጥለው/ ተገድለዋል:: 38 ሰዎች ቆስለዋል ቤተ ርስቲያኑን አቃጥለዋል:: ክርስቲያኖችም ሴሲቱን ሙሉ በአካባቢው ወደ ... መኖርና መሞታቸው የማይታወቅ በእርካታ



እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን የህይወትን አክሊል እሰጥሀለው ራይ 2:10



*ጥቅምት 4 ቀን 1999 ዓ.ም. በአጋሮ ወረዳ በበሻሻ ታች የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዓልን ለማክበር ሄደው የተሰዉ ሰማዕት ወ/ሮ ዓለምነሽ ደበላ*

«. . . . . . . . . . እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነፁ
ራይ 7፡14



መምሬ ከፍያለው ይግለጡ
ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም. በአጋሮ ወረዳ በበሸሻ ቃት የአቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዓልን ለማክበር ሄደው የተሰዉ ሰማዕት



**ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስደት ወይስ ረሃብ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን? ስላንተ ቀኑን ሙሉ እንገደላለን እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን**

**ሮሜ/8፤35-36**

***በሁሉም በታዎች ላይ ያላቸው የጋራ ጥያቄዎቻቸው***

1. ኢትዮጵያ ለምን የክርስቲያን ደሴት ትባላለች? እኛስ ለምን በክርስቲያን ስም እንጠራለን?
2. ኢትዮጵያ የዐረብ ሊግ አባል ለምን አትሆንም ?
3. በታፊር /በክርስቲያን/ ለምን እንገዛለን ?
4. የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛው እስላም ነው::
5. ከሐረርጌ ፣ ከአርሲ ፣ ከባሌ ፣ ከጅማና ፣ከኢሉባቦር ክርስቲያኖች ከአካባቢያችን ይውጡ:: የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ዓ.ም የሚለው ይቅርና እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ይባልልን ዓ.ም. የሚለው የአንድን ሃይማኖት ሀሳብን የሚያንፀባርቅ ነው:: በማለት ለጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ ግልፅ ደብዳቤዎች ጽፈዋል:: ለዚህም ማሳያ ሰለፊያ ጋዜጣ ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም. ያወጣው ጽሁፍ ይመልከቱ::

***ከስልቶቻቸው መካከል***

- በአለባበሳቸው በዝቶ ለመታየት መጣር
- መተንኮስና አጋጣሚውን መጠቀም
- የመስጊድና የመድረሳዎችን ግንባታ ማስፋፋት
- በዓለም ማህበረሰብ ዘንድ ጭቆና ያለባቸው እስኪመስል ድረስ መጮህ
- ሰሞኑን በዌብ ሳይቶቻቸውና በጋዜጦቻቸው የሚጮሁት ጩኸት እጅግ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ነው:: ሰለፊያ አልቅዱስ ጥቅምት፣ ህዳር 1999 ዓ.ም. የወጡት ጋዜጦች

ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን መሬት ከተሰጠ ይመጣል መከራ ገጽ

# ከጅቡቲ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች

[illegible]

የተከበራችሁ የቤተክርስቲያን መሪዎች! እርግጥ ነው ስለክርስትና እምነት ታሪክ ከናንተ ይበልጥ አናውቅም:: ይሁንና ኢትዮጵያውያን እንደመሆናችን የእስልምና እምነት በአገራችን ስለተስፋፋበትና ከክርስቲያን ወንድሞቻችን ጋር በመፈቃቀርና በመከባበር፣ በስምምነት በወዳጅነት ስለምንኖርበት ምስጢር የምናውቀው ቁምነገር አለ:: ስለዚህም አንዳንድ ነጥቦችን ልንገልፅላችሁ ተገደናል - ከታሪክ እንደምናውቀው::

የእስልምና ሀይማኖት በመነሻው ወቅት ከባድ ችግርና ፈተና እንዳጋጠመው ይታወቃል:: ዋናውን ችግር ለመጥቀስ ያህል በተለይም የመካው እስላም ኮሚውኒቲ ከተቋቋመ በኋላ ኡመተል መሀመድ (የመሀመድ ተከታ





## ምዕራፍ 4

## ከንግሥት ዩዲት እስከ ዘመነ መሳፍንት

በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል በሕገ አበው "አንድ አምላክ አለ" ብለው ያመልኩ ነበር:: ኋላ በቀዳማዊ አጤ ምኒልክና በወንድማቸው በዛጉዌ ምኒልክ፣ አማካኝነት አሪት ሃይማኖት በኢትዮጵያ ተሰብኮ ነበር:: ክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ሲሰበክ ግማሾቹ አሪትን አንለቅ ብለው የቀሩ ነበሩ:: እነዚህ የአሪት አማኞች ራሳቸውን አደራጅተው ንጉሥ እስከመሆን ደርሰው ነበር:: በዚህ ወቅት ቤተ መንግሥቱን ወገራ አድርገው ክርስቲያኑንና አሪት አማኙን በሰላም ወልቃይትን አልፈው ፖርት ሱዳን መደኔ ድረስ የሚያስተዳድር ንጉሥ ጌዲዮን ነበሩ:: እኒህ ንጉስ የአሪት አማኝ ነበሩ:: የአክሱም ነገሥታት በራሳቸው ድክመት መውደቅ ሰያሳዩ ከላይ የተጠቀሰው የንጉሥ ጌዲዮን ሴት ልጃቸው ክርስቲያኑን መንግሥት ደምሰው የአሪትን እምነት ለማስፋፋት ጥረት አደረጉ:: እኒህ ንግሥት በተለይ የደመሰሷቸው ከውጭ አገር በስደት መጥተው ገዳም በሰማቸው የተሰራውን በተለይ የ9ኙ ቅዱሳን ገዳም ደምስሰዋል:: ሌሎችን ገዳማትም መደምሰሳቸው ታሪክ ነው::

በ840 ዓም እስከ 882 ዓም ለ42 ዓመታት በውድም በግድም ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል:: በዚህ ወቅት ብዛት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ቅርሳቅርስ ተቃጥለዋል:: ነባሩ መንግሥት ከአክሱም ወደ ሸዋ መንዝ በስደት ሔዱ:: ንግሥት ዮዲት ሲሞቱ መንዝ ተደብቆ የነበረው መንግሥት ተመልሶ አክሱም በመግባት እንደ አባቶቹ አስተዳደር ይዞ ሊቆይ አልቻለም:: በዚህ ወቅት የአጤ ድል ነዓድ ልጅ ሞሰብ ወርቅን በንግርት ያገቡት መራ ተክለ ሃይማኖት መንግሥቱ ነጠቁና ከትግራይ አክሱም ላኮ መልዛ የዛሬው ወሎ ክፍለ ሀገር ሮኃ አዛወሩት:: ከ912 ዓም ጀምሮ ቤተ መንግሥቱን ከትግራይ አክሱም ወሎ ላስታ ከትሞ አገር በማስተዳደር ላይ የነበረው የዛጉዌ ሥርዎ መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን ሥራ የሰራ ቀላል አይደለም:: ቤተ ክርሥቲያን ከግብጾች ፈልቅቆ ለማውጣት ጥረት ያደረገ መሆኑ የቅዱስ ሐርቤ ታሪክ ሕያው ምስክር ነው::

በቅዱስ ላሊበላ ደብር ሰበካ ጉባኤ ገድለ ቅዱስ ላሊበላ የተባለው መጽሐፍ "በመጀመሪያ የሠራችውን ቤተ ማርያም ብሎ ሰየማት በስተኋላዋ የሠራችውን ቤተ መድኃኒዓለም ብሎ ሰየማት:: በስተፊቷ የሠሩትን ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት አንዲቱን ደብረ ሲና ብሎ ሰየማት ሁለተኛይቱን ቤተ ጎለጎታ ብሎ ሰየማት:: በስተቀኝ የተሠራችውን ቤተ መስቀል ብሎ ሰየማት፣ በስተግራም የተሰራችውን ቤተ ድናግል ብሎ ሰየማት:: እንደዚህም አድርጎ ሁለቱን የአማሩ ቤተ ክርስቲያኖችን ሰራ ሥራቸውም ልዩ ነው:: የተቃረቡም ናቸው:: ነገር ግን በመካከላቸው ያለ ቅጽር ይለያቸዋል እንጂ ከሊህም ከሁለቱ

...) በአሰብት አካባቢ አኩዋን ሙስ...ሊም (ወንድም እስላሞች) በመባል የ...ሃይማኖታችንን ትምህርት በሚገባ እየ...ሰው የመስገጃ (የመፀለያ) ቦታዎችን ...የቆረቆሩ የመሀመድን ትልቅ ነቢይ...ትና የእስልምናን ሀይማኖት ዕኑነት ...ማስተማር ዋጅባቸውን (ድርሻቸውን) ...ሀቃቸውን) እየተወጡ ናቸው፡፡ ይሁን ...ንጂ እነዚህ አኩዋን ሙስሊሞች ስለ ...ሃይማኖት በሚያስተምሩበት ጊዜ የሰ...ውን ሀይማኖት በማንቋሸሽና ምዕመና...ውን (ተከታዮቻቸውን) በመናቅ አል...በረም፡፡ አይደለምም፡፡ ምክንያቱም እ...ዲህ ዓይነቱ ድርጊት ሀጥያት (ሀራ...ም) መሆኑን ቀድመው ያውቁታልና ...ንም ተራ የሀይማኖት ሰባኪ ቢሆ...ም፡፡

በእስም የእስልምና ታሪክ ውስጥ ...ዚያ ሥልጣኔ በሊሰብት ዘመን ያለግ...ታ በውዴታ ሃይማኖቱን ተቀብሎ ...ክብርና በኢማኖ የኖረ የኢትዮጵያ ...ሙስሊም ሕዝብ መሆኑ በጣም የሚ...ስደንቅና ኢትዮጵያውያን ሙስሊም ...ና ክርስቲያኖች የምንኮራበት ጉዳይ ...ው፡፡ በዚህ ወቅት የነቢ መሀመድ ...አሊ ወሰላት ወሰላም) ዘመዶችና ...ሮች ምንም እንኳን የእስልምናን ...ይማኖት በግድ በሰይፍ ቢቀበሉም ...ኢትዮጵያ ሙስሊሙ ኅብረተሰብ ማን ...ሀይማኖቱ ትክክለኛነትና በነብያችን ...ሁ(ባ (ፍቅር) ነበር የተቀበለው ሀይ...ማኖቱን፡፡ ስለዚህ ከእስም ከሁሉም ...ላይ ግን ነብያችን ከመጀመሪያው ...መሬቱን እኛን ኢትዮጵያውያኖችን ...ው፡፡ (ባረክ አላሁ ሀበሽ) የሀበሽ ...ዝብ ይባረክ ብለዋልና ይህ ንግግራ...ው ሀይማኖታችን ኢትዮጵያ ውስጥ ...መስፋፋቱ በፊት ነበር፡፡ ለዚህ አባባ...ትንና እምነታችን አንድ ከእስላም ...መፅሐፍ የተገኘ የኢትዮጵያ ታሪክ በ...ጉኙ በማስረጃነት እንጠቅሳለን፡፡ በዚ...ቁረሾች የነቢ ተከታዮችን በሚያጠ...በት ዘመን ከእልቂት የተረፉት ...ሙስሊም ወንድሞቻችንና የነቢ ቤተሰ...ች ለነቢ እንዲህ አሉዋቸው ...ቁረሾች ሲያጠፉን ነው ተከታትለው ...ልና ወዴት እንግባ» ብለው ...ጭንቀት ሲጠይቋቸው ነቢም እንዲህ ...ው፡፡ «የሀበሽ ሀገር ወደዚያ ሂዱ ...ሐበሽ ሀገር ...ምድር ... ...ይ ሆናችሁ ፈጣሪን ብትለምኑ ...ሰማችኋል) ብለው አሉዋቸው፡፡ ...ስላም ወንድሞቻችን ወደ ኢትዮጵያ ...ዘው መጡ (ሀ ዩሆኑ)፡፡ በዚያን ጊዜ ...ነበረው የኢትዮጵያ ንጉስ ነገሥት ክርስቲያን መንግሥት ቢሆንም

በደስታና በክብር ተቀበላቸው፡፡ እነሱም የመጡበትን ሁኔታና የእስላም ተከታይ መሆናቸውን ገለፁለት፡፡ ይኽን የሰሙት ቁርሾችም እስከ ኢትዮጵያ ተከታትለው መጡና «እነኚህ የእስላም ተከታዮች ሀይማኖትህን እንዳይበክሉብህ ስጠንና እናጥፋቸው» በማለት ንጉሡን ለመኑት፡፡ ብዙም ገፀ በረከት አቀረቡለት፡፡ ክርስቲያኑ የኢትዮጵያ ንጉስም «ጋራ ሙሉ ወርቅ ብትሰጡኝ እነኚህን እስላሞች አሳልፌ አልሰጣችሁም» አላቸው፡፡ ከዚያም እስላም ወንድሞቻችን በግዛቱ ሀይማኖታቸውን እንዲያስፋፉ ፈቀደላቸው፡፡

መሠረቱ ይህ ሆኖ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ወላጆቻችን ምንም እንኳን በሀይማኖት ቢለያዩም እስከ አሁን የቆየ በሀገራችን የሀይማኖቶቻችን ባህል በህዝቦች መካከል የአንድነትና የፍቅርን የመከባበርን በጋን ገንብቶአል፡፡ እኛ የተለያዩ ሃይማኖት የምንከተል የኢትዮጵያ ሕዝቦች የአንድ ሃይማኖት ተከታይ ወግን በዓል በሚያከብሩበት ጊዜና ወቅት የሁሉም ሀይማኖት ተከታይ በጋራ በደስታና በፍቅር እያከበርን የምንኖር ከሌላው ዓለም ህዝብ የተለየን ነን፡፡ ይህም አንድ ወንድም አንድ ዝርያ በመሆናችንም ነው፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ ክርስቲያን ወንድሞቻችን ምዕመናን ላይ የተፈፀመው ቃለ እግዚአብሔር አስነዋሪ በደል ስን ሰማና ስናይ ከልብ የምናዝነውም በዚህ የተነሣ ነው፡፡ ክርስቲያን ወንድሞቻችን የሚሰሙበትና ፈጣሪያቸውን ከህጢያት ለመንፃት በሀብረት የሚለምኑበት ቤተክርስቲያናቸው እየተዘጋባቸው ሀይማኖት የለሽ (ባሀያት አምላኪ) ፀመሪል ለየመኪና መንግዱና በየሜዳው በመጥገቢታታቸው ከልብ አዝነናል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ የሀይማኖት መሪው ና መንግስት በዚህ አስከፊ ዘመን የክርስቲያንነት መብት ከመግፈፍና ምዕመናንን ከማንከራተት ይልቅ የሀይማኖት መሪው በቀሰሙት የሀይማኖት ትምህርትና መንግሥት ደግሞ ፈጣሪ በሰጠው ስልጣን ተጋግዘው ነፍሩን የክርስቲያን ሀይማኖት ማክበር ይገባቸው ነበር፡፡ የሀይማኖት መሪው ጳጳስና መንግሥት የክርስቲያን ሀይማኖት ሰባኪ ባህታዊ ከማሰር ይልቅ ማክበርና ማበረታታት ሊገባቸው ይህ አይነት ድርጊት በመደረጉ በጣም ትልቅ ውርደት ነው፡፡ ይልቅ ባገኛችሁት የፈጣሪ ስልጣን ተደስታችሁ ስለፈጣሪ ትልቅነት በማስተማር በብዙ ሺ የሚቆጠሩትን ምዕመናን ጥሩውንና

በጉውን ነገር ከመምከር ይልቅ ህዝቡ ወደመረጠው ጥሩ የፈጣሪ ቤት መንገድ በሚያመራበት ወቅት የፈጣሪን (የአላህን) ቤት መዝጋታችሁና ማዘጋታችሁ አስገቶናል፤ አሳዝኖናል፡፡ ኃጢአትም ነው፡፡ እግዚአብሔር የማይወደው፡፡ በዚያን ሰዓት ህዝቡ ቤተክርስቲያን ስትዘጉበት አላህ ተብሬዱን አውርደው እንጂ ሰው ለሀይማኖቱ ሲል ይሰዋል ይህ ሁሉ ህዝብ አንድ አይነት እንቅስቃሴ ቢጀምር በህዝቡና በታጣቂው መካከል ግጭትና አልቲት ቢፈጠር ማነው ተጠያቂው? ይህ ተግባር እኛን ሙስሊሞችን ከልብ አሳዝኖናል፡፡ ቆጳሱ ከላይ እንደገለፅነው የእግዚአብሔርን ቃልና ትምህርት ለክርስቲያኑ ህዝብ ከማስረዳትና ከማስተማር ይልቅ ሰምድራዊ ክብርና ስልጣን ሊሉ የክርስቲያን ሀይማኖት ተከታይ ምዕመናንን ማንገላታት ኃጢአትና ትልቅ ውርደት መሆኑን ቢገነዘቡት እንወዳለን፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን እስላሞች ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን ሲገላቱብን እንወድም መጥፎም ነገር እንዲደርስባቸው አንፈልግም፡፡ ምክንያቱም 1ኛ/ ወንድሞቻችን ደማችን ናቸው፡፡ 2ኛ/ ከላይ እንደገለፅነው ለኡመታል መሀመድና ለእስልም መስፋፋት ያሳዩት መንፈስና በፈፀሙት ከቡር ተግባር ባለውለታችን ናቸው፡፡ የሀይማኖት መሪዎች ግን ለምድራዊ ስልጣንና ክብር ብላችሁ የእግዚአብሔርን ቃል አትጋፉ ይሄ ድርጊት ደግሞ ሀይማኖትን ማፍረስ ማለት ነው፡፡ ሀይማኖት ካለምክንያት አይፈርስም፡፡ ታዲያ ህዝቡ ሀይማኖቱን እየወደደ የሀይማኖት መሪዎች ሀይማኖቱን የሚበትኑና የፀሎት ቤቱን የሚዘጉ ከሆነ ተልዕኮ አላቸው ኢያስኝምን? እናንተ ቢመክሳችሁም የኢትዮጵያ ህዝብ ሀይማኖቱን በግድ ስለአፈረሱበትና በዘር ስለአስገደዱት ሌላ ሃይማኖት አይከተልም፡፡ ከፍላጎት ውጭ በሃይል የሚሆን ነገር የለምና፡፡ የግድ ነገር ለትንሽ ጊዜ ነው ይላሉ አባቶቹ ሲተርቱ፡፡ በተከበረችው አገራችን ... አክራሪዎች ተልዕኮ ያለው ማንኛውም ግለ ሰብ ሆነ ድርጅት ...አለ እኛ የኢትዮጵያ እስላሞች እንቃወመዋለን፡፡ ቁረአናችንም የሰውን ሀይማኖት እያንቋሸሻችሁና እያፈራረሳችሁ በግድ እስላም አድርጉ አይልምና፡፡ ይልቁንስ ቁርአናችን የሚለው «ለኩም ዲንኩም ወላ የዲን» ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ሀራም ነው፡፡ ስለዚህም የኢትዮጵያ ክርስቲያን ወንድሞቻችን የአገራችን መሪዎችና የአረብ አክራሪዎች በፈጠሩት ሁኪታና ቱማታ ምክንያት ሀይማኖታችሁን ማናጋት የለባችሁም፡፡ ሶብርና ኢማን አላህ ይስጣችሁ፡፡ አላህ ከናንተ ጋርም ይሁን አሜን !!

==== ==== ==== ====





## ምዕራፍ 4

## ከንግሥት ዩዲት እስከ ዘመነ መሳፍንት

በኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል በሕገ አበው "አንድ አምላክ አለ" ብለው ያመልኩ ነበር፡፡ ኋላ በቀዳማዊ አጤ ምኒልክና በወንድማቸው በዛጉዌ ምኒልክ፣ አማካኝነት ኦሪት ሃይማኖት በኢትዮጵያ ተሰብኮ ነበር፡፡ ክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ሲሰበክ ግማሾቹ ኦሪትን አንለቅ ብለው የቀሩ ነበሩ፡፡ እነዚህ የኦሪት አማኞች ራሳቸውን አደራጅተው ንጉሥ እስከመሆን ደርሰው ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ቤተ መንግሥቱን ወገራ አድርገው ክርስቲያኑንና ኦሪት አማኙን በሰላም ወልቃይትን አልፈው ፖርት ሱዳን መደኔ ድረስ የሚያስተዳድር ንጉሥ ጌዲዮን ነበሩ፡፡ እኒህ ንጉስ የኦሪት አማኝ ነበሩ፡፡ የአክሱም ነገሥታት በራሳቸው ድክመት መውደቅ ሰያሳዩ ከላይ የተጠቀሰው የንጉሥ ጌዲዮን ሴት ልጃቸው ክርስቲያኑን መንግሥት ደምስው የኦሪትን እምነት ለማስፋፋት ጥረት አደረጉ፡፡ እኒህ ንግሥት በተለይ የደመሰሷቸው ከውጭ አገር በስደት መጥተው ገዳም በስማቸው የተሰራውን በተለይ የ9ኙ ቅዱሳን ገዳም ደምስሰዋል፡፡ ሲሉችን ገዳማትም መደምሰሳቸው ታሪክ ነው፡፡

በ840 ዓም እስከ 882 ዓም ለ42 ዓመታት በውድም በግድም ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል፡፡ በዚህ ወቅት ብዛት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ቅርሳቅርስ ተቃጥለዋል፡፡ ነባሩ መንግሥት ከአክሱም ወደ ሸዋ መንዝ በስደት ሔዱ፡፡ ንግሥት ዮዲት ሲሞቱ መንዝ ተደብቆ የነበረው መንግሥት ተመልሶ አክሱም በመግባት እንደ አባቶቹ አስተዳደር ይዞ ሊቆይ አልቻለም፡፡ በዚህ ወቅት የአጤ ድል ነዓድ ልጅ ሞሰብ ወርቅን በንግርት ያገቡት መራ ተክለ ሃይማኖት መንግሥቱ ነጠቁና ከትግራይ አክሱም ላኮ መልዛ የዛሬው ወሎ ክፍለ ሀገር ሮኃ አዛወሩት፡፡ ከ912 ዓም ጀምሮ ቤተ መንግሥቱን ከትግራይ አክሱም ወሎ ላስታ ከትሞ አገር በማስተዳደር ላይ የነበረው የዛጉዌ ሥርዎ መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን ሥራ የሰራ ቀላል አይደለም፡፡ ቤተ ክርሥቲያን ከንብረቶች ፈልቅቆ ለማውጣት ጥረት ያደረገ መሆኑ የቅዱስ ሐርቤ ታሪክ ሕያው ምስክር ነው፡፡

በቅዱስ ላሊበላ ደብር ሰበካ ጉባኤ ገድለ ቅዱስ ላሊበላ የተባለው መጽሐፍ "በመጀመሪያ የሠራችውን ቤተ ማርያም ብሎ ሰየማት በስተኋላዋ የሠራችውን ቤተ መድኃኒዓለም ብሎ ሰየማት፡፡ በስተፊቷ የሠሩትን ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት አንዲቱን ደብረ ሲና ብሎ ሰየማት ሁለተኛይቱን ቤተ ጎለጎታ ብሎ ሰየማት፡፡ በስተቀኝ የተሠራችውን ቤተ መስቀል ብሎ ሰየማት፣ በስተግራም የተሰራችውን ቤተ ድናግል ብሎ ሰየማት፡፡ እንደዚህም አድርጎ ሁለቱን የአማሩ ቤተ ክርስቲያኖችን ስራ ሥራቸውም ልዩ ነው፡፡ የተቃረቡም ናቸው፡፡ ነገር ግን በመካከላቸው ያለ ቅጽር ይለያቸዋል እንጂ ከሊህም ከሁለቱ

አንዲቱን ቤተ ገብርኤል ብሎ ሰየማት። ሁለተኛይቱንም ቤተ አባ ሊባኖስ ብሎ ሰየማት። እንደዚህ አድርጎ ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት አያያዘ። በቅጽር አንድ አደረጋቸው ሁለተኛም በቅጽር ለያያቸው። ሁለተኛም ቀጥሎ የሚአስደንቁ ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት ሠራ። ሥራቸው ግን የሁለቱም እየቅል ነው። ከሊህም አንዲቱን ቤተ ክርስቲያን ቤተ መርቆሬዎስ ብሎ ሰየማት። እንደዚህ አድርጎ ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት አያያዘ። ለብቻዋም አንዲቱን ቤተ ክርስቲያን ሠራ። ሥራዋም ልዩ ነው። መላእክት እንዳመለከቱት ምድሩን እየለኩለት እንዳሳዩት በትእምርተ መስቀል አስጊጦ ሠራት። እርሷንም ቤተ ጊዮርጊስ ብሎ ሰየማት። እንደዚህም አድርጎ አስሩን አብያተ ክርስቲያናት ሰርቶ ፈጸማቸው። ስራቸውም እየራሱ ነው መልካቸውም እየራሱ ነው" ሲል የቅዱስ ላሊበላ ገድል ከግእዝ ወደ አማርኛ የተተረጎመው ታሪኩን ጽፎታል።

ዶ/ር እያሌው ሲሳይ <u>የአገው ሕዝቦችና የዛጉዌ ሥርዎ መንግሥት ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 184 "የእነዚህ አብያተ ክርስቲያን የአሠራር ስልትም ሆነ የእያንዳንዳቸው ዝርዝር ሁኔታ ፍጹም የሆነ የኢትዮጵያዊነት ባሕርይ የተላበሰ ለዘመናት ተደጋግመው በተሰሩት የጥንት አክሱም ሥነ ሕንፃ ንድፎች ላይ ምስክርነታቸውን የሚገልጽና የሚታይ ነው። የላሊበላ 11 አብያተ ክርስቲያን ለዚህ ቀደምት የሥነ ሕንፃ ጥበብ መቀጠልና ሕያው መሆን ግንባር ቀደም ምሳሌዎች ይሁን እንጂ ሌሎችም ተመሳሳይ የሆኑና በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ሕንፃዎች በምድረ ኢትዮጵያ ይገኛሉ። ሌሎች አገሮች እነዚህን የመሰሉ የድንጋዮች ፍልፍል ሕንፃዎች የተነደፉበት የሥነ ሕንፃ ጥበብ ፈጽሞ የላቸውም። ኢትዮጵያ የድንጋይ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያን ሥራ በግብፅ ውስጥ ካሉት ጥንታዊያን ሕንፃዎች ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና ወይም ግንኙነት ፈጽሞ የላቸውም። ሁለቱም ሕንፃዎች በአይነትና በአሰራር የተለያዩ ናቸው። ልዩነታቸውም በአሰራራቸው ስልትና በባሕርያቸው ብቻ ሳይሆን እነዚህኞቹ ከተፈለፈሉበት ቋጥኝ ተለይተው እንደ ቤት ራሳቸውን ችለው በመቆማቸው ከዋሻዎች ውስጥ እና ውጭም በመፈልፈላቸው ጭምር ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

ወደኋላ ልመለስና የአክሱም ነገሥታት በ921 ዓም አጤ ድል ነአድ በመራ ተክለ ሃይማኖት አጤ ድል ነአድ ሲጠቁ ወደ ሽዋ መንዝ ተሰደዱ። የሚሉ ሲኖር አንዳንዶች ደግሞ አጤው ወደ ሽዋ አልተሰደዱም የተሰደዱት ሌሎች ልጆቻቸውና የቤተ መንግሥቱ ባለመዋል ናቸው ይላሉ። ይህ የነገሥታት ትውልድ ሽዋ ከገባ ጀምሮ ከአማራውና ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ተጋብቶና ተዋሕዶ የኖረው ተማሪ ተሥፋ ልደት የኋላው አጤ የኩኖ አምላክ የሐይቅ ገዳም ተማሪ ነበሩ። በዚህ ገዳም የቤተ ክህነትና የታሪክ ተማሪም በመሆን ቆይተዋል። በዚህ ወቅት ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር ግንኙነት መስርተዋል። አብዛኛው ደግሞ ለዛጉዌ ነገሥታት ለአጤ ይትባረክ ወታደር በመሆን አገልግሏል ተብሏል። በደሮም ተመካኝ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስልጣኑን በ1261 ዓም ከሮሃ ወደ ሽዋ አዛውረዋል። የሽዋ መንግሥት በ1261 ዓም እስከ 1519 ዓም በሰላም ኑሮአል። በነገራችን ላይ የአጤ አምደ ጽዮንንና የአጤ



ዘራዕይ ይቆብን ጀግንነት ሳይጠቀስ የማያልፍ ታሪክ አለ። እነዚህ ገናና ነገሥታት ለአገር አንድነት ያደረጉት ትግል ሊሰመርበት ይገባል።

አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ <u>ድብቁ መለኮታዊ ጥበቃ በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 111 "አጤ አምደ ጽዮን ክርስቲያን ንጉስ እንደ መሆኑ መጠን ክልሉን በተለይም ከአማራ ሀገር ቀጥሎ ወደ ታች እስከ ሕንድ ውቃያኖስ ያለው ሀገር በእስላሞች ተይዞ ስለነበር ያንን ለማስለቀቅ ብዙ ጦርነቶችን እንዳካሄዱ የንጉሡ ዜና መዋዕል ጸሐፊ በአንክሮ ገልጾታል" ሲሉ ጽፈዋል። በ1519 ዓም ላይ ግን የቱርክ ረዳት ተጨምሮበት አጤ ግራኝ አህመድ ተነስተው መንግሥቱን አናጉት። ይህን ያህል ዘመን የቆየው የሽዋው መንግሥት አንድም የታሪክ አሻራ ቤተ መንግሥተይ አልተወልነም የለም። ገዳማት መመስረታቸው እንዳለ ሁኖ ሌሎች ለቤተ መንግሥት መገልገያ ከተማ ፍርስራሹ አልተገኘም።

ግራኝ ተብሎ ተጽፎ ያገኘነው በእኔ አጻጻፍ አጤ አሕመድ (ግራኝ) ትውልድና ዘር በኩል የትግራይ አፋር ተወላጅ የሐረር ባላባት ከሆኑ የተወለዱ ሲሆኑ ቱርኮችና አረቦች ባስታጠቁአቸው የጦር መሳሪያ የአጤ ልብነ ደንግልን ጦር እይመቱ ምት መተው መላ ኢትዮጵያን በግድም በውድም ለ15 ዓመታት አስተዳድረዋል። የአጤ ልብነ ደንግል መንግሥት ከሽዋ ወደ ጎንደር መግባት መንስኤው እርሳቸው በአጤ ግራኝ አህመድ ድል መሆናቸው ነው። ልጃቸው አጤ ገላውዴዎስ አጤ ግራኝ አህመድን ድል ካደረገ በኋላ ደንቀዝን መስርተዋ። ሊቦ እውራጃ ውስጥ እንዲሁ በዘመኑ ለስንት ዓመት የተሰራበት መሆኑ ግልጽ ባይሆንም ቤተ መንግሥት አለ። ሌላው በዚሁ አካባቢ አንድ አስደናቂ ታሪካዊ ገበታም ይገኛል። የቤተ ክርስቲያኑን ስም መጥቀሱ ምናልባት ለሌቦች መጠቆም እንዳይሆን እንጂ ታሪካዊ ገበታው የተጻፈበት በአብራይስጥና በአርብኛ ሲሆን ትርጉሙም አብርሃም ይስሃቅን ለአምላኩ ሊሰዋለት በተዘጋጀ ግዜ ደሙን ሊያቁትበት ይዞት የነበረው ገበታ መሆኑን ጹሁፉ ይገልጻል። ይህን ታሪክ ሲናገሩ የሰማኋቸው

<u>አንድ አባት ሐምሌ 27 ቀን 1999</u> ዓም ነው። ከዚያም ጎርጎራ በአጤ ፋሲል ተመስርቷል። ኋላም ጎንደር በ1632 ዓም ተመስርቷል። ጎንደር ቤተ መንግሥትያ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከሆነ ጀምሮ ዳር ደንበር ለማስጠበቅ ጥረት ተደርጓል። አንዳንድ ግለሰቦች አሮሞዎች ከሩቅ አገር የመጡ አስመስለው ይናገራሉ። ይህ ከእውነት የራቀ ሲሆን ትክክለኛ ታሪክ ግን ከቦረና ወደ ደጋው ኢትዮጵያ የተስፋፉ ናቸው። እነዚህ አሮሞዎች ንዋሪዎን ሕዝብ እየገደሉና የነሱ ባሪያ እያደረጉ እስከ ትግራይ ተስፋፍተዋል። መልካቸው አቋማቸው ከሌላው ኢትዮጵያዊ የማይለዩ መሆናቸውን እንኳን የማይገነዘብ አንዳንድ ደነዝ ግለሰብ አፉ እንዳመጣለት ከውጭ መጡ ይላል። ሕዝቡን ገድለው መሬቱን ሰሙን ቀይረው እነሱ ሰፍረውበታል ከተባለ ትክክል ነው። በጎንደር ዘመነ መንግሥት ጀምሮ አብረው የሥልጣን ተቋዳሽ ኑረዋል። የሁሉም ነገሥታት የትውልድ ሀረግ ሲመዘዝ ዘሩን ይጠቅሳል። ለምሳሌ

በጎንደር የሚነገር አማርኛን በጥሞና ብናመሳክረው አረሞኛ ቋንቋ ቅልቅል ይታይበታል።

ጉርባ፤ሙጫ፣ሉባ እነዚህ በ3 ቃላት ለምን የአማርኛ መጠቀሚያ ሆኑ። ጉርባ ማለት ወጣት ልጅ እንደማለት እንጠቀምበታለን። ሉባ ማለት ደግሞ ብልህ ልጅ እንደማለት ነው። ሙጫ የሚለውን ደግሞ ትንሽ ልጅ ወይም ደግሞ ለማንኛውም ትንሽ ለማለት ሙጫ እንላለን። የአባ ባሕሪን ድርሰት ሳነብ አሮሞዎች በጌምድር ላይ ጦርነት ሲያደርጉ የተዋጉበት ቦታ የጠቀሰው እኔ ተወልጄ ካደኩበት አካባቢ በተለይ አያቴ እማሆይ የሹሜ ወርቄ የተወለዱበት መንደር መሆኑን አነበብኩ። ቱርኮች በምጽዋ ብቅ ብለው ባህረ ነጋሽ ይስሀቅን ወደነሱ በማስገባታቸው ምክንያት አጤ ሠርፀ ድንግል በ1573 ዓም ጦርነት ገጠሙት። በዚህ ጦርነት ወቅት ከሀዲው ባህረ ነጋሽ ይስሀቅ በደቡብ ኢትዮጵያ ተዋጊ ተመቶ ሞተ። የዛሬው ከተማ ጎንደር ከ1632 ዓም ጀምሮ እስከ 1761 ዓም የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ስትሆን ከ1761 ዓም እስከ 1845 ዓም ድረስ ያለው ዘመን መሳፍንት ተብሉ የሚጠራው አጥፊ ዘመን ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት ጠቅልሉ ከጎንደር የለቀቀው ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓም አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ከሞቱ ወዲህ ነው። በጎንደር ዘመነ መንግሥት ብዙ ልማቶች እንደነበሩ ቢጠቀስም። ዛሬ ድረስ ሕያው ምስክር ሁኖ የምናየው የፋሲል ግንብ የተገነባ ቢሆንም ቅሉ የጦር መሳሪያ ስላላመረቱ አጤ ቴዎድሮስ ይበሽቁ ነበር።

## ምዕራፍ፡ 5

## ከዘመነ መሳፍንት እስከ አጤ ምኒልክ!

በንጉሠ ነገሥት 2ኛው አጤ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ዘመን በ1747 ዓም ትግራይን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ደጃዝማች ስሑል ሚካኤል ይባሉ ነበር። እርሳቸው በባሕረ ነጋሽ አርኪኮ ብቅ እያሉ ከሚሄዱ ቱርኮች ጋር ተወዳጅተው የጦር መሳሪያ እያጠራቀሙ ራሳቸውን ማደራጀት ጀመሩ ኋላም ሸፈቱ። በቀድሞው ባህልና ወግ መሰረት የቤተ ክርስቲያን ታላላቅ አባቶች በሽምግልና መክረው እንዲያስገቧቸው ተብሉ ካሉበት አካባቢ ሰዎች ቢላኩም ደጃዝማች ከአቅዋማቸው ፍንክች የማይሉ ሆኑ። አጤ ኢያሱ ምታ ነጋሪት ክተት ሰራዊት ብለው ጦርነት ሲገጥሙ ደጃዝማች ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቁ ቢሆንም የአጤውን ሰራዊት ሊቋቋሙ አልቻሉም። ቀድሞ እምቢ ብለው የነበረውን ሽምግልና እሽ አሉ። ደጃዝማች እጃቸውን ሰጥተው ጎንደር በግዞት እንዲቀመጡ ተወሰነ። ከተወሰነ ዓመታት በኋላ ምሕረት ተደርጎላቸው የንጉሠ ነገሥቱን ልጅ ወይዘሮ አስቴር ኢያሱን እንዲያገቡ ተደርጎ ከደጃዝማችነት የራስነት ማዕረግ ተቀብለው የቀድሞ ግዛታቸው ትግራይ ተመልሰላቸው ሄዱ።



ንጉሠ ነገሥት አጤ ኢያሱ ሙተው ልጃቸው አጤ ኢዮአስ በኢትዮጵያ ሲነግሡ ለራስ ስሑል ሚካኤል ደስ አላቸው። ምክንያቱም አጤ ኢዮአስ ልጅ ናቸው። እንኳን ደስ አልዎ"ለማለት የሚመጡ መስለው 26 ሺህ የጦር መሳሪያ ከቱርክ ተቀብለው ከትግሬ ጎንደር ገቡ። ከዚያም ግንቦት 8 ቀን 1761 ዓም አጤ ኢዮአስ ኢያሱን በሻሽ አንቀው ገደሉአቸው። አንዳንድ ጸሐፊ "ራስ ስሑል ከትግሬ ጎንደር እንደገቡ ከአጤ ኢዮአስ ጋር በሰላም ብዙ ወራት ተቀምጠዋል" የሚሉ ሲኖሩ አብዛኛው ሠነድ ግን የሚለው ራስ ከፍተኛ የሆነ የሥልጣን ፍላጎት ስለነበራቸው የየጁ አሮሞዎችና የቋራ አማሮችን ጠብ በከፍተኛ ልዩነት እንዲያድግ ካደረጉ በኋላ አጤ ኢዮአስን ገድለው ሌሎችን የነገሥታት ዘሮች ከወይን አምባ አምጥተው እህታቸውን ለ70 ዓመቱ አዛውንት ድረው እርሳቸው አድራጊ ፈጣሪ ሁነው ሳለ የቋራ አማሮች የእትጌ ምንትዋብ ቤተሰቦች በከፍተኛ ቁጭት ሲነሱ የየጁ አሮሞዎችንና አማሮችን እንዲደባበዱ አድርገዋል" ይላሉ።

ዶ/ር ሀብተ ማርያም አሰፋ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሉች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 295 "ራስ ስሑል ሚካኤል የተባለው ሰው ተነስቶ ነገሥታቱን በየምክንያቱ አንዱን እየገደለ አንዱን እያነገሠ ኢትዮጵያ ለሥርዓት አልበንት አመራር ዳረጋት። ከጥንት ጀምሮ ለኢትዮጵያ አንድነት ምልክት የነበሩት ነገሥታት ከተዳፈሩ በኋላ በሌብነት፤በቀማኝነትና በስንፍና ወድቆ የነበረው ሁሉ አሁን በያለበት እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ በመባባል በያለበት ብጥብጥና ጦርነት ያካሄድ ጀመረ። ትምህርትና ብስለት በሌላቸው ደደብ አለቆች መሪነት የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሞት ፍርድ የተፈረደበት ለከፍተኛ የመጨረሻ ውድቀት የተጋለጠ አሳዛኝ ሕዝብ ሆነ። ዘመነ መሳፍንት በሚባል ዘመን የሌቦች አለቆች ወሮበላ እንዲከተላቸው ዋና መጠቀሚያ ያደረጉት የነበረው መሣሪያ ዘር እየቆጠሩ የጪዋ ልጅ ነኝ በማለት ነበር። እኔ በጣም የሚገርመኝ ወረበላዎቹ እርስ በራሳቸው ፊታውራሪ፤ደጃዝማች፣ ራስ ተባብለው ሕዝቡን እርስ በርስ እያፋጁ ኢትዮጵያን ያጠፋአት መሆናቸው ሲታወቅ መሳፍንትና መኳንንት መባላቸው ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

በላይ ግደይ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 171 "ራስ ስሑል ሚካኤል በ1761 ዓም አጤ ኢዮአስን በሻሽ አሳንቆ አስገደለው። በንጉሥ ሺሚና ሻረኑቱ የሚታወቀው ኃይሉ ራስ ስሑል ሚካኤል ባለሙሉ ሥልጣን በመሆን ለእርሱ አገዛዝ የሚመቹትን ነገሥታት ብቻ እየመረጠ በየጊዜው አንግሶአቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል። ራስ ስሑል ሚካኤል ኢትዮጵያን በፈላጭ ቆራጭነት በስልጣን ላይ ሲኖሩ አገሪቱን እንዲያስተዳድሩ የፈቀዱላቸው ከቤተ ክርስቲያኑ እስከ ቤተ መንግሥቱ ለትግራይ ተወላጆች ነበር። ዛሬ በወያኔ እንደአለው ሥርዓት ማለት ነው። ሌሎች ነገዶች መሳሪያ ታጥቀው የገንዛ ወገኑን እንዲወጋ አዘዙት እንጂ አገር ለማስተዳደር አልሰጡም።

ዶ/ር ላጲሶ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ 106 " በ1769 ራስ ሚካኤል ስሑል በጎንደር አጤ

ኢዮአስን ጨምሮ የኦሮሞና የአማራ የሥልጣን ባላንጣዎቹን ለመቅጣት 26 000 ወታደሮቹን ይዞ ወደ ጎንደር ከተማ በገባ ጊዜ "ካሉ በኋላ በገጽ 107 "ራስ ሚካኤል ስሑል በአመጽ እርምጃ በጎንደር አጤ ኢዮአስንና ዕጨጌ ሰላማን በማስገደልና ሁለት ሌላ አሻንጉሊት ነገሥታትን ሹም ሽር በማድረግ በአካባቢው ዘመነ መሳፍንት ተብሎ የሚታወቀውንና እስከ ዳ/ዊ ቴዎድሮስ ድረስ የሚቆየውን የጦርነት ዘመንና ሥርዓት ከመሰረተው በኋላ በኦሮሞና በአማራ የጦር አበጋዞች ሕብረት በጦር ሜዳ ተሸንፎ በሰኔ 1772 ወደ ትግራ ክልሉ በሽንፈት ተመለሰ" ብለዋል፡፡

በራስ ስሑል የአገዛዝ ዘመን ኑቢያ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ሱዳን ተብላ ትጠራ ጀመር፡፡ ደቡብ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያኑ መስጊድ እንዲሰራበት በኃላ የተላለቀው ስልጣን አፍቃሪ ራስ ስሑል ሚካኤል የኢትዮጵያን መንግሥት በማፍረሳቸው ነው፡፡ ይህ ስርዓት የለሽ ዘመነ መሳፍንት የኢትዮጵያ አንድነት ማፍረሱ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘርና በጎሳ ተከፋፍሎ እንዲደባደብ የተደረገበት ሲሆን የኢትዮጵያ ጠላቶች ሰላዮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡበት ወቅት ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ ጀምስ ብሩስ የአባይን ወንዝ ተከትሎ ኢትዮጵያ የገባበትና የኢትዮጵያ ቅርሳቅስ የዘረፈበት ዘመን ነበር፡፡ በዚህ ወቅት አንድ ታምር ተፈጠረ! ያም ባልታሰበና ባልተጠበቀ ቦታ መይሳው ካሳ የኋላው አጤ ቴዎድሮስ ተነሱና ቅድሚያ ቅኝ ገዥውን ቱርክን ሰናር ድረስ እየዘመቱ ያሰቃዩት ጀመር፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ የእርሳቸው ዝና ይበልጥ በቋራና በደንቢያ አልፎም ጎጃም አገው ምድር ይሰማ ጀመር፡፡ ደጃዝማች ገለሞ ከጭልጋ ቅማንት÷ፊታውራሪ ገብርዬ ከጋይንት፤ ራስ እንግዳ ከጎጃም ተራ በተራ ወደ ልጅ ካሣ ሠፈር መጡ፡፡

የልጅ ካሣ ጀግንነትና ቆራጥነት ከሕብረተሰቡ አልፎ ጎንደር ግንብ ጠባቂው 3ኛው አጤ ዮሐንስ ባለቤት ለእትጌ መነንና ለልጃቸው ለራስ አሊ ሰላም ይነሳቸው ጀመር፡፡ መሳፍንቶች እንደካሣ ያለ ወንድ ብቅ ሲል ወደ መንደራቸው እንዲመጣ ሺህ መልዕክተኛ ይልኩና ያስመጡታል፡፡ ውለው አድረው ሞራሉን አድቅቀው ይለቁታል፡፡ ይህን በማድረግ የተካኑት መሳፍንቶች ካሣን "ከማራቅ ማቅረቡ ሳይሻል አይቀርም በማለት የልጅ ልጃችን ትዋበች አሊን እንስጠዋለንና ይምጣ"የሚል ውሳኔ ይደርሳሉ፡፡ ልጅ ካሣ ጥሪውን ተቀብለው ጎንደር ሕደው ትዋበችን አግብተው ወደ ቋራ ተመለሱ፡፡ ሳይውሉ ሳያድሩ ወደ ገዳሪፍ ዘመቱና ቱርክ በዘመናዊ የጦር መሳሪያ የደነደነውና በወታደራዊ ስልት የሰለጠነ መሸጎ የተቀመጠውን የካሣ ሰራዊት ይነድፈው ጀመር በዚህ ወቅት ልጅ ካሣ ቆሰሉ፡፡

አንዳንድ የታሪክ መጽሐፍት በዚህ ወቅት ባለቤታቸው ወይዘሮ ተዋበች አሊ አብረው ሕደው ስለነበር በቱርክ ተማርከውባቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ልጅ ካሣ ከታሰሩበት ገብተው አስለቅቀው ይዘዋቸው ወደ ሠራዊታቸው ተቀላቀሉ የሚሉ አሉ፡፡ ልጅ ካሣ በዚህ ጦርነት መቁሰላቸው የሁሉም የታሪክ ደራሲያን ቃል አንድ ነው፡፡ እርሳቸው ቢቆስሉም ብዙ ንብረት ማርከው መመለሳቸው ታውቋል፡፡ ከሱዳን ወደ ቋራ እንደተመለሱ ብዙም ሳይቆዩ ባለቤታቸውን



በመያዝ ከማረኩት ንብረት ይዘው ጎንደር ሄዱ፡፡ እንደደረሱ ብዙም ሳይቆዩ ከሶ ታይቷቸው መድኃኒት ቀምሰው ዋሉ፡፡ በዚህ ወቅት እትጌ መነን "ለቆለኛ ወርቅ አያንሰውም" ብለው አንድ ወርቅ ሰጋ ስለላኩላቸው ልጅ ካሣ ተቆጡ ወዲያው ባለቤታቸውን ይዘው ወደ ቋራ ገሰገሱ፡፡

ልጅ ካሣ እትጌ መነን ሆነ ግንብ ጠባዋቂው 3ኛው አጤ ዮሐንስን ሆነ ሌሎችን መኳንንቶች ሳይሰናበቱ ጉዞአቸውን ወደ ቋራ አደረጉ፡፡ የባልና ሚስቱ መጥፋት በቤተ መንግሥቱ ሲሰማ እቴጌ መነን "ይህ የፍየል እረኛ ልጅ ምንኛ ቢንቀን ነው? ሳይሰናበተን ልጃችን ይዞ ሄደ" በማለት ይጮሁ ጀመር፡፡ በዚው ወቅት ልጅ ካሣን አንቆ ይዞ የሚያመጣ ጦር ወደ ቋራ ተላከ፡፡ ልጅ ካሣም የመጣውን ጦር ደምስሰው ማረኩ፡፡ ከጎንደር ወደ ቋራ የሄደው ሰራዊት መደምሰሱ ወሬው ጎንደር ሲሰማ እንዴት ቢደፍረን ነው ይህን ያደረገው ይባልና ይሳቅም ጀመር፡፡ እትጌ መነን ግን ተበሳጩ ደጃዝማች ወንድ ይራድ በዚህ ቀን "ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ አንገቱን አንቄ አመጣዋለሁ በማለት በብርሌ ጠጃቸውን እንደያዙ ፎከሩ፡፡ ደጃዝማች ወንድ ይራድ የአራት ደጃዝማቾች ጦር መሪ በመሆን ወደ ልጅ ካሣ ሰፈር ገሰገሱ፡፡ በሌሎች የታሪክ አጻጻፍ የደጃዝማች ወንድ ይራድ እንጅ ቀኛዝማች ወንድ ይራድ አይባሉም ደብተራ ዘነብ ግን ቀኛዝማች ይሏቸዋል፡፡ ስለዚህ ጦርነት ጉዳይ ደብተራ እንዲህ ይላሉ፡፡

ደብተራ ዘነብ <u>የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሲትማን ያሳተመው ገጽ 10 "መኳንንት ብዙ ነው 1000 ነፍጥ ተማረከ፡፡ ልጅ ካሣም አራት መቶ ጋሻና 22 ነፍጠኛ ይዘው ነው የገጠሙት፡፡ ተወይዘሮ መነንም አንድ መኮንን ቀኝ አዝማች ወንድ ይራድ እንዲህ ብሎ ፎከረ፡፡ ለወይዘሮ መነን ይህን የኮሶ ሺያጭ ልጅ አሁን እንደ ሙጭልጭላ አንገቱን አንቄ አመጣልሻለሁ አይዞሽ ብሎ ወይዘሮ መነን እንደ ደነገጡ አይቷልና ልጅ ካሣ ሸፈተ ባልዋቸው ጊዜ ጫቆ ተተያዙት መኳንንት አንዱ ቀኛዝማች ወንድ ይራድ ነው፡፡ የኮሶ ሺያጭ ልጅ ብሎ ልጅ ካሣን የሰደበ፡፡ ልጅ ካሣም እሱን እንደ ተያዘ ባዩ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፡፡ ወታደርንም ሁላ እንዲህ አሉት፡፡ ወታደር ባሬ ለምኘሀለሁ ኮሶ የሚመገብ እንግዳ መጥቶብኛልና ብለው ብዙ ኮሶ በተሰበሰበ ጊዜ አስቀድተው በታላቅ ጥዋ ሙሉ አድርገው ለቀኛዝማች ወንድ ይራድ እንዲህ ብለው ሰጡዎው፡፡ እናቴ ከገበያው ኮሶ ሳይሸጥላት ቀረ፡፡ እህል ታጣና ይህንን ኮሶውን ተመገቡ ባሉ ጊዜ እኩሌታው አስተፋው ልጅ ካሣ ጠራቸውን ከጭናቸው አኑረው ነው" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

ልጅ ካሳ ሲባሉ ሳለ ደጃዝማቹን ማረኩ፡፡ በኢትዮጵያ ባሕል መሰረት ደጃዝማች የማረከ ደጃዝማች ይባላልና ከዚህ ወዲህ ደጃዝማች ካሳ ተብለው ይጠሩ ጀመር፡፡ ደጃዝማች ካሣ እርሳቸውን ሊወጋ የመጣውን ሁላ አንድ ባንድ ድል ካደረጉ በኋላ ሌሎችን መኳንንቶችን ተራ በተራ ደብድበው በኢትዮጵያ ላይ አጤ ቴዎድሮስ ተብለው የካቲት 5 ቀን 1845 ዓም ነገሡ፡፡ ከዚህ ወዲህ የሀገርን ጥቅም ለማስጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ምኞት አደረባቸው፡፡

ጠመበንጃ አውሮፓ ተሰርቶ ከሚመጣ

ከሀገሬ ኢትዮጵያ ከአፈሩ ተነጥሮ ይውጣ!
የሃይማኖት አስተማሪ ከአውሮፓ ከሚመጣ
ከሀገሬ ቤተ ክርስቲያን ከገዳም ይውጣ
ኢትዮጵያ ዳር ደንበሯ ይጠበቅ
ድንቁርና ጠፍቶ እውቀት ይራቀቅ
ኢትዮጵያ በሁሉም ነገር ትላቅ

ብለው ሲነሱ ምድረ መኳንንት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የእርሳቸውን ዓላማ የማይደግፍ ሁላ ተገድሏል:: ሰው ቤት ውስጥ ገብቶ በላት ተቃጥሏል:: ነገር ግን እርሳቸው የማይሆንላቸው በሀገራቸው ምክንያት መሆኑን የዓይን ምስክር እስረኛው እንግሊዛዊ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል::

ዶ/ር ሔንሪ ብላንክ ዳኛው ወልደ ሥላሴ እንደተረጎመው የእሥራት ዘመን በአበሻ አገር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 184 "ቴዎድሮስ በራሳቸው ጉዳይ መታገሥ ይችላሉ፤ በአገር ጉዳይ ግን ፈጽሞ ትዕግሥት አልነበራቸውም" ሲሉ ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ያደጉት ዛሬ ወያኔ ለሱዳን ሊሰጠው ካለው ቦታ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም በመሆናቸው የኢትዮጵያን ታሪክና ወታደራዊ ኃይሏን ጠንቅቀው ስማቸው ባልታወቀ ፈላሲ መነኩሴ ተምረዋል:: እርሣቸውን እቅድ ያልተከተለውን ገድለዋል:: ታዲያ አንዳንዴ በገና ሲደረድሩ  እየበሸቃቸው እንዲህ ይሉ ነበር::

"ይሉኛል ይሉኛል ይሉኛል ጨካኝ
ሐሳቤን ሳያውቁ ምክሬን ሳይሰሙኝ"

በማለት ያዜሙ ነበር:: ጋፋት የብረታብረት እንዱስትሪ መስርተው ከሀገራቸው ውስጥ መድፍ ተሰርቶ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር ተጠብቆ ኢትዮጵያውያን በትምህርት ልቀው ተራቀው ማየት ነበር የእርሳቸው ዓላማ:: የዛሬው ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው በ1965 ዓም ጋፋት የአጤ ቴዎድሮስ የብረታብረት ፋብሪካ በተባለው መጣጥፋቸው የእውቀት ጥማት የገደላቸው መስሉ ስለታያቸው::

አበባው ይግዛው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ጥር 25 ቀን 1965 ዓም "አጤ ቴዎድሮስን የገደላቸው የጥበብ ጉጉታቸው ነው" ሲሉ ጽፈዋል:: ስለዚህ የአጤ ቴዎድሮስን ሕልም የተረዳላቸው መኳንንት አልነበረም:: የውጭ አገር ሰዎች በሃይማኖት ስም ሰላዮቻቸውን ልከው ከእርሳቸው ጋር ግጭት ፈጥረው ሲታሰሩ የገንዛ ወገናቸው የውጭ አጎብዳጅ ሀገሩን ካጅ ምድረ መኳንንት አሲሮ አሲሮ የእንግሊዝን ጦር መርቶ አምጥቶ አገሪቱን አስደፈረ:: እርሳቸውም በራሳቸው ሽጉጥ ጠጥተው ሞቱ:: ወይዘሮ ምንትዋብ ጎጃሜ አጤ ቴዎድሮስ አባታቸውንና ወንድሞቻቸውን ስለገደሉባቸው አጤውን እየሰደቡአቸው ለ14 ዓመታት አብረው ይኖሩ ነበር:: ወይዘሮ ምንትዋብ አጤ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ አሉ::



አባቴን ወንድሜን ቢገድሉ ነበር መናደዴ
በራሱ ቆረጡ ይቅር አለ ሆዴ

እያሉ ሲያለቅሱ ሌሎች የአጤ ቴዎድሮስን ሬሳ ሲመቱና ሲጎትቱ እርሳቸው ሬሳውን ሌሎች እንዳይመቱ ይከላከሉ ነበር:: የአጤ ቴዎድሮስን ሬሳ ከሚመቱት መካከል ካህናቱ ይበዙ ነበርና ወይዘሮ ምንትዋብ ወንድ መላይ አለሁ አለሁ ባይ፤ፈሪ ሬሳ ገዳይ፤ ብለው በጎደም ራሱን ሲሉት ቅንባ የሚያከለው ሻሹን አስጣሉት:: እኒያ የቤት ጀግና ግን አንዳንዴም እየፈከሩና እያለቀሱ እያዘኑ የዚያን ጀግና ሬሳ ልብስ እያለበሱ ሲታገሉ ባለ ሌላ ታምር መታየት ጀመረ:: የእንግሊዝ ወታደር የአጤ ቴዎድሮስን ዘውድ ከራሳቸው ላይ ሲያወጣ ጣል የማነን ዘውድ ማን ይወስዳል ብለው ፈረንጁን ጉርቦውን አንቀው ባለ እንግሊዛዊው አብሮ ሁለቱን መግደሉን

ቀሲስ ከፍ ያለው መራሂ ሰስቱ ምንትዋቦች በተባለው መጣጥፋቸው ታሪካቸውን ጽፈውታል:: እርሳቸው ታሪኩን ያገኙት እንፍራዝ ቤተ ክርስቲያን የአጤ ቴዎድሮስ ልጅ ራስ መሸሻ ቴዎድሮስ ጽፈው የተዉት መሆኑን ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ በልጅነታቸው ጀምሮ ዳር ደንበር ማስከበር ነበር ሕልማቸው:: የትግሬው ደጃዝማች ንጉሤ ለፈረንሳይ መሬት በባህር ደንበር ላይ መበስጠቱ አይገቡ ገብተው እርሱን ድል አደረጉ ፈረንሳዮች ቴዎድሮስ እንዳይመታቸው ሩጠው ጠፍተዋል::

አጤ ቴዎድሮስ ሲሞቱ በወቅቱ ጉልበታም መኳንንት የነበሩት የስቅጣው ዋግሹም ጎበዜ ገብረ መድህን 2ኛው አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው በኢትዮጵያ ላይ ግንቦት 10 ቀን 1860 ዓም ነግሰው የአጤ ቴዎድሮስን ዓላማ አንስተው ጎንደር ደጃዝማች ጥርሶ ጎበዜን ለመውጋት ሲሮጡ እርሳቸውንም ድል ሲያደርጉ ጎጃም በመሸፈቱ ወደ ጎጃም ዘምተው አንጹን ድል አድርገው ሲያባርሩ ባላምባራስ አዳልን ራስ ብለው ሲመለሱ ትግሬ የባለቤታቸው ትንሽ ወንድም ልማደኛው ደጃዝማች ካሳ አሁንም በድጋሜ እርሳቸውን ወግተው የኢትዮጵያን መንግሥት አፈረሱ::

ደጃዝማች ካሣ ቅድሚያ አጤ ቴዎድሮስን ለማስገደል እንግሊዞችን መርተው የመጡ ናቸው ይችን ታሪክ የወያኔ ሰዎች ሊሰሙ አይፈልጉም:: ደጃዝማች ካሳ 4ኛ አጤ ዮሐንስ ተብለው ሐምሌ 7 ቀን 1863 ዓም ሲነግሱና የዘውድ በዓላቸውን ባመቱ ቢያከብሩም ወዲያው በተለያየ ቦታ ግብጽ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለመያዝ ስትመጣ አጤ ዮሐንስ ድባቅ መተው መለሱ:: በዚህ ጦርነት ከፍተኛ የሆነ ጀግንነት ሰርተዋል:: በዚህ ድል እኛ ኢትዮጵያውያን ከልብ እናከብራቸዋለን::የሚገርመው ነገር ደግሞ አጤ ዮሐንስ ጀብድ የሰሩበት መሬት ልጆቻቸው ወያኔዎች ለኤርትራ ሰጡት:: በዚህ ጦርነት በተለይ የትግራይ ልጆች በብዛት ደማቸው የፈሰሰበት ጉዳጉዲትኔን ጉራዕ ሌሎችም ወረዳዎች ዛሬ የአጤ ዮሐንስ ወታደር ደሙ የፈሰሰበትን መሬት በታሪክ "ነበር" እያልን ማውሳት ብቻ ሆነ:: የአጤ ዮሐንስ ጀግንነት ይህ ብቻም አይደለም:: በ12ኛው ክፍለ ዘመን በቅዱስ ሀርቤ ተጀምሮ የነበረው

ኢትዮጵያውያን ልጆች ጳጳሳት ይሾሙ የሚለውን በማንሳታቸው ግብጾች 4 ጳጳሳት ልከውላቸዋል፡፡ በዚህም ክርስቲያኖች ልንከራባቸው እንችላለን፡፡ ነገር ግን በወሎ እስላሞች ላይ ሳያስተምሩ ለፈፀሙት ጭካኔ እንደግፍም፡፡

የአጤ ዮሀንስን ሌላው ስህተታቸው ጣልያንን በተመለከተ ሰሐጢ ዘምተው ሳይወጉ ተመለሱ፡፡ እንዲሁም ጎንደርን ድርቡሽ እንዲወረው የሆነው 1ኛ ጎንደሬዎችን ተሰሪ በተባለ ሥራውይታቸው በመፍጀታቸው 2ኛ በአካባቢው ጦር ትተው ባለመሄዳቸው ሲሆን 3ኛ ከሰሐጢ መተማ መዝመት ሲገባቸው እርሳቸው ግን ድርቡሽን ቅድሚያ ሳይወጉ ወደ ጎጃም ዘመቱ፡፡ አጤ ዮሐንስ ልብ የሚነካ አዋጅ ነበር ወደ ሰሐጢ ሲዘምቱ ያወጁት፡፡

አዋጅ!

"የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ልብ አድርገህ ተመልከት ኢትዮጵያ የተባለችው 1ኛ እናትህ ናት! 2ኛ ዘውድህ ናት! 3ኛ ሚስትህ ናት! 4ኛ ልጅህ ናት! 5ኛ መቃብርህ ናት! እንግዲህ የእናትን ፍቅር የዘውድ ክብር የሚሽትን ደግነት የልጅን ደስታ የመቃብርን ክባቲነት አውቀኸው ተነሳ ይህንንም አዋጅ ከሰማህ በኋላ ከመጋቢት 25 ቀን 1880 ዓም ጀምረህ ወደ ሰሐጢ ተጓዝ" የሚል አዋጅ አውጀው ወደ ሰሐጢ ተጓዙ፡፡

እርሳቸው ወደ ሰሐጢ ሲዘምቱ ጎንደር በድርቡሽ ሲወረር እርሳቸው ጣልያንን ጦርነት አልገጠሙም ነበር፡፡ የሕዝቡ መልዕክት ሲደርሳቸው የጣልያን መነኩሴ ከክርስቲያኑ ጣልያን ጋር ጦርነት ከሚገጥሙ ክርስቲያኑን ያጠፋውን ድርቡሽን ቢገጥሙ መልካም ነው እያሉ ለእኛ የበሰማም ቁሶች ሲነግሩአቸው እነሱም ይህን ለአጤው ሲያስረዱአቸው ከሰሐጢ መቀሌ ከመቀሌ ደብረ ታቦር ከዚያም አመድ በር ላይ ደርሱ፡፡ ከአመድ በር ላይ ውይይ ተደረገ፡፡ መኳንንቱ ቅድሚያ መተማ መዝመት አለብን አሉ፡፡ እርሳቸው እና አንዳንድ የእርሳቸው ደጋፊዎች ደግሞ ቅድሚያ ጎጃም እንዝመት አሉ፡፡

ገሪማ ታፈረ <u>የመከራ ድምል ከምጽዋ እስከ መተማ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 127 "አልሰማም እኔ ጃንሆይ በእውነቱ እንውረድ መተማ እንዝመት በሚሉት በየክፍሉ ትተን ከቤታችን ጠላት አጋጣሚ ሆኖ ድል ብንሆን ድንገት ልጆቻችን እኮ አያገኙም ግዛት አምጠው እያዩን ሸዋና ጎጃም ከመለዲ ጋራ ወርደን ብንገጥም ያየስ መቸም አይድን የሰማ አይሰቅም! የመተማው መውረድ ጥቂት ይቆየን አስቀድመን ሸዋ መዝመት አለብን ሺዋን ጋልበንበት አርጌሳ ድረስ ግርማችን አሳይተን ለደቡብ ንጉሥ ጎጃምን ነብኘተን እስከ ርእስ ርእስ ይህን ፈጽመን ነው በደም መለወስ ጦርነት የሚገጥም ሁለት ልብ ሆኖ ወገን አስጠቅቶ ጠላት አደንድኖ እንደ ትቢሓ ጢስ ያልቃል በኖ በኖ ወደ መተማ ስንዘምት አይታየኝም" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ስለዚህ አብዛኛው መኳንንት ቅድሚያ መተማ እንዝመት ሲሉ እርሳቸውና ጥቂት መኳንንቶች ግን ጎጃም ዘምቼ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ደፍቼ ሸዋ



ተሻግሬ ንጉሥ ምኒልክን ፈንክቼ መተማ እዘምታለሁ ብለው ጎጃም ዘመቱ ድል አድርገው ወደ ሸዋ መንገድ ሲጀምሩ ከንጉሥ ምኒልክ የተላከ ባሕታዊ "ዮሐንስ የሥላሴ ባርያ ሸዋ ብትዘምት ምኒልክን ድል ታደርጋለህ! 40 ዓመት ትነግሳለህ! ነገር ግን በነብስህ ትኮነናለህ! መተማ የዘመትክ እንደሆን ትሞታለህ ነገር ግን ትጸድቃለህ" ሲላቸው ቄስ አጤ ሲጸድቁ መተማ ዘመቱና ድል አድርገው ከበቅሎ ላይ ቆጭ ብለው ምርኮ ሲቀበሉ ሳለ በተባባሪ ጥይት ተመቱና ሞቱ፡፡ አጤ ዮሃንስ መተማ የዘመቱት ሊጸድቁ እንጅ ለጎንደር ሕዝብ ብለው አይደለም፡፡ ለምሳሌ ለያንዳንዳቸው የታሪክ ንጥብ አንዳንድ የታሪክ ሰነድ ዋቢ መጥቀስ አስፈላጊ በመሆኑ ከብዙ በጥቂቱ እነዚህን የታሪክ መጽሐፍት ለዋቢነት ልጥቀስ፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ <u>የኢትዮጵያ አንድነት እና አጤ ዮሐንስ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 504 "ያጼ ዮሐንስ ወታደር በጉዛምንና በማቻከል የተገኘውን የቤተ ክርስቲያን ሳንቃ እየነቀለ እያወጣ በጭምት አፋፍ የጥይት ማብረጃ ለማድረግ ተራውን (ተርታውን) አቁሞ ማገሩን እየፈለጠ ማንደድ ታቦቱም ከመንበሩ እያወጣ በየሜዳው በጣለው ጊዜ በንዴት ጳጳሱ አንተ ድርቡሽን አጠፋለሁ ብዬ መጣሁ ያልከው ለጎጃምአንተ ድርቡሽ ሆንክ ብለው አጤ ዮሃንስ መቆጣታቸውን ወደ አምባው ሌሊት እንዲገቡ በጨረቃ የተላኩ ያፄ ዮሃንስ ወታደሮች እንደፈጁ ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ተናደው ከላይ ብዙ ጭፍራ ሰደው ጎጃምን ክፉኛ ማስፈጀታቸው" ይሉና ገጽ 536 "አጤ ዮሐንስ ወደ ሸዋ ለመምጣት ሲነሱ በምስጢር ከንጉሥ ምኒልክ የተላኩ መነኮሳት መጥተው (ሕደው) ወደ ሸዋ የሄድህ እንደሆን ንጉሥ ምኒልክን ድል ታደርጋለህ በነፍስህ ግን ትጎዳለህ! ወደ መተማ የሄድህ እንደሆነ ግን በሰማዕትነት ትሞታለህ፡፡ በነፍስህ ትጠቀማለህ ቢሏቸው በሥጋዬ ተጠቅሜ በነፍሴ ከምጎዳ ሞት ይሻለኛል ብለው ወደ መተማ ሄዱ" ሲሉ ጽፈዋል፡፡ መዝበት አሰብኝ ያሉበትን አስመልክቶ ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገልጿል፡፡

አጤ ዮሐንስ ሞት የአጤ ምኒልክ እጅ ያለበት መሆኑን አፍወርቅ ገብረ እየሱስ <u>ዳግማዊ አጤ ምኒልክ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 56 "ያጤ ዮሐንስ ሞት ግን ባጤ ምኒልክ ብርታት ነው እንጂ በዚያ ደካማ ድርቡሽ ብርታት እንዳልሆነ ሁላችን እናውቃለን" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

## ምዕራፍ 6

## አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ ደንበር መደናበር ጀመራ!

ንጉሥ ምኒልክ 4ኛው አጤ ዮሃንስ ሞት ከሰሙ በኋላ ሚያዝያ ሚያዝያ 22 ቀን 1881 ዓም ወሎ ውጫሌ ሁነው "ገኘሁህ እኔ ነኝ ባለሀበት እርጋ"ብለው ሲያውጁ ሱዳን ድርቡሽ ገዳሪፍን አልፈው መደኔ ደርሰው ነበር፡፡ የአጤ ምኒልክ ኃይል የማይከተላቸው መሆኑን ካረጋገጡ ጀምሮ ከመደኔ ወደ ገዳሪፍ

ቀስ እያሉ መራመድ ጀመሩ:: ይህ በሱዳንና በኢትዮጵያ በኩል ያለው በዚህ ላይ እንዳለ ቅኝ ገዥዎች ማንጃበብ ጀመሩ:: ከዚህ ላይ ወደ ኋላ ልመለስና የኢትዮጵያን ስፋትና የሕዝቧን ጀግንነት አስመልክቶ ትንሽ ልበል:: ሕዝቧም የጠነከረ ሲሆን በተለይ ጀግንነትን በተመለከተ እንቁ የተባሉ ነበሩ አባቶቻችን:: እስኪ የሌላውን የታሪክ መጽሐፍ ልተውና ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈውን አንድ ታሪክ ልጥቀስ::

ብርሃኑ ደሴ ባሰው <u>የፍቅር መቅረዝ</u> በተባለው መጽሐፋቸው የኢትዮጵያ ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ 79 ግዜ እንደሆነ ምዕራፉንና ቁጥሩን ጨምሮ ጽፈዋል:: እኔ ደግሞ እርሳቸውም ያለፉት አለ እላለሁ:: እርግጥ ከሌሎች ደራሲያን በጣም ልቀው ሕደዋል:: ኢትዮጵያ የምትባል ጥንታዊት ትልቅ አገር ነበረች፤ቁመቷ አጠረ ወርዷ ጠበበ እንጂ ስሟና ሕዝቧ ዛሬ ድረስ አለ:: የዚች አገር ታላቅነትና የሕዝቧ ጀግንነት በተመለከተ ከሌላው የታሪክ መጽሐፍ ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው መዝግቦት ይገኛል::

አንዳንዴ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡ ሰዎች 41 ግዜ ስሟ ተጽፏል ይላሉ:: መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 14- 9 "ኢትዮጵያዊውም ዝሪ አንድ ሚሊዮን ሰዎችና ሦስት መቶ ሰረገሎች ይዞ ወጣባቸው፤ወደ መሪሳም መጣ:: አሳም ሊጋጠማው ወጣ፤በመሳሪም አጠገብ ባለው በጽፍታ ሸለቆ ውስጥ ተሰለፉ:: አሳም አቤቱ በብዙም ሆነ በጥቂቱ ማዳን አይሳንህም አቤቱ አምላካችን ሆይ በአንተ ታምነናልና፤ በስምህም በዚህ ታላቅ ወገን ላይ መጥተናልና እርዳን አቤቱ አምላካችን አንተ ነህ ሰውም አያሸንፍህ ብሎ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ" ሲል ጽፎአል:: ይህንና ሌሎችን የመሳሰሉ ጥቅሶች መሰብሰብ ይቻላል:: እንግዲህ እንባቢያን ከዚህ በላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ካነበብን በኋላ ዛሬ ለምን ኢትዮጵያ ልትደክም ቻለች? የመጣው ሁላ ለምን ይጠላታል? የሚለውን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ይቻል ነበር:: ነገር ግን ይህን አልፈን የመከከለኛዋ ኢትዮጵያን ታሪክ በመጠኑ ቃኝቼ ወደ ተነሳሁበት ልመለስ::

ነጋ ወልደ ሥላሴ <u>ባለታሪክ ኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 7 "ሆኖም ኢትዮጵያ የሚለው ስም በግል መጠሪያነት በተለይ የተሰጣት አንድ አገር ነበረች፤እሷም ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ናት:: አዋሳኞቿም በስተሰሜን ግብጽ ሆኖ እስከ አስንተኛው የዓባይ ወንዝ ፏፏቴ ድረስ የሚዘረጋ ከዚያም እስከ ኤሌፍንቲን ደሴት የሚደርስ በስተምዕራብ እስከ ሊቢያ መሐል በምሥራቅ ቀይ ባሕር በስተደቡብ ያልታወቁ የአፍሪካ አገሮች ናቸው:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኢትዮጵያ በስምሥራቅ የአፍሪካ ጠረፍ ላሉት አገሮች የነፃነት ምሰሶ ሆና ቆይታለች:: የኢትዮጵያ መንግሥት እስከ ቅድመ ልደት ክርስቶስ 1000 ድረስ ኀልውናው ነበረው:: እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከ1896 ዓም ጀምሮ በኃያላን የአውሮፓ መንግሥታት ዘንድ የሐበሻ መንግሥት በሚል ስያሜ ታወቀ" ሲሉ ጽፈዋል::



ዘውዴ ገብረ ሕይወት <u>የሕይወት ውጣ ውረድ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 193 "በኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚታወቀው ሶማሊያ ከቅኝ ገዥዎች እጅ ውስጥ ከመግባቷ በፊት ከቀደሙት የኢትዮጵያ ነገሥታት አንዱ አጤ ዘርዓ ያዕቆብ (1426-1460 በኢትዮጵያ (አቆጣጠር) የመንግሥታቸው አስተዳደር በምሥራቅ ክፍል እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ ተዘርግቶ እንደነበር ይታወቃል:: የዋቢ ሸበሌን ጅረት በመከተል ሠፍረው የሚገኙ ሶማሌዎች አዶና የሚሉዋቸው ከሶማሊያ የተለዩ ዘሮች ከአጤ ዘርዓ ያዕቆብ ጠረፍ ጠባቂ ወታደሮች ተቆርጠው የቀሩ ወይም በአገሩ ላይ የሠፈሩ ለመሆኑ ዋና ማስረጃ ሆነው የሚጠቀሱ ናቸው::"

ይሉና ገጽ 194 "በሶማሊያ የኢትዮጵያ ወሰን ከብዙ ዘመናት በፊት ጀምሮ ፥ ቀብሪ ደሐር፥ እየተባለ የሚጠራ አንድ የአውራጃ ግዛት አለ:: ስሙንም ያለጥርጥር ያገኘው ከትግርኛ ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም በጦርነቱ ወደፊት እንግፋ ለሞቱት ቀብር በኋላ ይሆናል ማለት ነው:: አጤ ምኒልክ የተጠቀሰውን ሰርኩላር ካሰራጩና የኢትዮጵያ ዳር ድንበር በዓለም ካሳወቁ በኋላ ጥቂት ቆይት ብሎ ነው ወደ አድዋ የዘመቱት" ሲሉ ጽፈዋል::

ከአክሱም ምስረታ በፊት የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሜረዊ የሚባለው በዛሬው ቋራ አካባቢ ነበር:: ከ880 ዓመተ ዓለም ወዲህ ቤተ መንግሥቱ ጠቅልሎ ከሜሮይ ወደ አክሱም ሲዛወር ሜሮይ መረዊ ሴሳም ሴላ ተብሎ የሚጠራው ከተማ የንግሥት ወይም የንጉሥ መቀመጫ ሆነ:: ንጉሠ ነገሥቱ አክሱም ሲቀመጥ ንጉሶች ወይም ንግሥቶች በተለይም ከ1 እስከ 12 ሕንደኬም ቤተ መንግሥታቸው በዛሬው ቋራ አካባቢ ሜርዊ እንደ ነበር ነው::

ብላቴ ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል <u>ዝክረ ነገር</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 819 ገልጸዋል:: ግንቦት 8 ቀን 34 ዓም ክርስትና የተጠመቀው (ባኮስ) ጃንደረባው የንግሥት ሕንደኬ ግምጃ ቤት ሹም ነበር:: ሐዋርያው ማቴዎስ ኢትዮጵያ ለማስተማር በመጣ ወቅት ቅድሚያ ከተጠመቁት ታላላቅ ሰዎች መካከል ንግሥት ሕንደኬ አንዷ ናቸው:: ይህ ከተማ እንዳልነበረ የሆነው ከ842 ዓም ወዲህ ነው:: ታዲያ ሜሮይ የሚቀመጠው ንግሥት ሆነች ንጉሥ እስከ ሳይላዕ ግብጽ ይገዙ ነበር:: የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ሆና የግዛት ወሰን እየደከመ የመጣው ከ7ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ወዲህ ነው:: ቤተ መንግሥቱ ከአክሱም ሮሃ ላሊበላ ሲዞወር አረቦች ሮማውያንን ከግብጽ አስለቅቀው ሕዝቡን ፈጅተው አገሩን በሰይፍ አስልመው ሲይዙት ለምልክት የተረፈው የአልክሳንደሪያ ክፍለ ሀገር ሲሆን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የነበሩት ቀስ በቀስ የዛሬው ታንዛንያና ኬንያ ሱማሌ ሱዳን ጆቦት ጅቡቲ ሁሉም የኢትዮጵያ ግዛቦት ሁነው ይኖሩ ነበር::

የግብጹ ከሊፋ የክርስቲያኖችን አባት ሊቃነ ጳጳሱን ሲያስር ንጉሠ ነገሥት አጤ ዳዊት በ1375 ዓም ካርቱም መጥተው ካልፈታህ አባይን ሊገድቡ የሚችሉ መሆናቸውን ሲልኩበት የታሰሩትን ፓትርያርክ ፈታ:: ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል ሲገኝ ግማሹ ለግብጽ ቤተ ክርስቲያን ተሰጥቶ

ነበር። የግብጽ ሊቀ ጳጳስ በሀገራቸው ውስጥ ባለው ችግር ምክንያት ይህ ክብር ያለው መስቀል ለአጤ ዳዊት ላኩላቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን የኢትዮጵያ ግዛት ከግብጽ ጋር ያዋስን ነበር። እንግዲህ ውድቀት የታየው ለመጀመሪያ ግዜ በ1744 ዓም አጤ ኢያሱ ሰናር አስገብረው ሲመለሱ በ1745 ዓም አልገብርም ብሎ ሲሸፍት ያንን ለማስገበር ሲዘምቱ ተደበደቡ። ለዚህም ዘመነ መሳፍንቱ ተመሰርቶ መንግሥት ጠፋ። እርስ በእርስ ሲዋጋ ከግማሽ በላይ ኢትዮጵያ በቱርክ ቁጥጥር ውስጥ ወደቀች።

ሱማሌም ተረሳች፣ኬንያም ተዘነጋች፣ቱርኮች በጎጃምና በጎንደር ከ1780 ዓም እስከ 1840 ዓም ድረስ 42 ግዜ ጦርነት አድርገዋል። ይህን ጦርነት የመሩት የአካባቢ የጎበዝ አለቆች እንጂ በመንግሥት ደረጃ አልነበረም። ከ42 ጦርነቶች መካከል 3ቱን የኋላው አጤ ቴዎድሮስ የመሩት ሲሆን እርሳቸው ከትልቅ ወንድማቸው ከደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ጋር በመሆን በልጅነታቸው ተዋግተዋል። አጤ ቴዎድሮስ የተዋጉት ገዳሪፍን አልፈው እንደነበር አይዘነጋም። ይህ ሁሉ ሲሆን ሱዳን የኢትዮጵያ ግዛት ነበር ማለት ነው።

የቀድሞው ኑቢያ የዛሬው ሱዳን በ18ኛው ክፍለ ዘመን አዲስ ስም ካገኘች በኋላ በዓለም ላይ የቱርክ የበላይነት እየቀነሰ ሲመጣ ለእንግሊዝ ግዛታቸውን እያስረከቡ ወጡ። ግብጾች በተራቸው ሱዳንን ሊመቱ በመነሳታቸው በዚህ ወቅት የሱዳን መሐዲስቶች ተጠናክረው ደብድበው ሲያባርሩአቸው 4ኛው አጤ ዮሐንስ ከሱዳን የሚባረሩትን ወታደሮች መንገድ ከፍተው በከሰላ ወደ ምጽዋ እንዲሄዱ አደረጉ። በዚህም ድርቡሾች ቂም ያዙ! በወሎ እስላሞች መጎዳትም ተጨማሪ ሆነላቸው። ከዚህ በኋላ ማሕዲስቶች ያላቸውን ጦር አደራጅተው ኢትዮጵያን ሊወጉ ከገዳሪፍ አልፈው ገላባት ሲደርሱ ቀም የሚላቸው ጠፋ። በዚህ ምክንያት ማሕዲስቶች ከ1878 ዓም ጀምረው ከገላባት መተማ አልፎ ጭልጋ ሲገባ የሚከላከል የለም። ምክንያቱም የጎንደር ሕዝብ በአጤ ዮሐንስ ተሰሪ ተደብድቦ አልቋል። ከሞት ያመለጠው አገር ጥሎ ሐረር ገብቷል። የቀሩት ቢበዛ ከባላንባራስ ያለፈ ሥልጣን ያለው ጎንደሬ በአጤ ዮሃንስ ዘመን አልነበረም። የተወሰኑት ሸዋ ገብተው ደጃዝማች የተባሉ ሲኖሩ ጎንደር ሲደበደብ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ከጎጃም ደንቢያ ሳር ውሃ ላይ ጦርነት ገጥመው ድርቡሽን አይመቱ ምት መተው ቅስሙን ሰበሩት ነገር ግን ድል የድርቡሽ ሆነ። በዚህ ወቅት የጎንደር ሕዝብ ተማርኮ ወደ ካርቱም ሲወሰድ እንዲህ ይል ነበር።

"ወገራ አሳላፊ ደንቢያ እንጀራ ጣይ
ተበላይ ጎንደሬ አትነሳም ወይ
ትመጫለሽ ብዬ ዙሬ ዙሬ ሳይ
ወይ ጥጋብ ወይ ኩራት ጎንደር ቀረሽ ወይ" አለ።

የጎንደር ሕዝብ በድርቡሽ ማለቅ የሰሙት የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጅ ወይዘሮ ምንትዋብ ከአባታቸው ጋር ዘምተው ያዋጉ ነበሩ። በእርግጥ ስለ እርሳቸው ቀሲስ ከፍ ያለው መራሂ ሰስቱን ምንትዋቦች በተባለው



መጣጥፋቸው ታሪካቸውን ጽፈዋል። ጀግና ሴት ሲሆኑ ድርቡሽን በለው እያሉ በማዋጋት ላይ ሳሉ ተማረኩ። ታዲያ ካርቱም ሲደርሱ "ስለሙ ሲባሉ አልሰልምም በማለታቸው ምክንያት ተገደሉ" ለሃይማኖታቸው ሲሉ የሞቱ ቆራጥ ሃይማኖተኛ ሲሆኑ የሰለሙት ኢትዮጵያውያን ጎንደር መጥተው ተናግረዋል። የወይዘሮ ምንትዋብ ተክለ ሃይማኖት ግጥም።

"አገር የምትገቡ የምትሻገሩ
ድመት በልታ ሞተች ብላችሁ ንገሩ"

ሲሉ ገጥመው ተገድለዋል። የጎንደር ሕዝብ በድርቡሽ ሲደበደብ ያለ የሌለ ኃይላቸውን በመያዝ የመጡና ደም መላሽ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሲሆኑ ለእርሳቸው ደንቢያ ሳር ውሃ ላይ መታሰቢያ ሐውልት ሊቆምላቸው ይገባል። በእርግጥ በስማቸው ሰንከሳር የተጻፈ መሆኑን በሰው ሲወራ ሰምቻለሁ። እንግዲያ ንጉሥ ምኒልክማ ከእንጦጦ አዘዞ ለመድረስ 6 ወር ፈጀባቸው። አዘዞ ደርሰው ብዙም ሳይቆዩ በጎጃም አድርገው ሸዋ ተሻገሩ። አጤ ዮሐንስ ጎጃምን ድል አድርገው ወደ መተማ ዘምተው ድርቡሽን ድል አድርገዋል። ነገር ግን በተባራሪ ጥይት መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓም ተመተው ቆሰሉና በበነገታው ሞቱ። ድርቡሽ ሸሽቶ ከሄደ በኋላ አጤውን የገደሉ ለድርቡሽ በርረው ተናገሩ። በዚህ ወቅት ድል ሁኖ የተባረረው ድርቡሽ ተጠናክሮ እንዲመለስ አደረጉ። ለአጤው ሞት በታሪክ ተጠያቂው አጤ ምኒልክ ናቸው።

ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 56 "ያጤ ዮሐንስ ሞት ግን ባጤ ምኒልክ ብርታት ነው እንጂ በዚያ ደካማ ድርቡሽ ብርታት እንዳልሆነ ሁላችን እናውቃለን" ሲሉ ጽፈዋል። ሊቀ ጠበብት አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ የአጤ ምኒልክን መጽሐፍ የጻፉት በ1901 ዓም ሲሆን አጤ ምኒልክ በሥልጣን ላይ ሳሉ ነው።

የሕይወት ውጣ ውረድ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 193 "ጥንታዊት ኢትዮጵያ በጣም ሰፊ አገር የወሰን ክልሏም አሁን ከሚታወቀው የሚያልፍ ነበር። ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በ1883 ዓም ለዓለም መንግሥታት ባስተላለፉት (ሰርኩላር) በምሥራቅ ያለውን የአገራችን ወሰን ሲገልጹ የኢትዮጵያ ግዛት ወሰን ከሶማሊያም የሚያልፍ መሆኑን አመልክተዋል። ይህም ቢሆን በአገሩ በርሃማ መሆን ለጊዜው ሳይቀናና የአስተዳደር ሥሪትም ሳይመሰረትበት የቆየ ነበር። ከዚህ የተነሣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ቅኝ ግዛት ለመያዝ ይጣደፉ ከነበሩት ሦስቱ ኃያላን መንግሥታት ፈረንሳይ፣እንግሊዝ፣ ጣልያን ይህን የአገር ክፍል ተከፋፍለው ሊይዙት ችለዋል" ቢሉ ጽፈዋል።

አውሮፓውያን አፍሪካን ለመከፋፈል 4 ሁነው ካሴሩ በኋላ ሶስቱ በኢትዮጵያ ዙሪያ መክበብ ጀመሩ። ጣልያን ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓም የውጫሌን ውል ከተዋዋሉ በኋላ አስመራን የአጤ ዮሃንስ እኅት ልጅ ደጃዝማች ደበብ ባርያው ይዘው አስረከቧቸው። ከዚያም ግማሽ ሶማሌን ያዙ። ፈረንሳይ በደጃዝማች ንጉሴ ወልደ ሚካኤል ያጣውን እድል በቀይ ባህር መሬት አጤ

ምኒልክ የዛሬውን ጅቡቲን የቀድሞውን ጀቦት በውል ሲሰጡአቸው እንግሊዝ ሱዳንንና ኬንያን፣ ግማሽ ሱማሌን በቅኝ ግዛት ሲይዝ ደንበር ለመደናበር ከአጤ ምኒልክ ጋር መነጋገር ተጀመረ፡፡ በዚህ ወቅት አጤ ምኒልክ በደቡብ ኢትዮጵያ ወደ ኬንያ ሆነ ወደ ጎንደር የተለያዩ መልዕክተኞች ሲልኩ ወደ ጎንደር የተላኩት ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ፣ ጭልጋ ሲደርሱ በወባ ታመሙ፡፡ ከሕመማቸው ተሽሎአቸው ወደ ገዳሪፍ ሲሄዱ ሱዳንን የያዘው የእንግሊዝ መንግሥት ተደናባሪ ሻለቃ ግዊን ከዚህ ቀም የሚለው ሰው ባለማግኘቱ የሚበቃውን ያክል ከልሎ ወደ መጣበት ሲመለስ የአጤ ምኒልክ ወኪል ደጃዝማች መሸሻ ሲደርሱ ምልክት እንጂ ሰው ባለማግኘታቸው የሆነውን ለአጤ ምኒልክ ተናገሩ፡፡ በዚህ ወቅት አጤ ምኒልክ ይህን ደንበር እንደማይቀበሉት ሚያዝያ 14 ቀን 1883 ዓም ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶርያ የጻፉት ደብዳቤ እንዳልተቀበሉት ሲሆን ይህን ደብዳቤ በሰነድ አምድ ቁጥር 3 ይመልከቱ፡፡

አስናቀ እንግዳ አረባዊ አጼነትና የአፍሪካ ቀንድ ፍዳ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 148" እንግሊዝ ሱዳንን በቅኝ ገዥነት በምታስተዳድርበት ግዜያት በኢትዮጵያ በኩል ከላይ ባለሥልጣን ሳይኖር እንግሊዝ የራሱን ሰው ሻለቃ (ሜጀር)ግዊን አስማርታ በመሰለው አዘጋጅቶ የነበረውን ንድፍ (ልኬት)ስ?ስእል ዛሬ የሱዳን መንግሥት ያንኑ የሻለቃ ግዊን ንድፍ በዓለም አቀፍ ተዋቂነት ያለው ህጋዊ የአገር ክልል አስመስሎ አቅርቦታል፡፡ እንዲያውም በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በጎንደር ክፍለ ሀገር ለሱዳኖች ቅኝ ገዥዎች ካስረከቧቸው ክልል አልፈው በመግባት ብዙ መሬት ይዘዋል፡፡"

"ሱዳንና ኢትዮጵያ በደንበር ያልተወሰኑ አንድ አገር ሁነው ለብዙ ዘመናት አብረው የኖሩ ሲሆን በተለይ ምስራቁ የፍንጂ ክፍል ግዛት ቅኝ ገዥዎች አካባቢውን ወርረው እስከተቆጣጠሩት እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ የግዛት አካል እንደነበር ይታወቃል፡፡ ቅኝ ገዥዎች ሕዝቡን የሚለያይ ደንበር ከማብጀታቸው በፊት በመሬቱ ላይ የነበሩ ነዋሪዎች መብታቸው ተጠብቆ ወደየት መወገን እንደሚፈልጉ ተጠይቀው ሳይረጋገጥ ነው፡፡ መሬቱ ሲከለል በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ለመከለል ብቃት ያላቸው ባለስልጣኖች ሳይኖሩ በአንድ የእንግሊዝ ሻለቃ ብቸኛ ተካላይ የተሰራው ሁኔታዎችን ያላሟላ ፈጽሞ የማይጸና ዋጋ ቢስ ያደርገዋል፡፡ ትናንትና መይሳው ካሳ አጤ ቴዎድሮስ ሰናር፣ወድ መድሀኔ ከካርቱም 180 ኪሎሜትር ምስራቅ በኢትዮጵያ ግዛትነቱ ከቱርክ ተስፋፊዎች ጋር የተዋደቁበት ታዲያ ሻለቃ ግዊን የከለለውን የገዳሪፍንና የደማዚንን አውራጃዎች በሙሉ ወደ ሱዳን ክልሉ ሲያቀርቡላቸው አጤ ምኒልክ አልተስማሙም" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

ዛሬ ላለውና ለሚመጣው ትውልድ ማለት የምፈልገው ነገር ቢኖር አጤ ምኒልክ የጌዊንን የድንብር ውል ፈጽሞ አልተቀበሉም፡፡ አጤ ምኒልክ ይህን በ1883 ዓም ከጻፉ በኋላ የአድዋ ጦርነት መነሳትና ድል ማድረግ ኋላም እርሳቸው መታመም ሁኔታውን የለዋወጠው ቢሆንም የጊዊንን ካርታ አለመቀበላቸውን ግን የተረጋገጠ ነው፡፡ በእጂ ያልገባ ሉንደን የሚገኝ የእኛ



ሰዎች የያዙት ሰነድ እንዳለ ሰምቻለሁ፡፡ ምናልባት በቅርቡ የኢትዮጵያ የድንበር ጉዳይ ኮሚሽኑ ያወጣዋል ከተባለው መጽሐፍ ላይ እንደሚወጣ ተነግሮኛል፡፡ በዚህ ሰነድም ላይ መሐተሙ ያረፈበት ቢሆንም የፈረመበት ኢትዮጵያዊ አለመኖሩን ተነግሮኛል፡፡ ማህተሙም ከሌላ ቦታ የነበረ ማህተም ዘድንች ተነስቶ የተቀመጠ ነው ተብሎም ተነግሮኛል፡፡ ይህን የተነገረኝን እንደባለው ይዘን እርሳቸው በጻፉት ላይ ግን ከዚህ መጽሐፍ ከወጣው ሠነድ ላይ ደንበራቸው የት እንደሆነ ዘርዝረው ጽፈዋል፡፡ ለዚህም ነው አልተቀበሉም የምለው፡፡ እርሳቸው ሲታመሙ የልጅ ልጃቸውን አልጋ ወራሽ ብለው ግንቦት 10 ቀን 1901 ዓም ለሕዝብ ከተናገሩ በኋላ ሲያርፉ (አጤ) ልጅ ኢያሱ ሚካኤል ይህን አውሮፓውያንን ከአፍሪካ ደብድበው ለማውጣት የነበራቸው ምኞት አይዘነጋም፡፡ እስኪ ትንሽ ስለኒህ ወጣት ፀረ ቅኝ ገዥ የሆኑትን አገር ወዳድ ታሪክ ስለ እርሳቸው ምን ይላል፡፡

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 115 "ዳግማዊ ምኒልክ በ1906 ዓም በታኅሳስ ወር ከሞቱ በኋላ አቤቶ ኢያሱ ወዲያው በጥር ወር የመልክተኞች መሪ አድርገው ወደ ነምሳ ላኩኝ ይላል ደጃዝማች በላይ አሊ ታሪኩን በመቀጠል እንዲህ አሉ አብረውኝ የሄዱት መልክተኞች ደጃዝማች ተሰማ ገዝሙ፥ልጅ አበበ ወልደዬና ልጅ ተፈሪ ቸርነት ናቸው፡፡ የነምሳ ሰው ሙሴ ሺሜር መንገድ እንዲመሩንና በሚቸግረን ሁሉ እንዲረዱን አደራ ተብለው ከእኛው ጋር ወደ ነምሳ ሄዱ" ይሉና ገጽ 117 "ያቀረብነው ጉዳይ የጦር መሣሪያ ስለ መግዛት ነበረ፡፡ ከአቤቶ ኢያሱ የታዘዝነው አንድ ሙቶ መድፍ ሰባ ሺህ ሚኒሽርና መውዜር ጠበንጃ ጥይትም ለአንድ ጠበንጃ 500 እየታሰበ እንድንገዛ ነው፡፡"

"ደጃዝማች ተሰማ ገዝሙ ጉዳያችንን ለማስረዳት ብዙ ጊዜ ሲናገሩ ሙሴ ሺሜር ንግግሩን እየተረጎሙ ይረዱን ነበር፡፡ ከብዙ ንግግር በኋላ መሣሪያውን እንድንገዛ ተፈቀደልን፡፡ የመሳሪያውንም ዓይነት አሳዩን፡፡ መድፍ ወይም ጠመንጃው አዲስ ዓይነት ነበረ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን በአገሩ ላይ አንድ አዲስ ነገር ደርሶ ጉዳያችን ለዋወጠው፡፡ እኛ እዚያው ቪየና ላይ እንዳለን የነምሳ አልጋ ወራሽና ባለቤቱ ለጉብኝት ወደ ሰርቢያ ሂደው ሳሉ በሰኔ ወር መጨረሻ አደጋ ተጥሎባቸው ሁለቱም ተገደሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በአገሩ ላይ ጦርነት ሆነ፡፡ አሳይተውን የነበረውን አዲሱን ዓይነት መሣሪያ ለነሱ ለራሳቸው የሚፈልጉት ሆነ፡፡ ስለዚህም እኛ መግዛት የምንችለው አሮጌውን ዓይነት መድፍና ጠመንጃ መሆኑን አስታወቁን እርሱንም እንኳ ከብዛቱ ቀነሱብን፡፡ የሸጡልን ምን ያህል እንደ ነበረ አሁን ዘንግቸዋለሁ፡፡ ሆኖም ሠላሳ ሺህ ጠመንጃና አንድ የተራራ መድፍ ይመስለኛል፡፡ ጥይትም እንዲሁ በመጠኑ ሸጠውልናል፡፡"

"በቪየና የተቀመጥነው ሰባት ወር ያህል ነው፡፡ እዚያው እንዳለን ትልቁ የአውሮፓ ጦርነት የሚጀምር ስለ ሆነ ወደ አገራችን በቶሎ መመለስ አስፈለገን፡፡ በጦርነቱ ምክንያት የባሕሩ መንገድ ይዘጋብናል የሚል ስጋት ነበረብን፡፡ ሙሴ ሺሜር ቀደም ብለው መሣሪያውን በነጋዴ መርከብ አስጭነው ወደ ጅቡቲ አስተላለፉት፡፡ እኛም በሐምሌ ወር መጀመሪያ ትሬስቲ ላይ

በነጋዴ መርከብ ተሣፍረን ወደ ጅቡቲ መጣን። አዲስ አበባ ስንደርስም የመልክታችንን ሁኔታ ለማስረዳት ከአቤቶ ኢያሱ ፊት ቀረብን። እሳቸውም ከቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስና ከአቶ ተሰማ እሸቴ ጋራ ሆነው ተቀብለው አነጋገሩን። ጉዳዩን የሚከታተሉት እነዚህ ሁለቱ ባለሥልጣኖች ቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስና አቶ ተሰማ እሸቴ ነበሩ" ሲሉ ጽፈዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከዳግማዊ አጤ ምኒልክ ወደ ልጅ ኢያሱ ሲሸጋገር እንዳልተለፋለት በማስመሰል አንዳንድ የቤተ መንግሥት ደራሲያን የዛሬውን ትውልድ ለማሳመን ጥረት ቢያደርጉም ቅሉ ወጣቱ (አጤ) ልጅ እያሱ ግን "ይንገሡ" ሲባሉ መልሳቸው "ፈረሴ ምጽዋ ውሃ ሳይጠጣ አልነግስም" አሉ ይህን ያሉትን ጀግና ዛሬ አንዳንድ ሰዎች የሰሩ አስመስለው አያዩአቸውም። እኒህ ወጣት በ12 ዓመታቸው አልጋ ወራሽ ሲሆኑ ሞግዚት ነበራቸው። ሞግዚታቸው ሲሞቱባቸው በ14 ዓመታቸው አገር መምራት ሲጀምሩ ቅኝ ገዥዎችን ከኢትዮጵያ ዳር ደንበር መንጥረው ለማውጣት ጥረት ማድረጋቸው ዛሬ ያለውን ደንበር ወሰን ሊቀበሉት ቀርቶ ሕልም እንኳን አላለሙበትም። ወጣቱ (አጤ) ልጅ ኢያሱ ቅኝ ገዥዎችን ከምስራቅ አፍሪካ ጠራርገው ለማስወጣት የነበራቸው ምኞት በአውሮፓውያንና ሥልጣን በፈለጉ መኳንንቶች በተለይም በደጃዝማች ተፈሪ ሴረኝነት ሊከሽፍ ቻለ። በወቅቱ የነበሩት ምኒስተሮች ይንገሡ ሲሏቸው ቅድሚያ የእርሳቸው ዓላማ ምን እንደነበር አሳሰቡአቸው።

ኀበዜ ጣፈጠ <u>አባ ጤና ኢያሱ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 57 "ሚኒስተሮችና መኳንንቶች በቅይታ ተመካክረው ለአቤቶ ኢያሱ የምክር ቃል አቀረቡ። የምክሩ ቃል ጃንሆይ አጤ ምኒልክ በሕይወታቸው ሳሉ አልገወራሼ ኢያሱ ነው ብለው አስታወቁን። አሁን እርሳቸው ዐረፉ። እንግዲህ ምን እስኪሆን እንጠብቃለን የዘውድ በዓልዎ የሚደረግበትን ቀን እንወስንና ዘውድ ደፍተው በአባትዎ መንበረ ዳዊት ይቀመጡልን የሚል ነው። አቤቶ ኢያሱም ምክራችሁ መልካም ነው፤እኔም ሳላስብበት አልቀረሁም። ነገር ግን አባቴን ራስ ሚካኤልን በፊት ንጉሥ አሰኝቼ በኋላ ንጉሠ ነገሥት መሆን ይገባኛል ብለው መለሱላቸው። ከዚያም አያይዘው ፈረሴ ከምጽዋ ውኃ ሳይጠጣ ዘውድ ሞኘ ንጉሠ ነገሥት አልባልም እያሉ መቆየታቸውን የሚታወስ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። እኔ በቅንፍ (አጤ)እያልኩ ነው የምጽፍ። ይህን ግልጽና ትክክለኛ ታሪክ አቶ ዘውዴ ረታ ውድቅ ሲያደርጉት ይታያሉ።

ዘውዴ ረታ <u>ተፈሪ መኮንን ረዥሙ የሥልጣን ጉዞ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 280" ኢትዮጵያ በኮሎኒሊስቶች የተወሰደባት ግዛቶቿ ተመልሰውላት ፈረሴ የምዕዋን ባሕር ውሃ ሳይጠጣ ዘውድ አልጭንም ብለዋል የሚለው ሰበብ መነገር ጀመረ። በውነቱ እንደዚህ አስበውም ከሆነ ይህን የተለሙትን ግብ ለመምታት ንጉሠ ነገሥት መሆን እንቅፋት ሊሆንባቸው እንደማይችል ማወቅ ነበረባቸው" ሲሉ ጽፈዋል።



(አጤ)ልጅ ኢያሱ አባታቸው ራስ ሚካኤልን ንጉሥ ካሰኙ በኋላ አውሮፓ የጦር መሳሪያ ለማስመጣት መልክተኞች ልከዋል። የ(አጤ)ልጅ ኢያሱ ዓላማ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር እንዲከበር ከፍተኛ የሆነ ጥረትና ሕልም ነበራቸው ይህን አስመልክቶ አባ ጤና ኢያሱ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 78 "ልጅ ኢያሱ የአባታቸውን የአጤ ምኒልክ የፖለቲካ መስመር ከመከተል አልፈው ዓይነተኛ መመሪያ አድርገውት ነበር። በዓለም አቀፍ ግንባር ደግሞ በብልሃት በተቀነባበረ የዲፕሎማሲ ትግል አማካይነት የኢትዮጵያን ጠረፎች ከባዕዳን እጅ እንደሚያስለቅቁ ተስፋ ማድረጋቸው አልቀረም" ሲሉ ጽፈዋል።

የሱማሌን ፀረ ቅኝ ግዥ የሆኑትን ሰብስበው ማደራጀታቸው ወሰናቸውን ለማስከበር ስላሰቡ ነው። በአሰብ አስተዳደር በአፋር ግዛት ብቻ ከ40 ሺህ በላይ ወታደር ማሰባሰባቸው ከአፋሯ ቆንጆ የወለዱአቸውን ልጅ ምኒልክ ማለታቸው ሕዝቡን ከሕዝብ ለማቀራረብና በሃይማኖት መለያየትን ለማስቀረት ያደረጉት ዓላማ የእርሳቸው ተግባር ሕዝቡ አንዴ ተነስቶ ቅኝ ገዥዎችን እንዲመታ ለማድረግ ስላሰቡ መፈክራቸው "ሃይማኖት የግል ነው አገር የጋራ ነው" የሚለውን ዓላማ ዛሬ አጤ ኃይለ ሥላሴ እንዳሉት ተደርጎ ይሰበካል። ይህ የአጤ ልጅ ኢያሱ ዓላማ የተረዱት ቅኝ ገዥዎች ልጅ ኢያሱ "ሰልመዋል" ብለው የእርሳቸውንና የእስላሞች ሥዕል+ ፎቶአቸውን ካርቱም ወስደው በነሱ ካሜራ አብረው የተነሱ አስመስለው ለመኳንንቶች አምጥተው ሰጡአቸው። መኳንንቶችን አጉል አማኝ ነን ባዮች በመነሳታቸው የተጀመረው የደንበር ማስከበሩ ጉዳይ ተረስቶ በርሳቸው ላይ ተዘመተባቸው።

መስከረም 17 ቀን 1909 ዓም ጀምረው አገር ያስተዳደሩት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ናቸው። በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን ኢትዮጵያ ያሰራችው ገጸ ምድር ካርታ አለ። የሀገር ካርታ አልባ ኢትዮጵያ የመንግሥቱ ማኅበር ዓባል አገር ልትሆን አትችልም። ካርታ እንደነበራት ኢትዮጵያ በወቅቱ ለመንግሥቱ ሙኅበር ጀኔቭ ከጻፈችው ደብዳቤ ላይ ሐምሌ 26 ቀን 1915 ዓም የተጻፈው ደብዳቤ "የአገሪቱ ካርታ" የሚለው ቃል የአገር አንድነት ለመጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ጥረት ተደርጓል።

ኢትዮጵያ ማሟላት የሚገባትን ሕጋዊ ሰነዶች ካቀረበች በኋላ መስከረም 16 ቀን 1916 ተፈቅዶላት የመንግሥቱ ማህበር ዓባል ሆነች። ምንም እንኳን ይህ ማህበር በ1928 ዓም በመርዝ ስትገደል ባይደርስላትም ሀገሪቱ ከአጤ ምኒልክ ወደ አጤ ልጅ ኢያሱ ከዚያም ወደ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ደርሶ ለማስፋፋት ጥረት ባያደርጉም የተረከቧትን አገር ለማስጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ትግል አድርገዋል። በእርሳቸው ዘመን የተሰራው ካርታ ዛሬ በዋሽንግተን ዲሲ ታላቁ መጽሐፍት ቤት ይገኛል። ራስ ተፈሪ መኳንንቶችን ተራ በተራ እያሰሩ አገሪቱን በቻቸውን ለመያዝ ሲያስቡ ብዙዎችን አጠቁ። ንጉሥ መሆን አለብኝ ብለው በአጫፋሪዎቻቸው በኩል ለንግሥት ተነግሮላቸው የጎንደር ንጉሥ ሁነው ነገሡ በዚያን ግዜ ከቀሩት መኳንንቶች መካከል የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ባለቤት ራስ ጉግሳ ወሌ፤ በመሆናቸው ጠብ ፈልገው ነው። ንጉሥ

ተፈሪም በጎንደር ላይ ሲነግሱ መተማ ቀረጥ በራሳቸው ቁጥጥር ስር ለማድረግ ወሰኑ። ለዚህም ራስ ጉግሣ ወሌ የማይቀበሉት መሆኑን ገለጹ።

ቀኛዝማች <u>ጉግሣ መጽሔት</u> ቅጽ 2 ቁጥር 1 ሐምሌ 1992 ዓም ገጽ 3 "በራስ ተፈሪና በራስ ጉግሣ መካከል ብዙ ችግሮች ተከሰቱ። ያም የዘረፉ ሁኔታም ጭምር ነው። ምክንያቱም የመተማው ግምሩክ ራስ ተፈሪ በራሳቸው ቁጥጥር ስር ለማድረግ ይጥሩ ጀመር። ራስ ጉግሣ በእኔ በገዥው እንጅ በራስ ተፈሪ ቁጥጥር አይሆንም። ማንኛውንም የጎንደር ንብረት እኛ ተረክበን እንደማንኛውም መኳንንቶች ግብር ለመንግሥት እንከፍላለን እንጂ በቀጥታ የራስ ተፈሪ ወኪል መተማ አይቀመጥም አሉ። በዚህ ምክንያት ከራስ ተፈሪ ጋር ተጣሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ በፈረንጅ ሹፌር (አብራሪ) በአየር ተደበደቡ ሞቱ" ሲሉ ጽፈዋል።

<u>ተፈሪ መኮንን ረዥሙ የሥልጣን ጉዞ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 296 "ንግሥተ ነገሥታት ሆነው የአባታቸውን ዘውድ የሚወርሱት ወይዘሮ ዘውዲቱ ምኒልክ ከእንግዲህ ወዲህ ሕይወታቸውን ለኢትዮጵያ አገራቸውና ለሕዝባቸው ደህንነት ሠውተው ከምድራዊ ዓለም በመራቅ በጾም በጸሎትና በንጽህና መኖር ስለአለባቸው ከባለቤታቸው እንዲለያዩ በታላላቆቹና በሃይማኖት አባቶች ተወስኖባቸዋል። ስለዚህ የንግሥቲቱ ባል በመሆኔ በንጉሥ ደረጃ የወርቅ ወንበር ተዘጋጅቶልኝ ተከብሬና ታፍሬ በሰፊው እንደላቀቃለሁ ብለው ሲያልሙ የነበሩት ትልቁ ጎንደሬ እንኳንስ የሥልጣኑና የወጉ ተካፋይ ለመሆን ቀርቶ ከሚስታቸው ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ ለመኖር እንኳ እንዳልተፈቀደላቸው በተነገራቸው ጊዜ ምን ያህል ብስጭት ምን ያህል ሐዘን እንደ ተሰማቸው መገመት ይቻላል"።

ይሉና ገጽ 298" የሸዋ ብልሃት የረቀቀ ስለሆነ ለሕዝቡ የተነገረው ንግሥት ራሳቸው ማንም ሳያስገድባቸው ከእንግዲህ ወዲህ ሕይወቴ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደህንነት ስለሆነ ከዚህ የተለየ ዓለም የለኝም በማለት በጾምና በጸሎት ተወስነው ለመኖር ቆርጠዋል ተብሎ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ንጉሥ ተፈሪ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱን ዶ/ር አነር በተባለው ሐኪም ገድለው ስልጣናቸው ቁጭ እንዳሉ ብዙ ሳይቆይ የጣልያን ወረራ ብቅ አለ። በዚህ ወቅት አጤው ማይጨው ዘምተው ድል ሆኑ። ጣልያን ለጊዜው ድል ሊያደርግ የቻለው በአየር መርዝ ጢስ ሲሆን እርሳቸው ቤተሰቦቻቸውንና ባለሟሎቻቸውን አስከትለው ለንደን ገቡ። የሀገሬ የፋርጣ አልቃሽ እንዲህ አለች።

በትግሬ በወሎ በጎንደር በጎጃም ቢመጣ መች ይገባት ነበር
በሸዋ ወለጋ ኢሉባቦር በከፋ ቢመጣ መች ይገባት ነበር
በጋሞ አሩሲ ሲዳሞ በባሌ በሐረር ቢመጣ መች ይገባት ነበር
በሰማይ መጣብን በማናውቀው ሐገር" ነበር ያለችው።

በዚህ ወቅት ጣልያን ለአገዛዙ ያልተመቹት 1ኛው የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅድሚያ አሻፈረኝ ብለው ከአገር ልጆች ጋር አብረው



ቆመው ጠላትን ወራሪውን እንኳን ሕዝቡ መሬቷ እንዳትገዛው ብለው ለምዕመናን ልጆቻቸው አስተምረው መስዕዋት ሆኑ። 2ኛው ኢጣልያን ጠላት አድርጋ የተነሳችበት በአማራው ሕዝብ ላይ ሲሆን የአማራ ክፍለ ሀገር ናቸው ከሚባሉት ቀርቶ በሌሎች ክፍለ ሀገር ውስጥ አርበኛ በመሆን ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር ወራሪውን ጠላት ጠዘጠዙት። እንግሊዞች የጊዊን ወሰን እንደያዙ ናቸው። ጅቡቲ ከፈረንሳይ ጋር የነበረውን ወሰን ሲቀበሉ ከሱዳን ጋር በሚዋሰነውን በመያዝ ከውጭ ጋር የሚያገናኘውን እንዳለ አድርገው ሱማሌንና ኤርትራን ከሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች ጋር ደብልቀው በወረቀት ላይ ነድፈው ለማስተዳደር ጥረት ሲያደርጉ ሲጀምሩ ቁርጠኛ የኢትዮጵያ ልጆች በያሉበት ይነድፏቸው ጀመር። በዚህ ወቅት ጣልያን ከጀርመን ጋር ስትሆን እንግሊዞች ቀደም ይጠሉአቸው የነበሩ የኢትዮጵያውን ከአጤው ጀምሮ ወደ ሱዳን ማስገባት ያዙ። አርበኞችንም ማድነቅ ጀመሩ።

<u>የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመናት</u> ትግልና የዘመናዊ ሠራዊት አመሰራረት 1855-1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 79 "ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛቷ ካርታ ውስጥ ብታስገባትም የአርበኞች ትግል እየጠነከረ በመሄድ ላይ ስለነበረ ጦሯ ከሰፈረበት አካባቢና ከታላላቅ ከተማዎች በስተቀር የኢትዮጵያን ለመቆጣጠር አልተቻለም" ይሉና ገጽ 82 "ሰኔ 10 ቀን 1940 ዓም የኢጣሊያ የጦር አዋጅ አናግራ ከጀርመን ጋር መሰለፏን ለዓለም ይፋ በማድረጓ የኢጣሊያን አዋጅ እንደሰሙ ጀ/ፕላት ለኢትዮጵያ አርበኞች የሚከተለውን መልዕክት አስተላለፉ። ወረቀቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በአውሮፕላን ተበተነ። መልዕክቱም ሰላም ለሁላችሁ ይሁን ከዛሬ ጀምሮ በእንግሊዝና በኢጣሊያ መካከል ጦርነት ተጀምሯል። የጋራ ጠላታችንን ተባብረን ለመደምሰስ ጠመንጃ ጥይት መድኃኒት ካስፈለጋችሁም ልብስና ምግብ የሚያስፈልጋችሁን ያህል ለማንሳት መልዕክተኞቻችሁ ወደፊት በሚነገራችሁ ቦታና ጊዜ እንዲያገኙ የሚል ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ከበደ ተሰማ <u>የታሪክ ማስታወሻ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 206 "በማግሥቱ ዱካን ለቀን ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ጉዞዋችንን ቀጠልንና ሐምሌ 25 ቀን 1932 ዓም የሱዳንን ወሰን አልፈን በኢትዮጵያ መሬት ገባን" ሲሉ ጽፈዋል። በወቅቱ ሱዳንን ይገዙ የነበሩ እንግሊዞች ቀደም ሲል ብቻቸውን ወስነው ደንበራችን ካሉት ላይ ቆመዋል። ኢጣሊያን በወረቀት ላይ ይሳል እንጂ ወደ ደንበር ብቅ አላለም። እንግሊዞችም አገሯ ደከማለች ብለው አዲስ መስመር ለመስራት አላቀዱም። በዚህ ወቅት ነው ደካዝማች ከበደ ተሰማ ከኢየሩሳሌም ካርቱም ከዚያም ገዳሪፍ ብሎም ዱካ ወደ ኢትዮጵያ ሊገቡ የመጡት።

ሕይወት ጎዳና <u>ያቺ ቀን ተረሣች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 400 "እንግሊዞች ሽፍቶች እያሉ ይጠሩን የነበረውን አሁን ቃላቸውን ለውጠው የኢትዮጵያ አርበኞች በሁሉም በኩል ኢጣሊያንን አጣደፉት እያሉ በሬዲዮን ሳይቀር ይናገሩ ጀመር" ሲሉ ጽፈዋል። ከዚህ ላይ ሲጤን የሚገባው ጉዳይ አለ።

# ክፍል ሶስት

## ምዕራፍ 1

## የኢትዮጵያ ዳር ደንበር በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን

ንጉሥ ተፈሪ አጤ ኃይለ ሥላሴ ተብለው ከስልጣን ከወጡ ጀምሮ ከላይ የተዘረዘረው እንዳለ ሁኖ እንደገና አንድ አድርገው ለማስተዳደር ጥረት ሲደረግ የወሰን ጉዳይ አንዱ ዋና መሆኑን ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ ገልጸዋል። ከዚህ ላይ አጤ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ከበደሉት ይልቅ የሰሩት ይበልጣል። መቸም እኛ ኢትዮጵያውያን ሁሌም መጥፎውን አጉልቶ ማሳየት በሀገራችን የተለመደ መሆኑ ባይካድም ከዚህ በታች የሚተነተነው የክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ለድንበር ማስከበር መሳካት አጤው መልካም ፈቃዱ ሳይኖር በስልጣናቸው ሊሰሩት እንደማይችሉ ግልጽ ነው። በእርግጥ የወጣቱ የሕግ ምሁሩ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ብስለት መኖር እንዳለ ሁኖ የአጤ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ ሳይጨመርበት ግቡን ሊመታ አይችልም። የክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ፤ ጽሑፍ እንደሚያመለክተው አጤ ምኒልክ ከተለያዩ የቅኝ ገዥዎች መንግሥታት ጋር የተዋዋሉትን ውል እርሳቸው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት የሰሩትን ጽፈዋል። አጤ ምኒልክ ጋንቤላን በውል የሰጡ መሆናቸውን ገልጸዋል። ያም እንግሊዞች ከሱዳን ሲለቁ ጋንቤላን ለኢትዮጵያ ሊያስረክቡ የተስማሙ መሆኑን ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ለደርግ መርማሪ ኮሚሽን የአስረከቡት በ57 ገጽ ሰነድ ዋቢ ነው። ከዚህ ከክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐብተ ወልድ ጽሑፍ ደንበርን በተመለከተ እርሳቸው የጻፉትን ብቻ ሰብስቤ ጠቅለል አድርጌ ከዚህ መጽሐፍ ላይ አቅርቤዋለሁ። ከዚህ በታች የጻፉትን ሰነድ ከመጻፌ በፊት አንዳንዱ ቃል ግልጽ ያልሆነውን ( )በቅንፍ እጽፋለሁ። ምክንያቱም ለወደፊቱ ዋናው ተገኝቶ ለማመሳከር ይቻል ይሆናል በማለት ሲሆን አንዳንድ ቃላት ፈረንሳይኛና እንግሊዘኛ ቋንቋ አለበት።

### "በኢትዮጵያና በፈረንሳይ ሱማሌ ጠረፍ"

ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ መስከረም 10 ቀን 1967 ዓም ለመርማሪ ኮሚስዮን ያቀረቡት ጽሑፍ በተባለው መጣጥፍ ገጽ 46-50 "አፋምቦ አመላለስ በምን አኳኋን እንዳስመለስኩ፤ አፋምቦ በኢትዮጵያና በፈረንሳይ ሱማሌ ጠረፍ አጠገብ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ስትራቴጂክ የሆነ ሥፍራ ነው። አውሳንና የፈረንሳይን ሱማሌ ተራራማ በመሆን ኮንትሮል የሚያደርግ ውሃም ያለበት በጣም ጠቃሚ ስፍራ ነው። ፈረንሳይም ሁል ጊዜ የጅቡቲ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ወደ አውሳና (ድሬዳዋ) ነበር አይናቸውን



የሚያዘነብሉት በ1906 የፈረንሳይና እንግሊዝ ጣልያን ኢትዮጵያን በየን ለመከፋፈል ያደረጉት ውል ማየት በ1944 ውል በኋላ እንግሊዞች ኢትዮጵያን ለቀው ሲሄዱ ፈረንሳይዎች አፍምቦን መያዛቸውን ተእንግሊዞች ሰሜን የፈረንሳይን አምባሳደር ጠርቼ ፕሮቴስታሌዎን አድርጌ በተሉ እንዲለቁ ብጠይቅ አገሩ የፈረንሳይ ስለሆነ አንለቅም አሉ። ተጃንሆይ ጋርም ተመንግሥት ጋር ተመካከርኩ። በኋይል ለመውሰድ ያን ጊዜ ራስ አበበ የጦር ሚኒስትር ነበሩ። ኃይል በዚያን ጊዜ ጅቡቴ ታሉት ፈረንሳዮች ጋር ለመዋጋት የሚበቃ እንደሌለ አስረዱኝ። ሃሳቤ ጅቡቴንም ለመያዝ ነበረ። ምንም በኃይል አለመቻሉን ሲታወቅ በዲፕሎማስ ብቻ የተቻለውን እንዳደርግ ታዘዝኩ"።

"የፈረንሳይን አምባሳደር ጠርቼ እናንተም የኛ ነው ስትሉ እኛም የኛ ነው ስንል የሚለየን በእኛ በኢትዮጵያ መካከል የተደረገው የጠረፍ ውል ነው። ተውሉ ጋር የተያያዘ ካርታ የስዕል ካርታ የሚባል አለ። ስለዚህ አሁኑኑ አንድ ስምምነት ፕሮቶኮል ፈርመን የሚለየን ለማድረግ እንስማማ ይህንንም ስናደርግ አፍምቦ በውነት የማን እንደሆነ ይታያል አልኩት! እሱም በመንግሥት ስም አሁን ጦርነት ላይ ነው ያለነው ይህንን ለማድረግ ጊዜም የለ አፍምቦንም አንለቅም አለ። እኔም አገራችን ይዘን አንለቅም አገሩ የማን እንደሆነ ለመነጋገር ስምምነት ለማድረግ አንድ በስምምነት እናድርግ ብንል እምቢ ታላችሁ የፈረንሳይን አምባሳደርነትህን ፕሪቭልጅ ሁሉ እንስቻለሁ ይህንንም የምናደርገው በመጨረሻ (በቪቪረኸም) ጊዜ እናንተ የኢትዮጵያን ነፃነት እናውቅም ብላችሁ የጣልያንን ይዞታ አውቃችሁ ነበር። እናንተም በጀርመን (ልፋት)" ኃይል ይሆን እንደሆነ የእኔ ነው " ስለተያዛችሁ የፈረንሳይን ነፃነት አናውቅም። ያቀረ ብትሉን የውል ሀሳብ መንግሥትህ ተቀብሎ ለመፈረም ፈቃደኛ የሆነ ጊዜ ስምምነቱን ስንፈርም አንድ መግለጫ እናወጣለን ይኸውም ኢትዮጵያንና ፈረንሳይ በአፊሲኤል እንደ ፀና አገርና መንግሥት የሚተዋወቁበት እስከዚያ ድረስ ግን እንደ ፕራይቬት ሰው ነው የምንመለከትህ ብዬ ማናቸውንም ፕሮቪልጅ አነሳሁ። ባንዴራ ማድረግ D.C ኦቶሞቢሉ ላይ ማድረግ እንዲከለከል ለፖሊስ ነገርኩ። ይህም የዲፕሎማቲክ ዶሜኒቲ መነሳት ለመንግሥቱ አስታወቀ መልሱን ሲጠባበቅ ቆየ"።

"ትትንሽ ቀን በኋላም ፈረንሳይ መንግሥት ደጉል በሀሳባችን ተስማምቶ ውሉን እንዲፈርም አዘዘው አምባሳደሩም ሙሴ ደ.ብሊስ ይባል ነበር። በዚህ አኳኋን ፕሮተኮሉንም ሁለት (--) የሚተዋወቅበትን አብሮ ተፈረመ። ያጤ ምኒልክን ውል መሠረት በማድረግ የውሉ ዓመት በፈረንሳይ በሱማሊና ለማድረግ በሁለቱም በኩል ኮሚሲዎን ተቋቋመ። በኛ በኩል እነኮሎኔል እርገቱ አቶ አበበ ገ/ጻድቅ ነበሩ። ኮሎኔል ክፍሌ አሁን ደጃዝማች ያን ጊዜ የጸጥታ ኃላፊ ነበር። በሥራው ጊዜ የገጠመን ችግር! በካርታ ሥራ ምንም ፕሬዚዎን-የሴላው በጣም ሽግ የሆነ አገሩን ሳያየው እቤቱ ቁጭ ብሎ ወሰኑ በዚህ በዚህ ሥፍራ እንዲህ ያለው ስም ባለው ተራራ ያልፋል እያለ ነው ያሰመረው። እቦታው ላይ ሲኪድ ፈረንሳይዎች ተብዙ ጊዜያት ጀምረው ሁሉ ምስክሮች ቢቀርቡም ሁሉም ለነሱ ጥቅም በሚሆን አኳኋን (የሉይከሉን) ስም ጭምር ሁሉ ምስክሮች ቢቀርቡም ሁሉም በነሱ የተገዙና አፍምቦ የፈረንሳይ ነው እያሉ የሚመሰክሩ ሆኑ። እኛ

ደግሞ የኛ መሆኑን የሚያስረዳ አንድም (ኤንስቶሊሽን) ቤት ሠፈር የመሰለ ያደረግነው የለም። በዚህ አኳኋን ስሙም ተለውጦ ወደነሱ ስለሚያደርገው ምስክር ሁሉ የነሱ ስለሆነ የምንከራከርበት መንገድ አጣን"።

"በዲፕሎማቲክ ታልሆነ በቀር በውሉ መሠረት የደምቡን ማግኘት የማይቻል መሆኑን ተተረዳሁ በኋላ ፓሪስ ሄድኩ እዚያም ተጠቅላይ ሚኒስትሩ መሊረኒ ማየር /ወዳጅ ነበር) ተገናኝቼ ሁሉንም አስረዳሁት። ፈረንሳይና ኢትዮጵያ ተድሮ ጀምሮ ያላቸው ወዳጅነት በፈረንሳይ ጥቅም በኢትዮጵያ ባቡር የጅቡቲ የኢትዮጵያ ኔቸራል ብር የፈረንሳይ አርኪዎሎጂ ሚሲዎን እንዲሁም የፖስተር ኢንስቲትና የፈረንሳይ ሉሲ መኖር ይህ ሁሉ እያለ ፈረንሳይ በአፍምቦ ምክንያት ከኛ ጋር መጣላት ጥቅም እንዳልሆነ እሱም በነገሩ አስብበታለሁ ብሎ ምላም ጋብዞኝ በሁለተኛው ቀን ተውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጋር ተሙሲ በዶ ጋር እንድነጋገር ለሱም ትዕዛዝ መስጠቱን በቀጠሮውም ተበዶ ተገናኝተን ተነጋገርን። እሱም ወደኛ ተመልሶ ዲሊሚቴሽን እንዲደረግ መስማማታቸውን አስታወቀኝ። በንግግሩም ጊዜ አቶ አበበ ገብረ ጻድቅ የሚያስፈልገውን (ዶክሜ) ይዞ ተኔ ጋር ፓሪስ ይገኝ ነበር። በዚህ አኳኋን በፈረንሳይ ሱማሌና በኢትዮጵያ መካከል ውሉን ተከትሉ አፋምቦን ወደኛ አድርጎ የዲሊሚቴሽኑ ሥራ (በ--ተጀምሮ በ--)አለቀ/ዶኩሚንቱን ማየት/ ያን ጊዜም የፈረንሳይ ጋዜጦች የፈረንሳይ መንግሥት ያደረገውን ክራቲክ አድርገው አገር በማይገባ ለኢትዮጵያ ተሰጠ ጃንሆይና አክሊሉ የፈረንሳይ ጠላት ናቸው...የሚል ካምፓኝ አድርገው ነበር። በፓርላማም ጉዳዩ ተነስቶ ክርክር ተደርጎ ነበር /ይህ ሁሉ ፈረንሳይ አርሺብ ይገኛል።/" ሲሉ ጽፈዋል።

## "ጋምቤላ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ያደረግሁት"

ንጉሠሴዎን 1954-557 በአጤ ምኒልክና በእንግሊዞች መካከል የሱዳንና የኢትዮጵያን ድንበር በተለይ የሚወስነው (በ---)የተፈረመው ውል የሚለው ጋምቤላ በእንግሊዞች እጅ ይቆያል ይኸውም እንግሊዝ እሱዳን እስካለች ድረስ ነው የሚል ነበር። በ1954 ተጃንሆይ ጋር እንግሊዝ የኀበኘን ጊዜ ለሚስተር ኤደን ጉዳዩን አነሳሁበት። ሱዳን በቅርብ ጊዜ ነጻ መሆን አይቀርም። ስለዚህ በውሉ መሰረት አሁኑኑ ጋምቤላን ብታስረክቡን በማለት! እሱም የሱዳን ነጻነት ገና ነው ሁለትና ሶስት ዓመት ቢያንስ ይወስዳል በውሉ መሰረት ሱዳንን እስከምንለቅ መጠበቅ አለባችሁ ብሎ አጥብቆ ተከራከረ። እኔም ሱዳን ነጻ መንግሥት እስክትሆን ጠብቀን በኋላ ተነሱ ወንድሞቻችን ጋር ጋምቤላን አስረክቡን እያልን መጣላት አንፈልግም/እናንተ መቼም ይህ ነው ሥራችሁ ስለዚህ አሁኑኑ አስረክቡን ብዬ አጥብቄ ጠየቅሁ። በመጨረሻም አንድ ፎርሙላ ላይ ስምምነት አድርገን ተለያየን። ይህም/ሱዳን ነጻ ተመውጣቱ ከሶስት ወር በፊት ጋምቤላን ለማስረከብ ሁለት መንግሥታት ተነጋግረው ጋምቤላን እንዲያስረክቡ።"

"ከሶስትና አራት ወር በኋላ አዲስ አበባንና ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ማርሻል ቲቶ ስለመጡ ተሳቸውና ተጃንሆይ ጋር ለጉብኝት ምጽዋ እንገኝ ነበር።



በረዲዎን ስንሰማ ታምስት ቀን በኋላ እንግሊዝ ለሱዳን ነጻነቷን የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ነበር። ሁለትና ሶስት ዓመት የተባለው ሁሉ ውሸት ሆነ። ጋምቢላን ሳይለቅ ለሱዳን አስረክበው ሊሄዱ መሆኑንና ተሱዳንም መንግሥት ጋር ኮንፍሊክት ክርክር እንደሚሆን ግልጸ ነበር። ጉዳዩን ለጃንሆይ አስረድቼ ወዲያውኑ ወደ አዲስ አበባ መጥቼ/አርብ ቀን ነበር አንድ ኖት አሰናድቼ ቅዳሜ የንግሊዝ አምባሳደር ጠርቼ ኖቱን ሰጠሁት። የኖቱም ቃል የሚለው/ በሙሉ መሰረት ጋምቤላን እንግሊዞች የሚይዙት ሱዳን እስካለ ድረስ ነው አሁን እንግሊዞች በድንገት ሱዳንን ስለሚለቁ በውሉና ተሱዳን ጋር በተስማማነው መሰረት ተሰኞ ጀምሮ/ የሁለት ቀን በኋላ/ ኢትዮጵያ ጋምቤላን ይይዛል/የሚል ነበር። እሱም ፕሮቴስ አድርጉ ለመንግሥተ የኖቱን ቃል አስተላልፋለሁ አለ።"

"ለሱዳን የውስጥ አስተዳደር ባለስልጣኖችም አንድ ቴሌግራም በአቶ መለሰ አንዶም በኩል/ያን ጊዜ የእንግሊዝን አፊሰር አሁን ካይሮ አምባሳደር/ አንድ ቴሌግራም ላክሁ ይህም የሚለው ለነጻነታችሁ ጥልቅ መልካም ምኞታችንንና ወደፊትም እንደወንድማማች አብረን እንድንሰራ! ጋምቤላ በኮሎኒአሊስቶች በኃይል ተይዞብን ስለነበር ተሰኞ ጀምሮ አኩፓይ ማድረጋችንን ግን ይህ ወዳጅነታችንን የማይነካና የሱዳንም ቆንሲልና ማናቸውም ቤትና ኤንስቶሌሽን ቢኖር ለጊዜው ለመቆየት መቻሉን የሚገልጽ ነበር። እነሱም በነጻነታቸው ለጊዜው በደስታ የተጥለቀለቁ ስለሆነ ተምስጋና ጋር በምናደርገው መስማማታቸውን የሚገልጽ መልስ ሰጡ።"

"እንደተባለው ሰኞ ባቅራቢያው የሚገኘው የፖሊስ ኃይል ጋምቤላ ገብቶ የኢትዮጵያን ባንዲራ አውለበለበ አድሚኒሴራሲዎኑንም ያዘ ምንም ኤንስደንት አልደረሰ። ተሶስት ወር በኋላ የሱዳን ዲሊጊሽን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሚመራ ጋምቤላ ስላላቸው ኤንስታሌሽን ለመነጋገር አዲስ አበባ መጡ። በንግግራችንም ጊዜ በቁጣ መልክ ለእንግሊዞች የፈቀዳችሁትን ጋምቤላን ለምን ለኛ ለአፍሪካኖች ተንፍጉናላችሁ ጋምቤላን መልሱልን በማለት ከሥረ ነገሬ መግባት ጀመሩ። እኔም እንግሊዞች ኮሎኒያሊስቶች አፍሪካን በሚከፋፈሉበት ጊዜያት በኃይል ፕሬሽን ያደርጉብን ነው አሁን ኮሎኒ ሁሉ ነጻ ይውጣ ሲባል እናንተ ይህን እንዴት ትጠይቃላችሁ ይልቅስ በወንድማማች መንፈስ የምትወስዱትን ኢቃ ዝርዝር ብንነጋገር ይሻላል ስትመጡም በዚህ ብቻ መሆኑን የተለዋወጥነው ኖት ያስረዳል።"

"ተዚያ በቀር ሌላ ጉዳይ ለመነጋገር የተስማማንበት ፕሮሲጀር አይፈቅድም አልኳቸው እነሱም ተቆጥተው ስብሰባውን ጥለው ወጡ/ ያን ጊዜ ተኔ ጋር ብላታ ዳዊት ምክትል ሚኒስትር እንዳልካቸው ዋና ዲሬክተር ነበሩ። በዚሁም እንዳልካቸው ደንግጠ ምን ይሆን ብሎ ጠይቆን ነበር ግድ የለም አሁን እንስማማለን ስለው እኔ መቸም ኤክስፔርያንስ የርስዎን ያህል የለኝም ብሎ አድንቆ ተወጡ በኋላ ለየአምባሳደሮች/ እንግሊዝ.አሜሪካን.እየዞሩ ስሞታቸውን ያቀርቡ ጀመር በኋላም እሱን ለብቻው ጠርቼ በረጅሙ አስረድቸው ተቆጣው ተመለሰ። አስፈላጊውን ስምምነት አደረግን ተዚያ በኋላ የጋምቤላ ጉዳይ በሱዳኖች ተነስቶ አያውቅም"።

## "በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል"

"በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል የሚወሰነውን ወሰን መሠረት በምን አኳኋን እንዲከለል እንዳደረግሁ እውጭ ጉዳይ እንደገባሁ ኢትዮጵያ ተሌሎች አገሮች ጋር ወሰን በኢንተርናሽናል ውል መሠረት በትክክል መወሰን ዋና ጉዳይ አርጌ ነበር ያየሁት። ይሂም በወልወል በደረሰብን ኤክስፔሪያንስ ነው። ተዚያም በኋላ ያፋምበ መጣ ትንሽ መንግሥት እንደመሆናችን መጠን የተከበብነው ያን ጊዜ በነኛው በኮሎኒያሊስቶች ስለሆነ አጥራችንን ደህና አርጎ ማጠር አስፈላጊ ነበር። ብዙ ጊዜ የወሰኑ ውል ታጤ ምኒልክ ጋር የተደረገው/+1897-/በ1 የሆነ ፕረሴዜምን የሌለው ነው። ኢትዮጵያ ተመወረረ በፊት 1935 ታንድ አገር ብቻ ነበር ወሰናችን የተከለለው። ይኸውም ተእንግሊዝ ሶማሌ ጋር ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት ነው ተጎረቤት አገር ጋር በየጊዜው (የፍርንቲኤር) ኢንሲደንት የነበረን/በኬንያ በኩል ተናንተ ጋር ያለ ኢንሲዴንት ፕሮቲስታሲዎን ያደረግንበት ወረቀት ይህን ቤት ይሞላል ብሎኝ ነበር። ይህን ሁሉ ለጃንሆይ ታስረዳሁ በኋላ መጀመሪያ ሉንደን ስሄድ በ1946 አንዱ ጉዳይ የተነጋገርኩበት ይህ ነበር። ተኔ ጋርም ጸሐፊ ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ ነበሩ። ዲማርኬሽን ለማድረግ የንግሊዝ መንግሥት ተስማምቶ ይህንኑ ለመነጋገርና አንድ የዲሊጌሽን ፕሮተኮል ለመፈራረም በቅርብ ጊዜ አንድ ዲሊጌሽን ወደ አዲስ አበባ እንዲሚልክ አስታወቀ"።

"የእንግሊዝ ዲሊገሽን ተመጣ በኋላ ውሉን መሠረት በማድረግ ካርታ ላይ መስመሩን ለማስመተር አንድ ተእነሱና ተእኛ የተዋጣ (ኪሚስስድ)ኮሚሲዎን ተቋቋመ። ሥራቸውንም ጀመሩ። ተእኛ በኩል እነ ኮሎኔል ክፍሌ አቶ አበበ ገብረ ጻድቅ ሌሎችም ነበሩ። ብዙ ጊዜም ሥፍራውን እየሄዱ ይጎበኙ ነበር። በመጨረሻም የተስማሙበትን መስመር ለየመንግሥታቸው አቅርበው ተፈቀደ። ተዚህም በኋላ መሬቱ ላይ ዲማርኬሽን ተጀመረ። ብዙ አመትና ብዙ ገንዘብም ተፈጀ በኋላ ሥራው አለቀ። ተትንሽ ዓመት በኋላ ቀደዱማ የሚባለው የውሃ ጉድጓድ ሕዝቡ ጠቃሚዎችን ነው እንደ አድባርም የምንቆጥረው ነው ብሎ አቤት ስላለ ጉዳዩ እንዲታይ ተደረገ በኮሚሲዎን። የጉድጓዱ አከፋፈል የሚበልጠው ወደኛ እንዲሆን ዘጠኝ ሥፍራ ያለው ጉድጓድ ለነሱ ደግሞ ሁለት ሥፍራ ያለ ጉድጓድ ነበር። ሐሳቡ ውሃ እናወጣለን በማለት የእኛም የነሱም ሕዝብ ወሰን እንዳያልፍና ኤንስዴንት እንዳይነሳ ነው። በዚህ ጉዳይ የሕዝቡ ስሜት ስለባሰበት ቀደዱማን እንዲመልሱ ለእንግሊዞች አስረዳኋቸው። እነሱም የሚበቃ ውሃ ተኛ ይበልጥ አላችሁ ግን እንስብበት ምን ታደርጋላችሁ በሉ ፈንታ የሰጠነውን ያገር ክፍል መልሱና እኛም ቀደዱማን እንመልስ ብለው ጥያቄያቸውን በጉድ ፈዝ ተቀበሉ። በዚሁ አኳኋን ጉዳዩ ተፈጽሞ የዚያን ክፍል እንደገና ወረቀት ላይ ምልክት እንዲደረግ ሆነ"።

"ተዚያም በኋላ ታመታት በኋላ ኬንያ ነጻ ስትወጣ ድንበራቸውን ተከልሉ ስስለቀየ ተሷ ጋር በወዳጅነትና በወንድማማች መንፈስ እስታሁን እንኖራለን። ተፈረንሳይ ሱማሌ ጋር ያለን ወሰን እላይ በተባለ አኳኋን ስለተወሰነ ተእንግሊዝም ሱማሌ ጋር ያለው ተጦርነት በፊት አለቀ። ተኬንያም ጋር በዚህ



አኳኋን ሲያልቅ የሚቀረን ተጣልያን ሱማሌና ተሱዳን ጋር ነው። ተጣልያን ሱማሌ ጋር ያለንን ለመወሰን ገና ሱማሌ በዩናቲድ ኔሽን ሞግዚትነትና በጣልያን አስተዳዳሪነት ባለች ጊዜ ተ1950-1960 ዩናይትድ ኔሽን ሬዞሌሽን *እንደሚያዘውና በሱም መሠረት ለመወሰን ተጣልያኖች ጋር ብዙ ጉባኤ ተደርጎበታል። ብዙም ተደከሟል። ያን ጊዜ የኛን ዲሊጌሽን ለወሰኑ ጉዳይ የሚመራው አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ ነበር። ጣልያኖች የውሉን ትርጉም ኢንተርፕረቲሽን በማይገባ እየለወጡ ጉዳዩን ይጎትቱ ነበር።ያልተስማማንበትን በሬዞሌሽኑ* መሰረት ወደ አርቢትረጅ ለፍርድ ብዙ ታክቲክና ሳቦታጅ እያደረጉ ጉዳዩን ይጎትቱት ነበር።ሁሉንም ለመረዳት (ፕርስሺርባሱንና) የዩናይትድኔሽን ዶክሜንት ማየት ያስፈልጋል። ለዚህ ሁሉ አቤቱታችንን ለሰላም ማሕበር ማቅረብ አላቋረጥነም። ጉዳዩም ሳያልቅ ሱማሌ ነጻ ወጣች 1960 ጣልያኖች ጉዳዩን የሚጎትቱበትን አንድ ምክንያት ሱማሌዎችንም በመፍራት ነበር።"

## በጣልያን ሶማሌና በሱዳን በኩል ያልዘጉት ፋይል!

"ሱማሌ ነጻ ተወጣች በኋላ ወሰኑን ለመክለል በየጊዜው ፕሮፖዛል አቅርብንላቸው ነበር። የነሱም መልስ ኡጋዴን የኛ ስለሆነ እንዋሰንም ነው። በሱዳን በኩል ያለውን ብዙ ጊዜ ተተነጋገርን በመሰረተ ስምምነት ላይ ደርሰናል። ዶክሚንቱን ማየት" ሲሉ ጽፈዋል። ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉን ተከተው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት አቶ ከተማ ይፍሩ ሳይሆኑ አይቀርም። አቶ ከተማ ይፍሩ ደንበርን በተመለከተ የፈጸሙት ተግባር እንዳለ እርሳቸው ጽፈው የተዉት ሰነድ አላገኘሁም። ሌላው ብዙ ጊዜ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቆይተዋል የሚባሉት ክቡር አቶ ምናሴ ኃይሌ ናቸው። አሜሪካ የሚኖሩ ሲሆን የሚያውቁትን እንደ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ እርሳቸው ቢጽፉ ታሪክ ቢናገሩ መልካም ነበር። ነገር ግን እንደሰማሁት ከሆነ ፈቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም ተብሎ ነው። ምናልባት እርሳቸው በሕይዎት እያሉ የሚያውቁትን ቢጽፉ ሳይሻል አይቀርም። ምክንያቱም ቀስ እያለ በመውጣት ላይ ያለው "የአጤ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች የጎንደርን መሬት ለሱዳን ሰጥተው ነበር" የሚለው ታሪክ እየወጣ ብልጭ ማለት ስለጀመረ የሚያውቁትን ቢጽፉልን መልካም ይሆናል። ከዚህ በመቀጠል በጣልያን ሶማሌ በኩል በእንግሊዞች የተተበተበውን፤ደግሞም የሶማሌ ኢትዮጵያውያን ማህበር ከኢትዮጵያ ጋር በፌሬዴሽን አብረን እንሁን ብሎ ያቀረበውን ጥያቄ ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ስላልተቀበሉ ሶማሌዎች ሲበሳጩ እንግሊዞች አንድ መርዘኛ ዘር ዘሩ።

ዶክተር ባጽሰ ጌ ድሌቦ <u>የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም</u> 1900-1966 መጽሐፋቸው ገጽ 159" ከዚህ በላይ የተነገሩት ማህበሮች የዋናውና የምክትል መሥሪያ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች ሥራ አስኪያጆች በግንቦት 27 ቀን 1938 የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርነሰት ቤቭን በአገሩ ፓርላሜንት ባደረገው ንግግር ከኢትዮጵያ የኦጋዴን ግዛት ጨምሮ በአፍሪካ ቀንድ በተለያዩ አካባቢዎች የተከፈሉ የሶማሌ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚገኙባቸው ቀበሌዎች በእንግሊዝ አስተባባሪነት በአንድነት መደራጀት አለባቸው በማለት

እስከዛሬ ድረስ በአፍሪካ ቀንድ መንግሥታት መካከል የፖለቲካና የአካባቢ ችግር ሲያስከትል ያለውን ጠንቀኛ አሳብ መሰንዘሩ ይታወሳል" ሲሉ ጽፈዋል። በሱማሌ በኩል ኢትዮጵያን እንደጠላት ማለየት ስለተጀመረ ነው ከላይ ክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ "ሱማሌ ነጻ ተወጣች በኋላ ወሰኑን ለመከለል በየጊዜው ፕሮፖዛል አቅርብንላቸው ነበር። የነሱም መልስ ኦጋዴን የኛ ስለሆነ አንዋስንም ነው" ያሉት ቅኝ ፈኞዎች የጋቷቸውን በመያዝ ነው።

ከዚህ ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 157-159 "የኢትዮጵያ የአገር ውስጥና የውጭ ጉዳዮች እንደዚህ ሆነው ሳሉ በእንግሊዝ ጦር ባለሥጣኖች በሚተዳደረው ሱማሊያ በሚያዝያ 27 ቀን 1935 የአገሩ ዜጎች የሶማሌ ወጣቶች ክበብ የሚል ማህበር አቋቁመው ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ለመሆን እንፈልጋለን በማለት ለእንግሊዙ ዋና አስተዳዳሪ ዊክሐም ጥያቄ አቀረቡ። አጤ ኃይለ ሥላሰን ንጉሣችን ናቸው ብለው ተናገሩ። በተጨማሪም በዘመኑ ለኢትዮጵያና ለሶማሊያ አንድነት የሚታገል በሶማሌ ተወላጅ ኡማር ኢብራሂም መሪነት የኢትዮጵያና የሶማሌ አንድነት ማህበር ተቋቁሞ አገርና ዓለም አቀፍ ትግል ያካሄድ እንደነበር አይዘነጋም በዚህ ወቅት የኢትዮጵያና የሶማሌ አንድነትን በሚመለከት የሱማሌዎች ጩኸት በሚል ርዕስ የኢትዮጵያና የሶማሌ አንድነት ማህበር በቀድሞ ኢጣሊያ ኮሎኔዎች ሊቢያ ኤርትራና የኢጣሊያ ሶማሊያ ጉዳይ ላይ በመስከረም 1939 በፓሪስ ከተማ ለተሰበሰበው የተባበሩት መንግሥታት ማህበር ያቀረበው የአቤቱታ ጥያቄ እንደሚከተለው ይነበባል በማህበሩ ቃል"

"እኛ የኢጣሊያ ሶማሊያ ይባል የነበረው ሱማሌ ተወላጆች ስለሰላምና ስለዓለም ሕዝቦች ነጻነት በፓሪስ ከተማ ጉባኤ ላላችሁ ባለቃልኪዳን መንግሥታት ከእናት አገራችን ጋራ አንድ እንድንሆን ቁርጥ አሳባችን መሆኑን እየገለጽን ያገራችን ዕድል እስከ አንድ ዓመት ድረስ እንዲቆይ የቀረበውን አሳብ በፍጹም የማንቀበለው መሆናችንን በማክበር እናመለከታለን። በዘር በልማድ በባህል በታሪክ በኃዘን በደስታ ኢትዮጵያውያን ነን። እናት እያለችን ሞግዚት ልንቀበል አንችልም። ጉባኤው ሳይመለስ የኢጣሊያ ይባል የነበረው ሱማሌ ከእናቱ ከኢትዮጵያ ጋር አንድነትን እንዲያገኝ እንጠይቃለን። ፊርማ የኢትዮጵያና የሱማሌ አንድነት ማህበር ፕሬዚደንት ኡማር ኢብራሂም"።

"የኢትዮጵያና የኤርትራ አንድነት ማህበርና የኢትዮጵያና የሱማሌ አንድነት ማህበር በሕብረት ከአዲስ አበባ ለፓሪሱ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ያቀረቡት የአቤቱታ ቃል ደግሞ እንደሚከተለው ይነበባል። በማህበራቱ የሕብረት ቃል። በኢትዮጵያ የኤርትራ አንድነት ማህበርና የኢትዮጵያና የሶማሌ አንድነት ማህበር ፓሪስ ላይ ለዕርቅ ወደ ተሰበሰቡት ለሃያ አንድ መንግሥታት እንደራሴዎች የተላከ! አቤቱታ! ክቡር ሆይ! ይህን የፈረምነው የኢትዮጵያና የኤርትራ አንድነት ማህበር እና የኢትዮጵያና የሱማሌ አንድነት ማህበር አባሎች ለኤርትራና ለሱማሌ ሕዝብ ሥቃይ ፍጻሜ እንዲደረግለት ለከፍተኛው ዕውቀትዎና ለትክክለኝነት መንፈስዎ ለሂሊናዎዎ ከዚህ የሚከተለውን አቤቱታ በማክበር ከእግርጌዎ አቅርበናል። በምሥራቅ



አፍሪቃ ጦርነቱ ከተፈጸመ አምስት ዓመት ሆኖታል። ነገር ግን በታሪክ በኸዖግራፊ በትውልድ በጥሪት በአስተዳደሪ በመንፈስ የኢትዮጵያ የሆኑት በእንግሊዝ የጦር ኃይል አይሮፕላኖች በየቦታው በተበተኑት ጹሑፎች ነጻነት ከእናት አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር አንድ እንዲሆኑ ተስፋ ሰጥተዋቸው የነበሩት ኤርትራና ሱማሌ ጦርነቱ ስላልተፈጸመ በእንግሊዝ አስተዳዳሪነት ውስጥ የቀሩ ሁነዋል። የእነዚሁ አውራጃዎች ሕዝብ ይህንኑ አስተውለው የባለቃል ኪዳኖችን ድል መንሳት በፍጹም ልባቸው በመመኘትና በጸሎት በጾጥታ ጠበቁ። አገራችን ባለቃ ልኪዳን አባል ሆኖ ባለቃል ኪዳኖችም በ1945 (1937) ድል አደረጉ። ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል መፍቀዳቸውን ከመለመን አንድ ጊዜ እንኳን አቋርጠው ስለማያውቁት ስለኤርትራና ስለ ሱማሌ ሕዝቦችም የዕድላቸው ሁኔታና ገና በባለቃልኪዳኖች መወሰን ያለበት ጉዳይ ነው ተባለ"።

"ክቡር ሆይ! ኤርትራና ሱማሌ ሕዝብም መሬቱም በማናቸውም አስተያየት ኢትዮጵያዊ መሆንና ሕዝቡ አንድነት ሁኖ በፍጥነት ከኢትዮጵያ ጋር የመዋሐድ ምኞቱን ሲገልጽ መኖሩን መሳልሰን እናስታውቃለን። እንዲህ ከሆነም ሕዝቡ ጠባብ በሆነ ወታደራዊ ደንብ አስተዳደር ሁልጊዜም በመጠራጠር ሌላ ረጅም ዘመን መኖር አይችልም። ከእናት አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር መዋሐድ በፍጥነት በመወሰን ለሥቃያቸው ፍጹም እንዲደረግ ከፍ ወዳለው ዕውቀትዎ አቤቱታችንን እናቀርባለን። ሕዝቡ ከሥቃይ ነጻ መሆን የሚገባው ጉዳይ በፍጥነት መወሰን እንደሚገባው ለማስረዳትም በቅርቡ ጊዜ አሥመራ ላይ የደረሰውን መዓት የሚነገር ጹሑፍ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከንልዎታል፤ ፊርማ" ይሉና" ከዚህ በኋላ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር አራቱ ኃያላን የአሜሪካ የሶቪዬት፣የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በመስከረም በፓሪስ ጉባኤ ተሰብስበው የቀድሞ የኢጣሊያ ኮሎኔዎች ጉዳይ ከየካቲት 1939 ጀምሮ በአንድ ዓመት በአራቱ ኃያላን መንግሥታት የጋራ ስምምነት ባያልቅ በመስከረም 1940 ለመንግሥቱ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ለማቅረብ እንደተስማሙ ይታወሳል። የኢትዮጵያና የኤርትራ የኢትዮጵያና የሱማሌ አንድነት ማህበራት በሕብረት ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የአቤቱታ ድምጽ ለመንግሥታቱ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ በመስከረም 1939 አሰሙ"።

"እስከ 1940 ድረስ ሁሉ የሶማሌ ተወላጆች ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን አንድ ለመሆን ጥረት ያደረጉ እንደነበር ታውቋል። በዚህ አኳያ በመጋቢት 1933 የሶማሌ ወጣቶች ክበብ በአብዱልቃድር ሰኸውዲን መሪነት ራሱን የሶማሌ ወጣቶች ሊግ በማለት በአዲስ ስያሜ አደራጀ። በሀጂ ኢብራሂም ቃል የሶማሊያ ወጣቶች ሊግ መሥራች አብዱልቃድር ሰኸውዲን ለኢትዮጵያ ስለሶማሌ የወደፊት ፌደሬሽን ጉዳይ ከለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ጋር ውይይ ለማድረግ የሊጉን የመልእክተኞች ቡድን አስከትሎ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የሊጉን የፌዴሬሽን አሳብ ባለመቀበላቸው የሊጉ ቡድን ከአዲስ አበባ ከተመለሰ በኋላ በሊጉ በቢሮው ሰቅሉት የነበረውን የአጤ ኃይለ ሥላሴ ፎቶግራፍ አውጥቶ ጣለ"ብለዋል።

## ምዕራፍ 2

## ባለሥልጣኖች በጎንደር መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ማቀድ!

አዛውንቶች ጨዋታው ሞቅ ሲል አንዱ ልክፍክፍ አድርጎ ሲተወው "አያ ንገረን እንጂ የሚያስተምር ከሆነ እንማርበት የሚያስቅ ከሆነ እንሳቅበት ÷ ውሃን ከምንጩ ነው" ይላሉ። ዋናው የዚህ መጽሐፍ መነሻ መሬት ስለሆነ የአጤ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች ለሱዳን መንግሥት የጎንደርን መሬት ለመስጠት ቃል ገቡ የተባለው ሐሜት ሳይሆን እውነት ሳይሆን አልቀረም። ታዲያ "ውሃን ከምንጩ" እንዳሉት መንስኤውን ፈልጌ ለማግኘት ብዙ ጥረት አድርጌአለሁ።

የሰማኋቸውን ሐሜቶች ለዚህ ምዕራፍ ማዳበሪያ እንዲሆኑ አድርጌያለሁ። ሐሜቱን ለማረጋገጥ ብዙ ሰዎች ጥያቄ አቅርቤ ነበር። ነገር ግን 12 ሰዎች ብቻ ሳስቀር ሌሎችን አልጠቀስኩም።ከ12 አንዱ ስማቸው እንዲነገር አይፈልጉም። በእርግጥ ከሌሎች የበለጠ ታሪክ ያለው ከኒህ ግለሰብ መሆኑን ተረድቻለሁ። ከነዚህ ሰዎች አነጋገር የተረዳሁት ነገር ቢኖር 3 ዓይነት ምክንያት መኖሩን ነው። በዚህ በ3 አይነት ምክንያት መሬት ለሱዳን ሊሰጥ የታቀደ መሆኑን ነው። እነዚህ 3 አይነቶች ምክንያቶች ከተለያዩ ክፍለ ሀገር ተወላጆች የተገኘ ነው።

አንባቢያን እነዚህን 3 ምክንያቶች ለያንዳንዳቸው ኒውስ አርዕስት በመስጠትና ዋቢ መጽሐፍት በመጥቀስ ከዚህ በታች እጽፋለሁ።

1ኛ "አጤ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ ከሆኑ ጀምሮ ፀረ ጎንደር አቋም ነበራቸው ስለዚህ ጎንደር መሬቱ ለሱዳን ቢሰጥ እርሳቸው አይገዳቸውም" ይላሉ።

2ኛ "ባለስልጣኖች በደቡብ ኢትዮጵያ ቀላድ እንደጣሉበት ሁሉ በጎንደር በተለይ ቆላው ላይ ቀላድ ሊጥሉበት ወሰኑ። ነገር ግን ጎንደሮች ከአጤ ኃይለ ሥላሴ÷ቀርበው ውሳኔው እንዲነሳላቸው ስላስፈቀዱ ባለሥልጣኖች ተናደዱ። ስለዚህ የአገራቱን ካርታ ለሱዳን በ250 ሺህ ብር ሸጡ "ይላሉ።

3ኛው "የአጤው ባለሥልጣኖች ከሱዳን መንግሥት ጋር ተነጋገሩ። ያም ጀብሃን ሆነ ሌሎች ኢትዮጵያውያን የትጥቅ ትግል እንዳይሞክሩ ለማድረግም ጭምር ነው" ይላሉ።



## ምክንያት አንድ

ዳኛው ወልደ ሥላሴ <u>ውጣ ውረድ የበዛበት ሕይወት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 25" በ1965 ዓም በጎንደር የታወቁ ባሕታዊ በየቦታው ሕዝብ በተሰበሰበበት ሥፍራ እየተገኙ ንጉሠ ነገሥቱን ሸዋ ሊገድላቸው ስለሆነ ወደ ጎንደር ቢመጡ እርሳቸውም ተርፈው ተለምነው ወደ ዙፋናቸው ይመለሳሉ ይህም ከሆነ በኢትዮጵያ ላይ የሚደርሰው እልቂት ይቀራል። እያሉ ሲሰብኩና ሲያስተምሩ ታሪኩን ክ/ታምራት ይገዙ ሰምተው ለንጉሠ ነገሥቱ አድርሰው ሰውየውም የታወቁ ባሕታዊ መሆናቸውን ጭምር ገልጸው ደጋግመው ቢያሳስቡም ንጉሠ ነገሥቱ የጎንደርን ሕዝብ በድየዋለሁ አሁንም ደግሞ መልሼ ወደዚያ አልሄድም ሲሉ ጥያቄውን ሳይቀበሉት መቅረታቸውን" ሲሉ ጽፈዋል። የጎንደር አባቶች አጤ ኃይለ ሥላሴ የጎንደርን ሕዝብ በድለውታል ይላሉ። በዚህና በሌላው ምክንያት የጎንደር ሕዝብ ፀረ አጤ ኃይለ ሥላሴ ቅስቀሳ ሲያደርግ የነበረ መሆኑ ዛሬ ድረስ በሕይወት ያሉ ይመሰክራሉ። የጎንደርን ሕዝብ አጤ ኃይለ ሥላሴ የበደሉት መሆናቸውን አስመልክቶ ከላይ ክቡር አቶ ዳኛው ወልደ ሥላሴ እንደገለጹት አጤውም አልካዱም።

የእርሳቸው አስተዳደር በጎንደር ሕዝብ ላይ ከ1933-1966 ዓም የልጅ እንዳልካቸው ካቤኔ ሲመሰርቱ ጀኔራል ነጋ ተገኝን መሾማቸው ካልሆነ በቀር 9 የክፍለ ሀገሩ ጠቅላይ ገዦች ተሹመው የሚመጡት ከአዲስ አበባ ሲሆን የጎንደር ሕዝብ በጉቦ ተዘርፎአል። ይህን ጉዳይ በግልጽ ቀኛዝማች ምስጋናው ማስንቆአቸውን ሲቃኙ ክብር ተመስገን የኛ ጌታ ብለው አምላክን ካመሰገኑ በኋላ ስለጎንደር ሕዝብ በጉቦ መሰቃየት ሳይገልጹ ወደ ሌላ ጨዋታ አይገቡም ነበር። ቀኛዝማች ምስጋናው፤
የጠገበው ሲሄድ የራበው ሲመጣ
ለጎንደር የሚያስብ እንዴት ሰው ይታጣ
ሁሉ በሽተኛ ሁሉ ራሴን ባይ
መልካም ሰው ለጎንደር ሳይሾም ነው ወይ?
ሲሉ የክፍለ ሀገሩን ችግር ቁልጭ አድርገው ይናገሩ ነበር። በዚህና በሌላውም ጉዳይ የጎንደር ሕዝብ በተለያየ ግዜ መሸፈቱ ይታወቃል። በአጤው አስተዳደር ላይ ሲሸፍቱ ሻሸን ጢስ ወጋው እንደሚባለው ሕዝቡን አብረው ይገርፉትም ነበር። በተለያየ ጊዜ የሸፈቱት የጎንደር ተወላጆች የአጤ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር በድሎናል በማለት ነው።

<u>የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመናት ትግልና የዘመናዊ ሠራዊት አመሠራረት</u> 1855-1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 58 "ሰሜን ጎንደር ሕዝብ አስተዳደሩን በመቃወም የኀበዝ አለቃ ፈታውራሪ አጥናፉ መሸሻን መርጦ ከፍተኛ የተቃውሞ ውጊያ አድርጎአል" ሲሉ ጽፈዋል። እኔ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ የተማሪው ማሕበር ወቅት በተለያዩ ክፍለ ሀገር የነበሩትን የሕዝብና የመንግሥት ችግሮች ዘርዝሮ ሲጽፍና የትግል መፈክር አድርጎ ሲነሳ

በጎንደር በኩል የደረሰውን ሳይጽፈው የቀረው ለምን ይሆን? ከታች የአቶ ነጋ ነወጠን በመንግሥት ተቃውሞ አድርገው በጹሑፍ አስረድተው በርሃ ገብተው የመንግሥት ወታደር ዘምቶ ሊይዛቸው ባለመቻሉ አጎታቸው ቢትወደድ አዳነ መኮንን በሽምግልና ማስገባታቸው እየታወቀ ሌላም የሕዝብ እንቅስቃሴ እንደነበር ግልጽ ሳለ ዝም የተባለበት ጉዳይ ሊገባኝ አልቻለም።

ኮሎኔል ዳዊት ገብሩ ከንቲባ ገብሩ ደስታ የኢትዮጵያ ቅርስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 320-321 "በሐምሌ ወር 1940 በበጌምድር ጠቅላይ ግዛት የስሜን አውራጃ ሕዝብ የተጣለበትን ግብር እንደበዛበት ገልጾ እንዲቃለልለት አቤት ቢል ተገዶ እንዲከፍል ስለተወሰነበት መሪዎቹን መርጦ በመንግሥት ላይ ጠፋን አነሳ። በዚህን ጊዜ ሊያስገድዱት ጦር ሠራዊት ይዘው የሄዱትን የአውራጃውን ገዥና የወረዳ አስተዳዳሪዎች ድል አድርጎ ማርኮ በየዋሻው አሠራቸው። ሕዝቡ እንደማይገብር ከታወቀ በኋላ የታሰሩት እንዲፈቱ የተማረኩትም እንዲለቀቁ በሽምግልና ከስምምነት ቢደረስም ጦር ሠራዊት በብዛት ተልኮ ጦርነት ታዘዘበት። በዚህ ጊዜ መኮንን ጋረድ ሲዋጉ ሞቱ። ፊታውራሪ አጥናፉ መሸሻ ግን የተቻላቸውን ያህል ከተዋጉ በኋላ የተወሰኑ ሰዎች ይዘው ጦር ሠራዊቱን ወረው ንብረቱንም ዘረፉት። ከዚህ በኋላ አሥራ ሁለት ዓመት በሽፍትነት አገሩ ውስጥ እየተዘዋወሩ ቆይተው በምህረት ገቡ። በደጅ ጠኝነት ጥቂት ጊዜ አዲስ አበባ አሳልፈው ወዳገራቸው ተመለሱ። ፊታውራሪ አጥናፉ በሸፈቱበት ሰዓት በፊቃድ አዲስ አበባ ቆይቼ ስመለስ ስለፀጥታው ሁኔታ ሲመክሩ የነበሩት ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ፣ጄኔራል መርድ መንገሻና ኮሎኔል ከፍሌ ዳዊት ገብሩ ጎንደሬ ስለሆነ ምሥጢር ተካፋይ ሆኖ ፀጥታው ሊጠበቅ ስለማይችል በምትኩ ሌላ መኮንን ይምጣ የሚል ሀሳብ አቀረቡ። ስለዚህ እኔ ወደ አዲስ አበባ ተጠርቼ ወደ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ስዛወር ኮኔል ይማም ጎሹ በምትኬ ወደዚያ ተላከ ዘመኑም 1941 ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ብ/ጄኔራል መልኬ ጌታሁን የትግል ፍጻሜ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 221 "ክቡር ጄኔራል ደበበ ኃይለ ማርያም የምድር ጦር ዋና አዛዥ ሁነው ከተሾሙበት ቀን ጀምሮ በመሃንዲስ መምሪያ ያለኝ አገልግሎት ጊዜ እንዳለቀ ለመገመት አዳጋች አልሆነብምኝ። የትውልድ አገራቸው ጎንደር የሆኑትን መኮንኖች አይወዱም እየተባለ በሰፊው ሲነገር እሰማ ነበር። በኋላ ግን የምድር ጦር ዋና አዛዥ ሁነው ከተሾሙ በኋላ በራሴ ላይ የደረሰውንና ከዚህ በፊት የሰማሁትን ሳመዛዝነው ትክክለኛነቱን ለማመን ችያለሁ" ይሉና ገጽ 258 "ይህን እንደመንደርደሪያ ጠቀስኩት እንጂ ብዙ የተዛባ አሰራሮች ነበሩ። ለምሳሌ አገራችን በጭንቅ ላይ በምትገኝበት ሰዓት በቅናትና በምቀኝነት ተገፋፍተው ጄኔራል ነጋንና እኔን ከሶስተኛ ክፍለ ጦር ለማንሳት የተደረገውን ርብርብ ሳልጠቅሰው አላልፍም። ደጋግሜ መናገር አይሁንብኝ እንጂ ሶማሌ የሶቪት ህብረትን ከጀርባዋ አድርጋ የአገራችን ወሰንና ክብር ትደፍራለች ተብሎ ከፍተኛ ሥጋት ስለነበር ኤርትራ ውስጥ ከሚገኘው ከ2ኛ ክፍለ ጦር በቀር በሙሉ ወደዚህ ግንባር ተደራቢ እየሆኑ መጥተዋል። የቀሩትም ቢኖሩ ተዘጋጅተው ለርዳታ እንዲጠብቁ ተደርጓል። ስለዚህ የኢትዮጵያ የጦር



ሠራዊት በሙሉ በኛ ትዕዛዝ ስር ነበር ማለት ትቻላል። ይህ በኛ ላይ ጥላቻ ባላቸው ሰዎች ዘንድ ለአገር አደገኛ መስሎ ታያቸው። አገራችን ያላትን ጦር በሙሉ ለሁለት ጎንደሬዎችና ለክብር ዘበኛዎች አስረክበን በአንድ ሌሊት ገስግሰው አዲስ አበባንና እኛንም በቁጥጥራቸው ስር ሊአውሉን ይችላሉ እያሉ መንግሥት ለመገልበጥ እንደተነሳን እያስመሰሉ ያስወሩብን ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ኮሎኔል አስናቀ እንገዳ ሽክም የማይከብደው ሕዝብ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 107 "በጎንደር ዝርፊያ ብዙ ባለሥልጣኖች እጃቸውን ሰድደዋል። የንጉሡ ዋና አድራጊ ፈጣሪ የነበሩና ባለሟል ጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ሳይቀሩ የማይገባ ተግባር ፈጽመዋል። በግብፅ አገር የተማሩ ግብፆችና ሱዳኖች አፈንዲ የሚሏቸው ብላታ ፀሐይ ደስታ የጎንደር ግምጃ ቤት ሹም በነበሩበት ጊዜያት ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ በጎንደር ሆስፒታል ውስጥ የነበረውን ሕሙማን የሚታከምበትን መድኃኒት በ13 መኪናዎች አስጭነው ወደ አዲስ አበባ ሊወስዱ ሲሉ ወልደ ጊዮርጊስ ለሸዋ ሲያስብ እኔ ደግሞ ለጎንደር ማሰብ አለብኝ ብለው መድኃኒቱ እንዳይሔድ በመከልከላቸው ብላታ ፀሐይ ደስታ ከሹመታቸው ተሽረው በአገሪቱ ከፍተኛ የተማረ ሰው እጥረት በነበረበት ወቅት ወደ አዲስ አበባ ተወስደው በደጅ ጥናት እየተንገላቱ ዕድሜያቸው በአሳዛኝ ሁኔታ ተፈጽሟል። ተገኝ ሐበሻ የተባሉ ዳኛ ከአዲስ አበባ ዳኝነት ተሹመው ወደ ጎንደር ተልከው ሕዝቡን በጉቦ ስለ አስቃዩት ቀኛዝማች ምሥጋናው አዱኛ በሰምና ወርቅ ግጥማቸው

"ሰው ሁሉ እሚቀኘው እየቆጠረ ነው
አዘራረፍ ማወቅ እንደ ተገኜ ነው

ብለው ተቀኝተዋል። ከአዲስ አበባው መንግሥት በአስተዳዳሪነትም ይሁን በዳኝነት ተሹሞ ወደ ጎንደር የሄደ ሁሉ አንዱ ከሌላው የማይሻል ዘራፊና ቀማኛ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ስሜ አይነገር ያሉ አዛውንት "አጤ ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ጎንደር ሲባሉ ሳለ ራስ ጉግሳ ወሌን በአውሮፕላን አስደብድበው ገድለዋቸዋል። ጣሊያን ኢትዮጵያን ሲወር ቤተሰቦቻቸውን በመያዝ ከዱ። ከእንግሊዝ ተመልሰው በጎንደር ለመግባት ሲያስቡ የአርማጭሆ አርበኞች "የከዳ ንጉስ መልሶ አይነግሥ" በማለት መልክተኞቻቸውን አላስገባም በማለታቸው አጤው በጎንደር ላይ ቂም ያዙ። ጎንደር የነበረው ከጠላት የተማረከው ንብረት ልቅምቅም አድርገው ወሰዱት። ሊወሰድ የማይችለውን ጣልያን የሰራውን ቤት እንኳን እንዲፈርስ ሆነ። በ1939 ዓም ጎንደር ቢመጡ ተነስቶ የሚሄድ ቢሆን የፋሲል ግንብ አዲስ አበባ በወሰድነው ብለው በመናገራቸው በጎንደር ላይ የነበራቸውን ጥላቻ ያመለክታል። አንዳንድ ሰዎች አጤው ጎንደርን ይወዳሉ ስለዚህም በቤተ መንግሥቱ ብላታ አድማሱ በቤተ ክኑቱ ሊቀ ሥልጣን አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህን በአየር ኃይል ጄኔራል አሰፋ አየነውን በወታደሩ ጄኔራል ነጋ ተገኝን እንዲቀርቡ አድርገዋል ይላሉ። እነዚህ ሰዎች ወደ ቤተ መንግሥቱ የቀረቡት ተወደው ሳይሆን ሕዝቡን ዝም ለማሰኘት ይቻላል ተብሎ በመታሰቡ ነው። ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም እንደሆኑ ሙሉ በሙሉ ጎንደሬም

አይደሉም ትግሬና የሸዋ ሰው ናቸው:: ሌሎች በጎንደር ላይ የሚደረገውን ሴራ የሚቃወሙ ሁሉ በዓይን ቁራኛ ሲጠበቁ መቆየታቸው አይዘነጋም:: የአጤው ባለሥልጣኖች በጎንደር ላይ ከነበራቸው ጥላቻ ብዛት የተነሳ የጎንደርን መሬት ለሱዳን ሊሰጡ የተስማሙት በገንዘብ የሸጡ በሕይወት አሉ:: እግዚአብሔርን ካልፈሩ ሊመሰክሩ ይችላሉ:: ይህ የመሬቱ መሸጥ ምክንያት ነው ሕዝቡ እንዲሸፍት ያደረገው" ሲሉ ነግረውኛል::

ስማቸው እንዳይነገር የፈለጉት አባት "አጤ ኃይለ ሥላሴ ገና ንጉሥ ሳሉ ጀምሮ ጎንደሮች ባንድ እንዳይቆሙ ለማድረግ ክፍፍሉን በንቀት ጀመሩት:: በጌምድሬውን "ፋርጣ" ይሉታል:: ፋርጣ ማለት የደብረ ታቦር የአውራጃው ከተማ ወረዳ ሲሆን ራስ ጉግሣ ወሌ ቤተ መንግሥታቸው የነበረው ደብረ ታቦር ሲሆን የሰሜን ጎንደር ሕዝብ አብሮ እንዳይቆም በጌምድሬውን እንዲንቀው አደረጉ:: ከዚያም ደጃዝማች አያሌው ብሩ እኅታቸውን ራስ ጉግሣ ወሌን አብረው ወግተው ገደሉ:: ለደጃዝማች አያሌው ብሩ የተገባላቸው ቃል ኪዳን ሰሜን ጎንደርንና በጌምድር ጎንደርን ራስ ተብለው ያስተዳድራሉ ተብሎ ነበር:: ራስ ጉግሣ ከሞቱ በኋላ ግን የተሰጣቸው ነገር የለም:: ለዚህም ነው የጎንደር ተጨዋቾች ማፌዝያ ቀኛዝማች ምስጋናው እያለው ሞኙ ሰው አማኙ ሰው አማኙ ካለ በኋላ ዘፈኑን ሲያስመቱ ሰው አማኝ ሸዋ አማኝ ሸዋ አማኝ ይሉ ነበር:: የጎንደር ሕዝብ አንድ ሁኖ እንዳይቆም ቀደም ጀምሮ ሰሜነኛው በጌምድሬውን እንዲንቀው ለማድረግ ብዙ ደክመዋል:: ብዙ ጥረዋል ነገር ግን ሁሉም ጎንደሬው አዲስ አበባ ሲገባ ፋርጤ ይባላል:: በዚያን ወቅት የዘሩት ዘር ዛሬ ድረስ ሊደርቅ አልቻለም:: በጎንደሬዎች በኩል መተማመን እንዲጠፋ እያደረጉ ናቸው:: ይህን የአጤ ኃይለ ሥላሴን ሴራ ደርግ ደምስሶ አንድ ጎንደር እንጂ ሁለት ጎንደር አይባልም ብሎ አጥፍቶት ነበር:: ዛሬ ደግሞ ወያኔ የአጤውን ሴራ አንስቶ በማራገብ ላይ ነው:: አንዳንድ የዋሕ ሴራው ያልገባቸው በበጌምድሬው ላይ ጥላቻ ያሳያሉ ይህ ተንኮል እንጂ እንኳን የጎንደር ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ነው:: አስተውሉ ይህ ሴራ የተጀመረው ቀደም ሲል መሆኑን ተረድታችሁ ጎንደሬዎች እንጂ ሰሜንና ደቡብ የሚባለውን ሰያሜ ማጥፋት ይኖርባችኋል" ሲሉ ነግረውኛል::

ጎንደር ከ7 ጎሳ በላይ ሕዝብ የያዘ ሲሆን ሕዝቡም የተዋሕደ ነው:: እንኳን የጎንደር ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሕዝብ እንጂ አንዳንድ ፖለቲከኞች እንደሚሉት የተለያየ ሕዝብ አይደለም:: በአስተዳደር ጉድለት ነበር ይህ ሊካድ አይችልም ትክክል ነው:: ዛሬ ሰልጥነናል የሚለው ትውልድ በተለይም ከዚህ በውጩ ዓለም ያለው ሕዝብ ይህን ከፋፋይ ሴራ ማምከን ይጠበቅበታል:: እኔ የሰማሁትን መጻፌ ለምክር ያመቻል በሚል እንጂ ቂምን ለማራገብ አይደለም:: በአንድ አካባቢ ስህተት ተፈጽሟል ብሎ መጻፍ ቂመኛ አልያም ከፋፋይ ሊያሰኝ አይችልም:: የአሜሪካ ሕዝብ በጥቁር ላይ በደል ያደረሰ መሆኑን ነጮች ታሪክ በመሆኑ እየነገሩ ነው:: ይህን የሚሉት ሌላ ስህተት እንዳይፈጸም ለማድረግ ያለፈን ታሪክ ጠብ ርግፍ አድርገህ ትተህ ለሚመጣው እጅና ጓንት ሁነን አገራችን እናሳድግ ለማለት ነው::



ለዚህም ነው የአሜሪካ ሕዝብ "ምን ይሰራልኛል እንጂ ምንድነው ቀለሙ" የሚለውን ትቶ እንሆ አቶ ራክ ሁሴን ኦባማን ለርዕሠ ብሔርነት መረጠ:: ከዚህ በላይ የጠቀስኩት የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በጎንደር ላይ የፈጸሙትን የዛሬው መንግሥት እየፈጸመው በመሆኑ ያነን ለአንባቢ ዘርዝሮ ለማቅረብ ነው:: ይህ በዚህ እንዳለ የአጤው መንግሥት በጎንደር ላይ ቀሳድ ሊጥልበት ወሰነ:: ቀሳዱን የማይቀበሉ መሆናቸውንና የአጤውን አስተዳደር በመንቀፍ በአቶ ነጋ ነወጠ፤አሞጽ በስውር ተካፋይ የነበሩ የሚያውቁትን የነገሩኝን ለአንባቢ አቀርባለሁ::

## ምክንያት ሁለት

ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ "በኢትዮጵያ የክፍለ ሀገረ ገዥዎች ስብሰባ ላይ ያልተያዘ መሬት ያሳችሁ ተብሎ ጠይቀው ነበር:: በዚህ ወቅት የጎንደር ክፍለ ሀገር ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ በጎንደር ትርፍ መሬት የለም ብለው መለሱ:: በኋላ ግን እርሳቸው ተነስተው ኮሎኔል ታምራት ይገዙ ጎንደር ጠቅላይ ገዥ ሁነው ሲመጡ አሁንም ይህ ጥያቄ ሲመጣ እርሳቸው ያልተያዘ መሬት እንዳለ ገለጹ:: እርሳቸው ብቻ ሳይሆኑ በጎንደር ዙሪያ አውራጃ ገዥ የነበረው ግለሰብ በራሱ አውራጃ ብቻ ያለውን ሳይሆን በጭልጋ አውራጃ በጎንደር ዙሪያ አውራጃና በወገራ አውራጃ ያለውን የበርሃውን መሬት ሳይቀር ግልጥልጥ አድርጎ ማስታወሺያ ወደ አዲስ አበባ ላከ" ሲሉ ገልጸውልኛል:: የኒህ ግለሰብ አባባል የሚያጠናክር ምስክር አገኘሁ::

በአቶ ወልደ ገብርኤል አሰጌና አቶ ሊቁ እጅጉ ተመሳሳይ ታሪክ ነግረውኛል:: "የአገር ግዛት ሚኒስትር ያልተያዘ መሬት መኖሩን አስታውቁን የሚል ደብዳቤ ጎንደር ላከ:: ቀደም ሲል ጎንደር ዙሪያ አውራጃ ገዥ የነበሩት የአጤ ቴዎድሮስ የልጅ ልጅ ደጃዝማች ካሣ መሸሻ ቴዎድሮስ ትርፍ መሬት የለም እያሉ ይጽፉ ነበር:: ኋላ እርሳቸው ጡረታ እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ ተስፋዬ አስናቀ የጎንደር ዙሪያ አውራጃ ገዥ ሁነው ሲሾሙ ከሁመራ እስከ መተማ ያልተያዘ መሬት መኖሩን ዘርዝረው ለአገር ግዛት ምኒስትር ጻፉ:: ከዚህ በኋላ የአዲስ አበባ ባለሥልጣን መሬቱን ቀላድ ሊጥሉበት ወሰኑ:: የባላባት ስለሆነ ቀላድ አትጥሉበትም ብለው ተቃውሞ ማሰማት ጀመሩ:: ይህን ይቃወማሉ የተባሉት ግለሠቦች ከክፍለ ሀገሩ እንዲነሱ ወደ ሌላ ክፍለ ሀገር እንዲዛወሩ ተወሰነ:: ለምሳሌ አቶ ነጋ ነወጠ፤ ወሎ እንዲዛወሩ የተጻፈላቸውን ማዘዣ ሳይቀበሉት ቀርተዋል:: በጎንደር ከዚህ በላይ የተገለጸው ሲሆን የሁመራውን በተመለከተ ደግሞ መላዕከ ሰላም ሲሳይ እየለ ከዚህ በታች የተጻፈውን ተናግረው ነበር:: እኔ ጉግሣ መጽሔት ሳዘጋጅ ላሰ አቶ ዋዲት ከበደ ነበሩ ጥያቄና መልሱን ሰርተው የላኩልኝ:: ጥያቄ የምለው የአቶ ዳዊት ከበደ ሲሆን መልስ የምለው ደግሞ የመላከ ሰላም መሆኑን ማስገንዘብ እወዳለሁ::

መልዓከ ሰላም ሲሳይ አየለ <u>ጉግሣ መጽሔት</u> ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም ገጽ 12" ሆኖም ሁኔታው ጥሩ ስላልነበረ የወልቃይት ባላባቶች እና ሌሎችም አብረው መክሩና የኔ ታናሽ ወንድም አብሮ ነበር አንድነት መክረው የመሬቱን

እርስትነት ቢጠይቁ በወቅቱ የወልቃይትን መሬት ያካፋፍሉ የነበሩት በየቦታው ያሉ የጭቃ ሹሞች መሬቱ በቀላድ የሚመራ እንጂ በባላባት ርስትነት የሚመራ አይደለም አሉ። ጥያቄ በቀላድ የሚመራ ሲሉ ምን ማለት ነው? መልስ "በቀላድ የሚመራ ማለት መሬቱ በመንግሥት የሚተዳደር ማለት ነው። በውኃሳ ጉዳዩ ጎንደር ላይ እየታየ ሳለ ደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ መሬቱ የወልቃይት ርስት መሆኑን አስመስክረው ያንን የምስክር ወረቀት ይዘው ወደ ጎንደር ሳይሄዱ ክረምት ሆነ በነሀሴ ደግሞ ተሁመራ ወደ ጎንደር መገናኛ የለም። በዚህ መሀል ጎንደር ላይ ወልቃይት በመንግስት የሚተዳደር ነው። ተብሎ ውሳኔ ተሰጠ ይሄ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም አዲስ አበባ አቤት ለማለት ሄድን። እኔም ጭምር ያለሁበት ነው። አዲስ አበባ መጣን። ከዚያ የአገር ግዛት ሚኒስትር ምላሹን ስንጠብቅ ሶስት ወር ሞላን። ከሶስት ወር በኋላ በወቅቱ ሚኒስትር ዴኤታ የነበሩት ደጃዝማች ሰለሞን አብርሃ ምንም ሳይፈርሙ አቤቱታችሁን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ክቡር አክሊሉ ሀብተ ወልድ አስተላለፉ። እዚያም ምላሽ ሳይሰጠን ዘገየ። ወደ ቢሾፍቱ ሄድን። ጥያቄ ቢሾፍቱ ማለት ደብረ ዘይት? መልስ አዎ ደብረ ዘይት።"

"ጥያቄ እዚያ ለምንድነው የሄዳችሁት? መልስ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አቤት ለማለት ነዋ! ጃንሆይ ወደ ቢሾፍቱ እንደሚሄዱ ቀደም ስላወቅን መንገድ ላይ ጠብቀን ችግራችንን የወልቃይትን ጉዳይ አስረዳን። ጃንሆይም ቤተ መንግሥት ቅረቡ ብለውን ሄዱ። ሆኖም ግቢ ሳንቀርብ በፊት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀረብነው ደብዳቤ ምላሽ መጣ። ጥያቄ ምን ተብሉ? መልስ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ዴኤታ ሰዩም ሀረጎት ፊርማ ወልቃይት በነበረበት አስተዳደር ይቆይ የሚል ውሳኔ ተሰጠን። እኛም ቤተ መንግሥት ቀርበን አቤቱታችንን ለጃንሆይ ሳናቀርብ ወደ ጎንደር ተመለስን። ጥያቄ ውሳኔው በዚያው ፀና? መልስ ከዚያ ደግሞ በ1959 ዓም ጃንሆይ ወደ አስመራ እንደሚመጡ ሰማንና ወደ አስመራ ሄድን። አስመራ ጃንሆይ ፊት ቀረብን። አሁንም ያንኑ የወልቃይትን ጉዳይ አንስተን ርስታችን ነውና ይመለስልን ብለን ጠየቅን። በዚህን ጊዜ ጃንሆይ ደሂ ጥያቄ በየሄድንበት እየቀረበ ነው ይላሉ። በዚያን ጊዜ የጎንደር ጠቅላይ ገዥ የነበሩት ኮሎኔል ታምራት እዚያው ስለነበሩ ተነስተው ርስታቸውን የወሰደባቸው የለም ይላሉ። ጃንሆይ እንዴት ነው? ብለው ግራና ቀኙን ሲጠይቁ በወቅቱ የኤርትራ አገረ ገዥ የነበሩት ልዑል ራስ አስራተ ካሳ እኔ አገሬ ነው አውቀዋለሁ!በቤጌምድር እና በስሜን በቀላድ/በመንግሥት የሚተዳደር መሬት የለም። የባላባት ርስት ነው። ብለው ለጎንደር ባላባቶች መሰከሩ። በሌላም በኩል ራስ እምሩ እኔም አውቀዋለሁ፤ቆላው ሆነ ደጋው የባላባቱ ርስት ነው አሉ። ጃንሆይም በሄሊኮፍተር ቦታው ድረስ ሄደው አዩ። እኛ ሳናውቀው ይሄ ሁሉ ልማት እየተካሄደ ነው ብለው ተገረሙ።"

"ጥያቄ መሬቱንስ ለመንግሥት ወይስ ለባላባቱ ወሰኑ? መልስ በ1959 በጥር ወር ላይ እንግዲያው እንደጥንቱ በባላባት ይተዳደር አሉ። ከዚያ በኋላ እስተ ደርግ ጊዜ ድረስ የጎንደር ርስት ሆኖ ቆየ። ትናንት እኮ ነው ወያኔ ገብቶ! ጥያቄ ያን ጊዜ ታዲያ የናንተ ክርክር የትግራይ ነው ወይም የጎንደር የሚል አይደለም? መልስ የጎንደር ለመሆኑማ ማንም ክርክር የሚያነሳ የለም።



በአውሬ የተሞላ ጥቅጥቅ ያለ ደን ነበር። ጥንት ጀምሮ የጎንደር ነገሥታትና ባላባቶች እዚህ እየመጡ ነበር ዝሆንና አንበሳ ሌላም አውሬ የሚያድኑት! የእኛ ክርክር የነበረው መንግሥት አያበውም ነው። እነሱ ያኔ በደቡብ ኢትዮጵያ እንዳደረጉት በቀላድ እንዲተዳደር ነበር። ያ ደግሞ በደቡብ ብዙ ችግር ያመጣ ነው። በቀላድ እንዲተዳደር ያደረጉት ቆላና ደጋውን ለማለያየት ነበር።

ጥያቄ እና ለባላባቱ ከተሰጠ በኋላ ምን የተደረገ ለውጥ ነበር? መልስ ለባላባቱ ከተሰጠ በኋላማ ምርቱም አደገ። በመኸር አንድ ኩንታል በሃያ እና በሃያ አምስት ነበር የሚሸጠው። በሰቲት ሁመራ ሼል የሚባል ድርጅት ነበር። በትንሹ ነበር የሚያስረክበው ልዑል ራስ አስራተ ካሳ ለምንድነው ጉልበታችሁን በከንቱ የምታፈሱት አሉን። እንዲያውም ማሕበር አቋቁማችሁ ለልማት ብድር ብትጠይቁ መንግስት ገንዘብ ይፈቅድላችኋል አሉንና ማህበር አቋቋምን። ጥያቄ ማህበራችሁን ማን ብላችሁ ሰየማችሁት? መልስ የሰቲት ሁመራ ሁለገብ የገበሬዎች ማህበር አልነው። ማህበሩን አቋቁመን አዲስ አበባ መጥተን ለልማት ባንኩ አመልክትን ብድር አገኘን። የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስትሮች ሳይቀሩ ወልቃይት ድረስ መጥተው አብረው እየሰሩና እያረሱ ብዙ ምርት ተሰበሰበ። መንግስት ሕዝብ ነጋዴና ገበሬው ተጠቀመ። በአንድ ዓመት ውስጥ አስራ ሁለት ሚሊዮን ብር ተገኘ። ጥያቄ ምንድን ነበር የሚመረተው? መልስ ጥጥና ማሽላ በብዛት ይመረት ነበር። ወዴትስ ነበር የሚላክ የነበረው? መልስ ጥጥና ማሽላ በብዛት ይመረት ነበር" ሲሉ ከዚያ በአስመራ በኩል በመርከብ ወደ አውሮፓ አገሮች ይላክ ነበር" ሲሉ መልሰዋል።

አቶ ነጋ ነወጠ፤ በጎንደር ዙሪያ አውራጃ የአርማጭሆ ባላባት ሲሆኑ በቆላው አገር ቀላድ አይጣልበትም በማለት ተቃውመው በርሃ ገብተዋል። እኚህን ሰው የመንግሥት ወታደር ዘምቶ ሲያገኛቸው የማይችል በመሆኑ አጎታቸው ቢትወደድ አዳነ መኮንን ናቸው ሸምግለው ከአጤ ኃይለ ሥላሴ ጋር ያስታረቋቸው። እኚህ ሰው የአጤውን መንግሥት ድክመት አንድ ባንድ ዘርዝረው በመጻፍ ለሕዝብ ማድረሳቸውን በወቅቱ ተባባሪ ነበራችሁ ተብለው የታሰሩ ዛሬ አሜሪካን የሚገኙ ነግረውኛል።



አቶ ነጋ ነወጠ፤

በተለይ የአጤ ኃይለ ሥላሴን አስተዳደር በመንቀፍ በአቶ ነጋ ነመጠ፣ የተዘጋጀውን ጹሑፍ ረድታችኋል ወይም ተባብራችኋል በማለት ታስረናል:: ለምሳሌ አቶ ገብሩ ካሳ፣ አቶ ፀጋ በላይ፣አቶ ፍስሐ መኮንን፣አቶ ዘዋለ ዘገየ፣አቶ አክሉግ አስካል፣አቶ አዲሱ አበበ፣አቶ ገሬማ ታፈረና አቶ አንዳርጌ እጅጉና ስማቸውን የዘነጋሁት በአቶ ሰሎሞን ከድር የፀጥታ ሚኒስት ትዕዛዝ ከጎንደር ተይዘን አዲስ አበባ ተወስደን ታሰርን:: አንዳንዶቹ አዲስ አበባ የነበሩ ከዚያው ታሰሩ" ብለው ሲነግሩኝ እኔ "የታሰራችሁበት መንስኤው ምንድን ነበር? በማለት ስጠይቃቸው አቶ ወልደ ገብርኤል "እኛ ዋናው መንስኤው የጎንደር መሬት ቀላድ አይጣልበትም በማለት ነው:: የአጤ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር በጎንደር ሕዝብ ላይ የሚያደርገውን አፈና ብቻ ሳይሆን ዋናው ዓላማችን የአጤው አስተዳደር በተለይ ካቤኔአቸው መቀየር አለበት በሚል ዋና ዋና ምክንያት ዘርዝረን በመግለጻችን ነው:: ይህን ታሪካዊ ጹሑፍ በመላ ኢትዮጵያ ሌሊት እንዲበተን ተደርጓል" ሲሉ ነግረውኛል:: አቶ ወልደ ገብርኤል የነገሩኝ አዲስ አበባ ሕደው ከታሰሩት መካከል ዛሬ አሜሪካን ያሉ አቶ ፀጋ በላይ፣አቶ ወልደ ገብርኤል አሰጌ፣አቶ አዲሱ አበበና አቶ አክሉግ አስካል፣ አቶ አንዳርጌ እጅጉ፣ ናቸው:: ለዚህ ምዕራፍ ማዳበሪያ ታሪኩን የነገሩኝም አቶ ሊቁ እጅጉ፣ አቶ ጫቅሌ ቁምንገሬና አቶ ኖራሁን ጫንያለው፣ አምሳ ለቃ (ደጃዝማች) አፈራ አዳነ ተመሳሳይ ታሪክ ነግረውኛል:: አቶ ፀጋ በላይ በወቅቱ ሲያደርጉት የነበረውን እጠር ባለ መልኩ ጽፈው ልከውልኛል:: እርሳቸው የቅስቀሳ ጹሑፍ እየጻፉ ለሕዝብ ያዳርሱ መሆናቸውን መገንዘብ ችያለሁ:: ከዚህ በታች ያለው የአቶ ፀጋ በላይ ጹሑፍ ነው::

## አንብበህ ለሚያነብ ስጠኝ!

"ከኤርትራ እስከ ወለጋ በሱዳን የሚዋሰነው መሬት ለሱዳን ተሰጠ! ኢትዮጵያውያን ሆይ! ዛሬ ኢትዮጵያ ሕዝቧ በርክቶ በቴክኖሎጅ የተፈለሰፈ መሣሪያ በእጅ እያለ መሬታችን እንዴት ለሱዳን ይሰጣል? ኢትዮጵያውያን ወገኔ አባቶቻችን ያሳለፉትን ዘመንና ታሪክ እናስታውስ:: ደጉ ንጉሠ ነገሥት አጤ ዮሐንስ አንገታቸውን የሰጡበትን ደንበሯን ጠብቆ ያቆየንን ሀገር ለባዕድ ስትሸጥ እንቅልፍ እንዴት እንተኛለን? ለሀገር ለዳር ደንበር ዝመት ተነስ! ተነስ ተነስ እንነሳ"

"የሚል እየጻፍኩ በጎንደር ጤና ጥበቃ ኮሌጅ በፋሲለደስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በከተማው በማስበተን በየመጠጥ ቤቱም ቅስቀሳ የሚያደርጉ ሰዎች በማዘጋጀት ከፍ ያለ ንቅናቄ ተጀመረ:: በኮሌጁ ውስጥ መረጃዎች ኖረው በኔ ላይ ከፍተኛ ክትትል ተደረገ፥ ለአለቃየም ለአቶ ጌታሁን አሰጉ በኔ ክትትል ስለሚያደርጉ ትብብር እንዲያደርግ ተገልጾለት ሥራ የሚመለከት መስሎ እኔን ይዞ ወደመካዝኖች መንገድ ጀመርን:: ዘወር ብሎ ተመልክቶ በሱዳን በተሰጠው መሬት ሕዝቡን የሚቀሰቅስ እሱ ነው ተብለሃል ልትያዝ ነው ተጠንቀቅ ሲል ገለጸለኝ:: ተመልሰን ወደቢሮአችን ገባን 16 ገጽ ለመለዮ ለባሹ ለመበተን የተጻፈ ነበር:: ከቢሮየ አውጥቼ ሌላ ቦታ አስቀመጥኩት:: በማግስቱ



እጅጠባብ ሞዳ ሱሪ ኩታ ለብሶ ነጋዴ መስሎ ከደረጃ ላይ ቁጭ ብሎ ስገባ ስወጣ ይመለከተኝ ነበር:: እኔ ወጥቼ ሳልመለስ ከቢሮዬ ገብቶ ይፈትሻል:: ነገር ግን ምንም ሳያገኝ ይቀራል:: ሁለት ቀን በዚህ ዓይነት ሞክሮ ሳያገኝ ቀረ:: በ3ኛው ቀን መኖሪያ ቤቴ በ2 መትረየስ በ6 ልዩ ልዩ ጠበንጃዎች የያዙ ወታደሮች ተከብቤ አድራሮለሁ::

ከንጋቱ 12 ሰዓት ሲሆን በር ተንኳኳ ተነስ ታጠቅ የሚል ድምጽ ሰማሁ:: እኔም ልብሴን ለበስኩና በር ከፈትኩኝ:: ወዲያው እጅ ወደላይ ተባልኩኝ የታዘዝኩትን ፈፀምኩ:: ልጆቼንና ባለቤቴን ወደውጭ አስወጡአቸው:: ወደቤት ክርስቲያን የሚሄዱ ሰዎች ሁለቱን አሳውቃቸውም 3ኛው ግን ፈታውራሪ ነጋሽ አሉላ በድንገት ይዘው እኔም አብረን ወደቤት ገባን:: እየጻፍክ የምትበትነው ወረቀትም ልትበትን የምትጽፈውንም ወረቀት አምጣ አሉኝ:: የፃፍኩትም የበተንኩትም ወረቀት የለም:: የሚል መልስ ሰጠኋቸው:: እነሱም አልጋየን ፍርናሹን ትራሱን ሳይቀር እያገላበጡ ፈተሹ ሳጥን ከፈቱ ወረቀት አገኙ:: አይተው መልሰው ተውት::

አንዲት ማስታወሻያ ደብተር አገላብጠው አዩ እርሷን ወስዶ ወደ 1ኛ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰድኩ ከቀኑ 8 ሰዓት ድረስ እዚያ ቆየሁ:: ከዚያ ወደ ፖሊስ ማሰልጠኛ ት/ቤት ተወሰድኩ:: ብቻየን መሳሪያ የያዙ ፖሊስ ጠባቂ ተደርጎ (ከመኪና ማቆሚያ) ጋራጅ ተቀመጥኩ:: ምግብ የለም ማታ ከትልቅ ማርቸዲስ መኪና ላይ ውጣ ተባልኩ:: ለፍጥኝ እጄን አስረው ቁጭ እንዳልኩ ከስፓንዳው ጋር ጥለው አሰሩኝ መንቀሳቀስ አልቻልም:: ከ3 ቀን በኋላ ምርመራ ተጀመረ:: ሻለቃ ሰሎሞን እባላለሁ ሲለኝ ሳየው ነጋዴ መስሎ መስሪያ ቤት ይመጣ የነበረው መሆኑን አረጋገጥኩ::

እውነቱን ብትነግረኝ ጥሩ ነው አለኝ:: የሰራሁት ካለ እነግርሃለሁ ያልሰራሁትን ደግሞ ሰራሁ ብዬ አልልም አልኩ:: ፖሊስ ተጠራ ውሰደው አለ:: ውጭ ስወጣ መልሰው አለ ስገባ በበሩ ተጠግቶ ቆይቶ በጥፊ መታኝ ወዲያው እጄን በጨርቅ ጠምጥሞ በፊቴ አሰረኝ:: 2ቱን እጄን ፈርቅቆ ጉልበቴን መሃል አስገባ አይኔን በጫሽ ተሸፍኖል የእንጨት ኳስ በአፌ ገብቷል በእግሬ መሀል ብረት አስገብተው ብረቱን ለሁለት ሲያነሱት ራሴ ወደታች እግሬ ወደላይ ሆነ እግሬን ይቀጥቅጠዋል:: እያረፈ ይቀጠቅጠኛል፡ እጁን እየሰደደ ብብቴን ያያል:: ላበት የለውም ሲል ኮሎኔል በለጠ የተባለው በል አውርደው ፈረስ ገስቶ ቢሞት እዳው የኛ ነው አለ::

በግርፋት ላይ እንዳለሁ ንገረን ስንልህ የምትነግረን ካለ በአንገትህ ሺቅብ ምልክት አሳየን የማትነግረን ከሆን በትክሻህ አሳየን ተባልኩ:: ትክሻየን እየነቀንቅሁ ወረድኩ በመሠረቱ በዚህ መሬት ምክንያት የተያዝነው 1ኛ እኔ ፀጋ በላይ 2ኛ አቶ ፍስሃ መኮንን 3ኛ አቶ አበበ አዲሱ 4ኛ አክሉግ አስካል 5ኛ አንድ ቆለኛ ስሙን አላውቀውም:: 6ኛ አበበ የተባለ የከበር ቢትወደድ አዳነ ዘመድ ጎንደር አለ! እዚህ ጎንደር 3 ወር ሙሉ ከታሰርኩ በኋላ አዲስ አበባ ተወሰድኩኝ:: 3ኛ ፖሊስ ጣቢያ ከባድ ወንጀል ምርመራ ውስጥ በግርፋት

ከተሳቃዮን በኋላ በገሊሙ ቢትወደድ አዳኙ መኮንን ከጃንሆይ አቤቱታ አቀርበው በሃስ ደሉት ተባሉ ታዘዘ፤ ጥቅምት 25 ቀን 1965 ዓም በተፈጸመበት ወቅት መሬቱን በይዞታው እንዲቀይ ተፈረደ"::

"አዲስ አበባ ተመስደን በታሰርንበት ወቅት የምንበላውና የምንጠጣው ሁሉም ይልኩልን የነበሩትን ማመስገን እወዳለሁ:: እንዲ፡ እነ፡ በውጭ ዳለም ቤት ነው የመጣላቸው እምብዛ ስርን ምግብ አራት በበግ ወጥ ይመጣልን ነበር:: እንደኛው ቤት ናት ስሜ አይታወቅም ለብርስ 2.2 ዲስኩ ቅልቅ በሬድ ሻይ እስከጎሬታ ድረስ ይልኩልን ነበር:: እነዚህ ሰዎች ለዘገራቸው ለወገናቸው የነሩ በመሆናቸው ውለታቸው ሊረሳ አይገባም:: ከዚህ በላይ በእኔና በሌሎች ኢትዮጵያውያን የደረሰብን ችግር ለአገራችሁ ዳር ድንበር ተቆርቋሪ በመሆናችን ነው:: እኛ ደግሞ መሬታችን ለሱዳን አይሰጥም በማለታችን ነው:: እኛ የታሰርንበትን ታሪክ ያህ ሲሆን የዛሬው ትውልድ ለአገሩ ለዳር ድንበሩ ይቆረቆር ይሆን?

የአሁኑ ትውልድ ግን በግር ወገን ምን እንደሆነ የሚያውቅ አልመሰለኝም:: ከዘላ ከጠሚ መኪና መሬ ከልልበጠ ለአገር ደንታ የለውም:: ቢትወደድ አስፋው ወልደ ሚካኤል "ቁሜ ሲይወብ ኢትዮጵያዊ ነኝ፤ ሙቶም አፅሜ ኢትዮጵያዊ ነኝ" ያሉት አርበኞቻችን ኢትዮጵያዊነታቸውን እንዳይከዱ ለማሳሰብ የተጠቀሙበት ምክር ሲሆን እኔም ለተተኪው ትውልድ የምለው ቀደም ለሱዳን ሊሰጥ ታዝቦ የነበረው መሬት በሕይወቴ እስካለሁ የኢትዮጵያ መሬት ነው:: ሙቶም አፅሜ የኢትዮጵያ መሬት መሆኑን ያምናል:: ስለዚህ የዛሬው ትውልድ የአባቶቹን መሬትር አገሩትን ዳር ድንበሩን ማስጠበቅ እንደለበት እመክራለሁ"ሲሉ ተናግረዋል::



አቶ ቢጋ በላይ



በሁመራ በኩል በአምዳይት ሱዳኖች ገፍተው ሲመጡ ሕዝቡን ልጅ ተድላ ወልደማርያም አስተባብረው ዘመቻ ሲጀምሩ የመንግሥት ወታደር ሲደርስ ሱዳኖች አፈገፈጉ:: ነገር ግን ሕዝቡን ያስተባበሩ ልጅ ተድላ ወልደ ማርያም ናቸው ብለው በአቶ ወልደ ገብርኤል አሰጌ ሲነግሩኝ ሁመራ የነበረ ሰው ስለዚህ የሚያውቅ ካለ ብዬ ስጠይቅ አቶ ከንፈ ተሰፋዬ "ልጅ ነኝ ብቻ ልጅ ተድላ ወልደማርያም ሲያስተባብሩ አስታውሳለሁ" ሲሉ ነግረውኛል:: በወቅቱ አዲስ አበባ ከንጉሡ ጋር ጥሩ ግንኙነት ነበራቸው ተብሎ የሚነገርላቸው የዛሬው ብፁዕ አቡነ መልከ ጸዴቅ "ጠቅለል ባለ መልኩ የጎንደርን መሬት ሕዝቡ ታግሎ አስቀርቷል። እገሌና እገሌ ናቸው ብዬ ስም ጠቅሼ መናገር አልችልም ነገር ግን ሕዝቡ በየደረጃው ታግሎ መሬቱን ማስቀረቱን መመስከር እችላለሁ" ሲሉ ነግረውኛል::

ሱዳኖች በሁመራ በኩል ገፍተው ሲመጡ ሕዝቡ ከመለሳቸው በኋላ እንደገና ወደ አብደራፊ ፊታቸውን በማዞር የኢትዮጵያውያንን ልማት አውድመዋል:: ይህ በአብደራፊና በሁመራ የተደረገውን አጠር ባለ መልኩ አስር አለቃ አባይነህ መሸሻ እንዲህ ይላሉ:: ይህ ከዚህ በታች ያለውን ታሪክ የነገሩኝ አስር አለቃ አባይነህ መሸሻ ናቸው::

የአስር አለቃ አባይነህ መሸሻ፡ "ሱዳኖች በአብደራፊ በኩል የኢትዮጵያውያንን የእርሻ ልማት ሰራተኞች ገድለዋል ... እግር ጉዳት አደረሱ:: በተለይ የቤተ እስራኤላውያን ልማት ዘርፈው ላይ ጉዳት አደረሱ:: በተለይ የቤተ እስራኤላውያን ልማት ዘርፈው በመሄዳቸው አብደራፊ ነዋሪ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ሱዳን ተሻግረው ብድር ለመመለስ ሲሉ ብዙ ልማት አጥፍተዋል:: ሕዝቡን አስተባብረው የዘመቱት አቶ ዋክሹም ነወጠ፤ አቶ ነጋ ነወጠ፤ የአስር አለቃ አጥኜ፤ አቶ ታፈረ ኃይሌ፤ አቶ አበሃይ ጫኒያለው አቶ ዘቀለ ጀንበር፤ የሻለቃ በየነ ልጅ ስሙን የዘነጋሁት የመቶ አለቃ ሌሎችም ስማቸውን የዘነጋሁት ሱዳኖችን ደብድበው መልሰዋል:: ይህ ከሆነ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት ፀጥታ አስከባሪ ወደ ሁመራ ረደም፤ ገላን ዘራፍ፤ አብደራፊ ሽመሊጋራ እስከ መተማ ድረስ ላከ:: ከተላኩት መካከል አንዱ እኔ ነኝ"::

"ሁመራ የገባነው መስከረም 19 ቀን 1959 ዓም ሲሆን ወዲያው እኛ ወደ አብደራፊ ተላክን:: ወዲያው 3ኛው ክፍለ ጦር አዛዥ ጄኔራል ተሾመ እርገቱ ከአስመራ ጎንደር ከዚያም መተማ በሽመሊጋራ አድርገው አብደራፊ መጡና ሱዳንን በሉት ብለው ስላዘዙ መሀል ድረስ ገብተን ወናኖቸው:: ከዚህ ወዲህ በደንበር የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ ሠራዊት ተቀመጠ:: የተወሰኑ ሲቪል የመንግሥት ሰራተኞች ገዳሪፍ ድረስ ሕደው ከተወያዩ በኋላ በአካባቢው ሰላም ሆነ:: በጠቅላላው ከሁመራ እስከ መተማ ለሰፈረው ሰራዊት ሆነ የመንግሥት አስተዳደር አዛዡ የጎንደር ክፍለ ሀገር ጠቅላይ ገዥ ኮሎኔል ታምራት ይገዙ ሲሆኑ ፀጥታውን በሚመለከት ደግሞ የጎንደር ክፍለ ሀገር የፖሊስ ሰራዊት አዛዥ ጄኔራል ስዩም ገሰስ እዝ ስር ነበር"::

"እነዚህን ለም ቦታዎች ዛሬ ወያኔ ለሱዳን ሲሰጥ ጉንብስ ቀና እያለ መሆኑን ሰምተናል:: ወደ ኋላ ልመለስና ሁመራ ስገባ በወቅቱ ከገላን ዘጋፍ በግምት 200

ኪሎ ሜሬት ቅልፈው ሱዳን ድንበር ላይ የሚያለሙ የትግራይ ልጆች ነበሩ:: በተለይ አቶ ተስፋዬ አድዋ፤አቶ ተስፋዩ ሊንሳ፤ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ከሁመራ ባላባቶች ጋር ተስማምተው መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ሱዳንን ገርፈው የሰደዱ ሲሆኑ ልማታቸውን አስከብረው ኑረዋል:: እኔ እስከማውቀው ድረስ የወልቃይት ልጆች ለአገራቸው ያደረጉት ልማትና ድንበር ጥበቃ ሊያስመሰግናቸው ይገባል:: ስማቸውን የማስታውሰው ፊታውራሪ ሰረበ ለማ፤ አቶ ጌታቸው ይርጋ፤ አቶ አበኀ አብተው፤ መላከ ሰላም ሲሳይ አየልኝና ሌሎች ብዙ ጀግኖች ተዋግተው አገራቸውን አስከብረው ነበር::"

"ዛሬ እንሆ እነዚህ ከዚህ በላይ ስማቸውን በጥቂቱ የጠቀስኳቸው ግለሰቦችና የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ ተዋግቶ ያስቀረውን መሬት ለሱዳን ሊሰጡ ነው:: ለሚቀጥለው ትውልድ የምመክረው ነገር ቢኖር ከሁመራ እስከ ጋንቤላ 1600 ኪሎ መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ታስቧል:: እኔ ዛሬ እድሜዬ ከ70 ዓመት በላይ ነኝ:: ስለ ሀገሬ ግን እንገበገባለሁ:: እበሳጫለሁ! ስለዚህ ዛሬ 20 ዓመት የሞላህ ወጣት አትርሳ አለብህ አደራ:: ቀደም የነበሩ አባቶችህ አንድ ሁነው ተባብረው ኢትዮጵያን አቆዩን እኛም በአቅማችን ተዋግተን አቆየን:: ዛሬ ወያኔ ለሱዳን ሲሰጥብህ እንደ ቀድሞዎች አባቶቻችን "እብሚ ለሀገሬ" ብለው ተነስና አንድነትህ አስከብር አደራ እልሃለሁ" ሲሉ ገልጸውልኛል::

እንግቢያን በአጤ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች ቀላድ አትጥሉብትም ሲባሉ ለሱዳን ሸጠዋል ይባላል:: እነዚህ አንዳንድ ግለሰቦች ከግል ጥቅማቸው ጋር አያይዘው በግዴለሽነት መሬቱን ለሱዳን ሊሰጡ በመታሰቡ የአካባቢው ሕዝብ የገጠሩ በሕይወቱ የከተማው በሥነ መንግሥት ተከራክሮ ያስቀረ መሆኑ ታሪክ የነገረን ሲሆን ዛሬም ይህ ተመሳሳይ ድርጊት በመፈጸም ላይ መሆኑን ማስገንዘብ እሻለሁ::

የአስር አለቃ አባይነህ መሸሻ!



## ምክንያት ሶስት

አቶ ዘውገ ፈንታ፤ "የኢትዮጵያን የሚያውቁት የደህንነትና የአገር ግዛት፤ የፖሊስ ጽፈት ቤት እንዲሁም ውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ባለሞያዎች ናቸው:: የተሳለውን ካርታ ርቀቱንና ርዝመቱን የሚያውቁት" በማለት በወቅቱ የገጸ ምድር ካርታ ድርጅት ሠዓሊው አስረድተውኛል:: በእርሳቸው አገላለጽ "አንድ እስክርቢቶ ጭረት ያረፈባት በጣም ብዙ ኪሎ ሜትር ስለሚሆን በትክክል መጠኑን ልነግርህ አልችልም:: ምክንያቱም የሀገር ጉዳይ ነው" ብለውኛል::

ግለሰቦች ይህን ካርታ በ250 ሺህ ብር ለሱዳን ሸጠዋል:: የሚባለውን ወሬ ደጋፊው ብዙ ነው:: የአቶ ዘውገ ፈንታን አባባል ሻለቃ ጌታቸው የሮም ወሬ ሳይሆን ትክክል ነው በማለት ከመጽሐፋቸው ውስጥ ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል መቶ አለቃ በቀለ ወ/ጊዮርጊስ፤ መሆናቸውን ገልጸው ነግረውኛል::: በገንዘብ ተሸጧል ከሚለው ላይ የሁሉም አንድ ሲሆን አቶ ዘውገ፤ ጀኔራል ነው ሲሉኝ ሻለቃ ጌታቸው የሮም ደግሞ መቶ አለቃ ነው አሉኝ:: የአቶ ዘውገ አባባል " ካርታውን ሰርተን እንደጨረስን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ስልክ ተደውሎ ካርታውን ለማንም እንዳይሰጥ በተለይ እገሌ እንዳይወስድ ምስጢር ነው ብለው አስጠነቀቁኝ" ሲሉ ነግረውኛል:: እኔ አቶ ዘውገን ከውጭ ጉዳይ ሚንስትር ስልክ ደውሉ ማን እንዳስጠነቀቃቸውና ለእገሌ አትስጥ ተብሎ የተነገራቸውን ስም ይንግሩኝ እንድሆን 3 ቀን በተለያዩ ጊዜ ጠይቄያቸው ከላይ ያሉትን መድገም ካልሆነ በቀር አስጠንቃቂውንም ሆነ እንዳይወስድ ስም ተጠርቶ የተነገራቸውን ስም እንዲነግሩኝ ብጠይቅ ፈቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም:: ይህ በገንዘብ ተሸጧል የሚለውን ወሬ ሳይሆን ትክክል ነው ጎንደር ድረስ ተሰምቷል ሲሉ አቶ ወልደ ገብርኤል ደግመውኛል::

ሻለቃ ጌታቸው የሮም <u>ስም ከመቃብር በላይ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 106-107 "ከወሎ ጠቅላይ ግዛት ደሴ ከተማ ተወለዱ:: የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም በተወለዱበት በደሴ ከተማና በኋላም አዲስ አበባ በመምጣት በከፍተኛ ነጥብ አጠናቀዋል:: በዚሁ መሠረት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ገብተው በመማር ላይ እንዳሉ በነበራቸው የወታደርነት ፍላጎትና ዝንባሌ የዩኒቨርስቲውን ትምህርታቸውን አቋርጠው በ1960 ዓም ሀረር ውስጥ በነበረው የጦር ሰራዊት አካዳሚ ት/ቤት ይገባሉ::"

"ከሀረር ጦር አካዳሚ በትምህርታቸው የላቀ ውጤት በማስመዝገብ በ1964 ዓም በክብር ተመርቀው የምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግ ያገኛሉ:: በትምህርታቸውና በአካል ብቃት እንቅስቃሴያቸው ከፍተኛነት ከተመረጡብት ወጣት መኮንኖች አንዱ በመሆን ወደ አርሚ አቪየሽን በረራ ሥራ ላይ እያሉ በ1966 ዓም በተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመፅ ሣቢያ የመንግሥት ሥልጣን ለመቆጣጠር ብቻውን ወታደራዊ ቡድን ውስጥ ይገባሉ:: በዚሁ ቡድን ውስጥም እየሠሩ ሳለ በ1967 ሕዳር 14 ቀን ቀደም ብለው በእስር ላይ በነበሩብት

ኪሎ ሜትር አልፈው ሱዳን ድንበር ላይ የሚያለሙ የትግራይ ልጆች ነበሩ:: በተለይ አቶ ተስፋዬ አድዋ፤አቶ ተስፋዬ ሊንሳ፤ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ከሁመራ ባላባቶች ጋር ተስማምተው መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ሱዳንን ገርፈው የሰደዱ ሲሆኑ ልማታቸውን አስከብረው ኑረዋል:: እኔ እስከማውቀው ድረስ የወልቃይት ልጆች ለአገራቸው ያደረጉት ልማትና ድንበር ጥበቃ ሊያስመሰግናቸው ይገባል:: ስማቸውን የማስታውሰው ፊታውራሪ ሰረበ ለማ፤ አቶ ጌታቸው ይርጋ፤ አቶ አቡሃ አብተው፤ መላከ ሰላም ሲሳይ አየልኝና ሌሎች ብዙ ጀግኖች ተዋግተው አገራቸውን አስከብረው ነበር::"

"ዛሬ እንሆ እነዚህ ከዚህ በላይ ስማቸውን በጥቂቱ የጠቀስኳቸው ግለሰቦችና የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ ተዋግቶ ያስቀረውን መሬት ለሱዳን ሊሰጡ ነው:: ለሚቀጥለው ትውልድ የምመክረው ነገር ቢኖር ከሁመራ እስከ ጋንቤላ 1600 ኪሎ መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ታስቧል:: እኔ ዛሬ እድሜዬ ከ70 ዓመት በላይ ነኝ:: ስለ ሀገሬ ግን እንገበገባለሁ:: እበሳጫለሁ! ስለዚህ ዛሬ 20 ዓመት የሞላህ ወጣት አትርሳ አለብህ አደራ:: ቀደም የነበሩ አባቶችህ አንድ ሁነው ተባብረው ኢትዮጵያን አቆዩን እኛም በአቅማችን ተዋግተን አቆየን:: ዛሬ ወያኔ ለሱዳን ሲሰጥብህ እንደ ቀድሞዎች አባቶቻችን "እብሚ ለሀገሬ" ብለው ተነስና አንድነትህ አስከብር አደራ እልሃለሁ" ሲሉ ገልጸውልኛል::

እንባቢያን በአጤ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣኖች ቀላድ አትጥሉበትም ሲባሉ ለሱዳን ሸጠዋል ይባላል:: እነዚህ አንዳንድ ግለሰቦች ከግል ጥቅማቸው ጋር እያይዘው በግዴለሽነት መሬቱን ለሱዳን ሊሰጡ በመታሰቡ የአካባቢው ሕዝብ የገጠሩ በሕይወቱ የከተማው በሥነ መንግሥት ተከራክሮ ያስቀረ መሆኑ ታሪክ የነገረን ሲሆን ዛሬም ይህ ተመሳሳይ ድርጊት በመፈጸም ላይ መሆኑን ማስገንዘብ እሻለሁ::

የአስር አለቃ አባይነህ መሸሻ



## ምክንያት ሶስት

አቶ ዘውገ ፈንታ፤ "የኢትዮጵያን የሚያውቁት የደህንነትና የአገር ግዛት፤ የፖሊስ ጽፈት ቤት እንዲሁም ውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ባለሞያዎች ናቸው:: የተሳለውን ካርታ ርቀቱንና ርዝመቱን የሚያውቁት" በማለት በወቅቱ የገጸ ምድር ካርታ ድርጅት ሠዓሊው አስረድተውኛል:: በእርሳቸው አገላለጽ "አንድ እስክርቢቶ ጭረት ያረፈባት በጣም ብዙ ኪሎ ሜትር ስለሚሆን በትክክል መጠኑን ልነግርህ አልችልም:: ምክንያቱም የሀገር ጉዳይ ነው" ብለውኛል::

ግለሰቦች ይህን ካርታ በ250 ሺህ ብር ለሱዳን ሸጠዋል:: የሚባለውን ወሬ ደጋፊው ብዙ ነው:: የአቶ ዘውገ ፈንታን አባባል ሻለቃ ጌታቸው የሮም ወሬ ሳይሆን ትክክል ነው በማለት ከመጽሐፋቸው ውስጥ ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል መቶ አለቃ በቀለ ወ/ጊዮርጊስ፤ መሆናቸውን ገልጸው ነግረውኛል::: በገንዘብ ተሸጧል ከሚለው ላይ የሁሉም አንድ ሲሆን አቶ ዘውገ! ጄኔራል ነው ሲሉኝ ሻለቃ ጌታቸው የሮም ደግሞ መቶ አለቃ ነው አሉኝ:: የአቶ ዘውገ አባባል " ካርታውን ሰርተን እንደጨረስን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ስልክ ተደውሎ ካርታውን ለማንም እንዳይሰጥ በተለይ አገሌ እንዳይወስድ ምስጢር ነው ብለው አስጠነቀቁኝ" ሲሉ ነግረውኛል:: እኔ አቶ ዘውገን ከውጭ ጉዳይ ሚንስትር ስልክ ደውሎ ማን እንዳስጠነቀቃቸውና ለእገሌ አትስጥ ተብሎ የተነገራቸውን ስም ይነግሩኝ እንደሆን 3 ቀን በተለያዩ ጊዜ ጠይቄያቸው ከላይ ያሉትን መድገም ካልሆነ በቀር አስጠንቃቂውንም ሆነ እንዳይወስድ ስም ተጠርቶ የተነገራቸውን ስም እንዲነግሩኝ ብጠይቅ ፈቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም:: ይህ በገንዘብ ተሸጧል የሚለውን ወሬ ሳይሆን ትክክል ነው ጎንደር ድረስ ተሰምቷል ሲሉ አቶ ወልደ ገብርኤል ደግመውኛል::

ሻለቃ ጌታቸው የሮም <u>ስም ከመቃብር በላይ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 106-107 "በወሎ ጠቅላይ ግዛት ደሴ ከተማ ተወለዱ:: የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም በተወለዱበት በደሴ ከተማና በኋላም አዲስ አበባ በመምጣት በከፍተኛ ነጥብ አጠናቀዋል:: በዚሁ መሠረት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ገብተው በመማር ላይ እንዳሉ በነበራቸው የወታደርነት ፍላጎትና ዝንባሌ የዩኒቨርስቲውን ትምህርታቸውን አቋርጠው በ1960 ዓም ሀረር ውስጥ በነበረው የጦር ሰራዊት አካዳሚ ት/ቤት ይገባሉ::"

"ከሀረር ጦር አካዳሚ በትምህርታቸው የላቀ ውጤት በማስመዝገብ በ1964 ዓም በክብር ተመርቀው የምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግ ያገኛሉ:: በትምህርታቸውና በአካል ብቃት እንቅስቃሴያቸው ከፍተኛነት ከተመረጡበት ወጣት መኮንኖች አንዱ በመሆን ወደ አርሚ አቪየሽን በረራ ሥራ ላይ እያሉ በ1966 ዓም በተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመፅ ሣቢያ የመንግሥት ሥልጣን ለመቆጣጠር ብቻውን ወታደራዊ ቡድን ውስጥ ይገባሉ:: በዚሁ ቡድን ውስጥም እየሠሩ ሳለ በ1967 ሕዳር 14 ቀን ቀደም ብለው በእስር ላይ በነበሩበት

ከፍተኛ ባለስልጣኖች ላይ የፖለቲካ እርምጃ በማለት በወሰነው ኃይል እርሳቸውም አብረው ተገድለዋል" ሲሉ ጽፈዋል::



መቶ አለቃ በቀለ ወልደ ጊዮርጊስ!

ሻለቃ ጌታቸው የሮም ጋር ስንወያይ "ይህ መቶ አለቃ በቀለ ታስሮ ከተፈታ በኋላ ከየቦታው የተሰባሰበው ደርግ ካርታውን የሸጠ መሆኑን እንዳወቀ አስሮ ከ60ዎቹ ጋር ገደለው" ብለውኛል:: ገጸ ምድር ካርታው ተሽጧል በማለት አቶ ዘውገ ፈንታ ያምናሉ አሟሟቱን አስመልክቶ ደግሞ እርሳቸው እንዲህ ይላሉ "እኔ በዚህ ወቅት ከአገሬ አልነበርኩም የሰማሁት ታሪኩን ነው:: አንድ ቀን መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እስረኞችን ሲጎበኝ እርሱ የታሰረበትን ምክንያት ሲጠይቅ በአገር ምስጢር ካርታ በመሸጡ ነው ብለው ሲነግሩት ከሀዲን አስራችሁ ትቀልባላችሁ በሉት" ብሎ በማዘዙ መገደሉን ሰምቻለሁ ሲሉ ነግረውኛል:: ሰማቸው እንዳይነገር የፈለጉት አዛውንት መቶ አለቃ በቀለ፣ የተጠቀሙበት
1ኛ ልጅ በመሆኑ
2ኛ ከእነሱ ያልሆነ ሰው በመሆኑ አዘውታል"::



"ምስጢሩ ሲጋለጥ የደህንነቱ ሰዎች ቢያስሩትም እንዲፈታ ሆነ:: እንዲያውም እነሱ እንዳይጋለጡ በሰፊው እንዳይመረመር አስደርገዋል:: የመቶ አለቃ በቀለ፣ ከውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሆነ ከካርታ ድርጅት አለቆች ጋር ግንኙነት ሊኖረው ይችላል:: ነገር ግን ይህን ተንኮል ለመፈጸም እርሱ ሊሆን አይችልም:: ሌሎች ባለሥልጣኖች ከሱዳን መንግሥት ጋር ግንኙነት አድርገው ከተስማሙ በኋላ እርሱ ካርታውን እንዲያደርስ አድርገውታል:: ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ይሰራ የነበረ አንድ ሰቪል ደርግ ደርሶበት ከአንድ በሲአኤ ከተጠረጠረ ግለሰብ ጋር የተገደለ ሲኖር ሌሎች ግን ሳይነቃባቸው የመለጡ ዛሬ ድረስ በሕይወት ያሉ ናቸው" ሲሉ ነግረውኛል::

ስም ከመቃብር በላይ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 372 "የመተማንና የሁመራን አካባቢዎች ለሱዳን አሣልፎ ለመስጠት የነበረውን ድርድርና ስምምነት አጥብቀው እንደሚቃወሙ ይጠረጠሩ የነበሩት የቤጌምድርና ስሜን አጠቃላይ ግዛት ፖሊስ አዛዥ ብ/ጄኔራል ሥዩም ገሠሠና አባሪዎቻቸው ናቸው የተባሉትን ሁሉ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ይደረጋል" ሲሉ ጽፈዋል:: ከላይ የዓይን ምስክሮች የተናገሩት ታሪክ ከዚህ ከፍ ተብሉ ከተነበበው የመጽሐፍ ጥቅስ ጋር ይገናኛል:: ቅድሚያ መሬቱ በቀላድ መያዝ የለበትም በማለት አድማ ያደረጉት ሰዎች ሁሉ እንዲዛወሩ ተደርገዋል:: የአቶ ወልደ ገብርኤል አሰጌና የአቶ ሊቀ እጅጉ ምስክርነት ከሻለቃ ጌታቸው የሮም አጻጻፍ ጋር ተመሳሳይ ነው:: መንግሥታት የተሰጣትን የራስ ገዝነት መብት በራሷ አፍርሳ ከኢትዮጵያ ጋር ኤርትራ ከተቀላቀለች ጀምሮ አንዳንድ የኤርትራ ተወላጆች ወደ አረብ አገርና ግብጽ መሰደድ ጀመሩ::

በአረቦች ድጋፍ ጀብሃ በ1954 ዓም ካይሮ ተመሰረተ:: አረቦች ቀደም ጀምረው ኤርትራ ነፃ አገር መሆን ይደግፉ የነበረው ለኤርትራ ሕዝብ ደህንነት ብለው ሳይሆን ቀይ ባህርን በቁጥራቸው ስር ለማድረግ አስበው ነበር:: ለዚህም ዋናው የኢትዮጵያ መንግሥት ከቀደም ጀምሮ የንጉስ ሰሎሞን ጋር የተያያዘ ግንኙነት መኖርና የእስራኤል መንግሥት መመስረት ቀይ ባህርን በሕብረት እንዳይጠቀሙበት ለማድረግ አረቦች ፀረ ኢትዮጵያ የሆኑ ጀብሃን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ግለሰቦች እንዲከዱ ለማድረግ ጥረት አድርገዋል:: በ1962 ዓም አውሮፕላን ጠልፈው ሱዳን ያረፉት ተማሪዎችን የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አስሮ ለማምጣት ያደረገው ድርድር በባዶ ተፈጽሟል:: ሱዳን እነዚህን ተማሪዎች ለኢትዮጵያ መንግሥት አሳልፋ እንዳትሰጥ አረቦች ጥረት አድርገዋል:: ደግሞም ተሳካላቸው ተማሪዎቹ ከሱዳን አልጀሪያ እንዲሄዱ ነው የተደረገው::

ያሬድ ጥበቡ የአመጹን እሁሪት ለመስበር በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 8 "ከ30 ዓመት በፊት ከባህርዳር በጠለፉት የእንቁላል ማመላለሻ አውሮፕላን ጀግንነታቸው ብቻ እያደነቅን እንድንኖር ለምንድን ነው የተፈረደብን? ምናልባት ዲፕሎማሲ አዲስ መስክም ስለነበር እየወደቁ እየተነሱ መማር ስለነበረባቸው ነው የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል:: ግን በድርጅት መስክስ የአቶ

ኢያሱ አመራር በፓርቲው ምን አተረፈው?" ሲሉ ጽፈዋል። በኢትዮጵያ ታሪክ አውሮፕላን መጥለፍ ያስተማሩ በዚያን ወቅት ከጠለፉት መካከል በሕይወት ያሉ አቶ ኢያሱ አየማየሁ ናቸው። የተማሪውን የትግል ታሪክ ስትመረምሩ የምታገኙት ሠነድ የአልጀሪያው ቡድን የሚለው ሁሌም የነአቶ ኢያሱ አለማየሁና አቶ ብርሃነ መስቀል ሌሉችም ሁነው የጻፉት ነው።

በአቶ አሰፋ ጫቦ "ጥናት መሰረት ዛሬ የአንቀጽ 39 መንስኤ እንዴት ወደ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ እንደደረሰች ሲያትቱ ያችን የብሔሮችን ጹሑፍ ያረቀቋት ጀብሃ ሲሆን ለነአቶ ኢያሱ አለማየሁ ተሰጥቶአቸው እነሱ ሉስ አንጀለስ ይማሩ ለነበሩት ለዛሬው ሊቀ ጠበብት እንድርያስ እሸቴ ልከውት እርሳቸው አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ይማሩ ለነበሩት ለአቶ ዋለልኝ መኮንን ልከዋታል። አቶ ዋለልኝ መኮንን እንደበተ ሩሉቱ በመሆናቸው የራሳቸው አድርገው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አደረሷት" ይላሉ። ይህ ብሔራዊ መፈክር ሁኖ የወጣው ሠነድ ውሎ አድሮ በኢሕአፓ መርሃ ግብር መካተቱ አይዘነጋም። ከዚያም ደግሞ ወያኔ አንቀጽ 39 ቀርፆ እንሆ ኢትዮጵያን እያፈረሰበት ይገኛል።

ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ አዛውንት "አረቦች በዚህ ወቅት በኤርትራ የተጀመረው እንቅስቃሴ በአጭር እንዲቀጭ ለማድረግ የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አረቦችን ለማስደሰት ሲሉ እነሱ የሚያዙአቸውን ሲፈጽሙ ኑረዋል። ዓረቦች ምንጊዜም ለኢትዮጵያ የማይተኙ መሆናቸውን የአጤው መንግሥት አልተረዳም ነበር። አረቦች ቅድሚያ ያደረጉት ኢትዮጵያ ከእስራኤል ጋር የነበራትን ግንኙነት እንድታቋርጥ ነበር።"

"አጤ ኃይለ ሥላሴ ከእስራኤል ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያቋርጡ አለበለዚያ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት አባል የሆኑ በሃይማኖት እስላም የሆኑትን አገሮች ሊያቋርጡ ይፈልጋሉ ሲሏቸው አጤው በዚያን ወቅት የዓለም አባት ለመባል ይፈልጉ ስለነበር በሳውዲያ አረቢያ ንጉሥ የቀረበላቸውን ጥያቄ ሳያቅማሙ ተቀብለዋል። በእርግጥ አረቦች ቃል የገቡላቸው እርሳቸው ከእስራኤል ጋር ያላቸውን ግንኙነት ካቋረጡ እነሱም የጀብሃን ታጋዮች መርዳት እንደማይፈልጉ ነገሩአቸው ነበር። ስለዚህ አጤ ኃይለ ሥላሴ ከእስራኤል ጋር የነበራቸውን ግንኙነት አቋረጡ። በተለይ ይህን ግንኙነት ማቋረጥ እንደሌለባቸው የሃይማኖት ሊቃውንቶች ተማጽነው ነበር። ነገር ግን አረቦች በቃላቸው አልጸኑም። እንኳን መርዳት ሊያቋርጡ ቀርቶ ይበልጥ እንዲጠናከሩ አድርገዋል" ሲሉ ተናግረዋል።

የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለስልጣኖች በጉቦም ሆነ በሌላ መንገድ የፈለጉትን ካስደረጉ በኋላ ቅድሚያ ከዘውድ ምክር ቤት ውይይት ተደረገበት። ችግር ሲፈጠር ወደ ሕዝብ ምክር ቤት ገባና የባሰ ተደባደቡበት። አንድ ግልጽ ሊሆንልኝ ያልቻለ ጉዳይ ደግሞ ውይይት የተደረገበት ቅድሚያ ከሕዝብ ምክር ቤት ወይስ ዘውድ ምክር ቤት ነው? የሚለውን ትክክለኛ ታሪክ ማግኘት አልተቻለም።



ፊንታዬ ወ/ዘሊባኖስ <u>የአባ ጠቅል አጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 307 "አንዳንዴ በየጊዜው ከሚነሱት ብሔራዊ ዓላማ ከነበራቸው ጉዳዮች መካከል በጣም አከራካሪ የነበረው የሰቲት ሁመራ የእርሻ ልማት እየተስፋፋ በሄደበት ጊዜ የኢትዮጵያና የሱዳን የድንበር ወሰንን አስመልክቶ የተነሳው ክርክር ነበር። በዚህ በኩል ለብዙ ዘመን ሳይከለል በቆየው በዚህ ወሰን አካባቢ በቅርቡ በተገኘው በሁለቱ አጎራባች አገሮች የወዳጅነት መቀራረብ ላይ ተመስርቶ ሰፋ ያለ መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ነው ተብሎ ያልተጣራ ወሬ ተናፈሶ ነበርና ይህንን ዓይነት የተዛባ ስምምነት እንዳይፈጸም በተለይ የቤጌምድርና የስሜን ጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎች አንድ ላይ በመቃወም ባቀረቡት ሀሳብ ሌሎች የምክር ቤቱ እንደራሴዎች ባለመደገፋቸው በተነሳው ክርክር ከፍ ያለ የሀሳብ መለያየት ላይ በተፈጠረው አለመግባባት እርስ በርስ መደባደብ ደርሰው እንደነበር አስታውሳለሁ። ስለሆነም በዚህ ምክንያት ጉዳዩ እልባት ሳያገኝ ቀርቷል" ሲሉ ጽፈዋል።

ክቡር አቶ ፊንታዬ ወ/ዘሊባኖስን ከዚሁ አሜሪካ ስላሉ ታህሳስ 12 ቀን 2001 ዓም በስልክ እናግሬያቸው ነበር። እርሳቸውን ያቀረብኩላቸው ጥያቄ "በመጀመሪያ ምክር ቤት እንዴት ለውይይት ሊያቀርበው ቻለ?" የሚል ጥያቄ ነበር ያቀረብኩላቸው እርሳቸው "በውነቱ እኔ እንዴት እንደተጀመረ አላስታውስም። የማስታውሰው ክርክሩን ነው። በስም ጠርቼ እገሌ አቀረበው ለማለት የዘነጋሁት ሲሆን ወደ ሕዝብ ምክር ቤት ለውይይት ያቀረቡት የአካባቢው እንደራሴዎች ናቸው። ለውይይት አጀንዳ ሊያዝ አይችልም ያሉት የሐረር እንደራሴ ሻለቃ አድማሴ ዘለቀ ናቸው። ሁመራ በወቅቱ ስመጥር የሆነው በአጭር ጊዜ ሥራ ብዙ ገንዘብ የሚገኝበት መሬት በመሆኑ ነው" ብለውኛል።

ይህን በተመለከተም በወቅቱ የኢትዮጵያ የካርታ ስራ ይሰሩ የነበሩት ፎቶ ግራፈሩን አቶ ዘውገ ፈንታንም ደጋግሜ ጠይቄያቸው ነበር። አቶ ዘውገ ፈንታ፤ እንዴት ሊጀመር ቻለ?ለሚለው ጥያቄ መልሳቸው" በተለይም ስሜን ኢትዮጵያን ለማልማት የዓለም ባንክ የሚሰጠው ገንዘብ ነበር በዚህ ወቅት የሁመራ ልማት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። የሁመራ ልማት ከፍ ማለት ሲጀምር ሱዳኖች ቅናት አድሮባቸዋል። በወቅቱ እንደተባለው በግብጽ ወይም በዓረብ አገሮች ግፊት ምክንያት ተነሳስተው ሳይሆን አይቀርም። ስለዚህ ደንበራችን ይወሰን ብለው ጠየቁ። በዚህ ምክንያት ምክር ቤት ሊደርስ ቻለ? እንዴት ምክር ቤቱ እንደሰማው አላውቅም" ብለውኛል።

ልጅ እግዓው ውብነህ <u>ራስ አሞራው ውብነህ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 146 "1964 ዓም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሰብሳቢነት ከጠቅላይ ሚኒስቴር እስከ ም/ሚኒስቴር የየጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴዎች የሕግ መወሰኛ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት እንዲሁም የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዜዳንትና አባሎች በተሰበሰቡበት በቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት ከሁመራ እስከ ጎጃም የሚያዋስነውን የኢትዮጵያና የሱዳን ወሰን ድምብር ስለሚያካልለው በውጭ

ጉዳይ ሚኒስቴር በጠቅላይ ሚኒስተሩ የቀረበው ሐሳብ ከተነበበ በኋላ በአጤ ምኒልክ ጊዜ ሱዳን በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር በነበረችበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሰው የሱዳንና የኢትዮጵያን ድንበር እንዲከለል" ሲሉ ጽፈዋል።

ሰፋ አድርገው ታሪክ ጠቅሰው የጻፉት ሲሆን በራስ አሞራው ውብነህ ተሰማ አባባል ደግሞ "የየጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴዎች" የሚለው ቃል ሳነብ ቅድሚያ ከዘውድ ምክር ቤት ሳይሆን ከምክር ቤት ውይይት የተደረገበት ይመስላል ከዚህ የሚቀጥለውን ሰነድ ማንበብ ይቻላል።

አምሳ ለቃ (ደጃዝማች) አፈራ አዳነ ራስ አሞራው ውብነህ የነገሩኝ ብለው ያጫዎቱኝ ታሪክ ከዚህ የሚከተለው ነው። "ከምክር ቤቱ ፓርላማው ከተደባደበበት በኋላ ጃንሆይ ይህን ጉዳይ ማን ያውቃል ብለው ሲጠይቁ ራስ አሞራው ውብነህ ያውቃል ተብለው ተነገራቸውና ተጠራን። ጃንሆይ ራስ የኢትዮጵያንና የሱዳንን ድንበር ታውቀዋለህ? ብለው ጠየቁን። እኛም አዎ ጃንሆይ አውሬ ስናድንበት የነበረው ጥርሳችን ሰብሮ ያሳደገን አገራችን ስለሆን ገዳሪፍን አልፎ መደኔ ይደርሳል አልናቸው። ጃንሆይ እርሱንማ አጤ ምኒልክ ተደናብረውታል አሉ። እኛም ጃንሆይ አጤ ምኒልክን የምናከብራቸው የአድዋን ድል በማድረጋቸውና ለኢትዮጵያ ስልጣኔ ማስገባታቸው እንጂ በድንበር ጉዳይ እኮ አናመሰግናቸውም" ብለን በመናገራችን ጃንሆይ ተበሳጭተው ካባቸውን አጣፍተው ሄዱ።"

"ለካ ካባቸውን ካጣፉ ይታሰር የሚል ትዕዛዝ ማስተላለፋቸው ነው። ወዲያው በዚህ መጡ ሳልላጠብደሎች እየገፈተሩ ምድር ቤት አስገቡን። ኋላ ተፈቅዶልን ሕደን እጅ እንድንነሳ ሆን ጃንሆይ አንተ እሚሉ አጤ ምኒልክን ተሳዳቢ ለ6 ወር ከቤትህ እንዳትወጣ አዘናል ብለው በቁም እስር ከቤታችን እንድንታሰር ሆን" ብለው የነገሩአቸውን አምሳ ለቃ (ደጃዝማች) አፈራ ሱዳን ሳለን አጫውተውኝ ስለነበር ለማረጋገጥ ጥር 20 ቀን 2001 ዓም ስልክ መታሁና ደንበሩን አስመልክቶ ስንጫወት ሳይረሱት ከ24 ዓመት በኋላ ያንኑ ታሪክ ነገሩኝ። ነገር ግን ስለራ አሞራ ውብነህ መጽሐፍ ላይ ቃል በቃል የተመዘገበ ባይሆንም ተቀራራቢ ነው።

ደንበርን አስመልክቶ የጻፉት ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይመልከቱት። በ1988 ዓም ከአሜሪካ ኢትዮጵያ ስሔድ ሱዳንና ኢትዮጵያ ጠብ ላይ ነበሩ። ይህ የራስ አሞራው ውብነህ አባባል ከጭንቅላቴ ገብቶ ቆይቶ ስለነበር ጎንደር አቶ ማሞ ስበር የት እንዳሉ ስጠይቅ አዲስ አበባ መሆናቸውን ነገሩኝ። ብፈልግ ማግኘት አቅቶኝ ተመለስኩ ኋላ በ1989 ዓም ላይ ስልካቸውን አግኝቼ ደውዬ አነጋግሬአቸው ነበር።

በ1989 ዓም የነገሩኝ "ደንበርን በተመለከተ የፓርላማው ስብሳቢ ለውይይ አጀንዳ አይያዝም በማለቱ ምክንያት ችግር ሊፈጠር ቻለ። የጎንደር የፓርላማ አባላት ብቻ ሳንሆን የእኛን አቅዋም ደግፈው እስከ መታሰር የደረሱ የሕዝብ እንደራሴዎች የሌሎች ክፍለ ሀገር እንደራሴዎች ተባባሪ ነበሩ" ሲሉ ነግረውኝ



ነበር። በቅርቡ ይህ የደንበር ጉዳይ ከተነሳ በኋላ አቶ ማሞ ስበርን ለማነጋገር ቀደም የማውቀውን ስልክ ስደውል የማይሰራ በመሆኑ የጠቀስኩት በ1989 ዓም የነገሩኝን ነው።

ከላይ ክክቡር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ ጽሑፍ መረዳት እንደሚቻለው በጅቡቲ፥ በኬንያ እና በሱማሌ በኩል በግማሽ የተሰመረበት መሆኑን ሲገልጹ በጎንደርና በጎጃም በዛሬው ኤርትራ በኩል እርሳቸው ያልጻፉት ያላለቀ ፋይል ነበር። ሱዳን ከእንግሊዝ ነጻ ከሆነች አንስቶ በጎንደር ክፍለ ሀገር ጎንደር ዙሪያ አውራጃ ታች አርማጭሆ ወረዳ ተወላጆች ሱዳኖች ጓንግ ወንዙን ተሻግረው ማርሰን ተመለከቱ። እነዚህ አርማጭሆዎች ሱዳኖችን ማረስ እንደሌለባቸው መከላከል ጀመሩ። ሱዳኖች አትረሱ ሲባሉ ግብር ለኢትዮጵያ መንግሥት እንከፍላለን በማለት ሲያርሱ ይከርሙና ባመቱ ፖሊስ ሚሊያ ያቋቁማሉ። ቦታውን በአርብኛ ስም ይቀይሩታል። በዚህ የሱዳኖች ድርጊት ያንገበገባቸው የአርማጭሆዎች የሱዳንን አራሾች የሚጠብቁትን ወታደሮች ተዋጉአቸው። በዚህ ጦርነት አቶ ገብሬ ተወልደ መድህን አቶ ድረስ አይናለምና አቶ አወቀ ዋናሁን፤ እንዲሁም ሌሎች 4 ሰዎች ሞቱ። ከዚህ በኋላ ሱዳኖች ክትት ብለው ነበር።

<u>ስም ከመቃብር በላይ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 367 "ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህን ሕያው ታሪክ በመርሳት የኢትዮጵያ አካል ከሆነው መሬት ላይ ክፍለውና ቆርሰው ለሱዳን በችሮታ ለመስጠት በድፍረት ተነስተው ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ ለመደራደር የሱዳን ፕሬዝዳንት የነበሩት ጄኔራል ኑሜሪ አዲስ አበባ መጥተው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት ላይ እንዲገኙ በማድረግ ከሸላሚው ንጉሥና ከተሸላሚዊው ጋር በ1964 ዓም ፎቶግራፍ ተነስተው ታሪካዊ መረጃ እንዲሆን አድርገዋል" ሲሉ ጽፈዋል። አንባቢያን የራስ አሞራው ውብነህ እና የሻለቃ ጌታቸው ደንበርን አስመልክቶ የጻፉትን ከዚህ የሚቀጥለውን ከየራሳቸው መጽሐፍ እንዳለ በየመጽሐፋቸው ላይ ገልብጬ (ኮፒ) አድርጌ ከዚህ በታች ያለውን ተመልከቱ።

በ፲፱፻፷፬(1964)ዓ.ም. በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሰብሳቢነት ከጠቅላይ ሚኒስቴር እስከ ም/ሚኒስቴር የየጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎች የህግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት እንዲሁም የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና አባሎች በተሰበሰቡበት በቤጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት ከሑመራ እስከ ጉሽም የሚያዋስነውን የኢትዮጲያና የሱዳን ወሰን ድምበር ስለሚያከልለው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር[1] በጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀረበው ሐሳብ ከተነበበ በኋላ በዓፄ ሚኒሊክ ጊዜ ሱዳን በእንግሊዝ ቀኝ ገዥነት ስር በነበረችበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሰው የሱዳንና የኢትዮጲያ ድምበር እንዲከለል ከእንግሊዝ በቀረበው ጥያቄ መሠረት በዓፄ ሚኒሊክ ተቀባይነት አግኝቶ በድንበሩ ላይ ተገኝቶ የሚከልል ሰው እንዲደረግ በተወሰነው መሠረት አንድ በቤጌምድር ሰሜን የሚገኙ ደጃዝማች መሸሻ የተባሉ ተገኝተው ከእንግሊዝ ከተላከው ወኪል ጋር ተገናኝተው ለመከለል በጉዞ ላይ እንዳሉ የዓፄ ሚኒሊክን ሞት ሰምተው በከለሉ ቦታ ሳይገኙ ወደ ኋላ በመመለሳቸው የእንግሊዝ ተወካይ በቦታው ተገኝቶ በራሱ መንግሥት በሚያመች ሁኔታ የኢትዮጲያ ርስት ንብረት የሆነውን ሁሉ ወደራሱ ክልሉ በማስገባት ድምበርተኛ ያልተገኘበትን ካርታ አንስቶ በሄደው መሰረት ሱዳን ነጻነቷን ባገኘችበት ጊዜ ይህ ህጋዊ ያልሆነውን ካርታ ይዛ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያው በዓፄ ሚኒሊክ ጊዜ የተወሰነ ካርታ ስለሆነ በዚያው መሠረት ሊፈጸም ይገባል ብለው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ባሉበት ለተባለው ጉባኤ ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት ጉባኤውና ንጉሠ ነገሥቱ ከተነጋገሩበት በኋላ አባት የሠራው ለልጅ እንደሚባል ዓፄ ሚኒሊክ የሰሩትን ማፍረስ ስለማይቻል ያው እንግሊዝ በሠራው ካርታ መሠረት ይፈጸም ብሉ ከተወሰነ በኋላ ክቡር ራስ ውብነህ ተሰማም በላይ በተገለጸው መሠረት ውይይት በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ እጃቸውን በማውጣት ለመናገር እድል እንዲሰጣቸው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ይጠይቁ ስለነበረ ከውሣኔ በኋላ ኮመደር እስክንድር ብዙ ጊዜ ያዩዋቸው ስለነበር የተቀመጡትም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉን ስለነበር ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ራስ ውብነህ እኩ ብዙ ጊዜ እጃቸውን እያወጡ ለመናገር ቢፈልጉ ጃንሆይ አልተመለከቱዋቸውም መሰል እባክዎት ያሳስቡላቸው ባሉዋቸው መሠረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እክሊሉ ኃብተወልድ ለጃንሆይ ራስ ውብነህ ጥያቄ አላቸው መሰል እጃቸውን ያወጣሉ ሲሉዋቸው ጃንሆይ ተመልክተው ተናገር ይሉዋቸዋል።



አምራውም ጃንሆይ ይህ የተባለው የሱዳን ጠረፍ እንግሊዝ ሱዳንን ቀ
አድርጉ ከመጣ ጊዜ ጀምሮ የእንግሊዝ ሱዳንና የኢትዮጲያ ድንበር
ከአትበራ አልፎ እያውቅም አሁን ሱዳን ነጻነቷን አግኝታም ከቀየች ወ
፲፱፻፶፱(1959)ዓ.ም. የእኛ የጠረፍ ጠባቂዎች ፖሊሶች ተገኝተው እን
ከተደረገ ወዲህ በልዩ ልዩ መደለያ እየተቀበሉ ጥንት ከእንግሊዝ ይዞ
የተባለውን ወንዝ ድምበር ባንድ በኩል አብጤር ከሚባለው ባንድ
ሑመራ አጠገብ ከአይሮፕላን ማረፊያ ጥግ ድረስ ለሱዳን አስረክበው
አስፍርቡታል፡፡

ይህች ከላይ የገለጽኳትን ድምበር እኔ ራሴ ያደከብት በርሃና ጹር
በትክክል የማውቀው የመሬቱን የእንጨቱን ዓይነት የማውቀው ነው፡፡
በዚህ ክፍል የሚገኘው ተወላጅ ቀርቶ የሱዳን ወገብ ሳይሆን የሱዳን
አዛውንቱም ቢሆን ይህ ከጥንግ ወዲህ ያለው ወሠን የኢትዮጲያ
ይመሰክራል፡፡

ጃንሆይ በዓፄ ሚኒሊክ ጊዜ አውሮፓውያን መላ የአፍሪካን አህጉር ቀ
በማድረግ ወርሰው ኢትዮጲያን ለመጉረስ በሚያኩበኩቡበት ጊዜ እንኳን
ያልሰጡትን ፈርተው ቢሰጡትም አይፈረድባቸውም አሁን በግርማዊ
ነገሥት ረዳትነት መላ የአፍሪካ ሀገር ነጻነቱን ሲጉናጸፍ እኛ ለሦ
ዘመናት በነጻነት የኖረችውን አገር እንዴት በፊታችን ፈርመን እንሰጣ

ጉልበት አተን በጉልበት ቢወስደው[1] ልጆቻችን ጉልበት ባገ
ይመልሱታል፡፡ በፊታችን መሆን የለበትም ባሉ ጊዜ ግርማዊ ጃንሆ
ማይሉ ከውሣኔ በኋላ በመቃወማቸው ይመስላል ተቆጥተው በመነሳት
ጥለው ይነሳሉ፡

ከዚህ በኋላ ፀሐፊ ትእዛዝ እክሊሉ ኃብተወልድ ጃንሆይን ተከትለ
ውብነህ ጉባኤውን ብቻ ሳይሆን ንጉሠ ነገሥቱንም ደፍረዋል፤ እንድጠ
ይፍቀዱልኝ ብለው ባመለከቱት መሠረት የሚመስልህን ሰው ይዘህ
ይሉዋቸውና ይመለሳሉ፡፡

ወዲያውኑ ራስ ውብነህ እንዳይሄዱ ይባላል፡፡ ፀሐፊ ትእዛዝ እክሊሉ ባ
1ኛ. ደጃ/ክፍሌ ዳዲ
2ኛ. ፀሐፊ/ትእዛዝ ተፈራ ወርቅ

3ኛ. ደጃዝማች ክፍሌ አርጋው
4ኛ. ደጃዝማች በደ ተሰማን ይዘው ራስ ውብነህን ያስጠራሉ፡፡

በኋላ በደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ ጠያቂነት ክቡር ራስ ለመሆኑ ሥራዎን ያውቁታል
ይሉዋቸዋል፡፡
ዐ አውቀዋለሁ!
ዲያ ካወቁ የንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ ምክር ቤት አባል ሆነው የዘውድን
ገር ማእረግ በመጠበቅ ፈንታ እንዴት ንጉሠ ነገሥቱ ውሣኔ ከሰጡ በኋላ
ቸውን ውሣኔ በማፍረስና በማዋረድ አፍራሽ የሆነ ነገር ይናገራሉ
ትዎቸው!
, ንጉሠ ነገሥቱን የሚያዋርድ አልተናገርኩም ንጉሠ ነገሥቱን
ሚያስከብር ነገር ተናገርኩ እንጂ! አላዋረድኩም፡፡ የምታዋርዷቸው እናንተ
ችሁ!!

እንዃን በአንደኛ ደረጃ የምወደው ሀገሬንና ነጻነቷን ነው! ጃንሆይን
ዳቸው በሁለተኛ ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የሚያጠያይቀን ነገር ያለ
መሰለኝም ብለው ሕዝብ ሳያውቀው ታፍኖ ከምቀር ሕዝብ እያየኝ ብታሠር
ል ብለው ከመቅጽበት ተቆጥተው በሩን ከፍተው በመውጣት ከመኪናቸው
፡ ገብተው ወደ መኖሪያ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡

በኋላ ፀሐፌ ትእዛዝ አክሊሉ ይመሩት ከነበርው ጉባኤ ተነስተው ጃንሆይ
ብት ክፍል ገብተው ጃንሆይ ራስ ውብነህ ቀደም ብለው ከተናገሩት ይልቅ
, ይበልጥ ሳደረግንላቸው ጥያቄ ምንም አላጠፋሁም በማለት በአንደኛ ደረጃ
ንና ነጻነቷን ነው የምወደው! ጃንሆይን የምወደው በሁለተኛ ደረጃ ነው
፡ እነሀ መታሰር አለባቸው እንዲታሰሩ ይፈቀድ ላሉት፦

ይ ሲመልሱ አክሊሉ እዋቂ ትመስለኝ ነበር ለካስ አታውቅም፤ እንዴት
ብሆም ውብነህ እኮ ዛሬ የሰራው ሥራ በአርበኝነት ከሠራው ሥራ የበለጠ
እንዴት ይታሠር ትለኛለህ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ መሣቂያና መዘባበቻ
ድርገን ነው! የተናገረውም እውነት ነው ሀገሩንና ነጻነቱን ይወዳል፡፡
ም አይጠላኝም! ብለው ለሱዳን የተሰጠው ውሣኔ አይተላለፍ ካሉ በኋላ
ንና ኢትዮጲያ ድንበር ሁለቱ መንግሥታት ተስማምተው ውሣኔ እስከተሰጠ
፡ በያሉበት በየይዞታቸው ይቆዩ ተብሎ ተወስኖ እስካሁን በዚያው ውሣኔ
ለ ነው፡፡



ሥም ከመቃብር በላይ

## ክፍል አራት

## የጠረፍ ድንበሮች ጉዳይ

## የኢትዮጵያና የሱዳን ጠረፎች ድርድር

ኢትዮጵያና አጐራባች አገሮችን በሚመለከት ሲጠኑ የሚገባቸው በቂ ትንታኔና ግንዛቤ ሊሰጥባቸው፣ምክኒያቶችና ውጤቶች ሊመረመሩባቸው የሚገቧቸው ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች አሉ፡፡ የኮንትሮባንድ ንግድን የወንጀለኞች ከአንዱ ወደ ሌላው መዘዋወርና መደብለቅ የዘር ትስስር የግጦሽ ሆነ የእርሻ መሬት ይዞታ የኃይል አጠቃቀምና ቁጥጥር የመሣሰሉት ሌሎችም ሕገ መንግስት ከሚደነግገው ውጭ ባለሥልጣናት የሚያከናውኗቸው ወይም ለመደራደር የሚያደርጓቸው ስምምነቶችና በርካታ ጉዳዮች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በእያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ ውስጥ በተደጋጋሚ የምገልፀውና አንባቢዎችም እንዲገነዘቡልኝ አጥብቄ የምጠይቀው፣ ትረካው ሁሉ የግሌን ምስክርነትና ትዝታዬንም የሚገልፅ መሆኑን ነው። የሱዳንና የኢትዮጵያን ግንኙነት የምገልፀውም በኔ ምስክርነት ሥር ያሉትን እንጂ ርዕሱን በመመልከት ሰፊና ጥልቅ የፖለቲካ ጉዳዮች ተዘርዝረው የሚቀርቡበት አይደለም፡፡ የእስከዛሬዎቹ የታሪክ ጸሀፊች መሪዎችን ለማስደሰትና የፖለቲካ አመለካከትን ለማንፀባረቅ ሲባሉ የሚቀርቡ በመሆናቸው በተራው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ልብ ውስጥ ያሉትን እውነታዎች ይጋርዷቸዋል። ስለሆነም ሣይገለፁ የታለፉትን፣ ተራ የሚመስሉ ጉዳዮችን በዚህ ቦታ አጠቃቅሜቸዋለሁ። በንጉሠ ነገስቱና በባለሥልጣኖቻቸውም ይሰጡ የነበሩ ውሣኔዎችን በጥቂቱ አሣያለሁ። ታሪክ የህዝብ መሆኑንም የሚመሰክሩ እውነታዎች እተርካለሁ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተጠቀሱት የተለያዩ ርዕሶች ላይ የጊዜ ጉዳይ በጥቅሉ እንጂ በተለየ ተረጋግጦ አልተገለፀም፡፡ ይህ የሆነው ታሪኩን ለመፃፍ ሲባል ከመነሻው ጀምሮ ዕለትና ወር እየተመዘገበ የተሰበሰበ መረጃ ስላልሆነ ነው። ይልቁንም በትውስታ የሚታሰበው የተገለፀበት ነው። የሱዳንና የኢትዮጵያን ግንኙነት በተመለከተ የማነሣው ታሪክ ከ1956 ዓ.ም ወዲህ ያለውን ጊዜ ያመለክታል። ይህም የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት የነበረበት ጊዜ በመሆኑ ባለሥልጣናቱም የዚያው ጊዜ ሰዎች ናቸው። በተጨማሪም ትረካው

<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር አካባቢ የሚገኙትን የመተማንና የሁመራን አካባቢ የሚያመለክት ነው።

በዚህች አነስተኛ ርዕስ ስር ለመጥቀስ የምሞክረው በኢትዮጵያና በሱዳን ጠረፎች ላይ ስለነበረውና እስከዛሬም ስለሚከናወን አንድ አገራዊ አጀንዳ ነው። ይህን በመሠለ ከተጎንጣይዋ ኤርትራ ጋር በምስራቅ ከምታዋስነን ጅቡቲ ጋር፣ከምስራቅ እስከ ደቡብ ካለችዉ ሶማሊያ ጋር እንዲሁም በደቡብ ከምትገኘው ኬንያ ጋር ድንበርን አስመልክት ሰላለው ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይደበቀው ሊያውቀው የሚገባው ጉዳይ ነው። ስለ አገር ማወቅ መብት እንጂ ስጦታ ወይም ችሮታ አይደለም። አገርን በሚመለከት ጥቂቶች ባሻቸውና ለነርሱ የሥልጣን ዕድሜ ሲባል በተመቻቸው መልክ የሚስተካከልና የሚሸራረፍ የሚጨመርና የሚቀነስ ሲሆን አይገባም። ዜጎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል ናቸው የሚለው ሕገ መንግስታዊ አንቀፅ የሚረጋገጠው እያንዳንዱ ዜጋ በአገሩ ላይ እኩል ድርሻ ሲኖረው ብቻ ነው።

በጦርነት በበሽታ በረሃብ የሚረገፈው ድሃው ሕዝብ ነው። ይህ እንሬ ብሎ ደሙን የሚያፈስስና የግዛት ሉአላዊነት ተረጋግጦ እንዲኖር የሚያደርግ ዜጋ ጦርነቱ፣በሽታውና ረሃቡ ከቶውንም በማይነካቸው ገዥዎቹ ፍላጐትና እምቢተኛነት አገሩን በሚመለከት ወሳኝ እንዳይሆን ሲደረግ ነበር። አሁንም ቢሆን ይሀ አለ። በርግጥ አምባገነንና ጨቋኝ ገዥዎች የሚያውቁትና የሚገነዘቡት የራሳቸውን እምነትና ቋንቋ ብቻ ቢሆንም አልፎ አልፎ ግትር አቋማቸው እያባነነ የሚያነቃቸውና የሚያስጠነቅቃቸው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መከሰቱ አየቀርም።

የግዛት ሉአላዊነት ተከብሮ ተረጋግጦና ፀንቶ የሚኖረው ድንበርተኛ በሆኑ አገሮች መካከል በሚደረስ አለም አቀፍ ተቀባይነት በሚያገኝ ስምምነት ነው። ይህ ስምምነት በተለያዩ ታሪካዊ ፖለቲካዊና ምናልባትም ወታደራዊ ሰበቦች ሊስተካከል ይችል ይሆናል። ይህም ቢሆን የሁለቱም አገር ሕዝቦች በመሬታቸው ላይ የመወሰን የዜግነት መብታቸው ሳይዘነጋ ነው። ምክንያቱም ወደፊት ሊያጋጥም የሚችለውን ማንኛውንም ዓይነት ችግር መቅረፍ የሚቻለው በነዚሁ በሚመለከታቸው ዜጐች ተሣትፎ ስለሚሆን ነው።

ዜጐችን ያላሣተፈ የድንበር ስምምነት ሰላም መታጣትና ለጦርነት መቀስቀስ ያስጥርጥር ሰበብ ይሆናል። በድንበር አካባቢ የሚኖረውን ሕዝብ የዜግነት መብትም የመወሰን ኃይል ያለው





<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

የአካባቢው ነዋሪ እንጂ የፖለቲካ ሥልጣን የያዘው ገዥ መደብ ሊሆን አይገባም። ስለዚህ የወሰን መስመሮችን እንደገና በማስተካከል ጊዜ የተወሰነ የሕዝብ ክፍል ያለ ፍላጐቱና ያለ ጥያቄው የሌላ አገር ዜጋ እንዲሆን ቢወሰንበት ማን በዜግነት መብቱ ላይ ሊወስን ይችላል የሚል አመፅ ይጀምራል። ይህ እንግዲህ በግድ ተገዛ የሚልና በግድ አልገዛም የሚል የማይቋረጥ ቅራኔ ያስከትላል።

ይህ አነስተኛ ርዕስ የታሪክ ተመራማሪዎችንና የፖለቲካ ጠበብቶችን ስሜት ኮርኩሮ ሠፊ ጥናት እንዲጀመርበት መነሻ እንዲሆንና እኔ በሕይወት አጋጣሚ ያወቅኋቸውን እውነታዎች በመግለፅ ምን ያህል ትክክል እንደሆኑ እንዲረጋገጥ በማሰብ ነው። በመሆኑም በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር በተለይም በጐንደር ክፍለ ሃገር በሁመራ መስመር ያለውን ለማሣየት እሞክራለሁ።

የኢትዮጵያ ሕልውና ከታወቀበት ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ጀምሮ የውጭ ጠላቶች ጦር ሰብቀው ሠራዊት አሰልፈው ነጋሪት ጉስመው በተደጋጋሚ የመጡብን በዚሁ በሰሜናዊ ምዕራብ የወሰን በራችን ነበር። ግብፆችና መሃዲስቶች ያከናወኗቸው ሙከራዎች በቂ ማስረጃዎች ናቸው። በርግጥ በቀይ ባሀር በኩልም ሙከራና አልፎ ተርፎ ግዛት ያተነጠቅንበት ታሪክ ቢኖርም ነገሥታት «ከተት ሰራዊት» በማለት የዘመቱበት ይሀኛው መሥመር ይበልጥ ይወሳስታ ። አፄ ቴዎድሮስና አፄ ዮሐንስ ሕይወታቸውን ያጡባቸው ጦርነቶች በዚሁ መስመር በመጡ ጠላቶች ነው። የነገሥታቱን መስዋዕትነት ስንዘክር አብሮቸው የዘመተው የትግራይ፣የጐንደር፣የጐየጐጃም፣የወሎና የሸዋ ሕዝብ አፅሙ የተከሰከሰበት ደሙ የፈሰሰበት ቦታ መሆኑም የማይዘነጋ ነው።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከአምስቱ ዓመት የኢጣሊያ ፋሽስት ወረራና ጦርነት በኋላ ከስደት የተመለሱትም በዚሁ በር ተጉዘው ነበር። የውጭ አገራት አሣሾች ጐብኝዎችና አጥኚዎች ይገቡና ይወጡ የነበረውም በዚ በር ነበር። ኢትዮጵያውያንም ወደ ግብፅና እየሩሣሌም በኋላም ወደ አውሮፓ ሲመላለሱ የነበረው ይሀን መስመር ተከትለው ነበር። እነዚህን በዝርዝር ያልተፈተሹ የመንደርደሪያ ነጥቦች የጠቀስኩት ይህ በር ምን ያህል ተፈላጊነት እንዳለው አመላካች ይሆናል በሚል ነው።

## ሥም ከመቃብር በላይ

ከ1964 ዓ.ም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ወይም ከ1971ዓ.ም በፊት የነበረውን ሁኔታ ታሪክ ተመራማሪዎች ሲፈትሹት ብዙ የሚገለፅ ጉዳይ ይኖር ይሆናል። አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ በተነሱበት ጊዜ ከውስጥ የተነሱባቸው መሳፍንትና ትናንሽ ነገስታት ይህን ዓላማቸውን ሲቻላቸው በፊት ለፊት ውጊያ ሲጨንቃቸው በሸፍትነት እያመፁባቸው የተረጋጋ መንግስት እንዳይመሰርቱ አድርገዋቸው ነበር። ይህ ሁሉ አልበቃ ያላቸው መሳፍንትና ስመ-ነገስታት በመጨረሻው አስተባብረው ያመጡት የእንግሊዛውያን ጦር ወደ መሀል አገር መግባት የቻለው በዚህ በር ነበር። ቴዎድሮስ እጅ ሰጥቶ መማረክ ወይም በሽሽትና በስደት መሞት ታሪካቸውን እንደሚያጎድፈው ወታደሮቻቸውንም እንደሚያሸማቅቅ ስላወቁ ራሳቸውን ሰውተው አለፉ።

አፄ ዮሐንስ የሩቅ ዓላማቸው የኢትዮጵያ አንድነት ነበርና ቴዎድሮስን ሲያስቸግሩ የነበሩትን መሣፍንትንና ትናንሽ ነገስታትን በኋላ በሚደረግ ውጊያም ሆነ ዲፕሎማሲያዊ ዘዴ እንደሚያሸንፉ በማወቅ ቅድሚያ የሰጡት በሰሜን ምዕራብ በኩል ይታጣባቸው የነበረውን የደርቡሾች ትንኮሳ ማክሸፍ ነበር። የጉንደር የጎጃም የወሎና የሸዋ መሣፍንት እብጠትና ከፋፋይነት የቤት ውስጥ ጉዳይ መሆኑን በማመን የደርቡሾች ጉዳይ ግን ይዋል ይደር የማይባል ፍፁም የባዕድ ሀይል መሆኑን በመረዳት ያደረጉት ዘመቻ ነበር። ዮሐንስ እንዳሰቡት ደርቡሾችን አሸንፈው በሕይወት ወደ ዙፋናቸው አልተመለሱም። ይህን ታሪክ የተረከቡት አፄ ምኒልክም በዘመናቸው ከእንግሊዞች ጋር ባደረጓቸው የተለያዩ ውሉችና ስምምነቶች ይህ እየጠቀስኩት ያለው የወሰን ድንበር ተከብሮ ኖሯል።

በልጅ እያሱ አጭር የአገዛዝ ዘመንም ይሁን በንግስት ንግሥታት ዘውዲቱ ጊዜ በዚህ ድንበር በኩል የሚጠቀስ ችግር ሳይደርስ ዙፋኑ በአልጋ ወራሹ በተፈሪ መኮንን እጅ ገባ። ተፈሪ መኮንን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ከተባሉ በኋላ ያለው የኢትዮጵያ ታሪክ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ጥያቄ የሚያስነሣ ነው።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ይህን የሰሜን ምዕራብ የድንበር ሁኔታ በነበራቸው ሥልጣንና ኃላፊነት ከታሪካዊ መነሻው እስከራሣቸው ዘመን የነበረውንና ያለውን መረጃ በውል መገንዘብ





## ሥም ከመቃብር በላይ

ይገባቸው ነበር፡፡ ለነምድሮስ በውጭ ወራሪዎች መወጋትና መውደቅ ለዮሐንስ መስዋዕትነ ሰበብ የሆነው ይህ መስመር ታሪኩ ተጠብቆና መስመሩም ተከብሮ መኖር ሲገባው ይህ የዘነጉት የሚመስል ተግባር በዘመናቸው ተፈፅሞ ነበር። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ይህን ሕያ ታሪክ በመርሣት የኢትዮጵያ አካል ከሆነው መሬት ላይ ከፍለውና ቆርሰው ለሱዳን በችሮ ለመስጠት በድፍረት ተነስተው ነበር በዚህ ጉዳይ ላይ ለመደራደር የሱዳን ፕሬዝዳን የነበሩት ጀነራል ኑሜሪ አዲስ አበባ መጥተው በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሽልማት ድርጅት ሳ እንዲገኙ በማድረግ ከሻላሚው ንጉሥና ከተሸላሚዎች ጋር በ1964 ዓ.ም ፎቶግራፍ ተነስተ ታሪካዊ መረጃ እንዲሆን አድርገዋል።



የኢትዮጵያና የሱዳን መሪዎች በድንበር ጉዳይ ላይ ከተወያዩ በኋላ

## ሥም ከመቃብር በላይ

የኢትዮጵያ መተማና ሁመራ አካባቢዎች እስከ ሱዳን ድንበር ድረስ እጅግ ሠፊ የሆኑ ሜዳማ አገሮች ናቸው። መሬቶቹ ከባህር ወለል በላይ እጅግም ከፍ ስለማይሉ የአየር ጠባያቸው እጅግ ሞቃታማ ነው። በተለምዶ አገላለፅ በረሀማ ናቸው። ነገር ግን የኢትዮጵያ መተማና ሁመራ የተለዩ በረሀዎች ናቸው። መሬቶቹ በሙሉ ለእርሻ የሚያመቹ ናቸው። በሁመራ ወረዳ ውስጥ አቋርጦ ወደ ሱዳን የሚፈሰው ብቸኛው ጅረት የተከዜ ወንዝ ነው።

የመተማና የሁመራ መሬቶች እጅግ የሚደነቁት በሰሊጥ ምርት ነው። የአካባቢው ገበሬዎች ከዚህ ምርት ጠቀም ያለ ገንዘብ ስለሚያገኙ ሀብታሞች ናቸው። ጥጥ፣ ማሽላና በቆሎም በብዛት ይመረታል። የዕጣን ምርቱም ለውጭ ገበያ እስከመቅረብ የደረሰ ክምችት አለው። ነዋሪው ሕዝብ ባህሉ ሆኖ ዘመናዊና ጥንታዊ መሣሪያዎችን በየዓይነቱ የታጠቀ ነው። ሲያኮርፍ ለመንግስት የማይገዛና የማይገብር ሕዝብ ይሆናል። ነገር ግን ኢትዮጵያ የሚለው የአገር፣ የዜግነት የርሱነት መገለጫውና መለያው ኩራቱና ክብሩ ነው።

የተከዜ ወንዝ የኢትዮጵያና የሱዳን የተፈጥሮ ወሰን አካላይ ሆኖ ረዥም ርቀት ይጓዛል። ከተከዜ በስተምዕራብ ያለው የሱዳን ግዛት መሬት በኢትዮጵያ ካለው የሁመራና የመተማ መሬቶች ጋር በለምነት ሲነፃፀር ፍፁም ተቃራኒ ነው። የሱዳን ግዛት መሬት እፍኝ የሚሞላ ምርት አይሰጥም። ደረቅና አሸዋማ ነው። ሱዳናውያን ለከብቶቻቸው የሚሆን በቂ ግጦሽ ሳር የላቸውም። የቤት መሥሪያ እንጨት ስለሌላቸው ቤቶቻቸው ከጭቃና ከአፈር የሚገነቡ ናቸው።

ሱዳናውያን መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት በማያስችላቸው መሬታቸው ላይ የማያገኙትን ጠቃሚ ነገር ሁሉ ከኢትዮጵያ ለማግኘት ያልተቋረጠ ጥረት ያደርጋሉ። በግዛታቸው ውስጥ የሌለውን እንጨት ድንበር ጥሰው በጉልበት በመጠቀም ቆርጠው ይወስዳሉ። በሰፊው መሬታቸው ውስጥ የማያገኙትን የእጣን ምርትም በመሣሪያ ተማምነው ሰቅመው ይጭናሉ። በኃይል አጠቃቀም የሚታጀበውን ዘረፋቸውን ለበቀል ኢትዮጵያውያን የአካባቢው ነዋሪዎችም በተመሣሣይ ሁኔታ ወሰን ተሻግረው ከብት ዘርፈው ይመለሳሉ።





## ሥም ከመቃብር በላይ

በሁለቱ ድንበረተኛዎች መካከል የሚከሰተው የዜጎች ፀብ እየተባባሰ በመሄዱ የየአገሮቹ ባለሥልጣናት ግንኙነት በማድረግ ሁመራንና መተማን ለሱዳኖች ለመስጠት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴና በጄኔራል አልኑሜሪ መካከል የውሣኔ ስምምነት ላይ ይደረሣል። የዚህ ስምምነት ምስጢር ለጎንደር ሕዝብ ሲደርሰው የእርማጭሆ፣ የወልቃይት ጠገዴ ዙሪያ፣ የሁመራና የመተማ ነዋሪዎችን ቁጣ ይቀሰቅሣል። ሕዝቡ መሬቱንና እርስትንም ለታሪካዊ ባላንጣው አሣልፎ የሚሰጠውን ውሣኔ ከሰማ በኋላ አልገዛም በሚል መነቃነቅ ይጀምራል። ሱዳናውያን በሀይል ሊያገኙት ያልቻሉትን አገር በሰላም ሊረከቡ ሲዘጋጁ መመልከት ባለመቻሉ ወሰን እየተሻገረ ግድያ ይጀምራል። የሱዳን መንግስትም የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ስምምነቱን ወደተግባር እንዲለውጡና ሕዝቡንም እንዲያስታግሱ መጎትጎታቸውን ይቀጥላሉ። ስምምነቱ በፊርማ እስኪፀድቅ ድረስም ሕዝቡም መሬቱም የነርሱ ስላይደለ ዲፕሎማሲያዊ ጥረታቸውን ያጣድፋሉ።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት ሕዝቡን በሠላማዊ ዘዴ ከማስረዳትና ስምምነቱም እንዲተገበር ከማድረግ ይልቅ በጦር ሀይል ተጠቅሞ ዜጎቹን ማንበርከክና አሣልፎ መስጠት እንደሚሻለው በማመን ይህን አማራጭ ተጠቀመ። በዚሁ መሠረት በብ/ጄኔራል ይማም ነሹ የበላይነት የሚመራ አንድ ወታደራዊ ኮሚቴ ተቋቋመ። በተሰጠው ትዕዛዝም ብ/ጄ ይማም ነሹ በደንብ የታጠቀ አንድ የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ጦር ይዘው ሁመራ ይደርሣሉ። የሚመሩትን ዘመናዊ ወታደር በመተማመን ከሕዝቡም ጋር አንዳች ምክክር ሳያደርጉ፣ የተከሰተውንም የድንበር ላይ ግጭት ሣያበርዱ የየአገሮቹ መሪዎች የወሰኑትን ለመተግበር ሙከራ ያደርጋሉ።

ለሱዳን በሽልማት ወይም በነፃ በረከትነት ሊሰጥ ያስማቅማማት የተወሰነበት ኢትዮጵያዊ መሬት ሁመራ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ነበር። የሁመራ አካባቢ ቃላት በበቂ ሁኔታ ሊገልፁት የማይችሉት እጅግ ሞቃታማ በረሀ ነገር ግን እጅግ ሲበዛ ደግሞ ለም የሆነ አገር ነው። ሁመራ በተለይ በሰሊጥ ምርት ተስማሚነቱን ለተገነዘበ ሁሉ ቦታው የሚያጓጓና የኔ በሆነ የሚያሰኝ ነው። ሁመራ በሰብልና በመኸር ወቅቶች ለሚገበኘው ሰው አካባቢው የሀብት

## ሥም ከመቃብር በላይ

እጅግ በስፋት የተንጣለለው ሜዳ ትራክተሮች ያለ አንዳች ሳንካ የሚፈነጩበት የመስኖ ውሃ በተፈጥሮ የሰበት ሕግ እንደልብ የሚንደረደርበት አቅምና ጉልበት እስካለ ድረስ ያለማቅማማት ከረሀብና ከድህነት ኢትዮጵያን ለማዳን የሚችል የምርት መጠን ሊታፈስበት የሚችል ነው።

በዚህ የልማት የውጭ ጠላቶችና አጎራባች አገሮች ለዚሁ የተለየ ቦታ የሚነገበገቡትም በዚህ የልማት ብታኑቱ ርግጠኛነት ስላሳቸው ነው። የመተማን ልማት ሰበብ በማድረግ የሁመራንና የአካቢውን ልማት የመግቢያ ቀዳዳ በማድረግ የፕሬዚዳንት ኑሜሪና የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስምምነት ምስጢር ይታወቃል። ይህ ስምምነት የአያቶቻቸውና የአባቶቻቸው ደም የፈሰሰበት፣ እጣንት የተከሰከሰበት ኢትዮጵያውያንን ከዚያ በፊት ንጉሡ ነገስቱ ሪፖርት ተደርጎላቸው የማያውቅ አስፈሪ ሕዝባዊ ቁጣቸውን መቀስቀሱን ይሰማሉ። ኢትዮጵያውያን ዜጎች የአገራቸውን መንግስት ክህደት በመገንዘብ ለተደረገው ሕገ-መንግስትን የጣሰና የኢትዮጵያዊነት መብታቸውን የደፈረ ስምምነት ላለመገዛት ለጦርነት ዝግጅት ይጀምራሉ። የኢትዮጵዊነት መብታቸውን የደፈረ ስምምነት ላለመገዛት ለጦርነት ዝግጅት ይጀምራሉ። በድንበር አካባቢ በተለምዶ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ሁሉ ይገታሉ።

ከዚህ አስቀድሞ ግን በድንበር አካባቢ በተለምዶ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ሁሉ ይገታሉ። የሁመራና የመተማ አካባቢን ሕዝብ መራራ ቁጣ የሰሙት ንጉሡ ነገስት በጊዜው ለአገር ግዛት ሚኒስትሩና ለፖሊስ አዛዡ ትዕዛዝ ይሰጣሉ። በዚህ ትዕዛዝ መሠረት አንድ የፈጥኖ ደራሽ ኃይል በአስቸኳይ ወደአካባቢው እንዲላክ ያደርጋሉ። የፈጥኖ ደራሹን ኃይልና በኋላም የኮሚቴ አባላት የሉብትን ቡድን ከአካባቢው ኢትዮጵውያን ዜጎች ጋር ውይይት የሚያደርግ የኮሚቴ አባላት የሉብትን ቡድን በመምራት ብ/ጄኔራል ይማም ጉሹ ይላኩና ሁመራ ይገባሉ።

በመምራት ብ/ጄኔራል ይማም ጉሹ ይላኩና ሁመራ ይገባሉ። የፈጥኖ ደራሹ ኃይል በተቆጣው ሕዝብ ጉያ ስር ፋይዳ የሌለው መሆኑን አዛዡ ይገነዘባሉ። ብ/ጄኔራል ይማም ጎሹ የሚመራው ጦር በዘመናዊ ትጥቅና ሥልጠና በጊዜው የተዋጣለት ነበር። ቢሆንም የአካባቢውን ባህል ጨርሶ የማያውቅ ስለሆነ በምን ዓይነት ሕዝብ መሀል እንደሚገኝ አልተረዳም። ወታደሩ ሲታዘዝ ወደ ግዳጁ ከመንቀሳቀሱ በስተቀር የሁመራና የመተማ ሕዝቦች አቤቱታና ቅሬታም ምን እንደነበረ አያውቅም። መሪዎቹ የአለም አቀፉን ሕግና የአገሪቱንም ሕገ-መንግሰት ጥሰው የሚፈፅሙትን አያውቅም። በሕገ-መንግስቱ ላይ የተጻፈውን ሁሉ «. . . በፈቃዳችን የሰጠነው . . . » የሚለውን ሐረግ «. . . በፈቃዳችን የምንነጣው . . .» የሚል ተዛምዶ እንዳለው በማሰብ ሕጉን ሲያፈርሱት ሕዝቡ ይቀበለዋል ብለው መገመት አልነበረባቸውም።





## ሥም ከመቃብር በላይ

የጎንደር ሕዝብ በተለይም በወሰን አካባቢ የሚገኘው የወልቃይት ጠገዴ፣ የአርማጭሆ፣ የመተማና የሁመራ ነዋሪ ታሪክ ማጣቀስ ይጀምራል። «ሱዳናውያን አገራችንን ወርረው ከአጼ ቴዎድሮስና ከአጼ ዮሐንስ ጋር ተዋግተዋል። ብዙ ሺህ አያቶቻችን በጀግንነት ተዋግተው ይህን ድንበር አስከብረው አስረክበውልናል። አጼ ዮሐንስ በድንበር ማስከበሩ ላይ ሲዋጉ መስዋዕት ሆነዋል። አሁን የታሰበው ውሣኔ የዚህን ሁሉ ታሪክ መካድ ነው። ይህ ወንጀል ነው። ማንም በኃይል እንድንቀበለው ማድረግ አይችልም።» ማለት ይጀምራል። ነዋሪው ሕዝብ የፈጥኖ ደራሹን ጦር እንደልብ ማግኘት ባለመቻሉ ቅሬታውን እየገለፀ የተቃውሞ ወረቀት መበተን ይጀምራል።

ብ/ጄኔራል ይማም ጎሹ እየመሩት የወሰዱት የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ጦር የታሰበውን ግዳጅ ሊወጣ የማይችል መሆኑን ውለው አድረው ተገነዘቡ። ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ለአለቆቻቸው ሪፖርታቸውን በማቅረብ ድጋሚ መመሪያ ይቀበላሉ። በሱዳን ወሰን አጠገብ የሚኖረው የጎንደር ሕዝብ የጀመረው የአመፅ እንቅስቃሴ ለብ/ጄኔራል ይማም ጎሹ ችግር አልነበረም። ይልቁንም ይህን በሞቃታማና በረሀማነቱ የሚነገርለትን የሰሜናዊ ምዕራብ መሬት ሲመለከቱት የርሣቸውም ልብ ሸፈተ። ገደብ የሌለው የሰሊጥ፣ የጥጥ፣ የማሽላና የበቆሎ ሰብል ሊያሣፍሱቸው የሚችለው ለምና ድንግል መሬት አጓጓቸው። የሕዝቡ ቁጣ መልካም መከታ እንደሚሆናቸው አመኑ። ከጠቅላይ አዛዥ ከሌ/ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ጋር በመነጋገር ለሱዳኖች የታሰበውን መሬት እርሣቸው ወስደው በፖሊስ ሠራዊት ስም ለማልማት ተነሱ። ለእርሻ የሚያገለግሉ ትራክተሮችን፣ የመጓጓዣ መኪናዎችንና በዚህም ዓ ይነት በሰሜንም በመሀል አገርም የሚገኙ የወታደራዊ አዛዦችና ሲቪል ባለሥልጣኖች ወደ ሁመራ ጠቅሰው ለመግባትና በእርሻ ሥራ ላይ ለመሠማራት ሲዘጋጁ በ1966 ዓ.ም. የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ አመፅ አሸማቀቃቸው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ቦታ ሱመለከቱ ለምን ለባዕድ ይሰጣል እኛስ ሌላው ቀርቶ በግል አቅም እንኳ ልናለማው እንችል የለምን በሚል አመለካከት ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ለላኳቸው ባለስልጣኖች ያስረዳሉ። የብ/ጄኔራል ይማም ጎሹ አቀራረብ ለዘመኑ ሥልጣናቸው

<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

መራዘምና ከልማቱ የሚገኘው ፈሰስም ያጓጓቸው ንጉሥ ነገስትና ባለሟሎቻቸው ሌላ መራራ ጣጣ ውስጥ በመግባት አስቸጋሪ ሁኔታ እንዳይገጥማቸው ሀታቡን ይቀበላሉ። የሕዝቡን ቁጣ ለማብረድና እስተሣሰቡንም ለመቀየር ሲባል አንድ የፖሊስ የልማት ቡድን የእርሻ ሥራ እንዲጀምር ይባላል። ለዚህም የሚያስፈልገው የገንዘብና የትራንስፖርት በጀት ይመደባል። ብ/ጄኔራል ይማም ኅሹም ከግላቸው ገንዘብ ሣያወጡ በፖሊስ ሠራዊት የልማት ቡድን ሥም ሥራውን ይቀጥላሉ።

የመተማመንና የሁመራን አካባቢዎች ለሱዳን አሣልፎ ለመስጠት የነበረውን ድርድርና ስምምነት አጥብቀው እንደሚቃወሙ ይጠረጠሩ የነበሩት የቤጌምድርና ሰሜን እጠቃላይ ግዛት ፖሊስ አዛዥ ብ/ጄኔራል ሥዩም ገሠሠና አበሪዎቻቸው ናቸው የተባሉት ሁሉ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ይደረጋል። በመንግስት ሥራና ኃላፊነት ላይ ተቀምጠው የመንግስትን ነውረኛ አካሄድ የማይቀበሉ ሁሉ ከአካባቢው ተነስተው ምንም ስለሁኔታው የማያውቁ ወይም ቢያውቁም ተባባሪ ይሆናል ተብለው በሚታመንባቸው የፖሊስ አዛዦችና ሠራተኞች የሥራ መደቦች ይሞላሉ። የአካባቢውን ኢትዮጵያውያን እመለካከት የሚደግፉ በጎንደር ወስጥ የሚሰሩ የፖሊስ መኰንኖችና ወታደሮች ሣይቀሩ እንዲዛወሩ ተደረገ። ብ/ጄኔራል ሥዩም ገሰሰ ከጠቅላይ ግዛቱ ፖሊስ አዛዥነታቸው ተነስተው በምትካቸው ለአካባቢው አዲስ የሆኑ ኰሎኔል ተሾሙ። ይህ ሹመት በራሱ የጠቅላይ ግዛቱን የፖሊስ አዛዥ የማዕረግ ደረጃ ያልጠበቀና ለጊል ጥቅም ሲባል የተፈፀመ ሴራ እንደነበረ ያስረዳል።

ይህ የሽግግር ወቅት ሁኔታ ከመጠናከሩና ከመነሳቡ በፊት ለነብ/ጄኔራል ይማም ኅሹ ያገለግላል የተባለ አንድ የፖሊስ ሻምበል የሆነ መኰንን ጎንደር ከተማ ውስጥ በጥይት ይገደላል። ይህን ግድያ ያከናወነው "ደም ለመመለስ በራሱ የሚንቀሣቀስ ሰው" መሆኑም በስፋት ይወራል። ይሁን እንጂ ብ/ጄ ይማም ኅሹ እንደተመኙት የአካባቢው ፀጥታ በፈጥና ደራሹ የፖሊስ ጦር እየተጠበቀ እርሻቸውን እንዲቀጥል አደረጉ። ላይ ላዩን በሚታየው ሰላማዊ ሁኔታ በውስጥ የተረገዘው ቁጣና እልህ ጎልቶ አልወጣም። ንጉሥ ነገስቱና መንግስታቸው ከሱዳን አመራር ጋር አደረጉት በተባለው ስምምነት ሳቢያ ለፀጥታ ማስከበር ሲባል ከተላኩት የፈጥኖ ደራሽ አባላት መካከል ጥቂት የማይባሉ ባመፁ ዜጎች ተገደሉ። ኢትዮጵያውያን ቁጣቸው በማየሉ ወሰን እየተሻገሩ ሱዳናውያንን መግደላቸውን ቀጠሉበት ውሎ አድሮ ግን





<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

እጠቃላይ ሁኔታውን የተረዱ ፖሊሶች በሌ/ጄኔራል ድረሴ ዱባለና በብ/ጄኔራል ይማም ኅሹ ላይ የተቃውሞ ወረቀት መበተን ጀመሩ።

ለአገር ሉአላዊነት ሳይሆን ከልማቱ የሚገኘው ገቢ ያጓጓቸው ባለስልጣናት አካባቢውን በኢትዮጵያ መንግስት ግዛትነት ሥር እንዲቆይ ሰበብ ይሆናሉ። የልማቱ ተግባርና ወጤቱም ብዙ ኢትዮጵያውያን ባለስልጣናትን የሚማርክና የሚስብ ይሆናል። መሬትን ቆርሶ ለመስጠት የተወጠነው ሴራ ሲከሽፍ ባለሥልጣናቱ በልማት ስም የተሟሟፈ ዘረፋ ውስጥ ገቡ። ይህ ስግብግብነት የተረዱትን ተቃዋሚዎች ለመበቀል የፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ፣ ብ/ጄኔራል ይማም ኅሹን የፍርድ አጣሪ ኰሚቴ ሊቋመንበር አድርገው ሌሎች ተባባሪ ጄኔራሎችንና ኰሎኔሎችንም በአባልነት መደቡ። በዚህ መሠረት ብዙ ወጣት መኰንኖችና ወታደሮች እየተወነጀሉ ታሠሩ ወይም አገልግሎታቸው ሣይታይ ወደ ገጠርና ወደ በረሀ እንዲዛወሩ ተደረገ። አስፈላጊ ቁሣቁሶችን ለማሟላት በፀጥታ ማስከበሩ ስም ብዙ መቶ ሺህ ብር በጀት በማስፈቀድ ሥራ መጀመር ፈለጉ ከነዚህ መካከል የደርግ ወታደራዊ መንግስት የደህንነት ኰሚቴ ሊቀመንበረ የነበሩት ኰ/ል ተካ ቱሉ የተባሉት አንዱ ሰለባ ነበሩ። ይህ ለአብነት የቀረበ መረጃ እንጂ ሌሎች ብዙ መኰንኖችና ፖሊሶችም ነበሩ።

ብ/ጄኔራል ይማም ኅሹ ከአዲስ አበባ ወደ ሁመራ እየተመላለሱ መሥራት ከበዳቸው። የተጀመረው እርሻም በተቃውሞውና በአባላቱም አውቆ መለገም እንደታሠበው ሊቀጥል አልቻለም። ባለሥልጣናት የጎነጎኑት ሴራ በሕዝቡ የተባበረ ጥረትና ኃይል፣ ሱዳኖች ሁመራንና መተማን የመውሰድ ተስፋቸው ሣይሟላላቸው ቀረ። አካባቢውን በስምምነት አሣልፎ ለመስጠት ወግኑ ላይ የደረሰውም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት በ1966 ዓ.ም. በተቀጣጠለው ሕዝባዊና ወታደራዊ ንቅናቄ ከመንበረ ስልጣኑ ተባረረ። የሁመራ፣ የመተማና ዙሪያ ገባውን ያለው የጠረፍ ነዋሪ ሕዝብም ኢትዮጵያዊ ዜግነቱ ቀጠለ።

በዚህ አጭር ታሪክ ውስጥ አገርን አሳልፎ ለመስጠት ሴራ የሚሸረበው ከቤተመንግስት ሊነሣ መቻሉን፣ የሕዝብን የዜግነትና የንብረት መብት ለመወሰን የፖለቲካ መሪዎች አስነዋሪ ተግባራትን መፈፀማቸውን ሕዝብ ምን ጊዜም የማይደፈር ኃያልነቱን በማረጋገጥ የመንግስትን ውሳኔ ሊያሽርና ሊያስቀለብስ መቻሉን፣ በአገርና በወገን የሉአላዊነትና የአንድነት

<u>ሥም ከመቃብር በላይ</u>

ስም የግል ብልፅግና ተልዕኮን እንዴት እንደሚያፀናክል፣ የተለያዩ አጋጣሚዎች ፀንቶ የኖረውን የግዛት መስመርም እንደተጠበቀ እንዲዘልቅ ማድረጋቸውን ለማመላከት ተሞክሯል። የተጠቀሰው ታሪክና የተሰጠውም ሀተታ በቂ ላይሆን ይችላል። ቁምነገሩ ታሪኩ እንዳይዘነጋና ተድበስብሶ እንዳይቀር ማድረግ መቻሉ ነው። ዛሬስ ሁመራን፣ መተማን፣ አሚድላን፣ ጋምቤላን በተመለከተ ከሱዳን ጋር ምንም አይነት የመሬት መስጠትና መቀበል ድርድሮች የሉም ይሆን? የአማራ ክልል፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ የጋምቤላ ክልል የፖለቲካ መሪዎችና ኢትዮጵያውያን ዜጎች አይንና ናጫ የሚሆኑባቸው ስምምነቶች የሉም ይሆን ለማንኛውም እኔ መነሻውን አስጨብጫለሁ። ዝርዝሩን ሥራ እንዲቀጥሉበት ለተመራማሪዎች በአደራ አስተላልፋለሁ።





## ምዕራፍ 3

## ደርግና ጻር ደንበር

አጤ ኃይለ ሥላሴ ለስልጣን ሲሉ ብዙ ሰዎች እንደገደሉ ሁሉ ሀገራቸውን ለማበልጸግ መልፋታቸው መካድ የለበትም:: እኔ የትውልድ ሀገሬን ታሪክ በተመለከተ ብዛት ያላቸው ደራሲያን የጻፏቸውን መጽሐፍት ተመልክቻለሁ:: የኢትዮጵያ ደራሲያኑ የሚያንጸባርቁት ሰፈርተኛ መሆናቸው ነው:: ይህን አሲ የሚል ካለ ዛሬም እውነቱን አልተረዳም ማለት ነው:: አንድ ደራሲ በብዛት ምሳሌ የሚጠቀመውና የሚደጋግመው ባደገበት አካባቢ መሆኑ ባልከፋ እኔም እጠቀማለሁ:: ነገር ግን አንዱን ግለሰብ ሲረዳው ኑሮ አንድ ቀን አልችልም ቢለው ቀደም ሲል የተረዳውን በመርሳት ሲቀየምና የሚያውቀውን ታሪክ ሲክድ ይታያል:: አብረው በአንድ ጉዳይ ላይ ሲሰሩ ኑረው በሌላው ጉዳይ ላይ ሳይግባቡ ቢቀሩ ከዚያ በፊት የነበራቸውን ግንኙነት ሲያጠፉት ይታያሉ:: ይህ በኛው ደረጃ ባሉት ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ማዕረግ ደርሰው በነበሩ ሰዎች ሁሉ የሚፈጸም ጉዳይ መሆኑን በተለያየ ወቅት የተጻፉትን ታሪክ ማመሳከር ይቻላል::
ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ፍጹም ናቸው የሚሉ ደራሲያን በሁለት አይናቸው የማያዩ ናቸው:: ቅድሚያ አጤ ኃይለ ሥላሴ ቅዱስ ናቸው ከማለት በፊት በሌሎች ክፍለ ሀገር የተደረገውን ሻጥር ማወቅ ይጠይቃል:: አሁን ችግር የገባነው በአንዳይና አስተያየት የሚያዩ ደራሲያን አጤው ቅዱስ ናቸው ሲሉ ሌሎች ጥሩውንና መጥፎውን የሚያዩትን ዜጎች መጥፎውን ብቻ እንዲያዩ እያደረጉ መሆናቸውን ተገንዝቤአለሁ:: ስለዚህ አጤ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ታላቅ ሥራ የሰሩ ሊከበሩ የሚገባቸው አባት ሲሆኑ አጤ ኃይለ ሥላሴ ያጠፉትም ጥፋት እንዳለ መታወቅ አለበት:: ይህ መጽሐፍ የእርሳቸውን ጠንካራ ጎንና ደካማ ጎን ለመጠቆም የተዘጋጀ ሳይሆን በእርሳቸው እየተመካኙ ብዙ ዜጎች የተበደሉ መኖራቸውን ለመግለጽም ነው:: የእርሳቸውን ደካማ ጎን ባንድ ክፍል ጠንካራ ጎናቸውን ባንድ ክፍል በታሪክ አስደግፎ ለመጻፍ የሚቻል ይመስለኛል:: እግዚአብሔር ይመስገን የሁነድ ችግር ያለብኝ አይመስለኝም የግዜ እጦት የገንዘብ ችግር እንጂ ይህን ልለፈው ለወደፊቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ ልንመለስበት እንችል ይሆናል::

ርዕሠ ብሔር አማን አንዶም ከመስከረም 2 ቀን 1967 ዓም እስከ ሕዳር 14 ቀን 1967 ዓም ኢትዮጵያን በርዕሠ ብሔር ናቸው:: እርሳቸውን ወደ ሥልጣን ያመጣቸው ደርግ 120 አባላት ያላቸው ወታደራዊ ቡድኖች ሲሆኑ ከስብሰባቸው መካከል ከእነሱ በላይ የሆነ ባለስልጣን በእርሰ ብሔርነት እንዲመረጥ ብቁ ሰው ፈልጉ ሲባል ስማቸውን ለደርጉ ያቀረቡ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ናቸው:: ጄኔራል አማን ቢሆኑም ጥሪውን በጸጋ ተቀብለዋል:: ነገር ግን እርሳቸው የአገር አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ

አልፈለጉም። ዛሬ አንዳንድ ሰዎች ጀኔራሉ ስህተት የለባቸውም ደርጉ ለመግደል ስለፈለገ እንጂ የሚባለው ከእውነት የራቀ መሆኑን የሚያብራሩ ብዙ ሠነዶች ማሰባበስ ይቻላል። ሻዕቢያ አስመራ ከተማን ለመያዝ የቀረው ትንሽ ኪሎ ሜትር እንደነበር አይዘነጋም። የሻዕቢያ ብርታት ሊያገኝ የቻለው በእርሳቸው ተጠልሎ ነው። ደርጉ ወታደር ወደ አስመራ ይላክ ሲል ርዕሠ ብሔር አማን አይላክም እያሉ ባለብት ወቅት ሻዕቢያ አስመራን ለመያዝ ተቃረበ። አገር ተደፈረ ምን ይደረግ ሲባሉ እርሳቸው "ሁሉንም ነገር ለእኔ ተውት" ይላሉ። በዚህ ምክንያት ወደ ደርጉ የስብሰባ አዳራሽ ይምጡ ሲባሉ እርሳቸው መሄድ አልፈለጉም። በዚህ ወቅት በሽምግልና አልመጣም ሲሉ ደርጉ ወጊ ጦር ልኮ አስገደላቸው። የርዕሠ ብሔር አማን ታሪክ በአጭር በዚህ ተደመደመ በሥልጣን የቆዩት 72 ቀን ሲሆን ከተራ ወታደር ጀኔራል ማዕረግ ያበቁአቸውን አጤ ኃይለ ሥላሴን አንድም ቀን ከእስር ቤት ሊጠይቋቸው አላሰቡም። አጤው ጅኒናር አማን አይጠይቀንም እያሉ ይናገሩ ነበር።

የሰዩም ጣሰው ማስታወሻ <u>የንጉሠ ነገሥ</u> በተባለው መጽሐፍ 103 "ጅኒናር አማንን ጥራልኝ እንዴት እርሱ እንኳ አይጎበኘኝም ወይ? እባካችሁ ጥሩልኝ ይሉ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል። ርዕሠ ብሔር ተፈሪ ባንቲ! ከኤርትራ ደርጉ ጠርቶ የኢትዮጵያ ርዕሠ ብሔር መርጠነዎታል ብሉ ሾማቸው። እርሳቸው ሹመቱን ተቀብለው የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ ጥረት አድርገዋል። ወቅቱ የሱማሌ ወረራ ጅምር ሲሆን በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ አገራቸውን ዳር ደንበር ለማስከበር ጥረት አድርገዋል። ታዲያ እርሳቸው ዘመናዊ ወታደር ብቻ ሳይሆኑ ዘመናዊ ምሁርም በመሆናቸው የኢሕአፓን አቀዋም ደግፈዋል በመባል በደርጎች በኩል አልተወደደላቸውም በዚህ ምክንያት ደርጎች ጥር 29 ቀን 1968 ዓም ገደሏቸው። መልካም አገር መሪ የሚወጣቸው እንደሚሆኑ ብዛት ያላቸው አስተያየት ሰጭዎች ይገልጻሉ።
በእርሳቸው የሥልጣን ዘመን አገርን ለመበተን ከውስጥ እስከ ውጭ የታቀደውን ኃይል ለመቋቋም ጥረት ማድረጋቸው አይዘነጋም። በእርሳቸው የመንግሥት ዘመን ዛሬ ያለችው ኢትዮጵያን ለማስከበር ጥረት ሲያደርጉ የጅቡቲን ሁኔታ የኃይል ድጋፍ አስፈላጊ በመሆኑ መውሰድ አለብኝ ብለው ለመጠየቅ ሙከራ አላደረጉም። አንዳንድ የታሪክ ሰዎች "የጅቡቲን ነፃነት መቀበል አልነበረባቸውም። ቢቀበሉም የባህር በር ጉዳይ ለወደፊቱ ኢትዮጵያ የምትጠቀምበትን ሁኔታ ማስተካከል ነበረባቸው" የሚሉ አሉ። ቅኝ ገዥዎች ሱማሌን ሲለቁ ትተውት የሄዱት መርዝ ታላቋ ሱማሌን እንዲያጠናክሩ መክረው ለቀዋል። በዚህ ወቅት በአጤው ዘመን ሱማሌ ልትወር መጥታ ተደብድባ ብትመለስም ደርግ ሥልጣን በያዘ ማግስት ቤተ መንግሥቱ ባዶ መስሏት ከአረብና ከአደጉ አገሮች በተቸረችው የጦር መሳሪያና የገንዘብና ቀሳቀስ ዳብራ ኢትዮጵያን ወረራ ጀመረች። በዚህ ወቅት ወራሪው የሱማሌ መንግሥት የኢትዮጵያ እስላም ምዕመናን እንዳይተባበር ቅስቀሳ ቢያደርግም የእስላም ሃይማኖት ምዕመናኑ የአገር የማዳን ጥያቄ እንጂ የሃይማኖት ጉዳይ አለመሆኑን አስመሩበት። የእምነት መሪዎች ለየምዕመናናቸው ጥሪ አቀረቡ። ለታሪክ ዋቢ የሚሆን መጽሐፍ አዘጋጁ። ይህን መጽሐፍ የግራ ቀኙን



የሃይማኖት መሪዎች ንግግር ያከተተ ሲሆን የእስላም ሃይማኖትን ወክለው ከተናገሩት ከመሐመድ አወል አሕመድ ንግግር ልጥቀስ።

ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ <u>በአገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለያየንም</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 32 "ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የላቀ አስተሳሰብና ቆራጥ ወኔ የረጋ መንፈስና ኩሩ ሞራል ያለው መሆኑን ያልተከሰተላቸው ወገኖች በጎሳ በቋንቋና በተለይም በሃይማኖት አሳበው በመካከሉ ለመግባትና አንድነቱን ለማፍለስ ሙከራ በማድረግ ላይ ናቸው። ግን አይችሉም። እውነት ቅድመ አብዮት በነበረው የአድልዎ ዘመን ጥቂቶችን ለማሳመን ችለው ይሆናል። ምክንያቱም አማኞችም ቢኖሩ ከአብዮቱ በፊት የነበረው ሁኔታ ሊያሳምኑን በቃ ለማለት የሚያስችለው ሲሆን ከአብዮቱ ወዲህ ግን ሁኔታዎች እንደተሻሻሉ በመምጣታቸው ወደፍጹምነት የሚደርሱ የእኩልነት ብርሃን በፍጥነት እየተለወጠ ነው። ጠላቶቻችን የሀገራችንን ሕልውና ለማጥፋት ቢፍጨረጨሩ ኩቶ አይችሉም፥ትናንትም እንኳን አልቻሉም ዛሬም አይችሉም ወደፊትም አብዮታዊት ኢትዮጵያ የማትበገር ለመሆንዋ እንደ ቀለበት የከበቧት ጠላቶች እርማቸውን እንዲያወጡ ሰፊው ሕዝብ ትምህርት እየሰጣቸው ሲሆን የዓለም ሕዝብ የዚህን ቆራጥ ሕዝብ የሞት ሽረት ትግል በአድናቆት እየተከታተለ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ሱማሌ የኢትዮጵያን መንግሥት ድል እንድታደርግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ በዚያን ወቅት አብዮተኛ ነን ባዮች ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በተለይ ወያኔ፥ኢሕአፓ ኢዲዩ አነግ ሌሎችም ተባባሪ ነበሩ። ኢዲዩ በተለይ በጎንደርና በትግራይ ይንቀሳሰቅ ስለነበር የኢትዮጵያ ሕዝብ የርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለማርያምን ጥሪ ተቀብሎ እንዳይዘምት ጥረት ያደርግ ነበር። ይህ ጸሐፊ ጎንደር ክፍለ ሀገር ጎንደር ዙሪያ አውራጃ የታች አርማጭሆ አባት አርበኞች ወደ ጎንደር ሲጓዙ በኢዲዩ እንዳይዘምቱ ሲከለከሉ ተመልክቷል። የኢዲዩ ልጅ የኋላው ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ አንድነት የተባለው ድርጅት ሳይቀር ሱማሌ ገብቶ እንደነበር ተጽፏል።

ኮሞዶር ጣሰው ደስታ <u>የኢትዮጵያ አንድነት ትዝታና ትግል</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 179 "እኔ እ.ኤ.አ.ነሐሴ 21 ቀን 1984 ዓም ሞቃዲሾ ገባሁ። ከነሐሴ 22 ቀን ጀምሮ ከልዩ ልዩ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር እየተገናኘን ስለድርጅታችን ዓላማና ግብ በኢትዮጵያ በሱማሌ ሕዝብ መካከል ሰላም ለምን አስፈላጊ እንደሆነና ስለአገራችን ጠቅላላ የፖለቲካ ይዘት ሳስረዳና ጥያቄ ስመልስ ከሰነበትኩ በኋላ በመጨረሻ ከፕሬዚዳንት ሲያድ ባሬ ጋር ተገናኝቼ በሞቃዲሾ ራዲዮ ጣቢያ ለመጠቀምና ቢሮም ከፍተን በሱማሊያ የሚገኙትን የኢትዮጵያን ስደተኞች ለማስተባበር እንድንችል ማስፈቀድ ቻልኩ" ሲሉ ጽፈዋል። የኢትዮጵያ የተማሪዎች ማሕበር ከተመሰረተ ጀምሮ በእኔ እምነት ለኢትዮጵያ የተሰራው ልማት ሳይሆን ኪሳራ ነው። ተማሪውን ያሳተፈው ኢሕአፓ ሱማሌ በኢትዮጵያ ላይ የምታደርገውን ወረራ የደገፈ መሆኑን ጽፈውልናል። ዛሬ ኢሕአፓ ተሳስቶ ነበር ብሎ መጻፍ ቀደም ከደርግ ጋር የሚያቆራኝ ሲሆን አሁን ደግሞ ከወያኔ ጋር አቆራኝቶ ባንዳ ያሰኛል። ነገር ግን ታሪክ በመሆኑ ከመጻፍ አንቦዝንም።

ጌታቸው አማረ ኢትዮጵያ ሪቪው መጽሔት ሚያዝና 1985 ዓም ወይም 1993 "ኢሕአፓ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ነበር የተሰለፈው ከተባለ የሶማሌ ጦር አብዛኛውን ሐረርጌን ባሌንና ሲዳሞን በቁጥጥር ስር እያዋለ እያለ ለምን ነበር ኢሕአፓ በመሃል አገር ይህንን ወረራ ለመከላከል የሚሯሯጡትን ወገኖቻችንን ባንዳ እያለ ሲገድል የነበረው" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ከዚህ በላይ የተነበበው ንባብ በኢሕአፓ ላይ ዜጎች የነበራቸውን ትዝብት ነው። ከዚህ ዝቅ ብሎ ደግሞ ኢሕአፓን ሲመሩ ከነበሩት መካከል የተጻፈውን በጥሞና መመልከቱ ይጠቅማል።

ክፍሉ ታደሰ ያ ትውልድ ቅጽ ሁለት ገጽ 128 "ደርግ ለሕብረት ግንባር ያደረገውን ጥሪ ብርሃን መስቀል በሙሉ ልቡ ተቀብሎታል። እንደሱ ሃሳብ ከሆነ ኢሕአፓ በዚህ ወቅት ታሪካዊ ድርድር አድርጎ ከደርግ ጋር አንድ ዓይነት ሕብረት መፍጠር ይኖርበታል። ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስ መነሻ ያደረገው ስለወቅቱ የኢትዮጵያ ሁኔታ ያቀረበው ትንታኔ ነበር። በብርሃን መስቀል አስተያየት በምስራቅ በኩል የሶማሊያ መንግሥት የአገሪቱን የግዛት አንድነት አደጋ ላይ ጥሎታል። በምዕራብ ቀኝ ዘመም የፖለቲካ ኃይሎች እንደ ኢዲዩ ያሉት አብዮታዊ ግንባር ጠልፎ ለመጣል ሙከራ እያደረጉ ይገኛሉ። የኢኮኖሚ ሁኔታውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ሂዶ ሐገሪቱ እየፈረሰች ስለሆነ በእሱ አስተያየት አገር ሳይኖር አብዮት ማካሄድ አይቻልምና ከደርግ ጋር አንድ ዓይነት ሕብረት መፍጠር ግዴታ ይሆናል" ሲሉ አቶ ብርሃን መስቀል መናገራቸውን ልዩነቱ ከዚህ መጀመሩን ጽፈዋል።

ባቢሌ ቶላ አንድ ትውልድ ለመምተር ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 149 "እጅግ ከባድ የነበረው ውስጣዊ ችግር የተቃጣው ደርግ ኢሕአፓ ላይ ጦርነት ካወጀ በኋላም እንኳ ደርግ ላይ ትጥቃዊ ተቃውሞ መደረግ የለበትም ባሉት ጌታቸው ማሩና ብርሃን መስቀል ረዳ ሁለቱ የአመራር አባላት ነበር ኢዲሕንና የሶማሌን ወረራን ለመከላከል ፓርቲው ከደርግ ጋር የሕብረት ግንባር ለመፍጠር መሞከር አለበት ብለው ተከራከሩ። ከሁለቱ በደንብ የታወቀው ብርሃን መስቀል ረዳ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል። በነገራችን ላይ ወያኔዎች በዚያን ወቅት የኢትዮጵያ ዳር ደንበር በሱማሌ እንዲደፈር ተባባሪ የነበሩ መሆናቸው አይዘነጋም።
ገብረ መድህን አርያና አብርሃም ያየህ፣ የወያኔው ታላቅ ሤራ በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ ክፍል 1 እና 2 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 127 "በሱማሌ ጦርነት ጊዜ ወያኔው በነበረው አቋም ላይ የምገልጸው አለኝ። በዚያ ወቅት በትግርኛ ወያኔው አንድ ጹሑፍ አውጥቶ ነበር። የሱማሌና የኢትዮጵያ ጦርነት ምን ይመስላል? የሚል። ወያኔ አንድ አቋም ወሰደች። ሱማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር የምታደርገው ጦርነት ፍትሐዊ ነው ብላ ኦጋዴን የሱማሌ ነው አለች። ጹሑፉ ወጣ እኛም ሕዝቡን ለማስተማር ተንቀሳቀስን። ይህ የመጀመሪያው ከባድ ጦርነት በነበረበት ከ1969 እስከ 1970 መጋቢት ወር ድረስ ነው። የሱማሊያ ጦርነት ፍትሐዊ ጦርነት ነው ወረራ አይደለም። ኢትዮጵያ ተስፋፊ እንደመሆኗ መጠን በኃይል የያዘችው መሬት ነው አለች። ወያኔ ለዚህም ውለታዋ ከሱማሊያ መንግሥት ብዙ የጦር መሣሪያዎች አግኝታለች።



እርዳታው በሱዳን ዙሮ ነው ትግራይ የገባው" ሲሉ አቶ ገብረ መድህን ተናግረዋል። እነ ኦነግና ሌሎችም ድርጅቶች መስሪያ ቤታቸውን መቃድሾ ያደረጉና በሶማሌ መንግሥት የሚረዱ እንደነበሩ አይዘነጋም። ጠንካራ መሪ ለድል ያበቃል እንደሚባለው በዚህ ወቅት ርዕሠ ብሔር ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሱማሌን የአስር አለቃ መለዮ ልብስ ለብሰው ተዋግተዋል።

ደመቀች መንግሥቱ ኢትዮጵ መጽሔት ቅጽ 7 ቁጥር 72 ሐምሌ 1997 ዓም ገጽ 32 "ሐረር ከተማ የደረሱት መኮንን የጊዜያዊ መንግሥቱ ከፍተኛ ባለሥልጣን መሆናቸውን ሰማን። ቆየት ብሎ ሁኔታውን ስናጠና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም እንደሆኑ ማረጋገጥ ቻልን። ጠላት አፍንጫህ ላይ ቆሞ እያናፋ ቁጭ ብለሃል!በየአልጋህ ላይ ወጥቶ ሚስትህን እስኪቀማህ ነው የምትጠብቀው? እያሉ የጦር መኮንኖቹን ይቆጡ ነበር። አንዳንዶቹ ይህቺ የአስር አለቃ ማዕረግ የለበሰችው ቆፍጣና ዕኮ መንጌ ናት እያሉ ያንሾካሹካሉ። ወዲያው እሳቸው ከሠራዊቱ ጋር ወደ አፍደም ግንባር ተንቃነቁ። ከሁት ቀናት በኋላ አብዮታዊ ሠራዊት ካራ ማራን ከጠላት መዳፍ ያስለቀቀ መሆኑን የሚያበስር ዜና ሐረር ከተማ ደረሰ" ሲሉ ሉሞ ተራ ተራ የተሰኘችውን ዘፈን ያዜሚት ድምጻዊ ተናግረዋል። ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ከሱማሌ ጦርነት ላይ መዋላቸውን ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ክደት በደም መሬት በተባለው መጽሐፋቸው ጽፈዋል። ይህ ጀግንነታቸው ግን ለ1983 ዓም ሳይሆን ቀርቷል ወደ ነበርኩበት ልመለስ።

እርሳቸው ዓለም አቀፍ ጦርነት እየተደረገባቸው ደንበር ለማስከበር ጥረት አድርገዋል። ሱዳን ሳለን የሚነገር ታሪክ ነበር። እርሳቸው ሱዳንን በግልጽ ሲጎበኙ ሲመጡ ከጃፋር ንበሪ ጋር ስለ ኢትዮጵያ ስደተኞች ጉዳይ ሲነጋገሩ አሉ ተብሎ የተነገረው "የኢትዮጵያ ስደተኞች ሱዳን አሉ ብለን የምናምነው ፖርት ሱዳንና ካርቱም ያሉትን እንጂ ገዳሪፍ ከሰላና ደባዚን ያሉትን ስደተኝ ናቸው አንልም አሉ" የእርሳቸው አባባል ምን ያህል ጃፋር ንበሪ እንደገባቸው ባይታወቅም በርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አባባል ግን ያሉት ከሀገራቸው ነው ለማት ነው። በጎንደርና በጎጃም በኩል ከሱዳን የሚያደናብረውን ጠረፍ በተመለከተ መንግሥት ለማስጠበቅ ጥረት ሲያደርግ ድርጅቶች መጠጊያ ስላደረጉት ሱዳኖች ሲጠቀሙበት ኑረዋል። ይህ ጸሐፊ በ1975 ዓም ሱዳን ሲገባ ቀድሞ ኢትዮጵያውያን ያርሱት የነበረውን ግራር ውኃ ድረስ ሱዳኖች ያረሱትን እህል ሲሰበስቡ ተመልክቷል። በሰኔ መቀር እንጨቱን ዙሪያውን ከርክረው ቅርፊቱን አስለቅቀውት ይከርማል። ይህ ተቆልሎ የከረመውን በሕዳርና በታህሳስ እጣን ይሆናል። ሱዳኖች ይህን እየቀረፉ ሲጭኑ ተመልክቷል። የበርሃ ሽመል የምንለውን ቅርቅሃ ቆርጠው አድርቀው እነሱ ሉሪ በሚሉት የጭነት መኪና ሲወስዱ ተመልክቷል። የቤት መስሪያ እንጨት ይወስዳሉ። የቤት መስሪያ እሳር ይወስዳሉ። የበርሃውን ንብ ማር ቆርጠው ሲጠቀሙበት ተመልክቻለሁ። በዚህ ወቅት ግጨው ተብሎ ከሚጠራው በርሃ የኢሕአፓ ሰራዊት ነበር።

ሱዳን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሆነ መንግሥት ይፈራል። በተለይም ርዕሠ ብሔር መንግሥቱን ይፈራቸው ነበር። አንድ ቀን ከሰላ እና ገዳሪፍን ሊይዝ ይችላል የሚል ፍራት ነበራቸው። በመንግሥት ደረጃ ሳይሆን ተራው ሕዝብ ሳይቀር ይፈራቸዋል። አንድ ቀን ከተባበሩት መንግሥታት ጽሕፈት ቤት የአሜሪካ ምዝገባ ይደረጋል ተብሎ የሰማው ላልሰማው በየምግብ ቤቱ ላሉት ኢትዮጵያውያን ተነገረ። ታዲያ ኢትዮጵያዊ ሽርጡን ሳያወልቅ ሁሉም ወደ ጽፈት ቤቱ ሲሮጥ ኢትዮጵያዊ አንድ ሱዳን ቁሞ ተመለከተና "ሐበሺ ማልኩም +ሐበሽ ምን ሆናችሁ" ብሎ ሲጠይቀው "ያ ሃጅ መንግሥቱ ጃ" ሃጅ መንግሥቱ መጣ" ብሎ ሲነግረው ሱዳናዊው ለሌሎች ሱዳን "ያ ጀማ ያ ሽይጣን መንግሥቱ ጃ" እናንተ ያ ሳይጣን መንግሥቱ መጣ እያለ ጀለብያውን ሰብሰብ አድርጎ በጥርሱ ነክሶ ሲሮጥ ሌሎች ሲሮጡ ዋሉ።

በ2000 ዓም የጭልጋው አራሽ እንደፋራሽ ጋር በሱዳንና በኢትዮጵያ የደንበር ጉዳይ ላይ ስንወያይ "ሱዳኖች ልብ ኑርአቸው የኢትዮጵያን መሬት ሊደፍሩ አይችሉም። ነገር ግን ወያኔ ኢትዮጵያውያንን አኮላሽቶላቸው እንጂ ደበደቡን" ሲሉ ሀዘናቸውን ገልፀዋል። ሱዳኖች በኢትዮጵያ መሬት ላይ አርሰው መብላት የጀመሩት ቀደም ብሎ ሲሆን ድርጅቶች ፈቅደውላቸው ነው ተብሎ ይወራ ነበር። በሰኔ 1983 ዓም የኢዲዩ ወሳኝ የነበሩ አቶ ታመነ አልያም ሊንን የተባሉ በዚያን ወቅት የትግራይ ልጆች ጠቅልለው ወያኔን ሲደግፉ አቶ ታመነ፤ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ሁነው ያለቅሱ ነበር። ዛሬ የት እንዳሉ አላውቅም ነገር ግን በዚህ ወቅት እርሳቸው አንድ ነገር ሲናገሩ ሰምቻለሁ። አቶ ታመነ "አንድ የሱዳን ባለስልጣን የድርጅት መሪዎች ጋር የተስማማንበት ጉዳይ አለ። ያም ሥልጣን ሲይዙ መሬት ሊሰጡን ፈርመውልናል ብሎ ነገረኝ። የየትኛው ድርጅት መሪዎች መፈረማቸውን ብጠይቀው ሳቀብኝ" ሲሉ ነግረውኛል ደርግ ዳር ደንበር ለማስጠበቅ ጥረት ማድረጉ እንደተጠበቀ ሁኖ ሱዳኖች ደግሞ ከግል ጥቅማቸውና ፀረ ደርግ አቅዋም ከመያዛቸው የተነሳ በደርግ መንግሥት ላይ አሲረዋል።

ርዕሠ ብሔር ጀኔራል ተስፋዬ ገብረ ኪዳን የኢትዮጵያ ርዕሠ ብሔር የሆኑት ከግንቦት 13 ቀን 1983 ዓም እስከ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም የ7 ቀናት መሪ ናቸው። በእርግጥ ዛሬ መተቸት እንችላለል። በእነዚህ በ7 ቀናት ውስጥ ምን ማድረግ ይችሉ ነበር? ለሚለው ጥያቄ ሌላው ቢቀር የዓለም ሕዝብን ጥሪ አድርገው አዲስ አበባን ወያኔ እንዳይዛት የማድረግ አቅም ነበራቸው ይላሉ። አዲስ አበባ የዓለም ከተማ ስለሆነች ሳይገቡ መደራደር እንጀምር ቢሉ ሌላው ቢቀር ለመለዮ ለባሹ ደህንነት መስማማት ይችሉ ነበር ተብሎ ይወራል። አበው ሲተርቱ "ክበሮ በሰው እጅ ታምሪያለሽ" እንደሚሉት ይሆናል። እርሳቸው በ7 ቀን ውስጥ ሊፈይዱት የሚችሉት ተግባር ለእኔ አይታየኝም። ወያኔን አዲስ አበባ አትግቡ ቢባሉ ገልብጠው መግባታቸው አይቀርም ነበር። ምክንያቱም ኃያሉ መንግሥት አረንጓዴ መብራት አሳይቷቸው ስለሆን ሽምግልናውን አይቀበሉትም። ያም ሆነ ይህ በታሪክ የ7 ቀን መሪ ይቅርና በኢትዮጵያ 6 ሰዓት መሪም ከነገሥታት ተርታ ተጽፎ ያለ ስለሆነ በዚሁ ለትውልዱ ለማስተዋወቅ ያህል ነው። እርሳቸው እርስ ብሔር ከመሆናቸው በፊት ተራ ወታደር መከላከያ ሚኒስተር ማዕረግ አገራቸውን ያገለገሉ ናቸው።



## ምዕራፍ 4

## ዳር ደንበር በርዕሠ ብሔር አቶ መለሰ ዜናዊ ዘመን!

ከላይ እንደተጠቀሰው ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ነበረች! ታዲያ በአንዳንድ ሥልጣን በናፈቃቸው ግለሰቦች ሰበብ ደመች። ከዚያ አልፋ ወደ ርዕሠ ብሔር አቶ መለሰ ዜናዊ ዘመን ደረሰች። እርሳቸው ግማሽ ኤርትራዊ የሆኑ በወያኔ ኮት ላይ ኢሕአዴግን ካባ ደርበው ወደ አዲስ አበባ ሠራዊታቸው ለአንድነት ሳይሆን ለልዩነት ተመመ። የርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም መንግሥት ዓለም አቀፍ ጥሳቻ ተደርጎበት እንክትክቱ ሲወጣ ወያኔ ኢሕአዴግ ኢአዲስ አበባ በመግባት የኢትዮጵያን አንድነት አፈረሰ። እርስ ብሔር አቶ መለሰ ዜናዊ፤ ኤርትራ በተሉ መገንጠል አለባት ብለው ለተባበሩት መንግሥታት ደብዳቤ ጻፉ። በዓለም ላይ ብዙ ደካማ ስራ በአገራቸው የሰሩ መሪዎች ነበሩ። ነገር ግን እንደ አቶ መለስ ዜናዊ የሚበዛበት የሚኖር አይመስለኝም። አገሬን አልፈልግም የሚል መሪ ያለ እርሳቸው አልተወለደም። ምናልባት ሰይጣን እንጂ ፍጡር ይህን ስራ አይሠራውም።

ልጅ ሚካኤል ዕምሩ ኢትእጽ መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 054 ታሕሳስ/ጥር 1996 ዓም ገጽ 11 "ኢትዮጵያ በሕግ የተረጋገጠላትን የባሕር በር ተነጥቃ መኖር የለባትም" ሲሉ ተናግረዋል። በደርግ የመጀመሪያ ወራት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አስጠንቅቀዋል። ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን ሲያጠፉ የተነሱ ናቸው። ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ በጣም የሚገርመው ደግሞ የአፋር ሕዝብ አሰብ አስተዳደር "እኛ ኢትዮጵያዊ እንጂ ኤርትራዊ አይደለነም" እያለ ኢትዮጵያዊነቱን ለማስጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ትግል በሚያደርግበት ወቅት እናንተን አልፈልጋችሁም ኢትዮጵያዊ አይደላችሁም ብለው በግድ በኤርትራ እንዲተዳደሩ ማድረጋቸው ሰይጣንነት እንጂ የሰው ልጅነት አይደለም።

ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ዜጋ መጽሔት 5ኛ ዓመት ቁጥር 2 ጥቅምት 1996 ዓም ገጽ 23 "አሰብ የኤርትራ አካል ነች የሚለው በመጀመሪያ የተደመጠው ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዋሽንግተን ለዓለም ጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል። የአሰብን አስተዳደር የአፋርን ሕዝብ ጉዳይ በተመለከተ ከዚህ በፊት አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች! የተባለው መጽሐፍ ጽፌ ለአንባቢ ማድረሴ ይታወቃል። አንባቢያን አሰብ አስተዳደር ከቀድሞ ጀምሮ ኤርትራ የክርስትና ስም ከማግኘቷ በፊት ስማ ባሕረ ነጋሽ ትባል ነበር። በዚህ ወቅት ኤርትራና አሰብ አስተዳደር በአንድ የተዳደሩበት ወቅት ፈጽሞ የለም።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ረቂቅ በተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀ የሕገ መንግሥት ረቂቅ ሚያዝያ 25 ቀን 1986 ዓም ገጽ 1 አንቀጽ 2 "የኢትዮጵያ

የግዛት ወሰን የፌዴራሉን አባሉች ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት የተወሰነው ነው" ይላል። ይህ ሕገ ችግር እንዳለበት ከሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም በቀር ማንም የሕግ ምሁር ትክክል አይደለም ብሎ እንኳን ቀደም ዛሬም የደንበር ችግር ከተፈጠረ ጀምሮ የተቸው የለም። በእርግጥ በአንቀጽ 39 ላይ ያልተጻፈ ጽሁፍ የለም። ችግሩ ያለው ራሱ ይህ ሕገ መንግሥት የተረቀቀበት ቀን አንዱ ነው። ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓም የውጫሌ ውል የተፈረበመት እስከ ዛሬ ችግር የተዘራበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሙ እንደጎርፍ የፈሰሰበት የአገሪቱ አካሏ ይበልጥ እየጠበበ የመጣበት መንስኤው የውጫሌው ውል የተፈረመበት ቀን ሲሆን ቀስ በቀስ ሌሎች ኤውሮፓ አገሮች የኢትዮጵያን ዳር ለዳር ከበው ያጣበቧት ይህን ተገን በማድረግ ነው። ይህን ቀን የምናስታውሰው ኢትዮጵያ ልትደክም የቻለችበት ቀን መሆኑን ነው። ለዚህም ነው ወያኔ ኢትዮጵያ ለማጥፋት ያሰበ መሆኑ ምልክቱ በዚህ ቀን አንቀጽ 39 የተረቀቀበት ቀን መልዕክት ነበረው።

ሌላው የወያኔው ረቂቅ "የግዛት ወሰን" የሚለውን ከዚህ እስከ ዚህ ብሎ ቦታ ስም ሊጠራ ያልፈለገበት ሌላ ዓላማ ስላለው ነው። ዓላማው ኢትዮጵያን ሊገዛ ለጠየቀው ሁሉ ለመሸጥ ያመቸው ዘንድ እየተዘጋጀ መሆኑ ነው። እንኳን በሌሎች ክፍለ ሀገር ያለውን ወሰን በቅጡ ሊጠቅስ ቀርቶ የራሴ ነው ለሚለው በትግራይ ሊያስምርበት አልፈለገም። ይህም ቢሆን ያቀደውና ያለመው ስላለው ነው። በምስራቅ! በሰሜንና በምዕራብ በደቡብ ይህ አገር ያዋስንዋል ተብሎ ያልተጻፈበት አንድ ነገር መኖር አለበት ባይ ነኝ። ልብ ያለው ሸብ ነው ልብ ያለው የለም እንጂ ቢኖርማ ይህ ሁሉ ጥፋት በአገር ላይ አይደርስም ነበር። ዛሬ የኢትዮጵያ መንግሥት ብለን የምንጠራው ወያኔ ሲመሰረት ጀምሮ የኢትዮጵያን ታሪክ ለማጥፋት ኤርትራን ከፍ ለማድረግ ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ራሷን የቻለች መንግሥት ለማድረግ የተነሳ ድርጅት እንደነበር አይክዱም። ኤርትራውያን ከተገነጠሉ በኋላ በፌዴሬሽን ለመግባት ሀሳብ የነበራቸው ሲመስል ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ግን አልወደዱም።

አቶ ታምራት ላይኔ <u>ዜጋ መጽሔት</u> 3ኛ ዓመት ቁጥር ሰባት መጋቢት-ሚያዝያ 1994 ዓም ገጽ 17 "ከአንዳንድ የኤርትራ መንግሥትና የሻዕቢያ ከፍተኛ መሪዎች ጋር ኢትዮጵያና ኤርትራ እንደገና በኮንፌዴሬሽን ወይም በፌዴሬሽን ሊዋሀዱ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ አስመራ በሀረድኩባቸው ወቅቶችና አዲስ አበባ በመጡበትም ወቅት እያነሳሁ እወያይ ነበር። በኤርትራ በኩል የመንግሥቱና የፓርቲው እምነት መሆኑን ባላውቅም ይህን ሀሳብ እንደግፋለን የሚሉ መሪዎች ግን ነበሩ። ሆኖም አቶ መለስ ይህን ውይይትና ጉዳዩንም በተመለከተ መወያየትና ማንሳት እንደሌለብኝ የኢሕአዴግን ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት እየጣስኩ ነው በሚል ሽፍን ሲነግሩኝና ማስጠንቀቂያ ሲሰጡኝ ስለነበር ብዙ ጭቅጭቅ ፈጥረንበታል" ሲሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ቀርበው ያነበቡትን መጽሔቱ አውጥቶታል።



## ምዕራፍ 5

## ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን ሊሰጡ ነው?

1600 ኪሎ ሜትር የኢትዮጵያ መሬት ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን ወያኔ ኢሕአዴግ ሊሰጥ ነው። ዛሬ ወያኔ ይህን አደረገ ብሎ መጻፍና መናገር ለአንዳንድ ጥቅም ለነካቸውና ወያኔን ለሚደግፉ ግለሰቦች "ይህ የቅንጅት ወሬ ነው" በማለት ያናንቁታል። ቀደም ሲል ይህ የነፍጠኞች ወሬ ነው! ሲባል ቆይቶ ሳለ ኋላ ደግሞ ይህ የቅንጅት ወሬ ነው! መባል ከተጀመረ ውሎ አድሯል። ደግነቱ እኔ ነፍጠኛም ቅንጅትም አይደለሁም። በመሰረቱ የግል ጥቅም የተጣበው ግለሰብ ሁሌም ምክንያት አያጣም። ምክንያት የውሸት ታናሽ ወንድም ነው። ወደኋላ ከተጻፈው መለስ ብለን ለማየት ስንሞክር የተጻፈውን ታሪክ ወያኔዎች በአገር ግዛት ምኒስትርና በሕዝብ ምክር ቤት በውጭ ጉዳይ ምኒስትር ጽፈት ቤት ያሉትን ሰነዶች ከማየታቸው በፊት እነሱ ስልጣን ሲይዙ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን እንደሚሰጡ ተስማምተዋል። ለሱዳኖች ቃል የተገባላቸው ምናልባት በ1981 ዓም መሆኑ ይጠረጠራል። ሱዳኖች የኢትዮጵያን መሬት ተሻግረው ማረስ የጀመሩት በ1984 ዓም መጨረሻ መሆኑን ሠነዶች አሉ። ምክንያት ደግሞ እነሱ የሚያበሳጩት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍቶት ሱዳንን መጠጊያ አድርጎ እነሱን እንዳይወጋ ለሱዳን መሬት ለመስጠት ቃል ገብተዋል። ለዚህም የቀድሞ የመተማውን ሀብታም የኋላው የኢዲዩ ሻለቃ አቶ አጣናው ዋሴንና ሌሎችንም ኢትዮጵያውያን ሱዳን እንዳይንቀሳቀሱ ከማድረጉም በላይ አፍኖ ለወያኔ አስረከበ። ለምሳሌ በጭልጋ በኩል ከሱዳኖች ጋር የአካባቢው ሕዝብ ግጭት የጀመረው ቀደም ሲል ጀምሮ ነው።

አማረ አፈለ ብሻው <u>አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 201 "በጎንደር አብደራፊና መተማ ሱዳኖች ከኢትዮጵያ መሬት መቀር እጣንና የቤት መስሪያ እንጨቱን ቆርጠው ከመውሰድ አልፈው የሱዳን ወታደሮች ከተማ ውስጥ እስከ ትጥቃቸው ገብተው ኢትዮጵያውያንን ሲደበድቡ የወያኔ ኢሕአዴግ ወታደሮች ምንም አይሏቸውም ነበር። በኋላ ሻዕቢያ በጫረው እሳት ወያኔም ገብቶ ሲነድ ፈልጎ ሲያበቃ አበረደውና ዛሬ ካለበት ሰላም ቢመጣም ቀደም ግን ኢትዮጵያውያን የጎንደር ሰዎች አልቀዋል። በኬንያ ቢሆን ብዙ ችግር ይደርስ እንደነበር የተጻፉትን ሰነዶች አሉ። አሰብ የነበረው የኢትዮጵያ ንብረት ሻዕቢያ ሲጠቀምበት ወያኔ ኢሕአዴግ ደስተኛ ነበር" ይል ነበር። በየካቲት በ1998 ዓም የታተመው መጽሐፍ ተገልጾ ነበር። እንዲሁም ግንቦት 1999 ዓም የተጻፈው መጽሐፍ ቀንጨብ አድርጎ ጠቅሶአል።

አማረ አፈለ ብሻው <u>የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 181 "በዚህ በየካቲት 1999 ዓም ጎንደር ጭልጋ ዘመድ ጥየቃ

ሕደው የነበሩ አንዲት ወዳጄ እያለቀሱ እንደነገሩኝ በጎንደር ክፍለ ሀገር በጭልጋ አውራጃ ያሉ ወረዳዎች አርሰው የሚበሉ ሱዳኖች በመሆናቸው ሕዝቡ አላሳርስም መሬቴን ብሎ ተነስቶ ጦርነት በመግጠሙ 87 ኢትዮጵያዊን ሱዳኖች በአሳት አቃጠሏቸው:: ከዚህ ወዲህ ሕዝቡ ባሶንዳ ከሚባለው የሱዳን ከተማ ገብቶ ሰው ገድሎ ሲመለስ የወያኔ ወታደር ጠብቆ ፈጃቸው:: በጭልጋ በብዛት ኤንትሬዎች ከብትና በግ እህል ሌላም ቁሳቁስ እንደጫኑ ወደ ሱዳን ይገባሉ:: ከሰላ ጤፍና ቡናውን ኤርትራውያን ተቀብለው ውጭ ይሸጣል:: ይህን ለንመለከት ለንብተን ጎንደር ስንመጣ የወያኔ ባለሥልጣን ግለሰብ ትክክለኛ ስሙ ይሁን የበርሃ ስሙ ባናውቅም ተዋውቆን አብረን ስናመሽ ይህን አለን። አቶ ምትኩ በጭልጋ አውራጃ ውስጥ ለም መሬት በተለይም ደለሎ ሽመለጋራ፥ ሽንፋንና ሌሎችንም የቋራ የእርሻ መሬት አርሰው የሚበሉት ሱዳኖች ናቸው:: ይህን ስምምነት የተስማማነው ቀደም ብሎ ነው:: ሱዳኖች መሬቱ የእነሱ መሆኑን በካርታ ላይ ሳያወጡ ወደ አዲስ አበባ ስንገባ 90 የጭነት መኪና ስለሰጡን እኛም ይህን መሬት ፈቅደንላቸዋል:: እናንተ ምን ታደርጋላችሁ እኛ እንኳን እናንተን ቀርቶ መከረነው አልሰማ በማለቱ ታምራት ላይኔንም ከርቸሌ ዘግተነዋል" ሲል የነገራቸው መሆኑን ወዳጄ ስለነገሩኝ ጽፌ ነበር::

ከዚህ በላይ የጻፍኩት በሕትመት ከዋለ ጀምሮ በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ያለው መሬት ወያኔ ለሱዳን የሰጠው መሆነን ይፋ ይሆን ጀመር:: እኔም ቀደም በስደቱ አብረውኝ የነበሩ ሰዎችን ከቦታ ቦታ ፈልጎ ማግኘትና ሱዳኖች የኢትዮጵያን መሬት ከመቼ ጀምረው ማረስ ጀመሩ የሚለውን ለማወቅ ጥረት ማድረግ ጀመርኩ:: በታሪክ ስማቸውን ዘግቦ ለማስቀመጥ ያመች ዘንድ ከወዳጆቼ ጋር ተማክረን የፈረስ ስም ስጠን አሉኝ:: አሁን ያለን ትውልዶች የፈረስ ስም ምን ማለት እንደሆነ የተረሳን ይመስለኛል። የሌሎችን ትተን የነገሥታቱን የፈረስ ስም ልጥቀስ ለምሳሌ አጤ ቴዎድሮስ ታጠቅ ሲባሉ አጤ ዮሐንስ በዝብዝ ሲሆኑ አጤ ምኒልክ ዳኛው፤ (አጤ) ልጅ ኢያሱ ጤና ሲሆኑ አጼ ኃይለ ሥላሴ ጠቅል ይባላሉ:: የርሰው ብሔር አቶ መለስ እኔ የሰየምኩላቸው ሁለት የፈረስ ስም ነው:: 1ኛው አገርበትን ሲሆን 2ኛው ሕዝብንግደል ቢባሉ መልካም ይሆናል:: ስለዚህ እኔም ጭልጋና መተማ አብደራፊ ያሉትን ወዳጆቼን እነሱ ባነሱት ታሪካዊ ቃል ታጠቅ ብያቸዋለሁ::

<u>አባ ታጠቅ</u> የተባሉት ቡድኖች ጋር በስልክ ስንነጋገር "አጤ ቴዎድሮስ የአባ ታጠቅ አጽማቸው ያረፈበት ገዳም ማህበረ ሥላሴ እንዴት ለሱዳን ይሰጥ? በሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ አጤ ቴዎድሮስ ያለ ጀግና ነበር ብለን እንዳንፈክባቸው ወያኔ መቃብራቸው ያለበትን ገዳም ለባዕድ አሳልፎ ሰጠብን:: ስለዚህ ለመሬታችን እኛ እንሞታለን እናንተም አትርሱን" ባሉኝ መሰረት ቃላቸውን ሳልቀይር እንዞ ጽፌዋለሁ:: እነ አባ ታጠቅ የነገሩኝ "ሱዳኖች እኛ እንደምናውቀው እንጨትና መቀር እጣን እየለቀሙ ይወስዱ ነበር:: በማረስም ቀደም ሳይበዛ ነበር:: ኢሕአዴግ ሥልጣን እንደያዘ በ1983 ዓም በሰኔ ወር መቀር ከርካሪዎች ቀደም ከሚከርክሩበት አልፈው ከመሃል ድረስ መሄድ ጀመሩ:: መተማና አብደራፊ ወታደሮቻቸው እስከ ትጥቃቸው ይገባሉ::



ሰክረው ሰው እየገደሉ ሲሄዱ መንግስት ዝም ብሎአቸዋል:: በ1984 ዓም ላይ የእርሻ ትራክትራቸው መሀል ድረስ ገብቶ ማረስ ሲጀምር በሕዝቡና በሱዳን አራሾች መካከል ጠብ ሲፈጠር የሱዳን አራሾች ወታደር ሲረዳቸው የእኛ አራሾች ግን ስንደበደብ ዝም ብሎ ይመለከት ነበር:: ከዚህ በኋላም ቢሆን ሱዳኖች ሕዝቡን ሲገድሉና ሲያሰቃዩ በእኛ መንግሥት በኩል ዝም በሉ እንጂ አይዟችሁ የሚለን አልነበረም::"

"ከ1988 ዓም ወዲህ በምን ምክንያት እንደሆነ ባይታወቅም መንግሥት አይዟችሁ ማለት ሲጀምር አራሹም ተደስቶ ያለ የሌለውን ሀብት አጠራቅሞ ለእርሻ መሰማራት ጀመረ:: በሁለቱ መንግሥታት መካከል ግጭት በመፈጠሩ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ደህና እድል በማግኘታቸው ለልማት ተዘጋጁ:: ነገር ግን ሱዳን ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን በግፍ ተገደሉ:: ሱዳኖች ኢትዮጵያውያን ገድለዋል:: እድለኛ የሆኑ ንብረታቸውን ተቀምተው ራቁታቸውን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በችግር ተሰቃይተዋል:: ለምሳሌ የተባበሩት መንግሥታት ሹፌር የነበረው አቶ ታሪኩ ዓለሜን ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል:: ለነዚህ ኢትዮጵያውያን ማንም አይዟችሁ ያላቸው አልነበረም:: አንዳንዶች ራሳቸውን እስከ መግደል ደርሰዋል::"

"በዚህ ወቅት ያለቀው ኢትዮጵያዊ አምላክ ይቁጠረው:: ይህ ከሆነ በኋላ በተለይ ከ1991 ዓም ወዲህ ወያኔና ሻዕቢያ ሲጣሉ የሱዳንና የኢትዮጵያ ግንኙነት ተሻሽሎ እንዲያውም ያለ ቪዛ በአውቶቢስ ከጎንደር ገዳሪፍ መግባትና መውጣት ተጀመረ:: የኢትዮጵያ የጭነት መኪናዎች በቀጥታ ፖርት ሱዳን ድረስ መሄድ ጀመሩ:: ከመተማ እስከ ጎንደር በ6 ወር ውስጥ 12 ድልድይ ተሰራ:: በዚህ ወቅት አልምቶ ሀብት ለማግኘት ኢትዮጵያውያን ወደ ጠረፍ መጥተው ለስራ ተሰማሩ:: በዚህ ሰዓት ሱዳኖች ኢትዮጵያውያንን ሲገድሉና ሲያስሩ ንብረታቸውን ሲዘርፉና ሲያቃጥሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ዝም አለ:: ሕዝቡ ግን በግሉ ንብረቱን ለማስጠበቅ ጥረት ሲያደርግ የኢትዮጵያ መንግሥ ለምን አገራችሁን አስከበራችሁ፤ለምን ንብረታችሁን ለማስጠበቅ ትጥቅ ይዛችሁ ተነሳችሁ ብሎ ጨፈጨፈን:: ይህ ነው ከሞላ ጎደል በደንበሩ በኩል ያለው" ሲሉ ነግረውኛል:: ከዚህ በላይ የአባታጠቅ ቡድኖች የነገሩኝን ከሰማሁ በኋላ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ይታተሙ የነበሩ መጽሔቶችን ከመደርደሪያ ማገላበጥ ስጀምር ልክ ነው በዚህ አካባቢ የዘገቡት መኖሩን አረጋገጥኩ::

ዞብል <u>አፍሪካ ቀንድ መጽሔት</u> ሰኔ 1985 ዓም የጻፈውን እንዳለ ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይመልከቱ:: አደራ መጽሔት ግልጽ አድርጎ መሬቱን ሱዳኖች እያረሱት ነው ብሎ ሳይሆን የጻፈው መልእክቱን ያስተላለፈው በግጥም ነው:: ሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ነው የሚባለው ለዚህ ነው:: የአካባቢውን ችግር ለሚገባው ገልጾ ጽፎአል::

<u>አደራ</u> መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 1. 1985 ዓም ገጽ 13
"መተማ የጎንደር ዘማች

ተቸግሮ በጎልም አፋች
እንደሞት ሁሉ ላንድ ሞት መተማ የሁለት ፊት ትግል
ያንዱን ዕድል ለሌላው ድል
ለታሪክ ሕሊና ቁስል
በዕድሜ ምዕራፍ ስታዋውል
ሐእሰት ዓዶት መተማ
ነጋ ጠባ ስታቅማማ
ደማች የፋሲል ከተማ" ሲል ጽፏል።

የአበው አነጋገር ከመሬት ጠብ አይልም። ያም "ማልቀስ የፈለገ ቁልቋል ከእሾኽም ይጠጋል" ይላሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ቁልቋል ሁኗል። ወያኔ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እሾኽም ሁኗል። ይህን አሊ የሚል ያለ አይመስለኝም። አልያም ከወያኔ ጥቅም ያላቸው ግለሰቦች ካልሆኑ በቀር የኢትዮጵያን ደህንነት የሚፈልግ ሁሉ ወያኔ ለኢትዮጵያ ሽሆ መሆኑን ያምናሉ። በሰኔ 1985 ዓም የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በሱዳን እየተሰቃዩ ናቸው የሚለው ዜና በኢትዮጵያ ተሰራጭቶ መንግስት ነኝ ባዩ ደግሞ በታህሳስ 1986 ዓም 17 ቀን የቆየ ስብሰባ ካርቱም ላይ አደረገ።

ደርቦ ሙጻይ መጽሔት መስከረም 1986 ዓም "አሁን በቅርቡ ሱዳኖች ሀጋዊ የወሰን ክልሉን እየጣሱ ድልብ መሬቱን ሲያርሱበት አልፎ ተርፎም አፈር ገፍተው የሚኖሩ ወገኖቹን በመትረየስ ሲጨፈጭፍበት የመንግሥት ያለህ? የዳኛ ያለህ? የባንዲራ ያለህ" እያሉ እየተማፀኑ ነው ሲሉ ጽፈዋል።

የአፍሪካ ቀንድ መጽሔት ታህሳስ 1986 ዓም ገጽ 5 "በሱዳን ዋና ከተማ በካርቱም ሲካሄድ የቆየው የኢትዮጵያና የሱዳን የሚኒስትሮች የጋራ መማከርት ጉባዔ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ተጠናቀቀ። በጠቅላይ ሚኒስትር በአቶ ታምራት ላይኔ የሚመራው የኢትዮጵያ ልዑካን 17 አባላትን የያዘ ሲሆን የሱዳን መንግሥት ልዑካን ቡድን የተመራው በምክትል ሚኒስትሩ በጄኔራል አዚቤር ሙሐመድ ሳላህ ነበር። ጉባዔው ከዚህ በፊት በሁለቱ አገሮች መካከል የተፈረሙትን ስምምነቶች በጥልቀት የመረመረ መሆኑ ተገልጿል።"

"የሱዳን መንግሥት ለስምምነቶቹ መጎልበት ከፍተኛ ትኩረት እንደሚሰጥ ከባለስልጣናች መግለጫ ለማወቅ አዳጋች አልሆነም። በቴክኒክ በትምህርት፣ በማስታወቂያ፣በንግድ፣በድንብር፣ ደህንነትና በመረጋጋት እንዲሁም በተለያዩ ሌሎች ጉዳዮች የተደረሰባቸው ስምምነቶች ሁለቱንም ወገኖች ማርካታቸውን በየበኩላቸው ይፋ አድርገዋል። ይህ በእንዲህ እያለ ፕሬዝዳንት አልበሽር የሀገራቸውን የፕሬስ ሰዎችን ስብሰባ ሲከፍቱ በአደረጉት ንግግር ላይ እግረ መንገዳቸውን የሁለቱን አገሮች ጉባዔ አንስተው አሞግሰዋል" ሲሉ ጽፈዋል። በዚህ ወቅት ከርዕሠ ብሔር አቶ ታምራት ላይኔ ጋር አብረው ከሄዱት መካከል አቶ ስዬ አብርሃ፣ ነበሩ። እርሳቸው የዚህን የስብሰባ ጉዳይ ደግሞ እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል።



አቶ ስዬ አብርሃ አዲስ ነገ ጋዜጣ ቅጽ 1 ቁጥር 32 ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓም ኢሕአዴግ አዲስ አበባ ሳይገባ በፊት የምዕራብ ጎንደር እና ምዕራብ ትግራይ ቆላማ አካባቢዮች በርከት ያሉ ዓመታት የደርግ ጦር ሰቋቸው ነበር። ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ የሽግግር መንግሥት እንደ ተመሰረተ በአካባቢው ሰራዊት አላስፈርንም ነበር። በዚህ ወቅት ተጓዳኝ ክሥተቶች ተከፍተዋል። በአንድ በኩል በጦርነቱ ምክንያት ተስተጓጉሎ የቆየው የዚህ ቀጠና የእርሻ እንቅስቃሴ ማንሰራራት ጀመረ። ለበርካታ ዓመታት ባድማ ሁኖ የነበረው ማሳ እና ተጥለው የቆዩት አሮጌ የኢትዮጵያ ትራክተሮች መላወስ ጀመሩ። በርካታ ኢትዮጵያውያን ለዚሁ ሥራ ወደ አካባቢው ተመለሱ። በሌላ በኩል ደግሞ የሱዳን መንግሥት ይህን የጥበቃ ኬላዎች ያለመኖር ሁኔታ በመጠቀም ሠራዊቱን ወደዚህ ቀጠና ማስገባት ቀጠለ። ሱዳናውያን አራሾች የሰራዊታቸውን ኮቴ እየተከተሉ መጠጋት ጀመሩ። ባለቤት የሌለው መሬት አገኘን ብለው ደኑን ማጥፋት የእርሻ መሬቱን እንዳሻቸው መያዝ ቀጠሉ።"

"የሽግግር መንግሥት ተመስርቶ በጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ የሚመራ የሚኒስትሮች ልኡክ ወደ ሱዳን ሲሄድ ከሄዱት ሚኒስትሮች መካከል አንዱ ነበርኩ። በዚህ የሞቀ ወዳጅነት ወቅት ሱዳኖች ይዘውት የወጡት ትልቁ አጀንዳ ድንበር እንካለል የሚል ነበር። እኛ በዚህ ጉዳይ ለመነጋገር ዝግጁ አልነበርነም። ስለዚህ የኢትዮጵያ እና ሱዳን ድንበርም የጠበቀ ዕውቀት አልነበረነም። እነርሱ ግን ስለ ጉዳዩ በደንብ የሚያውቁ ባለሞያዎች እና ሰነዶችን ይዘው ነበር የጠበቁን። እኛም እሺ ወይም እምቢ ሳንል ጉዳዩን ገሸሽ በማድረግ ውይይታችንን በሌሎች ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ብዙ ጥረት ብናደርግም አጀንዳውን ከመከላከያ እና ጸጥታ ጉዳይ ጋር በማያያዝ ነገሩን የማይታለፍ ለማድረግ መፈለጋቸውን ስንገነዘብ እቅጩን መናገር ነበረብን። ባላጠናነው እና ባላወቅነው ጉዳይ ላይ አሁኑኑ ድንበር ይከለል ማለት አንችልም። የሽግግር መንግሥት በመሆናችንም ድንበር የማካለሉ ውክልና (ማንዴት) የለንም አልናቸው ነገሩም በዚህ ቆመ።"

"ይህም ሁኖ ሱዳኖች በደንበር አካባቢ የጀመሩትን ጉዳይ አላቆሙም። ይባስ ብለው በእርሻ ሥራ መቋቋም የጀመሩትን ኢትዮጵያውያን ገበሬዎችን መተናኮል እና መጋፋት ጀመሩ። ይህ ሁኔታ እየባሰበት በመሄዱ ውስን የመከላከያ ኃይል በዚሁ አካባቢ ማስፈር ቀስ በቀስ ይህንኑ ማጠናከር ጀመርን። ሰራዊቱ ይህን በአራሾች ላይ የሚደርሰውን በደል እና በዐይናችን ፊት የሚደርሰውን ውድመት መቃወም ጀመረ። አንድ ቀን በዚህ አካባቢ የተመደበው የመከላከያ ሰራዊታችን አዛዥ የጽሑፍ መልእክቱን አስይዞ እቻው ወደ ሆነው የሱዳን ጦር አዛዥ አንድ መልእክተኛ ጓድ ይልካል። የተላከው ጓድ የተደረገለት አቀባበል የወዳጅ አገር ሠራዊት አቀባበል አልነበረም። ኑ ብለው ተቀብለው ትጥቃቸውን አስፈትተው አረዷቸው። ይህ ድፍረት እና ጭካኔ እንደ ተፈጸመ ሠራዊታችን አይምሬ የአጸፋ እርምጃ ወስዶ በአካባቢው የነበረው ጦር ወጣ ቀረ። እኔ በሐላፊነት እስከ ነበርኩበት ጊዜ ድረስ ሱዳኖቹ ወደዚህ አካባቢ ተተኪ ሰራዊት አልላኩም።"

"አቶ መለስ ሠራዊታችን በ1995/1996 አካባቢ የወሰደው ማጥቃት ብሉ የገለጸው ይህንኑ የአጸፌ እርምጃ ነው:: ይህን አካባቢ ሠራዊታችን በወሰደው የአጸፋ ርምጃ ምክንያት በእጃችን የገባ የእኛ ያልሆነ መሬት አድርጎ ማቅረብ ግን ትክክል አይደለም። የሱዳን ወታደሮች እና እነርሱን ተከትለው የመጡት የሱዳን አራሾች ወደዚህ ቀጠና የመጠጋታቸው ታሪክ ከፍ ብሉ ከገለጽኩት የነገሮች አንድት ጋር የተያያዘ ነውና ድንበር ሳይከለል በፊት እንዲህ ብሉ ፍርድ መሰጠት አይገባም ነበር።"

"የአቶ መለስ መንግሥት ከኤርትራ እና ኢትዮጵያ ድንበር ክርክር ጋር በአንዳንድ የጾረና እና የአካባቢዋ ቦታዎች ላይ ለኤርትራ ምስክርነት መስጠቱ እና የሂጉ ኮሚሽን በዚሁ ተመስርቶ እነዚህ አካባቢዎችን ለኤርትራ እንዲሰጡ መወሰኑን ኮሞሽኑ ሪፖርት ለመገንዘብ ችለናል:: አሁንም በአንድ በኩል ድንበር አልተካለልንም እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ ሰራዊታችን በወሰደው ማጥቃት ምክንያት የእኛ አራሾች ገብተውበት ሲጠቀሙበት የቆየ የእኛ ያልሆነ መሬት ነው ብሉ አስቀድሞ በኢትዮጵያ ላይ እየመሰከረ ነው:: አቶ መለስ ስለ ሱዳኖች እርቆ አስተዋይነት ከመናገሩ በፊት ስለ ጉዛ ራሱ አስተውሎ ቆም ብሉ ቢጠይቅ ይሻል ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 10 ቁጥር 11.1995 ዓም ሙሻዘር አምድ ገጽ 19 "የሱዳን ገበሬዎች 300.000 ሄክታር መሬት ከኢትዮጵያ ጠየቁ? ጦማር ሰኔ 10/1995 ዓም እውነት ብለዋል:: ማን ከማን ያንሳል ልጄ? ይልቅስ አባት ሳለ አጊጥ ጀምበር ሳለ ሩጥ ነውና የድንበር ኮሞሽኑና የሥራ ጊዜያቸውን ሳያጠናቅቁ ይሄን ነው በነካ እጃቸው ማስፈረድ" ሲል ጽፏል።

የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፍ ላይ ደንበሩን አስመልክቶ በጻፍኩት አተታ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ትክክል አይደለህም ብለው ወቀሱኝ። ምክንያቱም ወያኔ ምንም እንኳን ፀረ ኢትዮጵያ አንድነት አቅዋም ቢኖረውም ማሕበረ ሥላሴን ገዳም ይሰጣል ማለት ሐሰት ነው" አሉኝ። እውነት በመሆኑ ታሪኩ ሲወጣ ከአንድ ዓመት በኋላ አንዳንዶቹ አይናቸውን በጨው አጥበው "እባክህ ጠቃሚ ሰነድ ካለህ ላክልን" እያሉ የጠየቁኝ ቀደም ሲል የወቀሱኝ ናቸው:: እውነት ትታመማለች እንጂ አትሞትም። ከአሜሪካ ኢትዮጵያ ልማት ሊያለሙ ለሕዝብና ለአገር ሥራ የተሰራ መስሎ የታያቸው ብዙ ዜጎች ኪሳራ ደርሶባቸዋል።

የጭልጋው አራሽ እንደፋራሽ ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓም ሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ትምህርት ስንከታተል ቆይተን ጭውውት ስንጀምር የደረሰበትን ዘርዝረው እንዲህ ሲል ነገሩን:: "በጎንደር ክፍለ ሀገር ጭልጋ አውራጃ ቢካ ወንዝ አጠገብ ነበር ልማታችን ታዲያ ብዙ ንብረት ወድሞብናል ሰራተኞቻችን በሱዳን ታፍነው ተወስደውብናል:: ከሱዳን ጋር ሰላም ስለሆነ የኢትዮጵያ ደንበር ጠባቂ በአካባቢው የለም።



በትውልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነት አሜሪካዊ የሆነ ተሰባሰበን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከአቶ ስዩም መስፍን ጋር ለውይይት ስንቀርብ እርሳቸው::"

"እናንተ የፖለቲካ ድርጅት ደጋፊዎች ካልሆናችሁ ልማታችሁን አልሙ የሚጠብቃችሁ ወታደር እንሰጣችሁ ለተዘረፈው ንብረታችሁ ከባንክ የተበደራችሁትን ሆነ የግል ብራችሁን በሚመለከት ለወደፊቱ እንነጋገራለን:: ሰራተኞቻችሁ ይፈቱላችኋል ባሉን በ29 ቀን ተለቀቁልን:: የኢትዮጵያ መንግሥት አውቆ እንጂ ያዘረፈን ሱዳን እንዳልሆነ ልባችን ያውቃል:: እኛ የውጭ አገር ፓስፖርት ስላለን እንጂ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ታስረዋል! ተገድለዋል! ተዘርፈዋል፣ብዙ ጥፋት በአካባቢው ደርሶበታል" ካሉ በኋላ በሰዎች የሰሙትን ታሪክ እንዲህ ሲሉ "የሱዳን ወታደር መጥቶ ስንጃ ከተማ አካባቢ የኢትዮጵያውያንን ንብረት በጉንና ፍየሉን ነድቶ ወሰደ::"

"እነዚህ በስንጃ አካባቢ ንዋሪ የሆኑ 3 አርሶ አደሮች ሱዳን ገብተው ሶስት ሱዳናውያን ያዙ:: ከዚያም ንብረታችንን ስታመጡ ሰዎችን እንለቃለን ብለው በአርብኛ ቋንቋ ጽፈው እንዲተው አድርገው ሱዳኖችን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ መጡ:: ሱዳኖችም አንድም ግልገል ሳያጠፉ እየነዱ አመጡ:: ሰዎችም ተለቀቁ:: ወዲያው ወያኔ ወታደር ልኮ ለምን አስራችሁ አመጣችሁ ብሉ እነዚያንን አርሶ አደሮች መሳሪያቸውን ቀምቶ አሰራቸው:: ሰዎችም እኛ መዘረፋችን ለመንግስታችን አቤት ብንል የሰማን የለም በጉልበታችን ንብረታችን አስመልሰናል ስለዚህ ወንጀለኛ አይደለንም:: ብለው ቢከራከሩ ሰሚ አጥተው የታሰሩ መሆናቸውን ሰምቻለሁ" ሲሉ ነግረውኛል። ስማቸው እንዲጠቀስ ስላልፈለጉ ለዋቢ ጥቅስ ያመች ዘንድ የጭልጋው አራሽ እንደፋራሽ በሚል ሰይሜያለሁ።

በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ ጋንቤላን ወያኔ አሳልፎ ሊሰጥ መነሳቱ ነው:: ጋንቤላን በተመለከተ ያለቀለት ጉዳይ መሆኑ ከክቡር አክሊሉ ሀብተወልድ ማስታወሺያ የተወሰደውን ማንበብ ይቻላል:: ይህን ለም መሬት ወያኔ ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት መነሳት ማለት ጉዳዩ ምንድነው? የአካባቢውን ሕዝብ እርስብ በእርስ ማጫረሱ የማይበቃ ሁኖ እንዴት ዛሬ ደግሞ መሬቱን ለሱዳን ሊሰጥ ይነሳል:: ሱዳኖች እነሱ መሬት ጠፍቶባቸው ሳይሆን ፍላጎታቸው እስልምና ሃይማኖት ለማስፋፋት ታጥቆ ከተነሳው ከአረብ አገር በሚለገሱት ገንዘብ መሆኑን እንዴት ማጤን አቃተው? ለሱዳን ሱዳኖች በቀላሉ ቅልብስ የሚሉ ከመሆናቸው የመጣ ሌሎች ወያኔን የሚቃወሙ የሥነ መንግሥት የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሱዳን መሄድና የጦር መሳሪያ ገዝተውና ተውሰው በርሃ ገብተው እርሱን እንዳይወጉት ነው:: ወያኔ ሥልጣን እንደያዘ የደርግ መኮንኖች ሆኑ ሌሎች ባለሥልጣኖች በሱዳን ውስጥ እንዳይቀመጡ ከፍተኛ ጫና በማድረግ እንዲወጡ ማስደረጉ አይዘነጋም:: ለምሳሌ ጄኔራል ኃይሌ መለስ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችን ሱዳን እንድታስለቅቅ አድርጓል።

ወያኔ ሱዳን ከአገሯ እንድታስወጣ ሳይሆን የቀሩትንም አስራ እንድትሰጠው አደረገ:: አቶ አጣናው ዋሴ (ሻለቃ) ሌሎች ቁጥራቸው ያልታወቀ

ኢትዮጵያውያንን ሱዳን እስራ ለወያኔ አስረክባለች:: መቶ አለቃ ሞላ እንዴት ሞቱ? ወያኔና ሱዳን ናቸው:: ሌሎችም ብዙ ኢትዮጵያውያንን ሱዳን አስራ ለወያኔ የሰጠችው ያለ ምክንያት አይደለም:: ወያኔን በትጥቅ እንዋጋለን እያሉ ወደ ሱዳን የገቡ ብዙ ግለሰቦች ቀደም ሲል ነበሩ:: ከፋኝ ኢትዮጵያ የጀግኖች ግንባር ሊቀ መንበር ሊቅ ዶ/ር አንዱአለም ሙላው የኢሕአፓው አቶ መርሻ ዮሴፍ ሌሎችም ብዙ አለን ባዮች ሱዳንን ረግጠው ነበር:: ነገር ግን የሱዳን መንግሥት ከግል ጥቅሙ ጋር የሚራመድ በመሆኑ የሁሉም የትጥቅ ትግል ግቡን ሊመታ አልቻለም:: ወያኔ ሱዳንን የሚያስፈራራበት የራሱ ዱላ አለው:: ያም በርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ዘመን ሱዳንን የሚቃወሙትን ድርጅቶች ይረዳ ስለነበር ወያኔ አዲስ አበባ እንደገባ ቀጥቅጦ ነው ያባረረላቸው:: ሱዳኖች ወያኔን በመክሰን በአርብኛ የጻፉትን ወደ አማርኛ ተርጉመው መስታውት መጽሔት አውጥቶታል::

ዶ/ር ፒተር ኒዮተከክ <u>መስታውት መጽሔት</u> ቅጽ 1 ቁጥር 1 መጋቢት 1985 ዓም ግልጽ ደብዳቤ ለአቶ መለስ ዜናዊ በሚል ርዕሥ ገጽ 10 "በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ የሱዳን ስደተኞች ከኢትዮጵያ ሠፈራቸው እንዲፈናቀሉና የአክራሪው የሱዳን መንግሥት በቦንብና በጥይት እንዲቀበላቸው መደረጉ በኢትዮጵያና በሱዳን ሕዝቦች መካከል ለረጅም ጊዜ ፀንቶ በቆየው ልባዊ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል:: ዋናው መንግሥት በአሁኑ ጊዜ ራሱን እንደ ኢትዮጵያ ነፃ አውጪ እየቆጠረና እየቀረበ ሲሆን ከሱዳን ሕዝቦች ጋር ለሚደረገው ጦርነት ከርሰዎ መንግሥት ንቁና ለዘብ ያለ ድጋፍ እስካሁን ድረስ ለማግኘት ችሏል" ሲሉ ጽፈዋል ብዙ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል የነበራቸውን ስሜት አሁን ቀዝቀዝ ብሷል:: መንስኤው ወያኔን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከግራቀኝ ከውስጥ እስከ ውጭ ጩሀት ስላበዙበት ለማረሳሳት ሲል ዝም ያለ መሆኑን ሊረዱ አልቻሉም::

ወያኔ ዝም ያለ የመሰለው የሕዝቡን ጩሕት ረገብ ለማድረግ አስቦ እንጂ በትክክል የሕዝቡን ድምጽ ከልብ አዳምጦና ሰምቶ ሳይሆን ግዜ እየገዛ ነው:: የአባቶች አባባል "ያዴቆነ ሠይጣን ሳያቀስ አይለቅም" ይላሉ:: በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ የምወደው በውጭ አገር የተመሰረተው የደንበር ኮሚቴ ሌሎችን ምሁራን እያሰባሰበ መርሃ ግቡሩን አስፋፍቶ ለወደፊቱ በሕጋዊ መንገድ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር እስኪከለል መስራት እንዳለበት አሳስባለሁ:: ወያኔ ለዳር ደንበር ይቆረቆራል ብሎ ማሰብ ፈጽሞ ሊሆን የማይችል መሆኑን መገንዘብ ያሻል:: ወያኔ ከስልጣን ለመቆየት ሲል የማያደርገው ነገር የለምና ነው:: የትግራይን ሕዝብ እያወናበደ ኋላም የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀረ ደርግ እቅዋም ስለነበረው አወናብዶ ከሥልጣን የወጣ መሆኑ አይዘነጋም:: ወያኔ የትግራይንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የዓለምን ሕዝብ አጭበርብሮ ከስልጣን ላይ የወጣ ነው::



# ሱዳኖች በጐንደር ድንበር ጥሰው በመግባት የኢትዮጵያን መሬት ማረስ ጀምረዋል

● የአካባቢው ገበሬዎች በኃይል ርምጃ ተገድለዋል፤ ተፈናቅለዋል

ከ**ውል

የሕገራችን ያለፈ ታሪክ የጦርነት ታሪክ መሆኑ አሳዝኖን የዛሬ ትውልዶች ነገሮችን አስተካክለን፤ የተረጋጋና የሰከነ ውል መሠረቱ ያልጠፉ ታሪክን ለተተኪው ትውልድ ከማስረከብ ይልቅ አሁንም ሌላ የጦርነት ታሪክ ምዕራፍ የሚከፍት ሁኔታ ሊውጠነጠንና በመጭው ትውልድና በዚህች ቅድስት ሀገር የመከራ ቀንበር ሊጫንባቸው እያየን "ጊዜ ይፍታው" ብሎ ማለት ቸል ማለት ተገቢ አይደለም። ይህች ሀገር በሚያሳዝን መልኩ እየተሸራረፈችና ልዕልናዋ እየተጣሰ በምትገኝበት በአሁኑ ሰዓት ትናንት የከፋፍለህ ግዛውንና የተስፋፊነት ፖሊሲዎችን አውጥተውና ጦር ሰብቀው፤ ድንበራችንን ጥሰው፤ የተዳፈሩን የውጭ ኃይሎች በቆራጥ ኢትዮጵያውያን መራራ ትግል የሆፍረት ካባ ደርበው ይመለሱ ዘንድ ግድ ስሆነባቸው ሁሉ ዛሬ ነገሮች ሁሉ እነርሱ እንደሚፈልጓቸው ሆነው የተመቻቹላቸው መስሏቸዋል። ያለምክንያት አይደለም። እንደፈለጉን ሊያደርጉን በሚችሉበት ሁኔታ በመከተፈልና በመበታተን ላይ ያለን መስሎ ስለሚታይ ነው። በእርግጥም ለብዙዎች ሁኔታው እንዲያ ነው። ብሔራዊ ስሜታችን ላልቶ ኅጠኝነት አጥቅቶናል። የእናት ሀገር ፍቅራችን ቀዝቅዟል። የአንድነት ጥንካሬያችን ላልቷል። ምራላችን የወደቀ ይመስላል። እርስ በርሳችን ስንናቆር ተከብሮ የቆየው በራችን ባለቤት አልባ ሆኖ ይታያል። አብዛኛው ሕብረተሰብ ቀደም ብሎ ባለቀለት የኤርትራ ጉዳይ፤ በሐገር ውስጥ በሚፈጠሩ ማዘናጊያ ክስተቶችና በአስተዳደር ችግር ተወጥሮ ሲታመስ የዳር ሐገሩ ለነገ አስጊ ችግርን በሚፈጥር መልኩ ይገኛል። የዚህን ድርጊት እውነታ ቀጥሎ የምናየው ዘገባ ገሐድ ያሳየናል።

የጎንደር ሕዝብ ከተከዜ መለስ የበሩት የወልቃይት ጠገዴ፤ የሰቲት ሁመራና ጠለምትን የመሳሰሉትን ለም የቀድሞ ግዛቶቹ በክልል አንድ (በትግራይ) መጠቃለል ሲያጠያይቀው አሁንም ሌላ ውጋት አላጣውም። የአብደራፊ እና የመተማ አካባቢዎችና ሌሎች በጠረፍ የሚገኙ የክልሉ ገጠርና ትናንሽ ከተሞች በሱዳን ቁጃሮች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመታረስ ላይ ነው ያሉት። ይባስ ብሎ ከሚያርሱት እርሻ ውስጥ በሰፈረው የሱዳን ጦር ሠራዊት ትንኮሳ የአካባቢው አራሽ ገበሬዎች በቆየ ባድማቸው ላይ መገደልና መቁሰል የሁኔታውን እየከረረ መምጣት የሚያመለክት እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች በሐዘንና በቁጭት ይናገራሉ።

የጦር ኃይል ከትናቸው በማሰለፍ በሱሚናት፤ በሺመላ ጋራ፤ በደላሎ፤ በሰናር፤ በግራዋ፤ በኩረደም፤ በገላሉባን፤ በአብጽዮንና በመሣሡት ከጓንግ መሰብ እና ሌሎችንም የመተማና የአብደራፊ መሬቶችን የሱዳን ገበሬዎች ከአሥራ ሁለት ያላነሱ ትራክተሮችን በማሰማራት ሰሊጥ ማሽላና ጥጥ የመሣሡትን ማምረት የጀመሩት ከዛሬ ሦስት ዓመት አካባቢ ኢህአዴግ በአካባቢው እያለ ቢሆንም ተጠናክረው ገፍተው የመጡትና በአካባቢው ነዋሪ ላይ ጉዳት ማድረስ የጀመሩት ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ የገለፁልን በአካባቢው በንግድ ሥራ ተሰማርተው የሚገኙ አባት ናቸው።

እኛም በሱዳኖች ታረሱ ወደተባሉት የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ክልሎች በመንቀሳቀስ ጉዳዩን ለማጣራት በአቅራቢያው የሚገኙ ነዋሪዎችንና የሚመለከታቸውን የመንግሥት አካላት አነጋግረን ነበር።

የአጋጣሚ ነገር ሆነና በግጭቱ ወቅት የቅርብ ተመልካች የነበሩ ግለሰቦችን አገኘን። በግጭቱ ዕለት ስለነበረውና ከዚያም በፊትና በኋላ ስለተፈጠሩት ነባራዊ ሁኔታዎች እንዲያውቱን ጠየቅናቸው። ምንም እንኳን ሁኔታውን ለመንገር ፈቃደኛ ቢሆኑም ስማቸው እንዲጠቀስ እንደማይፈልጉ ከ
በኋላ ወደ ዋንኛ እርዕሰታችን
"እርግጥ ነው ሱዳኖች የኢኛን
በማረስ ላይ ነው ያሉት። "
ንግግራቸውን ከጀመሩ በ
ቀጠሉም "ግጭቱ የተፈጠረው
በእል ሊከበር ሳምንት
ሚያዝያ 3 ቀን 1985 ዓ.ም
በታውም በመተማና ሁመራ
በምትገኘው በሺመላ ጋራ
ነበር።

"በሱዳኖችና በእኛ ገበሬዎች
የተፈጠረው አለመግባባት ዋ
ሰዔ የእርሻ መሬት ጉዳይ ነው
ከቀን ቀን ሲስፋፉ ከእኛው ገበ
ድረስ መግባት ጀምረዋል። ገ
እንዴት በገዛ ሀገሬ እገፋለሁ ባ
በዚህ አይነት ጥሉ ከጊዜ ጊዜ
ሄደ። አለመግባባት መጣ። እሁ
ዝያ 3 ቀን 1985 ዓ.ም. ከቀ
ሰዓት በሺመላ ጋራ አካባቢ
ወታደሮች እማካኝነት በአ
አራሽ ገበሬዎች ላይ የተ
እርምጃ ግን ከበፊቱ የተለየ ነ
ሬዎቹ በሀገራቸው መሬት በ
ጥይት ተደበደቡ። አራት
ሲሞቱ ሁለት የሚሆኑት ቆሰ
ካባቢው ዘራፊንና ሌባን ለማ
ማርተው የነበሩ የቀበሌ ታጣ
የመከላከያ ሰራዊት አባላት ች
ፈጠረ በኋላ ደረሱ። ወዲያው የ
ካነሱና የቆሰሉትን በመርዳት ላ
ሌሊት ላይ ከመተማ የሐንስ
ችግሩ ተሰምቶ ኖሮ የእርሻው
ቶችና አንዳንድ ታጣቂዎች መ
ታው እንደደረሱ ከቅርብ ርቀ
ገኙት የሱዳን ወታደሮች እብ
ከአምስት ደቂታ ላላነሰ ጊዜ
ይህን ጊዜ የእርሻው ባለቤቶ
ኔታው በመበሳጨት ከአቅራ

-ትን እብሪተኛ የሱዳን ወታደሮችን ግጠም ቢፈልጉም በቦታው የነበሩት ህአዴግ አባላት ግጭቱ አስፈላጊ ዳልሆነ ስለገለፁላቸው ሴሊቱን ውንና ቁስለኞችን በመያዝ ከመተማ ጋስ የመጡት የኢህአዴግ አባላትና ለ ህዝቡ ከባለቤቶች ጋር በመሆን ቶ ነጋሽ ጽዋያ ለምነው ባመጡት ኡንትሬ መኪና ተመለሱ። ይህን ሰዓቱ 7:30 ይሆናል። በአካባቢው ሩ ታጣቂዎች እዚያው እንዲቆዩ ሬገ።

ሚቀጥለው ቀን ሚያዝያ 4 አሁንም የሱዳን ወታደሮች ከቦታው ባሉት ቂዎች ላይ ንፍተው በመምጣት ስ ከፈቱ። በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ከዚያኛው ወገን የተፈጠረው ታውቅም ከታጣቂዎች ውስጥ አንድ ። አቶ በርሔ የተባሉት ታጣቂ የቆሰሉት። (አቶ በርሔ በመተማ ስ ተኝተው አሁን ድረስ ሕክ ፎውን በመከታተል ላይ ናቸው።) ከተፈጠረ በኋላ የክልሉ ሕዝብ በሌውና በየገበሬ ማኅበሩ በተሰበ ት አጋጣሚ ሁሉ ከላይ የተጠ ሶን ግጭት መንስዔ በማድረግ የሱ ን ከአስራ አምስትና ከሀያ ኪሎ ር ባላነሰ ሁኔታ ወደ ክልላችን መግ ፍውንና ማረሳቸውን በተመለከተና ጋጋሚ በተለያዩ ቦታዎች በእ ኝነት የሚፈፅሙት ግፍ በቸልታ ሎፍ የሌለበት መሆኑንና በተለይ ሁለትና ሦሰት ዓመት ታይቶ ታወቅ ደረጃ እየተስፋፋ መምጣ ውን በጥያቄ ቢያቀርቡም የአካ የመንግሥት አካላት ሀይህ ጥያቄ ፀረ–ሰላምና ፀረ–ቻርተር ድር ቅስቀሳ የተጠነሰሰ ሌላ ሴራ እንጅ ፍላጎት አይደለም። ሱዳኖችም ተባለው አልገቡም። ችግር ካለም ረስ የሚችለው የሽግግር ሥቱ ነው። ነገር ግን ሁለት ወዳጅ ሀገሮችን ለማቃረን የሚደረገው ሉባሊታ አግባብ አይደለም" በማ ማስጠንቀቂያ የታቀላቀለበት ሰጥተዋል። የሚገርመው በተፈ ግጭት የተጎዱ የጥበቃ አባላትና

ሀይወታቸውን ያጡ ገበሬዎች መኖራቸው ከአፍንጫ ስር ያለ መረጃ መሆኑ እየታወቀ ከላይ ያየነውን አይነት መልስ ተሰጠ።

"የአካባቢው ሽማግሌዎች ጥረታቸውን በመቀጠል በሰላማዊ መንገድ ችግሩን ለመፍታት ሙከራ ቢያደርጉም የባለሥልጣናትን ትብብር ባለማግኘታቸው ሊሳካላቸው እንዳልቻለ ይናገራሉ። እንዲያውም ሁኔታው ስር እየሰደደና በየጊዜው ግጭቶቹ እየታዩ ከሕዝቡ አቤቱታ ሲቀርብ 'ጥያቄውን እኛ መመለስ አንችልም! ችግሩን ለበላይ አካል ስለገፍን መልስ በመጠባበቅ ላይ ነን' የሚል መልስ ከመንግሥት አካላት ሲሰጥ እንጅ በተጨባጭ ያየነው መፍትሔ የለም። አንድ ዱካ (በሱዳን ክፍለ ግዛት) የሚገኝ የሱዳን ኮሎኔል ወደ አካባቢያችን በመምጣት ከኛ ክፍለ ህዝቦችና ከሠራዊቱ አዛዦች ጋር ሲነጋገር "ሀይላችን ይወስነናል" በማለት መናገሩን ከቦታው የነበሩ ሠዎች ይናገራሉ።

"ነዋሪው ሀብረተሰብ ይህን መሰል የሰላምና የእርቅ ጥረቶችን በማድረግ እስከ አሁን ቢቆይም ከመንግሥት አካላት ቸል ከመባሉ በተጨማሪ ጥያቄው ሌላ መልክ ሲሰጠው፤ በሌላ መልኩ ሱዳኖች ዱሮ ከነበራቸው የጦር ሀይል በመጨመርና አራት መድፎችን፤ አየር መቃወሚያ፤ መትረየሶችን ጭምር ጦሩን በማስታጠቅ በሚያሳዝን ሁኔታ በመጠናከር ላይ ናቸው" ሲሉ በዝርዝር አስረድተውናል።

ይህንና የመሳሰሉትን ቁምነገሮች በቦታው ተገኝተን ካገኘን በኋላ ወደ ጎንደር ከተማ እንደተመለስን ስለ ጉዳዩ የሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ አንዱ ባለሥልጣን እነጋግረናቸው ሲመልሱ "ሱዳኖች እንዲህ አይነት እርሻ የሚያርሱት ከበፊት ጀምሮ እንጅ አዲስ ነገር አይደለም! ዘልቀው እየገቡ ደኖችን እየጨፈጨፉ ይወስዱም ነበር። በተለይ በጦርነቱ ወቅት ትኩረት ስላልተሰጠው ሰፊ ቦታ ይዘው ቆይተዋል። እርግጥ ነው የሱዳን ገበሬዎች አሁን ድረስ ያርሳሉ። ይህ ሁኔታ በቅርቡ ግጭት አስነስቶ እንደነበር ይታወሳል። ግጭቱም የእርሻ መሬትን በሚመለከት

ነበር። በገበሬዎችና በሱዳኖች እርሻ በሚገኙ ወታደሮች መካከል በተፈጠረው ግጭት ከሁለቱም ወገን ሰዎች ሞተዋል፤ ቆስለዋል፤ የአካባቢው ገበሬዎች እንደተፈናቀሉ መካድ አይቻልም። ዋናው ቁምነገር በሁለቱ ወዳጅ ሀገር ገበሬዎች መካከል የተፈጠረውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥረት ማድረግ ስለሆነ መፍትሔው በተለያዩ ቦታዎች የገቡ የሱዳን አራሾች እንዲመለሱ ከእነርሱ ባለሥልጣናት ጋር በተለያዩ ጊዜያት በቲህና በመተማ አካባቢ ንግግር ተደርጓል" ሲሉ መልሰዋል። በእርሻው አካባቢ የጦር ካምፕ ከመኖሩ በተጨማሪ የተጠናከረ ሀይልና መሣሪያ የመታየቱ ጉዳይ አዝማሚያው ችግር አይፈጥርም ወይ? ብለን ለጠየቅናቸው ሲመልሱ ሀበመሠረቱ እንደነገርኩህ በተደጋጋሚ በሠላማዊ መንገድ ነገሩን ለማብረድ ጥረት በማድረግ ላይ ነው ያለነው። ይህ የመሣሪያው ጉዳይ ሊሆን የቻለው በመንግሥት ደረጃ ሳይሆን በግለሰብ ሀብታሞች ነው። የሱዳን ጦር እንደኛ ጦር አይደለም! ስርዓት የለውም። ለጥቅም ሲሉ እንኳን ይሄን ሌላ ያደርጋሉ። በአጠቃላይ ችግርችን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነውሀ። በማለት አስረድተውናል።

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው የዚህ መንግሥት ባለውለታ ጎረቤቶቻችን በማንአሰብኝነት ድንበራችንን እየጣሱ ማረሳቸውንና መስፋፋታቸውን በዝምታ እንደቀላል ከታለፈና ትንሽ ከቆየ የቅኝ ግዛት ጥያቄ እንዳይመጣብን ስጋት አለ ሲሉ አንዳንድ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

መንግሥት የሀገሩን ድንበር የማስከበርና የሕዝቦችን መብት የማስጠበቅ ኃላፊነት ስላለበት በአራቱም ማዕዘን ሉአላዊነታችንና የግዛት አንድነታችን እንዲከበር በአስቸኳይ ጥረት ሊያደርግ ይገባል። እንደቀድሞዎቹ መሪዎቻችን ባዕዳን በሚግማቸው እንኳን ጥርኝ አፈር እንዳይወሰዱ አስወልቆ ማራገፍ ቢቀርም ድንበር ዘልቀው ሲሰፋፉ ቻል ማለት ጥሩ ውጤት አያመጣምና የሽግግሩ መንግሥት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።



# ምዕራፍ 6

## በድንበርን ብቻ ከተጻፉት ማስረጃ

<u>ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ</u> ሚያዝያ 1 ቀን 2000 ዓም ገጽ 2 "አሁን ያለውን አጋጣሚ በመጠቀም ይህ ለምና ሰፊ መሬት መሰጠቱን አንዳንድ የዜና አውታሮች በተለይም ሱዳን ትሪቢዩን ጋዜጣ በሰፊው መዘገባቸውን የተከታተልን በሰሜን አሜሪካ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ አቋቁመን በመጀመሪያ ነሐሴ 2 ቀን 1999 ዓም (ኦገስት 8 2007)በአማርኛና በእንግሊዘኛ በተጻፈ ግልጽ ደብዳቤ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ በጉዳዩ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መልስ እንዲሰጡበትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልጽ እንዲያደርጉ ጠየቅን:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስካሁን የሰጡት መልስ የለም:: ከዚያም በማከታተል ጥር 10 ቀን 2000 ዓም (ጃንዋሪ 19 2008) በተለያዩ ድኅረ ገጾች ባሰራጨነው ጽሑፍ! ድንበሩን አስመልክቶ አቶ መለስ ዜናዊ ከሱዳን ባለሥልጣናት ጋር ካርቱም መገናኘታቸውና የሁለቱ መንግሥታት ተወካዮች ደግሞ በተባለው ድንበር ደጋግመው መገናኘታቸውን የተሰጠው የድንበር መሬት ከጋንቢላ እስከ ሁመራ እንደሚደርስ ከሱዳን የዜና አውታሮች ያገኘነውን ልዩ ልዩ መረጃ ለመላ አገር ወዳድ አቀረብን" ሲሉ ጽፈዋል:: ከዚህ በላይ በዚህ እርስት ተጽፎበት የነበረው ስም በቅርቡ ተቀይሯል:: አዲሱ ስሙ የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ተብሏል::

ከጋንቤላ እስከ ሁመራ የተባለውን መጽሐፍ ለመጻፍ ስነሳ ብዙ ሰዎች "ወያኔ መሬት ለሱዳን ሊሰጥ የተዘጋጀ መሆኑን መረጃህ ምንድነው? የምትጽፈው ወያኔን ለማስጠላት ሳይሆን አይቀርም:: ደግሞም ጠቅላይ ምኒስትሩ ሆኑ የውጭ ጉዳይ ምኒስትር ጽፈት ቤት ያወጣው መግለጫ የተወራው ውሸት ነው ብሎ መንግሥት እየተናገረ አንተ እንዴት ይህን ልታወጣ አሰብክ" ብለው መከረውኛል:: እነዚህን ወዳጆቼን ወያኔ መሬት ሊሰጥ የተስማማ መሆኑን መቼ እንደተጀመረ ከፍ ብሎ የተጻፈውንና መረጃ ይገፎ ለማብራራት ብሞክር ሊሰሙ አላሹም:: እንዲያውም እነዚህ ወዳጆቼ "የኢትዮጵያ መንግሥት ሊሰጥ ያላሰበውን አሳስበህ ኋላ ሱዳኖች የአንተን መጽሐፍ እንደ መረጃ ይዘው ቢከራከሩ አንተ በታሪክ ተጠያቂ ትሆናለህ" ሲሉ ደግመው ደጋግመው ተከራከሩኝ:: እነዚህ ወዳጆቼ ሌላው ቀርቶ "የጀርመን ሆነ የአሜሪካ የአማርኛው ሬዲዮ ጣቢያ የተሳሳተ ዘገባ" አቅርቧል ሲሉም እየተናገሩ ነው:: ንብረታቸው የተዘረፈባቸው ሰራተኞቻቸው የታሰሩ መሆኑን የጭልጋው አራሽ እንደፋራሽ ደጋግመው ነግረውኛል:: ለዚህም ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ምክር ቤቱ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓም "ኢንቨስተሮች ተፈናቅለዋል" ብለዋል:: ለዚህም ንግግራቸው አቶ ስዬ ጥሩ አድርገው ቃል በቃል ተችተውታል:: ይህን

እርሳቸው የተቹትን ትችት ግማሹን ከዚህ በታች አቅርቤዋለሁ። እኔ የምጽፈው ለቅስቀሳ ሳይሆን በትክክል ታሪክ ጠቅሼ ነው።

አቶ ስዬ አብርሃ አዲስ ነገር ጋዜጣ ቅጽ 1 ቁጥር 32 ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓም "እ. ኤ.አ ከ2001 ጀምሮ የድንብር ኮሚሽን እና አንድ ልዩ ኮሚቴ ማቋቋማቸውን ሰምተናል። ይህ እየተሰራ መክረሙን በይፋ የተነገረን እ.ኤ.አ በ2008 ከሰባት ዓመት በኋላ ነው። ኢሕአዴግ ከዐዊ ኃይለ ሥላሴ እና ከደርግ ወረሰኩት ያለውን የድንበር ጉዳይ ለምን ፓርላማውን እንኳን ሳያሳውቅ ሲሄድበት እንደቆየ አልገለጸልንም። ሰሞኑን የተፈጠረው ሁኔታ ባይፈጠር ኖሮስ ይገልጽልን ነበር ወይ? የሚል ጥያቄም ይጭራል። የድንበር ከለላ የራሱ ሕግ እና ሥርዓት ያለው አንድ መንግሥት እንደ ፈለገ የሚያደርገው ጉዳይ ያለመሆኑ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቢነግሩንም ይፋ ሳይደረግ ለአገሪቱ ፓርላማ እንኳን ሳያሳውቅ ለሰባት ዓመት ሙሉ ሲካሄድ የቆየው ሥራ በምን ሕግ እና ሥርዐት ሲያካሂደው እንደ ቆየ መንግሥት ግልጽ አላደረገልንም። ድንበርን እንደ ገና የማካለሉ ተግባር እንደሚናፈሰው ወሬ ያለቀለት ሳይሆን እየተከናወነ ያለው ወደፊት የወሰን ምልክት ለማስቀመጥ የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ሥራና የሚመለከት ነው ይለናል መግለጫው። ድንበሩን የማካለል ተግባር በውስጡ በቅድም ተከለት የሚሰሩ ሥራዎች አሉትና ሌሉቹ ሳያልቁ ወደ የወሰን ምልክት ማስቀመጥ እንደሚካሄድ ነው። ከዚህ በፊት መሰረት ያለባቸው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መኖራቸውን እውነት ነው።"

"እነዚህ ግን የድንበር ማካለሉ ተግባር አካላት ናቸው። እነዚህን ቅድመ ዝጅግት ያልቾኳቸውን ሥራዎች እየሠራችሁ ከሆነ የሚናፈሰው ወሬ ትክክል ነው ማለት ነው። ችካል መትከል የሥራው የመጨረሻ ምዕራፍ ነው። ይህ ከተሰራ ጉዳዩ አለቀለት ታሪክ ይሆናል ማለት ነው። ነገር ግን ሳያልቅ በፊት ጉዳዩ ይፋ በመውጣቱ ነው ስሕተት ተሰራ የምትሉት?በድብቅ የጀመራችሁትን ሥራ ጨርሳችሁ ነበር ሁሉ ካላቀለት በኋላ መርዶ ነጋሪ አለመሆናቸው እና አስቀድመው ጉዳዩን ይፋ በማድረጋቸው ነው የአሜሪካ ራዲዮ ማቢያ እና የጀምረም ራዲዮ ማቢያ እጅግ አጸያፊ አሉባልታ አናፈሱ ተብለው የተወገዙት መግለጫው እስከ አሁን እየተሰራ ባለው ሥራ አንድም የኢትዮጵያም ሆነ የሱዳን ገበሬ አልተፈናቀለም ይለናል። እኛም የሱዳን ገበሬ ተፈናቀለ የሚል ዜና አይደለም የሰማነው። የሱዳን ባለሥልጣናት ራሳቸው ኢትዮጵያ ለሱዳን መሬት መስጠቷን ተናገሩ የሚል ዜና ነው የደረሰን። ሱዳኖች መሬት ተጨምሮላቸው ሲያበቃ እንዴት ተብሎ የሱዳን ገበሬ ተፈናቀለ የሚል ዜና ይጠበቃል? እኛ የሰማነው የኢትዮጵያ ገበሬዎች መፈናቀላቸውን ከዚያም አልፎ በሱዳን መንግሥት መታሰራቸውን ነው። ይህን የሰማነው በጀርመን ራዲዮ እና በአሜሪካ ራዲዮ በኩል በቀጥታ ከሰለባዎቹ አንደበት ነው። ታዲያ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች አይደሉም ማለት ነው ወይስ ሐሰተኛ የሰዎች ድምጽ ነው የሰማነው።"

"አቶ መለስ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓም በፓርላማ ጥያቄ እና መልስ ፕሮግራም ወቅት በዚሁ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ ሲሰጥ ኢንቬስተሮች መፈናቀላቸውን ተናግረል። እነዚህ ገበሬዎች አይደሉምን? አብዛኛው የዚያ



አካባቢ አራሽ የሚያመርተው ምርት ለገበያ የሚያቀርብ መሆኑ እየታወቀ አቶ መለሰ በአንድ በኩል አንድም ገበሬ አልተተፈናቀለም በሌላ በኩል ደግሞ ኢንቨስተሮች ተፈናቅለዋል ማለቱ እና ኢንቨስተሮችን በገበሬ ምድብ ለማስገባት ያልፈለገበት ምክንያት ለምን ይኸን ኢሕአዴግ ለገበሬው የቆመ ስለሆነ በገበሬው ተፈናቀለ ቢባል የላቀ ፖለቲካዊ ጉዳት ስለሚያመጣ ጉዳቱን ለመቀነስ ተብሎ ይህን የቃላት ምርጫ ውስጥ የተገባው? ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ ይሁን ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እየተነገረን ያለው የማካለሉ ሥራ እንዳልተከናወነ ነው።"

"ማካለሉ ባልተከናወነበት ሁኔታ ያላችሁበት መሬት የኢትዮጵያ መሬት አይደለምና እና ልቀቁ ብሉ ገበሬዎቹ/ ኢንቨስተሮቹ እንዲነሱ የተደረገው ታዲያ በምን ሐሳብ ነው? ነገሩ ያለቀለት ጉዳይ አይደለም እያላችሁ በሌላ በኩል ደግሞ የሱዳንም ሆነ የኢትዮጵያ ያልሆነ መሬት አለ ብላችሁ ለመለየት እንዴት ቻላችሁ?የትኛውን ቃላችሁ እንውሰድ? አንድም ገበሬ አልተፈናቀለም የድንበር ማካለል ሥራ አልተከናወነም ወይስ ማካለል እየተከናወነ ነው። በዚሁም ምክንያት ኢትዮጵያ መሬት በማስረከቧ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች/ ኢንቨርስተሮች ተነፋቅለዋል የሚባለውን ይህም እንደ ባድመ ለእኛ እንድትሆን ተፈረደልን ዐይነት ጨዋታ ሊሆን ነው እንዴ? ሲሉ" ጽፈዋል።

ግንቦት 7 ድምጽ ሐምሌ 3 ቀን 2000 ዓም "ለሱዳን በተሰጠው መሬት የኢትዮጵያውያኑ ቁጣ እየፈነዳ ነው። ከሁመራ እስከ ጋምቤላ ድረስ ያለውን ርዝመት 1600 ኪሎ ሜትር ስፋቱ ደግሞ 50 ኪሎ ሜትር የሆነውን ለም መሬት የአቶ መለሰ አገዛዝ በድብቅ ለሱዳን መንግስት በመስጠት በአገር ቤትም ሆነ በውጭው ዓለም በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተቀሰቀሰ ቁጣ እያደር እየጋመ ነው" ሲል ጽፏል። የኢትዮጵያና የሱዳን ድንብር ኮሚቴ ደጋግሞ መግለጫ አውጥቷል። መግለጫው በተደጋጋሚ የወጣ ቢሆንም በእጄ ካሉኝ ጥቂቶቹን መግለጫው የወጣበትን ቀንና ወር ለማቅረብ እሞክራለሁ።

1ኛ ጥር 10 ቀን 2000 ዓም
2ኛ ሚያዝያ 1 ቀን 2000 ዓም
3ኛ ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓም
4ኛ ሚያዝያ 18 ቀን 2000 ዓም
5ኛ ግንቦት 2 ቀን 2000ዓም
6ኛ ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓም
8ኛ ግንቦት 30 ቀን 2000 ዓም
9ኛ ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓም
10ኛ ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓም
11ኛ ሕዳር 2 ቀን 2001 ዓም
12ኛ ጥር 14 ቀን 2001 ዓም
13ኛ ጥር 27 ቀን 2001 ዓም

በኢትዮጵያ አንድነት ስም የተደራጁ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶችና በተለያዩ ክፍለ ዓለማት ያሉ ኢትዮጵያውያን መሬት ለሱዳን መስጠት እንደሌለበት ተቃውመው የአቅዋም መግለጫ አውጥተዋል። አሁንም በእጄ ከሚገኙት ከዚህ

በታች ያሉትን እጠቅሳለሁ። የወጡ መግለጫዎች እነዚህ ብቻ ናቸው ለማለት ሳይሆን በእጄ ያልገቡ እናጅ ብዙ ናቸው።
1ኛ ሐምሌ 26 ቀን 2000 ዓም ሳንሆዜ ካሊፎርንያ
2ኛ ነሐሴ 17 ቀን 2000 ዓም ኮሎምበስ ኦሃዮ
3ኛ 2000 ዓም ሲያትል ዋሽንግተን የጎንደር እድርና መረዳጃ ማሕበር!
4ኛ ጥቅምት 2001 ዓም ከሎንደን
ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓም የወጣው ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ያቀረበው ገጽ 2 "የመለሰ ዜናዊ መንግሥት ከአጤ ምኒልክ እስከ ደርግ የነበሩት መንግሥታት ለሱዳን የሰጡትን መሬት ነው እኛ እያስፈጸምን የምንገኘው ማለቱ ይታወሳል። ይሁንና ከአጤ ምኒልክ እስከ ደርግ የነበሩት የኢትዮጵያ መንግሥታት የአገር ሉዓላዊነትን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና የግዛት አንድነት በተመለከተ ሲቻል በረቀቀ ዲፕሎማሲያዊ መንገድ ሳይቻል ብዙ መስዋዕትነት በመክፈል ድንበሩን ጠብቀውና በአንድ ወቅት በምዕራባውያን ተወስዶ የነበረውን መሬት አስመልሰው ለሚቀጥለው ትውልድ ያስተላለፉ ሲሆን በተለይ ደግሞ የወያኔ/ ኢሕአዴግ መንግሥት ለሱዳን ገጸ-በረከት ለማስረከብ እየተደገሰ ያለውን ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትርና ጥልቀቱ ደግሞ ከ30 እስከ 60 ኪሎ ሜትር የሆነውን ውሃ ገብ የኢትዮጵያ ለም መሬት ለሱዳን መስጠት ቅድመ-ወያኔ በሆኑ መንግሥታት የማይታሰብ ጉዳይ ነበር። ይልቁንስ ከወያኔ/ኢሕአዴግ በፊት የነበሩ የኢትዮጵያ መሪዎች ይበልጥ የሚታወቁትና ታሪካቸው ሕያው ሆኖ እስካሁን የቆየው የቱርክ፣የድርቡሽና የሌሎች የኢትዮጵያ ባላንጣዎች በሰሜንና በምዕራብ በኩል ያደረጉትን ጥቃት በራሳቸውና በሕዝባቸው ከፍተኛ መስዋዕትነት ድንበሩን አስጠብቀው ማቆየታቸው ነው" ሲል መግለጫው ያብራራል።

## በነፃነት ድምጽ ሬዲዮና የቀረበ ጥናት

ሰኔ 1997 ዓም ሁመራ ለሱዳን ሊሰጥ ነው ብለው ቀድመው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተናገሩ ሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም ናቸው። አሜሪካ መጥተው ጎንደሮች ወልቃይቴዎች ከሚበዙበት ኮሎምበስ ኦሃዮ ሕደው "ወያኔ ሁመራን ለሱዳን ሊሰጠው ነው" ብለው ተናግረው ነበር። ሰሚ ግን አላገኙም ነበር። ያሉት አልቀረም ወያኔ ከሁመራ እስከ ጋንቤላ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ለሱዳን መስጠቱ ርግጠኛ ሲሆን ነው እንደገና ስለድንበሩ ጥያቄ የተደረገላቸው። ግንቦት 2000 ዓም ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምና ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ደንበሩን አስመልክቶ ከቪኦኤ ጋዜጠኛ አዲሱ አበበ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ክልሉን በተመለከተ ወያኔ የሚያደርገውን ቅጥፈት አጋልጠዋል። እንዲሁም ግንቦት 2000 ዓም ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው አሜሪካ በሚተላለፉ የነፃነት ድምጽ ራዲዮ ማለትም ኢትዮጵያዊነትና ነፃነት ለሬዲዮ እንዲሁም በተለያዩ (ፓልቶኮች) በውይይት መድረኮች ደንበሩን አስመልክቶ ቃለ ምልልስ ካደረጉ በኋላ ይህን ታሪካዊና አገራዊ ሰነኝ ለአድማቾችና ለተሰብሳቢዎች አስምተው ነበር።ቃለ ምልልሱንና ንግግራቸውን ሳይሆን ስነኙ ይህ ነው። ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው!

## ወይ ሀገሬ

(ከሲ.ማ. አበባው ይግዛው፣ ግንቦት 2000 ዓ. ም.)

ሀገሬ ኢትዮጵያ ደጋ፣ ወይና ደጋ፣
ቆላና በረሃ እጅግ ባለጸጋ፣
ወንዞችሽ፣ ሐይቆችሽ፣ ባሕሮችሽ በሙሉ፣
ወራሪ ባልነካው ሀብት የታደሉ፣
ብቁዋንቁዋ፣ በጎሳ ሳይከፋፈሉ፣
ምን አለ ብጋራ ሰልማት ቢውሉ።

ወይ ሀገሬ ክብሬ ኢትዮጵያዊነቴ፣
ተሸርሽሮ አለቀ፣ ደከመ ጉልበቴ።
አወይ ወገኖቼ፣ ትንሹም ትልቁ፣
የሀገርን ታሪክ፣ ባህል በሚንቁ፣
ቢጋጠወጦቹ እንዲህ ትሳቀቁ!?

እረ አገሬ! አገሬ ራስ-ጋይንት፣ ማማው ደብረ ታቦር፣
የሊቃውንት አምባ፣ የነጋሪት አገር፣
እንዴት በወያኔ፣ ታሪኩ ይደፈር!?
ወይ አገሬ! አገሬ አዲስ ዘመን! በለሳ ቋሊሳ፣ ዘሐጌና መና፣
እንዳላሳደገ ያንን ሁሉ ጀግና፣
ይጫወትበታል የወያኔ ሙና?!
አይ አገሬ! ወይ አገሬ ጎንደር! የፋሲል መዲና፣
የእነ ኢያሱ ዙፋን፣ እንዲህ አረጀና፣
በእነሰም አይጠሩ፣ ሆኖ ሊቀር ወና?!
አገሬ አርማጭሆ! ፊልፊልና ተንፈል!
የጀግኖች መፍለቂያ፣ የጎበዞች ክልል!
እንደምን ይደፈር፣ በምንደኛ ምልምል?!
አይ አገሬ! ወይ አገሬ ደባርቅ! የእነጋተው አገር! አገሬ ወገራ!
አገሬ ወፍ አርግፍ! ወልቃይት ጠገዴ! ደንሻና ሁመራ!
እንዴምን ይደፈር! በትግራ ኩታራ!?

ወይ አገሬ ጭልጋ! ወይ አገሬ ቋራ!
የአባ ታጠቅ አገር፣ የጀግኖቹ ጎራ!
አገሬ አዳኝ አገር! አገሬ መተማ!\
ለኢትዮጵያ አንድነት አካሉ እንዳልደማ፣
እንዴት በወያኔ ታሩኩ ይጋማማ!?

አይ አገሬ! ወይ አገሬ ሰሜን፣ ሰሜን አምባራስ!
የነጋሪት አገር! ባለብዙ ቅርስ!
እንዴት በኩታራ፣ክብሩ ይገሰስ?!
አገሬ ሳሃላ! ወይ አገሬ ፀለምት! አገሬ በየዳ!
ደራሰጌ! ራስ ዳሸን!
እንዴት በወያኔ፣ ድንበርህ ይሸንሸን!?

ኧረ ጃሎ በሉ! ነብዝ ጃሎ በሉ!
ምንሽር ወልውሉ! መውዜር አቀባብሉ!
ትናንትን ረስቶ፣ ባንዳው እንዳመሉ!
ተከዜን ተሻግሮ፣ ልግዛ ይላል አሉ!

ወይ አገሬ ሰሜን፣ አገሬ ወገራ!
ለጠገበው ጥይት፣ ለራበው እንጀራ፣
ይህ ነበር ታሪክህ፣ በጣም የሚያኮራ፣
በቁም ሊበላህ ነው የራበው አሞራ።

የሚመነጥረው፣ የሚጠርገው ቢያጣ፣
ጎንደርን እንደልብስ፣ ሲቀደው ጋሬጣ?!
ያ መልቲ ወያኔ፣ ይኸው ልብ አግኝቶ፣
በሰሰ ቀናውና በቋንቋ አዘናግቶ፣
ወልቃይት ጠገዴን፣ ደንሻና ሁመራን፣ ከጎንደር ሰይቶ፣
ሰሊጥ እምርተናል፣ ይበል አፉን ሞልቶ?!
ዕንቋይ* ሲቀባጥር፣ ወልቃይት ልብ በል፣ አርማጭሆም አዳምጥ፣
ትግራይ ያበቅላል ወይ፣ አንድ አገዳ ሰሊጥ?!
ተርቦ ተጠምቶ፣ የሚቀምሰው ሲያጣ፣
ወያኔ ተከዜን፣ ተሻግሮ ሲመጣ፣
ከእንግድነት በቀር፣ መች ነበረው ጣጣ።

እኒያ ደጋጎቹ፣ አገር ዘበኞቹ፣ የሀገሬ ጀግኖች፣
ዘራቸው የት ጠፋ!
አይናውጣው ወያኔ፣ ታሪክ ሲያከረፋ!
ያባቶቹን ርስት፣ ገበሬው ሲቀማ!
ሁመራ ተመርቶ! መቀሌ ሲሰማ!
ምናለ አርማጪሆ?! ምናለ ወገራ?! ይኸንን ሲሰማ?!

ለሰሚው ግራ ነው፣ እንዲህ ያለ ነገር፣
የ እርማጭሆ ሱሪ! የወልቃይት ሱሪ! የወፍ አርግፍ ሱሪ!
መች እንዲህ ነበረ!!!
"ስሜን አርማጭሆ! ወልቃይት ጠገዴ!
ማረሻው ምንሽር! መጎልጎያው ጓንዴ!"
የሚለው ቀረርቶ፣ ውሸት ነበር እንዴ?!
"እንበሳ ተኝቶ፣ ጊደር ሸናችበት፣
ከምን ያለው ጊዜ፣ እኛ ደረሰንበት?!
ያንበሳ ልጅ ሙቶ፣ የጅብ ልጅ ገነነ፣
አሳሳልፍ አለ፣ ጸጉሩ እየበነነ"
ይባል የነበረው፣ እውን እውነት ሆነ?!

* ሰሰምን ዕንቋይ ለማለት ነው



ሰሜን አርማጭሆ፣ ወልቃይት ጠገዴ፣
እንዲህ እንደዋዛ፣ ሰሙን ሰወጠ እንዴ?!
ወገራና ሰሜን፣ አርማጭሆም አብሮ፣
ለትግራይ ጉልተኛ፣ ተከዜን ተሻግሮ፣
ገብሮ ያውቃል ወይ?! ቅመም ምጥን ሽሮ?!
የትግሬ ህዝብ ሲራብ፣ ቆርሶ ባጎረሰ፣
መሶብ ቤት ሆነና እጁን ተነከሰ!
ተፈርቶ ተከብሮ፣ ጀግና እንዳልኖረ!
ባይን አውጣ ወያኔ፣ ቤቱ ተደፈረ።
የወልቃይት ነብዝ፣ የጠገዴ ጀግና፣
ቤቱ ተደፈረ፣ ቀየው ተወረረ፣ ዘመን አረጀና!!!
ያንን ጀግና ትውልድ፣ የኖረ ተፈርቶ፣
እንደምን ይሰለበው?! በቋንቋ አዘናግቶ?!
እየተቀጠረ፣ እንዳልፏንተበት!
የሁመራን ሰሊጥ፣ ባለቤት ሆነበት?!
ወይ አገሬ! ኧረ አገሬ! አገር አጥፊው አረም፣ ባገሬ ሲስፋፋ፣
ሁሉም ተዳክመ፣ የሚያርመው ጠፋ!
የጊዜ ጉዳይ ነው፣ እኔ አልቀርጥም ተስፋ!
አገሬ ነው የሚል፣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣
ጥቃቱ ይሰማው፣ ሲቆረስ አካሉ!

ወይ አገሬ! ኧረ አገሬ!
ለሱዳን ሲከለል፣ መሬቱ ተቆርሶ፣
ዘንድሮ አርማጭሆ፣ በወየታው ለቅሶ፣
እንደዚህ ያዜማል፣ መልሶ መላልሶ።
"አረጀ አርማጭሆ! አረጀ አብደራፊ!
ይቀደድ ጀመረ፣ እንደጨርቅ እራፊ!"
አንተ ከፉ ዘመን፣ ነፍሰህን አይማረው!
የወንዶቹን አልጋ፣ ትንኙ ወረረው!
የወንዶቹን ማሳ፣ የህዝቡን አጽመ ርስት፣
ሱዳን አርማጭሆን፣ ከብት አሰማራበት!?
ዘብ ሆነን እንዳልኖርን፣ በጠረፍ ጥበቃ!
በራሳችን ሰዎች፣ እንዴት እንጠቃ?!
ገደብ ይበጅለት፣ ይኸ ነገር ይብቃ!

"ከአባቴ ባድማ፣ ፍግ አታፍሱበት!
አሳቱ ቢጠፋ! ረመጡ አለበት!"
ሁመራ መተማ፣ መተማ ሁመራ፣
መች ተደፍሮ ያውቃል፣ በጠላት ወረራ?!
ዛሬ አስጠቃን እንጅ፣ እኩይ ባላጋራ!

ሱዳንስ ያውቀናል፣ በቅርቡም በሩቁ፣
ይብላን ለነህጎስ፣ ለነትግል ብርቁ!!!
ከዛሬ በስተቀር፣ ነገን ለማያውቁ!

"ውሽልሽል ነው! ውሽልሽል ነው እርቁ!
አውድማው ይለቅለቅ! በሮቹም አይራቁ!
እንኳን ከቀያችን! ሱተት ብሎ ገብቶ!
ከሩቁ ያውቀናል፣ ሱዳን መች ዘንግቶ!
የጀግኖቹን ቀዩ፣ የህዝቡን አጽመ-ርስት፣
እንዴት እናያለን፣ ሱዳን ሲኮስበት!?

"የትግራይ ምንደኞች፣ እየተሳሳቡ፣
ግዙን ብንላቸው፣ ሲሸጡን አሰቡ!
ኢትዮጵያዊ ሰማ! ልብህ ኢያመንታ!
መሀል ዳር ይሆናል! ዳሩ ከተፈታ!"

<u>ቶክራ፣</u> ኧረ ቆሰ-ብን! ኧረ ፈጨብን!
እንጠብቃልን እስኪያቦኩብን!
ከዋሉ ካደረ፣ አይሰማ የለ!
ድርቡሽ እንደገና፣ ቋራን እቃጠለ!?
የአርማጭሆን መሬት፣ ድርቡሽ ተካፈለ?!
ማሕበረ-ስላሴን፣ ገዳሙን ከሰለ!?

ምን ትጠብቃለህ?! ከወያኔ መንጋ?!
አካልህን ሲያፈርሰው! እንደ ደዌ ስጋ?!
ሰሜን አርማጭሆ፣ ወልቃይት ጠገዴ፣ አርግዟል! አርግዟል!
አልተገላገለም! ገና ምጥ ተይዟል!
ፈራን አላልናቸው?! እርዱን አላልናቸው?!
እነርሱን እንደዚህ፣ ምን አስቀዘናቸው?!
ለሱዳን ጥብቅና፣ ማነው ያቆማቸው?!
"ተሳላ ነው አገር! ተሳላ ነው! ይጓዛል እንደ ሰው!
በየበሩ ቆሞ! ጀግና ታልመለሰው!!!"



ምዕራፍ 7

## የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚቴ የድምጽ ሁነድ

የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ መግለጫ ከዚህ የሚከተለውን ከተለያዩ የዜና አውታር አጠራቅሞ ያወጣው ሲዲ ክር ላይ የተወሰደ ነው:: ኢሕአዴግ በምስጢር የሰጠውን የኢትዮጵያን ግዛት በማስመልከት ባለፉት ወራቶች ሲዘግቧቸው የነበሩትን ተጠናክሮ ቀርቧል:: ይህ ታሪካዊ መረጃ ይሆን ዘንድ በጥሞና እንዲያዳምጡትና ላልሰሙት እንዲያሰሙ እንጠይቃለን:: የጀርመን ራዲዮ ጋዜጠኛ ተክሌ የኋላ ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞች ተጋድሎ በንጉሰ ነገስቷ ድፕሎማሲ ጥረትና በብርታንያም የጦር መሳርያ እርዳታ በፋሽስት ኢጣልያን ላይ ድል ተቀናጅታ አጤ ኃይለ ሥላሴ በክብር ተመልሰው ወደመዲናቸው አዲስ አበባ የገቡበት 67ኛው የድል በዓል ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ታስቦ ውሏል::"

"አጤ ኃይለ ሥላሴ ከእንግሊዝ ሀገር የስደት ኑሮ በሱዳን በኩል አቋርጠው የድል ጉዞ ሲጀምሩ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ ያደረጉት ጎጃም ውስጥ በቀድሞው የመተከል አውራጃ አሁን ቢሬሻንጉል ግሙዝ በሚሰኘው መስተዳደር ድንበር ላይ በምትገኘው ከተማ ኦሜድላ ላይ ነበር:: ያ የኢትዮጵያ አጽመ እርስት እውነት ለባዕድ ተሰጥቶ ይሆን? ከሁመራ እስከ ጋምቤላ 1600 ኪሎ ሜትር ከ30 እስከ 50 ያህል ዘልቆ የሚገባ የኢትዮጵያ ለም መሬት በኢሕአዴግ መንግሥት ለሱዳን መስጠቱም ሆነ የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ በሕዝብ ስም ተቃውሞ በማሰማት ላይ ያለ የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰኘ ድርጅት ለዶቼቨሌ ማብራሪያ ሰጥቷል::"

"ኮሚቴው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያሰማው የማስጠንቀቂያ ድወል ዳሩ ማህል ሲሆን ማህሉ ዳር ይሆናል የሚል ነው:: ይህ አስደንጋጭ መግለጫ የሚሰማው በወጣትነት ዘመናቸው በሱዳን በኩል የግብጽንና የቱርክን ተስፋፊዎች እስከ ሰናር አውራጃ ድረስ በመዝመት ያስተዳደሩት አባ ታጠቅ ካሳ አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ በወደቁ 140ኛው ዓመት እንዲሁም አባ በዝብዝ አጤ ዮሐንስ ዳር ደንበር ለማስከበር መተማ ላይ በተሰዩፉ 119ኛው ዓመት ነው:: አሁን በቅድሚያ አካባቢውን የሚያውቁ አንድ እማኝ እናዳምጥ:: አቶ ፋሲል ሰንደቄ እባላለሁ ንዋሪነቴ በጎንደር ከተማ ሲሆን ለስራ አሁን ችግሩ በተከሰተበት አካባቢ ወደ መተማም ወደቋራም ወደታች አርማጭሆም ለስራ እንቀሳቀሳለሁ ሊመግብ ይችላል ተብሎ የተተነበየለት ከሁመራ እስከ ቋራ ድረስ ከታችም እስከ ጋንቤላ ድረስ ያለበት የኢትዮጵያ እምቅ ሀብት ያለበት በጣም አሳፋሪ በሆን ሁኔታ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ እወክላለሁ የሚል መንግስት

ምዕራፍ 7

## የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚቴ የድምጽ ሠነድ

የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ መግለጫ ከዚህ የሚከተለውን ከተለያዩ የዜና አውታር አጠራቅሞ ያወጣው ሲዲ ክር ላይ የተወሰደ ነው። ኢሕአዴግ በምስጢር የሰጠውን የኢትዮጵያን ግዛት በማስመልከት ባለፉት ወራቶች ሲዘግቧቸው የነበሩትን ተጠናክሮ ቀርቧል። ይህ ታሪካዊ መረጃ ይሆን ዘንድ በጥሞና እንዲያዳምጡትና ላልሰሙት እንዲያሰሙ እንጠይቃለን። የጀርመን ራዲዮ ጋዜጠኛ ተክሌ የኋላ ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞች ተጋድሎ በንጉሰ ነገስቷ ድፕሎማሲ ጥረትና በብርታንያም የጦር መሳርያ እርዳታ በፋሽስት ኢጣልያን ላይ ድል ተቀናጅታ አጤ ኃይለ ሥላሴ በክብር ተመልሰው ወደመዲናቸው አዲስ አበባ የገቡበት 67ኛው የድል በዓል ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ታስቦ ውሏል።"

"አጤ ኃይለ ሥላሴ ከእንግሊዝ ሀገር የስደት ኑሮ በሱዳን በኩል አቋርጠው የድል ጉዞ ሲጀምሩ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ ያደረጉት ጎጃም ውስጥ በቀድሞው የመተከል አውራጃ አሁን ቢሬሻንጉል ግሙዝ በሚሰኘው መስተዳደር ድንበር ላይ በምትገኘው ከተማ አሜድላ ላይ ነበር። ያ የኢትዮጵያ አጽመ እርስት እውነት ለባዕድ ተሰጥቶ ይሆን? ከሁመራ እስከ ጋምቤላ 1600 ኪሎ ሜትር ከ30 እስከ 50 ያህል ዘልቆ የሚገባ የኢትዮጵያ ለም መሬት በኢሕአዴግ መንግሥት ለሱዳን መሰጠቱም ሆነ የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ በሕዝብ ስም ተቃውሞ በማሰማት ላይ ያለ የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰኘ ድርጅት ለዶቼቨሌ ማብራሪያ ሰጥቷል።"

"ኮሚቴው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያሰማው የማስጠንቀቂያ ድወል ዳሩ ማሀል ሲሆን ማሀሉ ዳር ይሆናል የሚል ነው። ይህ አስደንጋጭ መግለጫ የሚሰማው በወጣትነት ዘመናቸው በሱዳን በኩል የግብጽንና የቱርክን ተስፋፊዎች እስከ ስናር አውራጃ ድረስ በመዝመት ያስተዳደሩት አባ ታጠቅ ካሳ አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ በወደቁ 140ኛው ዓመት እንዲሁም አባ በዝብዝ አጤ ዮሐንስ ዳር ደንበር ለማስከበር መተማ ላይ በተሰየፉ 119ኛው ዓመት ነው። አሁን በቅድሚያ አካባቢውን የሚያውቁ አንድ እማኝ እናዳምጥ። አቶ ፋሲል ሰንደቄ እባላለሁ ንዋሪነቴ በጎንደር ከተማ ሲሆን ለስራ አሁን ችግሩ በተከሰተበት አካባቢ ወደ መተማም ወደቋራም ወደታች አርማጭሆም ለስራ እንቀሳቀሳለሁ አካባቢው የመሰረተ ልማት ሁኔታዎች ቢስፋፉለት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊመግብ ይችላል ተብሎ የተተነበየለት ከሁመራ እስከ ቋራ ድረስ ከታችም እስከ ጋንቤላ ድረስ ያለበት የኢትዮጵያ እምቅ ሀብት ያለበት በጣም አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ እወክላለሁ የሚል መንግስት

ከጋምቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን መሬት ከተሰጠ ይመጣል መከራ ገጽ 127

ምዕራፍ 7

የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚቴ የድምጽ ሠነድ

የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ መግለጫ ከዚህ የሚከተለውን ከተለያዩ የዜና አውታር አጠራቅሞ ያወጣው ሲዲ ክር ላይ የተወሰደ ነው። ኢሕአዴግ በምስጢር የሰጠውን የኢትዮጵያን ግዛት በማስመልከት ባለፉት ወራቶች ሲዘግቧቸው የነበሩትን ተጠናክሮ ቀርቧል። ይህ ታሪካዊ መረጃ ይሆን ዘንድ በጥሞና እንዲያዳምጡትና ላልሰሙት እንዲያሰሙ እንጠይቃለን። የጀርመን ራዲዮ ጋዜጠኛ ተክሌ የኋላ ኢትዮጵያ በጀግኖች አርበኞች ተጋድሎ በንጉሰ ነገስቷ ድፕሎማሲ ጥረትና በብርታንያም የጦር መሳርያ እርዳታ በፋሽስት ኢጣልያን ላይ ድል ተቀናጅታ አጤ ኃይለ ሥላሴ በክብር ተመልሰው ወደመዲናቸው አዲስ አበባ የገቡበት 67ኛው የድል በዓል ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ታስቦ ውሏል።"

"አጤ ኃይለ ሥላሴ ከእንግሊዝ ሀገር የስደት ኑሮ በሱዳን በኩል አቋርጠው የድል ጉዞ ሲጀምሩ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ብላ እንድትውለበለብ ያደረጉት ጎጃም ውስጥ በቀድሞው የመተከል አውራጃ አሁን ቢሬሻንጉል ግሙዝ በሚሰኘው መስተዳደር ድንበር ላይ በምትገኘው ከተማ አሜድላ ላይ ነበር። ያ የኢትዮጵያ አጽመ እርስት እውነት ለባዕድ ተሰጥቶ ይሆን? ከሁመራ እስከ ጋምቤላ 1600 ኪሎ ሜትር ከ30 እስከ 50 ያህል ዘልቆ የሚገባ የኢትዮጵያ ለም መሬት በኢሕአዴግ መንግሥት ለሱዳን መሰጠቱም ሆነ የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ በሕዝብ ስም ተቃውሞ በማሰማት ላይ ያለ የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰኘ ድርጅት ለዶቼቨሌ ማብራሪያ ሰጥቷል።"

"ኮሚቴው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያሰማው የማስጠንቀቂያ ድወል ዳሩ ማሀል ሲሆን ማሀሉ ዳር ይሆናል የሚል ነው። ይህ አስደንጋጭ መግለጫ የሚሰማው በወጣትነት ዘመናቸው በሱዳን በኩል የግብጽንና የቱርክን ተስፋፊዎች እስከ ስናር አውራጃ ድረስ በመዝመት ያስተዳደሩት አባ ታጠቅ ካሳ አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ በወደቁ 140ኛው ዓመት እንዲሁም አባ በዝብዝ አጤ ዮሐንስ ዳር ደንበር ለማስከበር መተማ ላይ በተሰየፉ 119ኛው ዓመት ነው። አሁን በቅድሚያ አካባቢውን የሚያውቁ አንድ እማኝ እናዳምጥ። አቶ ፋሲል ሰንደቄ እባላለሁ ንዋሪነቴ በጎንደር ከተማ ሲሆን ለስራ አሁን ችግሩ በተከሰተበት አካባቢ ወደ መተማም ወደቋራም ወደታች አርማጭሆም ለስራ እንቀሳቀሳለሁ አካባቢው የመሰረተ ልማት ሁኔታዎች ቢስፋፉለት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊመግብ ይችላል ተብሎ የተተነበየለት ከሁመራ እስከ ቋራ ድረስ ከታችም እስከ ጋንቤላ ድረስ ያለበት የኢትዮጵያ እምቅ ሀብት ያለበት በጣም አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ እወክላለሁ የሚል መንግስት

ልቀቁ አትዋጉ ለምን ከሱዳን ጋር ትጋጫላችሁ በሚል ሕዝቡን የኢትዮጵያን ሕዝቡን አጋዚ ተብሎ የሚጠራው ሠራዊት ከፊት የሱዳን ጦር በመካከል አስገብተው ሕዝቡን አሳሩን እያሳዩት ነው ጌታዬ እና 1600 ኪሎ ሜትር ከሁመራ እስከ ጋንቤላ የሚደርስ መሬት ለሱዳን አሳልፈው ለመስጠት የሱዳን መንግሥት ደግሞ በተቃራኒው ከፖርት ሱዳን ሽሬ ድረስ የሚደርስ የባቡር መስመር እንዲዘረጋ ተስማምተዋል ነው።”

“መረጃዎች እንደሚያሳዩትና ያለው መንግሥት ከሽሬ ድረስ የባቡር መስመር ለመዘርጋት ከሱዳን በኩል ፈቃድ አግኝቷል። የኢትዮጵያን መሬት ግዛቱን አሳልፎ ለመስጠት ተስማምቷል። ይህን የተስማሙት በአገሪቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ የሉዑካን ቡድን አቶ አዲሱ ለገሰ ሁለት ጊዜ በአካባቢው ወደ መተማ መጥተው የክልሉ ምክትል ፕሬዝዳንት አቶ ዘለቀ የሚባሉ እንዲያውም በአሜሪካ ራዲዮ ግቢያ ሁኔታውን አላውቅም ብለው ሲያስተባብሉ ሰምተናል። ሌላው የሰሜን ጎንደር ምክትል ዞን አስተዳዳሪ ተሰባስቦ ነው ይህን ስምምነት እንደፈረሙ ሕዝቡ በሚገባ ያውቃል።”

“በመደርጌ በወርቃማ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ የሱዳን ጦር ሰራዊት ሰፍሯል። ከፍተኛ የሆነ ሰዕባዊ መብት እየተካሄደ ነው ያለው! በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጥቃት እየደረሰ ነው ያለው። ቤቶች ተቃጥለዋል! ሰዎች እየታፈኑ ይወሰዳሉ የት እንደሚወሰዱ አናውቅም። በላይ አርማጭሆ አካባቢ በታች አርማጭሆ አብደራፊ ወረዳ በአብደራፊ አካባቢ በርካታ ቤቶች ተቃጥለዋል። ሰፋሪው እንዲለቅ ከተደረገ በኋላ ቤቶችን በሙሉ የሱዳን ወታደር ካቃጠለ በኋላ ሕዝቡ ለአቤቱታ ወደ መንግሥ ቢሄድም መንግሥት ግን ካሳ ይሰጣችኋል ምንም የሚያሰጋችሁ ነገር የለም። ቤታችሁን አስመዝግቡ የተቃጠለባችሁ ካሳ ይሰጣችኋል። ከሱዳን መንግሥት ጋር ወይም ከሱዳን ሕዝብ ጋር ምንም ዓይነት ግጭት መግባት አይገባም በሚል አሳፋሪ ሁኔታ ሕዝቡ መሬቱን ግዛቱን ተወልዶ ያደገበትን አገር ለቆ እንዲወጣ ነው በመንግሥት በኩል ግፊት እየተደረገ ያለው።”

“አሁንም በሰሜን ጎንደር በዚያው በአብደራፊ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ ጦር ነው ሰፍሮ ያለው። ሕዝቡ አሁንም አካባቢያችን ለቀን አንወጣም እትብታችን የተቀበረበት አገር ነው። እነሱ ኢቃጠሉን እናተ ደግሞ ግደሉን በሚል ሕዝቡ አካባቢያችን ለቀን አንወጣም በሚል ጥቃት እየደረሰበት ነው። በዚህ አካባቢ አሁን የሰፈረው ከሰሜን ጎንደር ከታች አብደራፊ ጀምሮ እስከ ቋራ ከየትኛውም የአማራ ክልል በሰፈራ መልክ ባለፈው አምስት ዓመት መንግሥት አምጥቶ ያስፈራቸው ገበሬዎች ናቸው።”

“ከዋግምራ ከተለያዩ የወሎ ክፍሎች ከጎጃም ከሰሜን ሸዋ የመጡ ገበሬዎች መንግሥት አምጥቶ አስፈራቸው አሁን ደግሞ ግዛቱን ለሱዳን አሳልፎ በመስጠት በታቸውን ለቀው ከመጡ በኋላ አገራቸው ላይ ያለው መሬት ለሌላ ገበሬ ከተሰጠ በኋላ አሁን ደግሞ በዚህ ባሉበት ግዛት ለሱዳን ተሰጥቷል በሚል እጥፍ ድርብ ችግር ነው እየደረሰባቸው ያለው። ለአይን ምስክርነት



በጎንደር ሆስፒታል ቆስለው መጥተው ሕክምና እየተደረገላቸው ያሉ ገበሬዎች ይገኛሉ። ተክሌ የኋላ አድማጮቻችን ለሱዳን ሳይሰጥ አይቀርም ለተባለው የኢትዮጵያ መሬት የኢትዮጵያ መንግሥት አቅዋም ምንድነው? በዛሬው እለት ያነጋገርኳቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ አቶ ዋሕደ በላይ በሰነዶች ላይ የተመረኮዘ መግለጫ ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ሊሰጡን ቃል ገብተዋል። እንጠባበቃለን እንደደረሰን እንስደምጣለን።”

“አሁን ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ጋር የተነጋገረው የዋሽንግተን ዲሲ ዘጋቢያችን አበበ ፈለቀ ያጠናቀረውን ዘገባ እናስከትላለን። አበበ ፈለቀ የኢትዮጵያ መንግሥት በድብቅ ከሱዳን ጋር ባደረገው ስምምነት መሬት ቆርሶ ለመስጠት እያደረገው ያለው እንቅስቃሴ ባስቸኳይ መቆም እንዳለበት ተጠየቀ። ተቀማጭነቱ አሜሪካ የሆነው የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ለዶቼቨሌ እንደገለጸው ከሁመራ ጀምሮ እስከ ጋምቤላና ወለጋ ድረስ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ለሱዳን ለመስጠት እንቅስቃሴ ተጀምሯል። በዚህም ሳቢያ በርካታ ኢትዮጵያውያን መፈናቀላቸውንና ንብረታቸውም መውደሙ ተጠቁሟል። ጉዳዩ ዛሬ የተጀመረ አይመስልም። ሲባል ሲነገር ሲብላላ የቆየ እንጂ ባለፈው ነሐሴ ወር 1999 ዓም የኢትዮጵያ መንግሥት ለሱዳን መንግሥት መሬት ቆርሶ ለመስጠት በድብቅ ማድረጉን አስመልክቶ ግልጽ ማብራሪያ እንዲሰጡ ጠቅላይ ሚንስትሩ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሁለቱም ምክር ቤቶችና ለየግል መንግሥታትና ግልጽ ደብዳቤ መጻፋቸውን ያስታውሳሉ። ከዚህ አሜሪካ ውስጥ የሚገኙት የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ አባላት ከዚያም ወዲህም በድብቅ ይደረጋል ያሉትን ድርድር ለሕዝብ ይፋ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል። ኮሚቴው የሕዝብ ግንኙነት ሀላፊ”።

“አቶ ዳንኤል ኀበዜ ጉዳዩ ከድርድር አልፎ መሬት ወደማካለል ብሎም ሕዝብ ወደማፈናቀልና ንብረት ወደማውደም ማምራቱን ገልጸውልኛል። ችካል በሕቡ መትከል እንደተጀመረና ሕዝቡ ደግሞ ያንን እየነቀለ ሲያነሳ ያለው መንግሥትም ሕዝቡን ራሱን እንዳይከላከል የማገድ ሁኔታ ሁሉ እንደደረሰ ተረድተናል። ያው ቅርብ ጊዜም ያው ካምፖች ተቃጥለዋል። ንብረቱ ወድሟል። ንብረቱ እንዲዘረፍ ሁኗል። ሲሰሩ የነበሩ ወደ 30 የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በሱዳን ተወስደዋል። የዚህ ችግር ገፈታ ቀማሽ የሆነው ሕዝብ የድረሱልኝ ጥሪ ያሳዘናቸው አቶ ዳንኤል ወደ ሱዳን የተከለለው የኢትዮጵያ መሬት እጅግ ሰፊ መሆኑን ጠቁመዋል። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ አዋሳኝ ያለው መሬት ነው ወደ ሱዳን እየተሰጠ ያለው። ከሁመራ ጀምሮ እስከ ጋምቤላ ወለጋ ያለው መሬት 1600 ኪሎ ሚትር እርዝመት ያለው መሬት በቋራ ያለው መሬት ከ30 እስከ 50 ኪሎ ሚትር መሬት ይደርሳል። ከአንዳንድ አካባቢ ደግሞ 30 ኪሎ ሚትር መሬት ስፋት ያለው መሬት ነው። ለም መሬት ነው እየተሰጠ ያለው”

“እና እየሀ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያውቀው እንዲያው ምክር ቤቱ ሳያውቀው የኢትዮጵያ መሬት ለባዕድ አገር መስጠት እጅግ አሳስቦናል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ሊናገር አልቻለም እንጂ ራሱን ለመከላከል እንኳን ቢሞክር አጋዚ

በሚባል ሰራዊት እንዳትንቀሳቀሱ እየተባለ ማስፈራሪያ እየተሰጠ ነው። እና አካባቢው ከደለሉ ጀምሮ እስከ ሱፍ ውሃ አካባቢ ርዝመት ያለው ቦታ ነው በቋራ አካባቢ ያሉትን መሬቶችን ሰባት ገብያ የሚባሉትን አካባቢዎችን እየተሰጠ ነው በዚያ አካባቢ። የኢትዮጵያ መንግሥት ለሱዳን መሬቱን አሳልፎ የመስጠቱን መነሾ ደግሞ ሱዳን በምላሹ የተቃውሞ ኃይሳትን በግዛቷ እንዳይንቀሳቀስ ቃል መግባቷ መሆኑን አቶ ዳንኤል ኀበዜ ገልጸዋል።"

"የተሰጠው መሬት ሁሉ እነ አጤ ዮሐንስ ሕይዎታቸውን ያሳለፉበት መሬት ነው። እነ ቴዎድሮስ ገና በሕፃንነታቸው ጀምሮ እየተዋጉ ደንበሩን ሲያስከብሩ የቆዩበት መሬት ነው። የኢትዮጵያ መሬት ነው። ኢትዮጵያውያን ለአንድነት ልእዋላዋይነት አብረው በችግር ጊዜ ተባብረው ነው የሚቆሙ አሁን ያለው መንግስት ባድሜ አገራችን ደንበራችን ተወረረ ብሎ ኢትዮጵያውያን እህት ወንድሞቻችን አልቀዋል እና ይህም ደንበራችን ነው። እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያውቀው በድብቅ መስጠት ከሃዲነት ነው። በዚህ መሰረት ኮሚቴው ጉዳዩን በቅርብ እየተከታተለ ማጋለጥን እንደ ሚቀጥል ጠቁሟል። የሱዳን ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ ክልል ገብተው ንብረት ካቃጠሉ ገበሬዎችን ከወሰዱ በኋላ እዚያው እንደሰፈሩና ከውጭ ሄደው ልማት ላይ የተሰማሩን ኢትዮጵያውያን ባለሃብቶችን ጨምሮ የሌሎችን ንብረት መውደኑ አቶ ዳንኤል ኀበዜ ጠቁመዋል። የሱዳን ወታደር ኢትዮጵያ ካለው መሬት ውስጥ ገብቶ ካቃጠለና አራሾችን ከወሰደ በኋላ የፖሊስ አፊሱን ከፍቷል።"

"ከዚያ ያሉ ገበሬዎች አሁንም ወደ ከተማ ሕደዋል። ከመንግሥትም ጩኸታቸውን እያቀረቡ የማስፈራራት ችግርም እየገጠማቸው ነው። ሆኖም ግን ይሄ የአገር ጉዳይ ስለሆነ ንብረቱ ተቃጥሎ እስከ ትራክተሩ ተዘርፎ ሕዶ እንቨስትመንት ያካሄዱ ከውጭ እንኳን ከእስራኤል 4 ዜጋዎች ኢትዮጵያዊ ትውልዳቸው ከአሜሪካ ደግሞ 4 የአሜሪካ ዜጋ የሆኑ ኢትዮጵያውያን እንቨስት ያደረጉ ንብረታቸው ሁሉ ወድሟል። ይሔ በደለሉና በሱፍ ውሃ በቋራ አካባቢ ባለው እንቨስት ሲያደርጉ የነበሩ ናቸው።"

"ጠቅላይ ሚንስትሩም ሆነ ለተወካዮች ምክር ቤት ብሎም በየደረጃው ለሚገኙት የመንግሥት አካላት ለጻፉት ደብዳቤ እስካሁን ምላሽ አለማግኘታቸውን የገለጹት አቶ ዳንኤል ኀበዜ ሕዝብ ሳያውቀው በድብቅ ገዳሪፍና ካርቱም ላይ በተደረገ ስምምነት መሬት አሳልፎ መስጠቱ እንዲወገድና እንዲቆም ጠይቋል። የዶቸቬሌ ራዲዮ አበበ ፈለቀ ከዋሽንግተን ዲሲ። የተከበራችሁ አድማጮቻችን እንደምን አላችሁ ለአለፉት ሰስት ወራት በተከታታ የአዲስ ድምጽ ርዲዮ ከኢትዮጵያ የሚያገኛቸውን መረጃ ለእናንተ እያቀረበ በውጭ አገርም በጉዳዩ ተቆርቁረው የተለያዩ ጹሁፎችን የሚጽፉ ኢትዮጵያውያንን እያቀረበ ለናንተ በሱዳንና በኢትዮጵያ የተፈጠረውን ዳር ደብንር ሁኔታ እንድታውቁ ለማድረግ ሞክረናል። የዚህ ፕሮግራም ዋና ዓላማ ከዚያ አካባቢ ችግር የደረሰባቸው ኢትዮጵያዊ ችግራቸውን ኢትዮጵያውያን በሙሉ ተረድተን የኢትዮጵያ መንግሥትም ጉዳዩን አውቆ አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግላቸው ለማድረግ ነው። እና ጉዳዩንም በተጨባጭ



ከደረሰባቸው ወይም ጉዳቱ ከደረሰባቸው ወገኖችን እንድትሰሙ ነው የኛ ዓላማ በዚህ መሰረት ዛሬ አቶ ጥላሁን ተድላን ከኢትዮጵያ በቀጥታ አናግራለሁ አቶ ጥላሁን ተድላ ችግሩ ከደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን አንዱ ናቸው።"

"ሁኔታው እንዴት እንደተፈጠረና ምን ሁኔታላይ እንዳለ ያስረዱናል አቶ ጥላሁን ተድላ ጊዜዎትን ወስደው የደረሰበዎትንና በሌሎችም ኢትዮጵያውያን እንቨስተሮችም እንዳሉ ሰምተናል። የደረሰውን ለማስረዳት ፈቃድዎ ስለሆነ በአድማጮቼ ስም በመላው ዓለም ከልብ አመሰግናለሁ እግዜር ይስጥልኝ አቶ ጥላሁን። እ እሽ እስቲ ይንገሩኝ ምንድነው የሆነው በእርስዎም ሌሎችም የደረሰባቸው ምንድነው እስኪ ታሪኩን ከመጀመሪያው ጀምሮ እርስዎ ምንድነው ያልወት ንብረት እዚያ የደረሰብወት ምንድነው በሌሎችስ የደረሰው ምንድነው እንዴት ነው ነገሩስ የጀመረው? ኧ እንግዲህ እኛ በሰሜን ጎንደር ዞን በቋራ አካባቢ ሰንጠረዥ የሚባል ቦታ ኧ ቴዎድሮስ እርሻ ልማት በሚል ስያሜ ከ97 ጀምሮ በእርሻ ላይ እገኛለሁ።"

"ኧ በአሁኑ ወቅት የደረሰው ችግር በአቋቋምኩት የእርሻ ልማት ኧ 2000 ለ2001 የምርት ዘመን ቀደም ሲል እጠቀምበት የነበረውን አራት መቶ ሄክታር መሬት በማጽዳትና ለመዘጋጀት ላይ እያለሁ የሱዳን ጦር ሰራዊት ወደ እርሻው በመግባት ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎችን ዘርፎ ሲወስድ መውሰድ ያልቻለውን ማረሻና ኧ ቁሳቁስ የተለያየ ከማቃጠሉ በተጨማሪ በእርሻው ላይ የነበሩት 8 ሰራተኞቼን በማፈን መውሰድና በአሁኑ ወቅት ያሉበትን ለማወቅ ባለመቻላችን ችግር ውስጥ እንገኛለን። እህ ይህ የሆነው በዚህ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ነው? አዎ የዛሬ ሁለት ሳምንት አካባቢ ነው። በ13 ነው በኢትዮጵያ አቆጣጠር እህ አሁን ያለፈው የእርስ እርሻ የሚገኘው በየት ቦታ ነው ከዚህ ከእርስዎ በፊት ደግሞ በሌሎች አካባቢ ይመስለኛል ወደ አብደራፊ ወደ ሁመራ ወደላይ አካባቢ ተመሳሳይ ችግር እንደደረስ ነው የምንሰማው። በአጠቃላይ ችግር ደረሰበት የሚባለው ቦታ እርቀቱ እርዝመቱ ማለት ከ1600 ኪሎ ሜትር ድረስ እንደሚደርስ ነው ዳርዳሩ በሙሉ የምንሰማውና ከእርስዎ በፊት የሆነ ነገር አለ? የዚህ ዓይነት የሰሙት ነገር አለ በሌሎች ቦታዎች?"

"እንግዲህ አብደራፊ ለእኛ እሩቅ ቦታ ነው። ኧህ ይህ ወሬ ባለፈው ጊዜ የሆነ ግጭት ሕዝቡ ከሱዳኖች ጋራ ተጋጭቷል የሚባል ወሬ ነበረ። በትክክል ግን ከቦታው አልሄድኩም በወሬ የሰማሁት እኔ የማውቀው በኔላይ የደረሰውን ብቻ ነው። ኧህ በእኔና በሰራተኞቼና ንብረቴ በነበረበት በትክክል መናገር የምችለው። እንደሰማነው እርስዎ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች የሌላ አገር ዜጎች ሳይቀር በአካባቢው ቦታ ተመርተው እንደሚሰሩ ነው ካሉ የወዴት የወዴት አገሮች አሉ እርስዎች በምን መልክ ነው መሬቱን ከመንግስት አግኝተው ነው? ሕጋዊ የሆ ባለቤትነት መብት አለዎት? የእርስዎንና የሌሎችን እያጣቀሱ ይንገሩኝ? ሌሎች አንድ 3 የአሜሪካ ዜጎች አሉ።"

"እኔም በዜግነት አሜሪካዊ ነኝ ሁለት እንትን ያው ኢትዮጵያዊነቴን በዚሁ ለዚህ ስራ ያበቃኝ አንዱ እርሱ ነው። 1 እስራኤላዊ አለ። 2 ከሳውዲያ

ዓረቢያ የመጡ ባለንብረቶች አሉ:: በዚህ አካባቢ 6 ባለሀብቶች በሰፊው 4 መቶ ሔክታር ደረጃ ተሰማርተናል:: ሌሎችም በመቶ ሔክታር በ30 ሔክታር በ50 ሔክታር የተሰማሩ ሰዎች አሉ:: ይህን የተመራችሁት ከመንግሥት ጋር ተነጋግራችሁ ነው? ሕጋዊ የሆነ የባለቤትነት መብት አላችሁ ሁላችሁም? አዎ መንግሥት በትክክል የሚያስፈልገነን ነገር አዘጋጅቶ ቦታውን በግብርና ኃላፊዎች ተመድቦልን ተለክቶ 15 ዓመት የሊዝ እኔ በእርሻው ላይ ከተሰማራሁ 3 ዓመት ሁኖኛል:: አብረን ነው በአንድ ላይ ነው የተቀበልነው ሁላችንም:: ሰሞኑን ጉዳዩን እንደሰማሁት ይቅርታ ለመንግሥት እያስረዳችሁ እንደሆነ ነው የምንሰማው አሁን አስረድታችኋል ከመንግሥት ያገኛችሁት ነገር አለ?"

"አዎ ጉዳዩን አስመልክቶ በመሬቱ ለ15 ዓመት የሚቆይ ክራይ ከክልሉ መንግሥት በመውሰድና ለአለፉት አመታት እየተጠቀምኩበት እንደነበር በመጥቀስ የተከሰተውን ችግር ለመንግሥት አካላት እስከ ጠቅላይ ምኒስትሩ ድረስ በጹሑፍ አስታውቄያለሁ አመልክቻለሁ ኽህ መንግስትም ትኩረት ሰጥቶ ምናልባት መፍትሄ እንደሚሰጠን በመጠባበቅ ላይ ነን:: በእኛም በኩል እንግዲህ እኛም ይሄን እናንተን ሌሎችንም የምናቀርብበት በትልቁ ለዚህ ጉዳይ በመጀመሪያ መፍትሄ ያመጣል ብለን የምንገምተው መንግሥት ነው:: መብታችሁን አስከብሮ ዙሮም ደግሞ ከእናንተም አልፎ የአገሪቱን መሬት ነው መሬቱ እና ያነን ያስከብራል የሚል ተስፋ አለን:: በዚህ ምክንያት ነው እንግዲህ ይህን ፕሮግራም በተደጋጋሚ እየሰራን ያለነውና የሚያስተላልፉት መልክት ምንድነው አሁን ለሚያዳምጡዎ ኢትዮጵያውያን ለሚሰሙ የመንግሥት ባለሥልጣን ተወካዮች የእርስዎ መልዕክት በአሁኑ ሰዓት ምንድነው? እንግዲህ እኔ የምለው በኢትዮጵያዊነት ከአንተም ከራስህ ጀምሮ እኔም ስናገር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለታሰሩት ወንድሞቻችን በችግር ላት ላሉት ይሄ የሕይወት ጉዳይ ስለሆነ እኔ ከዚህ ከአሜሪካ ድረስ መጥቼ ይህን ሥራ ስሰራ ባንዲራየን ጥላ አድርጌ መንግሥት አምኜ እንዲሁም ወንድሞቼንና ሰራተኞቼን ኢትዮጵያውያን ደግሞ ያለችኝን ነገር በጋራ ተካፍለን አንዱ በሥራው አንዱ በኃላፊነት አንዱ በምን ተሰማርቶ እንግዲህ ለመስራት ደፋ ቀና እያልን ሳለ ነው ያ የሆነው::"

"እኒህ ሰዎች እንግዲህ ከመጥፎ ቦታ አልተገኙም:: ከስራ በቶ ናው የተገኙት:: እና እኔ አደራ የምለው ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለመንግሥትም ሆነ ተባብሮ እነዚህ ሰዎች (ርሊዝ) የሚሆኑበትን ነገርና ከአሉበት ችግር ነፃ እንዲሆኑ ነው እኔ የምማጸነው ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወገን ሕዝቡም መንግሥትም ተባብሮ እኒህን ሰዎች ነፃ እንዲያደርግልኝ እና እያንዳንዱ---ምክንያት ብዙ በሀዘን ላይ የተቸገረ ቤተሰብ አለ:: ለዚያም መፍትሄ ያስፈልጋል ያሉበትን እናውቅም:: በዚህ በውነቱ ለመንግሥትም በትልቁ እማፀናለሁ:: ለምትሰሩት ሁሉ ለእያንዳንዱ ከመንግሥት ጎን ሁናችሁ እንድትረዱን እፈልጋለሁ::"

"በጣም ጥሩ ነው እኛም እንግዲህ ይህን መልዕክት ለሕብረተሰቡ እናደርሳለን:: በተቻለ መጠን በዚህም አካባቢ ጉዳዩ አስቆጭቷቸው ራሳቸውን ተቆርቋሪ ኮሚቴ በሚል አቋቁመው የተለያዩ ኢትዮጵያውያን ኣንዳንዶቹ በጣም በዚህ



ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌላም ጉዳይ ላይ ለኢትዮጵያ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ተሰባስበው መንግሥትን እየጠየቁ ነው:: ከመንግሥትም አልፎ የሱዳንን መንግሥትን ለማናገር ቅድመ ዝግጅት አላቸው:: እና ሰውን በዚህ ጉዳይ ላይ ለማንሳሳት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው:: ግን አንዳንድ ጊዜ እርስዎ ነዎት እኔ የደረሰብኝን ለመናገር እንደኛ መብቴም ነው:: ሁለተኛ መንግሥትንም ነው እየተማፀንኩ ያለሁት እና የደረሰብኝን ለመናገር ወደ ኋላ አልልም ብለው ቀርበዋል:: ከእርስዎም በፊት አንድ ሌላ ሰው አቅርቤ ነበር::"

"አንዳንዶቹ ግን ምናልባት ምናልባት መንግሥትን ያስቆጣብን ይሆናል በሚል ፍርሃት ወደ ኋላ የሚሉ አሉ:: እና ይህን በመናገራችሁ በመንግሥት በኩል ምን ተፅዕኖ ያመጣል ብለው ያስባሉ? በዚህ ጉዳይስ መንግሥት ተፅዕኖ እንዳያረግ ወይም ፖለቲካ አድርጎ እንዳያየው ለመንግሥት ለራሱ በቀጥታ የሚያስተላልፉት መልዕክት አለ? እኔ ለዚህ የማፍርበት ነገር የለም:: ለምን እኔ አንደኛ ስርዓቱን አምኜ አገሬን ስለምወድና ----ወደ ሀገሬም ስመጣ በደስታ ነው:: መንግሥትም ጥሪ አድርጎልኝ ጥሩ መስተንግዶ ተደርጎልኝ --- መንግሥት ለሰጠኝ በጣም የሚያስደስትና የሚያስደንቅ ነው ያጋኘመኝ:: እና እኔ ስናገር እኔ ስለፖለቲካ የፖለቲካ ሰው ብሆን ኑሮ በአጠቃላይ ወደዚህ አልመጣም:: የፖለቲካ ሰው ወደ ግብርናም አይገባም:: እኔ ወደ ልማት እንጂ የፖለቲካውን እንትን አላውቀውም:: ስለዚህ ይሄ ወደ ፖለቲካ የሚዞር ነገር አይደለም:: ይሄ እኔ አሁን የምናገረው በትክክለኛ መንግሥትም አምኖበት በሰጠኝና (እስታፕሊሽ)ባደረኩበት ቦታ ላይ ከንብረቱ በላይ የሰዎቹ ሕይዎት ትልቅ ግምት ተሰጥቶት ሰዎቹ እንዲወጡ እንጂ ነገሮቹን ያው እንግዲህ ይህን ሥለተናገርኩኝ ወደ ፖለቲካ ይዞራል ብዬ አላስብም:: መንግሥትም በዚህ መልኩ እንደማያስብ እርግጠኛ ነኝ:: አቶ ጥላሁን ለሰጡን ማብራሪያ በጣም አመሰግናለሁ:: ወደፊትም እንዲሁ እየደወልኩ እጠይቅወታለሁ:: ሁላችንም ከእርስዎና ከሌሎች እንደርስዎ ካሉ ኢትዮጵያውያን ጎን ቁመን የእናንተ መብት እንዲቀበር ለማድረግ ጥረት እናደርጋለን እግዜር ይስጥልኝ አቶ ጥላሁን::"

"የኢትዮጵያ መንግሥት በምዕራባዊ ኢትዮጵያ ሱዳን ደንበር አካባቢ የኢትዮጵያ ይዞታ የነበረ መሬት ብዙዎች ባላወቁት ሁኔታ ለሱዳን አስረክቧል የሚለውን ዜና የሱዳን መንግሥት ባለስልጣናት አረጋገጡ:: በአለፈው ዓመት ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓም የምስራቃዊ ሱዳን ጠቅላይ ግዛት አል ገዳሪፍ አስተዳዳሪ አብዱረህማን አልኪዲር በዚያው እለት የተሰበሰበ የሱዳንና የኢትዮጵያ የጋራ ኮሚቴ 17 የኢትዮጵያ መንደሮች ለሱዳናውያን የማስረከብ እርምጃውን ይጀምራል ብለው ካስታወቁ ወዲህ የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰኘ የኢትዮጵያውያን ድርጅት በተደጋጋይ የኢትዮጵያ መሬት ለባዕድ መንግሥት ሊሰጥ ነው የሚል የማስጠንቀቂያ መለዕክት ሲያሰማ መቆየቱ ተመልክቷል:: ኮሚቴው መሬቱን ለሱዳን ተሰጥቷል ሲል ያወጣውን መግለጫ የሱዳን መንግሥት ባለሥልጣናትም አረጋግጠዋል::

"በኢትዮጵያ የሱዳን ኢምባሲ አማካሪ ሚስተር ማህመድ ሐሰን ባብኬር ይህ የሁለቱን አገሮች ደንበር ለማካለል በመካሄድ ላይ ያለ ተግባር ነው:: ግን የሱዳን መንግሥት ያገኘው ያተረፈው መሬት ሳይሆን የሱዳን መንግሥት ቦታ የነበረ ነው:: በሁለቱ አገሮች መንግሥታት መካከል ቀጣይነት ያለው የእረጅም ጊዜ ድርድር ሲካሄድ ቆይቷል:: እናም አሁን ነው ይህን ጉዳይ እልባት እንዲያገኝ ያደረገው:: የሱዳን ጦር ሰራዊት ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ገብቶ የኢትዮጵያውያንን የእርሻ መሬት እንዲይዝ ተደርጓል 30 ገደማ የሚደርሱ ኢትዮጵያውያንን ሱዳኖች አስረው መውሰዳቸው ይነገራልና ለምንድነው ይህን ዓይነት የኃይል እርምጃ የምትወስዱት ተብሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ይህ አሉት ነው እውነት አይደለም:: በፍጹም መልሴም በጣም ግልጽ ነው:: በኢትዮጵያ በኩል የወሰድነው እስረኛ የለም::" ይህ ከዚህ በላይ የተናገሩት ሱዳናዊው ናቸው::"

ይህን ከዚህ የሚቀጥለው ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ናቸው የሚናገሩት:: "በሺህ ዘጠኝ መቶ 7 እንደፈረንጆች አቆጣጠር ደንበሩ ከተወሰነ በኋላ በሺህ ዘጠኝ መቶ 9 ዓም ሜጀር ጌዊይ የተባለው እንግሊዛዊ ደንበሩን አካሏል:: ዲማርኬሽን አድርገዋል:: ሜጀር ጊዊን ያካለሉት ደንበር ስለዚህ በኢትዮጵያና በሱዳን መኻከል ያለው ድንበር (ዲምርት) ብቻ ሳይሆን በስምምነት የተወሰነ ተኳላል:: ዲማርክ ተደርጓል:: ሱዳን ነፃ ከወጣች በኋላ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት ሞያተኞች ተመድበው ጉዳዩን ካጠኑ በኋላ የደረሱበት ድምዳሜ የጌዊን መስመር ተብሉ የሚታወቀው የሻለቃ ጊዌን ያካለሉትን መስመር ከአንዳንድ አካባቢዎች ከሺህ ዘጠኝ መቶ 7 ስምምነት በተሻለ ሁኔታ ለኢትዮጵያ እንደሚጠቅም ነው የተገነዘቡት:: ከዚህ በመነሳት በ1972 እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር በኢትዮጵያና በሱዳን መሀከል በዚህ ጉዳይ ላይ ስምምነት ተደረሰ:: ይሄ ስምምነት 1ኛ የጊዌን መስመርን መቀበል ነው:: 2ኛ ከዳግላሽ ተራራ እስከ ተከዜ ድረስ --አካባቢ የጊዊን መስመርን ተግባራዊ ማድረግ በሁለቱ ወገኖች ዜጎችን እንዳያሰናክል ስለሚችል ያ አካባቢ ዳግም እንዲካለል ሪዲማርኬትድ እንዲሆን ሪዲማርኬትድ ከመሆኑ ዳግም ከመካለሉም በፊት የጋራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንዲወስድ ያ እስኪሆን ድረስ ዳግም እስኪካለል ድረስ ሪዲማርኬትድ እስኪሆን ድረስ በይዞታው ያለው ሁኔታ ረግቶ እንዲቀጥል --እንዲጠበቅ የሚል ስምምነት ነው የተፈራረሙት:: ይሄ እንደፈረንጆች አቆጣጠር 1972 ዓም በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥትና በሱዳን በኒቤሪ መንግሥት ወቅት ነው::"

ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ በተናገሩት ላይ ሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደ ማርያም ትክክል አለመሆናቸውን ሲተቹ "ይህንን እንደ (ኮሚኒኬ) ዓይነት ነገር ነው ስምምነት አይደለም:: ለሱም ቢሆን በ1972 ዶክረት ምናሴ ኃይሌ ነበረ መሪው ወይዘሮ ዮዲት አቶ ጌታቸው በቀለ ነበሩ እነዚህ ሰዎች በሕይወት አሉ:: 2ኛው በ1973 ደግሞ ሰጡ የተባለው ከዚያም ውስጥ ጀኔራል ወልደ ሥላሴ በረካ አሉ:: አሰፋ መንገሻ አለ:: መንግስቴ ደስታ አለ:: የእርሱንም መሪው ዶክተር ምናሴ ነበረ:: ከዚያ ላይ ሁላችሁም የምታስታውሱት ይመስለኛል:: በ1972



ላይ የጊዊን መስመር እንቀበላለን የሚል ከዚህ ኮሞኒቲ ውስጥ ነበረ ያም የተደረገው ምናልባት እንደሚመስለኝ ከነታየ ጥናት ጋር ተያይዞ ነው:: በኋላ ፓርላማ ውስጥ ትልቅ ረብሻ ተነሳ:: ኢትዮጵያም ውስጥ በአጠቃላይ እንዴት መሬት ይሰጣል መሬት ሰጡ አጤ ኃይለ ሥላሴ ተብሉ ነገሩ ቀረ ቆመ:: ያ-- ስምምነት እሱም ራሱ ይህን ያህል ስምምነት የሚባል አይደለም:: አግሪ ቱ አክሴብት ዘቤስክ ዲማርኬሽን ሜድ ባይ ሜጀር ጊዌን) ነው የሚለው:: በኋላ ግን በ1973 እንደገና ዶ/ር ምናሴ በሚመራው ቡድን በሚነጋገርበት ጊዜ እንደአዲስ ጀምረው ኢትዮጵያውያን የሚያርሱትን መሬት ሱዳኒዮች የሚያርሱትን መሬት የሚያጠና ኮሚቴ ይቋቋም የሚል ነው በ1973 ዓም በፈረንጆች አቆጣጠር ያደረጉት ስለዚህ በአጤ ኃይለ ሥላሴ በደርግም የጌዌንን መስመር እንዳለ ከላይ እስከታች እንቀበለው የሚል ስምምነት አልተደረገም::" አሉ ሊቀ ጠበቡቱ::

ይህ ደግሞ የርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ቃል ሲሆን በተቻለ መጠን ቃል በቃል ለመገልበጥ ሞክሬአለሁ ነገር ግን አየር በገዙበት አልሰማኝ ያለ ቃላት --- እያደረኩ ትቸዋለሁ "ስለዚህ በተደረገው ስምምነት መሰረት የደርግም መንግሥት ይህ ጉዳይ እንዲጠና ብሉ ወሰነ:: እንዲጢና ብሉ ወስኖ ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በጉዳዩ ላይ እውቀት አላቸው ተብሉ የሚገመቱ ፕሮፌሰሮችና ሞያተኞቅችን አሰባስቦ ኮሚቴ አቋቁሞ ኮሚቴው ነገሩን እንዲያጠናው ወሰነ:: ኮሚቴው አጥንቶ ሲያበቃ ለደርግ መንግሥት ሰጥቶ ግምጋሜ 1ኛ የጊዌንን መስመር መቀበል አማራጭ እንደሌለው 2ኛው የጉዌን መስመርን መተግበር በአካባቢው ሕዝብ ላይ ችግር እንዳይፈጥር:: ሕብረተሰቡን ማማከርና ማወያየት እንደሚያስፈልግ ነው ያረጋገጡት::"

አሁን ሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም ሲተቹ "አንድ በግድ መነገር ያለበት ይሄ በዩንቨርስቲው የተቋቋመው ኮሚቴ ጄኔራል ታየ ጥላሁን የአገር አስተዳደር ሚኒስተር የነበረ ጊዜ እርሱ ጠይቆ የተቋቋመው ኮሚቴና 5 ሰዎች የነበሩበት ሲሆን ከነዚህ ከ5 አራቱ አሁንም አሉ:: ወርቁ ተፈራ ብቻ ነው የሞተው:: ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ፕሮፌሰር ብርሃኑ አበበ፣ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደ አረጋይ እና እኔ አለን:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳለው እነዚህ የጉዌንን መስመር መቀበል አለብን ምርጫ የለንም ብለዋል ነው የሚለው ይሄ ፍጹም ከውነቱ የራቀ ነው" ሊቀጠበብቱ::

እርሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ "በመጀመሪያ የነበረው ድርድር ከመቋረጡ ባሻገር በዚሁ አካባቢ ያሉ ከዳግላሽ እስከ ተከዜ ባለው አካባቢ በድንበር ዙሪያ አንዳንድ ግጭቶች በኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይልና በሱዳን መከላከያ ኃይል መካከል አንዳንድ ግጭቶች ነበሩ:: በነዚህ ግጭቶች ምክንያት የሱዳን መከላከያ ኃይል የደንበር አካባቢውን ለቆ ወደውስጥ ገብቶ ነበር:: የሱዳን መከላከያ ኃይል ያንን የደንበር አካባቢ ለቆ ከመውጣቱ ጋር ተያይዞ በአካባቢው የነበሩ የሱዳን እንቨስተሮችና አርሶ አደሮችም ፍርሃት ስለአደረባቸው የሚያርሱትን መሬት ለቀው ሕደው ነበር:: ከጥቂት አመታት በኋላ ይህን ክፍት መሬት ከጥቅም ላይ እናውለው በሚል አንዳንድ

ኢትዮጵያውያን ኩባንያዎችም አርሶ አደሮችም ይሁን ሱዳኖች ያርሱት የነበረውን መሬት የተቆጣጠሩበትና የአረሱበት ሁኔታም ነበር የተፈጠረው::"

የአካባቢው ሰው "እኔ አውቃለሁ ቦታውነን መጥተው ሲያርሱት እያስለቀቅነ ቀለም እየቀባን እንጨቱን እንዳቅማችን ስናስለቅቀው ቦታችን ነው አውቀዋለሁ:: ይሄ ደንበር የኛ ነው የኛ መሬት ነው መሬቱ የኛ ነው:: እነሱ አያውቁትም በፍጹም አያውቁትም መንግሥት አያውቁትም:: እኔ የአገሩ ተወላጅ ነኝ:: ሱዳን ውስጥ ፍንጃ ከተማ ነዋሪ ናቸው አውቀዋለሁ ስለሚሉት የኢትዮጵያ መሬት ነው የሚናገሩት:: ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ "በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የነበረው አለመግባባት እየተስተካከለ ሲሄድ ይሀን ችግር ለመፍታት እንደገና ጥናት ሲደረግ ቆይቷል:: በተደረገው ጥናት መሰረት የተስማማንባቸው ጉዳዮች አሉ:: 1ኛ በአጤ ምኒልክ እንደተፈረመው በአጤ ኃይለ ሥላሴ እንደተፈረመው በደርግ እንደተረጋገጠው ሁሉ የእኛም መንግሥት የጉዌንን መስመር ይቀበላል:: ሲቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም "በአጤ ኃይለ ሥላሴ በደርግም የጉዌንን መስመር እንዳለ ከላይ እስከታች እንቀበለው የሚል ስምምነት አልተደረገም::"

"ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ !2ኛ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ይሀን የጉዌንን መስመር ተግባራዊ ለማድረግ በሚሰራበት ወቅት ጉዳት እንዳይከተል የጋራ ኮሚቴ ይቋቋማል ያን ጊዜ በተረጋገጠው መስመር መልኩ ከዳግላሽ እስከ ተከዜ ያለው ቦታ ብቻ ሳይሆን ከዛም በታች ያለው ዳግም እንዲካለል ሪዲማርኬሽን እንዲሆን በነዚህ ጉዳዮች ላይ ተስማማን:: በነዚህ ጉዳዮች ላይ ተስማምተን የጋራ ኮሚቴ አቋቁመን ጥናቶችን ሲያካሕዱ በአካባቢው ያለው ሕብረተሰብ እንዳይጎዳ ምን መደረግ እንደሚችል ሲወያዩ ቆዩ:: --ተጨማሪ ከአንድ ጉዳይ ላይ ለመስማማት ተቻለ:: የጉዌን መስመር የትም ይሁን የት የማካለሉ ስራ በሚሰራበት ወቅት አንድ ኢትዮጵያዊ ወይም አንድ ሱዳናዊ ከሚያርሰው መሬት ላይ መፈናቀል የለበትም የሚል ስምምነት ላይ ተደረሰ:: እደግመዋለሁ የጉዌንን መስመር ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ተግባር በምንሸጋገርበት ወቅት የጉዌን መስመር ለኢትዮጵያ ይጥቀም ለሱዳን ይጥቀም አሁን በአካባቢው እያረሰ ያለው ሕብረተሰብ አሁን እያረሰው ካለው መሬት ማንም ግለሰብ መፈናቀል የለበትም:: የማካለሉን ስራ ከመጀመራችን በፊት በዚህ መርህ ላይ እንስማማ እያፋቀርን በኢትዮጵያ በኩል በሱዳንም በኩል ተቀባይነት አገኘ::"

አቶ ተመስገን "---በዚያን ቀን የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስተር ጉዳዩን ሲያብራሩ አንዳንዱ ሴራ ነው አሉባልታ ነው:: ተቀባይነት የሌለለው ነው አድርገው ነው ያነሱት:: አሉባልታው ምንድነው አቶ ተመስገን ያሉት ያሉት እርሳቸው? ሰዎች መታሰራቸው ነው መፈናቀላቸው ነው ምን ነው አሉባልታው:: "አንድም ሰው አልተፈናለቀም ነው ያሉት? እርሳቸውማ እንደዚያ ነው:: ተፈናቃዮቹ ከመንግሥት ሊዝ ፈርመው ሲያበቁ ከ97 ዓም ጀምሮ ከዚያ ቆይተው ተፈናቅለዋል:: ከዚህ ዋሽንግተን ዲሲ የየሚገኘው የኢትዮጵያ መንግሥት ኢምባሲ ዋና ዲፕሎማትም ሰዎች መታሰራቸውን ከኢትዮጵያ



መሬት መወሰዳቸውንም ተናግረዋል:: ከእናንተ ውይይት በኋላ አስደምጠዋለሁ:: እሽ አቶ ተመስገን ምንድነው አሉባልታው ያሉት እርሳቸው? አይ ለእኛም በጣም የገረመን ይሀ ነው:: ይህንን ከተናገሩ በኋላ ---ችግሮች እንዳሉ ነው:: እኛም የጠየቅናቸው ችግሮች አሉ ወይ የሉም ነው ችግሮች አሉ በመጀመሪያ አሉባልታ ናቸው አሉና እንደገና አሉባልታ አይደለም ደግሞ በንግግራቸው አረጋገጡ:: አድምጫለሁ:: በእኛ በኩል---ዋና መሰረታዊ አድርገን ነው ጥያቄውን ያቀረብነው ከዚህ በተጨማሪ ከትውልድ ኢትዮጵያዊ በዜግነቱ አሜሪካዊ የሆነ እንቬስተር 400 ሔክታር ተሰጥቶት ከዚያ መሬት ላይ መፈናቀሉንና የእርሱ ሰራተኞች የሆኑ 28 ሰዎች አሁን በሱዳን ውስጥ በእስር ላይ እንደሚገኙ የአቀረበውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ ነው:: ሰውየውም ሌሎችም በዚህ መንገድ የተፈናቀሉ በአካል የሚገኙና ሁኔታው እንደተከሰተ ያረጋገጡ ስለሆነ አሉባልታውም ሴራውም የት ላይ እንደሆነ ግልጽ አይደለም::"

ርዕሠ ብሐር አቶ መለስ ዜናዊ "ከዚህ ጋር ተያይዞ ሱዳኖች ያነሱት ጥያቄ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ በመሬት ላይ ያለው አሁን ያለው ሁኔታ ይረጋል ነው ውላችሁ ተስማምታችኋል:: ይረጋል ብላችሁ ስታበቁ ከአጤ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የማስፋፋቱን ስራም አላቋረጣችሁም:: ይባስ ብሎም በ96 በፈረምጆች አቆጣጠር በ96 ዓም በአካባቢው የነበረው የሱዳን ሰራዊት ሲለቅ የሱዳን እንቨስተሮች የሚያርሱት የነበረውን መሬት ወስዳችሁ ለራሳችሁ እንቨስተርና ለውጭ እንቨስተር ሰጥታችኋል:: ይህ ትክክል አይደለም ይሄ ነገር መቆም አለበት:: እስኪካለል ድረስ የማስፋፋቱ ስራ የሚቀጥል ከሆነ --የሚል ተገቢ ጥያቄ ነበር ያነሱት:: ይህን ተገቢ ጥያቄ ለማስተናገድ በኢትዮጵያ በኩል የተወሰደው አቅዋም ምንድነው ከ96 በኋላም ቢሆን በአርሶአደሮች የተያዘው መሬት ከዚህ በፊት እንደተያዘው መቆጠር አለበት የእንቨስተሮች መሬት የግለሰቦቹ ሁለት ሶስትም ኩባንያዎች ስለያዙት እሱንም ልንመልስላቸው እንችላለን::"

"ስለዚህ አንድ የውጭ እንቨስተር እና አንድ የአገር ውስጥ እንቨስተር ይዞት የነበረውና የሱዳን መንግሥት በ96 ዓም የእኛ መከላከያ ኃይል ያፈናቀለውን መሬት ለኢንቨስተሮች እንዲመለስ ከዚያ ውጭ ግን ሱዳናዊ ባልታረሰ መሬት ላይ ካልሆነ በስተረቅ---ኢትዮጵያውያንን አፈናቅለው እንደማያርሱ ስምምነት ተፈፀመ:: ሱዳን አገር ያለው ምድር ኢትዮጵያዊ የሚያርሱትን መሬት በሙሉ ለይተናል:: ኢትዮጵያውያን ከማያርሱት መሬት ውስጥ ሱዳናውያን ሊያርሱት እንደሚችሉ ተምማምተናል:: እንግዲህ--ሱዳኖች እንዲያርሱ ተምማምተናል ባልታረሰ መሬት ውስጥ የምንለው የጊዌን መስመር የሱዳን መሬት ነው ብለው ከዚህ በፊት ካመለከቱበት ቦታ ላይ ነው:: ኢትዮጵያውያን በፊት የገጠሙት በኋላ መከላከያ ኃይላችን ሲቆጣጠር የገቡት ከ96 ዓም የያዙት መሬት እንደያዙት ይቆጠራል:: አይፈናቀሉም አይፈናቀሉም ብቻ ሳይሆን በሚካለልበት ወቅት ደንበሩ በሚካለልበትም ወቅት አይፈናቀሉም:: የሚል ስምምነት ነው የፈረምነው:: በማዕከላዊው የሱዳን መንግሥት በኢትዮጵያና በሱዳን መሀከል ስምምነት እንዲኖር ስለሚፈልግ የሱዳን መንግሥት በተግባር

አንዳንድ ሰዎች እንደሚገልጹት የእኔ የእኔ ነው የአንተን እንካፈል የሚል የኢትዮጵያም አቅዋም ተሸከሞን ነው ያደረው:: ይህን ተቀብሉ ነው ያደረው የሱዳን መንግሥት:: ይህን ተቀብሉ በማደሩ ጅሳጅልነት ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም:: እንደ እንዝባልነት ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም:: አርቆ አሳቢነት ነው--የጋራ ጥቅምን ማየቱን ያመለክታል::” ብለዋል::

ሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም ሲተቹ “ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲናገር የሱዳን ጠበቃ መስሉ ነው እንጂ በኢትዮጵያ በኩል ያለውን ሁኔታ ወይም ደግሞ የሕግ መብት ለማስረዳት የቀረበ አልመሰለኝም እኔ:: ሱዳኖች ደጎች ናቸው የኋሆች አድርጋችሁ አትዩአቸው እንደዚህ አይነት ነገር ሁሉ አለበት:: እነሱ ለራሳቸው በደንብ አድርገው አጥንተውታል:: እኔ እንኳን የማውቀው ሁለት የፔቸዲ ዲሰርተጅን የሰሩ ሰዎች አሉ:: በዚህ ጠረፍ ላይ” ብለዋል:: ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ “---ምንም በማይታወቅበት ሁኔታ የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን ተሰጠ፤ ኢትዮጵያውያኖች ተፈናቀሉ? ተብሎ የሚነገረው ተረት ተራ ተረት ቢሆን ጉዳት ባልነበረው አንድም የተፈናቀለ ኢትዮጵያዊ የለም:: አንድ አድን የተፈናቀለ ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን አንድም የሚፈናቀል ኢትዮጵያዊ የለም:: አሁን ብቻ ሳይሆን ደንበሩ ሲከለል አንድም የሚፈናቀል ኢትዮጵያዊ የለም::” አሉ::

ጋዜጠኛው “እስኪ ከዚህ ዋሽንግተን ዲሲ ያለው የኢትዮጵያ ኢምባሲ ዲፕሎማት ሚኒስትር ሙሌ አገር ፍቅር በተባለ በዚህ አካባቢው ባለው ራዲዮ ቀርቦ በተናገሩት ይህን እናድምጥ “ነብስ ገቢያ ላይ ወደዚያ የገቡና የተሰማሩ ሰዎች ይዘው ሕደዋል:: እነዚህ ሰዎች ቁጥራቸው እስከ 28 የሚደርሱ ሰዎች ናቸው:: ከአካባቢው አሁን ባለኝ መረጃ መሰረት ጠይቄ በቀጥታ ያገኘሁት ነገር ነውና የምናገረው እነዚህን ሰዎች አስረዋል ወስደዋል::”
በሱዳኖች ታፍሰው የወሰደው ከታሰሩበት መካከል ጋዜጠኛው በስልክ ሲጠይቃቸውና ታሳሪዎች ሲመልሱ ”ከእርሻ ቦታ ነው የመጣነው:: ያው መኪናም 8 ሰዎች ከአንድ መሸሮ የመጣነው:: የትኛው የማን መሬት ነበር የምታርሰው? የብስ ገቢያ ቋራ ወረዳ ይባላል:: ስንት ናችሁ አሁን እስር ቤት ያላችሁ? አሁን ያለነው ያው 2 ሴት 26 ወንድ ነን ያለነው:: ከሴቶቹ አንዷን አቅርብልኝ እኔና አንተ እያወራን ሰው ሳክልኝ እስቲ? እንኳን አሁን ቀን ራሱ ከሴቷ ጋር መገናኘት አንችልም:: አ ለምን? መብታችን በጣም ነው ታፍኖ ያለው! ዱላ ነው እኮ ያለነው ስቃይ ነው በቃ ርሃብ ነው ያለነው!”

ጋዜጠኛው “እስኪ ከዚህ ዋሽንግተን ዲሲ ካለው ድፕሎማቲ ሚስተር ሙሉ አገር ፍቅር የተባለወ የዚህ አካባቢ ራዲዮ ቀርቦ ከተናገሩት ይህን እናድምጥ:: ስለዚህ በደንበር አካባቢ ያሉ መንግሥታት የወረዳ የዞን የክልል በፌደራል ደረጃ ግንኙነት አለን ከሱዳን ጋር በየደረጃው ባሉ መንግሥታት እነዚህን ዜጎቻችን የአለአግባብ ነው የአሰራችሁ መልሱልን በሚል የጋራ ውይይት እያደረጉ ነው ያሉት:: እነሱ ደግሞ ወንጀል ሰርተው ነው ያገኘናቸው ይላሉ:: ኖ ይህ ትክክል አይደለም ከእርሻ ተግባር ላይ ተሰማርተው እያሉ ነው የወሰዳችኋቸው በግድ መልቀቅ መቻል አለባችሁ በሚል ይፋ የሆነም ደብዳቤ



ተጽፏል:: መሬቱ የኢትዮጵያ መሬት ነው:: በአለሃብቶች ተመርተው በኢትዮጵያ መንግሥት ተመርተው በአካባቢው በወረዳው አስተዳደር ወይም በዞኑ አስተዳደር ቦታ ተመርተው የሚሰሩ ናቸው::”

“ለሱዳን ተሰጠ የተባለው የኢትዮጵያ መሬት ድርድሩ ምስጢራዊ ነበር ይላሉ አንድ በስፍራው እንደነበሩ ቃላቸውን ለቪኦኤ ሰጥተዋል:: ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ እንዲሉ አዛውንቱ ምስጢራዊ ድርድሩ እንዴትና በነማን ተጀመረ ብለንም ጠይቀናቸዋል:: መሪኄታ የሚለውን የማዕረግ ስማቸው በቀር ለጊዜው ወይም እንድንገልጥ ያልፈቀዱት እኚሁ አዛውንት ቋራ ውስጥ ከልጅነት እስከ እውቀት የኖሩና ዛሬም በዚሁ አካባቢ በመምህርነት የሚያገለግሉ ናቸው:: ያወያየቸው ባልደረባችን አዲሱ አበባ ስለ መሬቱ ምስጢራዊ ድርድር ከማውጣታቸው በፊት የኢትዮጵያ መሬት ናቸው ስለሚሏአቸው አካባቢዎች እንዲገልጡለት ነበር የጠየቃቸው መርጌታ ይመልሳሉ:: ከሁመራ አንስቶ ያው ባህረ ሰላም የሚባል ወንዝ አለ ከሁመራ ዝቅ ብሎ አብደራፊ የሚባለው አለ:: አብርሃጅራ የሚባለው አለ:: እነዚህ መንደሮች ናቸው:: እንደ ገና ሙሴ ባንብ የሚባል አለ:: ደለሉ የሚባል አለ:: ሽመለጋራ የሚባል አለ:: የጠረፍ ከተማዎች ናቸው የምጠራልህ ያለሁ:: እሺ መተማ ዮኀንስ መርምያ ወርቅ እምባ ጉንዶ ተራራ ቲሃ ከተማ ስኳር ተራራ መተርሃት፤ፋዝራ፤አስከኝት ነብስ ገቢያ አላጢሽ በርሃ ሽመለ ጃዊ፤ አይማ ወንዝ እነዚህ ሁሉ የታወቁ ከአጤ ዮኀንስ ጀምሮ ከአጤ ምኒልክ እስከ አጤ ኃይለ ሥላሴ አሁንም እስከ ደርግ ድረስ ያው የኢትዮጵያ ከተሞችና የኢትዮጵያ የግመዝ ብሔረሰቦች የሚኖሩባቸው ናቸው::”

“እኔ ትውልዴ ከዚያው አካባቢ ነኝ:: ትምህርቴ በቤጌምድር አካባቢ ያው ተምሬ ልደግና የቅኔ ትምህርት ሆነ የአቋቋም ትምህርት እየተዘዋወርኩ በኢትዮጵያ ያሉትን ስማር የኖርሁ በኃይለ ሥላሴ ጀምሬ እንጂ የተወለድኩ እዚያው ቋራ ነኝ:: እሽ ይቀጥሉ አሁን ከተሞችን እየጠሩልኝ ነበር እሺ:: እነዚያ ከተማዎች ከ20 ከተማዎች በላይ ማለት ጠርቼልሃለሁ የማለት የደንበር ከተማዎች ናቸው:: በመጀመሪያ እኛ 40 ዓመታችን ነው በበዚያው አካባቢ ግን የነበሩት ግና እኛ የምናውቀው ከኃይለ ሥላሴ ከተረከቡ ግና የሚያርሷቸው የነበሩትን ሀብታሞችን በአጠቃላይ የአርማጭሆ ተወላጆችን የኢትዮጵያ ሃብታሞችን ከሁመራ አንስቶ እስከ ቋራ የጠረፍ ከተማዎች ለምሳሌ እን ዋክሹም ነወጠ የተባሉ ሀብታሞች እነ ቢትወደድ አዳነ የእነሱ ቤተሰቦች በአጠቃላይ ሲያርሷቸው የነበሩ ናቸው እነዚያ የአብደራፊ የደለሉ የሽመለጋራ ያልኩን ቦታዎችን ሁሉ የኢትዮጵያ ሀብታሞች ያርሷቸው የነበሩ ናቸው በኃይለ ሥላሴ ጊዜ:: እና እነዚህ ሁሉ የኢትዮጵያ ናቸው ነው የሚሉኝ እርስዎ:: እነዚህ የኢትዮጵያ ናቸው ከሁመራ አንስቶ እስከ ቋራ ድረስ አላጥሽ ተራራ ያለውን አካባቢ 70 ኪሞ ሜትር የገቡ አሉ ሱዳኖች 50 ኪሎሚትር የገቡ አሉ:: በእያቅጣጫው ማለቴ ነው:: በሁመራ አካባቢ ደግሞ 35 ኪሎ ሜትር በአብደራፊ ደግሞ 60 ኪሎ ሜትር በመተማ ደግሞ ነጋዴ ባህር ይባላል እስከ ጭልጋ አውራጃ ማለት ነው:: ማህበረ ሥላሴ ገዳም ታውቀዋለህ አጤ ቴዎድሮስ የተማሩበት እስከዚያ ገብተውበታል::”

"ሱዳኖች አዎ ሱዳኖች! ይሄ በትክክል ነው የምንግርህ! የገቡት ለምንድነው እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ነው? ወይስ በኃይል ነው! እንዴት ነው? እኛ መጀመሪያ ጊዜ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ያን ቦታ ከልለን የአገር ባላባቶችና የአውራጃ አስተዳደሮች ባሉበት ተከልሎ ያን ቦታ የቀድሞውን እናውቅም አሁን የምንግርህ በተጨባጭ ነው። ስለዚህ አውራጃ አስተዳደሮችም የችልጋ አውራጃ አስተዳደሪ ከቦታው ሕዶ ከልሎ የወሰን ድንጋይ አስፍረዋል። ስለዚህ አሁን ግን ያለው መንግስት ግና እኛ የሀገር ሽማግሌዎችን በ1996 ዓም በእኛ አቆጣጠር በኢትዮጵያ ማለት ነው። እኛ የተወሰነ ሰዎች ባላባቶችን ጠርቶ የወሰን ከተማ ከኢትዮጵያና ከድንበር ከተማዎችን ልንከልል ነውና እናንተ ባላባቶችን ተመርጣችኋል ተብለን 1ኛ አቶ አስማማው አድሮ 75 ዓመታቸው 2ኛ አቶ እሸቴ ፈረደ 70 ዓመታቸው ነው። 3ኛ አባ አረጋዊ ገብረ ሥላሴ የዳስ ነዋሪ ማለትም የአንድ ገዳም ነዋሪ 80 ዓመታቸው ነው:: አቶ ሲሳይ ብርሃኑ 70 ዓመታቸው ነው። እኔ ሁነን አቶ ስዩም መስፍንና አቶ አዲሱ ለገሰ ጠርተውነ ወደ ገዳሪፍ አውራጃ ወይም ወደ ገዳሪፍ ከተማ ተጠርተን ሕደናል::"

"የመተማ ከተማ አስተዳዳሪ አስተባባሪ! ማን ነበሩ ያኔ የመተማው አስተዳዳሪ? አቶ ሙሉዓለም ገድሌ ይባላሉ። ስለዚህ ከዚያ ሕደን እንዴት ነው ብለው ነገሩን አዲሱ ለገሰ እና ስዩም ያው ግብግ ተደርጎልኑ እኛ ቦታውን መከለል እንፈልጋለን ነዳጅ በዚህ እንዲሔድልን ከሱዳን ጋር ደግሞ መልካም ወዳጅነት እንድናደርግ እና ምን ይመስላችኋል እናንተ የአገር ሽማግሌዎች ናችሁ ሱዳን ከእኛ መሬት አለው ለሱዳን ልንሰጠው ነው እኛ አጠቃላይ ሳይሆን ነዳጅ እንዲያቀርብልን መልካም ግንኙነት እንድናደርግ እንደገና ደግሞ ያው የሱዳን ሀብታሞች ከእናንተ ጋር ገብተው እንዲያርሱ እንዴት ይመስላችኋል አሉን። እኛ በዚያን ወቅት ተበሳጭተን ኢትዮጵያዊነታችን ረስተነው እኛ 150 ብር ነው የሚከፈለን አበል አይሆንም እኛ ይህ የኢትዮጵያውያን ሃብት ነው። የኢትዮጵያውያን ጠረፍ ነው አትባራ የሚኖር ውሃ በፈሰሰ አትባራ ወንዝ ይህ የኢትዮጵያውያን ስለሆነ እኛ አባቶቻችን ሲያርሱት የነበረ ስለሆነ እንዲያው አይመስለነም እኛ አንስማማበትም ብለን አምስታችንም ነገርናቸው። ከነገርናቸው በኋላ እነዚህ ሰዎች ሻጥረኞች ናቸው። ጥሩ ሰዎች አላመጣችሁም ብለው ለወረዳው አስተዳዳሪ ተቆጡት። መልሳቸው በአመጣሃቸው ከሚና መልሳቸው ተብለን ከገዳሪፍ ተመልሰናል::"

"ሌላ ተተካ ታዲያ? ከዚያ በኋላ ሌላ ሽማግሌ ተመርጦ እነሱን የሚደግፉ ሰዎች ከነሱ የሚመስሏቸው አባሎች ተመርጠው ተፈራርመው እንደገና በ97 ዓም ሊሰናከል ቻለ። ይሔ ሊሰናከል የቻለው 97 ምርጫውን ተከትሎ ነው ሊሰናከል የቻለ እንጂ በዚያን ወቅት ተግባራዊ ሊሆን የቻለ እንጂ ይህ ምስጢራዊ ሰነድ ፊት ነው የተስማሙት። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያውቅ ምስጢራዊ ሰነድ ተስማምተዋል። ሁኔታው ሊፈጸም ሲል ምርጫው አሰናከለው ነው ያሉኝ እስኪ ከዚያ ላይ ግልጽ ያድርጉልኝ። እዎ ምርጫውን ተከልቶ ግርግር ሲሆንበት ፈራና ደብቆት ቆየ! ያ የተዳፈነ እሳት አሁን



ተጋጋመና አሁን እንደገና 150 ሺህ የሚሆኑ ገበሬዎች እየተፈናቀሉ በደለሉ በአብደራፊ በሁመራ በቋራ፣በነፍስ ገቢያ፣በሽንፋ አካባቢ ያሉ ገበሬዎች አጠቃላይ እየተፈናቀሉ ኒውሳን ገበሬ በመኪና የማያርሱ ተፈናቅለው ማረሻቸውን ጠቅልለው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል በአለፈው ዓመት። እናንተ አትሆኑም ተብሎ ከተመለሳችሁ በኋላ ሌሎች ሰዎች ተመርጠው ነበር ብለውኛል እኛ እነዚያ የተመረጡ ሰዎች ምንም አላደረጉም?"

"እነዚያ የተመረጡ ሰዎች ምን እንዳደረጉ ደርሰው የመጡ መሆናቸውን እንጂ ምን እንዳደረጉ አላወቅናቸውም። ምክንያቱም በስውር ነው የሄዱት በስውር ነው የተመለሱ። ስለዚህ ያው እንግዲህ። ተፈርሟል ማለት ነው? ተፈራርመዋል አዎ ያውቃሉ መፈራረማቸውን? አዎ ተፈራርመዋል! ምንድነው የተፈራረሙት! ምንድነው ውለታው! ያውቃሉ? ውለታው ምን መሰለህ አጤ ምኒልክና ኃይለ ሥላሴ አሁንም በደርግ የተዋዋሉት ውል አለ! የጉዌን መስመር ለምሳሌ ከአላጥሽ በርሃ አንስቶ እስከ ምንሃጅር ያለውና አካባቢ እንግሊዛዊው ጄኔራል ጉዌን የቀየሰውን ቦታ ለሱዳን ልንሰጥ ነው ስለዚህ እኛ በኦፊሴል ደረጃ ልንሰጥ ነው የጉዌን መስመር በዚያው ነው የተዋዋሉ። የጉዌስን ክለላ እንቀበላለን ነው? እንቀበላለን በፊርማ እናፀድቃለን ነው በዚያን ወቅት ኃይለ ሥላሴ እኛ እናውቃለን አላፀደቁም::"

"እንዲያውም ሱዳኖች ቢመጡ የአውራጃው አስተዳዳዊ ቀኛዝማች ማን ነው የሚባል ነበር የዚህ የጭልጋ አውራጃ ሕዶ ጠረፌኛ ነበር የሚባለው ጠባቂ ደንበር ጠባቂ አባሮ ነው የሰደዳቸው እንጂ በዚያን አካባቢ ኃይለ ሥላሴ ፈርመው አልሰጡአቸውም። እኛ እናውቃለን። የጉዌን መስመር የቱን የቱን ቦታ ነው ለሱዳን ያደረገው የቱን የቱን ቦታ ነው ለኢትዮጵያ ያደረገው ያውቃሉ? እንደማውቀው እኔ አሁን ነብስ ገብያ የሚባል አለ ነብስ ገብያ ማለት እንግዲያ አሁን ሱዳን የወሰዳቸው ቦታዎች አሉ። ፋዝራና ማከሰኝት ነብስ ገቢያ መትርሃዲ የሚባሉ ከተማዎች የእኛ ነበሩ አሁን እነሱን ሱዳኖች የሱዳን ጦር ይዟቸዋል::"

"ከ97 ጀምሮ ሊዝ ከመንግሥት ጋር ተፈራርመን ስናርስ ነበር ከዚህ ከምናርስበት ቦታ ነው የተባረርነው ሱዳንም የኔ ነው የምትለው የኢትዮጵያ መንግሥት በሊዝ የሰጠነን ቦታ ነው የሚሉ ሰዎች ባለፈው አነጋግሬ ነበረ ስለነዚህ ቦታዎች እስኪ ይንገሩኝ? እነዚህ ቦታዎች በመጀመሪያ መንግሥት ይህን ነገር ሊሰጣቸው የቻለ እነዚህ ሰዎች ከውጭ የመጡ ሰዎች ናቸው ሁለቱ እስራኤላዊ ናቸው። አንዱ አሜሪካዊ ነው። ሌሎች የሀገር ባለሃብቶች ነው:: ከነሱ ውስጥ አንዱ አቶ አሊ አብዱ ይገኛሉ::"

"አቶ አሊ አብዱ ተሸላሚ የሁመራ ባላባት ሀብታም ናቸው። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሸልመዋቸዋል። እርሳቸው ነው ዋናው አንደኛው እርሻ የተቃጠለው እርሻ የእርሳቸው ነው። እነዚህ ቦታዎች ነብስ ገቢያ፣ ነብስ ገቢያ ማለት ደግሞ ቋራ መሃል ነው። ነብስ ገቢያ ሲባል እናንተ ሩቅ አገር ሁናችሁ ወደመሀል ሱዳን እንዳይመስላችሁ ወደዚህ ወደ ቋራ ከተማ ነው። ነብስ ገቢያ

የኛ ነው ነብስ ገቢያ ማለት --ፋዝራ እነዚህ ሽመለ ጃዊ አላጥሽ በርሃ የሚባል ብርቅዬ አራዊቶች ያሉበትና የኢትዮጵያ የዱር አራዊት ብርቅዬ ያሉበት ሀገር እና እንዲያውም ለዓለም ብርቅየ የሆኑ ዝሆን፣ አንበሳ፣ ቀጭኔ፣ሰጎን እንቁላል ቀይ ዝንጀሮ፣ ቀይ ጦጣ፣ ትልቁ የዘንዶ ዝርያ ቀይ ተኩላ ያሉበት ብርቅዬ ያሉበት ቦታ ነው አሁን ሱዳን የወሰደው።"

"በትውልድ ኢትዮጵያውያን የሆኑ በዜግነት ደግሞ ከእስራኤል ከአሜሪካ የሆኑ ሰዎችም ነበሩ የሚያውቁት አለ ስለ ሰዎች የሚነግሩኝ ለነገር አለ" አዎ አንዱ አሁን በይሰሞን ተፈቶ መቷል አቶ መሃሪ ተፈቶ መቷል። ምክንያቱም እሱ 2 ሚሊዮን የሱዳን ፓወንድ ተሰጥቶ ተፈቷል። ከዚያ አካባቢ ምንድነው ሁኔታው ሰዎቹ ነዋሪው ምን ይላል? ውጊያው እንደቀጠለ ነው ያለው! ውጊያ አለ እንዴ? አዎ ውጊያ አለ በ27 ግንቦት 27 ቀን ከረፋዱ 3 ሰዓት ጀምሮ ሽምቅ ተዋጊዮች እና ሽምቅ ተዋጊዮች የሚሏቸው? የእኛ ሽምቅ ተዋጊዮች ናቸው የእኛ የኢትዮጵያውያን ሁኖ ሽምቅ ተዋጊዮች አካባቢውን የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያውያን ሽምቅ ተዋጊዮች ናቸው።"

"የኢትዮጵያን መንግሥት የሚቀዋወሙ? አዎ ግንቦት 27 ቀን ከረፋዱ 3 ሰዓት ጀምሮ ሽምቅ ተዋጊዮች እና የአብደራፊ ምክትል አስተዳዳሪ አቶ ሽምበል ቓላቸው የሚባለው በግንቦት 27 ቀን ተገኗል። የቀብራቸው ሥን ሥርዓት ጎንደር መጥምቁ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ግንቦት 30 ከጠዋቱ 2 ሰዓት ተከናውኗል። ሌላስ በኢትዮጵያውያን በኩል የሞቱ ብዙ አሉ ብዙ አሉ? አዎ አንድ 23-አሁን ችግሩ አገር እየተቆረሰ እኛ መቶ ምሉዮን ሕዝብ ነን እንባላለን ሱዳን 35 ሚሊዮን ሕዝብ አላት።እሱ ከኛ ቦታ ስትፈልግ እኛ ቦታችን እየቆረሰነ ለሱዳኖች ስንሰጥ ለሚቀጥለው ትውልድስ ምን ሊሆን ነው? ይህን ነገር የኢትዮጵያ ሕዝብ በደንብ እንዲያውቀው ነው የምንፈልገው አሁን እኛ ኢትዮጵያ ተደፍራለች አባቶቻችን ሙተዋል ድሮ እኛ የምንምኄደው በመጽሐፉ ነው። ኢትዮጵያ ታብጽን ሀበ ኢግዚአብሔር እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች አሁን ግን እጇን ተኮርኩማለች" ሲሉ ተናግረዋል።

ይህ ከዚህ በላይ የድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ያወጣው ክር እኔ ቃል ቤቃል ከድምጽ ወደ ጹሑፍ ስቀይር በተለይ የርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ሆኑ የአቶ ዳንኤል ኅበዜ አንዳንዴ ንግግር እያስቸገረኝ የቀረብኝ ይመስለኛል። ለወደፊቱ ከዋናው ክር ጋር እስኪመሳከር ድረስ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ሌላው ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ እጤ ምኒልክ ተስማምተዋል ያሉት ትክክል አለመሆናቸውን ከዚህ በታች ያለውን እጤ ምኒልክ ለእንግሊዝ መንግሥት የላኩት ደብዳቤ ለአንባቢያን አቅርቤዋለሁ። እጤ ምኒልክ ሆኑ እጤ ኃይለ ሥላሴ ብሎም የርዕሠ ብሔር ኮሉኔል መንግሥቱ መንግሥት የተስማሙት ውንድ የለም። በተለይም እጤ ምኒልክ እንኳን ሊሰጡ ቀርቶ ድንበራቸው የት እንደሆነ ደብዳቤው ያስረዳል። ይህ ከዚህ በታች ያለው የእርሳቸው ደብዳቤ ሲሆን እኔ ለአንባቢያን እንዳያስቸግር በማለት በዘመናዊ ተብየዋለሁ። ዋናው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሲሆን ማህተም አለበት። ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱ ማህተም ያረፈበት በሚቀጥለው ገጽ ይመልከቱ።



ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!

ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ ይድረስ ለወዳጃችን ከንግሥት ቭክቶሪያ፣ የታላቂቱ ብርታንያ የዓየርላድም ንግሥት የሃይማኖት ረዳት የሕንድ ነገሥታት ንግሥት፣ሰላም ለእርስዎ ይሁን። የከበረች የጤናዎን ደሕንነት በጣም እንጠይቃለን። በመስከረም 25 ቀን 1883 ዓም የተጻፈ ደብዳቤ ልኬ ነበር። መድረሱን አላወቅሁም፤ ታላቁ የእንግሊዝ መንግሥት እስከ ዛሬ ድረስ ለኢትዮጵያ መንግሥት ወዳጅ ስለሆነ በመልካም ነገር ሁሉ ማሰቡን እያወቅን እናመሰግናለን። አሁንም የመንግሥታችን የኢትዮጵያን ድንበር ለወዳጆቻችን ነገሥታት ማስታወቅ ስለወደድን ፅፈንላችኋልና እናንተም በመልካም ልቡናችሁ ትመለከቱታላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

የኢትዮጵያ ድምበር ይህ ነው!

ከኢጣልያ ድምበር ባህር ዳር ካለው ካራፍሊ አንስቶ ወደ ምዕራብ ከቿግራ ሜዳ ይዞ ማኺዮ ሃልይ፣ ዲክሳን ጉራ፣አዲባሮ ይደርሳል። ካዲባሮ አንስቶ የመረብ ወንዝና ያራተብ ወንዝ መገናኛ ድረስ፣ከመረብና ከአራተብ ወንዝ መገናኛ አንስቶ ወደደቡብ ያትባራ ወንዝ ከባህር ሰቲት ወንዝ መገናኛ ቶማት፣ የሚባል ከተማ ካለበት ይደርሳል። ከቶማት አንስቶ የገዳሪፍን ግዛት ይዞ ዓባይ ከተማ ካርጎግ ይደርሳል።

ከካርጎግ አንስቶ ነጭ ዓባይና የሶባት ወንዝ መገናኛ ይደርሳል። ከነጭ ዓባይና ከሶባት ወንዝ መገናኛ አንስቶ የሶባትን ወንዝ ይዞ አርቦሬ ጋላን ጨምሮ ሳምብሩ ባህር ደርሶ ወደ ምስራቅ ቦረኒ ጋላን ይዞ አሩሲን ሁሉ ይዞ እስከ ሶማሌ ድንበር ድረስ ኦጋዴንን ጨምሮ ወደ ሰሜን ተመልሶ አበራውልን ገደቡርሲን ኢሳ ሶማሌን ይዞ አምቦሳ ይደርሳል። ከአንቦሳ አንስቶ ያሰልን ባህር ጨምሮ የጥንቱ ዜጋችን የመሀመድ ልገፈርን ግዛት ሁሉ ይዞ በባህር ዳር ዳር እየሄደ አራፋሊ ይደርሳል።

ይህነን ዛሬ የያዝኩትን ድንበር ስለጻፍኩ እግዚአብሔር እድሜና ጉልበት ከሰጠኝ የጥንቱን የኢትዮጵያ ግዛት እስከ ካርቱም እስከ ኒያሳ ባህር ጋላ የተባለ ሁሉ ለማቅናት እፈልጋለሁ። ሺ400 ዓመት ሙሉ ኢትዮጵያ እንደ ክርስቲያን ደሴት በአረመኔ ባህር ተከቦ ሲኖር ከሩቅ አገር የመጣ መንግሥት አፍሪቃን እንካፈላለን ሲል ዝም ብዬ ማዳመጥ አሳስብም።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እስከ ዛሬ እንደጠበቃት እንግዲህም ወዲህ ይጠብቃታል ያሰፋታል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ እንጂ ለሌላ መንግሥት አከፋፍሎ ይሰጣታል ብዬ አልጠረጥርም። ቀድሞማ የኢትዮጵያ ደንበር ባሕር ዳር ነበር! የኢትዮጵያ ጉልበት ቢያንስ የሚረዳን ክርስቲያን ብናጣ የባሕር ደንበራችን ከእስላሞች እጅ ገባ! የባሕር ዳር ድንበራችንን በጉልበታችን እናገኛለን አንልም። የክርስቲያን ነገሥታት ክርስቶስ አመልክቶአችሁ የባሕር ዳር ድንበራችንን ትመልሱልናላችሁ። ባይሆንም ከባሕር ዳር አንዳን አንዳንድ ቦታ ትሰጡናላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። በሚያዝያ 14 ቀን ባዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ፤ በ1883 ዓም!



[illegible]



[illegible]

# ክፍል አራት

## ምዕራፍ 1
## የታሪክ ቅኝት ስለ ወልቃይት

ወልቃይት ወይም ወልቃይቴ ማለት ለአንዳንድ አካባቢ ወይም ደግሞ ይህን የተፈጠረውን ችግር በጥሞና ሳልተረዳ ሰው ሁኔታውን ሊያውቅ አይችልም:: ስለዚህ ወልቃይት የትና ከዜት አካባቢ እንደሆነ መንደርደሪያ ሳቅርብ:: ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች ወልቅጤንና ወልቃይትን ለይተው የማያውቁ ብዙ አሉ:: ድምጻዊ ሰሎሞን ተካልኝ ኮሎምቦስ አኳዮ ለስራ ጉዳይ ይሄዱና ከአንድ ቡና ቤት ሲገቡ ደስ የሚሉ ሁለት ኮረዳዎች አዩ:: ጨዋታው ደርቶ እያወጉ ባለ "የት አካባቢ ናችሁ" ብለው ድምጻዊው ጠየቁ:: ኮረዶች "ጎንደር" ይላሉ:: ድምጻዊው "ጎንደር የት" ብለው ሲጠይቁ "ከረዶች ወልቃይት" ብለው ይመልሳሉ:: ድምጻዊ ሰሎሞን ለአንዱ ስልክ ይመቱና "ኧረ ና ሳስተዋውቅህ ሁለት ውልቅጤ ቆንጃጅቶች አግኝቻለሁ" አሉ ተብሎ መሳቂያ ሁነው ነበር:: ለዚህም ነው ወልቃይትና ውልቅጤን ለይተው የማያውቁ ስላሉ ወልቃይት የት ለዚህም ነው ወልቃይትና ውልቅጤን ለይተው የማያውቁ ስላሉ ወልቃይት የት እንደሆነ ለማስረዳት ያሰብኩት:: በዚህ ባሳለፍናቸው ዓመታት ውስጥ ብዙ አዳዲስ ታሪክ መጻፍ ጀመረ ወያኔን በጥቅም ሲደግፉ የነበሩ ግለሰቦች የሚጽፉትና የሚናገሩት ታሪክ አዳዲስ መሆኑ አይዘነጋም:: ሌሎች ደግሞ ትክክለኛ ታሪኩን መስመር አሲዘው ያሳወቀ እንዲያውቅ ለማድረግ ጥረት አድርገዋል:: እኔ ስለ አንድ ነገር ታሪክ መጻፍ ስጀምር ረዘም ብዬ ታሪክ መሳብ ደስ ይለኛል:: ሁሌም በእኔ እምነት አንባቢያ እንዳይጠራጠር በታሪክ የተደገፈ ሠነድ ማቅረብ እወዳለሁ::

አለቃ ታየ ወልደማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 16 "ከለው ከሳባ ወደ ምዕራብና ወደ ደቡብ ያለ ያማራ የወልቃይት፣ የጠገዴ ሕዝብ አባት ነው:: ከነዚህም የኢትዮጲስ ልጆች የወንድማማቾቹ ነገድ ሕዝብ ሁሉ በመልካቸውና በቁርበታቸው ይመሳሰላሉ:: ከሌሎች ከአፍሪቃ ሕዝብ ተለይተው በልዩነት የሰው ልጆች ተብለው ይጠራሉ:: እኒህም ሕዝብ የያዙት አገር በጥቅሉ ባባታቸው ስም ኢትዮጵያ ተብሎ ይጠራል:: ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ባላባቶች የሴም ዘሮች 7 ወገን ናቸው:: እርሳቸውም አማራ ትግሬ፣ አገው፣በደው፥አስግዴ፣ በቅላ፣ሐባብ ናቸው:: በደው አሰግዴ በቅላ ሐባብ እኒህ 3ቱ ነገድ በእስልም ሃይማኖት ገብተው ከወንድሞቻቸው ተለይተው ልዩ ወገኖች ሁነዋል:: አማራ ትግሬ አገው ግን በፊት በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ በሕገ ኦሪት ያመኑ በኋላም በክርስቶስ ያመኑ በየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት የጸኑ ከጥንት ጀምሮ መንግሥት ያልጠፋባቸው ባዕድ ገዥ ያልገባባቸው የእግዚአብሔር ረዴት ያልራቃቸው ሕዝብ ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል::



አለቃ ታየ ወልደማርያም አጻጻፍ የአማራው አባት አሰግዴ ግንዱ ከወልቃይት ጠገዴ አርማጭሆ ከዚያም እያደገና እየሰፋ አማራ ሳይንት ድረስ የደረሰ መሆኑን ገልጸው ጽፈዋል:: ሌላው ደግሞ አለቃ ታየ ደህና አድርገው መልስ የጻፉበት ዋና የሆነው ከየመን ቅዱስ ቁርዓን ዘመናዊ ሁኖ ሲታተም "ሳባ የመናዊት" ናት የተባለውን የታሪክ ሰነድ ጠቅሰው መልስ ሰጥተዋል:: ከዚያም "አማርኛ ቋንቋ የወታደር ቋንቋ ነበር፥በተለይ በአጤ ላሊበላ ዘመን ያደገ ነው ብለው አለቃ አጽሜ ጊዮርጊስ በጻፉት መጽሐፍ ላይ አለቃ ታዬ ወልደማርያም መልስ ሰጥተዋል:: ገጽ 22 "አማርኛ ቋንቋ እንደነበረ በፊተኛው ክብረ ነገሥት ተጽፏል:: ከዚያ ዘመን ውስጥ ከነገሡት አያሌ የነገሥታት ስም ባማርኛ ቋንቋ ነበረ:: ይህም ሲታወቅ ወረደ ነጋሽ፣አግባ ጉም፣ አስጎምጉም፣ለትም ተላተም፣ዖደ ጎሽ፣አይዙር፣መራ ተክለ ሃይማኖት በመባላቸው ይገለጣልና ይታያል:: በፊት አማርኛ ቋንቋ ተሌለ ይህ ሁሉ ስም ከምን መጣ? ይህ ሁሉ በግዕዝ፣በትግርኛ፣ የሌለ ያማርኛ ስም ነው" ሲሉ ጽፈዋል:: ከክርስቶስ ልደት በፊት የነገሡትን የአማራ ስሞች ልለፍና ከክርስቶስ ልደት በኋላ የነገሡበትን ዓመት ከዚህ እጽፋለሁ::

1ኛ አግባ 105 ዓም
2ኛ ወሰን ሰገድ 585 ዓም
3ኛ ጉም 725 ዓም
4ኛ አስጎምጉም 730 ዓም
5ኛ ለትም 746 ዓም
6ኛ ተላተም 767 ዓም
7ኛ መራ ተክለሃይማኖት 912 ዓም ሌሎች የአማራ ስሞች ከነገሥታት ታሪክ ውስጥ ያሉ ብዙ ናቸው:: የሩቁ ታሪክ ከላይ የተጠቀሰ ነው:: የቅርቡ ደግሞ አማራዎች ከወልቃይት ወደ አርማጭሆና ደንቢያ ከዚያም ወደ ከምከም ቃሮዳና አልፎም አማራ ሳይትንታ መቃድሻ ድረስ ተስፋፍተዋል:: ከዚሁ ከምከም ሳይርቅ መና መቀጥዋ ትውልዱን ዘር የሚቆጥረው መራ ተክለ ሃይማኖት ነው:: ይህን ታሪክ አገዎችም ያምናሉ:: ለዚህ ጥናት ዋና ሁኖ የቀረበው ደግሞ በአገዎች የተጻፈው መጽሐፍ ይሆናል:: ታሪክ ነውና እገሌ ሲወልድ ብለን መቁጥር የታሪካችን አንዱ መሰረቱ ሲሆን አንዳንዴ መኳንንቶች ሕዝብን ከሕዝብ የሚለዩበት ዘዴ አድርገውት ኑረዋል:: በሌሎች የታሪክ ደራሲያን ዘንድ ደግሞ ከጫፉ ለመድረስ ሲባል ወደ ኋላ ተሕዶ ከግንዱ ይደረሳል ስለዚህ አንድ የታሪክ መጽሐፍ ጠቅሼ ሳልፍ ወደድኩ::

ዶ/ር አያሌው ሲሳይ የአገው ሕዝብና የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት በተባለው መጽሐፍ ገጽ 100 "እረፍተ ድንግል የተባለችው የላስታ ቡግና ሴት ዋግ ውስጥ ወፍላ ከተባለው አገር ልዩ ሥፍራው ፍላና ከሚባለው ቀለምሲስ የተባለውን ባላባት አግብታ ወልደ ጊዮርጊስን ወለደች:: ወልደ ጊዮርጊስ የሹም ዳርጎቴን ልጅ ወለተ ቅዱሳንን አግብቶ ፊልጶስን ላስታ ተሻግሮ ተቅዋመ መርቅን አግብቶ ታዴዎስን፥ታዴዎስ በጌምድር ወርሶ የሀሙስ ወንዝ ባላባት የሆንችውን ብርሃናዊትን አግብቶ ሊቀ ካህናት መርሀ ክርስቶስን፥ሊቀ ካህናት መርሀ ክርስቶስን ዋድላ ሄዶ ማርያም ስናን አግብቶ መራ ተክለ ሃይማኖትን መራ ተክለ ሃይማኖት ከመናመቀጥዋ ባላባት ሂሩተ እምላክን በአሁኑ ዘመን

የቅዱስ ሀርቤ ገዳም ከሚገኝበት የቀደሞ ስሙ አንደኛ ሩህ ከተባለው አግቡቶ በማምጣት መይራሪን፥ሀርበይን ወለደ" ሲሉ ጽፈዋል። መራ ተክለ ሃይማኖት ራሱ ከአማራ የተወለደ ሲሆን ትግሬዋን ሞሰበ ወርቅን ከማግባቱ በፊት ከአማራው ወገን የወለዳቸው ልጆች ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል።

ወደ ኋላ ልመለስና አለቃ ታዬ ከጻፉት ላይ ስንመጣ ምናልባት ዛሬ አንዳንድ ፀረ አማራ የሆኑ ዘመናዊ ደራሲያን የሚገልጹት ታሪክ ትክክል አለመሆኑን ከላይ የተሰመረበት ሲሆን በእኔ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ የተዋሕደ ሕዝብ መሆኑን ባምንም ቅሉ የአማራው መሰረት ወልቃይት ነው። ዛሬ ክላሽ ኮተ ጠበንጃ ታሪክ የሚያጽፍ በመሆኑ ወያኔ እነዚህን ወረዳዎች ወደ ትግሬ ለማስገባት ያደረገው ጥረት ከላይ ከተጠቀሰው ታሪክ ውጭ ነው። ለአንባቢያን ወልቃይት ማለት ታሪኩ ይህ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን የሚገኝበት በጎንደር ክፍለ ሀገር በወገራ አውራጃ ለም ወረዳዎች ናቸው። በነዚህ ወረዳዎች ውስጥ ታዋቂ የሁመራ ልማት ሲሆን የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ወድቆ የደርግ መንግሥት ሲመሰረት ሁመራን ጥር 1969 ዓም ኢዲዩ ዘርፏት ሲሔድ ሰኔ 1969 ዓም ደርግ "የመንጥር ጦር ሄደ ግንባር" እየተባለ ይዘፈንለት የነበረው የጦር ኃይል መልሶ ከያዘ በኋላ የመንግሥት ልማት በአንደኛ ደረጃ ተመደበች "የእረንጓደው ልማት" ይባልላት የነበረች የሁመራ ገበሬዎች አካባቢውን አስተራረስ የሚያውቁት ከዘመናዊው ምሁር ጋር አልተግባቡም። አርሶ አደሮች ለእርሻ መጽሐፍ አያስፈልግም ሲሉ ዘመናዊ ምሁራኖች ደግሞ በእንግሊዘኛ የተጻፈን መጽሐፍ መመሪያ አድርገው ማረስ አለብን ሲሉ አርሶ አደሮች እንዲህ አሉ

"በሬው ከሸዋ አራሹ ከጎንደር

ይጠፋል በቅርቡ የሁመራ መንደር"

እሉ እየተባለ ይሳቅ ነበር። የሁመራ እርሻ ልማት የጠፋበትን ምክንያት የግብርና ባለሞያዎች መርምረው ሊያቀርቡ ይገባል። ምሁራኑ በተማሩበት ትምህርት ብቻ በመመራት የአካባቢውን የመሬት ልማድ ባለመረዳት ነው። ዛሬ ያለን ትውልድ ታሪክ ለማወቅ ጥረት የማናደርግ በመሆኑ እንጂ ወልቃይት ማለት ሰፊና ትልቅ አገር ነበር። እድሜ ለቅኝ ገዥዎች ከወልቃይት እየተቆረሰ ወደ ሱዳን የገባው አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ መሀል ከመጣ በኋላ ነው "ዳሩ ዳር ሲሆን መሃሉ ዳር ይሆናል" እንደተባለው ወልቃይት ዛሬ መሀል መሆኑ ቀርቶ ዳር ሁኖ ይገኛል። ስለ ወልቃይት ማንሳት ማለት የጎንደሬዎች ብቻ እልያም ደግሞ አንዳንድ ሆድ አምላኬዎች የወልቃይት ልጆች የነሱ አስመስለው ያዩታል። በመሰረቱ በተለይ ወልቃይት የወልቃይቴ ልጆች እልያም የጎንደሬዎች ብቻ ሳይሆን የአማሮች አባት መፍለቂያ መሆኑን መረዳትና ዳር ደንበሩን ለማስጠበቅ መነሳት የአንድ ዜጋ ግዴታ ይመስለኛል። በእኔ እምነት ወልቃይቴ ማለት ጠባብነት አይደለም። ለምሳሌ ከነገሥታት የትውልድ ወረዳ ብንነሳ ስለ ቴዎድሮስ ሲነገር "ቋራ" ስለ አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ሲነገር "ሰቆጤ" ስለ አጤ ዮሃንስ ሲነገር "ተንቤኔ" ስለ አጤ ምኒልክ ሲነገር "አንጎለለ" የሚባለው የትውልድ መንደራቸውን ለመጥቀስ ነው። ከዚህ በላይ ምሳሌ እንደቀረበው ሁሉ አንዳንድ ልጆች ወልቃይቴ ነኝ ቢሉ ጠባብነታቸውን ለመግለጽ ብለው የተጠቀሙበት አይደለም። ወልቃይት ወደ ትግሬ ሊከለል




ታስበና ዛሬ ልጆቹን በሁት ከፈላቸው ወደ ሚለው ታሪክ ስንገባ ይሀን ይመስላል።

ወያኔ ሕውሓት ትግራይ ሪፓብሊክ ተብሎ የሚመሰረተው መንግሥት ከውጭ አገር ጋር ግንኙነት የሚያደርግበት ለም መሬትና ባህር ማግኘት እንዳለበት ጥናቱን ለአንድ ዓመት ካጠና በኋላ በ1968 ዓም ሪፓብሊክ ትግራይ መንግሥት ዳር ደንበር ብሎ ባሰራጨው "ማኒፌስቶ" ለመጀመሪያ ግዜ ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ከወሎ እንዲሁ አሸንጌን ከአሰብ አስተዳደር አሰብ እደቡን ጨምሮ የትግራይ ግዛት ነው ብሎ አወጣ። ይሀን ገፀ ምድር ካርታ ከሳለ በኋላ ከወልቃይት ልጆች ቅይጦችንና ሆድ አምላኬዎችን መያዙ አይዘነጋም ይህ ታሪክ ከግቡ እንዲደርስ ከሰሜን አውራጃ ወደ ትግሬ የተከለሉትን ወረዳዎችና ከወገራ አውራጃ ወደ ትግሬ የተከለሉትን የወረዳውን ተወላጆች አንጋፋውን ኢዲዩ ወጣቱን ኢሕአፓ እያሉ በደርግ ተሹመው ስሜን አውራጃ ገዥ የነበሩት አሰር አለቃ ገብረ ሕይዎት ገብረ እግዚአብሔር በሊማሊሞ ገደል ይሰዱአቸው ጀመር። ወያኔ ከአገር ውስጥ ያሉትን ብቻ ሳይሆን በስደት ዓለም ሱዳን ያሉትን የነዚህን ወረዳ ተወላጆች ጨርሷቸዋል።

ለአንባቢያን መሰረታዊ ታሪክ ማስጨበጥ የፈለኩት ወያኔን የተከተሉት በብዛት የኤርትራን መንግሥት ከፍ ለማድረግ ታጥቀው የተነሱ መሆናቸው ምልክቱ በ1968 ዓም "ማኒፌስቶ" ላይ አሰብ ከትግራይ ሪፓብሊክ ውስጥ የተቀረፀች መሆንዋን ከዚህ ዝቅ ብሎ ያለውን ካርታ በጥሞና ተመልከቱት። በዚህ ወቅት ሻዕቢያ አሰብ በኤርትራ ውስጥ አለመተዳደሩን ከታሪክ ያውቅ ስለነበር የኤርትራ ግዛት አድርጎ አይቆጥራትም ነበር። ከወያኔ ማኒፌስቶ ላይ ሲሳል እንዴት ያላለው ከቀደም ጀምሮ አሰብ አስተዳደር በባህረ ነጋሽ ውስጥ ተዳድሮ ስለማያውቅ ነው። አሰብን ወደ ኤርትራ እንዲሆን ጥረት ያደረጉት የዛሬው የኢትዮጵያ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ፣ ናቸው። በ1968 ዓም ከወጣው ካርታ ላይ ዛሬ አሰብ የትግራይ አስተዳደር ውስጥ ባትገባም ሌሎችን ከወሎና ከጎንደር የተከለሉትን እንሆ በትግራይ አስተዳደር ውስጥ እንዲሆኑ መደረጉ ከታሪክ ውጭ መሆኑን ከዚህ በፊት ደግሜ ደጋግሜ መጠቆሜን አረሳም። እኛ ብቻ ሳንሆን ራሱ የወያኔ ፈጣሪ ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ እንኳን እንዲህ ይላሉ።

ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፍወርቅ <u>አሰር መጽሔት</u> 1990 ዓም ጋዜጠኛ ላደረገላቸው ቃለ መጠየቅ ጥያቄ "ወያኔ በ1968 ዓም ማኒፌስቶ አሰብ ወደ ትግራይ ክልል አስገብተው ነበር። ስለዚህ እናንተ በዛን ሰዓት ምን አላችሁ?" መልስ ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ "እኛ ይህ ይመጣል ብለን አላሰብነም" የሚል መልስ ሲሰጡ ጋዜጠኛው እንደገና "የሪፓብሊክ ትግራይ ድንበር የተወሰነው ከጎንደር ወልቃይትን በመቁረስ እስከ ሱዳን ሲደርስ ከወሎ ደግሞ ሰቆጣ አሸንጌና አላማጣና ቆቦን ጨምሮ አሰብ ድረስ የሚሄድ ካርታ ነበር። የሕዝባዊ ግንባር በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠው መልስ ነበር?" ሲላቸው ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ አፍወርቅ "እዚህ ላይ መገንዘብ ያለበት ይሄ በ1968 ዓም የሕወሀት መግለጫ ምክንያታዊ ነበር ወይም አልነበረም ወቅታዊ ነው አይደለም" በሚል

ዘግተውታል። ከዚህ ላይ ታሪክን ጠንቅቀን እንድናይ ግድ ይላል። ከዚህ ዝቅ ብየም የምጠቅሰው ታሪክ ከጎንደር ወደ ትግሬ የተከለሉ ወረዳዎች በትግራይ ግዛት ውስጥ ለማስገባት የታሰበው ወያኔ ከተመሰረተ ከ1967 ዓም ወዲህ ሲሆን በሰነድ የተገለጸው ግን 1968 ዓም ነው።




ወያኔ ሲመሰረት ሪፓብሊክ ትግራይ ካርታ

አቶ ገብረ መድህን አእርያ እና አቶ አብርሃም ያየህ የወያኔው ታላቅሤራ በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 34 የወጣው ስዕል ነው። የሕወሓት ማኒፌስቶ 1968 ዓም ከወጣው ላይ የወጣ ካርታ!



## ምዕራፍ 2

### "ወልቃይት ወደ ትግሬ ሲከለል ጎንደሬዎች ዝም አሉ?"

ትግራይን ከኢትዮጵያ ሊገነጥል የተመሰረተው ድርጅት ከወያኔ ኮት ላይ የኢሕአዴግን ካፖርት ደርቦ የኢትዮጵያን ሕዝብ አጭበርብሮ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም አዲስ አበባን ከያዘ በኋላ በ1968 ዓም ያወጣውን ገጸ ምድር ካርታ ከሥራ ላይ ለማዋል ሲል አሰብን ትቶ ከወሎና ከጎንደር የወሰዳቸውን ወረዳዎች በትግሬ አስተዳደር ውስጥ አስገብቶ ይፋ ሲያደርግ የጎንደር ተወላጆች በገጠር ያሉት ቀደም ሲል ጀምሮ በውጊያ የነበሩት ውጊያቸውን አጠንካረው ሲነሱ በከተማ ንዋሪ የሆኑ ታዋቂ ምሁራን ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት እንዲሁም በቋራ በኩል ወደ ቤሪ ሻንጉል የተከለሉትን ወረዳዎች አስመልክቶ አቤት እያሉ መሆናቸውን ሰነዶች ዋቢ ሲሆኑ ክቡር አቶ ታየ ረታ ግን ብቻቸውን ለፍልፈው የቀሩ መሆናቸውን በአደባባይ በመናገራቸው መልስ በማስፈለጉ ከዚህ የሚከተለውን እንድጽፍ አስገደደኝ።

ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓም የሲያትል ዋሽንግተን የቅንጅትና ሕብረት ያዘጋጁት ስብሰባ ነው ተብሎ በዚሁ ቀን ተነግሮነአል። የኢትዮጵያን ደንበር ያውቃሉ የተባሉ ክቡር አቶ ታየ ረታ እና ክቡር አቶ ሽፈራው እንቆ ባህሪ መጥተው ነበር። በዚህ ስብሰባ ላይ ክቡር አቶ ታየ ረታ ሲናገሩ "ወልቃይት ሁመራ ወደ ትግሬ ሲከለል ብቻዬን ለፍልፌ ቀረሁ! ጎንደሬዎች ዝም አሉ "ሲሉ ተናገሩ። እኔም ጎንደሮች ዝም አለማለታቸውን አሳስቤአለሁ። ከቤቴ መጥቼ ቀደም የታተሙ መጽሔቶችን ባገላብጥ እርሳቸው የጻፉት ሳላገኝ ቀረሁ። ምናልባት እኔ ካለኝ ሰነድ ውስጥ ሳይሆን ቀርቶ ከሆነ ቢያብራሩልኝ ደስ ይለኛል። እርስዎ የጻፉት ሠነድ ቢኖርም እንኳን ጎንደሮች ዝም አላሉም። ይህን በተመለከተ ማብራራት ያስፈልጋል። ወያኔ በወልቃይት ተወላጆች ላይ የፈጸመው ግፍ በተመለከተ ሰሚ ጠፍቶ እንጂ ትግሉ ዛሬ ሳይሆን ከ1973 ዓም መጨረሻ ጀምሮ ነው።

ከፋኝ የተመሰረተው በወልቃይት ጠገዴ ጠለምት ልጆች ነበር የሚሉ አሉ። ኢዲዩ ሕዝቡን አስፈጅቶ ሱዳን ሲገባ ኢሕአፓ በራሱ ችግር ሲፈርስ በአቶ ጎሹ አግደውና በአቶ ምትኩ ባንቲ ላይ የካቲት 18 ቀን 1972 ዓም ከገደላቸው በኋላ ከአቶ አሰረስ አግደው ቤተሰቦች ጋር ሲዳማ ከአርማጭሆ ወደ ሽንፋ ገብቶ መሳሪያውን ለሱዳን አስረክቦ አውሮፓና አሜሪካ ሲገባ መሳሪያውን ለጎንደር ሳይሆን ለሱዳን ሰጥቶታል።

ከጅብሃ ጋር የነበረው ኢሕአፓ በ1973 ዓም መጨረሻ ላይ በወልቃይት አልፎ ግጨው ከተባለው በርሃ ሲሰፍር ቀስ በቀስ ከአርማጭሆ ሕዝብ ጋር የሻከረውን ጠብ ለማለሳለስ ጥረት በሚያደርግበት ወቅት በ1975 ዓም ጥር 18 ቀን የ84

ዓመት እዛውንት ቢትወደድ አዳነ መኮንንንና አቶ አበበ ጀንበርን ሌሎችንም በመግደሉ ከአርማጭሆ ሕዝብ ጋር ችግር ገብቶበት ወደ ቋራ ሲለቅ የትግራይ ትውልድ ዘር የነበራቸው አቶ ይርጋ ደስታ ትብብር በማድረግ ወያኔን ከወልቃይት ወደ አርማጭሆ እንዲገቡ ሲደረግ የቆላው ሕዝብ በነበሩት ድርጅቶች እምነት ባለመኖሩ ምክንያት ፥ከፋኝ፥ ብሎ ወያኔን እየወጋ ደርግንም እየወጋ ብዙ ዓመታት ከቆየ በኋላ የርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም መንግሥት አቢዮታዊ ፋኖ ብሎ የተወሰነ እርዳታ ያደርግላቸው እንደነበር አይዘነጋም:: ወያኔ አዲስ አበባን ሲይዝ በመጀመሪያ ኤሊኮፍተር የጣሉበት ከፋኞች ነበሩ:: እነዚህን ጀግኖች ለወያኔ መቅሰፍት የነበሩትን አንዳንዶች ቀንበር ሲጠብባቸው ከወያኔ ጋር በሽምግልና እንዲገቡ ተደርገው ገቡና ተገደሉ ለምሳሌ ኪዳነ ማርያምን መጥቀስ ይቻላል::

ሸተል አፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሰኔ 1985 ዓም ገጽ 24 "ኢሕአዴግ ጎንደር ከተማን ሲቆጣጠር እየገሰገሰ ሲመጣ ለስምንት ቀናት ያህል በከተማው ዙሪያ ከፍተኛ የሆነ የመከላከል ተግባርን ካከናወኑ በኋላ ኪዳኔና የሽምቅ ጦር አባላት የሁኔታውን መበላሸት በማጤን ስልታዊ ሽሽት በማድረግ ወደለመዱት በርሃ ገቡ:: ኢሕአዴግ ጎንደርን ተቆጣጠረ:: ከዚያም በኋላ በሰሜን ጎንደር ክልል በአርማደጋ፤ በጠለምት መሐልና በተከዜ ዳርዳር በአርማጭሆና በማያፀብሬ በብራ፡ዘዳንሻና በመሳሰሉት በርሃዎች እየተንቀሳቀሱ የኢሕአዴግን ጦር በተደጋጋሚ የገጠሙ ሲሆን እንደሚታወቀው ኪዳነ ማርያምና የተወሰኑ ጓደኞቹ በምኅረት እንዲገቡ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ሽማግሌዎችን በመላክ ከፍተኛ ጥረት ካደረጉ በኋላ በሃያ የማያንሱ ካህናትና ሽማግሌዎች የየአድባራቱን መስቀል በመያዝ አርማዛሊ ከተባለው በረሐ ዳር በአርማጻጋ ውስጥ ከሚገኙት ከእነ ኪዳነ ማርያም ጋር ጥር 10 /1985 ዓም በመገናኘት ድርድር ተጀመረ" ሲሉ ጽፈዋል::

ወልቃይት ጠገዴንና ሌሎችንም ወረዳዎች በተመለከተ መጽሔቶች ብዙ መግር ጋዜጦች ላይ የወጡትን ጹሁፎች ሰብስቦ ማንበብ የወልቃይት ሕዝብን ትግል ለመረዳት አያዳግትም:: ክቡር አቶ ታዬ ረታ ማስታወሻያ እንዲሆናቸው ከዚህ በታች ጸሐፊዎች በመጽሔትና በጋዜጣ የጻፉትን ስማቸውንና የታተመበትን ዓመተ ምሕረት ጠቁሞ ማለፍ በማስፈለጉ ትንሽ ልቁጠር:: በአገር ውስጥና ውጭ አገር የሚኖሩ የጻፉት ነው!

## መጽሔት

1ኛ ሙዳይ መጽሔት መጋቢት 1985 ዓም "የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ አዲሱን ካርታ አልተቀበለውም"የሚለውን ጹሑፍ ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ የመጀመሪያውን ይመልከቱ:: በውጭ አገር የወልቃይት እና ጠገዴ ሕዝብ ጉዳይ አስተባባሪ ኮሞቴ ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 2ኛ 11 ቁጥር 2 1996 ዓም "መልስ ያጣ የወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ ዕንባ"ተብሎ የወጣውን መግለጫ ከዚሁ ምዕራፍ በመጨረሻው ላይ ያለውን ይመልከቱ::



3ኛ አያናአዝጊ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም ገጽ 38 "ማርያም ሁመራይቱ ወይ ፍረጅ ወይ ውረጅ"

4ኛ መልዓከ ሰላም ሲሳይ አየለ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም ወልቃይት በትግራይ እና በጎንደር ሕዝቦች መሀል የተቀበረ ፈንጅ

## ጋዜጣ

1ኛ አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅዕ 7 ቁጥር 8 መጋቢት 6 ቀን 1993 ዓም "አ! ወልቃይት"
2ኛ አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 6 ጥር 24 ቀን 1993 ዓም "አ!ወልቃይት"
3ኛ አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 7 የካቲት 21 ቀን 1995 ዓም "አ!ወልቃይት"
4ኛ ጎሹ ገብሩ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 3 ጥቅምት 22 ቀን 1995 ዓም "የወልቃይት ጠገዴ ጀግና ሕዝብ ያስጠቃው ማን ነው?"
5ኛ ጎሹ ገብሩ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 4 ሕዳር 22 ቀን 1995 ዓም "የወልቃይት ጠገዴን ጀግና ሕዝብ ያስጠቃው ማን ነው?"
6ኛ የሰሜን ጎንደር ተወላጆች በጀርመን ሞገድ ጋዜጣ 2ኛ ዓመት ቁጥር 20 የካቲት 2 ቀን 1987 ዓም እውነተኞቹ የወልቃይት ተወላጆች በወያኔ ባንዳዎች አይወናበዱም::

## መጣጥፍ

1ኛ አሽብር ተቆርቋሪ የሌለው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ አሁንም ቢሆን ወያኔ በቆፈረቻቸው ጉድጓዶች የቁም ሥቃይ እያየ የወገን ያለህ ይላል::

2ኛ በአውሮፓ የሚገኙ የወልቃይት ተወላጆች መሰደብ ከአገር መቀማት አይብሰም ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል::

3ኛ በወልቃይት ሕዝብ ላይ የደረሰው ችግር ሕዝቡ እንዲወያይበት የቀረበ የመንደርደሪያ ሐሳብ ጹሑፍ (ወልቃይት ሳይጠፋ በሕብረት እንግፋ) በሚል ርዕስ የተጻፈ:: ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው ሠነዶች እንዳሉ ሁነው ሌሎችም ስለ ሌላ ታሪክ ሲጥፉ እግረ መንገዳቸውን ወልቃይት የትግሬ አለመሆኑን እያስመሩበት አልፈዋል:: ይህ በጎንደሬዎች ብቻ ሳይሆን ሌሎች ኢትዮጵያውያን የተጻፈት ነው::ለማንኛውም ባይበዛም ትንሽ ጠቆም ሳድርግ::

ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 7 ቁጥር 6.1992 ዓም ገጽ 36 "በሁመራ ዘንድሮ ከ200 ሺ ኩንታል በላይ ሰሊጥ ተመረተ አዲስ ዘመን ታህሳስ 25/92 ይላል" በሙሻዘር አምድ ሲያቀርብ መልሱ ደግሞ እንዲህ ይላል "ሁመራ ትግራይ

ከገባች በጣም ለመለመች" ሲል ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ አሹፎበታል። እንኳን የጎንደር ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁመራ የትግራይ ናት ብሎ የተቀበለ የለም። ለዚህም ነው ይህን ማስረጃ እየፈለስኩ የማቀርበው። ከትግራይ አብራክ የወጡት ኢትዮጵያውያን ሳይቀሩ መስክረዋል።

| | |
|---|---|
| 1ኛ ራስ መንገሻ ስዩም | 2ኛ አቶ ግደይ ባሕር ሹም |
| 3ኛ አቶ አቶ ታመነ (ሊንጎ) | 4ኛ ገብረ መድህን አእርያ |

5ኛ አቶ አብርሃም ያየህ የጎንደር መሆኑን በተለያዩ ጊዜ መስክረዋል።

ገብረ መድህን አእርያ አብርሃም ያየህ የወያኔው ታላቅ ሤራ በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 33 ገብረ መድህን አእርያ "በመሰረቱ ካርታ እኔም ሆንኩ ጥቂት ሰዎች ሆነን በዘፈቀደ የምንቀርጸው ነገር አይደለም። ካርታ በዓለም አቀፍ ሕግ ደንቦችና በአገር ደረጃ ከታሪክ በመነሳት በኤክስፐርቶች ተጠንቶ የሚቀረጽ ነገር ነው። በታሪክ የትግራይ ወሰን እስከ ሱዳን ጠረፍ ነው የሚል ነገር የለም። የትግራይ ክልል በማንኛውም ጊዜ ከሱዳን ጠረፍ ጋር የተያያዘ ነው የሚል ታሪክ ፈጽሞ የለም። ይሁን እንጂ የትግራይን ሪፓብሊክ እንመሰርታለን በሚል ከጎንደር ወልቃይትን በመቁረጥ እስከ ሱዳን ወስዶ እስከ አሰብ ድረስ አዲስ ካርታ ተንድፏል። ይህ ካርታ ፈጽሞ በታሪክ የሌለ ከመሆኑም ሌላ አሁንም ሆነ ወደፊት ከአጎራባች ክፍላተ ሀገር ጋር የሚፈጥረው ችግር ከፍተኛ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። የወሎንም ሆነ የጎንደርን መሬት የእኔ ነው ብሎ የሚነሳ ክፍል ከእነዚህ ሕዝቦች ጋር ከፍተኛ ቅራኔ መፍጠሩ የማይቀር ነው" ሲሉ ተናግረው እንደነበር ገልጸዋል።

የኢዲዩ ወሳኝ ሰው የነበሩ አቶ ታመነ ወይም ሊንጎ በ1983 ዓም ሎስ አንጀል ላይ ከኢዲኃቅ ጽፈት ቤት እንዲህ ሲሉ ተናግረው ነበር። "እኛ የትግራይ ልጆች እንኳን የትግራይን ታሪክ የኢትዮጵያን ታሪክ የማይጽፈውና የማያነበው ሁሉ ጠንቅቆ ያውቃል። የትግራይ መሬትም ከዜት እስከ ዜት እንደሆነ አበጥሮ ያውቃል። ወያኔ የትግራይን ሕዝብ ከጎንደርና ከወሎ ሕዝብ ጋር ሊያጣላው ብሎ መሬት ቆርሶ ሊወስድ ያሰበ መሆኑን ቀደም ጠራናፊት ሁነን ስንዋጋው ሳለ ጀምሮ መፈከሩ ነበር። ይህ በጠበንጃ የሚነጠቅ መሬት አንዳንድ ከአፍንጫቸው ላይ የሚያስቡ የወያኔ ደጋፊዎች ሊቀበሉ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን የወያኔ ሥልጣን ሲገረሰስ ቅሌት እንዳይሆንባቸው ሊያስቡበት ይገባል" ሲሉ ተናግረው ነበር።

ገ/ጻድቅ አበራ ኢትዮጵ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 3 ነሐሴ 1991 ዓም ገጽ 7 "ደርግ በ1967 ዓም የወረሳቸው ቤቶች በትግራይ ክልል በሙሉ ተመልሰዋል። ወልቃይት፣ጠገዴ እና ጠለምትን ከጎንደር አላማጣና ኮረምን ከወሎ ወደ ትግራይ ከልለዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

ውዱ ገበየሁ ዜጋ መጽሔት 1 ዓመት ቁ 5 የካቲት/መጋቢት 1992 ዓም ገጽ 30 "የወልቃይትና የጠለምት መሬት ወደ ትግራይ መሄድ አለመረጋጋት ያመጣል" ሲሉ ጽፈዋል።



አቶ ሐቢቡ ታከለ "በጎንደር ላይ ሰላም እንዲመጣ ከፈለጋችሁ ወልቃይት ጠገዴና ሌሎችም ወረዳዎች ወደ ቀድሞ ግዛታቸው ይመለሱ" ሲሉ ተናግረዋል።

መጽሐፈ ሲራክ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 5 ቁጥር 8 መጋቢት 7 ቀን 1992 ዓም ገጽ 7"ዋ ጎንደር ወልቃይት ጠገዴ እግር ኖሮት እሰም ለስደት ሲዳረግ ሁመራ ሌላውም ሲከተል የትውልድ መሬቴ የትም ሲነጉድ ወኔዬ ከውስጤ ገንፍሎ አላልኩትም በሀ አትሂድ ውበትሽ ሲነጠቅ ካልተቆጨሁ መሬትሽ ሲሄድ ካልተነሳሁ እትብቴን መልሽ እናታለም እኔስ ለራሴም አልበጀሁ" ሲሉ ጽፈዋል። የጎንደር ማህበር መርኃ ግብር ዋቢ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ማሕበሩ ሲመሰረት ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ወረዳዎችን ከሌሎች የጎንደር ክፍለ ሀገር ወረዳዎች ጋር አጣምሮ የያዘ መሆኑ ሰነዱ ዋቢ ነው።

የጎንደር ክፍለ ሀገር የመልሶ ማቋቋምና የልማት ማህበር ጥራዝ 1 መስከረም 1984 ዓም ገጽ 3 "ክልላዊ አስተዳደሩም በስሜን የተከዜን ወንዝ በማካለል ኤርትራንና ትግራይን፣ በምስራቅ ትግራይንና ወሎን፣በደቡብ የዓባይን ወይዝ በማካለል ጎጃምና በምዕራብ ሱዳን ነው። ክፍለ ሀገሩም 79.098 ካሬ ሜትር ስፋ ያለና በሰባት አውራጃዎች የጎንደር ከተማን ጨምሮ ወደ 3.7 ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርበት ሲሆን የተረሳና በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ሲፈራረቁበት የኖረ ክልል ነው" ሲል ጽፏል።

መይሣው ጋዜጣ ጥር 15 ቀን 1992 ዓም ገጽ 2 "ከየትኛውም ክ/ዘመን ጀምሮ በየትኛውም የታሪክ ወቅት ወይም በየትኛውም ንጉሥ ዘመን ነው ወልቃይት ጠገዴና ሁመራ በትግራይ ስር የነበረው ተብሎ መረዮች ቢጠየቁ መልስ የላቸውም። ሆኖ አያውቅም። በባሕልና በቋንቋ መመሳሰል የሚለው ከመጣ ታዲያ እምብርቱ ኢትዮጵያ መሬት ላይ ያለው አፋር መሆኑ እየታወቀ እስከ ቀይ ባሕር የዘለቀውን የአፋር ብሔረሰብ ለምን ለኤርትራ አሳልፋችሁ ሰጣችሁ ቢባሉ የሚሰጡት ምላሽ አይኖርም" ሲሉ ጽፈዋል።

ፊያሜታ ጋዜጣ ታህሳስ 15 ቀን 1990 ዓም ገጽ 5 "የህወሓት/ማሌሊት ኢሕአዴግ መሪዎች አዲስ አበባ ገብተው ቤተ መንግሥት ከተቆጣጠሩ በኋላ ወልቃይቶች በጎንደር በአዲስ አበባ እየሰበሰቡ ወልቃይት የትግራይ ክፍለ ሀገር እንደነበረ እንዲመሰክሩ ፊርማቸውን እንዲያስቀምጡ የሞከሩበት ጊዜም ነበር። ይሁን እንጂ ወልቃይት አገሩን አሳልፎ የሰጠ ማንም አልነበረም። ለወደፊቱም አይኖርም። አንድ ጊዜ አቶ መለስ ዜናዊ ለአንድ የወልቃይት ሰው ወልቃይት ትግራይ ነው አይደልም? ብሎ ቢጠይቅ አዩ ጌታዬ እርስዎ እንደሚሉት እኛ እንፈርም ነበር ነገር ግን የማይፈርም ሰው አለን እሱም ተከዜ ነው። ተከዜ ወንዝ ባይኖር ኖሮ ነበረ ሲል መልስ ሰጡ" ሲሉ ጽፈዋል።

ሙዳይ መጽሔት መስከረም 1987 ዓም "ኢሕአዴግ ፊርሞና አጽድቆ ያወጣውን ቻርተር በመጣስ አማርኛን አፍ መፍቻቸው ያደረጉ ጎንደሬዎችን

መሬት ቆርሶ ለክልል 1 መስጠቱ በታሪክም በሕግም ፊት አጠያያቂ ነው:: ከተከዜ ጀምሮ ደቡብ እስከ በሽሎና ጠፋን ወንዞች በተዘረጋው ምድር ላይ ያሉት ወረዳዎች ሕዝብ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ነው:: ከትግራይ ጋር በተከዜ ወንዝ ድልድይነት ጎረቤት ስለሆኑ ወዲያና ወዲህ ማዶ ያለው የአማራና የትግራይ ሕዝብ አንዱ የሌላውን ቋንቋ ይናገራል:: የአማርኛ ቃላት ደግሞ ቢያንስ 80 በመቶ ተመሳሳይ በመሆናቸው መናገሩ አዳጋች አይሆንባቸውም::"

"ይልቁንም የወልቃይት የጠገዴና የጠለምት መዘጋዎች ጥጥ ስለሚያመርቱ ብዙ የትግራይ ተወላጆች በጥጥ ለቀማ ወቅት በየዓመቱ ወደዚህ መዘጋዎች ይመጣሉ::አማሮች ከእነሱ ጋር ለመግባባት ሲሉ ትግርኛውን ይጠቀሙበታል:: ከእንግዶቹም መካከል እዚያው ሚስት እያገቡ የሚቀሩት ጥቂት ስላላይደሉ ሀገሬው ትግርኛውን ለማሻሻል ሲል ከእነርሱ ጋር በትግርኛ መነጋገር በማዘውተሩ ለወልቃይትና ለጠለምት አካባቢዎች ትግርኛ እንደ 2ኛ ቋንቋ ሆኖአል ማለት ይቻላል:: ወልቃይት ጠገዴ ጠለምት ወይም ሁመራ በአክሱም በሳሲታው ዛጉዬ በሸዋ ሆነ በጎንደር ዘመነ መንግሥት አንድም ጊዜ የትግራይ ግዛት አካል ወይም ገባር የሆነበት የታሪክ ወቅት የለም" ሲሉ ጽፈዋል::

በውጩ ዓለም በተለይ በሐዋርያና በጋፋት ጋዜጣ በሌሎችም መጽሔቶች እንዲሁም በጉግሣ መጽሔት በመጽሐፍትም ብዙ መጣጥፍ ወጥቶአል:: ክቡር አቶ ታዮ ረታ፣ሌላው ቢቀር ከመንደርም ይታተም የነበረው ሞረሽ መጽሔት ያወጣውን ጹሑፍ ረሱት? መጽሔቱ ሚኒሶታ ይታተም ነበረ:: ጹሁፍን ያገኘው አዲስ አበባ ይታተም የነበረ ሙዳይ መጽሔት መስከረም 1987 ዓም የወጣውን ጹሑፍ አላነበቡም? ልጥቀስ::

ሞረሽ መጽሔት ቅጽ 3 ቁጥር 2 1987 ዓም ገጽ 13 "ይህ በእንዲህ እንዳለ ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ከወገራና ከከምከም ጋር የታወቁ የአማርኛ ዘፈን፣ ውዝዋዜ፣ለቅሶ፣ወዮታ ፍከራ ቀረርቶ፣ሽለላ እና እንጉርጉሮ መፈለቂያ ቦታዎች ናቸው:: የጎንደር ዘፈን ተብሎ በፋሲለደስ ኪነት የሚቀርበው ዘፈን እስክስታና ውዝዋዜ አብዛኛው ከነዚህ ወረዳዎች የመነጨ ነው:: ይህ ሕዝብ በትግርኛ መዝፈን፣መወዛወዝ እስክታ መውረድ ወዮ ማለት መፈከር ማቅራራት ማንጎራጎር ከቶ አይችልም" ሲል የጻፈውን ቀንጭቤ አቅርቤአለሁ:: ጎንደሮች እንዲም ወልቃይት ሁመራ ጠገዴና ጠለምት ወደ ትግሬ መከለሉን አንቀበልም:: የወልቃይት ተወላጆች ወልቃይት፣ጠገዴና ጠለምት የትግራይ ነው ብለው አያምኑም::

ክቡር ቀኝቀዝማች ገብሩ ገብረ መስቀል የተባሉ አንድ አባት የተናገሩትን ታሪክ ከዚህ ላይ ልጥቀስ:: ወያኔዎች አንዴ ከቤታቸው ሄዱ:: ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ ደግሞ ከቤታቸው የቅዱስ ሚካኤል ጸበል አዘጋጅተው እንግዳ እያስተናገዱ ናቸው:: ታዲያ ወያኔዎች ከግቢያቸው ገቡና "ጌታው ቀኛዝማችን ጥራልን" ብለው አንድ ሰው ላኩ:: ያ የተላከው ሰውም ወደ ክቡር ቀኛዝማች ጠጋ ብሎ "ወያኔዎች ከውጭ ይጠሩዎታል" ሲያቸው ክቡር



ቀኛዝማች "ግቡ የቅዱስ ሚካኤል ፀበል ቅመሱ በላአቸው" አሉ:: ወያኔዎች መልዕክቱ ሲደርሳቸው ቤት ገቡና ከበሉና ከጠጡ በኋላ እርሳቸውን ሊጠይቋቸው እንደሚፈልጉ ነገሩአቸው:: ለውይይቱ ከተስማሙ በኋላ ወያኔዎች "ጌታው ቀኛዝማች ታሪክ ልንጠይቅዎ ነው የመጣነው" ይሏቸዋል::
ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ "እኔን ታሪክ ልትጠይቁኝ" ሲሉ ወያኔዎች "አዎ" አሉ:: ክቡር ቀኛዝማች ገብሩም "የኢትዮጵያን ታሪክ ከሆነ ምን ችግር አለው" ሲሉ ወያኔዎች አይደለም ልንጠይቅዎ የመጣነው:: ወልቃይት የትግራይ ግዛት ነው ይሆን ያውቃሉ" ሲሉአቸው ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ ገብረ መስቀል "በል እስክርቢቶና ወረቀት አምጣ ጻፉ:: እያቴ በ88 ዓመታቸው ሞቱ፣አባቴ ደግሞ በ85 ዓመታቸው ሞቱ" እያሉ መናገር ሲጀምሩ ወያኔዎች "አይ ጌታው ቀኛዝማች እኛ እኮ የፈለግነው ወልቃይት የትግራይ ግዛት መሆኑን ይንገሩን ነው ያልን" ሲሉ ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ "እኮ ስማ ልትደርስበት አይደለም እንዴ እኔ ደግሞ 82 ዓመቴ ነው ይሀን ደምርና ንገረኝ" አሉት::

ወያኔው "ይሀማ 255 ዓመት ይሆናል" ይላቸዋል:: ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ "እንግዲያውስ ልጆቼ በነዚህ ዓመታት ውስጥ ወልቃይት በትግራይ አለመተዳደሯን እናውቃለን:: ወልቃይት ሲተዳደር የነበረው በበጌምድ ግዛት ሁኖ ነው:: ሰው እሺ ቢል እምቢል የሚለው ተከዜ ወንዝ ደንበራችን ሁኖ በጉርብትና በመረዳዳት በግቢና በመተዛዘን አብረን መኖራችን ልክ ነው ይህ የታሪካችን አንዱ ገጽታ መሆኑን እናገራለሁ" ብለው እንቅጩን ሲነግሩአቸው ወያኔዎች ደህና አደሩ ሳይሉ ከቤታቸው ወጥተው ሕደዋል::



ክቡር ቀዛኝማች ገብሩ ገብረ መስቀል!

ስሜን አውራጃ ውስጥ ደግሞ አንድ አባት የተናገሩት ታሪክ ይህ ነው:: ፊታውራሪ ያይኔ ------- የተባሉትን አባት ወያኔ ጥያቄ አቅርበውላቸው ነበር:: የጥያቄው ፍሬ ነገር ከዚህ የሚከተለው ነው "ፊታውራሪ እንኳን የጠለምትን ታሪክ ቀርቶ የኢትዮጵያን ታሪክ ያውቃሉ:: ባለቤትዎ የትግራይ ተወላጅ ናቸው:: ስለዚህ ጠለምትና ጠገዴ ሰቲት ሁመራ የትግሬ መሆኑን ያውቃሉ አይደል?" ብለው ሲጠይቋቸው ፊታውራሪ ያይኔ "የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሕዝብ መሆኑን ልክ ነው አውቃለሁ:: አማራና ትግሬም ተጋብቶ መኖር የጀመረው ቀድሞ እንጂ በእኛ ጊዜ የተጀመረ አይደለም:: እኛ ወልቃይት ጠለምትና ጠገዴም የትግራይ ነው እንበል ነገር ግን የማይስማማ አንድ አለ" ሲሉአቸው ወያኔዎች "እርሱ ማነው የማይቀበል ብለው ሰውየውን ለማወቅ ሲቋምጡ ፊታራራሪ ያይኔ፣ ከበጌምድር ግማሹ የትግራይ ግዛት ነበር ብሎ የማይቀበለውማ ተክዜ ነው:: ስለዚህ እኛ የምናውቀው እነዚህ ቦታዎች የበጌምድር ግዛት እንጅ የትግራይ ግዛት ሁነው አያውቁም" ብለው ነግረዋቸዋል:: እኒህ አዛውንት ባይገደሉም ሌሎች በዚህ ዓይነት ታሪክ እየተናገሩ የተገደሉና የታሰሩ ቁጥር ብዙ ሺህዎች ናቸው:: ከወያኔ ያመለጡ የነዚህ ወረዳዎች ተወላጆች ብዙ ጠቃሚ ምክር ጥለውልን አልፈዋል:: ከሱዳን ወደ አሜሪካ እንዲሰደዱ ያደረጉአቸው መላከ ሰላም ሲሰይ አየለም እንዲሁ ታሪክ ትተውል አልፈዋል::





መልዓከ ሰላም ሲሳይ አየለ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም ገጽ 12" መቸም ኢትዮጵያ ከቀናች ጀምሮ ጎንደርና ትግራይ ተከዜ ወንዝ ነው ደንበራቸው:: አሁን ግን ወልቃይት የልማት አገር በመሆኑ ወልቃይትን ጠገዴን ጠለምትን የትግራይ ነው ብለው አወጁበት:: ከጥንት ከአክሱም ዘመን ጀምሮ ወልቃይት ሆነ ጠገዴ ወይም ጠለምት የትግራይ ሆኖ አያውቅም:: በኃይላቸውና በጠራቸው ብዛት የሚታወቁት አጤ ዮሐንስ እንኳን የትግራይ ነው ብለው አልወሰዱትም እስከ ትናንት ድረስ ጎንደርና ትግራይ ተከዜ ወንዝ ነበር ደንበራቸው:: እኛ በምናውቀው የወልቃይት ሰው ውል ሲዋዋል ሲጻጻፍ ማንኛውንም ነገር በአማርኛ ቋንቋ ነው ሀዘን ደስታውን በአማርኛ ነው የሚገልጸው:: እርግጥ ኩታ ገጠም በመሆኑ ከጊዜ ብዛት ትግርኛ ይናገር ይሆናል:: አሁን ሱዳን ውስጥ ተሰዶ ያለ የአማራና የትግሬ ሰው ሱዳንኛ ይናገራሉ:: ቋንቋቸውን ስለተናገሩ ሱዳናዊ ሆኑ ማለት ግን አይደለም" ይሉና " ሕዝቡ በጣም አዘነ ከዚያም ከፋኝ የሚል ወገን ሲዋጋ ቆይቶ የሞተው ሞቶ ሁለት ሺህ የሚሆን ሰው ታሰረ ይሙቱ ይኑሩ የሚያውቅ የለም እንጂ ያውም ምህረት ይደረጋል ብለዋቸው በምህረት ከገቡ በኋላ አሰሯቸው በዓለም ህግ መሰረት ምህረት ከተባለ በኋላ ሰው ታስሮ የትም አይጣልም:: አሁን እነዚህ ሰዎች የት እንዳሉ የሚያውቅ የለም"::

"ጥያቄ ወያኔ የአማራ ሕዝብ ነፍጠኛና ወራሪ ነው ብሎ ያምናል ምናልባት የወልቃይትን መሬት በወረራ የተወሰደብን ነው ቢሉስ? መልስ የጎንደር ሰው ተከዜን ተሻግሮ የወረረ ከጥንት ጀምሮ አይገኝም:: ወልቃይት ከጥንትም ነገሥታቱና ባላባቱ ዝሆንና አንበሳ ያድኑበት የነበረ ለም ቦታ ነው:: የጎንደር ሰው ከውጭ ወራሪ ጋር እየተዋጋ ሀገሩን አስከብሮ የነበረ ነው:: የወልቃይትን መሬት ለመውረር የመጡትን ከጥንትም ተዋግቶ በደሙ ያቆየው እነ ደጃዝማች ነሹ የደሙበት ሀገር እኮ ነው:: ጥያቄ በቦታው ግን ቀድሞም የትግራይ ተወላጆች የሰሊጥ እርሻ ጭምር እንደነበራቸው የቅብ ጊዜ ትዝታ ነው ይሄን እንዴት ያዩታል:: መልስ መልዓከ ሰላም በቅድሚያ ማወቅ የሚያስፈልገው ሁለቱ ሕዝቦች አብረው የኖሩ በጋብቻም የተሳሰሩ ናቸው:: ከትግራይ መጥተው ከወልቃይት ጋር የተጋቡ ብዙ ናቸው:: አዎ በልማቱ ላይ የትግራይ ሰዎችም ተሳታፊዎች ነበሩ:: እንዲያውም በትራክትር ነበር ያንን ሁሉ መሬት ያለሙት ይሄ ታዲያ የጎንደር ሰው የዋህ ነው ምንም አይልም:: አንተ የውጭ ሰው ነህና ግብር ትከፍላለህ ያላቸው ሰው የለም" ሲሉ መልሰዋል::

ክቡር አቶ ታየ ረታ ከዚህ በላይ የተነገሩት ታሪኮች ለቅምሻ ያክል እንጂ ብዙ የጎንደር ተወላጆች የወያኔን ካርታ የማይቀበሉ ብዙ ናቸው:: ብዙ ጹሑፎች ተጽፈዋል:: ሌላው ይቅር እኔ እንኳን ባቅሚቴይቱ የጻፍኩት አለ:: እራሴን ፀሐፊ ነኝ ለማለት ፈልጌ ሳይሆ ብዙ ጊዜ በወልቃይት ዙሪያ እጽፋለሁ:: በተለይም ወያኔ የትግራይን ምሁራን ወልቃይት የትግሬ ነው ብላችሁ ጻፉ ብሎ በማዘዙ አንዳንድ ግለሰቦች የወያኔን ስሜት እንጸባረቁ:: በተለይ አቶ

ግደይ በላይ በጻፉት መጽሐፍ ላይ ትክክል አለመሆናቸውን አስረግጬ ታሪክ እየጠቀስኩ ጽፌአለሁ::

አማረ አፈለ ብሻው ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ሐምሌ 1992 ዓም ገጽ 42 "ወልቃይት ጠገዴ፥ጠለምት የጎንደር አካል እንጂ ትግራይ አይደለም:: ወያኔ ቀደም ብሎ ሲመሰረት የትግራይን ችግር ለመቅረፍ ከጎረቤት ክፍለ ሀገራት ለም መሬትና የውጭ መገናኛ የባህር በር ለራሱ ለማድረግ ማሰቡ አልቀረም:: በጎንደር ወልቃይትንና ጠገዴን ጠለምትን ከወሎ ሰቆጣን ሌሎችንም ከአፋር አስተዳደር አሰብን ጨምሮ ሱዳን የሚያስገባ በዓለም ላይ የሚያስዋኝ ባህር ድንበር ከልሎ ተነስቶ ነበር:: ሳሉ ደስ አይበላቸው ሲሞቱ ነፍሳቸው አትማር ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ወደ ሥልጣን ከመጡ ጀምሮ የአፋር የአሰብ ወደ ትግራይ መከለል ሲቀር ሌሎችን ለም መሬቶች ለትግራይ ለማድረግ ታጥቆ ተነሳ::"

"ከፍ ተብሎ የተጠቀሰው የሁለቱ አባቶች ደብዳቤ በጥሞና ሳስተዋለው ትንቢት ነው:: ይህ ወገኔ ከማያውቀው ጋር ሁን ተባለ በማለት ያኮረፉ አካባቢው በኀበዝ አለቃ የሚታዘዙ ፋኖዎች ዛሬ ትግላቸውን ከአገር ቤት ውጭ አገር አስፋፍተዋል:: ለዚህም ነው ንግርት ያለው ደብዳቤ ነው ያልኩት:: ወያኔ ከታሪክ ያገኘው አለመሆኑን ቀደም የወያኔ አባል የነበሩት አቶ አረጋዊ በርሄ ጀርመን በ1991 ዓም ተጠይቀው መሳሳታቸውን ተናግረዋል:: ጀርመን የሚታተም መጽሔት ራዕይ ታህሳስ 1992 ዓም ገጽ 2 የዛሬ ዓመት እዚሁ ፍራንክ ፈርት ከተማ ተካሂዶ በነበረ ሌላ ስብሰባ ይኸው ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦላቸው ጫካ እያለን የሠራነው ስህተት ነው ነበር ያሉት ሲል ጽፏል:: ከወያኔ ጋር ሁነው የታገሉት በመጀመሪያው ጀምሮ ይህን እቅድ ያወጡት ሰዎች ተሳስተናል አይደለም የሚሉት" ሲል ተጽፎ ነበር:: ይህ ታሪክ በመሆኑ ሊካድ አይችልም::

የጎንደር ልጆች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ድምጻውያኑ በድምጻቸው ሁመራ የትግሬ አለመሆኑን ደግመው ደጋግመው እያሳሰቡ ናቸው:: የጎንደር ባህላዊ ድምጻዊ ሴት ከወንድ ስለ ሁመራ ያልዘፈነ የለም:: ትናንት አዚመዋል ነገም ያዜማሉ ከነገ ወዲያም፥ከዚያ ወዲያም ያዜማሉ:: ይርጋ ዱባለ፥እርጎዬ ሻምበል በላይነህና ሌሎችም ድምጻውያን አዚመዋል:: ሌላው ቢቀር ድምጻዊ የፋሲል ደምወዝ "አለ ነገር" የሚለውን ዘፈን በጥሞና ማዳመጥ መልካም ይመስለኛል::

"አለ ነገር ዘንድሮ አለ ነገር
በጎንደር በጎጃም በመሬ በሸዋ ዘንድሮ አለነገር
አረሱት ይሉኛል የሁመራን መሬት
የአርማጭሆን የመተማን መሬት
ያውም የኛን እጣ
እነሱ ምን ያርጉ ከኛ ሰው ሲታጣ"



የሚለው ዘፈን የሚረሳ አይደለም:: ይህን ዘፈን የሰሙ ስለ ሁመራ ወደ ትግሬ መከለል ያንገበጋቸው ተቀማችነታቸው አሜሪካ የሆኑ ትዮጵያዊት! ድምጻዊ ፋሲል ደመወዝን ካነጋገሩ በኋላ በዲቪዲ ተባዝቶ ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበት እንዲዳረስ አድርገዋል:: እርሳቸው የአገር ጉዳይ ሁኖባቸው እንጂ ዘፈን ገዝቶ አሳትሞ በተለይ እየተቀዳ በሚሸጥበት ዓለም ሊያተርፉ ፈልገው አይመስለኝም::

ይህን ሲያደርጉ ግን ወያኔ እንደሚያወራው ፀረ ትግሬ ሁነው አይደለም:: የትግራይ ልጆች ሁሌም ጎንደር ይኖራሉ:: ሁመራን ከሌሎች ጎንደሬዎች ጋር ሁነው አርሰው ሲበሉ የከለከላቸው አልነበረም ለወደፊቱም አብረን አርሰን እንበላም የሚል የለም:: ነገር ግን በአስተዳደር ወደ ትግሬ አይከለል ይህ ችግር ይፈጥራል በማለት እንጂ? የክቡር አቶ ታየ ንግግር የእፍ ወለምታ አይደለም:: ለ17 ዓመታት በቀልድ ሲነገር የነበረ ነው:: የመሀል አገር ሰዎች "ወያኔን አሳልፋችሁ የሰደዳችሁ ጎንደሬዎች ናችሁ" እያሉ ሲናገሩ ይደመጡ ነበር:: ጎንደርማ ወያኔን ገትሮ ይዞ ነበር:: ተባባሪ አልደርስለት ብሎ እንጂ? እንዲህ ብለው ስለተናገሩ ጎንደሬዎች ብስጭት ብለው በወያኔ ላይ እንዲነሱ ለማድረግ ታስቦ ከሆነ የሚሰራ አይመስለኝም:: ወያኔን ለመጣል አንቱም ሌሎችም ባንድ ሲቆም ብቻ ነው::

አቶ ታየ ረታ "ደንበሩን ለማየት ስንሔድ አሳሰራ ያሉት የአርማጭሆ ሽፍቶች ነበሩ" አሉ:: የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የኢትዮጵያን ዳር ደንበር ማስጠበቅ ነበረበት ነገር ግን ዝም ስላለ የአርማጭሆ ሕዝብ በራሱ መሳሪያ ደንበር ጠባቂ ሁኖ በማስከበሩ መንግሥት" ሽፍታ" ይላቸው ነበር:: እንኳን በዚያን ወቅት ዛሬም ሳይቀር ያጤው ባለሥልጣኖች ይህን" ሽፍታ" የሚሉትን ቃል ከጭንቅላታቸው ሊፋቅላቸው አልቻለም:: አቶ ታየ ረታ ሰኔ 10 ቀን 2 ሺህ ዓም ተናግረውታል:: እኔ "አቶ ገብሬ ተወልደ መድህን ሌሎችም ሽፍቶች አልነበሩም" የሚል ሰናገር:: አቶ ታየ ረታ "ይቅርታ ሽፍታ ማለቴ አገር ጠባቂ ማለቴ ነው! ለአንድ መቶ ዓመት ደንበራቸውን የጠበቁ መሆናቸውን አውቃለሁ:: ለምሳሌ አሁን የጠቀስከውን ሰው ስም አልተመዘገበም" ሲሉ ተናገሩ:: ሕዝብን የሚንቅ እንደናንተ ያለ በሥልጣን እያለ ተቀምጠው ሌሎች እንዴት በታሪክ ሊታወቁ ይችላሉ? አቶ ገብሬ ተወልደ መድህን ሌሎችም ለደንበራቸው ሲሉ ደማቸውን አፍሰዋል::
"ረግ ረግ ይላል ሲረግጡት መሬቱ
ገብሬ ተወልደ መድንህ የወደቀበቱ"
በማለት የአርማጭሆ ሕዝብ የሚያሞግሳቸውን ጀግና እንሆ ሽፍታ ተባሉ? ዳር ደንበሩን የሚያስከብር ወንድ ሽፍታ ሲባል እንግዲህ ወያኔ በዚህ ገብቶ ሻምበል ቻሌን ገድላችኋል በማለት እንሆ ከ200 በላይ የአርማጭሆ ሕዝብ ታስሮአል:: "ስም ይወጣል ከቤት ይከተላል ጎረቤት" ይባላል:: ሽፍታ ማለት እኔን በሚገባኝ በጎንደር አማርኛ የግለሰብ ንብረት ሆነ የመንግሥት ንብረት ዘርፎ የሚበላ ዓላማ የሌለው ለገንዘብ ሲል ያገኘውን የሚገድልና የሚዘርፍ ነው:: ቀደም ሆነ አሁን በቅርቡ የአርማጭሆ ሕዝብ የሞቱት አገራቸው በርሃው አንበሳና ቀጭኔ ነብር ዝሆን የሚያድኑበት መሬታቸውን ሱዳን ተሻግሮ ሲያርስባቸው ማረስ

የለባችሁም ብለው የተዋጉ ናቸው:: በአርማጭሆ ሕዝብ ላይ የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትና የወያኔ መንግሥት ልዩነት የላቸውም:: የወያኔ መንግሥት የአርማጭሆን ጀግኖች ሽፍታ ማለት ብቻ ሳይሆን ሰላም ነሾች ብሎ ፈርጆአቸዋል:: የሱዳን ወታደር የአርማጭሆን ሆነ ሌላውን ሕዝብ ንብረት ዘርፎ ሲወስድና ሲያስር የአካባቢው ሕዝብ ተደራጅቶ የታሰሩበትን ሰዎች ለማስፈታት ለድርድር አመች እንዲሆን ከሱዳን መሬት ገብቶ ሕዝብ ማርኮ በማምጣቱ ምክንያት የወያኔን ጦር መርተው ሻምበል ቻሌ አለሙ! ወደ ሕዝባዊው ሠራዊት ዘመቱ:: በዚህ ጦርነት ተገደሉ:: ወያኔ ተበሳጨ? የታሰሩትን ኢትዮጵያዊ ሳያስፈታ የተማረኩትን ሱዳኖች ለማስፈታት ያዘመተው ሰራዊት ተመታበት::

ክቡር አቶ ታየ ረታ "እኔ ደስ የሚለኝ ስሜንና በጌምድር ሲባል ነው" ብለዋል:: በእርግጥ አልፈርድም እርስዎ የአጤ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣን ሲሆኑ ዛሬም ያንኑ አረሱትም:: ይህን የከፋፍለህ ግዛው ተግባር ነበር አሁን ግን የለም:: በእርግጥ ወቅትና ጊዜ እየፈለገ ወያኔ በበጌምድርና በስሜን መካከል ሳይሆን በናትና በልጅ በባልና በሚስት የሚገባ መሆኑ አይዘነጋም:: ቢሆንም ደርግ ግንቦት 1966 ዓም ቅድሚያ ካስተካከለው ዋናው አንዱ ስሜንና በጌምድር የሚለውን ጎንደር ብሎ አስቀርቶታል:: ይህ ስሜንና በጌምድር ብሎ የአጤው መንግሥት ለያይቶ ለመግዛት የተጠቀሙበት ስልት ሲሆን እርስዎ ዛሬ እንኳን ከ40 ዓመት በኋላ ሊረሱት አልፈለጉም:: ለወዲፊቱ አንድ ጎንደር እንጂ ስሜንና በጌምድር የሚለውን ትውልዱ አይፈልገውም:: ነገር ግን "እኔ ደስ የሚለኝ ስሜንና በጌምድር ሲባል ነው" የሚለውን ረሳ ያድርጉት ለወደፊቱ አይሰራም::

"አቶ መለስ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ለሱዳን አይሰጥም" ብለው የተከበሩ አቶ ታየ ተናገሩ:: ክቡር ሆይ! ምነው ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር መሬት አልሰጡም? በዚሁ ቀን እርስዎ የኢትዮጵያን ገፀ ምድር (ካርታ) እየነኩ "እኔ አሰብን አለቅም አሰብ የኔ ነው" ሲሉ የተናሩት አሰብን ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ለኤርትራ የሰጡ ስለሆኑ አይደለም እንዴ? ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ አገራዊ ፍቅር ስሜት የላቸውም:: የአገር ፍቅር የሚባል እንኳን ሊጠጋቸው ቀርቶ በአካባቢያቸው አልፎ አልሄደም:: የአገር ፍቅር ቢኖራቸውማ ኑሮ ሌላውን ሁሉ ይተውት እንዴት የአባታቸውን አገር ከትግራይ ቆርሰው ለናታቸው አገር ለኤርትራ ሰጡ? ይህን ያደረጉ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ለሱዳን 1600 ሚትር መሬት አይሰጡም አይባሉም ይሰጣሉ:: አሁንም በደንበር ያሉ ሕዝቦች እነሱ እየሞቱ ያዘገዩት ይሁን እንጂ ቀርቷል ማለት አይደለም::

በሰማይ የሚጓዝ ጉም አይዘንም
አቶ መለስ ዜናዊ አይታመኑም::

ርዕሠ ብሔር አቶ መለስን ማመን ባለት ጉምን እንደ መዝገን ማለት ይሆናል:: ግራዝማች ስንታየሁ ታምራት ለሰዎች ምን ይላሉ ፕሮግራም አዘጋጆች በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 5 "በቴዎድሮስ በነአጤ ዮሐንስ
በምኒ ምኒልክ በኃይለ ሥላሴ በእንድ ላይ ነበርን



ከፉ ቀን መጣና አቆራረጠነ
እርግብና ዋኔ ከቤት ስለዋሉ
ድንቢጦች ተነስተው ወፍ ነን ወፍ ነን አሉ
ወልቃይት ጠገዴ እርሻ ማረስ ያውቃል
ጥቁር ነጭ አይለይም አንድ አርጎ ይወቃል
እሰማ ነበረ አባቴ ሲናገር
በሕይወቴ አላይም ወሰኔ ሲደፈር
ተቀልዶም አያውቅም በሚስትና ባገር
ጀግና እንቅልፍም የለው ተኝቶም አያድር
ጫቆና ሰራብ አዳኝ አገር ሁሉ
ቋራና መተማ በሙሉ
ጓንግን ከተከዜ አንገረብ ወንዞችን
ማን ይሻገረዋል ያለፈቃዳችን
መግቢያና መውጫውን መልካውን ማያውቁ
እንዋኛለን ብለው ገብተው እንዳያልቁ
ትዕዛዝ ይሰጣቸው እንዲጠነቀቁ" ሲሉ ጽፈዋል::



መልዓከ ሰላም ሲሰይ አየለ!

# ተመልካች

**ለዝግጅት ክፍሉ:-** ሰላም ጤና ይስጥልን በኢትዮጵያ የምትገኙ የነፃው ፕሬስ አዘጋጆች፣ ነፃው ፕሬስ በኢትዮጵያ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ የሕዝብን ጩኸት ከዳር እስከ ዳር ለማሰማት ያደረጋችሁትን ጥረት በክብር እናደንቃለን። ሆኖም ከሀገራችን ርቀትና በመንግሥት ተፅዕኖ ምክንያት፣ በጊዜው ኢትዮጵያ ዛሬም ድረስ ከሰታዋክ አጥተው በደብር በተ የሚማቅቁ ወገኖቻችንን ጩኸት ለማሰማት አልተቻላችሁም። ይህ በዚህ ክፍለ ዘመን 'ዲሞክራሲ' በሚል ስምምነት አዳጋች የሆነው አሳዛኝ ተግባር ዛሬም በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ነው። በሰሜኑ የሃገሪቱ ክፍል የቀድሞ የጎንደር ወረዳዎች በነበሩት በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ በሁመራ እና በጠለምት ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ ለመግለጽ መንግሥት እንዲያውቀው ተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም መንግሥት የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ በሚል ጉዳዩ መፍትሄ ምንም ዓይነት መፍትሄ አላስገኘልንም። በመሆኑም ይህን አስመልክቶ ለውጭው ዓለም የሕዝቡን ጥያቄ ወደ ጎን በመተው ምንም ዓይነት መፍትሄ አላስገኘልንም። በመሆኑም ይህን ለማጋለጥ በፊት፣ በነፃው ፕሬስ አማካኝነት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው እንዲደረግልን በማለት የደብዳቤውን ኮፒ ከዚህ ጋር ልከናል። በአክብሮትም በአካባቢው የሚደርሰውን ግፍ እንድታጋልጡልን በሚሰቃዩት ወገኖቻችን ስም እንማጸናለን።

## መልስ ያጣ የወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ ዕንባ

**ይድረስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**

ይህ አቤቱታ የሥልጣን ሁሉ ባለቤት ሊሆን የሚገባው ሕዝብ ኃይልና ሥልጣኑን በተነጠቀበት፣ ብሶትና በደል በመላው ኢትዮጵያ በተንሰራፋበት፣ ፍትህና ርትዕ አስከባሪ ባልተገኘበት በዚህ ሰዓት ከምድረ ወልቃይት እያስተጋባ ያለውን የብዙ ሺህ ሕዝብ ዕንባ ወደ ሰሆነው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሰማው በማለት ወተያዩ ዜጎች ስም የተዘጋጀ መልዕክት ነው።

እነሆ ወያኔ/ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በወልቃይት ጠገዴ ክርስ ምድር በጨለማ የተገደሉ፣ በኮሌጥሮ ቀሽና ሰው ሰራሽ በሆኑ ጉድጓዶች ውስጥ የታሰሩ፣ የዱር አራዊትን ያህል እንኳ ጩኸታቸውን ለወገናቸው ማሰማት የተሳናቸው፣ እናንት ድምጻችንን አስተጋቡልን ሲሉ የሚማጸኑ በርካታ ወገኖች አሉ።

በደሉ ለዓለምም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታፍኖ የሚካሄደውን ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ወገኖች ሆይ ታውቃላችሁን?

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሥርዓቱ የደረሰበትን ጥቃትና ውድቀት፣ እንዲሁም በቃይና መከራ እኛ የወልቃይት ጠገዴ ነዋሪዎች እንደሚገኙኛውም ኢትዮጵያዊ ስንጋፋውና ስንቃወመው ቆይተናል። በወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ ላይ የደረሰውንና የሚደርሰውን የግፍ ግፍ፣ ልዩ ባሰቱን ስለናቱ እንደሚያወያይ፣ እናት ለሆኑትም ሃገሩ የደም ዕንባውን አያደርስ ብሶቱን ይገልጻል። የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ የአብራክ ክፋይ የሆንን እኛ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ እንዲሁም በሌሎች ዓለማት የምንገኝ ኢትዮጵያውያን በዚያች የትው[...] ቀዬ እና ምድር የሚፈስሰውን ደምና ዕንባ የሚታትተ[...] ርር በመከታተል ልናደርግ የምንችለውን ሁሉ ለና[...] ብንቆይም የወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ በደል «በጨኸ[...] መካከል ተውጦ ያልተሰማ ጩኸት» ሆኖ ስላገኘነው [...] ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይወቀው በማለት ይህን አቤ[...] ለማቅረብ ተገድደናል።

[illegible] አላደረግምን? በኢትዮጵያ [...] ዘመናት ሁሉ የወልቃይትና ጠገዴ ሕዝብ የነገ[...] ያወገኑት ችግር ከማንም በላይ ተከፍሏል። የውጭ ኃይ[...] ወረራ በመቋቋም በአርበኝነት ብዙ አንቱ የሚባሉ ጀግ[...] አፍርቷል። በከተም ሆነ በደገ ኢትዮጵያዊነትን ለጥ[...] ሆነ ለከፋፋይ መርዘኛ ሃሳብ ከቶውንም ለድርድር አላቀ[...] በማለት በብዙ የሃገር ጠላቶች ገና በጠዋቱ ጥርስ የተነከ[...] መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋልን?

[illegible] ተጋድሎ ሐርነት ሕዝቢ ትግራይ [...] የታላቋ ትግራይ ትግርኝ ሕልሙን እውን ለማድ[...] የተፈጥሮ ድንበር የሆነውን የተከዜን ወንዝ በማ[...]





አካባቢውን በቁጥጥሩ ስር ለማዋል ጥረት ማድረግ የጀመረው ዛሬ ሳይሆን ትናንት በረሃ እያለ ነበር። እጅግ ለም የሆነችን የሰሜን ምዕራብ ጎንደር ክፍለ ሃገር ግዛት (ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ሰቲት ሁመራ እንዲሁም ጠለምት ወረዳዎች) በማንአህሎኝነት ነጥቆ ለመውሰድ ዘመቻ በከፈተበት ጊዜ ሁሉ ሕዝብ ለሃገሩ አንድነት ወገና የጠቁበ ዘረኝነት ስሜትን በመቃወም ከልጅ እስከ አዋቂ ተከላከሉ አሳፍር ሲመልሳቸው ቆይቷል።

[illegible] "አስከበቃሰት" [illegible] ከፍተኛ [illegible]

ይህ ሕዝብ ለወያኔዎች መስፋፋት ብርቱ እንቅፋት በመሆን ለብዙ ዓመታት መፈናፈኛ አሳጥቶአቸዋል። ለዚህም ነው ታዲያ የወልቃይትና ጠገዴ ክርስ ምድር የደም ቋምበቀል የሚዘንብበት፣ ትውልድ እንደእንዝመራ የሚታጨድበት። [illegible] በዚህ ሕዝብና ትውልድ ላይ አሰቃቂ መዓት አውርደውበታል።

የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪ የሆኑት አቶ መለስ ዜናዊ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የተናገሯቸውን ብዙዎች የሚያስ ታውሱት ነው። ነገር ግን ምንስ የሰው ልጅ በበቀል ሲያምን፣ ጉልበተኛው ጉልበት የሌለውን… ጊዜ ያለጠው ጊዜ የከዳውን፣ ጠመንጃ የያዘ አቅመ ደካማውን እስት ዘእስት ባልተቋረጡ የጥላቻ በትሮች ሰፀዋዊ ፍጡራንን ማሰቃየትና ማጥፋት ከአስር ዓመታት በላይ እንደምን ሳይቋረጥ ሊቀጥል ይችላል?

በመሠረቱ ወያኔ/ኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን ከወጣና ሕዝቦች ሁሉ ለሰላምና መረጋጋት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ በተሳሰሩው የምሀረት አዋጅ የወልቃይትና ጠገዴ አርበኛ ሕዝብ አዋጁን አምኖና ምሀረቱን ከልቡ ተቀብሉ መሣሪያውን በማስረከብ ሰላማዊ ሕይወቱን ለመምራት ወደ ተለመደው የግብርና ኑሮው ተመልሶ ነበር። ይሁን እንጂ የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ያተረፈው ነገር ከወጥመድ እንደገባ የዱር አውሬ መከራን መቀበልና መቀጥቀጥን ነው።

[illegible]

በተ[illegible] የታሪክ ምስክር የሆኑ አባቶች ከጠቀ ቀሪው በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምነው ትውልድና ሌላውም ሕዝብ ለተፈለገው የአካባቢው ንጥቂያ የማይመችና ማንነቱንም አሳውላጭ ለሳለ በጥንካሬ ስልቶች እንዲሟሸሽ፣ የትውልድ ሂደቱ እንዲመክንና ሥርዓቱ በመረጠለት የትግራይ ክልል ውስጥ እንዲዋጥ ተደርጓል።

ከዚህ ጋር በየጊዜው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የሁመራና የሰቲት ዝበራዎች ከየአካባቢያቸው ተግዘው ወደ ተቀፈሩ የቀልቶ ጉድጓድ እስር ቤቶች እንዲገቡ ተደርጓል። [illegible] ተደርጓል። ከዚህ ያመለጡና የተረፉ ብዙዎች ተሰደዱ፣ ቀሪዎቹም ሰብዕናቸውን አጥተው ሞራላቸው ተከላሽቶ፣ ከመኖር ይልቅ ለመኖርን በሚያስመርጡ ግፎች ከብራቸው ተገፍፎ፣ ከራሱቹ ከልመና ደረጃ እንዲደርሱ ሲደረግ ሌሎች ደግሞ በበሽታ ተጠፍረው ቶአሊጋ ቁራኛ እንዲሆኑ ተደርጓል። በ21ኛው ክፍለ ዘመን… ሚስቶች በባሎቻቸው ፊት የሚደፈሩበትን ቅጣት ሳይወድ ተቀብሉ የሚገኘው የወልቃይት እና ጠገዴ ምድር መሆኑን ዓለም ያውቀው ይሆን? ሰውስ ያምነን ይሆን?

እውነቱ ግን ይህ ነው። እውርን ቢደጋግሙት ያነውራልና፣ ዝበዝ ያልቀሰበትን፣ እናት ያነባችበትን ትውልድ ዕንባ የተራጨበትን በመቶ መብርብር የሰው ልጆችን ክብር የሚነካ በመሆኑ ጊዜና ታሪክ ይፍረደው እንላለን።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፣ በወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ሁመራ እና ጠለምት ወረዳዎች ወገኖችህ ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍ ሰላማዊ መፍትሔ እንዲያገኝ በማለት ለወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት የሕዝብ አቤቱታ አቅርበን ነበር። እስካሁን ድረስ የቂሰጠን መልስ የለም። ጭራሹንም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተላከው ኮፒ በፖስታ ቤቱ በኩል ሶስት ጊዜ መከራ ተደርጎ ተቀባይ ጠፍቶ ተመላሽ ሆኗል። ሆኖም ይህን በሕዝባችን ላይ የሚደርሰውን በደልና ግፍ ለመላው የዓለም ኅብረተሰብ፣ መንግሥታትም ሆነ ድርጅቶች ማቅረባችንን እንቀጥላለን!!

በውጭ አገር የወልቃይት እና
ጠገዴ ሕዝብ ጉዳይ አስተባባሪ ኮሚቴ
ለማንኛውም ጥያቄም ሆነ አስተያየት አድራሻችን
P.O.Box. 360983
Columbus, OH 43236- 9997

# የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ አዲሱን ካርታ አልተቀበለውም

ይህንኑ ዓቢይና አንገብጋቢ ችግር መነሻ በማድረግ የሚመለከተውን በር እንኳኳለን ። ስብሰባዎችን ተካፍለ ናል ። ጠረጴዛዎችን አንኳኩተናል ። ሰው አነጋግረናል ። እናም ወደቢያ ትሩ እንሰፍ ።

ግንቦት 15ቀን 1984 ዓ.ም ታትሞ የወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ " ስለብድር ስምምነት " በሚል ርዕሶ ሥር የተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት 13/84 ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የተነጋገረባቸውን ዝርዝር ጉዳዮች ለንባብ ማብቃቱ ይታወሳል ። ምክር ቤቱ በሰፊው ከተወያየባቸው አጀንዳ ዎች መካከል የምርጫ ኮሚሽን አሥራ አራቱን የምርጫ ክልሎች ለመጠቆም ይረዳል በማለት ያወጣውን ካርታ ይመለከታል ። በዚህም መሠረት የኢ ትዮጵያ ሶማሊያ ድርጅቶች ለአጀንዳ ያዘቀውን ጉዳይ ምክር ቤቱ በሰፊው ከተወያየበት በኋላ የምርጫ ኮሚሽን ክልሎችን በሚመለከት ያወጣው ካርታ ይፋዊ የሆነ ብሔራዊ ካርታ አለመ ሆኑንና ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ግልፆ ካሁን በኋላ ከአገልግሎት እንዲ ታገድ ወስኗል ። ከዚህም ጋር በማያ ያገ ካርታው ምክር ቤቱ ሳያየውና ሳያጸድቀው የወጣ ከመሆኑም በላይ በአፈጻጸም ላይ አፍራሽ አስተዋጽኦ አበርክቶ በመገኘቱ ከአገልግሎት እን ዲታገድና በምርጫ ኮሚሽኑ በኩል ማስተባበያ እንዲሰጥበትም ትእዛዝ አስተላልፏል ።

ስለአዲሱ ካርታ ያለው እው ነታ ይህን ይምሰል እንጂ የተወካ ዮች ምክር ቤት ውሳኔ ተግባራዊ ምላሽ ሲያገኝ ግን አልተስተዋለም ። ሌላው ቀርቶ ማስተባበያውን ለመስጠ ት እንኳ ፈቃደኛ ሆኖ የተገኘ የለም ። ይኸው የኢህአዴግን ዓላማና እምነት የሚያንፀባርቀው ካርታ ሥራ ላይ ይውል ዘንድ በአንዳንድ ክልሎች ግፊት የመደረጉን ያህል በወልቃይት ጠገዴም ላይ ሁመራን ጨምሮ በክ ልል 1 ሥር (በትግራይ) ለማስገባት ከመሰናዶ እንበቱ እስከተግባራዊ እንቅስቃሴ ድረስ ብዙ ሙከራዎች ተደርገዋል ። በመሠረቱ ብዙዎቹም የክልል 1 እንቅስቃሴ አየተባለ ነጋ ጠብ ተጠቅሷል ። የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ በበኩሉ በአዲሱ ካርታ እንደ ማይስማማና ተፈጥሮ አደላደሉ ከስ ጠችው ከጥንቱ ወገዝ የጎንደር ክልል ውጭ አዲሱን ካርታ ለመቀ በል ፈቃደኛ እንዳልሆነ በተለያየ መድረክና አቀራረብ ራሱን ግልጽ አድ ርጓል ። የተከበረን ወንዝ ተሻግሮ ፡ በረሀ አቋርጦ ፡ ግብር እንዲከፍል ፡

ቢኝነት እንዲጠይቅና ሌሎችንም ጥያ ቄዎች ለክልል 1 ሹማምንት እንዲያ ቀርብ ሲጠየቅ ሁሉ የሁመራ ፣ የጠለ ምትና የቤቲት ሁመራ ሕዝብ ቅሬታ አልገባውም ማለት አይቻልም ። በየ ጊዜው አቋሙን እየገለጸና እየተፈራ ረመ ወደ ሚመለከተው አካል የላካ ቸው ደብዳቤዎች ህያው ማረጋገጫ ዎች ናቸው ።

ሌላው ቢቀር ጥር 30/85 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የጎን ደር ተወላጆች በዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ባደረጉት የጎንደር የመልሶ ማቋቋምና የልማት ማህበር ስብሰባ ላይ የሁመራ ፣ የወልቃይት ጠገዴና የጠለምት ክልል በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ከተሰብሳቢው ተጠይቆ የተሰጠው ምላሽ ከላይ ለማሳየት የሞከርነውን እውነታ ግልጽ ያደርገ ዋል የሚል እምነት አለን ።



በተጠቀሰው ስብሰባ ላይ ከተነ ሱት ጥያቄዎች መካከል በወልቃይት ጠገዴ አካባቢ ያለው ፀጥታ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል ? አዲሱ ካርታ በክልሉ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቷል ወይ ? የተሰኙት ጥያቄዎች ይገኙ በታል ። በዚህም መሠረት የልማት ማህበሩ ሊቀመንበር በሰጡት ሥል ጣዊ ምላሽ የክልሉን ፀጥታ በተመለ ከተ እስከአሁን በተጨባጭ የሚታ ወቅ ነገር እንደሌለና ሠላም እንዳይ ጠፋ ከመጠበቅ በቀር ለጊዜው ሌላ አማራጭ እንደሌለ ያስረዳሉ ። በሌ ላም በኩል አዲሱን የአስተዳደር ክልል በማስመልከት የማህበሩ ፀሐፊ

ለሆኑት ለአቶ ፍትሐዬ አሰፉ ... ቀርቦ በሰጡት መልስ የወል... ጠገዴ ሕዝብ እስከአሁን ይዞት... ውና በሕግ ከሚታወቀው ... ክልሉ ውጭ አዲሱን ካርታ ... በል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ፣ በቀ... አስተዳደር ክልል (በክልል 1) ... ይታቀፋል በሚል አንዳንድ ቡ... ወይም ድርጅቶች የሚያስተጋ... ወሬ የማይጨበጥ ተስፋ ... በመግለጥ ለሚመለከተው አካ... ቃውሞ ድምፁን ማሰማቱን ... ስባው ተሳታፊ አስታውቀዋል...

እም ይህን በየሰው አእምሮ ... የሚንሳሳውንና ጦርነት ይካሄ... ተብሎ በግል ጋዜጣ ሳይቀር ... ጣቱ ፣ ጋዜጠኞች በህግ ፊት ... ርበ ምክንያት የሆነውን ክል... ቃላይ ሁኔታ በተመለከተ የ... ከ/ሀገር መልሶ ማቋቋሚያና ... ማህበር ሊቀመንበርና ፀሐፊ ... ሲል ለክቡር አቶ መለስ ዜ... ኩት ግልጽ ደብዳቤ " ... ጵያ ድምጽ ሬዲዮ የሽግግሩ ... ሥት የተወካዮች ምክር ቤ... የጵያን አስተዳደር በ14 ክ... ድቋል ብሎ ያስተላለፈው ... ረክ ከንፈደሬሽል ከተመሠ... ጋር የተቀራረ እንዳልሆን... እለን ። ከሆነ ግን ይህ ንድ... መንግሥቱ ረቂቅ አካል ሆኖ ... ጸድቆ ወደ ፊት ለሕዝብ ... ረጠው ሕገ መንግሥት ... ጉባኤ ማቅረብ እንዚህን ወ... ዞች የትግራይና የጎንደር ... ካሁን ጀምረው ለፍጅት እ... መጋበዝ ነው ከሚባል በ... ምክንያትና ትርጉም አይኖረው... ጨማሪም በሽግግር መንግሥ... ቤት ውስጥ የጎንደር ሕዝ... ጠው ተወካይ ባለመኖሩ እ... ዳት የሞከርነውን ቁስሉንና ... በግምባር የሚያስረዳበት አ... በመሆኑም ከዘንድ ዓለም ... የውን መብታችንና ታሪካችን... የሚመረጥ ሕጋዊ ምክር ቤ... ማይነካብን እናምናለን ... ውን ልማት በተመለከተ ... ደረጃ ተንቀሳቅሰ በነበረበ... ከወልቃይትና የጠገዴ ... ቀጥሎ ከፍተኛ ተጠቃሚ... ራይና የኤርትራ ወንድሞቻችን... የካርታውን ንድፍ መውጣ... ራጨት አንድነታችንን ለሚ... ኖች በጣም አስደሳች ሆኖ... ስለዚህ ይህ አሳዛኙ እቅ... ኑት ካልታረመ ወሬው ...



ክራሞት

ጀምሮ በሁለቱ ወንድማማቾች ሕዝቦች መካከል በቀላሉና በጥ ቂት ትውልድ ሊታረም የማይችል ቅራኔና እልቂት በመጋበዝ የተሰበሰ ውን የዲሞክራሲ ፋና በዓለም ፊት እንዳየጨልም በመስጋት ይህን የተ ቀጣ የቅስፈት ስይፍ በወቅቱ የመቅ ጨት ኃላፊነት በክቡርነትዎ ላይ የተቀ መጠ እንደመሆኑ የበኩላችንን በቅን አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ሃሳብ በጎንደር ተወላጅነት ግዴታችን ተካ ፍለተንና ተፃፍፍቱን በትህትና እናቀ ርባለን ። " ሲሉ የአደጋውን አስከ ፊነት ሳይጠቁሙ አላለፉም ።

ከዚያ ወዲህ ያለው ሁኔታ ግን ከህግም ከኃላፊነት ደረጃ ውጭ ሁመራ ፣ ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት በክልል አንድ ሥር እንደተጠቃለለ ሁሉ ሕዝቡ ምሬቱን በሆዱ አርግዞ ያለ ባለቤት የቆየባቸው ጊዜያት ጥቂቶች አይደሉም ። አንዳንድ ክል ሎች የመሠረተ ልማቶችን እየዘረጉ ያሕዝባቸውን የእድገትና የብልጽግና ተቋርጭረና ተጠራ የሌለው የጎንደር ሕ ዝብ ግን በልማትም ሆነ በሌላው እንቅ ስቃሴ ከድጥ ወደማጥ የሚሰበበት ምክ ንያት ዛሬም ግልጽ አይደለም። የትናንት መሪዎቹ በስሙ እየነገዱ ድህነት ፣ ሥቃ ይና መከራን አውርሰውት እንዳላለፉ ሁሉ የዛሬዎቹ ገዥዎቹ ፣ ደግሞ የራ ሱን ዕድል በራስ መወሰን መብት ለየክልሉ ሲሰጡ እያሉ ለጎንደር ሕዝብ ግን ያልውንም እንዳያጣ በማ ድረግ ላይ ናቸው ። ይህ ግን ተፋቅረ ውና ተከባብረው የኖሩትን ኩታ ገጠም ሕዝቦች ከማቃቃር በቀር ፋይዳ አይኖረውም ። ሕዝቡ ጅርተና በሰጠው መብት በመጠቀም ዳር ድን በሩ እንዲከበርለት ሲጠይቅና አቤቱታ ሲያቀርብ ህጋዊ ምላሽ መስጠትና ለልማት ራሱን እንዲያዘጋጅ ሁኔታ ዎችን ማመቻቸት እንጂ ተቀባይነት የሌለው ካርታ እየቀረጹ በማውጣት ተፋቅሮና ተከባብሮ ያኖረን ሕዝብ እርስ በእርስ ማቃቃርና ሠላም መን ሳት ሕገወጥነት ብቻ ሳይሆን በታ ሪክም ፊት አስጠያቂ ይሆናል ።

## ምዕራፍ 3

### “ትግርኛ በመናገሩ ብቻ በጥላቻ እንዲታይ ሁኖአል”

ለአቶ ጎሹ ገብሩ፤ መልሱ ያስፈለገበት ምክንያት በሌላው የጎንደር አውራጃዎችና ወረዳዎች መካከል ልዩነት ሲፈጥር ያለ በመሆኑ ግልጽ ለማድረግ ነው። ወያኔ ያዘጋጀው የተንኮል ሴራ ያልተረዱ አንዳንድ የወልቃይት ልጆች “ወያኔና ደርግ በወልቃይት ላይ የጥፋት ዘመቻ ሲያካሂድ ሌሎች የጎንደር ክፍለ ሀገር ወረዳዎች ዝም ብለዋል” እያሉ መናገር የጀመሩ በመሆናቸው እንዳለ ሁኖ በቅርቡ ደግሞ አጎሹ በመጻፋቸው የጎንደርን ሕዝብ የሚያቀራርብ ሳይሆን የሚያራርቅ በመሆኑ መልሱ አስፈለገ። እኔ ለእርሳቸው መልስ ለመስጠት የፈለኩበት እውነታ ቢኖር ቃሉን ከዚህ በፊት በወያኔዎች ተፈልስፎ ወያኔን በሚደግፉ አንዳንድ የወልቃይት ልጆች የሚነገር ቃል በመሆኑ ነው። እምናለሁ መቶ በመቶ አቶ ጎሹ የወያኔን ሴራ እንደማይደግፉ ነገር ግን እርሳቸው ሳያስቧት ያመለጠች አርፍተ ነገር እንዷን ቃል ወያኔዎች ሲጠቀሙባት በማየቴ ግልጽ ለማድረግ ነው። ወያኔ የትግራይ ሕዝብ ቀደም ቅድሚያ ኢትዮጵያ ከዚያም ትግሬነትን እንቀበላለን ብሎ ስላስቸገራቸው አንድ መላ ፈለገ። ውጭ አገር የመቅረጽ ልምድ ያላቸው ሰዎችን ቀጠሩና ካሜራቸውን አስተካክለው እንዲቀርጹ አሰማሩ። ሕዝቡን ለስብሰባ ሐውዜን ጠራ። ይህንም ወሬ ደርግ እንዲሰማ አደረጉ። ደርግም ፈታሽ ኤሊኮፍተር ልኮ ሲያስጠና የደረሰው መረጃ ትክክል ነው። ወያኔ አስገድዶ የትግራይ ሕዝብ ወደ ስብሰባው እንዲሔድ አደረገ። ከዚህ በኋላ ደርግ አይሮ ልኮ ንጹሕ ሕዝብ ደም በከንቱ እንዲፈስ ሆነ። ከዚህ በኋላ ወያኔን አልደግፍም ያለውን የትግራይን ልጆች ያንን የሥዕል ድም ቪዲዮን ክር በውጭ አገር ያለውን ለማሳመን ቻሉ። በዚህ ዓይነት ሴራ የተካኑት ወያኔዎች ወልቃይትን ከጎንደር ለመለየት ሲሉ ያልፈነቀሉት ድንጊያ የለም። በጥቅም ያደሩ አንዳንድ ሆድ አምላኬዎች ከወልቃይት ልጆች መካከል መለመሉ። እነዚያ ሌሎችን የጎንደር ልጆች “እኛን ወያኔ ሲደበድብን የት ነበራችሁ” እያሉ ሕዝብን እየለያዩ ነው።

ታጋይ ብርሃኔ ገ/ጻዲቅ <u>የኢትዮጵያ ራዲዮ</u> ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም “የዘመናት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሶት የወለደው ጀግናው የኢሕአዴግ ሠራዊት ደርግ ይጠቀምበት የነበረውን የአዲስ አበባ ራዲዮ ጣቢያ ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮታል። ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም” ብለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አወጁ። በዚህ ቀን የተደሰቱ ዘረኞች ሲኖሩ አገር አፍቃሪዎች ግን አለቀሱ። ከዚህ ወዲህ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወያኔ ይከፋፍለው ጀመር። እንኳን “ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮታል” የተባለው ተገለበጠና “ለጠባቦች ጥቅም ተቆጣጥሮታል” መባሉ ነው። አገሪቱን ከፋፍሎ አዲስ የኢትዮጵያ ገጸምድር ካርታ ለሕዝብ ይፋ ሲያደርግ ቅድሚያ የተቃወሙት የጎንደር ምሁራን ናቸው። ወገኖቻችን ወልቃይት ጠገዴንና ጠለምትን ከጎንደር አንለይም።



በቋራ አካባቢ ቤሪ ሻንጉል ለተባለው ክልል የሰተጠው ወረዳ ከጎንደር ወገኖቹ ሊለይ አይገባም ብለው ደብዳቤ የጻፉትን ከዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ይዩ።

ጎሹ ገብሩ <u>ሐዋርያ ጋዜጣ</u> ቅጽ 8 ቁጥር 4 ሕዳር 22 ቀን 1995 ዓም ገጽ 17 “በአጠቃላይ አነጋገር ወልቃይት በምትባለው ትንሽ መንደር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ከወያኔዎች ስቃይ አልፎ በታገለለት ሌሎች ክ/ሀገራት በሚኖረው ወገኑም ጥሩ አቀባበል አልተደረገለትም። የደመቀ ኑሮውን ትቶ እንዲሰደድ በወያኔዎች ሲገደድ ሳለ ወደ መቀሌ አንድም ሰው አልተሰደደም። የተሰደደው ወደ ጎንደር ነበር። ያገኘው ስጦታ ግን ትግርኛ በመናገሩ ብቻ በጥላቻ እንዲታይ ሆኖአል። ምንም እንኳ ይህ ዓይነቱ ተንኮል የወያኔዎች እጅ ኖሮት ከጎንደር ሕዝብ ጋር ለመለያየት የተደረገ ዘዴ መሆኑ እየታወቀ አንድም የጎንደር ምሁር ወይም ድርጅት ሁኔታው አሳዝኖት ይህ ዓይነት ድርጊት ስህተት መሆኑን ያብራራ ማንም የለም” ሲሉ ጽፈዋል። አቶ ጎሹ ያሉት ትክክል አልመሰለኝም። የጎንደር ምሁር ሁሌም ስለ ሁመራ ወልቃይት ከመናገር የቦዘነበት ቀን የለም። ሌላው ቢቀር የጎንደር ማህበር ሲመሰረት ጀምሮ ወልቃይት ከጎንደር መለየት የለበትም ብሎ በመነሳቱ አይደለም እንዴ እስከ ዛሬ አንዲት ጎጆ ሳይቀልስ የቆየው። የጎንደል ልማትና ማህበር የሰራው ሕንጻ ባይኖርም መርሃ ግብሩ ግን ምስክር ነው።

<u>የጎንደር ክፍለ ሀገር</u> አውራጃዎችና ወረዳዎች ምክትል ወረዳዎች በተሰኘው መጣጥፍ ገጽ 1 “የጎንደር ክፍለ ሀገር 7 አውራጃዎች 28 ወረዳዎች 119 ምክትል ወረዳዎች” ሲል ከጻፈው መጣጥፍ ላይ ወልቃይት ሆነ ጠገዴ ጠለምት ሌሎችም ወረዳዎች በጎንደር ክፍለ ሀገር ውስጥ መሆናቸውን ገልጿል። ዋናው የድርጅቱ መርሃ ግብርም ይህን ይዞ የተጻፈ ነው። እርስዎም እንዳሉት ከፋኝ የተመሰረተው በወልቃይት ልጆች ሲሆን መስራቾች ሁሉም ይሙቱ ይኑሩ እኔ ባላውቅም ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ከፋኝ ኢትዮጵያ የጀግኖች ግንባር የተባለው ድርጅት መፈክር አንግበው የተነሱ ብዙ የጎንደር ልጆች ነበሩ። አቶ በሪሁን አስፋውና ሌሎች ብዙ የጎንደር ምሁራን ለማጠናከር ጥረት አድርገዋል። በተለይም ይህን ድርጅት ለማሳደግ በገንዛ ገንዘባቸው የለፉት ከፍተኛ ጥረት ያደረጉት ሊቅ ዶ/ር እንዱዓለም ሙላው፤ አይረሱም። ሌሎች ይረሱ እርሳቸው ግን ሊረሱ አይገባም። ሕይወታቸውን ሸጠው ሱዳን ድረስ ሕደው አምራኩባ ከተባለው የስደተኞች መንደር ከፋኝ ኢትዮጵያ የጀግኖች ግንባርን ለማጠናከር ያደረጉት ጥረት ሊረሳ አይችልም።

<u>የአርበኞች ድምጽ መጽሔት ነሐሴ 1991 ዓም ገጽ 28</u>
አረጀን መሰለኝ መረሳት ጀምረናል
የኛኑ መልሰው ሰዎች ይነግሩናል
ወልቃይት ጠገዴ ትግራይ እንደነበር
ተከዜ ተረስቶ የማይጠፋው ደንበር
ለካስ ክላሽን ነው ታሪክ የሚያጽፈው
ቱባው ጀሌ ሆኖ በዝምታ ሲያልፈው
የእግዜር ቁጣና ጊዜው ሲመቻቹ
ድል መንሣት ያለ ነው የላዩን የታቹ
ታዲያ ይህም ቢሆን ተራ ጽዋ አለና

የነገን ማሰብ ይሻል በጥሞና
ጸጸት ማስከተሉ የማይቀር ነውና" ይላል።

አቶ ጎሹ ገብሩ እርስዎ እንዳሉት የወያኔ ሴራ መኖሩ ባይካድም ጎንደሬው ግን ከፋኝ ኢትዮጵያን አንድነት ግንባር አባል የሆኑት ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ጎንደሬዎች ከጸሐፊ እስከ ገበሬ ከገበሬ እስከ ከያኒ ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት፤ የትግሬ ነው ብሎ ያመነ የለም። በተለይ የጎንደር ማህበር ተመስርቶ ሁኔታውን ሳልሰሙት እያሰማ ሕዝብ ማጠናከሩ አይካድም። የዚህ ማህበር አባላት በአሜሪካ ቅርንጫፍ ሲከፈት ጽሬት ቤት ወልቃይቴዎችን አቅፎና ደግፎ የያዘ መሆኑ አይዘነጋም። እርስዎ የጎንደር ልማት ማህበር እንደማይደግፉ ባውቅም ቅሉ ታሪኩ ሊካድ አይገባም። የጎንደር ልማት ማህበር በኮሎምቦስ አኳዮ ጠንካራ የነበረ በወልቃይት ልጆች ነው። ከብዙ በጥቂቱ ለምሳሌ እነዚህን እስኪ ልጥቀሳቸው።

1ኛ አቶ ላቀው ሕሩይ፤ 2ኛ አቶ ክንፌ ተስፋይ፤3ኛ አቶ ሲያምር ቸኮል፤ በሌሎች ክፍለ ዓለም ያሉትን የወልቃይት ልጆች መጥቀስ ይቻላል። በተለይም አውሮፓ ጀርመን ከሚኖሩት መካከል ወያኔን ባለመደገፋቸው በባንዶች የተደበደቡት አቶ ለፌቀ አብርሃም አንረሳቸውም። እርሳቸው "ወልቃይት የጎንደር ግዛት ነው። እኛም ጎንደሬዎች እንጂ ትግሬዎች አይደለነም "በማለታቸው ወያኔ አስደበደባቸው። የወልቃይት ልጆች እንኳን አገር ውስጥ ያሉት ቀርቶ ተሰደው በሔዱበት አገር ሁሉ ወያኔ እየተከታተለ እያስደበደባቸው መሆኑን ታሪክ ዘግቦታል። አንባቢያን ይታያችሁ የወልቃይት ልጆች ሱዳን ያሉት አልቀዋል። ወደዚህ ወደ አሜሪካ ስንመጣም ኮሎምቦስ አኳዮ የወልቃይት ልጆች ከአንድ አካባቢ ሰብስብ በማለታቸው ወያኔ ባንዶችን አስገብቶ ስለከፋፈላቸው አቶ አባይ መንግሥቱ ለብዙ ዓመታት ከኖሩበት ከተማ ለወቅ አኳዮ በመግባት የወያኔን ሴራ በማጋለጥና የወልቃይት ተወላጆች ወያኔን መደገፍ እንደሌለበት ጠንክረው እያተጉሉ ያሉ መሆናቸው ያስመሰግናቸዋል። ሕዝብን ማክበር ማለት እንደ አቶ አባይ መንግሥቱ እንጂ ውጭ ሁኖ መተቸት አስፈላጊ አልመሰለኝም። ወደ ኮሎምቦስ አኳዮ ስንመለስ ጎልመስ ያሉት ብቻ ሳይሆን ወጣቶች ሳይቀር ወያኔ በወልቃይት ሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን የጥፋት ዘመቻ እየተጋፈጡ ያሉ ብዙ ናቸው። አቶ ቻላቸው አባይ፤ እንዲሁም ገባ ወጣቱ አቶ በየነ ማማይ፤ ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል።

አቶ ጎሹ አስተውሉ እንጂ እንዴ ኧረ ስንት የጎንደር ልጆች በወልቃይት ምክንያት ደማቸው በወያኔ ፈሷልና አጥንታቸው ሽኽ ሁኖ ይወጋናል። ልንረሳቸው አይገባም። ከዚህ ላይ ጎንደሬዎች ወልቃይቴዎችን አቅፈው የያዙ መሆናቸውን አስመልክቶ ክፍል 4 ምዕራፍ 2 የተጻፈውን ሠነድ ሊመለከቱ ይችላሉ። እርስዎ የሚያነቡት ዲሞክራሲያን ብቻ በመሆን ሌሎችን ሠነዶች ስለማያዩ እንጂ የጎንደር ተወላጆች ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁኔታውን የሚያውቀው ያልጻፈ የለምና ወቀሳው ትክክል አይደለም። የእርስዎ አባት ክቡር ቀኛዝማች ገብሩ ገብረ መስቀል ስለ ወልቃይት ጎንደሬነት አስመልክቶ የተናገሩትን ከላይ የተጠቀሰውን ሊመለከቱ ይችላሉ። ወልቃይቴዎች ትግርኛ በመናገራቸው አልተናቁም።



ሕዳር 11 ቀን 1984 ዓ.ም

ር አቶ መለስ ዜናዊ
ትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ፕሬዚደንት
ስ አበባ

ር ፕሬዚደንት፦

ከአክሱም ምሥረታ በፊት ጀምሮ የትግራይና የጎንደር ሕዝብ በበር፤ ቋ፤በባሕል፤በጋብቻ፤በስም፤በሃይማኖት፤በአገር ፍቅር ስሜት፤ በጂኦግራፊና በኢኮኖሚ ተሳሳይ አነጋገር በታሪክ በኑሮና በባሕል ተግባሮ፤ የተከዜን ውሃ በጋራ እየጠጣ ድምበር ርስ ከጥንት የወረሰውን የአበውን ታሪክና ቅርስ አክብሮና ተደጋግፎ በመኖር ኢትዮጵያን ሺህ ዓመታት የታሪክ ባለሃብት ያደረገ፣ ሲቀር ቢውል ከአንድ ቅድመ አያት የሚቆጠር ወጥ ሕዝብ ነው።

በመሆኑም የጎንደርና የትግራይ ሕዝብ አንድ ብሔረሰብ እንጅ ሁለት ብሔረሰብ ቅበለ የትና መቆጠር አልነበረበትም። አንዱ በተመቸውና በተማለለት ጊዜም ሌላውን ታትና መደገፍ እንጅ ማሳፈርና መናቅ ባሕሉ ሆኖ አያውቅም።

በንቀትና በእብሪት አግዛዝ ምክንያት ግዙፍ ሠራዊት የነበረው የመንግሥቱ ኃይለ ም መንግሥት በቀላሉ ተንኮታኩቶ ሲወድቅ ታይቷል።

ትግራይና ጎንደር ባለፈው 17 ዓመታት የጨለማ ዘመን ውስጥ በሰው ሕይወት ትነትና በኢኮኖሚ ውድመት በኩል ያላቋረጠና ከፍተኛ የጋራ ጉዳት ደርሶባቸዋል። ው በመነሳታቸውና በመታገላቸው ኢትዮጵያን ከጭቆና አገዛዝ ነፃ አውጥተው አሁን ት የፖለቲካ ነፃነት /ዲሞክራሲ እና የኢኮኖሚ ተስፋ ጭላንጭል በር ላይ ሊያደርሷት ል።

የነዚህ ሕዝቦች የታሪክና የአንድነት ዕውነተኛ ገፅታ ይህ ሆኖ ሳለ ሰሞኑን ራሕ ኮንፈደንሻል " የሚባለው የ15ቀን መጽሔት ባወጣው ዕትም ከኢትዮጵያ ሽግግር ግሥት አገኘሁት ብሎ የሳለው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች የአስተዳደር ክልል ካርታ ለጎንደር ክና ቅርስ ቀዳሚ ባለቤት የሆኑትን ለም ቦታዎች ማለትም ሰቲት ሁመራን፤ ወልቃይትን፤ ዴንና ጠለምትን ከተፈጥሮና ከታሪክ አካላቸው ከጎንደር ለይቶ የተከዜን ድምበር በመጣስ ግራይ አስተዳደር አካል በማድረግ ቦታዎቹን የትግራይ ልማት ማኅበራ ሕዝቡን 2ኛ ደረጃ ግራይ ዜጋ ለማድረግ መታቀዱን ስለተረዳን በተቃጣብን የውርደት በትር እጅግ በጣም ንቀናል/ አዝነናል።

በተጨማሪም ቁምድርቡ የተወለደበትን ቋራን አፅሙ ያረፈበትን ማሕበረ ሥላሴን የሕንስ የተሰዋበትን መተማን እስመልከት ቀዳማውን አገር በሙሉ ዘሩንና ስሙን አካባቢው ስምቶት ለማያውቃው "ቤኒሻንጉል" ለተባለ ብሔር አካባቢ ለማድኖር ጓሣ ለመስጠት መታተላነ ከርታው አሳዶቿልባ ይህ ዕቅድ ከእማዴዳ እስከ መተማ ባለው ቀዳማ መሬት ላይ ከዘንተ ዓስም ጀምሮ ከብቱን እንደልቡ ከቦታ ቦታ እያዘዋወረ የሚያሰማራውን ደቸኛ የቋራ፤ የአለፋ፤ የጣቁስ ፤ የተንከል፤ የጭልጋ፤ የሜቀኛ የአዳኝ አገር ሕዝብ እስከ አሁን ፀንቶ የኖረለትን ሕጋዊ መብቱን የሚጋፋ ነው።

ከጥቂት ተናት በፊት የኢትዮጵያ ድምፅ ሬዲዮ የሽግግሩ መንግሥት ምክር ቤት የኢትዮጵያን አስተዳደር በ14 ክፍሉ አፅድቋል ብሎ ያስተላለፈው ዜና "አዋሪክ ክንፈዴንሽአ ከቀመው ክርጅ ጋር የተቀረፀ እንዳልሆነ ተሰፋ አለን። ከሆነ ግን ይህን ጉድፍ የሕግ መንግሥት አድዳቲ ጉባዔ ማቅረብ እነዚህን ወንድማማች የትግራይና የጎንደር ሕዝቦች ካሁን ጀምረው በደጅት እንዲሰባሰቡ መጋበዝ ነው ከሚባል በቀር ሌላ ምክንያትና ትርጉም አይኖረውም። በተጨማሪም በሽግግሩ መንግሥት ምክር ቤት ውስጥ የጎንደር ሕዝብ የመረጠ ተወካይ ባለመርሳ እኛ ይህን ለማበረዳት የምክርነውን ቁስሉንና ታሪኩን በገምባር የሚያስረዳ አላገኘም። በመሆኑም ከዛንተ ዓስም ጀምሮ የቆየውን መብታችንንና ታሪካችንን በሕዝብ የሚመረጥ ሕጋዊ ምክር ቤት እንደሚደንክብን እናምናለን።

ይህን ዕቅድ በተግባር ላይ ለማዋል ቢሞከር በጎሬኛነት በሚመጣውና በተገሬነት በሚመከተው ወንድማማች ሕዝብ መካከል የሚደርሰው ዕልቂት ተላልና ቁስሉ ለብዙ ትውልድ የማይሽር ስለሚሆን ይህ በከባድ መሥቀዕትነት የተገኘ ድልና የተሰፋ ጭላንጭል በዚህ ምክንያት እንዳይጠቀብንና እንዳይወድቅብን "በራሱ የተከፋፈለ ቤት አይጸናም" የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንዳይደርስብን ያስጋል።

ለ17 ዓመትት የተሰቃየው አልበቃው ብሎ ይህን ወንድማማች ሕዝብ ለእስር በርስ ግጭት መዳረግ በወርቅ ቀለም ሊጻፍ የሚገባውን ይህን ዓቢይ የትግራይ ፤ የጎንደርና የወሎ ሕዝብ የትግል ታሪክ ጊደትና የድል ውጤት የሀፍረት ማቅ መልበሻና የወደፊት ትውልዶች ዕርግማን ማድረግ እንዳይሆንብን ያሰባል።

የአካባቢውን ልማት በተመለከተ ለምሳሌ ሰቲት ሁመራን ብንጠቅስ ልማቱ በከፍተኛ ደረጃ ተንቀሳቅሶ በነበረበት ወቅት ከወልቃይትና ከጠገዴ ተወላጆች ቀጥሎ ከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚዎች የትግራይና የኤርትራ ወንድሞቻችን ነበሩ። በዚህ ሁኔታ የጎንደር ሕዝብ ይደሰት ይበረታታ ነበር እንጂ ምንም ዓይነት ቅሬታ ወይም ማጉረምረም እንዳልነበረበት በሁላችንም ልቦና ውስጥ እስካሁን የሚበራ ሕያው ትዝታ ነው።

ይህ የሚያንፀባርቀውም በጎንደር ሕዝብ ዓይን የትግራይና የኤርትራ ሕዝብ በድምበ ሳይገታ በአንድ ቤተሰብነት ተሳስሮ በክፉውና በበጎው ጊዜ አንተ ትብስ፤አንተ ትብስ ተባብሮ አብሮ የመኖር ዘላቂ ባህርይ ያለው አንድ ወጥ ሕዝብ መሆኑን ነው።

የክርታው ጉድፍ መውጣትና መሥራቤት አንድነታችንን ለሚጠሉ ወገኖች በጣም አስደሳች ወሬ ሁኖላቸዋል።

ስለዚህ ይህ አሳዛኝ ዕቅድ በፍጥነት ከልታረመ ወሬው ካሁን ጀምሮ በሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች መካከል በቀላሉና በጥቂት ትውልድ ሊታረም የማይችል ቅራኔና ዕልቂት በመጋበዝ የተሰበከውን የዲሞክራሲ ፋና በዓለም ፊት እንዳያጨልመው በመስጋት ይህን የተቃጣ የቅስ ስደፍ በወቅቱ የመቅጨኔት ኃላፊነት በክቡርነትዎ ላይ የተጣመጠ እንደመሆኑ የበኩላችንን በ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ሀሳብ በጎንደር ተወላጅነት ግዴታችን ተንሳስተንና ተገፋፍተን በትኅትና አቅርበናል።

ከማክበር ሰላምታና ከበጎ ምኞት ጋር

ዳኘው ወልደ ሥላሴ
ም.ሚ.ቁ. 70556
ስልክ ቁ. 201851
አዲስ አበባ

ፍትሕአየ አበጉ
ም.ሚ.ቁ. 26800
ስልክ ቁ. 513870
አዲስ አበባ

ግልባጭ ፡ - ለክቡር አቶ ታምራት ላይኔ
- ለኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ምክር ቤት



## ምዕራፍ 4

## ለወልቃይት የጎንደር ልጆች!

የሐዋርያት ሥራ 23.11 "በሁለተኛው ሌሊት ጌታ በአጠገቡ ቆሞ-ጳውሎስ ሆይ! በኢየሩሳሌም ስለ እኔ እንደ መሰከርክ እንዲሁ በሮሜም ትመሰክርልኝ ዘንድ ይገባሃልና አይዞህ አለው" ሲል ተጽፏል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጌታን መንግሥት እየመሰከረ ሲታሰር ሲደበደብ ሲሰደድ ኑሮ በመጨረሻው ራሱን ለጌታ ሲመሰክር አልፏል:: በሀገራችን ኢትዮጵያ በጎንደር ክፍለ ሀገር በወገራ አውራጃ የወልቃይት ተወላጆች "ጎንደሬዎች እንጂ ትግሬዎች አይደለነም" ሲሉ ታስረዋል! ተገድለዋል! ተሰደዋል! ዛሬ ድረስ ቀጥራቸው ይነስ እንጂ መሳሪያ አንስተው በመዋጋት ላይ ናቸው:: ከአገር ውጭ ያሉ እንዲሁ የወያኔን ሴራ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ሆነው በማጋለጥ ላይ ይገኛሉ:: ይህ ታሪክ ለተወላጆች ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ኢትዮጵያውያን አጠናካሪ መሆኑ ግልጽ ነው:: ወልቃይትን በተመለከተ የሩቁን ታሪክ ትተን የቅርቡን ታሪክ ብንጠቅስ ለኢትዮጵያ ታላቅ ተግባር የፈጸሙ ጀግኖች የወለደች ናት:: እኔ ስማቸውን የምጠቅሰው ግለሰቦች በታሪክ ተጽፈው ካገኘሁት መረጃና በዓይን አይቼ ምስክር የምሆንባቸውን ስም ብቻ ጠቀስኩ እንጂ ሌሎች ብዛት ያላቸው ታሪክ ሰሪዎች መኖራቸው አይዘነጋም:: ስለዚህ ሌሎችን ስማቸውን ያልጠቀስኩበት ካለማወቄ መሆኑን አንባቢያን እንድትረዱልኝ አሳስባለሁ:: ጣልያን አገራችንን በወረረችበት ወቅት ብዛት ያላቸው የወልቃይት ልጆች ለሀገር ክብር ሲሉ ደማቸውን አፍሰዋል:: አቶ ገሪማ ታፈረ የጎንደር ክፍለ ሀገር አርበኞች ፀረ ጣልያን ጦርነት ለማድረግ መጀመሪያ ጥይት በጣልያን ላይ የተኮሱትን መዝግበዋል::

ገሪማ ታፈረ ጎንደሬ በጋሻው በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 17 "በወልቃይት ፊታውራሪ መስፍን ረዳ+አባይ ወልደ ማርያም+መለሰ ኃይሉ÷ቸኮል ብቅአለ" የመጀመሪያውን ጥይት ተኳሽ ጀግኖች ሲመዘግቡ ዛሬ ወደ ትግሬ በክላሽ የተከለሉትን ወረዳዎች በጎንደር ውስጥ መሆናቸውን ያሳያል:: ለምሳሌ ከዚሁ መጽሐፍ ገጽ 17 "በጠገዴ+ በጠለሉ+ በወልቃይት በጠለምት" እያሉ ጽፈዋል:: በነዚህ ወረዳዎች ቅድሚያ በጣልያን ላይ ጠይት የተኮሱት ስማቸውን ከጠቀሷቸው ገጽ 17 "አዳነ መኮንን፤ዓለማየሁ ንጉሴ፤ገብረ ማርያም ፈንታ፤ አያናዬ ይልማ፤ ገብረ ሕይወት ሲሳይ፤ ቃታው ፏፏቴው፤ ተከሌ፤ መንግሥቱ፤ ነጋ አበራ፤ደበብ፤ እንዴት ሳርግህ፤ ጎሹ ለውጡ፤ መኮንን ነጋሽ፤ ደስታ ማሩ፤ በየነ አባ ጋራ፤ ፊታውራሪ መስፍን ረዳ፤ አባይ ወልደ ማርያም፤ መለሰ ኃይሉ፤ ቸኮል ብቅአለ፤ ቀኛ ጥሩነህ ፈለቀ፤ፊታውራሪ በላይ እረታ፤ ደስታ ይግዛው፤ ታፈረ ወርቁ፤ አምባው ፈለቀ፤ እየለ ተሰማ፤በላይ አረጋይ፤ ሺፈራው አምባው፤ ቸኮል ሺበሽ፤ ሞገስ አሊ" ሲሉ የመጀመሪያውን ጥይት ተኳሾች ጽፈዋል::

ግደይ ባሕር ሹም አሞራ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 189 "አባት አርበኞች የወልቃይት ታጋይ መሪዎች የሆኑ ፊታውራሪ የሽወንድም ናደው፤ፊታውራሪ ሰረበ ለማ ፤ልጅ ተድላ ወልደማርያም፤ ባላምባራስ በዛብህ አደመ ልጅ አስማማው መንግሥቱ" ሲሉ ጽፈዋል። የአቶ ግደይ ባህር ሹምን መጽሐፍ ጥቅስ የጠቀስኩት ከዚህ ላይ አቶ ገርማ ታፈረ ካልጠቀሱት አባት አርበኞች መካከል ለመጨመር በመፈለጌ ነው። የአቶ ግደይ፤ ትግራይ ይንቀሳቀስ የነበረውን ሲመሰረት ጠራናፊት ይባል የነበረውን ኋላ የኢዲዩ ጦር የሆነውን ሠራዊት ይዘው በወልቃይት ሲገቡ የተደረገላቸውን አቀባበል ሲጽፉ ከዘገቡት ስሞች መካከል ሲሆን ሌሎች ታላላቅ አርበኞች በወልቃይት ነበሩ። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ስሞች ጋር የተወሰኑ ተቀራራቢ የሆኑ ጨርሶም ሳይጠቀሱ የቀሩ ስሞች ልጨምር። በቅርቡ ከወጣ አንድ በራሪ ወረቀት የተገኘ ጹሑፍ ነው።

ከስሜን አሜሪካ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች ኢትዮጵያውያን የተሰጠ መግለጫ ከተባለው መጣጥፍ ገጽ 1 "የሩቁን ትተን የቅርቡን ብንመረምር እንኳ ፊታውራሪ መለሠ ኃይሉ፤ ፊታውራሪ ጎሳ፤ ፊታውራሪ ሠረበ ለማ፤ ፊታውራሪ የሽወንድም ናደው፤ ቀኛዝማች አያልነህ አዛገ፤ ፊታውራሪ ቢተው ገፉ፤ ግራዝማች ተገኘ ቢተው፤ ባሻይ መአዛ ፊታውራሪ መስፍን መ/ቶ ፍትሃለው ደምስስ ባላምባራስ በዛብህ አደመ፤ ቀኛዝማች ገብሩ፤ አዝማች ይርጋ ነጋሽ፤ ደጃች ደስታ ማሩ፤አቡሃይ አብተው፤ ሁሪ ጎላ እና በዚህ ውስጥ ስማቸውን አካተን ለማቅረብ ያልቻልን እጅግ በርካታ አገር ወዳዶችና ጀግኖች ሕዝባቸውን አስተባብረው ሲመሩና ሲያስተዳድሩ የኖሩባት የአገራችን ክፍል ለመሆኗ አጠያያቂ ሊሆን የሚችል አልነበረም" ሲሉ ጽፈዋል። በነገራችን ላይ ይህን ጥቅስ ከዚህ ለማስገባት የፈለኩት ስሞችን ለመጨመር ፈልጌ መሆኑን ለአንባቢያን ማሳሰብ እወዳለሁ። አገር ከወራሪ ነፃ ስትወጣ የሁመራ የእርሻ ልማት መስርተው ለኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ሲያስገባ የነበሩ ናቸው። በአጤውና በባለሥልጣኖቻቸው ድክመት ሁመራን ለሱዳን ለመስጠት ቃል በተገባበት ወቅት በልጅ ተድላ ወልደማርያም አስተባባሪነት ሱዳንን የመለሱ መሆኑ አይዘነጋም።

አሞራ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 99 "ያኔ ሁመራ ከተማ ከተያዘች በኋላ ሁለት መቶ ሰባ ሺህ ብር ከሁመራ ባንኮች የተገኘውን ገንዘብ የሁመራ ባንክ በእኛ በሁመራ ባላባቶችና አዝማቾች ብቻ የሚተዳደር ንብረት ነውና ከዚህ ቅስቅስ አይልም ብለው ለአሳደሙት ከእነ ደጃዝማች ታየ ጎላ አፈሙዝ ነጥቄ ገዳሪፍ ጽፈት ቤት ድረስ ወስጄ እንዳደረስኩ ሟቹ ዶ/ር ኻለቃ ተፈራ ባዘዘኝ መሰረት አድርሁሉት" ሲሉ ጽፈዋል። ከሁመራ ባንክ ኢዲዩ የወሰደውን ብር ብዛት በተመለከተ መላከ ሰላም ሲሳይ አየለ "ከሁመራ ባንክ የተወሰደው ከ3 ምልዮን ብር በላይ ሲሆን ጥጥና ሰሊጡ ሳይቀር ተጭኖ ሱዳን ገብቷል" ሲሉ ነግረውኛል። ደርግ ሁመራን ሰኔ 1969 ከያዘ ጀምሮ የወልቃይት ሕዝብ ሱዳን ተሻግሮ አምራኩባ ከሚባል ቦታ ላይ ከትሞ ሌሎችን የኢትዮጵያን ሕዝቦች እያስተናገደ የላከ ሕዝብ ነው። የወልቃይት ሕዝብ ለኢትዮጵያ አንድነት ትግል ሲሉ የተሰቃዩ ካህናት ሳይቀሩ ደክመዋል። መላከ ሰላም ሲሰይ አየለ፣ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። እኔ መጽሔቱን ማተም ሳቆም ሉስ አንጀለስን



ለቅቄ ሲያትል ስመጣ ሐምሌ 18 ቀን 1995 ዓም ቁጭ ብለን ስንጫወት ልብ የሚነካ ቃላት ተናገሩ።


"ለአገር ለዳር ደንበር የለፋው ልጅ ተድላ ወልደማርያምን ኢሕአፓ በ1979 ዓም ነሐሴ ቋራ ላይ ገደለው። እነ አቶ ጌታቸው ይርጋንና ሌሎችን ጀግኖች ወያኔ ከሱዳን መንግሥት ጋር በመስማማቱ አስረው ገደላቸው። እኔን ከባለቤቴ ጋር ለያይቶን ሳንተያይ ከዚህ ላዐም በሞት ተለየች። ልጆቼ ግማሾቹ አውስትራልያ ሲሰደዱ ግማሾችን የአሚሪካ መንግሥት አምጥቶልኝ ከኔ ጋር አሉ። ለወልቃይት ሕዝብ አሌንታ ይሆናሉ የተባሉት ታስረዋል። ሽሬ ላይ ከ1000 በላይ ታስረው ይሰቃያሉ። ከመያዝና ከሞት የተረፉት እንሆ ከፋኝ ብለው በዱር በገደል ይሰቃያሉ" ሲሉ አጫወቱኝ። እርሳቸው የነገሩኝ እነ አቶ ጌታቸው ይርጋንና ሌሎችን ከሱዳን አስሮ ለወያኔ የተሰጡ መሆናቸውን ነው። አቶ ግደይ ባህር ሹም አሞራ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 284 "ጌታቸው ይርጋና ሌሎችም አርበኞች የወልቃይትና የአርማጭሆ ደግኖች በሥዩም ትእዛዝ በሱዳን ታፍነው ጥይት እንዳይጮህ ሰው እንዳይሰማቸው ብዙም ሳይርቁ ዶካ ከተባለው ከተራራው በደርቡሾች ካራ ታርደው ከአንገታቸው ከበርሃ ጥለው ለአሞራ ሰጧቸው። በራስ ልጅ በሥዩም ሰው እየተሸጠ በጭካኔ ታርዶ ለአሞራ ተሰጠ። ልዑል ራስ መንገሻ ዘር ይፋረዳቸው በእሳቸው እንዳይበቃ ደግሞም በልጃቸው መሪያችን እያለ ታጥቆ እንዳልተዋጋ ከህደትና ትዕቢት ሆነ የሰው ዋጋ" ሲሉ ጽፈዋል። አቶ ግደይ የጻፉት በግጥም ሲሆን እኔ በስድ ንባብ ጽፌዋለሁ። ከላይ መላከ ሰላም ሲሳይ እንዳሉት ከሞት የተረፉት ዛሬም ቢሆን እየተዋጉ ናቸው።

እኔ የትጥቅ ትግል የምጠላ ብሆንም ታሪካቸውን መመዝገብ የግድ ይመስለኛል ሻዕቢያ ለኢትዮጵያ አጥፊ መሆኑ ባይካድም ለጊዜው መፈናፈኛ በማጣት ከሻዕቢያ ተጠግተው ወያኔን እየወጉ ያሉት የዱር ኢዲዮች የቅርቡ ከፋኞች የአሁኑ የአርበኞች ግንባር በሚል ስም የሚዋጉት የወልቃይት ልጆች ናቸው። የወልቃይት ልጆች ቀደም ሲል ዘመናዊ ተማሪዮች የኢሕአፓ በመሆን የሞቱና የቆሰሉ የተሰደዱ ናቸው። በጠቅላላው ታላላቅ የወልቃይት የሁመራ ሰዎች ለኢትዮጵያ አንድነት ታግለዋል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ጄኔራል አሰፋ አያናን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ከ1966 ዓም ወዲህ ደግሞ የተለያዩ ድርጅቶች ሲመሰረቱ ታግለዋል። በተለይም ኢዲዩን ለማሳደግ ያደረጉት ትግል መጠቀስ አለበት። በነገራችን ላይ ወይዘሪት አዜብ ወይም ለምለምን ያሳደጉ ወይዘሮ ማንሃሉሽ ጎላ ናቸው። ወይዘሮ ማንሃሉሽ ጎላ ከደርግ ጋር የተጣሉት በአረመኔነቱ ምክንያት ጥላቻ ስላደረባቸው ነው። የኢዲዩን መርሃ ግብር ይዘው እንደገና ጎንደር ገብተው ለሌሎች የተማሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለአቡነ እንድርያስ ሳይቀር አድለዋቸው በርሃ ገብተዋል። ወይዘሮ ማንሃሉሽ ጎላ ኢዲዩ ሲደክም ሱዳን ተሰደው የኖሩ ሲሆኑ ምግብ ቤት ከፍተው ማንኛውንም የሰው ልጅ እየረዱና እያገዙ የኖሩ ሲሆን ስደተኛው ሕዝብ" እማምዬ" ብሎ ይጠራቸው ነበር።

ከሱዳን ወደ አሜሪካ መጥተው ሉስ አንጀለስ አብረን እንኖር ነበር። አንድ ቀን ከቤታቸው ሀጂ ቡና አፍልተው እየጠጣን ሳለ ስልክ ተደወለ። ወይዘሮ ማንሃሉሽ ትግርኛ አቀላጥፈው ይናገራሉ ታዲያ ስልክ ወዳይዋ የሚያወሩት

በትግርኛ ሲሆን እርሳቸው የሚያናግሯቸው በአማርኛ ነው:: " ለምን በትግርኛ አትናገሪም" የሚል ጥያቄ ከወይዘሪት ለምለም ወይም አዜብ ሲቀርብላቸው መልሳቸው "ትግርኛ እኮ ወያኔ አስጠሉኝ ብለው መለሱላቸው:: እንደገና ወንድማቸው ደጃዝማች ታዋ ጎላ ሙተው ሐዘን ተቀምጠው ሳለ ወይዘሪት አዜብ ስልክ ደውለው እርሳቸው በትግርኛ ሲያወሩ ወይዘሮ ማንዛሉሽ፣ በአማርኛ ተናገሩ:: ወዲያው ደግሞ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ከትምጣቸው ስልኩን ተቀብለው በአማርኛ አናገሩአቸው::ወይዘሮ ማንዛሉሽ ወያኔን የሚደግፉ ወልቃይቴዎች በትግርኛ ሲያናግሯቸው እርሳቸው የሚመልሱት በአማርኛ ነው::

ወይዘሮ ማንዛሉሽ ጎላ አገራቸውን አጥብቀው ይወዳሉ:: በዚህ አረጋዊ እድሜያቸው ወያኔን አጥብቀው ይጠላሉ:: ወይዘሮ ማንዛሉሽ ለኢትዮጵያ አንድነት አቅዋም ያለውን ድርጅት ይደግፋሉ:: የጎሳና የጎጥ ድርጅት ደግሞ አጥብቀው ይጠላሉ:: እርሳቸው ወልቃይት ወደ ትግራይ መከለሉን አጥብቀው ይቃወማሉ:: ወያኔን የሚጠሉት ወልቃይት ወደ ትግራይ በመከለሉ ብቻ ሳይሆን የወያኔን አስተዳደር ለወደፊቱ የኢትዮጵያን አንድነት ይበትናል ብለው ይናገራሉ:: ወይዘሮ ማናዛሉሽ "ወያኔ በኢትዮጵያ እስካለ ድረስ በሕይወቴ ወደ ኢትዮጵያ አልሄድም ብለው ዛሬ ኮሉምበስ ኦኻዮ ይኖራሉ:: በቅርብ የማወቅ እድል አግኝቼ እርሳቸውን ጠቀስኩ እንጂ እጅግ ብዙ የወልቃይት ልጆች ወያኔን አይፈልጉም:: ለወደፊቱ ታሪካቸው ተለቅሞና ተበጥሮ እንደሚጻፍ አምናለሁ:: በእርግጥ አ|ወልቃይት ያልታተመ መጽሐፍ ብዙ የአካባቢውን ሰዎች ጠንካራ ጎንና ደካማ ጎን ዘግቦ የያዘው መጽሐፍ ለታሪክ ተመራማሪ በር ከፋች ይሆን የሊም እምነቴ የጠነከረ ነው::



ወይዘሮ ማንዛሉሽ ጎላ ጎሹ!



እያናእዝጊ <u>አ|ወልቃይት</u> ያልታተመ
"የፍየል ግልገሎች መንትያ ተወልደው
የናት ሆድ ኸርንኩርኩር አፈጣጠራቸው
የጧት ዕድላቸው አንደኛው ብራና ሌለኛው
ቅራና ሆነ እጣ ፈንታቸው
ብራናው በመቅደስ ሲከበር ሲወደስ
ቅራናው ካመድ ላይ እየሁ ሲልከሰከስ
አምላክ ወልደ እግዚአብሔር ለይኩን እንዳለው
ለካ እጣ ፈንታ ነው ክጥንት የበየነው
አንደኛው ቆራጥ ነው
ሁለተኛው ባንዳዳው" ሲሉ ጽፈዋል::

## ምዕራፍ 5

## ወያኔ ለሆናችሁ የወልቃይት ልጆች!

ወደዋናው የምዕራፉ መነሻ ወደሆነው ከመግባቴ በፊት ባንዳ ማለት ምን ማለት ነው? ባንዳ ጥሬ ቃሉ የሀገር ፍቅር የሌለው| ለወገኑ የማይቆረቆር! ሆዱ ከሞላ ለምንም ለማንም የማይቆጭ| በቅርሱና በታሪኩ የማይኮራ ለጥቅም ሲል ለመታዘዝ የተዘጋጀ|ክብርና ኩራት የማይሰማው ብሔራዊ ሥንደቅ ዓላማ የሌለው ከወላጆቹ የወረሰውን ሃይማኖት እንኳ የሚጠላ፣ በጠቅላላው ለሆዱ የሚታዘዝ ከውሻ የበሰ በሆዱ ያደረ ማለት ነው:: ወገኖቻቸው ለአገር አንድነት ሲታገሉ እነሱ ለጥቅማቸው የሚስዝበዝቡ ተፈልፍለዋል:: አገሪቱ ተቆርሳ ለጎረቤት አገር ስትሰጥ ዝም ብለዋል:: ባንዶች ከዚህ በፊት ሕዝባቸውንና አገራቸውን የካዱት ለጥቅም ሲሉ ነው:: ለጥቅም ያደረ ሰው ደግሞ ከአህያ ተለይቶ አይታይም:: በእርግጥ በአርያ ስላሴ የተፈጠረን ሰው ከአህያ ጋር ማመሳሰሉ ትክክል ባይሆንም በሆዳምነቱ ግን ትክክል ነው:: አህያ ጥሬ ከሰጧት ወደ ቤቷ አትሔድም:: ጥሬ ካገኘችበት ቤት አትለቅም ስለዚህ በሆድዋ ተገዛች ማለት ነው:: ባንዳ ወገኑን ገድሎ እንካ እንጀራ ብላ ሲባል የሚበላ ሰው "ለምን ገደልክ ሲባል መልሱ የእንጀራ ጉዳይ ነው" ይላል::

በጣሊያንኛው ሹምባሽ ቡልቃሽ እያሉ ይጠሯቸው ነበር:: እነ ደ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳን የኢትዮጵያን ሥንደቅ ዓላማ ረግጠው የሮማን ባንዴራ ያከበሩት ባንዶች ዛሬም የልጅ ልጆቻቸው ኩራት መስሉአቸው እንስተውታል ባንዳ የራሱ ሕዝብ እንዲሰለጥን አይፈልግም:: ቅኝ ግዛት ሊይዝ የመጣ መንግሥት ያንን ሕዝብ አደንቁሮ ለመያዝ ያስባል እንጂ እንዲሰለጥን እያስብለም በዚህ ምክንያት ጣልያን ኢትዮጵያውያን እንዳይማሩ ለማድረግ ጥረት ያደረገው በገንዘቡ በገዛቸው ባንዳ ባለሥልጣን ምክንያት ነበር:: ከዚህ

በላይ ስለ ባንዳ ሰፋ ብሎ የተብራራ መሆኑ እንዳለ ሁኖ በጎንደር ክፍለ ሀገር በወገራ አውራጃና ያሉ አንዳንዶቹ በሆዳቸው ተገዝተው "እኛ ትግሬዎች እንጂ ጎንደሬዎች አይደለንም" ያሉ ስላሉ እነዚህ ሰዎች ለምን ይህን አሉ ተብሎ ሲፈተሽ መልሱ ሁለት ሁኖ ይገኛል። 1ኛው ወያኔ ውሸ ይመስል አጥንት ዲቃሎችን የራሱ አድርጎ የያዛቸው ሲሆን 2ኛው ደግሞ ለሆዳቸው ያደሩ ባንዳ ግለሰቦች በመኖራቸው ነው።

የወያኔ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ የማይደግፈው መሆኑን አውቆ በገንዘብ ሕዝቡን ገዝቶታል። ለምሳሌ መስሪያ ቤት አንድ ሰራተኛ ሲቀጥር ጥያቄና መልስ ካደረገለት በኋላ ለሁለተኛ ግዜ ይጠራና "ባለህ የትምህርት ደረጃ ልንቀጥርህ ተዘጋጅተናል ነገር ግን ማሟላት ያለብህ ጉዳይ ያለ ያም የኮር አባል ካልሆንክ ሥራውን ልታገኘው አትችልም" ሲባል ቆራጥ ከሆነ ግለሰቡ "እኔ የምኮራው ባለኝ የስራ ልምድና በትምህርቴ እንጂ የኮር አባል አልሆንም" ብሎ ይወጣል። ሆዳም ከሆነ ግን ሥራውን ለመቀጠር ሲል "እሽ ይነገረኝ" ይላል። ይህ ግለሰብ የተማረ ከፍተኛ የሥራ ልምድ ቢኖረውም የኮር አባል በመሆኑ የተሥተካከለ ስራ ሊሰራ አይችልም።

ይህ ግለስብ እያወቀ እንዳላወቀ ሁና የአገር ጥቅም ሲጎዳ ይመለከታል። ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ወገኖቹ እየተበደሉ እያየ እንዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎአል። ለዚህም እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ይቅርና በስደት ያሉት የጥቅም ሰዎች የገዙት ቤት፤በነፃ የተሰጣቸው መሬት እንዳይነጠቁ ሲሉ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር ሲደፈር ዝም ማለትን መረጡ። ይህ የአገር ጠላት ከመሆን ተለይቶ አይታይም። በተለይ ይህን ምዕራፍ በተመለከተ ጠንከር ያለ ነቀፌታ የማቀርበው ከውጭ ወደ አገር በሚገባው ወገኔ ላይ ይሆናል። እኛ ዛሬ በአሜሪካን ሆነ በሌሎች አገሮች ያለን መኪና ጠብቀን ሆነ ሳንቲም ቆጥረን፤ ቤትና ግድግዳ አጥበን ሆነ ሳህን ወልውለን ታክሲ ነድተን ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ወገናችን የተሻለ መኖራችን አይዘነጋም። ይህን ደም ተፍተን የምናገኘው ዶላር ወደ ኢትዮጵያ ሲለወጥ ብዙ ነው። እኛ ስላለን ብቻ የሌላውን እድል መሻማታችን በታሪክ የሚያስወቅሰን ይሆናል። ይህ ብቻም አይደለም ወያኔም ለራሱ የሥነ መንግሥት የፖለቲካ ቁማር አድርጎ ስለወሰደው አንዳንድ ጥቅማጥቅም ማስገኛ መንገድ አድርጎ መመሪያ ሰጥቶበታል።

<u>ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ኤምባሲ፤ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት</u> የተሰኘው መረጃ ገጽ 3 "በውጭ አገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን በመረጡት አጀንዳና አደረጃጀት ዙሪያ እንዲሰባሰቡ በማድረግ በቀጣይነት ጥቅሞቻቸው እየተከበረ ተሳትፎዋቸው እንዲጠናከር ይደረጋል። በአገር ውስጥና በውጭ አገሮች የሚኖራቸው መብትና ጥቅም እንዲረጋገጥ ወደ አገር ቤት እንደልብ እንዲመላለሱ ንብረት በሕጋዊ መንገድ እንዲያስገቡና ቤት እንዲሰሩ፤ኢንቨስትር እንዲያደርጉ፤ገንዘብ በሕጋዊ መንገድ እንዲያስተላልፉና የባንክ ሂሳብ እንዲከፍቱ የትውልድ ኢትዮጵያዊ



መታወቂያ እንዲያገኙ ማገዝና በዚህ ዙሪያ የሚከሰቱ እንቅፋቶችን ከነሱ ጋር አብረን መንቀሳቀስ ይኖርብናል።"

"በዚህ ዕቅድ ውስጥ በውጭ የሚኖሩ የኮሚዮኒቲ አባላት በመረጡት አጀንዳና በፈለጉት አደረጃጀት ዙሪያ ተሳትፎዋቸውን ለማጠናከርና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሰፈሩ ጉዳዮች አተገባበር ቅደም ተከተል በአሁኑ ወቅት የጥቂት ተቃዋሚ ድርጅቶች አባላት  የተከተሉትን አፍራሽ አቅጣጫና በየአህጉሩ እየመሠረቱት ያለውን የግንኙነት መረብ (ኔት ወርክ)ሊመክትና በሂደትም ሊያከሽፍ በሚችል አግባብ መሆን ይገባቸዋል። ከዚህም እንፃር በዕቅዱ ውስጥ በውጭ አገሮችም ሆነ በአገር ውስጥ የሚከናወኑ ጥናቶች ለብቻቸው ተነጥለው የሚሰሩ ሳይሆን የኮሚኒቲ አባላትን እያሰባሰብን መረጃ እየሰጠንና እያደራጀን ጎን ለጎን የምንተገብረው ይሆናል" ይልና ገጽ 22 "ከውጭ አገር መጥተው በቀጥታም ሆነ በሽርሽርና በኢንቨስትመንት ላይ ለሚሠማሩና ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ብድር ለሚጠይቁ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ያለው አሠራር ተፈትሾ ቀልጣፋ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት" ይላል።

ወያኔ ከዚህ በላይ ያሰራጨውን ሰነድ ተጠቅሞበታል። ከውጭ አገር እድሉ ስላላቸው ብቻ ገብተው ነዋሪውን ሕዝብ የተጋፉ ብዙ ናቸው። አንዳንዶቹ የድሃ ቤት ፈርሶ መሬት ሲሰጡ በደስታ የተቀበሉት ብዙ ናቸው። ባንዳ ማለት ከዚህ የበለጠ ምንም ነገር የለም። ስለ ባንዳ ይህን ከጻፍኩ በኋላ ስለ ወልቃይት ልጆች ወያኔን ስለደገፉት አንዳንዶች ልጽፍ በማሰቤ ነው። ከላይ እንደጠቀስኩት ባንዳ ማለት ለሆዱ ያደረ ማለት ሲሆን ከወልቃይት ልጆች አንዳንድ ባንዳ የሆኑ አሉ። ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከቶጠረ ጀምሮ አምላክ ከልሎ የሰጠን የተፈጥሮ ደንበር ተከዜ መሆኑ እየታወቀ ባንዶች "እኛ ትግሬዎች እንጂ ጎንደሬ" አይደለነም አሉ። ስለዚህ ትግሬ ነን በማለታቸው የዘፈን ምሳሌም ከኪሮስ አለማየሁ ዘፈን ልጥቀስላቸው። ድምጻዊ የኪሮስ አለማየሁ፤ "አይበልናዶ" አሉ። ይህን አይበልናዶ የሚለውን የትግርኛ ቃል ወደ አማርኛ ስንቀይረው "አላልናችሁም" የሚል ነው። በትክክል ሳልረዳው ቀርቼ ከሆነ እናንተው ባንዶች አስተካክሉኝ። ጎንደሬ እንጂ ትግሬ አይደለነም ያሉት የወልቃይት ልጆች ደግሞ ወያኔን እናንተን ቀደም ጀምረው መክረው ነበር። "ተው ወያኔ አያዋጣችሁም ከወገኖቻችሁ ጋር አትጋጩ" በማለት ሲመክሩ መቆየታቸው አይዘነጋም። ለዚህም ነው አሁን "አላልናችሁም" የሚሉት። ወያኔም የነዚህን ለጥቅም ያደሩ መሆናቸውን በመገንዘብ ገንዘብ ለሚፈልገው ገንዘብ ሰጥቶ አንበሸበሻቸው። አሁንም እነዚህ ወገኖች ከስተታቸው ላይ ስህተት እየጨመሩ መሄድ እንጂ ትምህርት አልወሰዱም። ድምጽዊ ሻምበል በላይነህ ደግሞ "ከጥፋት ላይ ጥፋት፤ከስተትላይ ስተት" ብለዋል።

ግደይ ባሕር ሹም <u>አሞራ</u> በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ 202 "ታሪክ ይውቀሳቸው እንጂ አገር እንደያዙ አዲስ የትግራይ ክልል ብለው ደጋግመው በአወጡት የመልክዓ ምድር (ካርታ) ላይ ከአማራው ጋር ለማቀያየም፥ወልቃይትና ጠገዴን ተሻግሮ አዲስ ድንበር ከመጠየቅ ይልቅ ትናንት ደጃዝማች ገብረ

ሥላሴ በወጨፎ ጠመንጃ የሸጡትን አውጋሮ፣የእምኒሐጅር የጎሉጅ፣ የተሰነይንና የከሰላን በር የኤርትራ ክፍለ ሀገር ኩታ ገጠም ድንበር ለምን አሳወሱትም” ሲሉ ጽፈዋል:: ከፍ ተብሎ የተጠቀሰው የታሪክ ጥቅስ የሚያመለክተው ወያኔ ወልቃይትን ወደ ትግሬ ሲከልል ተባባሪ በመሆን አብረውት የቆሙ አንዳንድ የጥቅም ተቋዳሽ ግለሰቦች አልያም አጥንት የቆጠሩ በዘር ትግሬ ነን ያሉ ካልሆኑ በቀር ወልቃይት የትግሬ ነው ብለው ሊቆሙ አይችሉም::

ራስ መንገሻ ስዩም ዶቼ ቬሌ ጀርመን ራዲዮን ሰኔ 11 ቀን 1990 ዓም የአማርኛው ጣቢያ ተጠይቀው ሲመልሱ “ወልቃይት የትግሬ ሁኖ አያውቅም:: የጎንደር ነው” ሲሉ መልሰዋል:: ለትግሬ ከራስ መንገሻ የሚቀርብ የለም:: ምክንያቱም የክፍለ ሀገሩ ጠቅላይ ገዥ ሁነው የኖሩ ሲሆን የዛሬው የትግራይ ትውልድ ባያመሰግናቸውም ለትግራይ ግን ሰርተዋል:: የሚገርም ነገር ደግሞ ዛሬ ተኩራርተው የሕወሓት ታጋዮች ነበርን የሚሉት አንዳንድ የወልቃይት ልጆች ወልቃይት በአማራ የተወሰደብን መሬት ነው ብለው የትግራይን ሕዝብ ሲቀሰቅሱበት እየሰሙ ሕዝባቸውን ሲጨርሱት ተባባሪ መሆናቸው ነው::

ታጋይ ገሠሠ ረታ ታሪክ አጉዳፊው የአልባንያው ደብተራ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 71 “ በአማራ የተወሰዱብት እንደ ወልቃይት ጠገዴ ሁመራ አሉውሃና ሌሎች የትግራይ መሬቶች እናስመልሳለን” እያሉ ይቀሰቅሱ እንደነበር የሕወሓት ታጋይ ጽፈዋል:: የወልቃይት የጎንደር ልጆችን እንዚህን የአገር ወዳዶች ያስገደሉአቸው ባንዶች የወያኔ ቡችሎች ናቸው:: የወያኔ ቡችሎች ባንዶች በቁሳቁስ በቤትና በመሬት እየተገዙ ወገኖቻቸውን አስፈጅተዋል:: ዛሬ አገር ወዳዶችን ባንዶች ፈጅተዋቸው ባንዶች በዝተው በትግርኛ አልቅሱ÷ በትግርኛ ዝፈኑ እያሉ ያሲቃዩአቸዋል:: ባንዶች ሌላም ጉድ ሰርተዋል:: አገር ውስጥ ወልቃይት ንዋሪ የሆኑትን ወገኖቻቸውን በትግርኛ ካላለቀሳችሁ በትግርኛ ካልዘፈናችሁ ተብለው ትውልድ አገራቸውን ለወያኔ ሰቀው ወደ ጎንደር እንዲሰደዱ አድርገዋ:: ወያኔ ሁመራን ለትግሬ ሳይሆን ለሱዳን ሲሰጥባችሁ ከእንቅልፋችሁ አትነቁም? በጎንደርና በሌላው አውራጃዎች ቤትና ቁሳቁስ ተቀብላችሁ ከሆነ አገርን አሳልፎ ከመስጠት በታሪክ ተወቃሽ ከመሆን ለመዳን አታስቡም?የጎንደር ተወላጆች ሆነ ቁጥሩ ይነስ እንጂ ሌላው ኢትዮጵያውያን አይታችኋል ሁመራ የኢትዮጵያ እንጂ የሱዳን አይደለም” ብሎ ሲነሳ እንኳን አትባንኑም?

ማንም ሰው ሳይገባው በልጅነቱ አልያም ባጋጣሚ ሊሳሳት ይችላል:: ፍጹም በዚህ ምድር የለም:: ነገር ግን አዋቂ ማለት ከስተቱ መታረም ነው:: አባቶቻችን ሲተርቱ “አውቆ የስራ ነቢይ ነው! ሲመክሩት የሰማ አዋቂ ነው” ይላሉ ምክሩን አልሰማ ብላችሁ ቆይታችኋል:: ወያኔ የሚሰማው ካገኘ አንዱን ደብር ካንዱ ደብር ጋር ያለያያል:: ጠብ ለመፍጠር የማይፈነቅለው ድንጊያ የለም:: ለዚህም ዋቢ የሚሆን ወያኔ መንግሥት ከሆነ ጀምሮ ሕዝቡን ባንድነት ሊመራ ያወጣው መርሃ ግብር የለም:: የሚገርመው ነገር መሳሳት የጀመረ ሰው ከስህተቱ መማር አለመቻሉ ነው:: ትግሬዎች እንጂ ጎንደሬዎች አይደለንም



ብላችሁ ወገኖቻችሁ ሲጎዱ ዝም ብላችሁ ስታዩ መቆየታችሁ አይዘነጋም:: ታዲያ ከ17 ዓመታት እንቅል በኋላ መንቃታችሁ ባልከፋ ነገር ግን የባሰ ደግሞ ስህተት ላይ ወደቃችሁ:: በቅርቡ ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳን 10 ትዕዛዝ ያለው መግለጫ አውጥታችኋል::

ከሰሜን አሜሪካ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች ኢትዮጵያውያን የተሰጠ መግለጫ! ገጽ 2 አንቀጽ 1 “የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ እራሱን በራሱ የማስተዳደር ሕገ-መንግሥታዊ ጥያቄዎችን እንጠይቃለን” ይላል:: ራስ ገዝ አስተዳደር መብት የሚሰጠው እንዴት መሆን እንዳለበት የተረዳችሁት አልመሰለኝም:: ምናልባት ታይፕ ሲደረግ ሳይታረም ቀርቶ እንደሆን እንጅ ጥያቄያችሁ “የአገሩን ስርዶ በአገሩ በሬ መንደሩን ተወላጁ ያስተዳድር ለማለት ፈልጋችሁ ይሆናል እንጂ ካሳበዳችሁ በቀር ራስ ገዝ ብላችሁ የምትጠይቁ አይመስለኝም:: ወደ ኋላ መለስ ብለን የኢትዮጵያን አስተዳደር ስናጤን በደርግ ዘመነ መንግሥት ራስ ገዝ አስተዳደር የነበራቸው ትንሽ ክፍለ ሀገራት ነበሩ:: ጎንደር 7 አውራጃ 28 ወረዳና 119 ምክትል ወረዳ ያለው ክፍለ ሀገር እንኳ ራስ ገዝ አስተዳደር ይሰጠኝ ብሎ አልጠየቀም:: ሊጠይቅም አይችልም እንኳን ግማሽ አውራጃ:: ወይም ደግሞ ወያኔ አደናግሩ ብሎ ልኮአችሁ እንደሆን እንጂ ይህን ጥያቄ እንደማትጠይቁ ርግጠኛ ነኝ:: ከላይ እንዳልኩት አንድም ሲጻፍ ተሳስቷል አልያም ወያኔ አደናግሩ ብሎ አሂል:: ለኢትዮጵያ ውድቀት ራቢጣ ያመጣው ጣጣ አያልቅምና ምናልባቶ ራቢጣዎች ከትበዋችሁ ይሆን? ለነገሩ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስም ግማሽ ራቢጣ ስለሆኑ አንዳንዶች ወደ አዲስ አበባ ጎራ ስትሉ የርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊን ውሽማ አልያም ቅምጥ ወ/ት አዜብን ልትጠይቁ ገብታችሁ ሳለ ተከትባችሁ ይሆናል:: ይቅርታ ወ/ት አዜብ ማለቴ በኢትዮጵያ ፍትሃብሔር ህግ መሰረትባልና ሚስት አይባሉም::

መጽሐፈ ሕግጋት በተባለው መጽሐፍ ገጽ 1161 “ጋብቻ ባንድ የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹም ፊት ሊደረግ ይቻላል:: እንዲሁም ሕጉ በሁለቱ ወገኖች ሃይማኖት ወይም ባገር ልማድ መሠረት የሚደረጉትን ጋብቻዎች ያውቃል (ይቀበላል) ጋብቻ ለማድረግ አንድ ወንድና አንዲት ሴት በክብር መዝገብ ሹም ፊት ሲቀርቡና የሕዝብ የክብር መዝገብ ሹምም ፈቃዳቸውን ሲቀበላቸው ጋብቻ ተፈጸመ ይባላል” ይላል:: ስለዚህ በሃይማኖት አልያም ደግሞ በባህል ፊት ወይም ደግሞ በህግ ያልተጋቡ በመሆናቸው ባልና ሚስት አይባሉም:: 20 ልጅ ቢወልዱም 60 ዓመት አብረው ቢቀመጡም የሰሚኒያ ባልና ሚስት አይባሉም:: አንዳንዴ የጭን ገደር ይባላሉ:: አልያም ደግሞ ውሽማ ቅምጥ ተብለው ይጠራሉ:: በ1967 ዓም ጀብሃ የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ ምንሃጅር ላይ ጣላት:: ተብሎ ሁመራ ሲነገር ልጅ ተድላ ወልደማርያም የሁመራን ሕዝብ እየመሩ ኤርትራ መሬት ገብተው ጀብሃ የደበደቡ ስለመሆናቸው ታሪክ የመሰከረላቸው ጀግና ሲሆኑ እናንተ ግን የወልቃይት ጀግኖች ብላችሁ ስም ከዘረዘራችሁበት ላይ የእርሳቸው ስም ሳይጠቀስ ቀረ?::

ለካ ራቢጦችን ደብድበው ያባረሩ መሆናቸውን እናንተንም አስቆጥቶ ኑሮአል:: የራቢጣ ተማሪዮች ቀደም ትግሬ እንጂ ጎንደሬዎች አይደለንም ብላችሁ ሄዳች

ሁ:: ውሳችሁ አድራችሁ ደግሞ ወልቃይት ጠገዴ ራስ ገዝ ያስፈልገዋል ብሳችሁ ተነሳችሁ? ገጽ 3 ቁጥር 9 "በወልቃይት ጠገዴ የሚቋቋሙ የማኅበራዊ አገልግሎት ተቋማት ትምህርት ቤትና የመሳሰሉት ባሰያየምም ይሁን በይዘት በወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ታሪክና ማንነት ላይ ተመስርቶ እንዲሆን እንጠይቃለን" ይላል:: ተመልከቱ ቀደም ሲል ወያኔዎች ማንነታችሁን ሊያስክዱ ታሪካችሁን ሊያጠፉ ሕዝባችሁን ሊያስድዱና ሊያደህዩ መሆናቸውን አስመልክቶ ስትነገሩ መኖራችሁን አትረሱትም:: ያም የሚከፈተው ትምህርት ቤት ሆነ ተቋም በማታውቁት ስም በመሆኑ ዛሬ ራሳችሁ ከጥያቄያችሁ አንዱ አድርጋችሁ አቅርባችሁታል:: አበው ሲተርቱ "ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው" ይላሉ::

መከራ መከሮአችሁ ከሆነ የጀመራችሁትን ማጋለጥ ጨምሩበት የተፈጸመውን በደል ዘርዝራችሁ አቅርቡት:: ገጽ 1" ከአብራኩ የተፈጠሩ ተወላጆች ትምህርታቸውን ጨርሰውም እንኳ ያለ ሥራ እየተንከራተቱ ከሌሎች አካባቢዎች እየመጡ ሲቀጠሩ በግልጽ እያየን ነው" ይላል:: ከሕዝባችሁ ጋር አትቀያየሙ ብለው ወገኖቻችሁ መከረዋችሁ ነበር:: ነገር ግን እናንተ ማየት አልቻላችሁም ከ17 ዓመታት በኋላ ማየት ስትጀምሩ ከሌሎች ወገኖቻችሁ ጋር ሁናችሁ መነሳት ሲኖርባችሁ ብሳችሁ ቁጭ አላችሁ:: ከሌሎች አካባቢ እየመጡ ሲቀጠሩ የምትሉት ዛሬ ከወያኔ በቀር ከሌላ ክልል ሕዶ የሚሰራ ማንም የለም:: ስለዚህ ገልጻችሁ መነሳት አልፈለጋችሁም::

ለዚህም ነው ወይ ሀዱ
አልያም አታወናብዱ

የምለው:: የሚገርመው ነገር ደግሞ ይህ ሁሉ ሲሆን ሁመራ ለሱዳን ሲሰጥ መሆኑን ሳትገልጹ መቅረታችሁ ወያኔ አወናብዱ ብሎ የላካችሁ መሆናችሁን ያረጋግጣል:: ይህ ሁሉ ሕዝብ እያለቀና በመሬቱ ላይ ሱዳኖች አርሰው እየበሉና እየተዝናኑ ቅድሚያ መሬታችን ይከበር የሚል ጥያቄ እንኳን ሳይጠቀስ ይቅር? ይህስ እውነትም ወያኔ የላካችሁ ናችሁ:: ቀደም ሲል ባህርዳር ወይዘሪት ለምለም የርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ውሽማ ሰብሳቢነት የወልቃይትን ችግር ለመፍታት እንሞክር ተብሎ የታቀደ መሆኑ ሲታወቅ ኋላም በኮሎምቦስ አጓዮ በተደረገው ስብሰባ ከላይ የተነበበው አሳፋሪ መግለጫ ከወጣ በኋላ የተወሰኑ ሰዎች አዲስ አበባ ሕደው ስብሰባ ተደርጎ ያለ ምንም ስምምነት መበተኑ ታውቋል:: ስለዚህ በዚያም ሆነ በዚህ የወያኔ እጅ ያለበት ነው:: ወያኔ ከ300 ሺህ ሕዝብ በላይ ከትግራይ አምጥቶ ወልቃይት አስፍሯል:: የወልቃይት ነዋሪው ሕዝብ ወያኔን ያልደገፈ አገሩን እየለቀቀ ተሰዷል:: የቀሩት ቀንበር የጠበበባቸው መፈናፈኛ ያጡት ናቸው:: ይህ በዚህ እንዳለ እናንተ የራስ ገዝ መብት ይሰጠን ብላችሁ እንድትጠይቁ ተደረገ:: ከዚያ በኋላ ጨዋታው የወልቃይት ሕዝብ ይምረጥ ሲባል ነው:: ከትግራይ ወልቃይት መጥቶ የሰፈረው ሕዝብ "እኛ ወደ ትግራይ እንድንከለል እንወዳለን" ብለው እንዲመርጡ ሊደረግ ነው:: ከዚያ በኋላ የወልቃይት ሕዝብ ትግሬ እንጂ ጎንደሬ አይደለሁም ብሎ ድምጹ ሰጥቷል ሊባል የታቀደ መሆኑን ከውስጥ አወቅ ምንጮች መውጣት ጀምረዋል::



ገጽ 2 "በወልቃይት ጠገዴ የተሰማሩ ኢንቨስተሮች በዓመት ከመቶ ሺህ ብር በላይ ግብር እንዲከፍሉ ሲደረግ አርሶ አደር ገበሬው ከሃያ እስከ ሠላሳ ሺህ ብር በአማካይ ግብር የሚከፍልበት አካባቢ ነው:: ሌላው ቀርቶ በወልቃይት በመቶ ብር የምትከራይ ጎጆ 30% ለመንግሥት ገቢ የሚሆንበት ሲሆን በአንጻሩ በአዲስ አበባ ከተማ ግን ከሃያ ሺህ ብር በላይ ገቢ ያለው ነው 30% ለመንግሥት ገቢ የሚያደርገው" ሲሉ ጽፈዋል:: ድሮም የወልቃይት ተወላጆች የጎንደር ልጆች ተናግረው ነበር::

ተናግሬ ነበር ከአጥር ተንጠልጥዬ
ሕወሓት ገዳይ እንጂ ገዥ አይሆን ብዬብለዋል::

ይህ እንደሚሆን ቀደም ሲል ጀምሮ የታወቀ በመሆኑ የወልቃይት ሕዝብ ከስደት ላይ ስደት እየደረሰበት ነው:: አንዴ እሁድ ቀን መምህር አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሰብኩ ምዕመናኑ ጭብጨባ ጀምሮ ሞቅ ሳይል በመተው መምህር አባ "የምታጨበጭቡ ከሆነ አጨብጭቡ የምትተውት ከሆነ ተውት" ብለዋል:: ስለዚህ ወያኔን የማጋለጥ ተግባር ከሆነ ጠንክር በሉና ማጋለጥ ሞክሩ አለበለዚያ ግን አታወናብዱ ተመለሱና ወደ ወያኔ ሕዱ?

ገጽ 3 ከሌሎች አካባቢዎች እየመጡ አካባቢያችንን የሚያስተዳድሩ ወገኖች ባለፉት 17 ዓመታት እንደታየው ጥፋት እየፈጸሙ ሲነሱና በሕግ ሲጠየቁ የታየበት ሁኔታ መኖሩ እየታወቀ አሁንም በመንግሥት በኩል ይህ ከሌሎች አካባቢ የሚመጡ ሰዎችን በወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ላይ የመጫን አሰራር ስለቀጠለ ከአሁን በኋላ ይህን መሰሉ አሰራር እንዲቆም እንጠይቃለን" ይላል:: ለመሆኑ ዛሬ ነው እንዴ ያወቃችሁት? ወያኔ ከገባ ጀምሮ ሲፈጽመው የነበረ መሆኑ ተረሳ? ለመሆኑ በተወሰኑ ወረዳዎች ከመቼ ወዲህ ነው የራስ ገዝ ጥያቄ የሚሰጠው? ስለዚህ ገና ብዙ የሚፈተሽ ጉዳይ መኖሩ እንዳለ ሁኖ ትንሽ ጭላንጭል በማውጣታችሁ በእኔ በኩል መልካም ጅምር ሲሆን ለወደፊቱ ከመላው ጎንደር ሕዝብ ጋር አብረን እንራመድ ብላችሁ ትነሱ ይሆናል የሚል እምነቴ ነው:: ትግሬዎች እንጂ ጎንደሬዎች አይደለንም የምትሉ ካለፈው ስሁተታችሁ ታርማችሁ ከወገኖቻችሁ ጋር አብሮ ቀጣዩ የሁመራ መሬት ዓለም አቀፍ ደንበሩ እስኪታወቅ ብዙ ተግባር የሚጠበቅባችሁ ይመስለኛል::

ይህ በአንዳንድ ግለሰቦች የሚነሳው ጉዳይ እናንተ የወረዳው ልጆችን ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን ሌሎችን የክፍለ ሀገሩን ተወላጆች ብቻ ሳይሆን መላው የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተባብረን ዳር ደንበራችን እንዲከበር መታገል አማራጭ የሌላው ጉዳይ ነው:: ሰፈርተኝነት ለማንም አይጠቅምም:: ሠፈርተኝነት የሚያመጣው ለአካባቢው ድክመት እንጂ አንድነት አይሆንም:: የሰፈርተኝነት መነሰኤ ወደ ልዩነት ይመጣል:: ልዩነት ደግሞ ውሎ አድሮ አደገኛ ይሆናል:: ሰፈርተኝነት ወደ ግለልተኝነት ይመራል:: ግለልተኝነት ደግሞ ወደ ቡድን ይዞራል:: ቡድን ደግሞ ወደ ማህበር ይቀየራል፤ ማህበር ደግሞ ወደ ሥነ መንግሥት ፖለቲካ ድርጅትነት ይለወጣል::

“ማህበር” የሚለው ቃል እንዴት ሊመጣ ቻለ? ማህበር በምን ምክንያት ይመሰረታል? የልማት ማህበር ማለት ምንና ምንን ያጠቃልላል? የሚለውን በጽሞና መመልከት ያስፈልጋል። ማህበር የሚለውን ቅድሚያ በተረዳሁት መሰረት ላብራራ። ማህበር ማለት በአባቶቻችን ባህል መሰረት የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች በከተማ ሆነ በገጠር ሰብሰብ ብለው በወር አንድ ግዜ የሚገናኙበት ሲሆኑ ሃይማኖታዊ ነው። የወንዶች ማህበር በመላዕክታንና በቅዱሳን በጻድቃን ስም የሚመሰረት ማህበር አለ። አንዳንድ ማህበር ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ሲሆን ግዙፍና ጠንካራ ወሀራዊ መዋጮ ያለው ከመካከል አንዱ ቢቸገር አራጣ ብድር የሚበደርበት ገንዘብ ያለው ማህበር አለ። እንዲሁም እናቶቻችን የሴቶች ማህበር ሲኖራቸው በብዛት በቅድስት ማርያም በባዕታ በኪዳነ ምህረት ስም የጽዋ ማህበር ይጠጣሉ። ይህ ከዚህ በላይ የገለጽኩት በብዛት በገጠር ያለና ሃይማኖታዊ የጽዋ ማህበር ነው።

በዘመናዊው የማህበር አጠራር ከወሰድነው ደግሞ የአንድ አካባቢ ሕዝቦች በስራና በሌላ ምክንያት ከሩቅ አገር ይሄዱና ይኖራሉ። ታዲያ እነዚህ ሕዝቦች በተወሰነ ግዜ እየተገናኙ አብረው ይውላሉ። የበረቱ ከሆነ ራሳቸውን የሚረዱበት ወይም ደግሞ ለአካባቢያቸው ተባብረው አንድ ነገር ይመሰርታሉ የዚህ አይነት ማህበር አንዳንዴ ከፍና ዝቅ ሲል በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በርታና ደከም ሲል ሳለ አንዳንድ ተንኮለኞች እየገቡ የልማቱን ማህበር ለግላቸው መጠቀሚያ ለማድረግ ሲሉ ወደ ሥነ መንግሥት የፖለቲካ ድርጅት ተቀይሯል። የወያኔ ጥንስስ ቅድሚያ ተጋሩ ይባል የነበረው የልማት ማህበር ሲሆን ሜጫና ቱለማ ይባል የነበረው የልማት ማህበር ወደ ሥነ መንግሥት ፖለቲካ ተለውጦ እነማን የወሰደ መሆኑ አይዘነጋም። “ልማት ማህበር” የሚለው ትልቅ ነው። የአንድ ክፍለ ሀገር የልማት ማህበር ቢመሰረት ሊደገፍ የሚገባ ሲሆን የአንድ አውራጃና የአንድ ወረዳ የልማት ማህበር ፈጽሞ ሊመሰረትና ቢመሰረትም ሊሰራ አይችልም። ሊሰራ የሚገባው በአንድ ወረዳ ውስጥ ያሉ ልጆች በአካባቢያቸው የፈረሰ ቤተ ክርስቲያን ወይም ትምህርት ቤት ለማሰራት አጭር እቅድ ነድፈው ለአንድ መርሃ ግብር ሊያሰሩና ከሌላው ወገናቸው እርዳታም ሊጠይቁ ይችላሉ። በዚህ በኩል ብዙ ትብብሮች ሲደረጉ ተመልክቷል። የጎንደር የልማት ማህበር ከተመሰረተ ወዲህ የወያኔን እቅድ የማይደግፍ በመሆኑ ማለትም በጎንደር ክፍለ ሀገር 7 አውራጃ 28 ወረዳና 119 ምክትል ወረዳ መሆኑን በማስተማሩ ወልቃይት ጠገዴንና ከስሜን አውራጃ የወሰደውን ወረዳ ሕዝብ አልቀበለው በማለቱ አንድ አፍራሽ ሴራ ፈጸመ።

አቶ ክንፈ ገብረ መድህን ተወልደው ያደጉት ጎንደር ዳባት በመሆኑ የሚያውቃቸውን ልጆች አሜሪካ ሰላሉ ራሳቸው ዋሽንግተን ዲሲ መጥተው እንደሚደግፉአቸው ቃል ገብተው ከትልቁ የልማት ማህበር ሌላ ማህበር እንዲመሰረት ሆነ። በእርግጥ ይህ ራስ አገዝ ጎንደር ማህበር የወልቃይንት ወረዳ ልጆች የኳስ ጨዋታ ላይ ሳይጋብዛቸው ቀረ። ነገር ግን እነ አቶ በረከት ስሞዖን ለማበረታታት ሲጠሩአቸው ከአሜሪካ የሄዱት ልጆች በተለይም አቶ ሀቢቡ ታከለ “በጎንደር ሰላም ይውረድ ከተባለ ወልቃይትና ጠገዴን ሌሎችንም ወረዳዎች ወደ ነበሩበት መልሱ” ብለው በመናገራቸው የወያኔ ባለሥልጣኖች



ተበሳጭተው ወጥተዋል። ይህም ማህበር ደከም ማለት ሲጀምር ደግሞ የወልቃይት የልማት ማህበር ተብሎ ተመሰረተ ይህንም ማህበር ባንዶች ካልሆኑ ሌሎች የወልቃይት ልጆች ተቃውሞ አስሙበት የሚሰራ አይመስለኝም። አሁን በቅርቡ ደግሞ የትኛው አርማጭሆ እንደሆነ ባላውቅም የአርማችሆ የልማትና መደራጃ ማህበር ተመስርቷል። አርማጭሆ ሁለት ወረዳ ሲሆን ላይ አርማጭሆና ታች አርማጭሆ ይባላል።

እኔ የወረዳ የልማት ማህበር ሊመሰረት አይገባም ስላቸው፣ አንዳንዶች “አንተም ከመሰሎችህ ጋር ሁነው የወረዳ ማህበር ማቋቋም ትችላለል” ይሉኛል። በእኔ እምነት እንኳን በወረዳ በአውራጃ የሚቋቋም ማህበር ኤድስ ነው። ኤድስ በሽታ ሕዝብ መያዙ ብቻ ሳይሆን ታማሚውን ጤነኛው ፈርቶ አልቀርበው በማለቱ የኤድስ በሽተኞችን ማግለል እንደሌለብን የሃይማኖት አስተማሪዎች በማስተማር ላይ ናቸው። ልድገመውና እንኳን የወረዳ የአውራጃ የልማት ማሕበር ኤድስ ነው። ሕዝብ ከህዝብ የሚያለያይ በሽታ ነው። ወያኔ የሚፈልገው ይህን ነው። ታዲያ በዚህ አይነት የልማት ማህበር ሊመሰረት አይገባም። የጎንደር ሕዝብ አንድ ሁኖ ለልማት እንዲነሳ ስለማይፈልግ የጎንደር ማህበር ከተመሰረተ ጀምሮ እስከዛሬ አንድ ክፍል ቤት አልሰራም።

ወያኔ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን ሊሰጥ ሲነሳ በተለይ አርማጭሆ ሕዝብ መሬቴን አልሰጥም ብሎ ሲቃወም በውጭ ያሉትን የወረዳውን ልጆች ሰላይ በነበሩ ሰው የአርማጭሆ ልማትና ማደራጃ ማሕበር ብለው እንዲመሰርቱ አደረገ። እቅዱ ይህን የአርማጭሆ ልጆች ብቻቸውን ለልማት መደራጀታቸውን ሌላው የጎንደር ሕዝብ ሰምቶ አብሮ እንዳይቆም ለማድረግ አስቦ የጠነሰሰው ሲሆን በቅዱ መሰረት ተመሰረተ። ከዚያም ግማሾቹ የወያኔ ሰዎች እንዳሉበት ሲታወቅ እነሱን የተቃወሙት ለብቻቸው የአርማጭሆ መረዳጃ ማህበር ብለው መሰረቱ። አልሸሹም ዘወር አሉ ይሉሃል ይህ ነው። ይህን ማድረጉ ብቻ ሳይሆን የአርማጭሆ ሕዝብ መሬታችን ለሱዳን አንሰጥም ብሎ ሲዋጋ የወያኔን ጦር መርተው የመጡት የአርማጭሆ ተወላጅ ሻምበል ቻሌ አለሙ ሲሆኑ ከወገኖቻቸው ጋር ተታኩሰው ተገደሉ። ወያኔ የተወሰኑትን አሳምኖ ለሻምበል ቻሌ ቤተሰቦች መርጃ ገንዘብ እንዲዋጣ ልመና እንዲያደርጉ አሰማራ።

አሽብር ተቆርቋሪ የለለው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ አሁንም ቢሆን ወያኔ በቆፈራቸው ጉድጓዶች የቁም ሥቃይ እያየ የወገን ያለህ ይላል በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 10 “ መረዳጃ ማህበር አቋቁመው ሕብረተሰባቸውን ቢረዱ የሚያስመሰግን ሥራ ነበር። ነገር ግን ጠግቦ ሲተፋ ሲያድር ለነበረው አንዳንድ የወያኔ ቅጥረኛ ሻምበል/ሻለቃ ድጎማ ለማድረግ መራወጡ የሚያሳዝን ትዝብት ነው። መረዳት የነበረባቸውስ ከግብርናቸው ላይ እያሉ በነዚሕ ሻምበል/ሻለቃ በታዘዘው የአጋአዚ ጦር የተጨፈጨፉት የድሃው አርሶ አደር ቤተሰቦችን ነበር” ሲሉ የተሰማቸውን ጽፈዋል። ለምን ገንዘብ አስፈለገ ሲባሉ መልሳቸው “ለሻምበል ቻሌ አለሙ ቤተሰቦችን ልንረዳ ነው” ሲሉም መልሰዋል። ወያኔ

ከልቡ ካሰበ ለምን ለኮሎኔል ናቃቸው ጫቅሌ፤ቤተሰቦች ይረዱ ብሎ አልጠየቀም:: ኮሎኔል ናቃቸው በሻዕቢያና በወያኔ ጦርነት ወቅት ጀብድ ሰሩ::

ተወልደ ገ/ተንሳይ (ኮ/ል) ባድመ እንደምክንያት የፍፃሜው መባቻ በተባለው መጽሐፋቸው ኮሎኔል ናቃቸውን በተመለከተ ገጽ 389 "በ31ኛ ክጦር የብርጌድ አዛዥ በመሆን በሰኔ 3/90 ዓም አኩሪ ጀግንነት የፈፀሙ፤በዘመቻ ፀሃይ ግባት በደምበ ገዳሙ የነበረውን የጠላት ኃይል እየቀጠቀጡ ግርመ የደረሱ ጠላት በኛ ባድመ ብሎ በተነሳበት ወቅት እጅግ አኩሪ ጀግንነት የፈፀሙ በመጨረሻ ማጥቃት የ38ኛ ክ/ጦር አዛዥ በመሆን በሩባተጋሩ የነበረውን የጠላት ኃይል እየደመሰሱ ሽምበቆ የደረሱ ጀግና ወታደር አዛዥ ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህን ጀብድ ለሰራ ገንዘብ እናዋጣ ቢባል እንኳን ከውጭ ጠላት ጋር ነው የተዋጉት ይባል ነበር:: ሻምበል ቻሌ የወያኔ መሳሪያ ሁነው መቆየታቸው ብቻ ሳይሆን መሬት ለሱዳን ይሰጥ ብለው ሲዋጉ የሞቱ በመሆናቸው መዋጮ የሚያስፈልግ መስሎ አይታየኝም:: በነገራችን ላይ ቀደም አርማጭሆ ባንዳ አልነበረም:: የጣሊያን ባንዳ እገሌ ነው ተብሎ ስሙ ሲጠራ ሰምቼ አላውቅም:: ምነው የዛሬው ትውልድ የአባቶቹን ጋሻ ማንሳት አቃተው? አብረን ለደንበራችን ለመሬታችን እንቁም ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተነሳበት ወቅት በተወሰኑ የወያኔ ሰዎች ተሻጅለው በመጀመሪያ የአርማጭሆ ልማትና ማደራጃ ማህበር እንዲሁ ደግሞ የአርማጭሆ መረዳጃ ማህበር መመስረታቸው ለአርማጭሆ እየሰሩ ሳይሆን እየጎዱት መሆኑን አልተረዱም:: በጣም የሚገርመው ደግሞ በጎንደር ብቻ ሳይሆን በመላው አገሪቱ አንቱ ይባላሉ ተብሎ የሚገመቱ ከንዲህ ዓይነቱ ከወያኔ ሴራ ሳያስቡት መግባታቸው እኔን ብቻ ሳልሆን ብዙ ኢትዮጵያውያንን አስገርሟል::

ወያኔ ቅድሚያ ራስ አገዝ ጎንደር ኋላ ደግሞ የወልቃይት የልማት ማህበር፤ ቆይቶ ደግሞ የአርማጭሆ የልማትና ማደራጃ ማህበር በቅርቡ ደግሞ የአርማጭሆ የመረዳጃ ማህበር ብለው እንዲመሰርቱ መክሮ አስመስርቶአል:: እምነቴ ለአንድ ሀገርና ለአንድ ሃይማኖት ተቆርቋሪ ነኝ የሚል ማንኛውም ሰው ለጥቅም መገዛት የለበትም:: አንድ ሰው ለጥቅም ከተገዛ በዘመኑ ቋንቋ ባንዳ ሲባል በሃይማኖት መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ይሁዳ ይባላል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመረጣቸው ሐዋርያት መካከል ይሁዳ አንዱ ነበር:: ነገር ግን ጌታውን ለ30 ብር የሸጠ መሆኑ ታሪክ ይነግረናል:: ጌታችንን ካስገደለ በኋላ በድርጊቱ አፍሮ ገንዘቡንም ሳይበላው ራሱን ሰቅሎ የሞተ መሆኑን ነው መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳን የሚነግረን:: ስለዚህ አንድ ሰው ለጥቅም ካደረ ሃይማኖተኛ አይሆንም:: አንድ ሰው ለጥቅም ካደረ ለአገር ተቆርቋሪ ሊሆን አይችልም:: ባንዳና ይሁዳ ይባላል! ስለዚህ ሳታውቁት ተሳስታችሁ ከሆን መመለስ ይቻላል:: ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ም/13 ቁ 11 "ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፥እንደ ልጅም አስብ ነበር፥እንደ ልጅም እቆጥር ነበር፤ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ" ይላል:: በታሪክ ከመወቀስ ዳኑ::



# ክፍል አምስት

## ምዕራፍ 1

## ለወያኔ ደጋፊዎች የትግራይ ልጆች?

የወያኔ ደጋፊዎች ያልተረዳችሁት ታሪክ ቢኖር እናንተ ከጋምቤላ እስከ ሁመራ ላለው የኢትዮጵያ መሬት ዳር ደንበር ልትቆረቆሩ ቀርቶ ጠባብ ሁናችሁ በተደራጃችሁበት የክፍለ ሀገር መሬታችሁ እንኳን ተቆርቋሪ ልትሆኑ አልቻላችሁም:: ለዚህም ነው የእናንተው መሪ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ የትግራይን መሬት ለኤርትራ ሲሰጡባችሁ እንኳን ድምጻችሁ አልተሰማም:: እንዳንዶችስ በሚያሳፍር "መሬት ከኤርትራ ሄጉ ስለሰጠን የድጋፍ ሰልፍ ማድረግ አለብን" እያላችሁ ቅስቀሳ ስታደርጉ የነበራችሁ ናችሁ:: ዛሬ የደንበር ጉዳይ ሲነሳ "ይህ የቅንጅት ወሬ ነው" የሚሉት አባባል ከጠባብነት የተነሳ ነው::

ጌታቸው ወልዴ የአፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሐምሌ 1985 ዓም ገጽ 2 "ነፍጠኞች ሲፈራ ፍከራ ያበዛል ይባል የለ! መጽሔታችሁ በመሰረቱ የማን እንደሆነችና ምን እንደምትሰራ እናውቃታለን:: ዛሬ ይህች ኢትዮጵያ የምትባለው ፀሐይ ወጥቶሳት ብሔር ብሔረሰቦች በቋንቋቸውና በታሪካቸው ኮርተው እየኖሩ ነው:: እነ ነፍጠኞች ግን ዛሬ መሬትና ሰማይ ዞሮባቸዋል! የባሰም ሊዞርባቸው ነው:: ቁጭ ብሎ መብላት ምርጥ መዝናኛ ቦታ ከእንግዲህ አይገኝም:: ሚሊዮን ጊዜ ስለባንዴራ ቢያወሩ በክልል አስተዳደር ባንዴራውን ለማየት አንፈልግም:: ስለአንድነት ሺ ጊዜ ብትደነፉ ከነፍጠኞች የሚመጣ አንድነት እና ተለጣፊ ኢትዮጵያዊነት ገደል ይግባ:: ለአንተ ሥልጣን ሲሰጥህ ነበር ወይስ ለመሐይማን ፕሮፌሰሮች ከታሪክ የማትማሩ በዚህ ጦርነት ተነሳ ብላችሁ በመጽሔፍ ጉራ አታብዙ" ሲሉ ጽፈዋል:: በ1983 ዓም አካባቢ ጀምሮ ወያኔዎች ትቢታቸው እንኳን ሰው አምላክ የሚደፍራቸው አልመሰሉም:: ወያኔዎች መለስ ብለው የአክሱምን ሥርዕዎ መንግሥት አወዳደቅ ታሪክ ቢመረምሩ ኑሮ ይህን የመሰለ ትቢትና ጥላቻ ሊናገሩ አይችሉም ነበር:: ከአክሱም ሥርዕዎ መንግሥት ይቅርና እኛ ከተወለድን ወዲህ እንኳን የቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ገርስሶ ይጥላል ብሎ ያሰበ አልነበረም:: የእርሳቸው መንግሥትም ወደቀ የደርግ መንግሥትም እንዲሁ ወደቀ:: ያውም በኢትዮጵያዊነት ሽማ አሸብርቆ የነበረ መንግሥት ስለዚህ ወያኔዎች ለሁሉም ጊዜ አለውና ባትደነፉ መልካም ነው:: ለነገሩ የኢትዮጵያን ታሪክ በጥሞና ለመረመረው የትግራይ ልጆች ሥልጣን ሲይዙ ሁሌም ብጥብጥ መፍጠራቸው አይዘነጋም:: እኛ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ትግራይ ውስጥ የተፈፀመውን ሥህተት ብንጠቅም "ነፍጠኞች፤ትምኪተኞች" እንባላለን::

እስኪ ከትግራይ አብራክ የወጡት አቶ ግደይ ባህር ሽ-ም የጻፉትን መጽሐፍ ጥቅስ እንውሰድ፡፡

<u>*አሞራ*</u> *በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 231 "የዛሬውን ትውልድ አይበለውና ትግሬ ለእምነቱና ለጀግንነቱ ከአባቶቹ ጀምሮ በታሪክ ያስነገረ ነበር፡፡ እንደአሁኑ የትግሬ ወጣት ትውልድ ለጥፋት ለመገንጣጠል ሳይሆን ጥንት አባቶቹ ውሻ የጌታውን ንብረት አጥብቆ እንደሚጠብቅ ሁሉ የዱሮው የትግራይ አርበኛም አገሩን ኢትዮጵያን በሰሜን ቀይ ባሕር በጥቂት ባንዶች ተመርተው ከሚዝቱ ከባእዳን ወራሪ ኃይላት በፊታውራሪነት ጠብቆ እየተዋጋ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት አረበኞች ጋር በመተባበር አገራችን በወራሪ ሳትቆራረስ እንድንትዋል አስከብሮ ያቆየት አገር ለመሆንዋ በዘመኑና በጊዜው የነበሩ የታሪክ ጸሐፊዎች ነግረውናል፡፡ ታዲያ ወደ ባህሪው ልመለስና ልግለጽላችሁ የምፈልገው ትግሬዎች በአርበኝነት ድል ሲኖራቸው ለስምምነት በጠባይ ከፉኛ ነሳቸው፡፡ እንደ ውሻ እርስ በእርስ መናከስ ማን ችሎአቸው፡፡ ቅናት ምቀጥነት ጭቅጭቅ ተዘርታ የበቀለችው ከትግሬ ጓሮ ነው ብል ፍጹም አልተሳሳትኩም፡፡ የትግራይን ምድር ዙረው ቢምሱት የትም ቦታ የንትርከና የእልክ ሥር አይጠፋም ማለት እችላለሁ፡፡"*

*"እርስ በእርሱ የሚናከስ ጎሳ (ዘር)ለመሆኑ ዘመነ ነገሥታትና ዘመነ መሳፍንት ጓላም ዘመነ ነገሥታት ታሪክ ላይ በጥሞና ብትመለከቱት የትግራይ መሳፍንትና ነገሥታት ተስማምተው የኖሩበት ዘመን ግልጽ አይደለም፡፡ ለረጅም ዘመናት ከአክሱም ሥልጣኔ ጀምሮ ያለፉት የትግራይ ነገሥታትና መሳፍንት አብዛኛዎቹ ሥልጣናቸው በኃይልና በጦርነት የተቀሙ ነበሩ፡፡ የእያንዳንዱ ንጉሥ ሠራዊት ለንጉሡ በጣም ታማኝ ሲሆን ነገሥታቱ ወይም መሳፍንቱ ግን ተስማምተውና ሥልጣኑን ተከፋፍለው በሰላም መኖር አይወዱም አልለመደባቸውም ነበር፡፡ ከአክሱም ሥልጣኔ ዘመን ጀምሮ አብዛኛዎቹ አንዱ አንዱን እየደቆሰ ንጉሥነትን ይቀማ ነበር፡፡ አያሌ ታሪክ ጸሐፊዎች ጠቅሰውታል፡፡ ይህ የአሁኑ የትግራይ ትውልድም ድሮ ከአባቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ በወረሰው ባህሪው መሠረት እርስ በእርሱ ተስማምቶና ተማምኖ መኖር አይችልም፡፡ እያንዳንዱ አንዱ በአንዱ ለማጥፋት ተንኮል እየሰማ ከእገሌ ብቻ መሆን አለብኝ የሚል ትዕቢትና ትምክህት ወጥሮት የወገኑን ድርሻ ነጥቆ ለብቻው አትረፍርፎ ለማከበት ወገኑን ለማጥፋት በግልጽና በእጅ አዙር ሲተነኩልና ሲተናነቅ ይታያል" ሲሉ ጽፈዋል፡፡*

ወያኔዎች እናንተ ለሕዝብም ለአገርም የምትበጁ አይደላችሁም፡፡ ኢትዮጵያን ልትሸጡ የተነሳችሁ ናችሁ፡፡ አንዱን ዘር ካንዱ ጋር እያጋጫችሁ በማለያየት የኢትዮጵያን ሕዝብ አብሮ ለጋራ ጥቅሙ እንዳይቆም እያደረጋችሁ ነው፡፡ በእናንተ እምነት ከትግራይ በስተረቅ በሌሎች ክፍለ ሀገራት ችግር እንዲፈጠር መርዝ በመርጨት ላይ ናችሁ፡፡ ይህንም የምታደርጉት የእናንተ ፍላጎት ብቻ እንዲሟላ ስለምታስቡ ነው፡፡ ሻዕቢያ አይደር ትምህርት ቤት ሕጻናትን ፈጅቶ የትግራይ ወረዳዎችን ሲይዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅጽበት አብሮአችሁ ቁሞ አቅም ያለው ዘምቶ አቅም የሌለው በጸሎቱ የልጆች ደም ተመልሶ የተወሰደ



መሬት ተመልሶ ገብቶአል፡፡ ነገር ግን ከ70 እስከ መቶ ሺህ ሕዝብ ያለቀበትን መሬት የሰጠ ገዥያችሁ ነው፡፡ በሂጉ የተወሰደ መሬት ሕጋዊ አይደለም ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲጮህ እናንተ ድምጻችሁ ጠፋ? ከአገር ውስጥ ያሉት እንዳንድ ችግር ኑሮባቸው ይሆናል፡፡ ነገር ግን ውጭ አገር ያላችሁ የወያኔ አባላት ምን ዝም አሰኛችሁ? ለወደፊቱ የወሰን ጉዳይ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ክፍለ ሀገር ይልቅ በትግራይ ላይ ያነጣጠረ ይሆናል፡፡ በተለይም በርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ አቅዋም ኢትዮጵያን ማድቀቅ ሲሆን የእርሳቸው አቅዋም ትግራይን ያለሙ ይመስለናል፡፡ ይህ በጥሞና ታቅዶ የተሰራ መሆኑን የወያኔ ደጋፊዎች አልተረዱትም፡፡ እነሱ የሚያዩት በተለያዩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በስልጣን ላይ መቀመጣቸውን ልማቱ ከሌላው ክፍለ ሀገር ይልቅ ትግራይ መልማቱን ሌላውንም አንዳንዱን ቁሳቁስ በመመልከት ሲሆን አርቀው አላሰቡም፡፡

<u>ለኢ.ፌ.ዳ.ሪ.ኤምባሲ፣ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ቆንስላ ጀኔራል ጽ/ቤት</u> የተሰኘው መጣጥፍ ገጽ 7 "ዋና ዋና ተግባራት የአክራሪውን የተቃዋሚ ጎራ ለማዳከም እንረዳ በውጭ አገሮች ያሉ ቀንደኛ አስተባባሪ የሆኑ አባላትን በመለየት ዝርዝራቸውን ለዋናው መ/ቤት ማስተላለፍ፡ ከዋናው መ/ቤት በሚደርሳቸው የእነዚህ አክራሪዎች የተለያየ መረጃ /በዘር ማጥፋት ወንጀል በገንዘብ ዝርፊያ በመንግሥትና በሕዝብ የተሰጣቸውን ኃላፊነት አላግባብ ተጠቅመው የኮበለሉትን ወዘተ.. ለአብዛኛው የኮሚኒቲ አባላት ማጋለጥ የሚያስችል የሕዝብ ግንኙነት ሥራ መሥራት፡፡ከእነዚህ መካከል በዘር ማጥፋትና የሕዝብና የመንግሥት ንብረት በመዝረፍ የተሳተፉትን መሪ-ተዋንያን በሕግ ለመጠቀም የሚያስችል የተጠናከረ እንቅስቃሴ በማካሄድ ተጠያቂዎቹን ለፍርድ ማቅረብ፡፡ አክራሪ ተቃዋሚዎች ከሚኖሩባቸው አገሮች መንግሥታት ጋር በድፕሎማሲያዊ መስመር በመገናኘት የአገራችንን ሰላምና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ እንቅስቃሴዎችን በየአገሮቻቸው እንዲካሄዱ የተለያዩ የሕግ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ነጥቦችን በማንሳት በጋራ መተባበር የሚቻልባቸውን ሁኔታዎችን መፍጠር ከዚህም አንጻር የአክራሪ ተቃዋሚዎቹ መሪዎች የሚኖሩባቸውን አገሮች ዜግነት የወሰዱ ስለሆነ በእኛ አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደሌለባቸው የእነሱንም ሆነ የአገራችንን ሕጎች በመጥቀስ ማስረዳት አክራሪ ተቃዋሚዎቹ ሕገ-ወጥ የማስፈራሪያ መንገዶችን በመጠቀም ንፁሃን ዜጎች በሰላም የሚኖሩባትንና የፈለጉትን የፖለቲካ አቋም እንዳያራምዱ ተፅዕኖ የሚያደርጉና የአገሮቹን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች የሚጥሱ መሆናቸውን ማሳየት" ይላል፡፡

ከዚህ በላይ የተጻፈው መረጃ የሚያመለክተው እያንዳንዱ ሰው ባለው አገር ፍቅር ተጠቅሞ ለትውልድ አገሩ ለማሰብ ሲነሳ በውጭ አገር ያለው የወያኔ አባላት ያልተባለና ያልሆነ ነገር እየሰሩ ይወነጅላሉ ማለት ነው፡፡ ለእነሱ መመሪያ የሰጣቸው ከአዲስ አበባ መሆኑን ከላይ የተነበበውን መመልከት ይቻላል፡፡ ውጭ አገር ያለውን ኢትዮጵያዊ በዚህ መልክ ካስቃዩት አገር ቤት ያለውን ኢትዮጵያዊማ ያለበት ችግር ማን ቆጥሮ ይዘልቀዋል፡፡ ስለዚህ በውጭ አገር ያለው ኢትዮጵያዊ በአገር ቤት ወያኔ የሚያደርገውን ድርጊት ትክክል

አይደለም ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ አድርጎ ድምጹን ያሰማ በወያኔዎች ሰላይነት ይሰቃያል ማለት ነው። ወያኔዎች ሕግና ሥርዓት እናስከብራለን ብለው ያላዝናሉ። ደግሞም በዓለም አቀፍ ሕግ እንመራለን ብለውም ይጮኻሉ። አንድ ወንጀለኛ ሰው በሰራው ወንጀል ተከሶ ይታሰራል እንጂ ንብረቱ ይዘረፍበታል የሚል ሕግ የለም።

ሻለቃ መላኩ ተፈራ ኢትኦጵ መጽሔት ቅጽ ቁጥር 7 ታሕሳስ 1992 ዓም ገጽ 40 "ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም ወያኔ-ሻዕቢያ/ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር በመኖሪያ ቤቴ በቀጠና 5 ከፍተኛ 9 ቀበሌ 09 የቤት ቁጥር 213 የነበረኝ ንብረቴ በሙሉ በወያኔ-ሻዕቢያ/ ኢሕአዴግ ከመዘረፉም በላይ ከጄቡቲ ስመለስ የነበረኝ ንብረትም የማዕከላዊ ምርመራ ማስተባበሪያ መምሪያና የልዩ አቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ባለስልጣናት አቶ ዘርዓይ ይህደጎ፣ ሻለቃ ግበው መለስና ግብረአበሮቻቸው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 422/ለን በመተላለፍ ቀምተውኛል። ያለ ሕግ በጉልበት የተወሰደብኝ ንብረቴ በሙሉ እንዲመለስልኝ 5 ጊዜ ለጻፍኩት ማመልከቻ ከባለስልጣናቱ የተሰጠኝ መልስ ንብረቱ ሳይሆን እንደተለመደው ተራ ስድብ ዛቻና ማስፈራሪያ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ጥቅስ ሁለት ትምህርት ይሰጠናል።

1ኛ ይዘገያል እንጂ የሰው ልጅ ፍርዱን የሚያገኝ መሆኑን ነው። ሻለቃ መላኩ ተፈራ በሕዝብ ላይ ያደረጉት ግፍ እርሳቸው እንዲሁ እስረኛ መሆናቸው። የእርሳቸው ስልጣን የማይገረሰስ መስሎአቸው ነበር ያን ሁሉ በደል በሰው ላይ ሲያደርሱ ነበሩ። 2ኛ ወያኔዎች የኢትዮጵያውያንን ንብረት መዝረፋቸው ነው። ሻለቃ መላኩ አንዴ ታስሬአለሁ ብለው በመጻፋቸው እንጂ ብዙ ሕዝቦች እንገደላለን እያሉ ያላወጡት ቤቱ ንብረቱ በወያኔ የተዘረፉ ብዙ ናቸው። በውጭ የቀሩ አዛውንት የነገሩኝ "ከአዲስ አበባ ለስራ ጉዳይ ውጭ ስወጣ ቤቴን ለአንድ ዳኛ በ1000 ብር አከራይቸው መጣሁ። ብዙም ሳይቆይ ወያኔ ገባ። ወያኔዎች ወዲያውኑ ቤቴን ወርሰው ለዚያው ዳኛ በ150 ብር አከራዩት። በወኪል ክስ ስመሰርት ክሱን የሚያየው ሰው ያ ዳኛ ሲሆን የራሱን ቤት ሰርቶ አከራይቶ በ150 ብር ክራይ ይኖራል። ክሱ 12 ዓመት እስካሁን አልተፈረደም" አሉ። ወያኔዎች የመንግሥት የሆነውን ንብረት ሳይሆን የተራ ዜጎችን ንብረት ሳይቀር ወርሰዋል።

በቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የነበሩ የተወሰኑ ግለሰቦች ያከማቹትን ንብረት ደርግ ወረሰ። ይህን ከግለሰቦች የወረሰውን ንብረት የመንግሥት ንብረት አድርጎ ይዞት ነበር። ወያኔ ይህን የመንግሥት ንብረት ሽጠ ብሩን ከራሱ ካዝና አስገብቶ በተለያዩ የወያኔ አባላት ስም አከፋፍሎ ትግራይ ውስጥ ልማት እንዲለማ አድርጓል። መፈክራቸው "ትግራይ እስክትለማ ሌላው አገር ይድማ" ብለው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሳያፍሩ አወጡት። እናደርጋለን ብለው ባሰቡት መሰረት አደረጉ በመላ ኢትዮጵያ የልማት አውታር ለመዘርጋት ታቅዶአል በማለት ቅስቀሳውን ሲያናፉት ቆዩ እውነቱ ግን ልማት ሲለማ የታቀደው ትግራይ ውስጥ ብቻ መሆኑ ከዚህ ዝቅ ብሎ ያለውን ሠንድ ያመለክታል።



ወልዱ ሃይሌ ሩሕ መጽሔት 1ኛ ዓመት ቁ 1 ጥቅምት 1993 ዓም ገጽ 10 "የመሪዎች የልማት ራዕይ ለአንድ አገር ልማትና ብልጽግና የወሳኝነት ድርሻ አለው። እይታው ከአድማስ አድማስ የሰፋ መሪ ማግኘት እንደመታደል ይቆጠራል። ሰላምና መረጋጋትም ይኖራል። ራዕይ በዘርና በተወለደበት አካባቢ ብቻ የተሸበበ መሪ ለተወለደበት አካባቢም ሆነ ለአገሩ ጠንት ከመሆን ሌላ ምንም ፋይዳ ያለው ተግባር ሳይከናወን ያልፋል። ፕሬስና ኢንፎርሜሽን መምሪያ አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ ምን ዓይነት ኢንቨስትመንት በየትኛው ክልል ማካሄድ እንደሚቻል የሚጠቁም ነው የተባለ ብሮሸር ተዘጋጅቷል። በብሮሽሩ ውስጥ እየደተጠቆመው ከሆነ ከሐምሌ 1984 እስከ ጥቅምት 30/1992 ዓም ባሉት ጊዜያት 41.54 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያላቸው 5061 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደዋል። እስከ መጋቢት 30/1991 ባሉት ጊዜያት ፈቃድ አግኝተው ስራ የጀመሩት 1469 ፕሮጀክቶች ብቻ መሆናቸው ተገልጿል። የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰዱት ባለሃብቶች መካከል 3/4ኛ የሚሆኑት ፕሮጀክቶቻቸውን በስራ ላይ ለማዋል ያልቻሉበትን ምክንያት በዚህ ጽሑፍ በዝርዝር ለማቅረብ ያዳግታል" ሲሉ ከጻፉ በኋላ ገጽ 11 ከዚህ የሚከተለውን ሠንድ ለንባብ አቅርበዋል።

| ክልል | የሕዝብ ብዛት | የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተመዘገበ ካፒታል | የሥራ ፈቃድ ያገኙ ባለሀብቶች | ሥራ የጀመሩ ፕሮጀክቶች |
|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 3,593,000 | 4.24 ቢሊዮን ብር | 401 | 279 |
| አፋር | 1,185,000 | 572.70 ሚሊዮን ብር | 82 | - |
| አማራ | 15,860,000 | 3.106 ቢሊዮን ብር | 399 | 124 |
| ኦሮሚያ | 21,694,000 | 6.48 ቢሊዮን ብር | 1149 | 399 |
| ሶማሌ | 3,,602,000 | 144.97 ሚሊዮን ብር | 19 | 7 |
| ቤኒሻንጉል | 523,000 | 331.78 ሚኒዮን ብር | 44 | 21 |
| ደቡብ ሕዝቦች | 12,132,000 | 2.13 ቢሊዮን ብር | 624 | 344 |
| ጋምቤላ | 206,000 | 56.53 ሚሊዮን ብር | 15 | - |
| ሐረሪ | 154,000 | 441.01 ሚሊዮን ብር | 1973 | 255 |
| አዲስ አበባ | 2,424,000 | 21.47 ቢሊዮን ብር | 136 | 13 |
| ድሬደዋ | - | 35.38 ሚሊዮን ብር | 219 | 19 |
| ድምር | - | 41.54 ቢሊዮን ብር | 5061 | 1469 |

ከዚህ በታች ደግሞ የማቀርበው ዝርዝር በኢትዮጵያ ውስጥ የአንድ ጎሳ መንግስት የተመሰረተ መሆኑን ያሳያል። የአንድ አገር መከላከያ ኃይል በአንድ ጎሳ ብቻ ተይዞ እንዴት ሕዝብ ሰላም ይኖራል።

ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ነሐሴ 1996 ዓም ገጽ 23 "የችግራችን አንዱ መፍትሔ ከእንግዲህ በግልጽ መነጋገር ነው ብለናል። በአሁኑ ጊዜ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ70 ሚሊዮን በላይ ነው:: ከዚህ ውስጥ ሕወሓት እወክለዋለሁ የሚለውን ከ3.4 ሚሊዮን የሚሆን የትግራይን ሕዝብ ነው:: ሕወሓት ማለትም የትግራይ ሕዝብ የነፃነት ንቅናቄ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት አስኳል ነው:: ሕወሓት የትግራይ ሕዝብ ብቸኛ ወኪል ስለመሆኑ እርግጠኛ ባንሆንም ዛሬ በአገራችን የሚሰራው የተሳሳተ ተግባር ግን የትግራይ ሕዝብ ፍላጎት አለመሆኑን አፋችንን ሞልተን እንናገራለን:: ይልቁንም የትግራይ ሕዝብ ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በማስተናነቅ በሕዝብ ሥልጣን ላይ የመቆየት ዓላማ ያላቸው አጥፊ ግለሰቦች በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ እየሰሩ ናቸው የሚል ጥርጣሬ አለን:: የእነዚህ ግለሰቦች ጠባብ ፍላጎት ግን ለዛሬው ሰላማችንና ለተከታታይ ትውልዶች ጦስ እንደሚሆኑ ይታየናል:: አሁን ሰሞኑን ከተሾሙት 17 ጄኔራሎች መካከል ከ10 በላይ ሕወሓት የበቀለበት የአንድ ብሔረሰብ አባላት ሆነው ተገኙ:: ይሉኝታ የለም! ያሳፍራል! የፌዴራሉ ሕገ.መንግሥት አንቀጽ 87/1 ግን የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮችን የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ ይሆናል ይላል:: ይህ ሕገ-መንግሥታዊ አንቀጽ የሠራዊቱን አመራር አይመለከት፣ እንደሆነ አናውቅም:: በመጨረሻ ጥቂት ጥያቄዎችን እንጠይቅና ሃሳባችንን መቋጫ እንባጅለት:: የሸዋ አማራ አገዛዝ እያሉ የመጡት ዛሬ እነሱ ምን እየሰሩ ናቸው? በዚህ አካሄድ በአገራችን ሰላም ይኖራል? በየሕዝባቸው ስም ተደራጅተው ኢሕአዴግን መሥርተዋል የሚሉ ወገኖች ምን ይላሉ? በመሰረቱም ይህን ኢ-ፍሀትሓዊ ሥርዓት እየተንከባከበ ያለው ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ አሁን በተያዘው የተሳሳተ መንገድ ሰላም ጠፍቶ ጥፋት እንዳይከተል የሞራል፤የሕግም ኃላፊነት አለበት:: የተሾሙት ጄኔራሎች ማን ናቸው?"

| የተሰጣቸው ማዕረግ | ስም | ብሔር |
|---|---|---|
| ሜጀር ጄኔራል | ሰዓረ መኮንን ይመር | ትግራይ |
| ሜጀር ጄኔራል | ብርሃነ ነጋሽ በየነ | ትግራይ |
| ሜጀር ጄኔራል | ታደሰ ወረደ ተስፋዬ | ትግራይ |
| ሜጀር ጄኔራል | ዮሐንስ ገ/መስቀል ተክለ ማርያም | ትግራይ |
| ሜጀር ጄኔራል | ገዛኢ አበራ ደስታ | ትግራይ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | መሃሪ ዘውዱ ገ/ማርያም | ትግራይ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ኃይለ ሥላሴ ገ/ሚካኤል | ትግራይ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ፀጋዬ ተሰማ ንጉሥ | ትግራይ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ኃይለ ሥላሴ ተ/ ኃይማኖት | ትግራይ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ሙሉጌታ በርሄ ይልማ | ትግራይ |
| ሜጀር ጄኔራል | ዓለሙ አየለ ተሰማ | አማራ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ተመስገን አበበ ካሳ | አማራ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | አሳምነው ፅጌ ተበጀ | አማራ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ባዩ ወንድ አፈራሁ | አማራ |



| | | |
|---|---|---|
| | ኃይሌ | |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ኃይሉ ጎንፋ ኢ.ዶሳ | ኦሮሞ |
| ብርጋዴል ጄኔራል | አልሀዲ መሀመድ ሰይድ | አይታወቅም |
| ብርጋዴል ጄኔራል | ፍስሀ ኪዳኑ ፊንታ | አይታወቅም |
| ምንጩ | አስኳል ጋዜጣ | ነሐሴ 11 ቀን 1996 ዓም |

ወያኔ በርሃ የገባሁት የአማራ የገዥ መደብ ጭቆና ስላበዛብኝ ነው እያለ ያላዝን እንደነበር አይዘነጋም:: በደርግ የነበረውን ይቅርና ዘረኛ ነበር ተብሎ የሚወቀሰው የአጼው መንግሥት ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ተካፍሎ የሰራ መሆኑን አማራ ያልሆነ ቢመሰክር መልካም ይሆናል:: ይህን እውነታ ጥሩ አድርገው የሚያውቁ አምባሳደር አሐዱ ሳብሬ እንዲል ይላሉ::

አምባሳደር አሐሱ ሳቡሬ ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅጽ 1 ቁ 6ጥር 1996 ዓም ገጽ 32 "አማራው የርዕሠ ብሔርነቱን ሥልጣኑን ይዟል ይባል እንጂ በእውነቱ ሥልጣኑን አካፍሎ ነው ከሌሎቹ ጋር ሲሰራ የኖረው:: አማራ ስለሆንኩ ሥልጣኑን ለብቻዬ ይገባ ልግዛ ብሎ ያለበት ጊዜ አልነበረም:: እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ተነስቶ አያውቅም" ሲሉ ጽፈዋል::

የህወሓት ኮሞኖስት ሃይል የ10 ዓመት ጉዞ ግምገማ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 12 የአማራ ገዥ መደቦች ተቀናቃኝ የነበሩትን የትግራይ ገዥ መደቦች ለማዳከም ሆን ብለው የትግራይን ሕዝብ ለማደህየት በመንቀሳቀስ በህዝብ ላይ ከፍተኛ አድሎዎን ስለፈፀመበት በትግራይ የነበረው ብሔራዊ ጭቆናም እጅግ አስከፊ ነበር" ይላል:: ይህ ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ የሚያሳየው የትግራይን ሕዝብ ፀረ አማራ አድርገው ለማስነሳት በማሰባቸው ነው:: ለንገሩ ተሳካላቸው ብዙም ዘር ዘሩ የሀሰት ታሪክ አጻፉ የትግራይን ደራሲያን ሁሉ አሳመኑ:: ለዚህም ከ1984 ዓም ወዲህ ብዛት ያላቸው የሐሰት መጽሐፍ ተጻፉ:: በተለይ ትግሬን ትልቅ ለማድረግ ሌሎችን ክፍለ ሀገር ለማውደም ታጥቀው ተነሱ:: ወሎንና ጎንደርን ሕዝቡን በመፍጀትና መሬቱን ለመያዝ ብዙ ጣሩ:: የሀሰት ስብከት የሰበኩ መሆናቸውን እኛ ሌሎች ከምንጽፈው ይልቅ ራሳቸው ወያኔዎች የጻፉት ዋቢ ይሆኑናል::

ታጋይ ገሠሠ ረታ ታሪክ አጉዳፊው የአልባንያው ደብተራ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 71 "የህወሓት መሪዎች የትግራይን ሕዝብ ድጋፍ በተለይም ለጋ ወጣቱ ወደ ትግሉ ሜዳ ለማሰለፍ ይጠቀሙበት ከነበረው ሌሎች የቅስቀሳ ዘዴዎች አንዱ በጥላቻ ላይ የተመሰረተ ፕሮፖጋንዳ መካሄድ ነው:: የአማራ ገዥ መደቦች የትግራይ ሕዝብ ታሪካዊ ጠላቶች ናቸው: ለስደት የዳረጉትን አማሮች ናቸው:: በአማራ የተወሰዱበት እንደ ወልቃይት ጠገዴ ሁመራ አሉውሃና ሌሎች የትግራይ መሬቶች እናስመልሳለን ወዘተ እያሉ ነጋ ጠባ በመቀስቀስ ሕዝቡ በሌላው ወገኑ ላይ የከረረ ጥላቻ እንዲኖረው ለማድረግ ይሞክሩ ነበር:: ይህንንም በተጨባጭ በዘፈኖቻቸውና በፅሁፋቸው ተቀርፆ

የሚገኝ ሐቅ ነው" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ቅስቀሳ አድርገው የትግራይን ወጣት አሰልፈው ደርግን የጠላሁን ሁሉ ሰብስበው እያስመሩ ሥልጣን ያሉ:: የኢትዮጵያውያንን ክብርም አዋረዱ::

ሊቀ ጠበብት መድኃኔ ታደሰ ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ግንቦት 1997 ዓም ገጽ 8 "በሀገራችን አንድ ኃይል ብቻውን ማስተዳደር የሚችልበት ሁኔታ የለም" ሲሉ ጽፈዋል:: ለአንባቢያን ማሳሰቢያ ከዚህ በላይ የጠቀስኩት የወያኔ ቡድን ጠባብነት የሚጠቀም መሆኑን ባምንም ይህን ለታሪክ ልንጠቀምበት እንጂ ጥላቻን ልናጸባርቅበት አለመሆኑን አሳስባለሁ:: በእኛ በኢትዮጵያውያን መካከል በዘር ልዩነት የለብነም:: ነገር ግን ሥልጣን በሚያፈቅሩ አንዳንድ ግለሰቦች ሕዝብ ከሀዝብ እየለያዩ የሚያባሉን ቡድኖች ናቸው:: ተመልከቱ ደቡብ አፍሪካን ተመልከቱ የአሜሪካን ሕዝብ ጥቁሩን ሕዝብ እንደ እቃ ይጫወቱበት የነበሩት ዛሬ ወጣቱ ነጭ ቀርቶ አዛውንቶች የአፍሪካውያንን ልጅ ርዕሠ ብሔር አቶ ብራክ ሁሴን አባማን የመረጡት ቂም በቀል ባለመያዛቸው ነው:: በእኔ በራሴ ከማንም ጋር ቂምና በቀል የለኝም:: አገሬን የገደሏትን ሕዝቧን ያጠፏትን ግለሰቦች ግን መጥፎ ተግባራቸውን መጻፍ ማለት ጥላቻ ማብዛት አለመሆኑን እምናለሁና ሌሎች ጠባችን በአመለካከት እንጂ በጎሳ በሃይማኖት አለመሆኑን ማወቅ ይኖርብናል እላለሁ::

አቶ ስዬ አብርሃ ዋሽንግተን ዲሲ ኢትዮጵያውያንን ስብሰባ ጠርተው ንግግር ሲያደርጉ የሰሙ አቶ ብርሃኑ በላይነህ፤ እንዲህ አሉ ተብሉ ሰማ:: "ታስሮ መውጣት እንደዚህ አርቆ የማሰብ ጭንቅላት የሚያሰፋ ከሆነ የወያኔ ባለሥልጣኖች ሁለት ሁለት ዓመት ቢታሰሩ የጠባብ ሸሚዛቸውን አውልቀው ይጥሉት ነበር" ብለዋል አሉኝ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ሰላምንና አንድነትን በመሆኑ አስቀድሞ "ተሰባበሩ ወይ ተባበሩ" የሚል መፈክር አንስቶ ለብዙ ዓመታት ከጮኸ በኋላ ቅንጅት ተመስርቶ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓም ታሪካዊ ምርጫ አድርጎ ነበር:: መራሹ ወያኔ ቀደም ሲል የመንግሥት ካዝና ሲገለብጥ የለመደ የምርጫ ኮረጆ ገልብጦ ምርጫውን አሸንፌአለሁ አለ:: አላሸፈንክም! በሚል ክርክር ከቆየ በኋላ በተፈጠረው ግርግር 193 ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ሰዎች አለቁ:: ወዲያው የቅንጅትን መሪዎች አስሮ እኔ ያልኳችሁን ካልፈጸማችሁ የሞትና የእድሜ ልክ እስራት እፈርድባችኋለሁ" ብሎ በዛተው መሰረት ፍርድ ጥፋተኞች ናችሁ ብሎ ፈረደ:: የወያኔ አባላት አንድ እንድትገነዘቡት የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር የኢትዮጵያ ሕዝብ ቂመኛ ሕዝብ አለመሆኑን ለአቶ ስየ አብርሃ ያደረገው አቀባበል ምስክር ሊሆን ይገባል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ አቶ ስየ አብርሃን ይቅር ያላቸው ያጠፉት ጥፋት አንሶ ሳይሆን በመጨረሻው ሰዓት ለኢትዮጵያ ጥቅም ሲሉ በመታሰራቸው ምክንያት መሆኑን ልትረዱ ይገባል::

እ!ወልቃይት ያልታተመ!
ወያኔ አሁንስ ምን ትሉ
ውሉውና ውሉ ከጠላቱ ጋራ
ለእህት ለወንድሙ ትልቅ ባላንጋራ



የባድሜ ሽንፈት በቋራ ሲከሰት
ያውም ጨካኝ በጣም የለየለት
ግዳይ ላቀረበ ከሞተ አስከሬን ላይ የቆረጠ ለአንገት
ኧረ ጎበዝ ወያኔ ምከሩ ላለፈው ግድየለም
ጦቢያ ፀንታ ኖረች በአባቶቻችን ደም
ትግራይ በስምህ ሲነግድ በስምህ ሲኮራ
አየን የጠጅ ልጅን ውሉውና ውሉ ከጠላቱ ጋራ" ሲሉ ጽፈዋል::

ወያኔ የትግራይን ሕዝብ ለመታደግ የተፈጠርኩ ነኝ ይለናል:: ወደ ኋላ መለስ ብለን ታሪክ ስንቃኝ ግን የትግራይን ሕዝብ ሌሎች መንግሥታት ካጠፉት ይልቅ ያጠፋው ወያኔ መሆኑን ነው:: ሻዕቢያን ለመርዳት የሻዕቢያ ደጀን ሁኖ የትግራይን እንቡጥ ወጣቶች በኤርትራ ምድር ደርግን እንዲገጥሙ አድርጎ ፈጅቷቸዋል:: እኛ ይህን እያልን ስንናገር ወያኔዎች "ይህ የነፍጠኞች ወሬ ነው" ይሉናል:: እውነት መናገር ነፍጠኛ ካሰኘ ልባል አላፍርበትም:: ሱዳን ሳለሁ ጀምሮ የትግራይ ልጆች ማለቃቸውን እንሰማ ነበር:: ዛሬ አንዳንድ አባሎቻቸው ከታሪክ ተጠያቂነት ነፃ ለመሆን ይመስላል ተግባሩን አውግዘው እውነቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እየገለፁ ናቸው:: ወያኔን ከመሰረቱት 11ዱ የሆኑት አቶ አሰገድ ገ/ስላሴ ወ/ሚካኤል እውነቱን ጽፈዋል::

አሰገደ ገ/ስላሴ ወ/ሚካኤል ጋሀዲ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 131 "አንድ ነገር ላስታውሳችሁ:: ህወሓት በሳሕልም ሆነ በመላ ኤርትራ እስከ ከ1976 ዓም ቁጥሩ 65900 ከሆኑ ሠራዊት ተዋግተዋል:: ጀብሃን ተሻግሮ ለማለፍና መንገድ ለማስከፈት የተደረገው ጦርነት ካልሆነ በስተቀር 4 ዓመት ከ9 ወር በላይ ሻዕቢያን ለማዳን የተደረገው ጦርነት የህዝባዊ ግምባርም ሆነ የህወሓት መሪዎች ለአንድ ቀንም ቢሆን በመጽሔትም ይሁን በሌላ የመገናኛ አውታር ዘግበውትም አያውቁም" ሲሉ ጽፈዋል::

## ምዕራፍ 2

## ወያኔና የትግራይ ሕዝብ አንድ አይደለም

ገብረ መድኅን አርአያ አፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሕዳር 1986 ዓም ገጽ 15 "ገና ሕወሓት ሲፈጠር ይዞት የወጣ ፕሮግራም ፀረ ኢትዮጵያ አንድነት፤በጎሣ (ጠባብ ብሔርተኝተኞች) የተቀነባበረ ለኢትዮጵያ ሳይሆን መጀመሪያ ኤርትራን ለማስገንጠል ቀጥሎም የትግራይ ሪፐብሊክ መንግሥት ለመመስረት የተነደፈ ነው:: አሁን በአስመሳይ ምላሳቸው የሚናገሩት ለኢትዮጵያ ሰላምና ዲሞክራሲ የሚለው በጥር ወር 1981 ዓም ቀጥሎም 1982 ዓም ባካሄዱት ጉባኤ ያስራጩት ፍጹም ሕብረተሰቡን ለማወናበድ የወጣ የሽፍን ፖሊሲ ነው:: ኢትዮጵያ ሲሉ ኤርትራ ውጭ ማለት ነው:: መሰረታዊ የወያኔ ፖሊሲ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላም በፍቅር በአንድነት ለመኖር እንዲችል ነው የሚል እምነት የለኝም:: እነዚህ የማሌሊት መሪዎች በሰኔ 1983 ዓም ቻርተር ብለው

ያወጡት በአንቀጽ ሁለት ሐ/ ማንኛውም ብሔር ብሔረሰብ የራሱን ዕድል በራሱ እስከ መገንጠል (ነፃነት) ይደርሳል በሚል ሐረጋቸው ያወጡት ይፋ ቢሆንም ይህ መገንጠል (ነፃነት) የሚለው አንደኛ ፖሊሲ የኢትዮጵያ ሕዝብ ካልታገለው በኢትዮጵያና በሕዝቦችዋ የሚያደርሰው አደጋ እጅግ የከፋ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

አሞራ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 202 "ታሪክ ይውቀሳቸው እንጂ አገር እንደያዙ አዲስ የትግራይ ክልል ብለው ደጋግመው በአወጡት የመልክዓ ምድር (ካርታ) ላይ ከአማራው ጋር ለማቀያየም፥ወልቃይትና ጠገዴን ተሻግር አዲስ ድንበር ከመጠየቅ ይልቅ ትናንት ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ በወጨፎ ጠመንጃ የሸጡትን አውጋሮ፤የእምኒሐጅር የጎሉጅ፤የተሰነይንና የከሰላን በር የኤርትራ ክፍለ ሀገር ኩታ ገጠም ድንበር ለምን አላወሱትም" ሲሉ ጽፈዋል።

**Kshsay Berhe <u>Ethiopia:Demcratization and Unity</u>** በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 284" **TPLF and thereby the EPDRF and Ethiopia have been anti Ethiopia from the very beginning, when they wrote a manifesto in 1976 in which they declared their aim to be the independence to Tigray from Ethiopia, thess indiduals had only the borders of Tigray in their program, the Limitations of Tigray, like the lack of a port,**"*ሲሉ ጽፈዋል። ወያኔ ሲመሰረት ጀምሮ ፀረ ኢትዮጵያ ሁኖ የተነሳ መሆኑን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ የትግራይ ሕዝብ ጠንቀቆ ያውቀዋል።* የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጅም ዘመን ታሪኩ ያስመዘገበው ያስተዋይነቱ የትግዕስቱ ማስረጃ ጠቅሰና ታሪክ ዘርዝሮ ማስረዳት ይቻላል።

ግደይ እቁባይ <u>ልሳነ ሕዝብ</u> መጽሔት ቅጽ 2 ቁ 11 ሰኔ 1997 ዓም ገጽ 3 "አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕወሓትን ከትግራይ ሕዝብ ነጥሉ መመልከት የቻለ አይመስለኝም። የትግራይ ሕዝብ ስለወደደውና ስለፈለገው አይደለም። የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት አገዛዝ ይበልጥ የተበደለና የተጨቆነ እንጂ የደላውና የተመቸው ሕዝብ አይደለም። የትግራይ ሕዝብ ምንም የተሻለ እማራጭ አልቀረበለትም" ሲሉ ጽፈዋል።አንድ ለማሳሰብ የምፈልገው ታሪክ ቢኖር የትግራይን ሕዝብ ሌሎች ድርጅቶች ገብተው ማደራጀት አልቻሉም። እንዚያ ሕዝቦች ሌሎችን ድርጅቶች ቢደግፉ በበነገታው ከቤታቸው ታፍነው መወሰዳቸው መሆኑን ልናውቅላቸው አልቻልነም።

ብሥራት አማረ <u>ኢትአጵ መጽሔት</u> ቅጽ 4 ቁጥር 044 የካቲት 1995 ዓም ገጽ 23" ለውትድርና አልሰለጥንም ያለ ገበሬ መሬት አይሰጠውም፤የንግድ ፈቃድ አይሰጠውም ወይም ይወሰድበታል ይታሰራል እስከ መገደልም ይደርሳል። ከ1970-1971 በመጨረሻዎች በርካታ ተማሪዎችና ምሁራን በቀይ ሽብር ምክንያት ከከተማዎች እየሸሹ ወደ ትግሉ በሺህዎች የሚቆጠሩ ነበሩ የተቀላቀሉት። እነዚህ አዲስ ሰልጣኞች በስልነጣ ጣቢያቸውና በተመደቡበት ቦታ ሆነው ለሚያነሱት ጥያቄዎች ሳይቀር እንደተሳሳተ የፖለቲካ ዝንባሌ



እየተቆጠረ የሞት ዕዋን እንዲጎነጩ ተገደዱ። በሺዎች የሚቆጠሩ ምሁራን ተገደሉ" ሲሉ ጽፈዋል። አንባቢያን የትግራይ ሕዝብ በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ያለ ሕዝብ መሆኑን ልንረዳ ይገባል። ለዚህም ነው ወያኔንና የትግራይን ሕዝ ለይተን ማየት ያለብን፡፡ የትግራይ ሕዝብ በተለይ ትግራይ ውስጥ ያለው የሌሎች የኢትዮጵያውያንን መጎዳት ላያውቅ ይችላል። በነገራችን ላይ የተማረውንና በውጭ ያለውን የትግራይ ተወላጆች ከብዙኑ ጋር አብረን ማየት የለብንም፡፡

በውጭ አገር ሁነው ወያኔን የሚቃወሙ ቁጥራቸው ይነስ እንጂ የትግራይ ልጆች መኖራቸው አይዘነጋም። እነዚህ ግን ወያኔን የሚነቅፉት እነሱ ባሉት የማይሄድላቸው በመሆኑ እንጂ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ በድሏል ብለው ጠንከር ያለ ትግል አልሞከሩም። እነሱ ራሳቸው ከትግራይ የተወለደ በቤተ ክህነቱ ሆነ በቤተ መንግሥቱ ኢትዮጵያን ማስተዳደር አለበት ብለው ያምናሉ፡፡ የተማሩት የትግራይ ልጆች ስልጣን ከትግራይ እጅ እንዲወጣ አይፈልጉም። ወያኔን ይጠላሉ የሚጠሉበት ግን በእነሱ አስተሳሰብ ስለሄደላቸው እንጂ በሌላ አይደለም። በስደት ዓለም ያሉት በትግራይ ስም ተደራጅተው ነበር። አሁን በቅርቡ አንድ የሰማሁት ዜና አለ። ያም በጎሳቸው ስም ብቻ ተደራጅተው የነበሩ ከብዙ ውትወታ በኋላ ከ4 ሰዎች በስተረቅ ሌሎች በኢትዮጵያ ስም ለመደራጀትና ሰፋ ያለ አመለካከት መያዛቸውን ነው። ግፉበት በርቱ ያሰኛል። ነገር ግን አማራው በጎሳ መደራጀት ከኤድስ ለይቶ አያየውም። ታላቁ ሊቀ ጠበብት አስራት ወልደየስ የአማራ ድርጅት ሲመሰርቱ አማራው እየተገደለ በመሆኑ ያንን ለመታደግ ብለው ሲነሱ ተቃዋሚ የነበረው አማራው ነበር። አማራው ለብቻ መደራጀትን አንፈልግም። አማራው በሌሎች ጎሳዎች ቀደም ተጠቃሚ ነበር ተብሎ ሲለፈለፍ ነበር ግን አልተጠቀመም።

ለምሳሌ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ገዥው አማራ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። በተለይ የሸዋ አማራ ነገር ግን የሸዋ አማራ ደብረ ብርሃን ለገቢያ የሚመጣው የበግ ለምድ እንደለበሰ ነበር። በእርግጥ ከ20 የማይበልጡ በቤተ መንግሥቱ ይንደላቀቁ የነበሩ መሆናቸው ባይካድም። ከሌሎች ጎሳዎች ጭምር የሥልጣንና የጥቅም ተጋሪ ሲሆኑ ሌላው አማራ ግን ከዋለልኝ መኮንን ጹሑፍ ጀምሮ በመወገዝ ላይ ያለ ሕዝብ ነው። የእኔን የዘር ሀረግ ለመዘርዘር ጊዜው ባለመሆኑ ባልፈውም የተወለድኩበት ጎንደር ደብረታቦር ፋርጣ ግራሪያ ወርቄን ጽዮን ሲሆን አባቴም በባዶ እግራቸው ይሔዱ እንደነበር አስታውሳለሁ። እንኳን ሽፍን ጫማ ነጠላ ጫማ ለእግራቸው አልነበራቸውም። እኔ አሜሪካ ከመጣሁ በኋላ መቀየራቸውን አውቃለሁ። ስለዚህ አብዮተኞች ሆኑ ዘረኞች ይህን አማራ እንደበላ አድርገው ሲከሱት መኖራቸው አይዘነጋም። ይህን ከወላጅ አባቴ ጀምሮ እስከ ክፍለ ሀገር አልፎም በሌሎች አካባቢ የአማራው ሕዝብ በእኔ አባት አይነት የነበረ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ይህን በአማራው ሕዝብ ላይ በሀሰት ይከሰስ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም የትግራይም ሕዝብ በዚህ ዓይነት መከሰሱ እርግጠኛ ነኝ። በእርግጥ ወያኔ ከሌላው ክፍለ ሀገር የኢትዮጵያን ንብረት ጭኖ ትግራይ ማስገባቱ

አይካድም።ይህ ማለት የትግራይ ሕዝብ ፈቅዶ የተቀበለው ንብረት ነው ማለት አይደለም። በውጭ አገር ያለው ምሁራን ለብቻው በመደራጀቱ የትግራይ ሕዝብ ሊወቀስ አይገባም። ወያኔ የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ ለሱዳን ሲሰጥ መሆኑን የትግራይ ሕዝብ ያውቃል ማለት አይደለም። በእርግጥ የተማረውና በውጭ አገር ያለው ጥሩ አድርጎ ያውቃል። ሊወቀስ አይገባም።

ወያኔ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዳይቀራረብ ስለፈለገ ድርጅታቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ስለተጠላ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ እንዳይነሳባቸው ስለፈለጉ "ወያኔንና የትግራይን ሕዝብ፣የትግራይን ሕዝብና ወያኔን መለየት አይቻልም" እያሉ ያሳዝናሉ። በመሰረቱ ወያኔና የትግራይ ሕዝብ አንድ አይደለም፡ ይህን ቅድሚያ ማወቅ ይጠይቃል። ይህ ቡድን በጥቅም የሚገዙ ግለሰቦችን ይዟል። ከሸዋ ወንድ ወሰን ከበደ፣ከወሎና ከጎንደር አቶ ታምራት ላይኔንና ሌሎችን ብዙ የጥቅም ሰዎችን እንደገዛ ሁሉ ትግራይ ውስጥ ለጥቅም ሲሉ የተገዙ ሊኖሩ ይችላሉ። ያ ማለት ደግሞ የትግራይን ሕዝብ ይወክላሉ ማለት አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጅም ዘመኑ ያስመዘገበው ተቻችሎ የመኖር ታሪክ አስተዋይነቱ መጋባቱና መዋደዱ በዘርና በሃይማኖት በመደባለቁ ይህ አንቱ የሚያሰኘውን ተግባር እንሆ ወያኔ ሊያጠፋው እየተሯሯጠ ነው። በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተለያዩ ፈተናዎች ደርሰዋል ነገር ግን በሕዝቡ በኩል ምንም አይነት ጉምጉምታ ታይቶ አይታወቅም። ይህን አኩሪ ታሪኩን ነው ወያኔ በጥቂት እውቅ ባይ የሥልጣን ጥመኞች የሥነ መንግሥት ፖለቲካቸው መሳሪያ ለማድረግ ሌት ተቀን የሚለፉት ሕዝቡ የማይለያይ ሁኖ ሲያስቸግራቸው መታወቂያውን ቀየሩት። አንድ ጉዳይ ለማስፈጸም ከአንድ መስሪያ ቤት ሲገባ ተሉ ተቀሳጥፎለት ይሄዳል። የዋህ የሆኑት በዚህ ብቻ ተታለው ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለዩ የሉም ማለት አይደለም።

እንባቢያን እኔ ለወደፊቱ የሚያስፈራኝ በአቶ መለስ ዜናዊይና በአንዳንድ አፍቃሪ የሻዕቢያ ደጋፊዎች የሚጠነጠነውን ከፋፋይነት ሌሎች ኢትዮጵያውያን እንዳያስተጋቡት ነው። ምክንያቱም ወደድነም ጠላን ዛሬ የኢትዮጵያ መንግሥት መፍለጥና መቁረጥ የሚችሉት የወያኔ አባላት ናቸው። በዚህ ምክንያት በየክፍለ ሀገሩ ንብረት እየተዘረፈ ትግራይ ገብቷል። በተለይም በጎንደርና ከወሎ ጋር ከፍተኛ የሆነ ችግር ይፈጠራል። አቅም አለን ብለው ከሁለቱ ክፍለ ሀገራት መሬት ቆርሰው ወደ ትግራይ ወስደዋል። ወያኔን የሚደግፉ የትግራይ ልጆች አልገባቸው ብሎ እንጂ ከጎንደርና ከወሎ ሕዝብ ጋር ሊያጣላቸው ስለፈለገ መሬት ቆርሶ ሲሰጣቸው በደስታ የተቀበሉ የሉም ማለት አይደለም። ይህን አድርጎ ደጋፊዎቹ ካደረጋቸው በኋላ ደግሞ ሁመራን ለሱዳን አሳልፎ ሊሰጥ ሲስማማ የወያኔ ደጋፊዎች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ትዝብት ገባቸው።

በ1990 ዓም ሻዕቢያ የትግራይ ልጆችን በግፍ በደበደበ ግዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ ቆሞአል። በእርግጥ አንዳንድ እነሱን የመሰሉና ሲጀመር ጀምሮ ሥልጣን የናፈቃቸው ቡድኖች ከሌላው ጎሳ የተወለዱ የሻዕቢያ አሽከር የሆኑ



ነበሩ። በገንዘብ የምገዛ ብሆን ኑሮ እኔ ቅድሚያ እሆን ነበር። በዚያን ወቅት በተለይ ባድሜን ከሻዕቢያ ለማስለቀቅ በሚደረገው ግብግብ ወራት አንዳንድ ምሁራንና ዛሬ ድረስ ሰላም የማይሉኝ ወዳጆቼ ከሻዕቢያ ጋር መሞዳሞዳቸውን አጥብቄ በመቃወሜ እኮራበታለሁ። በዚህ ወቅት ወያኔ ያጠፋ ቢያጠፋ በራሳችን ይቅር ብለን አብረን ቆመናል። ከዚህ ወዲህ ብዙ ችግሮች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ደርሷል። በተለይም በ1997 ዓም ምርጫ ወያኔ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሲጋጭ የወያኔ አባላት ብቻ ሳይሆኑ ዘር ቆጥረው ማለት ይቻላል ከወያኔ ጋር አብረው ቆሙ። በምርጫ 97 ወቅት ውጭ አገር የነበሩ የወያኔ ደጋፊዎች ባንድ ሰብሰብ አሉ። የተጣሉ ታረቁ ሌሎችን ለመዋጋት አንድነት ፈጠሩ። እነሱ እንደዚህ ቢሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን አስተዋይ ሕዝብ መሆኑን አስመዝግቧል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋይና አመዛዛኝ ነው። አቶ ስዬ አብርሃ፣አሜሪካ ሲመጡ እክብሮ የተቀበላቸው ከነበረው ስህተታቸው በመመለሳቸው መሆኑን ጠንቅቆ አምኗል። ይህን ያህል ሲሆን በተለይ በውጭ አገር ያላችሁ የወያኔ አባላት እንዴት ማስተዋል አቃታችሁ። ወያኔ ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ ሕዝብና በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን ጥፋት ከላይ የዘረዘርኩት አንዳንድ የወያኔ አባላት እንደማትቀበሉት አምናለሁ። ረጋ ብላችሁ ስታስቡት ግን እናንተን አቶ መለስና ሌሎች አንዳንድ አፍቃሪ ኤርትራ ግለሰቦች ከኢትዮጵያውያን ጋር ለይተው ካስጠሉአችሁ በኋላ እነሱ ግማሽ ትግራይን ለሻዕቢያ አስረክበው ርዕሰ ብሔር ኮሎኔል መንግሥቱ እንዳደረጉት አውሮፕላናቸውን አስነስተው አስመራ ቢገቡ ምን ታደርጋላችሁ? ለዚህ ቅድሚያ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አንድ ሁናችሁ ካልሰራችሁ ከሌሎች ክፍለ ሀገራት ይልቅ ጉዳት የሚደርስባችሁ በናንተ ላይ መሆኑን ማሰብ የተሳናችሁ ለምን ይሆን? ዛሬ ዓለም አንድ እየሆነች በመብራት በኤሌክትሪክ መገናኛ በድረ ገጽ ተወጥራ ባለችበት ሰዓት ኢትዮጵያውያን በጎሳ ወጥመድ ተይዘን እንገኛለን። እኔ ጠበንጃን የጠላሁት ቀደም ብዬ ነው። ጦርነት ከባድ ነው! ብዙ ሕጻናት በጦርነት አልቀዋል። ብዙ ንብረት በእሳት ሲጋይ አይቻለሁ። ዛሬ የወያኔ ባንዶች ሽፍታ እያሉ የሚገድሏቸው የአርማጭሆ ሕዝብ በጦርነት ሲያልቅ አይቻለሁ። ያን ሕዝብ ያስጨረሰ ኢዲዩ ደብዛው ጠፍቷል። ያ ትውልድ ያፋጀው ኢሕአፓ ሲከፋፈል ኑሮ ዛሬ በግለሰብ ስም መጠራት ከጀመረ ውሉ አድሯል። ይህን የጠበንጃ አብዮት ከአንድ ቦታ ላይ መቆም ይኖርበታል የሚለውን አቅዋሜን የሚጠሉ ወገኖቼን አልፈርድባቸውም።

የወያኔ ኢሕአዴግ ወታደሮች በአደባባይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይፈጁታል። የአገሪቱ ሀብት በአንድ ክፍለ ሀገር ብቻ ይፈሳል። በአገሪቱ የበላይነት ወሳኝነት ያላቸው የአንድ ክፍለ ሀገር ሰዎች ናቸው። አገሪቱን የባህር በር አሳጥቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር መንዝሮ አንድ እንዳይሆን አድርጎታል። የኢትዮጵያን ሕዝብ አይደለም የዓለምን ሕዝብ አጭበርብሮ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓም ምርጫ በጠበንጃ ወስዷል። መሪዎቹን አስሮ አሰቃይቷል። ይህ አልበቃ ብሎ 1600 ጋሻ ወይም ኪሎ መሬት ለጎረቤት አገር ሊሰጥ ደፋ ቀና እያለ ነው። በዚህ መካከል የአካባቢው ተወላጆች ከንብረታቸው ከቤታቸው

ሲፈናቀሉ መርዳት ሲገባው የተፈናቀለ የለም ብሎ በአደባባይ ያሳዝናል። ምንም እንኳ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠበንጃውን ያስወረደው ቢሆንም አንዳንዶች እየደበቁ ባስቀመጡት ጠበንጃ መሬታቸውን የሚያርሰውን ሱዳንን በመውጋታቸው ለምን ወጋችሁ ብሎ ደበደባቸው። በዚህና በሌላውም ምክንያት ሕዝቡ ትግስቱ አልቆ ወያኔ የመጣው በጠበንጃ ስለሆነ የሚወርድ በጠበንጃ ነው የሚሉትን ሰዎች ተስፋ ቆርጠው ከዚህ ውሳኔ በመግባታቸው ምክንያት ባልፈርድባቸውም ግን መታየት ያለበት ጠበንጃ ምንግዜም ሰላም የማያመጣ መሆኑን ነው። ጠበንጃ የሚያመጣው ነገር ቢኖር የጠገበን ነብር አባሮ የተራበን ነብር ማስገባት ነው ይህ ደግሞ ውጤቱ ሁሌም ጠበንጃ ነው። ስለዚህ የሰላም ትግል አማራጭ የሌላው ጉዳይ ነው። የደቡብ አፍሪካ የሰላም ታጋይ ርዕሠ ብሔር ማንዴላ ለ27 ዓመት ሲታሰሩ በሚኒታቸው ከሰላም ትግል ፍንክች አላሉም።

<u>ባድመ እንደምክንያት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 363 የኢትዮጵያ ሕዝብ ከታሪኩም ቢሆን በማንም አገር ሉአላዊነት ላይ ጣልቃ የመግባት ፍላጎት የለውም። የጥቅም ግጭት አለን ከሚሉ አገሮች እንኳ ቢሆን አብሮ መስራት አብሮ በመኖርና አብሮ በማደግ የሚያምን ማሕበረሰብ እንጂ በጠላትነት የማየት ልምድ የለውም። የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎትና እምነት በመጣስ በአገሩ ሉአላዊነትና ብሔራዊ ጥቅም ላይ ጥቃት በሚሰነዝሩ ኃይሎች ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ምቹ አይደለም። ኢትዮጵያውያኖች ከታሪካቸው ነፃ ሕዝቦች ኅበዝ ሕዝቦች ጥቅማቸውን ለማስከበር ሲሉ እርስ በርሱ ቢዋጉም ጠላት ሲመጣ ግን የውስጥ ቅራኔያቸውን ወደጎን በመተው ወራሪውን ኃይል በአንድነት የሚመክቱ በነፃነት የኖሩ ሉአላዊነታቸውን ፍፁም የማያስደፍሩ በዚህ ጀግንነትም ከአፍርካ አህጉር ተለይተው የሚታወቁ ሕዝቦች ናቸው። ይህ ነባር ታሪክ የኢትዮጵያውያን መለያ ታሪክ መሆኑ እየታወቀ በሜካ አስተሳሰቡ ተዘፍቆ የኖረና ያለ የኤርትራ መንግሥት ኃይል በማከማቸቱ ጉልበት የፈጠረ መስሎት በኢትዮጵያውያን ላይ በከፈተው ጦርነት በአጭር ጊዜ ውስጥ እጅግ አሳፋሪ በሆነ መንገድ ሽንፈቱን በዓለም ሕብረተሰብ ፊት ገሃድ ሁነዋል። ከሻዕቢያ መንግሥት ወረራ ከበስተጀርባ ሁነው ሲያጫፍሩና ሲያዳምቁ የነበሩ ኃይሎች ድጋፍም ታክሎበት ይደረግ ስለነበረ ሽንፈቱም የሻዕቢያ መንግስት ብቻ መሆኑ ቀርቶ የአጫፋሪዎቹና የፈንጅ አቅራቢዎቹ ሽንፈት እንደሆነም በግልጽ ገሀድ ሁኗል። የኢትዮጵያውያን የጀግንነት ምስጢር ለጠላት ሁሉ ጊዜ ምቹ ሁነው አለመገኘት ነው። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ጥቃት ሲነሳ ደሙ ይፈላል፣ ፀጉሩ ይቆማል፣አብሮ ይዘምታል አብሮ ይዋጋል አብሮ ድል ይቀናጃል የአገሩን ሉአላዊነት ያስከብራል" ሲሉ ጽፈዋል።

መድኅኔ ታደሰ <u>የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 156 "የሚገርመው የኢትዮጵያ መንግሥት ህግሐኤንና ኤርትራውያንን ለማስደሰት ያደረገው ጥረትም ከኢትዮጵያውያን ይልቅ ያልተረዱት ኤርትራውያን ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል። ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ንብረት ዘርፎ ለመውሰድ ሲነሳ መውሰድ የለብህም በማለት የታገለው በስልጣን ላይ ያለው የወያኔ ቡድን ሳይሆን ከታች ያለው የትግራይ ሕዝብ ነው። ለምሳሌ በ1986



ዓም እስከ ሚያዝያ 1990 ዓም ትግራይ ውስጥ 3 ኃይል ነበረ። የመጀመሪያው ከሕዝቡ የመጣ ሮሮህ ነው። ያም የትግራይ ሕዝብ ዓላማ "ቅድሚያ ኢትዮጵያ ቀጥሎ ትግግራይነት" የሚለው ኃይል የሻዕቢያ ተሳቢ ተሸከርካሪዎች ከኢትዮጵያ ጭነው የሚወስዱትን ቁሳቁስ ማቃጠልና ከኤርትራ የሚገባውን እቃ አለመግዛት አመጽ ጀመረ። ይህ ኃይል ጥላቻው እየበረታ ሲሄድ ሁለተኛው ኃይል የዚህን ሕዝብ ስሜት ሊጋራ ታጥቆ ተነሳ። ያም ሁለተኛው ኃይል ዓላማ "ቅድሚያ ትግሬነት ከዚያም ኢትዮጵያዊነት" የሚለው ኃይል ኋላ ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊን አስጨንቆ በኤርትራ ላይ የምጣኔ ሀብት የኢኮኖሚ እገዳው እንዲበረታ ያደረገው ውሎ አድሮ አንጃ ተብሎ የተባረረው ኃይል ነው። ሶስተኛው ኃይል ደግሞ በርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው "ቅድሚያ ኤርትራ ቀጥሎ ትግራይ ከዚያም ኢትዮጵያዊነት" የሚለው ኃይል አቅም ስላነሰው ሊንበረከክ ቻለ።

ነገር ግን ይህ ሶስተኛው ኃይል ከኤርትራ ጦርነት በኋላ ሁለተኛውን ኃይል አባሮ ብቻውን ቀጭ ብሏል። ዛሬ ይህ የመጀመሪያው ኃይል ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዳይገናኝ ይህ ሶስተኛው ኃይል "ወያኔንና የትግራይን ሕዝብ፣የትግራይን ሕዝብና ወያኔን መለየት አይቻልም ሁለቱም አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው" በማለት ማላዘን ጀምሯል። ስለዚህ ዛሬ አንዳንድ የዋሕ ሰዎች ትግርኛ ተናጋሪውን ወያኔ አስመስሎ የሚያይ አሉ። ይህ መጥፎ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ለወያኔ ቅስቀሳ እየተዘጋጀንለት መሆኑን መረዳት አለብን። ባለፈው በ1997 ዓም የቅንጅት ምርጫ ወቅት የትግራይ ልጆች ከሌላው ኢትዮጵያውያን ጋር ሁነው የታገሉ መሆናቸው አይዘነጋም። ሊቅ ዶ/ር ኃይሉ አርአያን አልፈን ሌሎች ብዙ የትግራይ ልጆች ታግለዋል። አቶ ክፍሉ ታደሰ ግንቦት ሰባት በተባለው መጽሐፋቸው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የነገሩአቸውን ጽፈዋል። ያም ወያኔ ሕዝቡን አስሮ ካሳደረ በኋላ ከ60 እስከ 70 የሚሆኑ የትግራይ ልጆችን መፍታቱን ነግረዋቸው ጽፈዋል። እንዲሁም ተዋናይ (አርቲስት) ደበበ እሸቱ የትግራይ ልጆች ያደረጉትን ዘርዝር አድርገው ጽፈዋል።

ደበበ እሸቱ <u>የእምነቴ ፈተና</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 135 "የትግራይ ተወላጆች የኛ ደጋፊዎች ናቸው። ሰዓት ሳይወስኑ መሽ ረፈደ ሳይሉ ልክ እንደራሳቸው ሥራ በማየት ነበር የሚደክሙት። በሕዝባዊ ስብሰባዎች በአዲስ አበባ፣ በክልሎችም በመስቀል አደባባይም አብረውን ሳይለዩን፣ፕሮግራሙ እስኪያበቃ ድረስ ከያንዳንዳችን ባልተናነሰ መንገድ አስተዋጽኦ በማድረግ ደግፈውናል፣ረድተውናል። ምንጊዜም ምስጋና ይገባቸዋል። ኢሕአዴግ ቅንጅትን ዘረኛ ብሎ ሲለጥፍብን አንጀታቸው እያረረ ለምን የማያውቁትን ይዘሳብዳሉ? ሌላው ቢቀር እኛን ምን ሊሉን ነው? በማለት ፕሮግራማችን ጥራቱንና ብቃቱን የጠበቀ እንዲሆን የሚለፉ ኢትዮጵያውያን ናቸው"ሲሉ ጽፈዋል።

<u>አውደ ኢትዮጵያ ልዩ እትም 1</u> 2000 ዓም ለምሳሌ 1997 ምርጫ ምክንያት የጠፋው 193 ሕይወትና 763 የቆሰሉ ዜጎች ፍርድ ይጠብቃል የተባለው

መጣጥፍ ገጽ 3 “እንጸልካቸው ወ/ገብርኤል እድሜ 26 ክልል ትግራይ የሞተበት ጥይት” ሲል ጽፎአል። እንግዲህ ሆደ ሰፊ መሆን ማለት በሃይማኖትና በጎሳ መለያየት መጥላት ይገባል። እንባቢያን ይህን እያልኩ የምጽፈው ወድጄ አይደለም እየፈራሁ ነው። ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ስም የኢትዮጵያን ሕዝብ የበደለ በመሆኑና ኢትዮጵያን ያፈራረሰ በመሆኑ የሚበሳጭ እንዳለ ስለተረዳሁ ነው። ስለዚህ በትግራይ ሕዝብና በሌላው ሕዝብ መካከል ልዩነት የለም። ሥልጣን የናፈቃቸው የሚያመጡት ችግር እንጂ በሕዝቡ መካከል ልዩነት ኑሮ አያውቅም። ሕዝቡ ተባብሮ ተረዳድቶ የኖረ ለወደፊቱም በዚህ ዓይነት ትብብር እንዲኖር ሁላችን ሆደ ሰፊ መሆን ይኖርብናል።

## ምዕራፍ 3

## የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ!

ዳኛው ወል ደሥላሴ ውጣ ውረድ የበዛበት ሕይወት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 98 “ወገኑን አይወድም እየተባለ የሚወራለትና ስሙ የሚጠፋው የጎንደር ሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ ጄኔራል ነጋ ተገኝ የሚባሉ የራሱን ልጅ በአስተዳዳሪነት ሲያገኝ” ሲሉ የጎንደር ሕዝብ ተወላጁ ተሹመው ሲመጡለት የተደሰተ መሆኑን ገልጸዋል። ለአንድ አካባቢ ደህናው ነገር አስተዳዳሪው የአካባቢው ተወላጅ ቢሆን ይመረጣል። ተወላጆች በየክፍለ ሀገራቸው ቢያስተዳድሩ ችግሩ ይወገዳል! ኢትዮጲያ የብዝ ጎሳዎች ጎተራ ስትሆን የያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የየራሱ ተወካይ በሀላፊነት መቀመጥ ይኖርበታል። ይህን ብሎ መጠየቅ ሌሎች ዘረኝነት ሳይሆን አገርን ለማሳደግ ያመቻል። ወሎየው የአስተዳደር ችሎታ ቢኖረውና ወለጋ ሀዶ በአስተዳደር ጎንደሬው ሐረር ቢሄድ! ትግሬው ሲዳሞ ሕዶ ቢሾምና ጎጃሜው አፋር ቢሾም፤አርሲው ትግሬ ቢሾምና ኡሊባቡሩ ጎንደር ቢሾም ወለጌው ትግሬ ቢሾም ጋሞጎፋው ወሉ፤ ቢሄድ የተቀላጠፈ ሥራ ለመስራት አይችልም። ምክንያቱም ተሹሞ የሄደበትን ክፍለ ሀገር የሰውን ጸባይና ባህል ሌላውን ሁኔታ እስኪለምድ ድረስ ስራው ይጓተታል።

ይህ አሰራር በደርግ ዘመነ መንግሥት በአንዳንድ ክፍለ ሀገራት ተጀምሮ ደህና መሄድ መራመዱ አይዘነጋም። ሞያ ያለው ግለሰብ ቢሆንም ለአካባቢው ባይተዋር ከሆነ ጥሩ አይመጣም። ስለዚህ የአባቶችም አባባል “የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ” የሚባለው ያለ ምክንያት አይደለም። በእርግጥ ማዕከላዊ መንግሥት ቅድሚያ ተጠሪ አድርጎ የሚሾማቸው የክፍለ ሀገሩን ልጆች መሆኑ እንዳለ ሁና ሌሎች ባለሙያዎች ደግሞ ሌላውን ስራ ለመስራት ይችላሉ። በአንድ ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪው ተጠሪው የክፍለ ሀገሩ ተወላጅ ከሆነ በኋላ ሌሎችን ማዕከማዊ መንግሥት የሚመድባቸው ሰራተኞች ቢላኩ ከሞያ ጋር የተገናኘ በመሆኑ ችግር አይፈጠርም። ይህን ባህል ለማዳበር ደግሞ ቅድሚያ የተስተካከለ የማይዛባ ማዕከላዊ መንግሥቱን ሕገ መንግሥት መኖሩ ይገባል።



በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በስልጣን የነበሩት ሰብሰቦች መሆናቸው አይዘነጋም። በ14 ክፍለ ሀገር በብዛት የአንድ ክፍለ ሀገር ተወላጆች ነበሩ። ይህ ሌሎች ኢትዮጵያውያንን አስከፍቷል። ሌላውን እንተዎው ለ60 ዓመታት ኤርትራ በቅኝ ግዛት የተዳደረች መሆንዋ አይካድም። ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት ብዙ ጥረት ተደርጓል። ክቡር አክሊሉ ሀብተወልድ ልፋትና ኤርትራውያን አገር ፍቅር ብለው ታግለው በተባበሩት መንግሥታት የተሰጣቸውን የራስ ገዝ አስተዳደር አፍርሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲቀላቀሉ በጠቅላላ አስተዳደሩ በነሱ ተወላጆች ተይዞ ቢሆን ኑሮ ችግሩ አይበዛም ነበር። አጤው ግን ያደረጉት አስተዳደሩን በእርሳቸው ሰዎች አስይዘው ትምህርት ቤትና ኩባንያ ኤርትራ ውስጥ ከፈቱ የኢትዮጵያን ንብረት አፈሰሱ። ለ3 ዓመታት የመላው ኢትዮጵያ የዓመት መጠን (ባጀት) ኤርትራ ከወጣው ጋር እኩል ሆኑ ነበር። ኤርትራውያን ያዩት አስተዳዳሪ ሁኖ የመጣውን ግለሰብ እንጂ በነዚህ ግለሰቦች አማካይነት የተከፈቱትን ተቋማት ሊያዩ አላሹም። እስኪ በ1960 እስከ 1966 መግቢያ ላይ የነበሩትን የየጠቅላይ ግዛቱን ገዥዎች ስም እንመልከት።

1ኛ ኤርትራ ልዑል ራስ አሥራተ ካሣ፤
2ኛ ትግራይ ራስ መንገሻ ሥዩም፤
3ኛ ወሎ ደጃዝማች ማሞ ስዩም፤
4ኛ ጎንደር ሌ/ኮሎኔል ታምራት ይገዙ፤
5ኛ ጎጃም ደጃዝማች ደረጀ መኮንን፤
6ኛ ሸዋ ራስ መስፍን ስለሽ፤
7ኛ ሐረር ደጃዝማች ወልደ አማኑኤል፤
8ኛ ባሌ ሜ/ጀኔራል ጀጋማ ኬሎ፤
9ኛ ወለጋ ደጃዝማች ካሣ ወልደ ማርያም፤
10ኛ ጋሞ ጎፋ ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ አበበ፤
11ኛ ሲዳሞ ሌ/ጀኔራል ነጋ ኃይለ ሥላሴ፤
12ኛ ከፋ ደጃዝማች ፀሐይ ዕንቁ ስላሴ፤
13ኛ ኢሉባቦር ደጃዝማች ወርቁ ዕንቁ ስላሴ፤
14ኛ አርሲ ደጃዝማች አእምሮ ሥላሴ፤ ናቸው።

ለምሳሌ ድንበርን ለመከለል በተደረገው ድርድር ወቅት ሊደናበሩ የሄዱት ግለሰቦች ከአካባቢው ሕዝብ ጋር ካደረጉት ግንኙነት ይልቅ ለንደን ቅኝ ገዥዎች ሥለው ካስቀመጡት ሰነድ ፍለጋ ነው። የአካባቢው ተወላጆችን ማነጋገር ሐፍረት መሰላቸው። ለዚህም በሄሊኮፍተር ከደንበሩ ደርሰው ይመለሱ ነበር እንጂ “ከዜት እስከዜት ድረስ ነው እናንተ እና አባቶቻችሁ ታርሱት የነበረው አስረዱን” ብሎ የጠየቃቸው የለም። እነዚህ በአጤው እየተመለመሉ በተለያዩ ከፍተኛ መስሪያ ቤት የተሰገሰጉት ትንሽ ግለሰቦች የአካባቢውን ሕዝብ ጠይቀው ሠነድ ሊያዘጋጁ አልፈለጉም። ለምሳሌ በአሜሪካ ድምጽ ራዲዮን በጎንደር ክፍለ ሀገር በጭልጋ አውራጃ ካነጋገራቸው መርጌታ ሲናገሩ “ወያኔ ድንበርን ለመከለል ፈልጎ ሳለ እነሱን ሰብስቦ ገንዘብ እየሰጠ

መሬቱን የሱዳን ነው ብላችሁ ፈርሙ"ብሎ ሲጠይቃቸው አንፈርምም ብለው ተመልሰዋል:: እነዚህ ሰዎች እንቢ ሲሉት ሌሎችን ባንዶች ገንዘብ አምላኬን ሰብስቦ ወስዶ እንደነበር መርጌታ ተናግረዋል:: ለዚህም ነው እነዚህ በመጀመሪያ ሕደው የነበሩት ደንበራችን እናውቀዋለን ያሉት:: ኢትዮጵያ ዛሬም 14 ክፍለ ሀገር ያላት አገር ናት:: ወያኔ ክልል ብሎ በ9 ቢሸነሽነው 14 ክፍለ ሀገር ናት:: በደንበር ላላችሁ ክፍለ ሀገራት ተወላጆች የማሳሰበው ጉዳይ ቢኖር ሕብረት ይኑር ነው:: ለወደፊቱ ለኢትዮጵያ አንድነት መሰረቱን ሊያናጉ የሚችሉ የተወሰኑ ክፍለ ሀገራት አሉ:: በተለይም ከታሪክ ሠነድ ከምንረዳውና እኛም ደርሰን ካየነው እውነታ ለወደፊቱ ሐረር÷አሰብ÷ትግራይ÷ ጎንደርና ጎጃም ሌሎችም ክፍለ ሀገራት አረንጓዴ ሳይሆኑ ደም የሚፈስባቸው ናቸው:: ከዚህ በፊት ደም ፈስባቸዋል ለወደፊቱም ደም ይፈስባቸዋል:: ባለቤት አሪ የሚለው ደግሞ ከምክትል ገዥ ጀምሮ ተወላጁ ማስተዳደር ሲችል መሆኑን ጠንቅቀን መረዳት ይኖርብናል::

1ኛ ሐረርጌ አስቸጋሪውና ከሁለት አገር ጋር የሚያገናኘው የወሰን ችግር ያለበት ሲሆን በ1969 ዓም ሐረር አቅራቢያ ድረስ ሱማሌ ገብታ ልታጠፋው የነበረ መሆኑ አይዘነጋም:: ይህንም ጥፋት የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት ሳይከፋፈል አንድ ሁኖ ያስቀረው መሆኑ ታሪክ ሕያው ምስክር ነው:: ሐረርጌ ከቀደም ጀምሮ ቅኝ ገዥዎች ያሰፈሰፉበት አጤ ግራኝ አህመድን ቱርኮች ረድተው በመምጣት የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም እንደ ጎርፍ የፈሰሰበት ሲሆን ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ያላሰለሰ ጥረት ወደ ማዕከላዊው መንግሥት ቢገባም ጠላቶች በሃይማኖት እያመካኙ ከፍተኛ የደም ጎርፍ እንዲፈስ ሁኖበታል:: የአጥፍቶ መጥፋት ኃይሎችስ ዛሬ በዚህ አካባቢ አቅድና ዓላማ ሳይኖራቸው ይቀር ይሆን?

<u>መስዓዕትነት እና ፅናት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 98" በዚህን ጊዜ ነበር በጠቅላላ በኡጋዴን ግዛታችን የኢትዮጵያ ሠራዊት የሞት ሽረት ውጊያ የፈጸመው በወልወል፣በገላዲን፣በቀብሪደሃር፣በሙስታሂል፣በአቧሬ፣ በቀላፎ የነበረው የ3ኛ ክፍለ ጦር ብርጌዶችና ሻለቆች የሶማሊያ ታንክና መድፍ በመጋፈጥ ከነቤተሰቦቻቸው በዚያ እጅግ ሰፊ በሆነ በርሃ ላይ ውድ ሕይወታቸውን ለአገራቸው አንድነትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ክብር ሲሉ ሰጥተው ያለፉት:: የተረፉት የጦር ባልደረቦች በጅጅጋ ካራማራ ተራራ ላይ መሽጉ በሚካናይዝድ ታንኮች፣ብረት ለበሶችና ከባድ መድፎች በአየር መቃወሚያ መሳሪያዎች እየተረዳ የሚገሰግሰውን የሲማሊያ ጦር የወገን ጦር በፍፁም መቋቋም አቃተው:: የሶማሊያ ወራሪ ጦር በወገን ሰላማዊ ሕዝቦች ላይ ከባድ ጉዳት አደረሰ:: በገጠሩ ደጋ ስፍራዎች በጋራ ሙለታና በኤጀርሳ ጎሮ ቀደም ብለው በሚሰጥር ለሽፍትነት ተግባር ሰርገው የገቡት ቤተ በማቃጠል የልማት ድርጅቶች ላይ አደጋ በመጣል ከፍተኛ የማጥቃት ድርጊታቸውን ጀመሩ:: በጅጅጋ፣ካራማራ ተራራ ላይ ይከላከል የነበረው የወገን ጦር ከሶማሊያ ጦር የሚወርድበትን ያፈሰሱበት አጥንታቸውን የከሰከሱበት የአባቶቻችንና የአያቶታችን መሬት እየተደፈረ መጣ:: የወገን ጦር ወደኋላ በማፈግፈግ ባቢሌ አካባቢ ዳከታ በተባለ ከፍተኛ መሬት ላይ እንደገና የመከላከያ ምሽጉን



አዘጋጀ" ይሉና ገጽ 102 " በጥር ወር 1970 ዓም የኢትዮጵያ ሚሊሺያ ሠራዊትና መደበኛ ነባሩ ጦር ክፍሎች የተቀዳጀ የመልሶ ማጥቃት ዝግጅት በማድረግ በኤጀርሳ ጎሮ እና በዳከታ አቅጣጫ በወገን አየር ኃይል እየተረዳ ጦርነቱን ጀመረ:: በእውነቱ የሶማሊያ ጦር ተቋቁሞ ሊዋጋ ቀርቶ አግበስብሶ ያመጣውን ከባድ መድፎች፣ብረት ለበሶች፣ታንኮችና አየር መቃወሚያ መሳሪያዎች ይዞ በቅጡ ማፈግፈግ ስላልቻለ ሁለት ሶስተኛውን ያህል ወገን ማርኮ ተረከበው" ሲሉ ጽፈዋል:: በዚህ ወቅት ሶማሌዎች በሃይማኖት ለማሳበብ ጥረት ቢያደርጉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሃይማኖት መሪዎቹ እስከ ተራው ሕዝብ ባንድ ቆሞ "በሀገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለያየንም "የሚል መጽሐፍ ጽፎ ለአገር አንድነት የተነሳ መሆኑ አይዘነጋም::

2ኛ አሰብ ራስ ገዝ አስተዳደር ከአፋር ጀምሬ ብዘረዝር የወደፊቱ አስከፊ ችግር ይገጥመናል የሚል ፍራቻ አለኝ:: በመሰረቱ አሰብ አስተዳደር አፋር የኢትዮጵያ እንጅ የኤርትራ አይደለም:: አሰብን የአፋር አስተዳደር ከጅቡቲ ጋር ያለው ደንበር የተሰመረበት ነው:: ከኤርትራ ጋር ግን ገና ብዙ ጦርነት የሚያስነሳ ኢትዮጵያውያንን ደም የሚያፋስስ ቁርጠኛ የኢትዮጵያ አስተዳዳሪ ምኒልክ ቤተ መንግሥት እስኪገባ ድረስ የሚጠብቅ ይመስለኛል:: ይህ የእኔ ሕልም ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ሕልም መሆኑን አልጠራጠርም:: ዛሬስ ከኛም አልፎ የአደጉ አገሮች ሳይቀር ቀልብ የሚስብ እጃቸው የሚገባበት የአሰብ ጉዳይ መሆኑ አይቀርም:: የአረቡ ዓለም የኤርትራን ሕዝብ ፈልጎ ሳይሆን ቀይ ባህርን ፈልጎ ንብረቱን ያፈሰሰ ሲሆን የዓረቡ ዓለም እንሆ ፊታቸውን ወደ ቀይ ባህር አዙረዋል:: አሰብ ወደ ኢትዮጵያ ካልተከለለ ለወደፊቱ በኤርትራ ሰላም አይኖርም:: አንዳንድ ግለሰቦች አሰብንና ኤርትራን ለይተን አናይም ሁለቱም አብረው ወደ ኢትዮጵያ ይቀላቀሉ ይላሉ:: በመሰረቱ አሰብና ኤርትራ ልዩነት አላቸው:: ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ሊጨመሩ አይገባም እኛ አንድ ሕዝብ ነን ስንል እነሱ አይደለነም ብለዋል:: 30 ዓመታት ተዋግተዋል ወያኔ ፈቅዶላቸው ከኢትዮጵያ ሲነጠሉ የአሰብን አስተዳደር ጨምሮ ሰጣቸው:: ስለዚህ ኤርትራውያን ኢትዮጵያዊ አይደለነም ብለው ወግተውን የሄዱትን የኛ ናችሁ ለምን እንላለል? ወገኖቻችሁ ነን የሚሉንን የአሰብ አስተዳደር ተወላጆች ጥያቄ ማክበርና መተባበር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው::

3ኛ ትግራይ ክፍለ ሀገር አሁንም ከኤርትራ ጋር ደንበሩ በትክክል አልተሰመረበትም:: ይህ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት አልቋል የተባለለት ውሳኔ ከተወሰነ ብዙ ዓመታት አስቆጥሯል:: ነገር ግን እስከ ዛሬ አንድም ውጤት አልታየም:: በዚህ በኩል ገና ብዙ ችግር የሚያመጣ መሆኑን ከዚህ በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም የፈሰሰበት መሆኑ መረሳት የለበትም:: በትግራይ መሬት ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደም ፈሷል:: ባድሜም ሆነ ሌሎች ወረዳዎች የትግራይ ክፍለ ሀገር አስተዳደር ውስጥ ሁነው የቆዩ መሆናቸውን ከዚህ በፊት ጽፌአለሁ:: አማረ አለፈ ብሻው መጋቢት 2 ቀን 1991 ዓም <u>ካለፈው ስህተታችን እንማር</u> በሚል መጣጥፍ ገጽ 9-10 "እነዚህ የተጠቀሱት ወረዳዎች በታሪክ ከአክሱም ሥልጣኔ ጀምሮ የትግራይ ክፍለ ሀገር እንደሆነ ታሪክ

የያዘው ሐቅ ነው:: ይህ መሬት ቀደም ጀምሮ በትግራይ ክፍለ ሀገር ይተዳደር እንደነበር ብዙ የኢትዮጵያ አዛውንቶችና በተለይ የትግራይ ክፍለ ሀገር ተወላጆች የሚናገሩት ታሪክ ነው:: ሻዕቢያ እነዚህን ወረዳዎች ለመውሰድ የቃጣው ጨርሶ ከታሪክ ውጭ የመስፋፋት ሙከራ ለማሳየት ካልሆነ በስተቀር እነዚህ ወረዳዎች በባህረ ነጋሽ በኤርትራ ይተዳደር ነበር የሚል ታሪክ የለም:: ሽራሮና ባድሜ ሻዕቢያ አቅም አለን ብሎ ለመውሰድ የከጀለው በመሳሪያ እንጂ በታሪክ አይደለም:: ወያኔ በጠበንጃ ተመክቶ ከታሪክ የሌለውን ከጎንደርና ከወሎ ለም መሬቶችን ወደ ትግራይ እንደከለላቸው ሁሉ ኤርትራ ደግሞ በአቅሟ ከትግሬ ለም መሬቶችን ለመውሰድ የተነሳችው ታሪክ ኑሯት ሳይሆን በኃይል መመካት መሆኑን ለማንም ግልጽ ነው" ሲል ከተጻፈ በኋላ ለጹሑፋ ማጠናከሪያ ከታሪክ የወሰድኩበትን እገልጻለሁ::

1ኛ ዶ/ር ሀብተ ማርያም አሰፋ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሉች ገጽ 733
2ኛ ጦቢያ ጋዜጣ ቁጥር 12 ሰኔ 25 ቀን 1990 ዓም ገጽ 7
3ኛ ሐዋርያ ጋዜጣ ሕዳር 1991 ዓም አቶ ተስፋዬ ሰቋር ቃለ ምልልስ
4ኛ ልዑል ራስ መንገሻ ስዩም በአሜሪካን ራዲዮ የአማርኛው ቃለ መጠየቅ ሲደረግላቸው የሰጡት መልስ "የግዛት ጥያቄ ማንሳት ያለባት ኢትዮጵያ እንጂ ኤርትራ ልትሆን እንደማትችል" ተናግረዋል:: እርሳቸው ሲያነሱት የፈለጉት ከላይ አሞራ ከተባለው መጽሐፍ የተገለጸውን መሬት ሳይሆን አይቀርም:: በትግራይ ውስጥ ባሉት ወረዳዎች ከታሪክ የትግራይ ክፍለ ሀገር እንጂ የኤርትራ አለመሆኑን ደግሜ ደጋግሜ ስጽፍ ቆይቻለሁ::

4ኛ የዚህ መጽሐፍ መነሻ የሆነው ከጋምቤላ እስከ ሁመራ ያለው 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ወደ ሱዳን ሲሰጥ የታቀደለት ነው:: ሁኔታው በኢትዮጵያ አስተየዳዳሪዮች የግል ጥቅም ሲሆን ይችላል:: በዘመነ መሳፍንት ወቅት በጎንደርና በጎጃም በኩል መሳፍንቶች ሕዝቡን በማስተባበር ከ42 ግዜ በላይ ጦርነት ገጥመው ከቁርከ ተከላክለው አቆይተዋል:: በመሰረቱ አፍንጫ ሲነካ ዓይን ያለቅሳል እንደሚሉት ለጎንደር የመጣው ጥፋት ጎጃምን የማረበት ወቅት የለም:: ከላይ እንደተባለው ሱዳን ይህን አካባቢ ሕዝብ ለማስለም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ነው:: በጎንደርና በጎጃም በወለጋ በኩል በድንበር ጉዳይ ቅርበት ስላለው በንግድ አመካኝቶ ሕዝቡን ማፋጀትና ሕብረት እንዳይኖረው ማድረግ ተግባራቸው ሲሆን ይህን ሴራ ሕዝቡ ጠንቅቆ ያውቃል:: ታዲያ ወያኔ ሕዝቡ አንድ ሁኖ እንዳይነሳ ለማድረግ የማይነፈቅለው ድንጊያ የለም:: ስለዚህ በወለጋ በጎጃምና በጎንደር በኩል ችግር መኖሩ አይዘነጋም::

5ኛ ኢሉባቦርና ከፋ፣ጋሞጎፋ ሲዳሞ ባሌ፣ እነዚህ ክፍለ ሀገራት ከውጭ ድንበር አገር ጋር ይገናኛሉ:: በዚህ በተያዘው የዘር ክፍፍል ምክንያት የውጭ ኃይሎች ለጥቅማቸው ሲሉ እየቀሰቀሱ ችግር ሲያመጡ ይልቹ ይሆናል:: የዛሬው ትውልድ ሆነ መጭው ትውልድ ካለፈው የኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርት ወስደን ልንጠነቀቅ ይገባል:: እነዚህ የውጭ ኃይሎች እስስቶች ስለሆኑ መምጫቸው አይታወቅም:: አንዴ በሃይማኖት በሌላ ጊዜ ደግሞ በንግድ አልያም ደግሞ በጎሳ እየከፋፈሉ ዳር ደንበራችን እንዲደፈር ለማድረግ ይመኛሉ:: ስለዚህ እኛ



ማድረግ ያለብን ጉዳይ ቢኖር በንግድ ሆነ በሃይማኖት አልያም ደግሞ በጎሳ አመካኝቶ ከወገኖቻችን ጋር ሊያጋጩን የመነሳው ለእኛስ አዝኖ ሳይሆን ለራሱ ከእኛ ጥቅም ስላለው ነው:: ስለዚህ ሁላችን ነቅተን መጠበቅና አገራችን ማክበርና ማስከበር የያንዳንዱ ትውልድ ድርሻ ነው:: ስለዚህ ልብ ያለው ሸብ ነው እንደተባለው ሸብ ልናደርግ ይገባል::

6ኛ ወሎና ሸዋ፤አሩሱ ከውጭ ጋር የሚያገናኝ ድንበር የላቸውም:: በተለይ ወሎ በአጤው አስተዳደር ወቅት ቢሆን እንደ ቀደሙ የአሰብ የራስ ገዝ አስተዳደር ስለተጀመረና በደርግም ይህ የአሰብ ራስ ገዥ አስተዳደር ተጠናክሮ ስለነበር ማሀል ሆኖአል:: ሸዋ አርሲ ከውጭ ማለትም ዓለም አቀፍ ድንበር ጋር አይገናኙም:: ለዚህ ሳይሆን አይቀርም አንዳንድ ግለሰቦች የማሀል አገር ተወላጆች ደንበርን አስመልክቶ ግድ የሌላቸው ናቸው:: ይህ እምነታቸው ብዙ ዘር እየዘሩ የጠላት ተባባሪ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ደንበር ብሎ የሚጮኸውን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ቅስም የሚሰብሩ ናቸው:: በዚህ በደንበሩ ጉዳይ ብዙ ግለሰቦች መግለጫ ሰጥተዋል:: ብዙ ድርጅቶች ተንገብግበዋል:: አንዳንድ ግለሰቦች ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን እነሱ የሚመሩትን ድርጅት ወይም ደግሞ ለሚሰማቸው ሰው የሚያሰሙት ወሬ ከጠላት ጋር የሚያስወግናቸው ነው::

አንባቢያን የአገር ጉዳይ የአንድ ክፍለ ሀገር ብቻ ሳይሆን የሁሉም ነው:: አንድ ተረት አለ ያም "ሁለት ሰዎች ተኝተዋል ታዲያ ጅቡ የአንዱን እግር ሲበላው ሌላው ሰምቶ ምን ነው የሚያንፈንፈው ሲለው ዝም በል ጅቡ አንድ እግሬን እየበላው ነው" አለው ይባላል:: ጅቡ አንድ እግሩን ጨርሶ ወደሌላው እግሩ እንደሚሄድ አልገባውም:: የኢትዮጵያ ጠላቶች የሚፈልጉት ልዩነት ነው:: ተራ በተራ ካስጠቁ በኋላ ድል ያደርጋሉ:: ይህን የኢትዮጵያን ጠላቶች ተንኮል ለምን አንዳንድ ግለሰቦች እንዳልተረዱት አልገባኝም:: ተመልከቱ ዛሬ ደንበርን በተመለከተ ስታወሩ አድማጭ የላችሁም:: ከፋፋዮች በግል ጥቅም በቂም የተያዙ እርቀው የማያስቡ ናቸው:: ጠላቶቻችን የሚፈልጉት ይህን አይነት ሴራ ስለሆነ ከልብ ልታስቡበት ይገባል:: በታሪክ ሁሉንም ነገር ጠቅልሎ ለቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ስለተሰጠ እንጂ "አገር የጋራ ነው፤ ሃይማኖት የግል ነው" የሚለው መፈክር የተናገሩ (አጤ) ልጅ ኢያሱ ሚካኤል ናቸው:: ስለዚህ ይህን የአጤ ልጅ ኢያሱን መፈክር "አገር የጋራ ነው፤ ሃይማኖት የግል ነው" የሚለው ማክበር ይኖርብናል:: ስለዚህ ዳር ደንበር የሁላችን ናት ብሎ መነሳት ይኖርብናል በ1968-69 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቤቱን ዘግቶ ልጆችን ለርሃብ ትቶ የዘመተው ለአጋዴ መሆኑን ማጤን ይኖርብናል:: ባድሜን ተዋግቶ መልሷል:: ዛሬም ሁመራና መተማ ጋንቤላ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሬት መሆኑን መረዳትና ከዚህ በፊት የነበረው ዓይነት ትብብር ያስገልጋል::

አገርና ሃይማኖት አንድ አይደለም:: ኢራክና ኢራን ያን ያክል ደም የተፋፉሱት የመሬት ጉዳይ ሁኖባቸው እንጂ ሃይማኖታቸው ሁሉም እስላሞች ናቸው:: አንዳንድ ጠባብ ግለሰቦች በሃይማኖት ተሳበው አያገባንም የሚሉት ምክንያት ከአገር ጋር ሊገናኝ አይችልም:: ስለዚህ በጥሞና ማሰብና አገር የጋራ ነው የሚለውን መፈክር ይዘን ለአንድነት መነሳት አማራጭ የለውም::

## ምዕራፍ 4

## ይድረስ ለድርጅቶች

<u>መምሕር አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ</u> ታህሳስ 26 ቀን 2001 ዓም ሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ወንጌል ሲሰብኩ ብዙዎችን አስቀሰሱ። እርሳቸው "አደራችሁን የማንም ፖለቲካ ድርጅት ለመደገፍ አይደለም። በጎች እንኳ ሊያጠቃቸው ከመጣ አውሬ የሚድኑት ትንንሾችን ማሀል አስገብተው ትልልቆች ዳር በዳር ከበው በኩርሚያቸው እየገፉ አያስቀርቡትም። ችግሩ የሚመጣው እንደ በግ ሩጣ ከወጣች ነው። በእኛም አገር የቸገረው ሕብረት ማጣት ነው። ለ34 ዓመታት አንድ ባንድ እየተመረጠ እየተበላ ነው ከመበላት ለመዳን ቅድሚያ እኛ ሕብረት ሊኖረን ይገባል" ሲሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማገናኘት በኢትዮጵያ የተፈጠረውን ዘርዝረው ለ48 ደቂቃ አስተምረዋል። በዚህ ቀን እርሳቸው አንድ ጥያቄ ምዕመናኑን ጠየቁ "ለሀገራችን ሆነ ለሕዝባችን ሰላም ለማምጣት ቅድሚያ ምን ማድረግ አለብን? ብለው ሲጠይቁ ምዕመናኑ በአንድ ድምጽ "ከራሳችን ጋር እንታረቅ ከአ እንጀምር" የሚል መልስ ይሰጣል። መምሕርም ቀጠል አድርገው "ከራሳችን መታረቅ ከፈለግን ስንቶቻችሁ ናችሁ ለስጋ ወደሙ የተዘጋጃችሁ" ብለው ሲጠይቁ አንድም የለም። የተረዳሁት ጉዳይ ቢኖር ከእኛው ጋር ካልታረቅን ወደ ድርጅቶች መግባቱ አስፈላጊ አይመስለኝም።

አቶ ስዩ አብርሃ <u>አዲስ ነገር</u> ጋዜጣ 2000 ዓም "ሻዕቢያ በእኛ ውስጥ ችግር በተፈጠረ ቁጥር ከዚያ ትርፍ ለማግኘት እችላለሁ ብሎ የሚጎተተው ገመድ ካለ ጣልቃ ሊገባ ይችላል። ራሱ የኢትዮጵያ ፖለቲካ አያያዝስ ለእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ምቹ ሁኔታን እየፈጠረ አይደለም ወይ? የራሳችንን ችግር በመግባባት ብንፈታ የውጭ ኃይሎች ዕድል አያገኙም ነበር" ሲሉ ተናግረዋል። በትጥቅ ትግል ብዙ ደም ፈሷል። ብዙ ሕዝብ አልቋል። ብዙ ሰው አገሩን ጥሎ ተሰዷል። ብዙ የምጣኔ ሀብት ኢኮኖሚ ወድሟል። የጎረቤት አገሮች ነፃ ጉልበት አግኝተዋል ንብረቱን በርካሽ ገዝተው ተጠቅመዋል። ሕዝቡን እያስተናገድን ነው ብለው ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ገንዘብ እየተቀበሉ ሀገራቸውን አዳብረዋል። በሕይወቴ ያየሁት ነገር ቢኖር በመጽሔት ሆነ በመጽሐፍ ያልተጻፈ በጎንደር ክፍለ ሀገር በጎንደር ዙሪያ አውራጃ ላይ አርማጭሆ ወረዳ በ1971 ዓም የ21 ቀን ጦርነት ሲደረግ ነበርኩኝ። ቤቶች ተቃጥለዋል! በዚህ ሰዓት ሳይቃጠል የቀረ ቢኖር ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሲሆን የወደመው ንብረት ብዛት የሚያውቅ ያለ አልመሰለኝም። የአካባቢው ሁኔታ ሕዝቡን ለችግር አጋልጦ ሰጥቶታል። የቤት መስሪያ እሳር በግንቦት አይገኝም። ቤት የተቃጠለበት ሕዝብ ክረምት ዝናቡ ሲሄድበት ከርሟል። የመጣው የደርግ ጦር ድርጅቶችን አስጠግታችሁል በማለት ቤቱን ሲያቃጥል እህሉ አብሮ ወድሟል! የሚበላ ጠፍቶ በሰኔ ጫብሴ የሚባል ከመሬት ተምሶ የሚወጣ ስር



ሲበላ ተከርሟል። ይህ ጫብሴ የሚባለው ስር ቅድሚያ ተቀቅሎ ተከትፎ ከወራጅ ውሃ ላይ ተጥሎ ቢያንስ 3 ቀን ውሃ ከሄደበት በኋላ ተቦክቶ እንደ ቂጣ ተጋግሮ ይበላል። ሌላው ስር ስሙ ጠፋኝ እንጂ ተምሶ ሲቀቀል እንደ ድንች ይሆናል። ይህ ሲበላ ከርሟል። ይህን በዓይኔ ተመልክቻለሁ።

ይህ ሕዝብ በርሃብና በዝናብ ሲሰቃይ የከረመው የትጥቅ ትግል በመኖሩ ነው! እኔ የጠቀስኩት የዓይን ምስክር በነበርኩበት ወቅት ያየሁትን እንጂ ሌሎችም በኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት ውስጥ ብዙ ጦርነት ተድጓል። ታዲያ ዛሬም የሚዜመው ተመሳሳይ ሁኔታ ነው። በእርግጥ የትጥቅ ትግል የመረጡትን ድርጅቶች ልፈርድባቸው ባልችልም የተሻለ ትግል ምርጫ የለም ወይ? ሰላማዊ አመጽ ባንዴ የሚመጣ አለመሆኑን ለምን አልተረዳነም። ሕዝቡን በአንድነት ቄሱም ሸሁም ነጋዴውም አሽከርካሪውም አብራሪውም መስሪያ ቤቶችም ጽፈት ቤታቸውን እንዳይከፍቱ ሁሉም ከቤቱ እንዲውል የዚህ ዓይነት ሠላማዊ አመጽ ቢደረግ ወያኔ ሌላው ቢቀር አፈናውን ሊያቆም ይችላል። አገር እየቆረሰ መስጠቱን ሊተው ይችላል። ከላይ መምሕር አባ ገብረ ሥላሴ እንዳሉት "ችግሩ የሚመጣው እንደ ሩጣ ከወጣች ነው" ያሉት የዚህ አይነት አድማ ለማድረግ ሲታሰብ እንደ በጓ አንዱ አፈንግጦ እየወጣ ሕዝቡን ያስደበደበው መሆኑን የወያኔን መንግሥት ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ ነን ከሚሉትን የዚህ ዓይነት የጥቅም ሰዎች እንዳሉ አረጋግጠናል።

ሠላማዊ ትግል በሩ ክርችም ብሎ ተዘግቷል ይላሉ። በእኔ እምነት ክርችም አድርገው የዘጉት ራሳቸው እንመረሃለን የሚሉት ግለሰቦች ቆራጥነት ስለጎደላቸው ነው። ክህደት ሰላበዙ ነው። የሥልጣን ሱስነት ስለተጣባቸው ነው! ወያኔን ዘረኛ እያሉ እነሱ ከወያኔ የበለጡ ዘረኛ በመሆናቸው ነው። ለሕዝቡ የገቡትን ቃል ኪዳን መፈጸም ሲሳናቸው ነው። አሁንማ ታስሮ መፈታት ጀብድ ሁኖአል። ለውጭ አገር የሞኖሪያ ፈቃድ ማመልከቻም ተቃዋሚ ድርጅት በመሆኔ ታስሬ ነበር እየተባለ ነው። ታዲያ እንዴ ተጀመረና ተደከመ? አታጋይ ይሉሃል ይህ ነው። በእውነቱ ሊቀ ጠበብት መስፍን ወልደማርያም "ሰላማዊ ትግል አልተጀመረም" ያሉት ትክክል ናቸው። ዳኛ ወ/ት ብርቱካን ዴሚቅሳም "ሰላማዊ ትግል ተጀመረ እንጂ አልተፈጸመም" ያሉት ለዚህ ነው። በገቡት ቃል መሰረት እንሆ በወያኔ ወሕይን ቤት እየተንገላቱ ናቸው። ምናልባት ከዚህ በፊት በሌሎች ግለሰቦች የደረሰው የሞራል ድክመት በእርሳቸውም እንዳይደርስ አእምሮ ሰባራ ሁነው የገቡትን ቃል ኪዳን እንዳይሰብሩት አደራ እላለሁ። ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዱን ግባ ባለው አለ እንደተባለው መጠንከር አለባቸው። አቶ ስዬ አብርሃ "በእኔ እምነት የሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል አማራጭ በኢትዮጵያ ተጀምሯል እንጂ አላለቀም። ሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግልን ከመንግሥት ለውጥ ባሻገር ነው ማየት ያለብን። የትጥቅ ትግል መንግሥትን ለመቀየር ያስችል ይሆናል፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዐትን በቦታው ለማስቀመጥ የተረጋጋ ማኅበራዊ ኑሮን ለመፍጠር ግን የሚያስችል አይደለም" ሲሉ አቶ ስዬ አብርሃ ተናግረዋል።

ልዑል እግዚአብሔር ይህን ዓለም ከፈጠረ በኋላ በሰማይ የሚበሩ የማይሞቱ የማይታመሙ የማይጨበጡና የማይዳሰሱ ቅዱሳን መላእክትን ፈጠረ። የእነዚህን ቅዱሳን መላእክታን ቁጥር የሚያውቅ የሥነ መለኮት ሊቅ እንዳለ እንጃ እኔ አላውቅም። እንደባባላቸው ግን የመላዕክቱ አለቃ ሳጥናኤል ይባል እንደነበር ያስተምራሉ። ሳጥናኤል ከሁሉ በላይ መሆኑን በመረዳቱ እኔነኝ የፈጠርኳችሁ ብሎ ይነሳል። በዚህ ወቅት ቅዱስ ገብርኤልና ቅዱስ ሚካኤል ሌሎችን መላዕክት አስተባብረው የፈጠረን አምላክ ሳጥናኤል ሳይሆን እግዚአብሔር ነው። ለአሁኑ በአካባቢያችን ባይኖርም እስኪመጣ ድረስ ባላችሁበት ርጉ ቢሉም ሌሎች የእነሱን ትዕዛዝ ከመስማት ይልቅ የሳጥናኤልን ትዕዛዝ በመስማታቸው ምክንያት ከሁለት ይከፈላሉ። በዚህ ወቅት ጦርነት በሰማይ ላይ ይሆናል። ሳጥናኤል ድል ይሆንና ከክብሩ ይባረራል። ስሙም ከሳጥናኤል ወደ ሰይጣን ይቀየራል። ሰይጣን ብቻ ሳይሆን ጋኔን፣ ርኩስ መንፈስ፣ ዲያቢሎስ፣ ሌላም ሌላ ተብሎ ይጠራል። ይህ ከዚህ በላይ ያነበብነው ትንሽ ስለ ሰይጣን ለምን እርሱ እኔ ፈጠርኳችሁ አለ? ወደሚለው ስንመጣ ለዚህ ትቢት ያበቃው ስልጣን በመፈለጉ ነው። ስልጣን የፈለገ ሴት ሆነ ወንድ ካህን ሆነ፣ወታደር ሌላም የሰው ልጅ ሁሉም የሰይጣን ትዕዛዝን እየሰራ መሆኑን መጽሐፍቱ ይናገራሉ። ለዚህም ነው በዚህ በመላዕክት ጦርነት ወቅት ተይዞ ታስሮ የነበረው ሰይጣን ወደ መሬት የተጣለ።

<u>የዮሐንስ ራዕይ</u> 6.12 “ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጉር ሆነ፤ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፣ በለስም በብርቱ ነፋስ ተናውጣ ቃርያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ” ሲል ጽፏል። እነዚህ ወደ ምድር ወደቁ የተባሉት ሰይጣናት ናቸው። እነዚህ ታስረው የነበሩ ሰይጣን ከቅዱሳን መላዕክት ጋር ታግለው ጥቃት ስለደረሰባቸው ወደ ምድር ተጣሉ። የቅንጅት ባለሥልጣኖች የተጣባቸው የስልጣን ስግብግብነት በራሳቸው ተጣልተው ተበታተኑ። እነሱ መበታተናቸው ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ “ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ” ብሎ ያስተባበራቸውን ሌሎችን ሕዝቦች ሳይቀር በታተኗቸው። እኔ እገሌ ቅዱስ እገሌ እርኩስ አልልም ነገር ግን ሁሉም ረክሰዋል። የሕዝቡን አንድነት በትነዋል። ለአንድ ዓመት ያክል የተጻጻፉትን የስም ማጥፋት ወረቀት ማንበብ ይዘገንናል። ከላይ ለምሳሌ የሳጥናኤልን ክብር እንደገለጽኩት ሁሉ እነዚህ የቅንጅት መሪዎች ታስረው በነበሩ ወቅት በተለይም በውጭ አገር ያለው ኢትዮጵያዊ ፀሐይ፣ ዝናብ፣ ቀን ጨለማ፣ ሳይል እንዲፈቱ የጮኸው ሊከፋፍሉት አልነበረም። የተፈታው ሰይጣን ዛሬ በዓለም ላይ ሰላም እንደነሳው ሁሉ እነዚህም ከእስር የተፈቱት ወገኖቻችን ሰላም አልሰጡም በእርግጥ ሰላም ማምጣት ይቻላል ያም ይቅር መባባል ሲኖር ነው።

የኢትዮጵያ የሥነ መንግሥት ፖለቲካ ድርጅቶች ለማን እንደቆሙ የተረዱ አልመሰለኝም። አንዱ ሥህተት ይፈጽማል። ሁለቴ ይደገማል ሶስቴ ይሰለሳል። የኛው የሥነ መንግሥት ፖለቲካ ድርጅቶች የአገር ጉዳይ ሳይሆን የግል ማህበር አድርገው ማየት ከጀመሩ ከራርመዋል። ሌላው ትልቁ ቁምነገር ለምን እንደቆሙና ለማን እንደሚሰሩ አንዳንዶቹ የተረዱ አይመስለኝም።



ምክንያቱም አገሪቱ ከሌሎች ሕዝቡ ከሌላ ለማንና ለምን እንደሚታገሉ አልተረዱም። ዘመኑ ያመጣው የድህረ ገጽ (ወይብ ሳይት) ላይ መግለጫ መስጠት ትግል ከሆነ አርፋችሁ ቁጭ በሉ። ወያኔ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘርና በሃይማኖት ለያይቷል ትላላችሁ እናንተስ ብትሆኑ እርሱ ከሚሰራው የተለያችሁበት ምንድነው? ልዩነታችሁ ወያኔ በመሰሪያ አስገድዶ ጠበንጃውን ወድሮ መግደል ሲሆን የናተው ደግሞ በዘር እያጠዛችሁት ነው? ተመልከቱ ውሾች አጥንት ሲያገኙ እኔ እግጥ እኔ እግጥ ሲናከሱ ሲዳሙ ይውላሉ። ነገር ግን ጅብ ሲመጣባቸው ሁሉም አጥንታቸውን ጥለው የጋራ ጠላታቸውን ለማጥቃት ይተባበራሉ። የግል ጠላታቸውን በሕብረት ከመለሱ በኋላ ወደ አጥንት ጠብ ይገባሉ። የኢትዮጵያ ታሪክ ያስተማረን በሥልጣን ምክንያት ይጣላሉ ነገር ግን ጠላት አገራቸውን ሊነጥቃቸው ሲመጣ ተባብረው ያጠቃሉ ይህን ታሪክ የዛሬው ትውልድ ሲሸረው ይታያል። በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘመን ደጃዝማች ጓንጓል የሚባሉ የወሎ ባላባት ሸፍተው አውሳ በርሃ የገቡ ነበሩ። ጣልያን ኢትዮጵያን ሊወር በ1888 ዓም ሲመጣ እኒህ ደጃዝማች ለአጤ ምኒልክ የይቅርታ ደብዳቤ ጽፈው አብሬ ልሙት ብለው የገቡና የአድዋን ድል የተጎናጸፉ ናቸው።

ጳውሎስ ኞኞ <u>አጤ ምኒልክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 167 “ደጃዝማች ጓንጉል ዘገየ በአጤ ምኒልክ ላይ ሸፍተው ከምኒልክ ጭፍሮች ጋር በጦርነት የተፈታተኑ ናቸው። በዚህም በትግራይ ዘመቻ ጊዜ በምኒልክ ላይ እንደ ሸፈቱና በረሃ እንደገቡ ናቸው። ምኒልክ 24 ቀን መርሳ ላይ ሠፍረው ሳሉ የደጃዝማች ጓንጉል መልክተኛ ከአጤ ምኒልክ ዘንድ መጣ። መልዕክተኛውም ጃንሆይ ከእርስዎ ተጣልቼ በረሃ ገብቻለሁ። አሁን ግን በአገሬ ላይ የውጭ ጠላት ስለመጣባት የርስዎና የኔ ጉዳይ ቀርቶ ይማሩኝና መጥቼ ከእርስዎ ጋር ሆኜ ያገሬን ጠላት ልውጋ ብለዋል ብሎ ተናገረ። አጤ ምኒልክም ተደስተው ይምጣ ምሬዋለሁ ብለው ላኩ። ደጃዝማች ጓንጉልም መጥተው ካጤ ምኒልክ ጋር ተገናኙ። ሠራዊቱም በእንደዚህ ያለ ጊዜ መጥቼ ከጌታዬ ጋር ልሙት በማለታቸው እግጅ ተደነቀ” ሲሉ ጽፈዋል። (አጤ)ልጅ ኢያሱንና ቤተሰቦቻቸውን አጤ ኃይለ ሥላሴ መግደላቸውና ማሳደዳቸውን በሚመለከት ሰንድ ማገላበጥ አያስፈልግም። ነገር ግን የ(አጤ) ልጅ ኢያሱ ልጅ ማለትም ልጅ ዮሐንስ ኢያሱ ለአባታቸው ገዳይ ለአጤ ኃይለ ሥላሴ ለንደን ሳሉ ይጽፉላቸው ነበር። ልጅ ዮሐንስ እያሱ የኢጣልያንን ጉዳይ በተመለከተ ሰፋ አድርገው ነው የጻፉላቸው።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ <u>ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ</u> ቅጽ ሁለት ገጽ 152 “ግርማ ሆይ!እንዲሁ ያሉትን መረጃዎች የምንልክልዎት አንድን ሕዝብ ግፍ እንዳይደርስበት ጠባቂ ለሆነው የዓለም ማኀበር አባል አገሮችና እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጅ አገሮች ለሆኑት ሁሉ እርዳታቸው እንዳይለየን እንዲገልጹላቸው በማለት ነው። ፍጹም ትሑት አሽከርዎ፥ፈርማ፥ ዮሐንስ ኢያሱ ሐምሌ 18 ቀን 1930 ዓም” ሲሉ ጽፈውላቸው ነበር። ጽፈዋል። ልጅ ዮሐንስ ኢያሱ ከአባታቸው ገዳይ ጋር ደብዳቤ የሚጻፉት አገራቸውን ከአባታቸው አብልጠው በመውደዳቸው ነው።

ልጅ ዮሐንስ ኢያሱ በጎንደርና በወሎ 56 ደጃዝማች ብለው ጣልያንን የወጉና ያዋጉ ጀግና አቤ ኃይለ ሥላሴ ከሉንደን ሱዳን ካርቱም ሲገቡ ቅድሚያ ለመያዝ ያሰቡት ልጅ ዮሐንስ ኢያሱን ነበር። አሜድላ ሲደርሱ ልጅ ዮሐንስ እንዲመጡ ተልከባቸው ደብረ ማርቆስ ተገናኙ ከዚህ ግዜ ጀምሮ በግዞት ኑረዋል። ሌሎች ባንዶች አገርን ከወራሪ ጋር ሁነው የጎዱና ሕዝብን ያስጎዱ ወዳጅ ሲሆኑ ልጅ ዮሐንስ እያሱ ግን እንደ ጠላት ታስረው ኖሩ።

የልጅ ዮሐንስ ኢያሱ እና የደጃዝማች ጓንጓል አገር ወዳድነት ዛሬ ላለነው ኢትዮጵያውያን ልንከተለው የሚገባን ነው። ለምሳሌ ወያኔ በሻዕቢያ ሲወረር አያገባነም ያሉ ደግኖች ነበሩ። ለዚህም አስመራ ድረስ የሄዱ የአገርን አንድነት እንዲናድ የተባበሩ ናቸው በዚሁ ዘመን በኢትዮጵያ ርሃብ ገብቶ በነበረበት ወቅት ሕዝቡ ወገኑን ለመርዳት ሲያስብ እነዚህ ዓይነት ግለሰቦች ሕዝቡ ርዳታ እንዳያደርግ ቅስቀሳ ሲያደርጉ ነበሩ ዛሬ ደግሞ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ወያኔ ለሱዳን ሊሰጥ ነው ሲባል አያገባንም ያሉ የድርጅት አሉ። የአቶ የኢያሱ ኢሕአፓ አባል የሆኑ ሰው ለአገሩ የሚንገበገብ ግለሰብ ከሰርግ አግኝቶ ሰላም ካላቸው በኋላ "የደንበሩን ጉዳይ እንዴት ተመለከትከው ሲላቸው የኢሕአፓው መሪ መልሳቸው እናንተ ጎንደሮች የራሳችሁ ሲነካባችሁ ትንገበገባላችሁ" በማለት ተናገሩ። እኒህ ግለሰብ በጎንደር ላይ ግዜያቸውን ያሳለፉ ወላጆቻቸውም ጎንደር የነበሩ ናቸው። አልገባቸው ብሎ እንጂ ጎንደሬዎች ጨኸታቸው ለኢትዮጵያ አንድነት እንጂ ለጎንደር ብቻ አስበው አያውቁም። ወያኔ አዲስ አበባን በመያዙ የደርግ መንግሥት ሠነድ ተቃጥሎአል ብለው ካልሆነ በቀር በ1969 ዓም አጋዴን ለማዳን በሬውን እየፈታ ልጆቹን በትኖ የዘመተው ጎንደሬ ዛሬ ማንነቱን በካደ ግለሰብ ሊሰደብ አይገባውም። ጎንደሬዎች እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለዳር ደንበራቸው የታገሉ ናቸው። ሻዕቢያ ባድሜን ሲይዝ ወረራ በመሆኑ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር አብረው ዘምተዋል። በኢትዮጵያ የሚመሰረተው ድርጅት በራሱ ድክመት እየጠፉ አስቸገረ እንጂ ጎንደሬዎች ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጋር ለሠላም መተባበራቸው አይካድም።

በአሜሪካን አገር ብዙ መቶ ሺህ ኢትዮጵያውያን እንኖራለን። ታዲያ የኢትዮጵያውያን ከቤተ ክርስቲያን በቀር በኢትዮጵያ መረዳጃ ማሕበር ሥም የተከራየነው ካልሆነ በቀር ሕንጻ አልገዛነም። ታዲያ በሲያትል የጎንደር እድርና መረዳጃ ማሕበር የራሱ ሕንጻ አለው። ይህ መረዳጃ ማሕበር ለቅንጅት መሰብሰቢያ አዳራሹን ሰጥቶ እንዲገለገሉበት አድርጓል። የማሕበራቱ አባላት ከቅንጅት ሆነ ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅት ውስጥ በአባልነትና በደጋፊነት ገብተው የሚታገሉ መሆናቸው ተረስቶ "እናንተ ጎንደሮች የራሳችሁ ሲነካባችሁ ትንገበገባላችሁ" በማለት ተናገሩ። ጎንደሬዎች ያለ ኢትዮጵያ ሕልምና ምኞት በቀር ሌላ አሳብ የለነም። ባይሆን እንከባበር መናናቅ ይቅር ከሆነ አዎ እንላለን። ይህን በተመለከተ ሠነድ ጠቅሶ ዘርዝሮ መጻፍ ይቻላል። ስለዚህ የድርጅት መሪዮች ንቀታችሁን ተውን የምትፈልጉን ለስብሰባ ማዳመቂያ ሳይሆን የሀገራችን ችግር የሁሉ መሆኑን ልትረዱ ይገባል።



የቀድሞ ጠ/ሚኒስትር ሚካኤል እምሩ ኢትዮጵ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 045 መጋቢት 1995 ዓም ገጽ 8 "እነዚህ ከእንዲህ አይነቱ አደረጃጀት ነፃ ወጥተው መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያጠቃልል አመለካከትና አድራጎት ተቀዳጅተው በአንድነት ካልተንቀሳቀሱ በስተቀር የኢትዮጵያን ሕዝብ ተስፋ ሊያሟሉ አይችሉም" ሲሉ ከመጽሔቱ ጋር ባደረጉት የመጨረሻ ክፍል ተናግረዋል። ይህ ከፍተኛ የሕዝብ ቅስቀሳ ተደርጎ በድረስ ድረስ ቅንጅት ተመስርቶ ምርጫ 1997 ዓም ውጤት ማምጣቱ አይዘነጋም። ቅንጅት ተመስርቶ አብረው የተሰለፉት በአንድ ዓላማ ሁነው ሊሰሩ አለመፈለጋቸውን ሠነዶች ዋቢ ናቸው። መልመድና መለማመድ ያለብን ነገር ቢኖር በውይት መተማመን ነው። በዚህ ወቅት በአቶ ልደቱ አያሌውና በእንጅነር ኃይሉ ሻውል በኩል ከሮ አለመግባባት ፈጥሮ የነበረ መሆኑን የተጻፈውን መጽሐፍት ማንበብ ይቻላል።
ዶ/ር ብርሃኑ ነጻ የነፃነት ጎህ ሲቀድ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 485 "በተለይ በልደቱና በኢንጅነር ኃይሉ መካከል ማን ምን ቦታ ላይ ይሁን በሚለው ጉዳይ በተፈጠረው ያለመስማማት ብዙ ወርቃማ ጊዜዎችን ያለ ሥራ አሳለፉ። ቅንጅቱ ለሚጠብቀው ሰላማዊ ትግል በቅጡ መዘጋጀት የነበረበትን ጊዜ በአመራር አካባቢ በተፈጠረው ክፍተትና ከአመራሩ በታች ያለነውን የድርጅት አባላት አስተባብሮ ማሰራት ባለመቻሉ ለተወሰነ ጊዜ ሽባ ሆነ" ሲሉ ጽፈዋል። ዛሬ ቅንጅት የነበረውን ተሰሚነት እንዴት ሊያጣ ቻለ? ቅንጅትን በተመለከተ እንዴት ተቋቋመ እንዴት ፈረሰ ለሚለው ብዙ መጣጥፎች ወጥተዋል። ብዙ መጽሐፍትም ታትመዋል። በእርግጥ እነዚህ መጽሐፍት መታተማቸው ለወደፊቱ ስህተት እንዳይደገም ትምህርት የሚሰጡ ናቸው። ቅንጅትን አስመልክቶ የተጻፉት መጽሐፍት ከእጄ የገቡት እነዚህ ናቸው።

እስክንድ ነጋ ምርጫ 97 መረጃና ትንታኔ 1997 ዓም
ልደቱ አያሌው ታህሳስ 1998 ዓም የአረም እርሻ
ማርቆስ ረታ ጥር 1998 ዓም የልደቱ ባንዳዊ ስሌት
ክፍሉ ታደሰ ግንቦት 1998 ዓም ግንቦት ሰባት
ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ግንቦት 1998 ዓም የነፃነት ጎህ ሲቀድ
ታምራት ታረቀኝ ጥቅምት 1999 ዓም ማንነት ሲጋለጥ ከመፀሐድ እስከ ቅንጅት
ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ሥላሴ ታህሳስ 2000 ዓም ቅንጅት ከየት ወዴት
ደበበ እሸቱ ታህሳስ 2000 ዓም የእምነቴ ፈተና
ታምራት ቢ ስመኝ 2000 ዓም "የዲሞክራሲ መሠረቶች በኢትዮጵያ የዓላማ አንድነት ለድል ወሳኝ ነው " ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መጽሐፍት በቅንጅት ወቅት የነበረውን ደካማና ጠንካራ ጎን ገምግመው ጽፈዋል። እኔ እንደተረዳሁት እነዚህን መጽሐፍት በጥሞና ማንበብ ይጠቅማል በተለይም በሥነ መንግሥት በፖለቲካ መሪና አደራጅ የሆነ ሰው ሊማርባቸው ይችላል። ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መጽሐፍ ማንበብ የሚረዳው ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓም አዲስ አበባ ላይ የተፈጠረውን መድረክ እንዲጠነክር ትምርት ይሰጣል። አዲስ የተመሰረተው መድረክ ከቅንጅት መፍረክረክ ምን ሊማር ይችል ይሆን?።

# ምዕራፍ 5

## የኢትዮጵያ ምሁራን

ዲያቆን በረሁን ወንድወሰን እስራት እንዳይፀናባችሁ አታፊዙ በተባለው የስብከት ክራቸው“ አንዳንድ ሰዎች መሰልጠንን መሰይጠን አድርገው ወስደውታል። ለምሳሌ መሰ+ወደ መስ ለውጠውታል” ሲሉ አስተምረዋል። እኒህ የወንጌል ሰባኪ የኢትዮጵያንን ምሁራኖችን ጠባይ ተረድተውታል።እኔ የምመለከተው የነበረው እነዚህ የሰየጡትትን ምሁራን ከፋፋይነታቸውን ለጥቅም ሲሉ መነታረካቸውን ነበር። ከመሰልጠን ወደ መሰይጠን መለወጣቸውን አልተረዳሁም ነበር። እነዚህ ምሁራን ከመሰልጠናቸው ብዛት የሀገራቸውን ማንኛውንም ታሪክ ሆነ ሃይማኖት እንደባብ ልብስ ውልቅ አድርገው ጥለውታል። እነሱ መተዋቸው ባልከፋ ሌሎች እንዲተው መጣራቸው ሆነ መሰይጠናቸው የባሰን። ዛሬ ዘመናዊ ሊቆች ሳይሆኑ ከሀዲትና ዘረኝነት እያስተማሩ ያሉት የሃይማኖት አባቶች ጳጳሳትና ካህናት ዲያቆናት ናቸው። በዚህ ባሳለፍነው 17 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ(ኦርቶዶክስ) ተዋሕዶ ቤተ ክርስቶያን ያለውን ድክመት ሊክድ የፈለገ ካልሆነ በቀር እውነቱ የት ላይ እንዳለ የሚጠፋው ያለ አይመስለኝም።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት የተዘጋጀ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያፈረሱት አባ መርቆሬዎስና ተከታዮቻቸው በቅዱስ_ሲኖዶስ ተወግዘው ተለዩ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 15 “ከፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ አልተሾመም” የሚል ምዕራፍ ሳነብ ደነገጥኩ። ልባቸው እያወቀ አይናቸው እያየ እነዚህ ጳጳሳት ይህን መጽሐፍ አወጡ? ሰውን አይፍሩት ለእግዚአብሔር አገልግሎት የቆምን ነን የሚሉ ጳጳሳት ሲሳሳቱ ማየቱ ለእኛ ለልጆቻቸው ሀፍረት ነው። ይህን መጽሐፍ በጥሞና ሳነበብ ቤተ ክርስቲያን እንድትጠፋ የተፈረደባት በአባቶች መሆኑን ያመለክታል። ምክንያቱም እውነቱን የሃይማኖት አባቶች ከካዱት ሌሎች ምሁራንማ እንግዲያ ዓላማውያን ናቸው። ዛሬ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ጳጳሳት አብዛኛው ዘመናዊ ተማሪዎች ሲሆኑ ሰልጥነዋል። ከላይ ዲያቆን በሪሁን ወንደሰን እንዳሉት “ሰልጥነዋል ሳይሆን ሰይጥነዋል” ሊባሉ የሚችሁ ጳጳሳት ቤተ ክርስቲያን አፍርታለች። የክርስትናን ታሪክ ለሚመረምረው ለቤተ ክርስቲያን ጥፋት ምዕመናኑ ሳይሆን የተማሩ አባቶች ናቸው። እምነት አለኝ ባይ አባቱን ገዳይ ይድረስ ለጳጳሳት መቼ ይሆን ይህን በልግን አፍቅሮታችሁት የምትተውት?

የሐዋርያት ሥራ ም/ 20 ቁ/28 “ በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄዱሁ በኋላ ለመንጋው



የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ” ይላል። የሃይማኖት አባቶችን ለቀቅ አድርገን ወደ ዘመናዊው ምሁራን ስንመጣ ደግሞ የባሱ ናቸው።

ዶ/ር ላጵሶ ጌ ድሌቦ ኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 12 “አውሮፓውያን የፈጠራ ታሪካቸውን አስተማሩን የነፃ ትምህርት እድል ሰጡን። እኛም ያስተማሩንን አጠናን። ያንን ለሌሎች አስተማርን” ሲሉ ጽፈዋል። ለዚህም ነው አውሮፓውያን የሰየጠኑት “የሰው ልጅ ከዝንጀሮ የተወለደ ነው” ሲሉ አስተማሩ። ያንን ትምህርት ለሌሎች አደረሱት የኛም ምሁራን ተምረው ለሌሎች አደረሱ። አውሮፓውያን በተለይም ራሻ ዓለምን ያጭበረበሩበት “የራስን እድል መራስ ወሰን እስከ መገንጠል” የሚለው ከእነሱ ሳይሰራ የቀረውን ወደ አፍሪካ ወረወሩት። ሌሎች አውሮፓ እነሱ አንድ ሁነው የጋራ ገንዘብ ሲያወጡና ሕብረታቸውን ሲያጠናክሩ የአገሬ ምሁራን ይህን እየተመለከቱ መሻሻል ሲያደርጉ አይታዩም። እንዲያውም ይባስ ተብሎ ልዩነቱ በከፍተኛ ደረጃ በመስፋፋት ላይ ነው። የሀገሩን ክብር ማስጠበቅ የሚችል ራሱ ሕዝቡ መሆኑን ቅድሚያ ምሁራን መረዳት አለባቸው።

አሰፋ ጫቦ ዜጋ መጽሔት 2ኛ ዓመት ቁጥር 8 ሚያዝያ 1993 ዓም ገጽ 24 “ትናንት በኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና አይበገሬነት በጦር ሜዳው የበላይነታቸውን ያጡ ነጮች መልካቸውን በመቀየር እኛን መስለው በመግባት ሕዝቡን ከፋፍለው ለመበቀል ባላቸው ፍላጎት አስፈፃሚ በሆኑ መሪዎቻችን መጥተውብናል” ሲሉ ጽፈዋል። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ለስም ግብረ ሰናድ ድርጅቶች ቁጥር ብዙ ነው። ታዲያ ሕዝብ ሳይሆን የሚረዱ የሕዝቡን ባሕላዊ መተባበር ሳይቀር ለማላላት ጥረት እያደረጉ ነው። ተመራማሪ ነን ባዮች ዛሬ የትምህርት መመረቂያቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ባህላዊ ቁሳቁስ ላይ የተመሰረተ ነው። በተለይ በአማራው ባህልና በተዋሕዶ ሃይማኖት ላይ ለምሳሌ በአማራው ባህል ከዘፈን እስክታ ጀምሮ ልቅሶና እንጉርጉሮ ምኝ የእዝን መተባበርን ሳይቀር ዝበሬው በወበራ አብሮ ማረስና አብሮ ማረም ማጨድ ሳይቀር የአንድነት ማተብ በመሆን ይህን ሊቆርጡ ሲነሱ ሳይገባቸው አስተርጓሚና ተባባሪ የሆኑት ምሁራን ናቸው። ምሁራኖች ሁሌም በራሳቸው ማንነት የማይኮሩ በመሆናቸው ዜና እንኳን በአውሮፓውያን ዘጋቢዮች ካልተመዘገበ እውነተኛ ዜና መስሎ አይታያቸውም።

ታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓም አንዱን ወዳጄ ምሁር ስልክ መታሁና ቅድሚያ “እንኳን ለብርሃን ልደቱ ለጌታችን ለመዳህኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል በሰላም አደረሰም” ካልኩ በኋላ ባለ በሌለ የሀገራችን ጉዳይ ስንብተከተክ ቆየን። ከዚያ እኔ ከሁመራ እስከ ጋንቤላ ለሱዳን ሊሰጥ ነው የተባለውን መሬት በተመለከተ አልሰማሁም? ስል ጠየኳቸው። ምሁሩ “በአውሮፓውያን ጋዜጠኞች ያልተደገፈ በመሆኑ” አሉኝ። እኔም አውሮፓውያን ካላወሩት አይቀበሉም ማለት ነው?ስላቸው መልሳቸው “አዎ” አሉኝ። ሌሎች

አውሮፓውያን ጋዜጠኞች ያልመዘገቧቸውን ድርጊቶች ጠቅሼ ለማሳመን ብሞክር ሊቀበሉ አልቻሉም። ካልጠበኩት ምሁር የሰማሁት በመሆኑ ደነገጥኩ። የእኛ ምሁራን ገንዘብ ስላጠራቸው እንጂ ቢኖራቸው ኑሮ እንደ ከያኒ ማይክል ጃክሰን ነጭ ለመሆን ግዜ አይፈጅባቸውም ነበር። እግዚአብሔርም አውቆ ሰማዩን አርቆ እንደሚባለው ሁኖባቸው ለዚህ የሚያውሉት ገንዘብ የላቸውም። ከላይ ልክ ሊቅ ላጽሶ እንዳሉት አውሮፓ የተማሩትን ትምህርት ለኢትዮጵያውያን እያስተማሩ ናቸው። በዘርና በሃይማኖት ሕዝቡ እንዲለያይ ያደረጉም እነዚህ ምሁራን ናቸው።

<u>የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመናት</u> ትግልና የዘመናዊ ሥራዊት አመሰራረት 1855-1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 143 "ኮሎኒያሊስቶች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ አክብሮት ያላቸው ቢሆኑም በዚያው መጠን ጥላቻቸው ከፋ ያለ በመሆኑ ኢትዮጵያን ማዳከም ከተቻላቸውም ለመከፋፈል ወደኋላ ብለው አያውቁም። በበኩላቸው ለዚህ ስሜታቸውና ዕቅዳቸው የሚሰጡት ምክንያት ኢትዮጵያውያን እብሪተኞች አውሮፓውያንን የሚጠሉ እንደሌሉች አክብሮት አይሰጡንም። ከመጠን ያለፈ ሚዛን የሳደለው (ናሺናሊዝም) የሀገር ፍቅር ያደረባቸው ናቸው ወ.ዘተ..ለዚህ ሁሉ አስቸጋሪ ባህርይና ድርጊት በግንባር ቀደም ኃላፊው አማርኛ ተናጋሪውና ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን በአክራሪነት የሚያምኑ ወገን ነው የሚል እምነታቸውን ሳይደብቁ ጊዜና አጋጣሚ እየጠበቁ አማርኛ ተናጋሪውን ከሌሎች ጋር በማጋጨት በቅደም ተከተል ኢትዮጵያን ከመገዝገዝ ታቅደው አያውቁም። አዲሱ ዘዴ ብረትን በብረት በሚል ብልሃት በመጠቀም እርስ በርሳችን የማፋጀት አስተዋፅኦ አድርገዋል" ሲሉ ጽፈዋል። የኢትዮጵያ ዘመናዊ ምሁራን የቀድሞዎቹ የሚማሩት ሕዝብን የሚያገለግሉበት ትምህርት እንጂ እነሱ ቀጭ ብለው ሕዝብን የሚበድሉበት ትምህርት ተምረው የተመለሱት በጣም ጥቂት ነበሩ።

የዛሬው ግን ቅድሚያ የናቁት ባህላቸውንና ታሪካቸውን ፊደላቸውን ነው። ምናልባት ደጋግሜ ስለ ባህልና ታሪክ ይታሰብበት እያልኩ ስጽፍ ወድጄ ሳይሆን ፈርቼ ነው። ምክንያቱም ምሁራኖች ፈትኜ ስለተረዳሁ ነው። ሐምሌ 1 ቀን በ1991 ዓም ኳስ ጨዋታ አንድ የማውቃቸው ሊቀ ጠበብት ከሌሎች ምሁራን ጋር ቆመው ይጫወታሉ። ሁሉ ጉግሣ መጽሔት ሲገዙኝ ሊቀ ጠበብት "እባክህ አንተ ቄስ ነገር ስለሆንክ የቄስ ጹሑፍ ይሆናል የጻፍከው አልገዛም" አሉኝ። እኔም ጀመርኩት እንጂ አልቀሰስኩም። ዛሬስ ምነው ገጫቸበት በሆነ ያሰኛል ግን ስለማልችል ቄስ አይደለሁም የቄስ ጹሑፍም አልጻፍኩም" ብዬ ማብራሪያ ሰጥቼ ገዙኝ። ከዚያ በኋላ እንደገና በሰኔ 29 ቀን 1994 ዓም ዋሽንግተን ዲሲ የኳስ ጨዋ ላይ ከዘመድ ቤት ተገናኘንና ያላገኙትን እትሞች ሰብስቤ 8 መጽሔት ሰጠኋቸው።

እርሳቸው መጽሔቱን ሊወስዱት አልፈለጉም ኑሮአል። ከተቀመጡበት ወንበር ላይ ትተውት ሔዱ። እኒህ ሰው ምክትል ሚንስትር የደረሱ ናቸው። በዚሁ ቀናት ከኳስ ሜዳው ላይ ሌላም ምሁር ድክመት አስተዋልኩ። አንዱ ሊቅ ዶ/ር መጽሐፍ ገዝተው መጡና እኛ ከተቀመጥንበት ተቀመጡ። ወዲያው አንድ



ሰው መጽሐፍ ይዞ ይዞራል እኔ ስገዛ ተመለከቱ ምሁሩ "መጽሐፍ ማንበብ ትወዳለህ?" ሲሉ ጠየቁኝ እኔም እወዳለሁ አልኳቸው። ታዲያ ሊቅ ዶ/ሩ "ሰውየውን ስለማውቀው ገዛሁት አማርኛ ማንበብ አልወድም ለአንተ ይሁን" ሲሉ ሰጡኝ። እኔም አመስግኜ ተቀበልኩ። አንዴ ሊቀ ጠበብት ተሾመ ገብርኤል፣ ለዶክተር እገሌ መጽሔት ላክለት ብለው አድራሻ ሰጡኝና በተከታታ ላኩላቸው። ታዲያ አንድም ቀን ደረሰኝ ብለው ስልክ አልመቱም።

አትላንታ የኳሱ ጨዋታ ወቅት የኒህ ሊቅ ዶ/ር መጽሐፍ በገቢያ ላይ ውሎአል። እኔም ከሌሎች መጽሐፍ ከሚሸጡ ደራሲያን ጋር ምሳ ለምሳ እየተለዋወጥን ቆየንና ኋላ እኒሁ ምሁር መጽሐፍ ከሚሸጡበት ደረስኩ። እኔም ማንነቴን ገልጬ ከዚህ በፊት መጽሔት እልክላቸው እንደነበር ስነግራቸው ከራስ እስከ እግሬ ተመለከቱና "አንተ ነህ  አትመስልም ልጅ ሆንክብኝ" አሉኝ። በጥሞና ካስረዳኋቸው በኋላ ቀድመው እርሳቸው ፈረሙና ከፈል ብለው መጽሐፉን በጃቸው ይዘው ገንዘብ ሊቀበሉ ቋመጡ። እኔ" የራሴ መጽሐፍ አለኝ" ስላቸው ደማቸው ፈልቶ" በመጀመሪያ አንተ ክፈል ባለቤቴ ስትመጣ ተማክሬ እገዛሃለሁ። የአንተን መጽሐፍ ከዚህ ቀጭ አድርገዂው ሕድ" እንዳሳያት አሉኝ። እኔም ባለቤትዎ ሲመጡ እገዛለሁ ብያቸው ልሄድ ስል" እንዳሳያት መጽሐፉን ትተህው ሕድ" አሉኝና ትቼው ከሄድኩ በኋላ ለምን ተውኩላቸው አልኩና ከ5 ደቂቃ በኋላ ስመለስ ገልበጥበጥ እያደረጉ ሲመለከቱ ደረስኩና "ሊገዛ የሚችል መጽሐፍ ነው የአንተ መጽሐፍ $20 ሲሆን የእኔ ደግሞ $25 ነው ስለዚህ ልዩነቱን ከፈልና ውሰድ" አሉኝ ነገር ግን ባለቤታቸው አልተመለሱም ነበር።

አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች የተባለውን መጽሐፍ እንደታተመ ወዳጄ "ምሁራኑን ለመታዘብ ስለምትፈልግ እስኪ ለዶ/ሮች መጽሐፍ በያድራሻቸው ላክላቸው" አሉኝና የ110 ምሁራን አድራሻ ሰጡኝ። 110 መጽሐፍ ለ110 ሊቆችና ዶክተሮች ባድራሻቸው ላኩኝ። ከነዚህ መካከል ዶ/ር ፍቅሬ ቶለሳ ሂሳቡን ልከውልኛል። ከነዚህ ከ110 መካከል አንዱ በቅርቡ መጽሐፍ ጽፈው እንድሸጥላቸው ስልክ ደውለው ጠየቁኝ። ከዚህ ያለነውን ሊበልጡ የተነሱ ምሁራን ለዚያ እርሶ አደር ወገኔ እንዴት ዋስ ጠበቃ ይሆኑታል? የሀገራችን ሰው ደግሞ መፈክሩ "የተማረ ይግደለኝ" እያለ ነው። ጥር 20 ቀን በ1996 ዓም ባህር ዳር ጠላ ቤት የሰማሁት አንዱ "የተማረ ይግደለኝ" ይላል እየደጋገመ ሌላው ይህን ቃል መስማት የሰለቸው" ዩንቨርስቲው በር ሕድና ተኛ ኢሕአዴግ ምሁራንን አባሮ ከናይጀሪያ 57 አስተማሬዎች አምጥቷልና ባልተወለደ አንጀታቸው ይረግጡሃል" ብሎ መለሰለት። የፈረንጆች ሁለት ሺህ ምሊንየም ላይ አሜሪካ ችግር ይፈጠራል ሲባል ብዙ ምሁራን ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ነበሩ። ከዚያ በፊት የጠፏትን በዚህ ወቅት መጠጊያ ሊያደርጓት ተመለሱባት ታዲያ እነዚህ ምሁራን ይታመናሉ?

ሕዳር 19 ቀን 2001 ዓም ሲኤን ኤን የተባለው ኬብል ኩባንያ በዓለም ላይ በግብረ ሠናይ ተሰማርተው ለሕዝብ አገልግሎት ላደረጉ ከ4000 በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ውድድር አድርጎ ነበር። ታዲያ በዚህ ቀን አቶ ዮሐንስ ገብረ

ጊዮርጊስ የተባሉ ኢትዮጵያዊ ሕጻናት የሚማሩበት መጽሐፍ አዘጋጅተው የሚረዱ በመሆናቸው ሲሸለሙ ተመልክቼ ከደስታዬ ብዛት አልቅሻለሁ:: መማር ማለት እንዲህ የዛሬ አበባዎችን የነገ ፍሬዎችን ሕጻናት መንከባከብ ሲገባ አብዛኛው የኢትዮጵያ ምሁራን ለግሉ ጥቅም ሲስገበገብ ይውላል:: የዛሬው ምሁራን ከአባቶቻችን የወረሰው ጥንካሬ የለም:: ሌላው ቀርቶ የሚሳቅበት አርሶ አደሩ ለማረስ በምን ዓይነት ዘዴ እንደሚጠቀም ይህ ተምሬአለሁ የሚለው ሊያጠናው አልፈለገም የኢትዮጵያ አርሶ አደር ለዘመናት ሲያርሰው የነበረው መሬት በተፈጥሮ ማዳበሪያ እንጅ ከአውሮፓ በገባው ማዳበሪያ አልነበረም:: ዛሬ የኢትዮጵያ መሬት እንደምሁራኑ የአውሮፓ ማዳበሪያ ለምዶ ያንን ካላገኘ እህል ሊያበቅል አልቻለም::

አውሮፓ ተገዝቶ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣው ማዳበሪያ በመጀመሪያ አውሮፓውያን ምርምሩን ያደረጉበት በአውሮፓ መሬት ሲሆን ይህ ማዳበሪያ ኢትዮጵያ መጥቶ ሊሰራ አይችልም:: ምክንያቱም መሬቱ ተመሳሳይ አይደለም:: የአውሮፓ መሬት በረዶና ፀሐይ የሚፈራረቅበት የራሱ የሆነ ተፈጥሮ ያለው ሲሆን አውሮፓውያን ከብዙ ዓመታት ሙከራ በኋላ ያገኙት ነው:: አባቶቻችን መሬቱ እህል የማያበቅል መሆኑን ያውቁታል:: ስለዚህ ለአንድ ዓመት ረፍት ይሰጡታል:: ከብት እንዲከርምበት ይደረጋል:: ሌላም ሌላ መላ አላቸው:: በዚህ ዓይነት እህል አምርተው እነሱም በልተው ሌላውን አብልተው ኑረዋል:: ስለዚህ ምሁራን ያደረጋችሁት ነገር ቢኖር የአውሮፓን ባህል ለሰው እንዳስተማራችሁት ሁሉ የኢትዮጵያን መሬት የአውሮፓ ማዳበሪያ አስለምዳችሁ አርሶ አደሩ እህል ዘርቶ እንዳያበቅል አደረጋችሁት::

ደርግ አካባቢው ደን እንዲኖረው ደን ተከላ ብሉ የጀመረው እቅድ መልካም እንደ ነበር ሠፈራው ለአርሶ አደሩ መሬት ትርፍ እንዲኖረው አድርጎ የነበረ መሆኑን ወደ ኋላ መለስ ብለው ዛሬ "ደርግ ነበር መንግስት" ማለት የጀመሩ አርሶ አደሮች በ1997 ዓም ኢትዮጵያ ሕጂ የሰማሁት መሆኔን አረሳሁም:: ወያኔ የአርሶ አደሩ የነብስ አባት ነኝ ብሉ አርሶ አደሩንና የከተማውን ሕዝብ አለያይቶታል:: ለገበሬው "ይህ የከተማው ሕዝብ ባላገር ብሉ ይሰድብህ ነበር! እህል ግዛ ስትለው ሲከራከርህ ይውል ነበር! ኢሕአዴግ ከአውድማህ መጥቶ አንተ በጠራሄው ዋጋ እህልህን ይገዘሃል" እያለ ከአውድማ ጭኖ ይወስዳል:: ሰኔ ግም ሲል አርሶ አደሩ በርካሽ ለወያኔ ከሸጠው መልሶ በዱቤ ይገዛል:: ከተሜው ደግሞ እንደዱሮው ተከራክሮ መግዛት አይችል የወያኔን እጅ አይቶ እንዲያድር ተደርጓል:: ይህን የሚያደርጉት አንዳንድ ምሁራን ናቸው:: ስለዚህ መማር ማለት የሕዝብን ብሶት አብሮ መጋራት መሆኑ ተረስቶ ዛሬ መማር ማለት ሕዝብን ማደህየትና መናቅ ማንቋሸሽና ሆኖአል:: የኢትዮጵያ ምሁራን የአውሮፓን ሥልጣኔ ተቀብለናል ብለው ያስባሉ:: ነገር ግን ስብሰባና ግብዣ ሲጠሩ ተሉ የማይመጡ ምሁራን ናቸው:: ከአውሮፓውያን የሚወሰድ ሰዓት ማክበርን በውይይት መተማመንን የሀሳብ ፍጭትን ማስለመድ መሆን ሲገባው የኛዎቹ ደግሞ የተገላቢጦሽ አድርገውታል:: ሌላው የሚገርመው ምሁራኑ ሕብረት እንደማጣታቸው ሁሉ የቤተሰብና የወገን ፍቅር ማጣታቸው ነው::



ሊቅ ዶ/ር ጌቱ ገላይ ጭማቂ ጹሑፍ በተባለው መጣጥፋቸው
"አህያ መጣች ተጭና ጠላ
ያገራችን ሰው ወንድሙን ጠላ"
ሲሉ ጽፈዋል:: ይህን ሁለት ዘለላ ግጥም ዘርጋና ሰፋ አድርጋችሁ ብትመለከቱት ዛሬ በተማረው ሕዝብ ዘንድ መጠላላት ሞልቷል:: ምነው እንደመጠላላቱ ሕብረቱን ለማጠናከር ቢገፉበት? ወንድም ወንድሙን ከዷል:: እናትና አባት ልጃቸውን ከደዋል:: ልጆች ወላጆቻቸውን ከደዋል:: በተለይም ገንዘብን በተመለከተ ክህደቱ በዝቷል:: አንባቢያን አንድ ሰው በገንዘብ ከካዳችሁ ራቁት እንጂ አትቅረቡት:: ምክንያቱም በገንዘብ ከካደ በኋላ ከማፈሩ የተነሳ ሊገል ስለሚችል መራቅ ይመረጣል! ዘመኑ አስቸጋሪ ዘመን ነው:: አንድ አልረዳኝ ያለው ነገር ቢኖር ሕግን ኢትዮጵያውያን እንደፈለስፍነው መናገሩን ይተውት ይናቁት ነገር ግን ቋሚ የሆነ ሕገ መንግሥት እንኳን አልተቀረጸም:: ለምሳሌ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የነበረው ከሠንደቅ ዓላማው ላይ የዘውድ ምልክት ነበር! ብሔራዊ መዝሙርም እንዲሁ ነበር:: በደርግም ወቅት ከሠንደቅ ዓላማው ላይ አርማው ብሔራዊ መዝሙር ተለውጧል:: በወያኔ ኢሕአዴግም እንዲሁ ከሠንደቅ ዓላማው ላይ የተደረተው ምልክት አሳፋሪ ነው:: ከሠንደቅ ዓላማው ላይ ያለው ምልክት ሕብረተ ሰቡን የሚወክል ነው ቢባልም በሌሎች አገር ይህ ምልክት መጥፎ ነው:: ብሔራዊ መዝሙር እንዲሁ ቀርጿል:: ነገ ደግሞ ሌላው ቡድን መንግሥት ሲወስድ ሁሉንም መቀያየሩ አይቀርም:: ለምን ይህን እንኳን ምሁራን ሊወያዩበት አልሞከሩም?

የኢትዮጵያ ምሁራን ቁጥራቸው ብዙ ነው:: በተለይ ይህ አገር አጥፊው ትውልድ ያ ቂመኛ ትውልድ አቅዋም የለሽ ሁኖ አገሪቱንና ቤተ ክርስቲያንን በማፍረስ ላይ ይገኛል:: ከ1940 ዓም ወዲህ የተወለደው ትውልድ ሥልጣን የመያዙ ዓላማ ያልተሳካለት ትውልድ ተስዶ ሆነ አገር ቤት የቀረው እንሆ አገርና ታሪክ አጥፊ ሆነ:: ምክትል ርዕሠ ብሔር አቶ ታምራት ላይኔ የዚያ ትውልድ አባል የነበሩ ኢሕአፓን ትተው ኢሕዴን የመሰረቱ ከዚያም ደግሞ ብአዴን የመሰረቱት በርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ሰረከ ተብለው ታስረው ሲወጡ "ኢየሱስን አገኘሁት" ብለው ሁለት እጃቸውን አንስተው ማልቀስ ተግባራቸው ሆነ:: ሌሎችም እንዲሁ በተለይ በስደቱ ዓለም ያለችውን ቤተ ክርስቲያን እያመሳት ያለው የዚያ ትውልድ ምሁር ነው:: መማር ማፍረስ መበተን መሆኑን የተረዳሁት በቅርቡ ዓመታት ነው:: በእርግጥ የአጥፊው ምሁር አቅም በገዞ እንጂ አገር እንትድተላመ የሚያስብ ምሁር የሉም ማለት አይደለም አሉ::

የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 29 ቁጥር 9 "ሰላም ለእናንተ ይሁን" ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠላቶች እነሱ እንዳሰቡት ሙቶ ይቀራል ብለው ነበር:: ነገር ግን መቅደላዊት ማርያምና ሌሎች ሴቶች ከመቃብሩ ደርሰው ባጡት ግዜና ደንግጠው ሲያለቅሱ በነበረበት ወቅት "ሰላም ለእናንተ ይሁን" ብሎ ተገለጸላቸው:: ታዲያ አምላክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "ሠላም ለናንተ ይሁን" እንዳላቸው ሁላ ኢትዮጵያውያን ማንኛውም አማኝ "ሠላም ለኩልክሙ"ይላል:: ይህ ቃል ግዕዝ ሲሆን አማርኛው "ሰላም ለእናንተ

ይሁን"ማለት ነው። ሰላም በአርብኛ እንዲያውም እንደምን አደራችሁ ሲሉ "ሰላማ ሊኩም" ይላሉ የማታውቀው ሰው ባጋጣሚ ቢያገኘው "ሰላም" ይለዋል። ሰላም በሕብሩም እንደ ግዕዙ ሰላም ማለት ሲሆን ሰላም በፕሊፕን ቋንቋ ተጋሎ አመሰግናለሁ ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ለእናን ይሁን ባለው መሰረት እኛም አምላካችን ለኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰጥልን ለአንድነት የሚያስብ አስተዳዳሪ እንዲሰጣት ወይም ያሉን መሪዎች ሃይማኖታዊ ምግባር ይዘው ለሕዝቡና ለአገሪቱ ሰላም እንዲሰጡን በያለንበት ሰላምን እንለምን። ያሉት መሪዎቻችን ጠበንጃ "አምላኬ" ከሚሉ እግዚአብሔር አምላኬ ብለው ስሙን እንዲጠሩ ልዑል እግዚአብሔር ልብ ይስጣቸው። መሪዎች ሃይማኖታዊ ምግባር ስለጎደላቸው ለአገር ሆነ ለሕዝብ ሰላም አልሰጡም። መሪዎች ሰላም ካሰቡ ፍርድ ቤቶች መድሎ አይፈጽሙም። ድሃ ተበደለ ሕዝብ ተቸገረ የሚል ፍርድ ቤት ካለ ሰላም ያገኛል።

የካባ ሲሳይ አምባው <u>የጣረ ይወጣል</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 91
"ሁለት ሺህ ዓመት ሞላ በአገራችን
በቃ በላት አምላክ ቸሩ ፈጣሪያችን
አንተን ስትማፀን አክብራ ቃልክን
ምሕረት አውርድላት አምላክ አባታችን
በእምነት ተዋሕዳ ቃልክን ተቀብላ
ልዑል እግዚአብሔር ሆይ ሁንላት ከለላ
ሁለት ሺህ ዓመት ሲጀምር አንድ ብሎ
ድረስ ለኢትዮጵያ አምላክ ሆይ በተሉ።
እንፀልያለን ቀንና ሌሊት
ኢትዮጵያን ባርክላት የዓለም መድኃኒት
ልጆችዋ በሰደት ሰንከራተት
ምሕረት አውርድላት የፍጥረት አባት
የሚታረስ ምድር እያለን መሬት
ወራጅ ውኃ ተርፎ እያለ በጅረት
እርሃቡ ገደለን ሰላማን ሕብረት።
ድርቅ በርትቶባት የሚበላ ጠፍቶ
ሰላም ሰላማን ዝናብ መዝንብ ቀርቶ
ችግር በሽታ ሁሌም ሲያጠቃን
እግዚአብሔር ይብቃ ብለህ ሰላሙን ስጠን
ታምርህ ይብዛላን ለእኛ ለልጆችህ
ለሕዝበ ኢትዮጵያ ይምጣልን ሰላምሕ" ሲሉ ጽፈዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን በስደቱ ዓለም በተለይም አሜሪካ ከመጣን ሰንባብተናል። ታዲያ ሕዝቡን አንድ አድርጎ የያዘው ተቋም ሁለት ናቸው። እነሱም የኢትዮጵያውያን የሰሜን አሜሪካ የእስፖርት ፌዴሬሽንና የኢትዮጵያ ቀጥተኛ (አርቶዶክስ) ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። እነዚህን ተቋም ምሁራን ለመበተን ጥረት እያደረጉ ናቸው። አንዳንድ ሰዎች ከግል ጥቅማቸው ጋር በማያያዝ ገንዘብ ካላገኙበት ጥቅም የሰጠ መስሎ አይታያቸውም።



ለወደፊቱ ብዙ ኢትዮጵያውያንን የሚያገናኝ ከጎሳና ከሃይማኖት የፀዳ ተቋም መሆኑ ሲታወቅ ዛሬ የወያኔ ደጋፊዎች ለማጥላላት ጥረት ሲያደርጉ ይገኛሉ።ከዛሬ 26 ዓመት በፊት ቁጥራቸው አራት የእግር ኳስ አፍቃሪ ኢትዮጵያውያን ቡድኖች የተጀመረው የኢትዮጵያ እስፖርት ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ በያመቱ ኢትዮጵያውያን እንድንገናኝ መንገድ የከፈተ ማዕከል ነው። ይህ የተቀደሰ ማዕከል የተጀመረው በ1977 ዓም ወይም በ1984 ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ብዛት ያላቸው የአሜሪካን ከተሞች ከኒትባዎችና ታላላቅ ሆቴሎች የሚያውቁት ግዙፍ ማዕከል ነው። ይህ ማዕከል ኢትዮጵያውያንን ማገናኘትና ባሕላቸውን እንዳይረሱ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን በያመቱ ከሰበሰበው ገንዘብ ከመቶ ሺህ ዶላር በላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ለድርቁ የለገሰ ነው። በአገሪቱ እንቱ የተባሉት ታላላቅ ሰዎች የክብር እንግዳ አድርጎ ይጋብዛል። ከዚህ አገር የተወለዱት ኢትዮጵያውያን ባሕል አለን ብለው እንዲኮሩ ከኳሱ ሜዳ ላይ በኢትዮጵያውያን የባሕል ድምጻውያን በአገር በቀል ልብስ አሸብርቀው የክብር እንግዶች እየተመለከቱ ቀኑ ዘፌን ይዋላል።

ይህ የሰውነት ማጠንከሪያው የእስፖርት ፌዴሬሽኑን ከማይወዱት መካከል ወያኔ ነው። ሁሌም በኳሱ ምክንያት ኢትዮጵያውያን ይሰባሰባሉ። ታዲያ የሥነ መንግሥት የፖለቲካ ድርጅቶች ይህን እድል ተጠቅመው የየራሳቸውን ስብሰባ ያካሂዳሉ። በዚህ ስብሰባ ላይ ወያኔ ድክመቱ በባለሞያዎች ተብጠርጥሮ ይነገራል። በዚህ ተቋም ሌሎች የሥነ መንግሥት የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ ወያኔ በ1990 ዓም ተጠቅሞበታል። ጉዳይ ፈጻሚ አምባሳደር ብርሃኔ ገብረ ክርስቶስ የአይደር ተማሪዎች የደበደበበትን በስዕል ድምጽ ቪዲዮ ክር በማሳየት ኢትዮጵያውያን አብሮአቸው እንዲቆም ጥሪ ያቀረቡበት አትላንታ ላይ ነበር። ዛሬ ወያኔ በዚህ ተቋም ላይ ዘመቻ ማድረግ ጀምሯል።ዛሬ እንደ ኳሱ ሁሉ ኢትዮጵያውያንን በዓለ ጥምቀትን ከሜዳ ላይ ታቦት አውርዳ በማሳደር ለማንነታችን ኩራት የሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሉስ አንጀለስ የተጀመረው በዓል ታላቅ እየሆነ መጥቶአል። ይህን ቅዱስ ዓላማ የጀመረችው ድንግል ማርያም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሉስ አንጀለስ ስትሆን ከአደር አደር ሌሎች በአካባቢዋ ያሉት ቤተ ክርስቲያን ታቦታቸውንና ምዕመናናቸውን አስተባብረው በዓሉ በታላቅ እንዲከበር እያደረጉ ነው። በዚህ የጥምቀት በዓል ወንጌል ይሰበካል። ሕዝቡ ከአገሩ ቢርቅም በዓመት አንድ ጊዜ ይህን የመሰለ በዓል አክብሮ እንዲውል የተደረገው በተወሰኑ የቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና የሃይማኖት አስተማሪዎች ጥረት ነው። በዚህ አጋጣሚ የሉስ አንጀለስን ቤተ ክርስቲያኖች ጅምራችሁ ከፍ እንዲልና እየጠነከረ እንዲመጣ ጥረታችሁን አምላክ ይባርክላቹ ለወደፊቱም በርቱ እላለሁ።

ከዚህ በላይ በተወሰኑ የኳስ አፍቃሪዎችና የቤተ ክርስቲያን አክባሪዎች ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ የሚሰጡት ጥቅም ባጭር የተጠቆመ ሲሆን በምሁራን በኩል ግን የተመሰረተ ተቋም የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያቀራርብ የለም። በምሁራን በኩል የተመሰረተው ተቋምማ ልዩነትና ጠብ ናቸው። ዛሬ ዶ/ር እገሌ የድርጅት መስራችና መሪ ናቸው። ዛሬ ዶ/ር እገሌ የቤተ ክርስቲያን

መስራችና መሪ ናቸው:: ሌሎች የመሰረቱትን ተቋም መበተን እንጂ ማሳደግ የማይችሉ ምሁራን ናቸው:: የሀገራቸው ደንበር ሲደፈር አይሰማቸውም:: ቀይ ባሕር ከኢትዮጵያ መራቋ አልበቃ ብሎ ጠላቶቻችን ዛሬ ደግሞ በዓባይና በአጋዴ ላይ ተጠናክረው ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ ሲሰበሰቡ ምሁራን ዝም አሉ?

የካባ ሲሳይ አምባው <u>እግዚአብሔር አልረሳኝም የለመንኩትን አልነሳኝም</u> ያልታተመ:: "አገሬ ኢትዮጵያ ለዘላለም ኑሪ
ምኞቴ ነውና እንድትከበሪ
ሀገሬ ኢትዮጵያ ኑሪ ለዘላለም
ጥሉ አይጥልሽም ባለ መድኃኒዓለም
አምናለሁ መኖርክን ጌታ ከመንበርህ
አትርሳት አገሬን ይድረሳት ምሕረትህ
ሕዝቡ ተቸግሮ የሚበላውና የሚጠጣው አጥቶ
ኢትዮጵያ ፀሎቷ ነውና አይቀርም ተጠምቶ
እንጀራ ሆንና የሰው ቁምነገሩ
አልቀበር ብሎአል ሰው ሁሉ ካገሩ
እናቴ ኢትዮጵያ ምን ይሆን እድልሽ
አልወጣልሽ ያለው ከልጅ ከምሁርሽ
ኢትዮጵያ አገሬ በጣም ትልቅ ነበርሽ
እጅ ጠባብ ለባሽ ብዙ ልጅ አፈራሽ" ሲሉ ጽፈዋል:: የኢትዮጵያ ምሁራን ባህላቸውን ታሪካቸውንና ሃይማኖታቸውን ጠልተዋል:: የእኛ ምሁራን የሩቅ ተመልካች የራሱን ፈንካች ከሆኑ ከርመዋል:: ለዚህም ብዙ የታሪክ ሰነድ ማገላበጥ ይቻላል:: የኛው መማር ማለት መሰልጠን፤መሰይጠን መሆኑን ካወቁ ጀምሮ በሃይማኖታቸው በታሪካቸው በፊደላቸው ላይ ንቀት አደረባቸው::

ዓለማየሁ ሞገስ ደርሶ <u>መልክዐ ኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 236
"በቀደም አግኝቸው መሸሻን ከመንገድ
ጥያቄ ብሰጠው በታሪክ ረገድ
ሊመልስ አስቦ ልቡም ተጨንቆ
ባይኑም አስተዋለ በአንጎሉም ጠየቀ
ብዙ ወሸከተ እየዘባረቀ
እንዲያው ደከመ እንጂ ምንም አላወቀ::
ተስማን ጠርቼ ባጨዋውተው
እንኳንስ ሊመልስ ምንም አልገባው
ወዲያው ከተፍ ሮለ ደግሞ አቶ ጣሰው
እሱም እንደነሱ እጅ እግሩ ጠፋው::
ባልሳችን ረስተው የዛሬ ልጆች
ቋንቋችን ዘንግተው ያሁን ወጣቶች
ላይ ታች ሲሉ እያየሁ ሁላቸውንም
ጠርቼ ብጠይቅ አንዱን በቀደም
አማርኛ ለካስ ፍጹም አያውቅም" ሲሉ ጽፈዋል::



## ምዕራፍ 6

## እንደ ቀይ ባህር ዓባይንና አጋዴን እንዳናጣ?

ርዕሠ ብሔር ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም <u>አዲስ ዘመን ጋዜጣ</u> የካቲት 27 ቀን 1982 ዓም ገጽ 15 "እንደሚታወቀው ሀገራችን የምትገኝበት አካባቢ እንደዛሬው ሁሉ ቀድሞም በየዘመኑ የተነሱ ገናና መንግሥታትን ትኩረት የሳበ ስትራቴጂካዊ አካባቢ ነበር:: በዚህ የተነሳ ከተስፋፊዮች ቅኝ ገዥዎችና ወራሪዎች ጋር በርካታ ጦርነቶች ተካሂደዋል:: በዚህ አንጻር በተለይ ከውጭው ዓለም ጋር መገናኛ በራችን የሆነውን የቀር ባሕርን እለኝታችንን ማስከበሩ ብዙ ጦርነቶች ውስጥ የዳረገን መሆኑ የሚታወቅ ነው:: ከዚህ አካባቢ የሚቀጣጠለው እሣት በአጠቃላይ የሀገሪቱን ሕልውና አደጋ ላይ የጣሉባቸው ተደጋጋሚ አጋጣሚዎች እንደ ነበሩ የሚዘነጋ አይደለም:: እንደውነቱ ከሆነ የሀገራችን የረጅም ጊዜ ታሪክ አንድነታችንና ሕልውናችንን የማስከበር የጦርነት ታሪክ ነው ለማለት ይቻላል:: በአንድ ወቅት ገናና ሥልጣኔ ደረጃ ላይ ደርሳ የነበረችው ሀገራችን በኋላቀርነት ታፍና መቆየት መሰረታዊው ምክንያት ይህ ነው" ሲል ከሸንገው ያነበቡትን አዲስ ዘመን ጋዜጣ የካቲት 27 ቀን 1982 ዓም አውጥቶታት:: ይህ መጣጥፍ 40 ገጽ ሲሆን የዳሰሱት ብዙ ቁምነገሮችን ነው::

ሹመት ሲሻኝ <u>የኤርትራ ሕዝቦች የአንድነት</u> ትግል በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 16" አብዛኛዎቹ ምዕራባውያን ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ሥር ባሉት በጥቁር ሕዝቦች መካከል የፖለቲካና የሞራል መነቃቂያ ምሳሌ ትሆናቸዋለች ብለው ስለሚሰጉ በክፉ ዓይን ይመለከቷታል:: አንዳንዶቹ እንዲያውም ጊዜ ካገኘች እንደ ጃፓን ታይል ይሆናል የሚል ፍራቻ አላቸው:: ይህ ዓይነት አዝማሚያ ስላላቸውም ኢትዮጵያን የሚሸራርፍና ኃይሏን የሚወስን ሁኔታ ቢያዩ ደስ ይላቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል:: ሊቀ ጠበብት ሹመት ከላይ ያነሱት ታሪክ ኢትዮጵያን ለማድከም ዋናው አንዱ መሳሪያ ይህ ነው:: ከዚህ በፊት ጦርነት ሲያማዝዙና ደም ሲያፋስሱ የነበሩ ቦታዎች የኢትዮጵያ ምሁራን አልታያቸውም:: በዓለም ላይ ብዙ ታላላቅ አገሮች ኃያል ሲሆን ኢትዮጵያን ለማንበክከር ያልተነሳ ማንም አልነበረም:: ኢትዮጵያን ከዓለም በፊት ለመውረር የመጣው ሕንድ በ1985 ዓመተ ዓለም በአጤ ራማ የተመራ ሲሆን በዓባይ በኩል ይምጣ በቀይ ባሕር በኩል ግልጽ የሆነ ቦታውን የሚጠቁም ሠነድ ላገኝ ባልችልም ንጉስ ራማ የሞተው ትግራይ ውስጥ መሆኑን የሞተበትም ዛሬ ድረስ ራማ ተብሎ ይጠራል::

ጋኖች እለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ አሉ አባቶቻችን እለቁና ዛሬ ያለው ኢሕአዴግ መንግሥት ጀግኖች ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስከሰው ከወራሪ ጠብቀው ያቆዩልንን አገር ለሥልጣን ማስንበቻ ተብሎ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ለሱዳ ሊሰጥ ታቅዷል:: ወደኋላ ተመልሰን ታሪክ ስንቃኝ

አባቶቻችን ኢትዮጵያን ያቆዩልን ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ጀምረው የመጡብንን ወራሪ ድል እያደረጉ ነበር:: ለምሳሌ በ1985 ዓመተ ዓለም ከሕንድ የመጣው ንጉሥ ራማ ተደብድቦ ቀርቷል::

በ1600-1500 ዓመተ ዓለም መካከል ግብጽ ልትወር መጥታ ተጠቅታ ስትመለስ ኢትዮጵያውያን ተከትለው ግብጽን ለ400 ዓመታት ቅኝ ግዛት ገዝተዋል:: ጥቁር ፈርዖኖች ኢትዮጵያውያን ናቸው:: ኢትዮጵያውያንን ከብጽን ያስወጣቸው የፋርሥ ወራሪ ሲሆን ኢትዮጵያ ከዛሬው ሱዳንና ግብጽ ደንበር ላይ ጠረፏን አስከምራ ኑራለች:: ፋርሥን ከግብጽ አባሮ ያስወጣው የክሪኩ አሌክሳንዴር ሲሆን እርሱም ኢትዮጵያን ለመውረር አቅዶ ቅድሚያ ራሱ ለስለላ ገብቶ በንግሥት ሕንደኬም ሰላዮች ተደርሶበት ታስሮና ተዋርዶ ተመልሷል:: የግሪኩን ወራሪ ከግብጽ ያባረረው የሮማውያኑ ወራሪ ሲሆን ግብጽን ይዞ ኢትዮጵያን ሊወር ስለመጣ ኢትዮጵያውያን ወግተው መልሰውታል የሮማውያኑን ወራሪ ከግብጽ ያባረረው ከክርስቶስ ልደት ወዲህ የተነሳው የእስልምና ሃይማኖት ኃይል በመጀመሪያ በኢትዮጵያ ላይ ቀጥተኛ ጦርነት አልገጠመም ነበር:: ነገር ግን የእስልምና ሃይማኖት ኃይል ተስፋፊዎች ኢትዮጵያ ከባህር ማዶ የነበራትን ግዛት እንድታጣ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ የባሕር ኃይልና የበላይነት እንዲመታ ሆኑ:: ትልቁ ውድቀት ከዚህ ቢጀምር ከባህር ወዲህ ያለውን ግዛቷን ከሌሎች ወራሪዎች ጋር እንደ በሃይማኖት በሌላ ጊዜ በንግድና በጉልበት ለመያዝ ቱርኮች በመምጣታቸው አባቶቻችን አሳፍረው መለሱአቸው::

የቀድሞ የባሕር ኃይል መለዮ መለዮ ለባሾችና ሲቪልሠራተኞችየኅብረት ሥራና መረዳጃ ማህበር ነው ኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍና ባሕር ኃይል በተባለው መጽሐፍ ገጽ 44 "አዲሱ የአረቦች የእስልምና ሃይማኖት እንቅስቃሴ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኃይሉን አጠናክሮ የአክሱማውያንን የባሕር ማዶ ግዛትና ኃይል በመደምሰስና በመቆጣጠር ብቻ ሳይወሰን በዘመኑ የታወቁትን ሁለቱን ኃያላን የሮማውያንንና የፋርሳውያን ኃይሎች ጭምር በመደምሰስና በአክሱም መንግሥታትም ላይ የገለልተኝነትና ውድቀት ተፅዕኖ በማሳደር ለዓባይ ሸለቆ ለቀይ ባሕርና ለኤደን የባሕር ሰላጤ የንግድ እንቅስቃሴ ሰላም ፀጥታና ዋስትና ለመስጠት በብቃት ተደራጅቶ የነበረው የየብስና የባሕር ኃይላችን ቀስ በቀስ እንዲደክምና በቀላሉ ለማንሰራራት በማይችሉበት ሁኔታ እንዲወቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል" ሲሉ ጽፈዋል::

የአውሮፓ ወራሪ ዜጎችን ለማስፈታት ብሎ የእንግሊዝ ጦር ቢገባ ብዙ ሳይቆይ ወጥቶ ሲሄድ ግብጽ ኢትዮጵያን ልትወር ስትመጣ ተደብድባ ተመልሳለች:: ወዲያው ጣልያን በምጽዋ በመምጣቷ ዶጋሊ ላይ ድል ሆነች:: ድርቡሽ ሕዝብንና ቤተ ክርስቲያንን አቃጥሎ ሲመለስ የኢትዮጵያ ልጆች መተማ ላይ ብድራቸውን መልሰዋል:: ኢጣልያን አድዋ ላይ ድል ሁና ተመልሳ ነበር:: ከዚያም እንደገና አየርና መርዝ ይዛ ኢትዮጵያን ወረረች:: ለተወሰኑ ዓመታት የኢትዮጵያን ዋና ከተማ ተቆጣጥራ የኢትዮጵያን ሕዝብ በጋዝ መርዝ ብትፈጅም አባቶቻችን በጀግንነታቸው ጣልያንን አባረው ክብራችን



አስከብረው ኢትዮጵያን አቆዩን:: ሱማሌም ልትወር መጥታ ተደብድባ ተመለሰች:: የትናንቷ ኤርትራም ወረራ ጀምራ እንደ ክርስትና አባቷ ጣልያን ተደብድባ ተመልሳለች::

የቸገረን የውጭ ወራሪ አንለው የአገር አስተዳዳሪ የኢትዮጵያውያንን ክብር አስደፋሪ የሆነው የአቶ መለስ ዜናዊ መንግሥት 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ከጋንቤላ እስከ ሁመራ ለሱዳን ሊሰጥ ጉንብስ ቀና እያለ ነው:: ላሚቱ ጃርት ወልዳ እንዳትልሰው ወጋት እንዳትተዎው ልጅ ሆነባት የተባለው ተረት በኛ ደርሶ የውጭ ወራሪ አንለው ጥቁር ነው! የአገር አስተዳዳሪ አንለው አገር ገንጣይና አስገንጣው ሕዝብን በሃይማኖትና በዘር ከፋፋይ ነው? ይህን ሰው ማን እንበለው? ሰው ወይስ ሰይጣን? ፍጥረቱ ከሰው ሲሆን ተግባሩና ሥራው ደግሞ ሠይጣን ነው:: አንባቢያን ልብ ወለድ እንዳይመስላችሁ ከዚህ በላይ በጻፍኩት ስድ ንባል ላይ መሰረት ለማስያዝ የታሪክ መጽሐፍት መጥቀሱ ለአንባቢያን ይጠቅማል::

1ኛ ሕንድ ኢትዮጵያ መውረሯን አስመልክቶ አለቃ ታየ ወልደማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ገጽ 18-19 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ኑቢያ አክሱም ዛጉዌ ገጽ 35 የየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል የ1660 ዓመት ታሪክና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልማትና እቅድ መስከረም 1983 ዓም ገጽ 32

2ኛ ግብጽ ኢትዮጵያን ለመውረር መጥታ ተጠቅታ ኢትዮጵያውያን አባረው ግብጽን ብቅኝ ግዛት የያዙ መሆናቸውን አስመልክቶ አባ ተሥፋ ሥላሴ ሞገስ ቅዱስ ማርቆስ ኢትጵያዊ ነው የተዋሕዶ አንበሳም መድኃኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በተባለው መጽሐፋ ገጽ 101 ከላይ የተጠቀሰው የአቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ መጽሐፍ ገጽ 17-117-118-119 የተጠቀሰ ሲሆን ኢትዮጵያውያን ግብጽን የገዙት ስማቸው ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ገጽ 118-119 "ሰበቆን÷ሻባካ፥ሰበኩስ÷ሻባታቃ÷ ወይም ታራቆስ÷ታርሐቃ÷ ሻባካ÷ ባታካ÷ታርሐቃ÷ታትታመሙን፥ፒያንኪ÷ሻበሻ፥ሻ÷ባታቃ፥ታርሐቃ፥ታትሙን" ሲሉ ዘርዝረው ጽፈዋል:: ብላቴ ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል ዝክረ ነገር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 819 "የኢትዮጵያ ንጉሦች ግብጽን እየቀላቀሉ ይገዙ ነበር" ሲሉ ጽፈዋል::

3ኛ ፋርስን አስመልክቶ መራሪስ አማን በላይ የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 113 እንዲሁም የአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 139-141-142 ሌሎችንም መመልከት ይቻላል::

4ኛ የግሪኩን ወራሪ አስመልክቶ ጳውሎስ ኞኞ የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 7"መለስ ብለን ከታሪካችን ውስጥ በመጠኑ ብንመለከት የሚያኮራንና የሚያስመካን ታሪክ ማግኘት እንችላለን:: ከክርስቶስ ልደት በፊት በግሪክ ላይ ነግሦ የነበረው ታላቁ አልክሳንደር ግዛቱን

እያሰፋ ከመቆዶንያ ግብጽ ድረስ ተሻገረ። ብዙ አገሮችም በጦር ሳይሆን ገና በዝናው እየፈሩ ገበሩለት። ኩዌንቱስ ኩርቲውስ የተባለው የዘመኑ ታሪክ ፀሐፊ የአሌክሳንደርን ግዛት ማስፋፋትና ለጦርነት መነሳት ሲገልጽ ወጣቱ ለጦርነት ሲነሳ የምወረው ግብጽን ብቻ አይደለም ኢትዮጵያን ጭምርት ነው ማለቱን ጽፏል። አልክሳንደር ዝቶ እንደተነሳው ከግብጽ ጀምሮ ሕንድ ድረስ አስገበረ። በመሐል ግን ኢትዮጵያ ከገባሪዎች ተነጥላ ቀረች።"

"አልክሳንደር ስለ ኢትዮጵያ ጀግንነት ሰምቶ ነበርና ከኢትዮጵያውያን ጋር ጦርነት ለመግጠም ፈራ። ስለ ኢትዮጵያውያን የሚነገረው ጀግንነት እውነት ስላልመሰለው ራሱ አለክሳንደር ኢትዮጵያ ውስጥ ለመሰለል ተነሳ። ክሮኒክልስ አፍ ጆን ቢሾም አፍ ኒኩ በሚባለው መጽሐፉ ላይ እንደሚተርከው አሌክሳንደር ከምርጥ የጦር አለቆች ጋር ሆኖ ሁሉም ተራ ሰው መስለው ለመሰለል ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሕንደኬም አለክሳንደር ተራ ሰው መስሎ ወደ ኢትዮጵያ ለመሰለል መግባቱን ሰማች። ንግሥቲቱ እነዚህን እንግዳ ተራ ሰዎች ወደ ቤተ መንግሥቷ አስጠርታ እንዲህ አለች። ዓለምን አንቀጥቅጠህ የገዛህ ታላቁ እስክንድ ዛሬ በሴት እጅ ተይዘሃል" አለችው ሲሉ ጽፈዋል። ሌላው ከላይ የተጠቀሰው የአቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ መጽሐፍ ገጽ 176 እንዲሁም የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 113 ተብራርቷል።

5ኛ የሮማውያንን ኃይል ኢትዮጵያ ወግታ የመለሰች መሆንዋን ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ገጽ 267 እና መራሪስ አማን በላይ መጽሐፍ ከላይ የተጠቀሰውና ሌሎችም ብዙ መጽሐፍት ዘግበዋል። ከክርስቶስ ልደት ወዲህ የተደረጉት ጦርነቶችን በ14ኛው ክፍለ ዘመንና ኋላም በ18ኛው ብሎም በ19ኛው ክፍለ ዘመን በ15ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ለማንነቷ ተዋግታለች።

<u>የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘናት ትግልና</u> የዘመናዊ ሠራዊት አመሰራረት 1855-1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 262 "1973 ዓም የዓረብ ማኅበር አባል አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ሊቢያ ላይ ባደረጉት ስብሰባ ኢትዮጵያ እስራኤል ቀይ ባሕርን እንድትቆጣጠር ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ስለሆነች የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት በማውገዝ የአጋዴን ወንበዴዎችን መርዳትና ኤርትራን ሙሉ ነፃነትን እስክታገኝ ወንበዴዎችን መደገፍና ማበረታታት ያስፈልጋል የሚል ውሳኔ አሳልፈው ነበር" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ከላይ ጥቅስ የተወሰደው መጽሐፍ ዓመቱ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ሲሆን በኢትዮጵያ 1965 ዓም መሆኑ ነው። አረቦች ትግላቸው ግቡን መቷል። ገንዘባቸው አልጠፋም ሰርቷል። ያ ማለት ኢትዮጵያን ከቀይ ባሕር ለማራቅ ያደረጉት ሴራ ተሳክቷል።

ሜጀር ጀኔራል ሁሴን አህመድ <u>መስዋዕትነት እና ዕናት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 92" ቀደም ብሎ በተገለጸው መሠረት የኢትዮጵያ ጆኦ ፖለቲካዊ ሁኔታ በአፍሪቃ ቀንድ በቀይ ባሕር፣በሕንድ ውቅያኖስ፣ እንዲሁም በዓባይ ምንጭ የፖለቲካ ሁኔታ ልዩ ትኩረት ያለው በመሆኑ ከ18ኛው ክፍለ



ዘመን ቀደም በ16ኛው ክፍለ ዘመን በውጭ ወራሪዎች የአገራችን ህልውና ለበርካታ ዓመታት የተፈተነበት ጊዜ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ <u>ክህደት በመደም መሬት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 43" ኢትዮጵያ የግብፅንና የሱዳንን የውሃ ፍላጎት ሰማንያ በመቶ የሶማሊያን ፍላጎት መቶ በመቶ የምታሟላ ሀገር ነች። የሶማሊያ ሕዝብ በአብዛኛው ዘላን እንደመሆኑ መጠን ችግሩ ውሃና ግጦሽ ነው። ውሃውም ግጦሹም ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። የደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ወንዞች ማለትም ዋቢ ሸበሌ፣3 ቢሊዮን ሜትር ኩብ፣ገናሌና ዋጻ 4 ቢልዮን ሜትር ኩብ፣ በጠቅላላው 7 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ወደ ሶማሊያ ይፈሳሉ። ከሰሜንና ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ከዓባይ 50 ቢሊዮን ሜትር ኩብ፣ከባሮ 14 ቢሊዮን ሜትር ኩብ፣ ከባርካ 0.6 ቢሊዮን ሜትር ኩብ፣ ከዳንድር ረሀድ 4 ቢሊዮን ሜትር ኩብ በጠቅላላው 80 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ወደ ሱዳንና ግብጽ ይፈሳል። በኢትዮጵያና በኬንያ ድንበር ላይ ባለው የሩዶልፍ ሐይቅ ውስጥ በኦሞ ወንዝ አማካኝነት የሚጨመረው አማካይ ውሃ መጠን በማለት 15 ሚኒሊዮን ሜትር ኩብ ነው። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ 100 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ በነፃ ለጎረቤት ሀገሮች በየዓመቱ ትሰጣለች።"

"በዚህም ምክንያት የሱዳን፣ የግብጽና የሶማሊያ ሕልውና ከኢትዮጵያ ውሃዎች ጋር የተያያዘ ነው። በዚህም መጠን የመከላከያና የውጭ ፖሊሲያቸውም በዚሁ ጥቅማቸው ላይ የተመሰረተ ነው። ሊወገድ የማይችል የተፈጥሮ ቁራኛነት ነው።" ይሉና ገጽ 44-45" የቀይ ባሕር አዋሳኝ ሀገሮች በጠቅላላው የዓረብ ሀገሮች እንደሆኑ ከባድ ጥረት እንጻለ ይታወቃል። የዓረብ ሀገሮች የኤርትራን ነፃነት ሙሉ ሙሉ ያደረጉትና ለትግሉ ብዙ ገንዘብ ያፈሰሱት ይህንን ዓላማ እውን ለማድረግ ነው። የቀይ ባሕር ፍፁም አረባዊ መሆን ደግሞ በመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን የኃይል ሚዛን በማዛባት እስራኤልን ለተጨማሪ አደጋ ሊያጋልጣት ይችላል። ስለዚህም ኤርትራ የዓረብ ሊግ አባል እንድትሆንና በሌላ በኩል ደግሞ ወገናዊነቷን ጠብቃ ከአሜሪካና ከእስራኤል ጋር እንድትሆን ያልተቋረጠ የፖለቲካ ትግል በማካሄድ ላይ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

መሰረታዊ ጠላቶቻችን ኢትዮጵያን ከዓለም ገጸ ምድር (ካርታ) ለማጥፋት ከተነሱ ውለው አድረዋል! በነገራችን ላይ ሳናውቀው እኛው ኢትዮጵያውያን ተባባሪ ሁነናል። ከላይ እንደጠቀስኩት በሃይማኖት አሳበው ወንድሞቻችን መጥፎ ትምህርት አስተምረው የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማፋጀት ታጥቀው ተነስተዋል። አንዳንድ ሰነዶች የሚያቀርቡት ታሪክ ቢኖር በኢትዮጵያ ውስጥ ሠላም እንዳይኖር የኢትዮጵያን እስላም በተለይ በቅርቡ የተፋፋመው ያጥፍቶ መጥፋት ቡድን በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ላይ የፈጸመው አስነዋሪ ተግባር ከአረቦች የፈለቀ መሆኑ አይዘነጋም። አረቦች ከምንግዜውም በላይ ዛሬ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተነስተዋል። አረቦች በህጋዊ መንገድ ኢትዮጵያውያንን እንደ ባርነት ቆጥረው ገዝተው እየወሰዱ ናቸው።

ለምሳሌ ከሚሄዱት ኢትዮጵያውያን የእስላም ስም ካልተሰጣቸው በቀር የመግቢያ ፈቃድ ቪዛ ሊያገኙ አይችሉም። ይህ የአንድን አገር ማንነት መድፈርና ማስደፈር ነው። ዜጎች የሚበሉት ሲያጡ ሊሰደዱ ይችላሉ። ይህ በዓለም ላይ ያለ ሲሆን ኢትዮጵያውያንን ግን የወያኔ መንግሥት በህጋዊ ሰነድ አዘጋጅቶ በመሸጥ ላይ ነው። አረቦችም በመግዛት ላይ ናቸው። አረቦች ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር ማራቃቸው ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ሰላም አጥታ ልማት በዓባይ እንድታተኩር አይፈልጉም። እነሱ ከግብጽ ገዝተው ለመውሰድ ስለሚፈልጉ የኢትዮጵያን ብልጽግና አይፈልጉም።

እስልምና ሃይማኖት መስራች ነቢዩ ሙሐመድ “ኢትዮጵያውያንን ካልወጓችሁ አትውጓቸው” ብለው ትዕዛዝ መስጠታቸው አይካድም። ነገር ግን ይህን ትምህርት አረቦች ሊቀበሉት ቀርቶ ሊሰሙት አይፈልጉም። ለዚህም ነው ፀረ ኢትዮጵያ አቅዋም በመያዝ ከ8ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ጀምሮ እስከ ዛሬ እኛን ሊያጠፉ በመጣር ያሉት። የዓባይ ውሓ ከአዳራሹ ከጣና ወጥቶ ለሱዳንና ለግብጽ መሬት ሕይወት የሚዘራበት የሆነው ሲጀመር ጀምሮ ነው። ዓባይ ብቻውን አይደለም የሚሰደደው ሌላውን የኢትዮጵያን መሬት ሸርሽሮ በጥብጦ ይዞ ይጓዛል። የዓባይ ወንዝ ከሀገሪቱ መልክአ ምድር አንድ አስረኛውን ክልል ቢሸፍንም ከዓለም አቀፍ ሕግጋት እንጻር በውሃ ሀብት የመጠቀም መብት የሁሉም ሃገሮች መሆን ሲገባው ግብጾች ግን ኢትዮጵያ በዓባይ ላይ ልማት እንድታለማ አትፈልግም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስማምቶ በአንድነቱ እንዲኖር ዓረቦችና ግብጾች አይፈልጉም። ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ገንዘብ ገዝታ የምታመጣው ጳጳስ ግብጽ ነበር። እነዚህ ጳጳሳት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰርቶ እንዳይበላ የበዓላት ብዛት ደርበው ደራርበው ለኛዎቹ የበስማም ቄሶች ይነግሯቸዋል። የእኛዎቹ የበስማም ቄሶች ደግሞ “ይህ የጳጳሱ ቃል ነው” ብለው እያወገዙ በሚሰራበት ቀን ሕዝቡ ቁጭ ብሎ እንዲውል ያደርጉታል። መጽሐፍ ቅዱስ ጠንቅቆ ሕዝብ እንዲያውቅ አይፈልጉም። መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቀው አውቀው ዶግማና ቀኖና ለይተው የሚያስተምሩትን “ፀረ ማርያም ናቸው” አስብለው ያስገድሏቸዋል። ሕዝቡ በጥረቱ የሚያለማውን ልማት አውግዘው ያጠፉታል። ለምሳሌ ወይን በአገራችን ይመረት ነበር። የግብጾች ጳጳሳት ወይን እንዳይመረት አስከለከሉ። ምክንያቱ ምንድነው ሲባሉ "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም የሚፈተትበትን የባላገር መጫወቻ ሆነ" ብለው እንዲከለከል አስደረጉ። ወይን የሚመረትበት ቦታ ደጋ ቀመስ ሲሆን ዛሬ ይህ አካባቢ “ወይና ደጋ” ይባላል። ይህ ስም ቀደም ብሎ ወይን የሚመረትበት ቦታ መሆኑን ነው ታሪክ የሚዘክረው። ወይን ዛፍ ተመንጥሮ ከጠፋ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ተቀድሶ የሚቆረብበት ዘቢብ እስከ መታጣት ደርሶ ሳለ መልሰው ራሳቸው የግብጽ ተወላጆች በንግድ ከውጭ አገር ዘቢብ እንዲገባ አደረጉ። የዘቢብ ችግር ዛሬ ድረስ አለ። ኢትዮጵያ ያሉ ቄስ ቤተሰብ ያላችሁ “ምን ልላክላችሁ” ብትሏቸው መልሳቸው “ዘቢብ” ነው።



ዛሬ ጠላቶቻችን ገዝግዘው ገዝግዘው ቀይ ባሕርን ከወሰዱ በኋላ ፊታቸውን ያዞሩት በዓባይ በኩል ነው። ለምሳሌ በዘመነ ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ዘመን ጎጃም ውስጥ ብር ሸለቆ ከተባለው ለም መሬት ላይ የተጀመረው ልማት እንዴት እንደከሰረ ማሰብ ይገባናል። በዚያ ልማት ወቅት ጣሊያኖችን ማርኮ ልማቱን ያስቀረ ኢሕአፓ ነው። በዚህ ምክንያት አካባቢው ከልማት ይልቅ ወደ በርሃነት እንዲለወጥ ሁኗል። በዚህ ልማት መቋረጥ የተጠቀመችው ግብጽ ናት። ለምሳሌ ይህ ልማት ኑሮ ቢሆን ኑሮ ከብር ሸለቆ አልፎ በሌሎች አውራጃዎች በተለይም በነቆምጬ አምባው ታታሪ አስተዳዳሪ አይነት ቢያገኘው በአባይ ላይ ከፍተኛ የሆነ ልማት ይካሄዳል። ይህ ከሆነ ደግሞ የዓባይ ውሃ በልማት ላይ ይውላል ማለት ነው። የዓባይ ውሃ በልማት ከዋለ ወደ ሱዳንና ግብጽ የሚፈሰው መጠኑ ሊቀንስ ነው። ስለዚህ በግብጽ ታቅዶ በሱዳን መንግሥት ጠቋሚነት ይህን ልማት እንዳይለማ ኢሕአፓ እንዲያዘጋው ታዘዙ። ሲጀመር ጀምሮ በአረብ አገሮች ሰልጥኖ ወደ ሻዕቢያ ነፃ መሬት የገባው ኢሕአፓ ትዕዛዙን ፈጸመ። ዛሬም ጠላቶቻችን መተማን ከወሰዱ ከመተማ ጣና ያለውን ርቀት ተመልከቱ። ዓባይን በራሱ ገብተው ሊቆጣጠሩ ማሰባቸውን ምሁራን ማሰብ ተሳናቸው?

አያናዝጊ አ!ወልቃይት ያልታተመ።
“ዓባይ ነኝ ምን ነካው ይህ ሕዝብ ምን ሁንዋል
ከጥንት ጀምሮ ሲወቅሰኝ ይኖራል
እኔ ምን አጠፋሁ እኔ ምን በደልኩኝ
ቀርቶ ማደርያ ማረፊያ እንኳን የለኝ?።

ስፈጠር ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ
ትዕዛዜን ጠብቄ ቁልቁል በበርሃው ተምዘግዝጌ ስፈስ
አንድ እንኳ ያሳሰበ በመስኖ ለማረስ
ዓባይ ቢጠሩህ አትስማ
ምን አስቀምጠሃል ከግብፆች ከተማ
ይሉኛል አፍ ሞልተው
በሕብረት ሳይሰሩ እነሱ አንድ ሁነው
እኔ ከዛ ቦታ ከግብጾች ከተማ ደግሞስ ምንስ ኑሮኝ
ማንስ ነውከጥንት ጀምሮ ቁልቁል ሲነጉድ ይዞኝ።

እነሱው ተጠቅመው አፈሩን ቆልለው
እናንተን እርስ በርስ አጋጭተው አጣልተው
መሆኑ መች ጠፍቶኝ
እናንተ አንድ ሳትሆኑ እኔን የምትወቅሱኝ
ይቅር መገደቡ ቁጭ ብሎ ባንድነት የተመካከረ
ተናግሮ አናጋሪ ማን አለ እስኪ እኔን ለማስቀረት ማነው የጣረ
ዓባይ በጣናላይ ሂደ ተንነባሎ
እኔው ውሃ እርሱም ውሃ ብሎ
እርስ በርሳችሁ ደምን ከማፋሰስ

ዓባይን ገድቦ ነበር ማረስ ማንደፋረስ ማረስ" ሲሉ ጽፈዋል።

ከሕደት በደም መሬት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 53 "1928 ዓም ኦጋዴን የኢትዮጵያ አካል ሆኖ በኢትዮጵያ አስተዳደር ውስጥ ቢቆይም አስተዳደሩ የራስ–ገዝ ጠባይ የነበረውና ሕዝቡም ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ዘመን ነበር። ከዚያም ተካታትሎ በኢጣሊያንና በእንግሊዝ አስተዳደር ሥር የቆየበት ዘመን በድምር 19 ዓመት ሲሆን እነኝህም ዓመታት የኦጋዴን ሕዝብ አስተዳደሩን ለማማረር ያበቁት የግፍና የጭቆና ዘመናት ነበሩ"።

ይሉና ገጽ 65 "ዛሬ ሶማሊያ ተዳክማለች። ዚያድ ባሬ ለአገዛዙ እንዲያመቸው ብሎ በፈጠረው የዘር (ጎሳን) ልዩነት ውጥረቱ እንዳለ ነው። ሶማሊያ ከባድ የሆነ እልቂትና የፖለቲካ ትርምስ ውስጥ ከገባች ዓመታት ተቆጥረዋል። ሕዝቦቿ በመጀመሪያ የፈለሱት ወደ ኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያም እጆችዋን ዘርግታ ተቀብላቸዋለች። ያለፓስፖርትና ያለብዙ ጥያቄ እንደልብ ገብተው በሰላም የሚኖሩበት፤ የሚሰሩባት አንዳንዶቹም የከበሩበት ሀገር በመሆኗ ብዙ ሶማሌዎች ስለ ኢትዮጵያ ያላቸውን አስተያየት እንዲለውጡ አስገድዷቸዋል። ምንም እንኳን ሱማሊያ የጠነከረ ማዕከላዊ መንግሥት ባይኖራትም የተለያዩ መሪዎችና የፖለቲካ ሰዎች በግል እንደሚናገሩት ዛሬም የታላቋ ሲማሊያ ሀሳባቸውን አልለወጡም። ምንም ዓይነት መንግሥት በሱማሊያ ቢፈጠር ይህ ፖሊሲ የሚለወጥበት ጊዜ አልተቃረበም። የሶማሊያ ፖሊሲ ከአረባዊነትና ከአክራሪ የእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ያለና የሚኖር የኢትዮጵያ ሥጋት ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

ዛሬ በወያኔዎች ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኦጋዴን ጉዳይ የዘነጋ ይመስላል። ከላይ አባይ የሚያመጣውን ችግር እንደዘረዘርኩት ሁላ የቅርቡ ጠላት ሳቢው ኦጋዴ ነው። ኦጋዴን በተመለከተ ከዚህ በፊት ብዙ ደም ፈሶበታል። ይህን መሬት በነዳጅ የተትረፈረፉ አገሮች በሃይማኖት እያመካኙ ሰላም እየነሱ ነው።

ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተ ማርያም የጦር ሜዳ ውሎ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 19 " እንግሊዞች ከሰሜን ሶማሌላንድን ጥላ ስትወጣ በአረብ አገሮች መሀከል ወደፊት ሠላም ሰፍኖ ተፈቃቅረው የሚኖሩባትን ሁኔታ አመቻችታ ሳይሆን የሶማሌ ዩዝ ሊግ፤የሶማሊያ ሊግ እና ግሬተር ሶማሌላንድ የተባሉ ፓርቲዎች አቋቁማና ታላቃዋን ሶማሌ መንግሥት የሚል ጠንቀኛ መረሃ ግብር አስታጥቃ ነው የወጣችው። የሁሉም ፓርቲዎች ዓላማቸው የሶማሌ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች በሙሉ በአንድ መንግሥት ሥር መተዳደር አለባቸው፥ የሱማሌ ጎሳ የሆነ በሙሉ በአንድ መንግሥት መጠቃለል አለበት የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ሶማሌዎች በሙሉ በአንድ መንግሥት ሥር መጠቃለል አለባቸው የሚሉ ነበሩ። የታላቅዋ ሶማሌ ተቀዳሚ ዓላማ የእንግሊዝ መንግሥት ቀብሮት የሄደውን ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳውን ፈንጅ ማፈንዳት ነበር። በተግባር መተርጎም የሚቻለው እንዴት ነው? ሲባል ከኢትዮጵያ ከኬንያ መሬት ቆርሶ በመውሰድና ጅቡቲን በሙሉ ወደ ሱማሊያ ጠቅልሎ በማስገባት ታላቅዋን ሲማሌ መመሥረት ነው" ሲሉ ጽፈዋል።



## ምዕራፍ 7

## የአጤ ቴዎድሮስ አጽም የት ይረፍ?

አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አምበሣ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 238 "አጤ ዮሐንስ ደብረ ታቦር በመጡበት ዘመን ራስ መንገሻ የአባታቸው የአጤ ቴዎድሮስ አፅም ከመቅደላ ወደ ትውልድ አገራቸው እንዲሄድና በማኅበረ ሥላሴ ገዳም እንዲያርፍ ሲሉ በማሳሰባቸው በ1871 ዓም በመጋቢት ወር ከመቅደላ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን ከአረፈበት ከርሠ መቃብር ወጥቶ ወደ ቤገምድር ተጓዘ። በጉዞውም ላይ እንዲያ ይጠላቸው የነበረው የወሎ ሕዝብ ከልጆቻቸውና ከዘመዶቻቸው ጋር በመተባበር እያጀበና እየከበከበ በሚያርፍበት ቦታ ሁሉ እየደገሰ ቤገምድር ደንበር ድረስ በክብር ሸኝቷል" ይሉና "ይሁን እንጂ የንጉሠ ነገሥቱ ፍኖተ አፅም እንደተለመደው ክብር ሳይጓደልበት በየአረፈበት ጸሎተ ፍትሐት ሳይለየው ወዳጅ ዘመዳቸው እያለቀሰ ከመቅደላ ፈልሶ በማኅበረ ሥላሴ ገዳም አረፈ" ሲሉ ጽፈዋል። ኢትዮጵያውያን አንድ ሁኖ እንዳይነሳ የወያኔ መንግሥት ቅስሙን ሰብሮ አንገት አስደፍቶ የምንኮራበት የጀግና ስም እንዳንጠራ ሊያደርገን ሲያቅድ ምን ይሁን ትላላችሁ?

አንዳንድ ወገኖቼ የሚሉኝ "4ኛው አጤ ዮሐንስ የሞቱበትን መተማን ወያኔ ለሱዳን ይሰጣል ማለት ዘበት ነው። ታሪካቸው መሆኑን ያውቃሉ" እያሉ ያዘናጉኛል። በመሰረቱ ወገኖቼ አልገባቸው ብሎ እንጅ ወያኔ ለታሪክ የሚሰጎድ አይደለም። ለታሪክ የሚሰጎድማ ቢሆን ኑሮ 4ኛው አጤ ዮሐንስ ግብጽን ተዋግተው ድል ያደረጉበትን ጉራዕንና ሌሎችንም ወረዳዎች ለኤርትራ አይሰጥም ነበር። ሌላው ቀርቶ በ1992 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ ባድሜንና ሌሎችንም ወረዳዎች በደሙ ያስመለሳቸውን መሬት እያወቀ ለሻዕቢያ አይሰጥም ነበር። ይህን ያደረገ መንግሥት አጤ ዮሐንስ የሞቱበትን መተማን ሊከላከል አይችልም። ስለዚህ የዋሕ ባትሆኑ መልካም ነው። ወያኔ ማህበረ ሥላሴ ገዳሙን አሳልፎ ሊሰጥ መሆኑን ከላይ ሰነድ እየተጠቀሰ ተጽፏል። ስለዚህ ወያኔ ለታሪክና ለአገር አንድነት ይቆማል እያሉ አንዳንድ ሰዎች ቤት ልማት ኢትዮጵያ ውስጥ የተቀበሉ ግለሰቦች የሚሉት እንጂ ተግባሩ የሚያረጋግጠው አገር አሳልፎ መስጠት ነው። ስለዚህ እኔ የምጠይቀው የኢትዮጵያን ሕዝብ ኢትዮጵያ አንድ ትሁን ካልን ለአገር የተዋደቁት ጀግኖች አጽም መጠበቅ ይኖርበታል።

ትተኪው ትውልድ በእኛ ላይ የወቀሳ ናዳ እንዳያወርድብን የአጤ ቴዎድሮስ አጽም ያረፈበት ቦታ ማስቀረት ካልቻልን አጽማቸውን አውጥተን ሰኞ ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓም ደማቸው ከፈሰሰበት ለ10 ዓመት ከተቀመጠበት መቅደላ መዳኀኒዓለም ይመለስ ብሎ መነሳት ያስፈልጋል። አልያም ደግሞ ተደራጅቶ

በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት መሬቱ መስጠት የለበትም ወታደር ጠረፉን ይጠብቅ የአካባቢው ደህንነት ይጠናከር ብሎ መነሳት አመጽ መቀስቀስ አይደለም:: የአካባቢው ሕዝብ በመነሳቱና በውጭ አገር ያሉት ቁጥራቸው ትንሽ የሆኑ ምሑራን በማጋለጣቸው አሁን ለጊዜው ረገብ ያለ ቢመስልም "ያደፈቀን ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም" እንደሚባለው ወያኔ አቅዷልና ሲተኛላት ስለማይችል ለኢትዮጵያ ሰላማዊ ትግልና ሰላማዊ የሆነ ጥያቄ አንስቶ ደንበርን ማስጠበቅ የማንኛውም ግለሰብ መብት ነው:: ይህን ጥያቄ በማንሳቴ የድርጅቴ ፈቃድ ይሰረዝብኛል! ቤቴን እቀማለሁ!ዘመዶቼ ከስራ ይባረራሉ እኔም እንዳልገባ የመግቢያ ፈቃድ እከለከላለሁ በሚል ሆዳምነት ዝም ማለት ከአጥፊው ጋር አንድ ሁኖ መቆጠር መሆኑን መረዳት አለብን::

የታሪክ ምሑራን ለአገራችን አንድነት የታገሉ ግለሰቦች አጽምና ታሪክ ቦታ እንዲኖራቸው ከፍተኛ የሆነ ሐላፊነት አለባቸው:: ስለዚህ የአጤ ቴዎድሮስ አጽም ነገር ሲነሳ በዚህ በ3ኛው ሺህ መግቢያ ያለው ሁላ ተወቃሽ ነው:: የሕዝብ ሚድያዎች ሌላውን ወሬ ከማናፈስ ይልቅ አጽማቸው ያረፈበት ቦታ በሥርዓት ይጠበቅ አልያም ደግሞ ደማቸው ከፈሰሰበት መቅደላ መሄድ አለበት ብሎ መቀስቀስ ብተና አይደለም:: ያጤ ቴዎድሮስን አጽም ከመቅደላ ማሕበረ ሥላሴ ልጃቸው ራስ መሺሻ ቴዎድሮስ በ1870 ዓም የወሰዱበት ምክንያት አንደኛ ማሕበረ ሥላሴ የኢትዮጵያ ማህል አገር በመሆኑን ስላወቁና ሌላው ደግሞ ለወደፊቱ የዓረቦች መስፋፋት አሳስቦአቸው ትውልዱ አጽማቸው ያረፈበት ቦታ በመሆኑ ይጠበቅ ብሎ ይነሳል ብለው አስበውም ይሆናል:: ሌላው የራስ መሺሻ ዓላማ አባታቸው አጤ ቴዎድሮስ የተከፋፈለች ኢትዮጵያ አንድ ለማድረግ ቅድሚያ ጥንቅላታቸው በእውቀት የታነጸበት የታሪክ ትምህርት የተማሩበት ማህበረ ሥላሴ ገዳም መሆኑን አምነው ይሆናል:: እነዚህን መሰረተ ጉዳዮች የዛሬው ትውልድ አመዛዝኖ ተገቢውን ቦታ እንዲሰጣቸው ይህን መጽሐፍ ለሚያነቡ ሁላ አደራዬ የጠበቀ ነው::

ኢትዮጵያውያን በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሆነ በደርግ ዘመነ መንግሥት ውጭ ወጥቶ መኑሮ መቅረት ተለምዷል:: በሀገራቸው የመኖር እድል ስላላገኙ ከቤተዘመድ ተለይቶ ብቻን ሲንከራተት ኑሮ ወደ ማይቀረው ዓለም መሄድ ተለመደ:: ታላላቅ በሀገር አስተዳደርና በወታደራዊ መሪ ሁነው የሠሩ ኢትዮጵያውያን አገራቸው ላይ መኖር አቅም አቅቶአቸው ተሰደው እየሞቱ ነው:: ወደድነም ጠላን አገራቱን በርዕሠ ብሔርነት የመሩት ሳይቀሩ በሥርዓት አልተቀበሩም:: ምንም እንኳን ለሰባት ቀን አገር የመሩ ርዕሠ ብሔር ጀኔራል ተሥፋዬ ገብረ ኪዳን በሥርዓት አልተቀበሩም:: ወደድነም ጠላን ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አገር መርተው ብዙ ጥፋት ያደረሱ መሆናቸው ባይካድም በአንጻሩ ደግሞ ብዙ ልማት የሰሩ መሆናቸው ግልጽ ነው:: ታዲያ እርሳቸው ሲሞቱ የት ይቀበሩ?

የትኛው የኢትዮጵያ ርዕሠ ብሔር ነው ታሪኩ ሳይሸራረፍ ለተተኪው ትውልድ የተላለፈው? ሌላው የእኔ ቢጤው ሕዝብ ቀርቶ የታሪክ ጠበብቶች ናቸው የሚባሉ ሳይቀሩ የዕርሠ ብሔሮችን ስም በተርታ አይጠሩም:: ለወደፊቱ



አስተውሉ ሲናገሩና ሲጽፉ "አጤ ቴዎድሮስ፣አጤ ዮሐንስ፣አጤ ምኒልክ፣አጤ ኃይለ ሥላሴ፣መንግሥቱ ኃይለ ማርያም"ብለው ሲጠሩ ከመሀል ብዙ መሬዎች ተረሱ:: ለምሳሌ መባል ያለበት "አጤ ቴዎድሮስ፣አጤ ተክለ ጊዮርጊስ፣አጤ ዮሐንስና አጤ ምኒልክ፣ልጅ እያሱ፣ንግሥት ንገሥታት ዘውዲቱና አጤ ኃይለ ሥላሴ፣ርዕሠ ብሔር አማናዶምና ርዕሠ ብሔር ተፈሪ ባንቲ፣ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያምና ርዕሠ ብሔር ተሥፋዬ ገብረ ኪዳን ርዕሠ ብሔር ታምራት ላይኔና ርዕሠ ብሔር መለስ ዜናዊ"ብሎ መጥራት አይፈልጉም:: ይህ እንዲለወጥ የአንድነት አቢዮት መጀመር አለበት:: ከላይ እንዳልኩት በሥርዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ መርጦ ያነገሣቸው ባለመሆናቸው ከሥልጣን ሲወርዱም ተገለው አልያም በቅርቡ ደግሞ አገር ጥለው መጥፋት ተጀመረ::

መቼ ይሆን የአገሪቱን መሬዎች በሥርዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ አልቅሶ የሚቀብራቸው? ልቅሶም ይናፍቃል? አጤ ቴዎድሮስ የተበታተነች አገር አንድ ለማድረግ ቆርጠው ሲነሱ የገጠማቸው ችግር ከውጭ ወራሪ ጋር ተባብሮ እርሳቸውን ማስገደሉ ነው:: ሌሎችም መሬዎች መቃብራቸው አይታወቅም:: ዜና መዋዕላቸው በሥርዓት አይጻፍም:: ይህ እንዲሆን የአንድነት አቢዮት መስተጋባት አለበት:: ከዚህ በፊት በአንድ መጣጥፌ አልፎ አልፎ የምጠቅሰው ነገር ቢኖር ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ስደተኛ ናቸው:: ሰው ናቸው ሲሞቱ የት ይቀበሩ? አስከሬናቸው እንዴት ይገባል? ማን ነግ ለኔ ብሎ በሥርዓት አክብሮ ይቀበላል:: ስለ አገራቸው የሚንገበገቡ ኢትዮጵያውያን እየናፈቁ እድሜያቸውን በስደት አሳልፈው ሲሞቱ ሬሳቸው የሚመለሱ ብዙ ናቸው:: ከመሞታቸው በፊት ለምን አገራቸው አይገቡም?ኀበዝ ብዙ ችግሮች እየመጡብን ነው::

ከላይ እንዳልኩት የአገሪቱን መሬዎች ታሪክ በተመለከተ ሁሉንም ላንወዳቸው እንችል ይሆናል::ነገር ግን እውነቱን ልንደብቅ አይገባም:: በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተመለከትኩት ጉዳይ አንዱን የአገር መሪ በራሱ መነጠር አይቶ መጥላት ሲገባው ሌሎች በንጉሡት ላይ ተነስቶ መጥላት አግባብ አይደለም:: መሬዎች ሰዎች ናቸው:: ስዕተት አለባቸው:: መጥፎ የሰሩትን መጥፎ ብሎ መጥቀስና ጥሩ የሰሩትን ጥሩ ብሎ መጻፍ በእኛ ዘንድ አልተጀመረም ለምን? ካንድ ወዳጄ ጋር የአጤ ቴዎድሮስ አጽም ያለው ማህበረ ሥላሴ ሲሆን ወደ ሱዳን ሊከለል ነው ይህን በተመለከተ ምን ታስባለህ? ስላቸው የመለሱልኝ መልስ አስደነገጠኝ" ይህ የማህል አገር አማራ ትቢት ሊመታ የሚችለው የነዚህ ዓይነት ጀብደኞች ታሪክ ሲጠፋ ነው:: ምነው በተሉ ማህበረ ሥላሴ ወደ ሱዳን ተከልሉ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ባንሰማ ደስ ባለኝ?" ሲሉኝ ስለ ወዳጄ አፈርኩ:: በትክክል ስለ ኢትዮጵያ አንድነት የሚያስቡትን ሰዎች አደራ ለማለት የምፈልገው ነገር ቢኖር የአጤ ቴዎድሮስ አጽም የት ይረፍ? ይህን አይነት አላፊነት የሚሸከም ትውልድ ይኖር ይሆን?::

ቴዎድሮስ ለፋ ጣረ ኢትዮጵያ እንድትኮራ
ሕይወቱን ሰዋላት ትውልዱ እንዲኮራ
አንተ አዲሱ ትውልድ በአንተነትህ ኩራ
ቴዎድሮስ ተጥሎብሃል የታሪክ አደራ::

## ምዕራፍ 8

## ጠቅላላ ሠነድ ከሃይማኖትና ከታሪክ መጽሐፍት


1 መጽሐፍ ቅዱስ
2 ቅዱስ ቁርዓን
3 በቅዱስ ላሊበላ ደብር ሰበካ ጉባኤ ገድለ ቅዱስ ላሊበላ
4 አንበር መስቀልየ በዲባ መስቀል መስቀሌን በመስቀለኛ ላይ አኑር
5 ድርሳነ ኡራኤል
6 ሰኔ ጎለጎታ
7 አባ ቀውስጦስ የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ይግባኝ ለክርስቶስ
8 ይድነቃቸው ተሰማ ሰምና ወርቅ ተሰማ እሸቴ
9 መምሕር ብሩክ ገብረ ሊባኖስ ማደስ ወይስ ማፍረስ
10 አስቻለው ከበደ ከርከቤዴል ሳዶፍ ኢትዮጵያና የሰማይ ኃያላት
11 አለቃ ታየ ወልደማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ
12 ጳውሎስ ኞኞ የኢትዮጵያና የኢጣሊያን ጦርነት
13 ሀዲስ አለማየሁ ትዝታ
14 ማርሴል ግሪዮል ተርጓሚ ላቀች አከሊሉ የንጉሠ ነገሥቱ ትውስታ በ1929 ዓም
15 ግደይ ባሕር ሹም አሞራ
16 ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ ሞት የተፈረደባቸው 15 ሺህ የኢትዮጵያ ሠራዊት አይ ምጽዋ
17 ሻለቃ ስለሺ ፍስሃ አንድነት ለአንድነት
18 የህወሓት ኮሚኒስት ሃይል የ10 ዓመት ግምገማ ሐምሌ 1977 ዓም
19 ቀደሰ አለማየሁ ሞገስ ደርሶ ሁሉም ሉሁን ይወቅ
20 ዶ/ር ኃይሌ ወልደ ሚካኤል አብርነት በኢትዮጵያ
21 መምህር ስፍሀ ጽዮን ካሣ መርኖ አጳም ወግዕዝ አጳምና ግዕዝ
22 ያሬድ ግርማ ኃይሌ የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር
23 ሐጂ ሙሐመድ ሣኒ ሐቢብ እስልምና እና የታላቁ ነቢይ የሙሐመድ ታሪክ
24 ሒራ አሳታሚና አከፋፋይ የግል ማህበር የሐበሻው ሂጅራና ሙሃጂሮች
25 ዶ/ር ላጵሶ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሠረቶችና መዛሪያዎች
26 አህመድ ሙነወር ሰይድ ኢብራሂም የእስልምና ድንጋጌ የአመጣጥ ታሪክ
27 ዲያቆን ቢጋሻው ደሳለኝ የመስቀሉ ሥር ቁማርተኞች
28 ዶ/ር እያሌው ሲሳይ የአገው ሕዝቦችና የዛጉዌ ሥርዎ መንግሥት ታሪክ
29 አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ድብቁ መለኮታዊ ጥበቃ በኢትዮጵያ
30 ዶ/ር ሀብተ ማርያም አሰፋ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሉች
31 በላይ ግደይ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ
32 ዶ/ር ላጲሶ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ
33 ዶ/ር ሔነሪ ብላንክ ዳኛው ወልደ ስላሴ እንደተረጎመው የእስራት ዘመን በአበሻ አገር
34 ብርሃኑ ጣሰው የፍቅር መቅረስ
35 ነጋ ወልደ ሥላሴ ባለታሪክ ኢትዮጵያ
36 ዘውዴ ገብረ ሕይወት የሕይወት ውጣ ውረድ
37 አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ





38 አስናቀ እንግዳ አረባዊ አጤነት የአፍሪካ ቀንድ ፍዳ
39 መርስዔ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ
40 ኅበዜ ጣፈጠ አባ ጤና ኢያሱ
41 ዘውዴ ረታ ተፈሪ መኮንን ረዥሙ የሥልጣን ጉዞ
42 ከበደ ተሰማ የታሪክ ማስታወሻ
43 ጄኔራል ነጋ ተገኝ የኢትዮጵያ የረጅም ዘመናት ትግልና የዘመናዊ ሠራዊት አመሰራረት 1855-1974
44 ሕይወቴ ሕዳሩ ያቺ ቀን ተረሳች
45 ዶ/ር ላጵሶ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም 1900-1966
46 ዳኛው ወልደ ሥላሴ ውጣ ውረድ የበዛበት ሕይወት
47 ኮሎኔል ዳዊት ገብሩ ከንቲባ ገብሩ ደስታ የኢትዮጵያ ቅርስ
48 ብ/ጄኔራል መልኬ ጌታሁን የትግል ፍጻሜ
49 ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ሽክም የማይከብደው ሕዝብ
50 ሻለቃ ጌታቸው የሮም ስም ከመቃብር በላይ
51 ብላቴ ጌታ ማኅተመ ስላሴ ዝክረ ነገር
52 ፊንታዬ ወ/ሊባኖስ የአባ ጠቅል አጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት
53 ልጅ አግባው ውብነህ ራስ አሞራው ውብነህ
54 የስዩም ጣሰው ማስታወሻ የንጉሡ ገመና
55 ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ በአገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለያየንም
56 ኮሞዶር ጣሰው ደስታ የኢትዮጵያ አንድነት ትዝታና ትግል
57 ክፍሉ ታደሰ ያ ትውልድ ቅጽ ሁለት
58 ገብረ መድህን እርአያ እና አብርሃም ያየህ የወያኔው ታላቅ ሤራ
59 ባብሌ ቶላ አንድ ትውልድ ለመምተር ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ
60 ገብረ መድህን እርያ አብርሃም ያየህ የወያኔ ታላቅ ሤራ በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ
61 አማረ አፈለ ብሻው አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች
62 አማረ አፈለ ብሻው የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ
63 ገሪማ ታፈረ ጎንደሬ በጋሻው
64 እያናዚጊ አ!ወልቃይት ያልታተመ
65 መጽሐፈ ሕግጋት
66 ታጋይ ገሠሠ ረታ ታሪክ አጉዳፊው የአልባንያ ደብተራ
67 ተወልደ ገ/ተንሳይ ኮ/ል ባድመ እንደምክንያት
68 መዳኅኔ ታደሰ የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት
69 Kshsay Berhe Ethiopia:Demcratization and Unity
70 70 0ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የነፃነት ጎህ ሲቀድ
71 በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ
72 የካባ ሲሳይ አምባው የጣረ ይወጣል
73 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ኑቢያ አክሱም ዛጉዬ
74 አባ ተሥፋ ስላሴ ሞገስ ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው የተዋሕዶ አንበሳ
75 መራሪስ እማን በላይ የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ
76 ጳውሎስ ኞኞ አጤ ምኒልክ
77 ቀ/ ኃ/ሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሕይዎቴና የኢትዮጵያ ርምጃ ቅጽ 2
78 ሜጀር ጄኔራል ሁሴን አሕመድ መስዋዕትነት እና ጽናት

79 የቀድሞ የባሕር ኃይል መለዮ ለባሾችና..የኢትዮጵያ የባሕር ጠፈና ባሕር ኃይሏ
80 ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ ክህደት በደም መሬት
81 አስገደ ገ/ስላሴ ወ/ሚካኤል ጋሀዲ
82 ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ሀብተ ማርያም የጦር ሜዳ ውሎ
83 የካባ ሲሳይ አምባው እግዚአብሔር አልረሳኝም የለመንኩትን አልነሳኝም
84 ገሪማ ታፈረ አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ
85 ዓለማየሁ ሞገስ ደርሶ መልክሀ ኢትዮጵያ


## ከመጽሔትና


86 ዶ/ር ሒሩት ወልደ ማርያም ሐመር መጽሔት 15ኛ ዓት /ቁ 16 የካቲት 2 ሺህ ዓም
87 አበራ ለማ ኢትአጵ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 13 ሰኔ 1992 ዓም
88 ርዕሠ ብሔር አቶ ኢሳያስ አፍወርቅ ሓንቲ አንድ ዋን ኢትዮጵያ
89 ጌታቸው ረዳ ዜጋ መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁጥር 8 ሰኔ 1994 ዓም
90 መሪራስ አማን በላይ ጉግሣ መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁ 1 ሐምሌ 1993 ዓም
91 በቡድን ኢትእጵ መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 057 ሚያዝያ 1996 ዓም
92 ሙዳይ መጽሔት ሰኔ 1985 ዓም
93 ቀኛዝማ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ሐምሌ 1992 ዓም.ሐ
94 መልዓክ ሰላም ሲሳይ አየለ ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 1 ሐምሌ 1994 ዓም
95 ጌታቸው አግሬ ኢትዮጵያ ርቪው መጽሔት ሚያዝያ 1985 ዓም ወይም 1993
96 ደመዘቅ መንግሥቱ ኢትአጵ መጽሔት ቅጽ 7 ቁጥር 72 ሐምሌ 1997 ዓም
97 ልጅ ሚካኤል እምሩ ኢትአጵ መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 074 ታህሳስ/ጥር 1996 ዓም
98 ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ዜጋ መጽሔት 5ኛ ዓመት ቁ 2 ጥቅምት 1996 ዓም
99 አቶ ታምራት ላይኔ ዜጋ መጽሔት 3ኛ ዓመት ቁጥር 7 መጋቢት ሚያዝያ 1994 ዓም
100 ደርበ ሙዳይ መጽሔት መስከረም 1986 ዓም
101 ዞብል አፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሰኔ 1985 ዓም
102 አደራ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 1 1985 ዓም.ሐ
103 የአፍሪካ ቀንድ መጽሔት ታህሳስ 1986 ዓም
104 ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 10 ቁጥር 11/1995 ዓም.ሐ
105 ዶ/ር ፒተር ኒዮተኮክ መስታውት መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 1 መጋቢት 1985 ዓም
106 ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፍወርቅ እሰር መጽሔት 1990 ዓም.ሐ
107 ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 7 ቁጥር 6/1992 ዓም
108 ገ/ፃድቅ አበራ ኢትአጵ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 3 ነሐሴ 1991 ዓም
109 ውዱ ገበየሁ ዜጋ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 5 የካቲት/መጋቢት 1992 ዓም
110 ሙዳይ መጽሔት መስከረም 1987 ዓም
111 ሞረሽ መጽሔት ቅጽ 3 ቁጥር 2/1987 ዓም
112 አግሬ አፈለ ብሻው ጉግሣ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ሐምሌ 1992 ዓም
113 አርበኛው መጽሔት ነሐሴ 1991 ዓም
114 ጌታቸው ወልዴ አፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሐምሌ 1985 ዓም
115 ሻለቃ መላኩ ተፈራ ኢትአጵ መጽሔት ታህሳስ 1992 ዓም
116 ወልዱ ሃይሌ ሩሕ መጽሔት 1ኛ ዓመት ቁጥር 1 ጥቅምት 1993 ዓም
117 ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 1 ነሐሴ 1996 ዓም
118 አምባሳደር አህዱ ሳብሬ ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅ 1 ቁ 6 ጥር 1996 ዓም
119 ረዳት ፕሮፌሰር መድኃኔ ታደሰ ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ግንቦት 1997 ዓም





120 ገብረ መድኅህ አርአያ አፍሪካ ቀንድ መጽሔት ሕዳር 1986 ዓም
121 ግደይ እቁባይ ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅ 2 ቁ 11 ሰኔ 1997 ዓም
122 ብሥራት አግሬ ኢትዮአጵ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 044 የካቲት 1995 ዓም
123 ሚካኤል እምሩ ኢትዮአጵ መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 045 መጋቢት 1995 ዓም
124 አሰፋ ጫቦ ዜጋ መጽሔት 2ኛ ዓመት ቁ 8 ሚያዝያ 1993 ዓም


## መጣጥፍ


125 ሜጋ ማከፋፍያ ኃ/ተ/ የግል ማህበር
126 ሹመት ሲሻኝ የኤርትራ ሕዝቦች የአንድነት ትግል
127 ዲያቆን ናትናኤል ታምራት እግዚአብሔር ለምን ዝም አለ?
128 ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ ሊትማን ያሳተመው
129 ቀሲስ ክፍ ያለው መራሂ ሰስቱ ምንትዋቦች
130 ክቡር ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ መስከረም 10 ቀን 1967 ዓም
131 ያሬድ ጥበቡ የአመጹን አዙሪት ለመስበር
132 የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ረቂቅ ሚያዝያ 25 ቀን 1986 ዓም
133 ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ ቋሚ ጽ/ቤት ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት
134 አሸብር ተቆርቋሪ የለለው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ
135 ዶ/ር ጌቱ ገላይ ጭማቂ ጹሑፍ
136 ርዕሠ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለሸንጎ የቀረበ 1982 ዓም


## ጋዜጣ


137 አበባው ይግዛው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ጥር 25 ቀን 1965 ዓም
138 አቶ ሰዬ አብርሃ አዲስ ነገር ጋዜጣ ቅ 1 ቁ 32 ቅዳሜ ግንቦት 23 ቀን 2000 ዓም
139 አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 7 ቁጥር 8 መጋቢት 1993 ዓም
140 አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 6 1993 ዓም
141 አያናዝጊ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 7 1995 ዓም
142 ኅሹ ገብሩ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 3 1995 ዓም
143 ኅሹ ገብሩ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 8 ቁጥር 4 1995 ዓም
144 መጽሐፈ ሲራክ ሐዋርያ ጋዜጣ ቅጽ 5 ቁጥር 7 1992 ዓም
145 መይሳው ጋዜጣ ጥር 15 ቀን 1992 ዓም
146 ፊያሜታ ጋዜጣ ታህሳስ 1990 ዓም


## ዘማሪያንና ድምጻውያን


147 ዘማሪት ፀዳለ ኅበዜ እቤቱ የሆኑብኝን እስብ የሥዕል ድምጽ ክር
148 መምሕር አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ቤተ ክርስቲያን ሲያስተምሩ
149 ዲያቆን በሪሁን ወንድወሰን እስራት እንዳይፀናባችሁ አታፊዙ
150 ኪሮስ አለማየሁ ዘፈን "አይበልናዶ" አላልናችሁም!
151 ሻምበል በላይነህ ዘፈን "ታሪክ ይመስክር"
152 ይርጋ ዱባለ ዘፈን "ወልቃይት ጠገዴ"

153 ፋሲል ደምወዝ ዘፈን "አለ ነገር ዘንድሮ አለ ነገር"

## በራሪ ወረቀት

154 ከኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ሚያዝያ 1 ቀን 2000 ዓም
155 ግንቦር 7 ድምጽ ሐምሌ 3 ቀን 2000 ዓም
156 ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓም ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
157 የጎንደር ክፍለ ሀገር የመልሶ ማቋቋምና የልማት ጥራዝ መስከረም 1984 ዓም
158 ታጋይ ብርሃኔ ገ/ ጻድቅ የኢትዮጵያ ራዲዮ ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም
159 የጎንደር ክፍለ ሀገር አውራጃዎችና ወረዳዎች ምክትል ወረዳዎች
160 ከሰሜን አሚሪካ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች ኢትዮጵያውያን
161 አውደ ኢትዮጵያ ልዩ እትም 1/2000 ዓም

## በቴሌቭዥን የቀረበና ጥያቄና መልስ በውይት የተነገሩ

162 የኢትዮጵያና የሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚሽን የሲዲ ክር
163 ርዕሠ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ለወጣቶች ንግግር ሲያደርጉ
164 አቶ ማሞ ስበር፣ ጥያቄና መልስ
165 አቶ ፀጋ በላይ፣ ጥያቄና መልስ ብሉም ደብዳቤያቸው
166 አቶ ወልደ ገብርኤል አስጌ፣ ጥያቄና መልስ
167 አቶ ሊቀ እጅጉ፣ ጥያቄና መልስ
168 ስሜ እንዳይነገር ያሉኝ፣ ጥያቄና መልስ
169 ሻለቃ ጌታቸው የሮም፣ ጥያቄና መልስ
170 አቶ ዘውገ ፈንታ፣ጥያቄና መልስ
171 ክቡር አቶ ፈንታዬ ወ/ሊባኖስ፣ ጥያቄና መልስ
172 ብፁዕ አቡነ መልከ ጸዲቅ፣ ጥያቄና መልስ
173 የአስር አለቃ አባይነህ መሸሻ ገለፃ
174 አምሳለቃ )ደጃዝማች) አፈራ አዳነ ጥያቄና መልስ
175 አቶ ጫቅሌ ኩምነገሬ ጥያቄና መልስ
176 አባ ታጠቅ ቡድን የተመለከቱትንና የሆነውን የገለፁልኝ
177 አቶ ታመነ ወይም ሊንጎ የኢዲዩ ወሳኝ ሰው በጨዋታ።
178 የጭልጋው አራሽ አንደፋራሽ ንብረታቸውን ሱዳን የወረሰባቸው።

በነገራችን ላይ ይህን መጽሐፍ ማንም እንዲመለከትልኝ ምክር አልጠየኩም። በእኔ ብቻ ታርሞ ለንባብ የቀረበ በመሆኑ ድክመት ቢታይበት ተጠያቂው ራሴ ነኝ። ስለዚህ በምታዩት ድክመት አንባቢያንን ምክራችሁን እሻለሁ።

አሳስቦ ሳስጀመረኝ አስጀምሮ ሳስፈጸመኝ
ልዑል እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን!

መልዕክት ከአያናዚጊ ለዚህ መጽሐፍ አንባቢያን የአደራ ጥሪ አ!ወልቃይት እያልኩ በተደጋጋሚ በሐዋርያ ጋዜጣ እጽፈው የነበረውን መጣጥፍ ያነቡ ነበር? እንግዲያውስ ያነን መጣጥፍ መጽሐፍ አድርጌ ለማውጣት ጀምሬአለሁና አንባቢያንን ትብብራችሁን እጠይቃለሁ።

1ኛ ስለ ወልቃይት የምታውቁትን ታሪክ ከዚህ በሚከተለው አድራሻ ላኩልኝ። P.O.BOX 492 Seattle WA 98111 U.S.A አማካይነት ቢልኩልኝ ሊደርሰኝ ይችላል።

2ኛ የወያኔ ኢሕአዴግ መንግሥት በወልቃይት ሕዝብ ላይ ያደረሰውን ግፍና ሰቆቃ በሚመለከት የታሰሩና ጠፍተው የቀሩ ሰዎችን ስሞች ቢቻል ከፎቶ ግራፋቸው ጋር!

3ኛ ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ላይ ያደረሰውን ችግር በሚመለከት የሚያውቁትን ስሞች ቢቻል ከፎቷቸው ጋር!

4ኛ ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ቤተሰቦቻችሁን በግፍ አስሮና አሰቃይቶ የገደላቸውን ስማትታት ቢቻል ከፎቶግራፍ ጋር ታሪካቸውን!።

5ኛ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የድንበር ጉዳይ ላይ የምታውቁትን ታሪክ! ለወደፊቱ ለትውልድ ይድረስ የምትሉትን!

ኢትዮጵያውያን እንዲያውቁት ለማድረግ የምታውቁትን ታሪክ ላኩልኝ። የምትልኩትን ደብዳቤ ከፖስታው ላይ ለአያናዝጊ እያላችሁ ጻፉበት! ስለ ትብብራችሁ ከልብ አመሰግናለሁ።

አ!ወልቃይት
በቅርብ ቀን ለንባብ ይቀርባል

ከማክበረ ሠላምታ ጋር
አያናዝጊ ኮሎምቦስ ኦሃዮ!